የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ !!

ቁጥር ሁለት



ፍስሐ ያዜ

2010 ዓ.ም

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ቁጥር 2

ገነት፣የሕይወት ዛፍ፣ኢትዮጵያ

ፍሥሐ ያዜ ካሣ

2010 ዓ.ም

@BOOKALEM

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ እትም፤ መጋቢት 2010 ዓ.ም

ቡክአለም የቀረበው መጽሐፍ
@BOOKALEM

ዋና አከፋፋይ
ፋንታሁን መፃሕፍት መደብር

ስልክ 0924 40 84 61 / 0927 94 95 12

አድራሻ፡- አ/አ ትንሿ ስቴዲየም ፊት ለፊት
ናሽናል ታወር

ፍሥሐ ያዚ

@BOOKALEM

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ማስታወሻነቱ፤ ለዮሐንስ ዘካርያስ

@BOOKALEM

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል በ 2007 ዓ.ም‹‹የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ››በሚል ርእስ ለህትመት በቅቶ ለአንባብያን የደረሰና አሁንም ድረስ እየተዳረሰ ያለ ነው።ይህኛው መጽሐፍ ደግሞ የዚያኛው መጽሐፍ ተከታይ ክፍል ሆኖ፤ በቀደመው ርዕስ፤ነገር ግን ‹‹ቁጥር ሁለት›› የሚል ተጨምሮበት በ 2010 ዓ.ም ለህትመት የበቃ ነው።በመሆኑም ይህን ከማንበባችሁ በፊት ያኛውን፤(ቁጥር አንዱን) ብታነቡ የተሻለ መሆኑን መጠቆም እፈልጋለሁ።

በተጨማሪም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አልፎ አልፎ በየዕሁፉ ጣልቃ፤‹‹ከዚህ ቀደም እንደተገለፀላችሁ....››የሚል ነገር ከገጠማችሁ፤ያ ማለት በመጀመሪያው መጽሐፍ በሰፊው የተብራራ ታሪክ ነው ማለት መሆኑን ከወዲሁ ተገንዘቡልኝ።

በመጽሐፉ ውስጥ ጥቂት ሰዎች አክብሮት ሳይገባቸው፤ ነገር ግን አንቱ ተብለው የተገለፁበት ሁኔታ አለ። አንቱታው የአክብሮት ሳይሆን፤እንዲሁ አንቱ እየተባሉ ሲጠሩ መስማት ስለለመድን፤ አሁንም ሰዎቹ ሲገለፁ በአንባቢው አእምሮ ያው ምስልና ገፅታቸው እንዲከሰትለት በማሰብ እንጂ አንቱታና ክብር የማይገባቸው የእርኩሳን ስብስብ መሆናቸው ተዘንግቶ አለመሆኑ ከወዲሁ ግልፅ ሊሆንላችሁ ይገባል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በየጉባኤው በሚደረጉ ገለፃዎች ላይ አንዳንድ ሐይማኖታዊና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣረሶች ቢኖሩ፤ያ የ G 20 አገራት መሪዎችና የቫቲካኑ ጳጳስ፤እንዲሁም የኔፊሊም ድቅል የሆኑት የእንግሊዝ ንግስትና ሌሎች ተሰብስበው ስለ ኢትዮጵያ ሲዶልቱ የተናገሩት እንደወረደ ስለሰፈረ መሆኑን ከወዲሁ ማሳወቅ እፈልጋለሁ።

መልካም ንባብ።

@BOOKALEM

November 11 /2014 እ.ኤ.አ Australia Melbourne
የ G 20 አገራት መሪዎች ጉባኤ

የ 2014ቱ የ G 20 አገራት መሪዎች ዓመታዊ ስብሰባ November 14 እና 15 2014 በአውስትራሊያ ሜልቦርን ነበር የተካሄደው::መሪዎቹ ግን ‹‹ብቅድመ ሁኔታዎች ዙሪያ ለመወያየት›› በሚል ይፋዊ በሆነ መንገድ ዓመታዊ ጉባኤያቸውን ከሚያደርጉበት ዕለት ሁለት ቀናት ቀደም ብለው ነበር ሜልቦርን የገቡትና ከ November 11 ጀምረው የዝግ ጉባኤያቸውን ማካሄድ የጀመሩት::

ይህ የዋናው የመሰብሰቢያ ጊዜያቸው ከመድረሱ ጥቂት ወራት አስቀድሞ ደግሞ June 3 2014 በ G 8 አገራት መሪዎች አማካኝነት ለአስቸኳይ ስብሰባ ተጠርተው ወደ ኒዮርክ በማቅናት በጉጉት ይጠብቁት የነበረውን ውጭና ውስጥ የማብራት ጥበብን ተለግሰው እንደነበር ይታወሳል:: በመሆኑም በዚህ በሜልቦርኑ ዝግ ጉባኤ ሁሉም የ G 20 አገራት መሪዎች ውጭና ውስጥን በማብራት ረገድ በእኩል ደረጃ ላይ ያሉ ሆነው ነው የዝግ ጉባኤያቸውን በማለዳ የጀመሩት::

በቀዩ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ተሰብሳቢዎቹ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀምጠዋል::በአዳራሹ መድረክ ላይ ደግሞ የቫቲካኑ ጳጳስ በዝምታ ተውጠው ቀጥ ብለው ቆመዋል::አዳራሹ በአስፈሪ ፀጥታ ተውጦ ከቆየ በኋላ፤ጳጳሱ ዘለግ ባለ ድምፅ መናገር ጀመሩ::

‹‹ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››የጋራ ድምፅ::

‹‹ክቡራን!ሁሌም ታዛገሮች ሁኑ!የሚሰጣችሁን ትዕዛዝ በሙሉ ሃይላችሁ ያለ አንዳች ስህተት ለመተግበር ተዘጋጁ!ልዑላችን የኛ ታዛዥ ሆኖ ለዘመናት እንደኖረው ሁሉ እናንተም ልትታዘዙት ምንጊዜም ዝግጁ ሁኑ! ልትሰሙት፤ የሚለውን ልትፈፅሙለት ይገባል!ስለሚሰማችሁ ስሙት፤ ስለምትሰሙት ይሰማችኋልና!

‹‹የልዑላችንን ትዕዛዝ እርሱ በፈቀደልንና እርሱ በፈለገው ዘመን ለማስፈፀም ሲባል በቤተ ክርስቲያናችንና በየ ቤተ እምነቱ በኩል መሰራት የነበረበትን ስራ በኛ በኩል በጥሩ ሁኔታ ሰርተናል፤አሁንም እየሰራን ነው:: የሚቀረው ነገር የአፈፃጸም ጉዳይ ብቻ ሆኗል::

እኔም ሆንኩ ዛሬ የምትተዋወቋቸው ታላቋ ሴት እንግዳችን በቅርብ ልንሸኝ እንችላለን::እርሳቸው ወደ ፒራሚዳቸው፤እኔ ወደ ሞት::የምድር ሰው ሞት ብሎ በሚጠራው ምድራዊና ጊዜያዊ ሞት ማለቴ ነው::ይህ ሊሆን ግድ ነው::ሞት ማለት ሽግግር ማለት ነው::እኔና እናንተ ደግሞ ጊዜያዊው

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

የሞት ሽግግር ሊናፍቀን የሚገባ ባለ ተስፋና፤በባለ ድሉ ልዑላችን ስር ያለን የአሸናፊው የሳጥናኤል ታማኝ አገልጋዮችና፤ እንደ ልጁ የቆጠረን ሰዎች ነን!

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሹመትና በሽልማት የምንኖር፤ሁሉ በእጃችን ሁሉ በደጃችን የሆንን፤ድንቅና ለልዑላችን አስተዳደር እጅግ አስፈላጊ የሆንን ፍጡሮች ነን።ስለዚህ እኛ በሽግግሩ ስናልፍ በኛ የሚተካው ተተኪ ልክ እንደ እኛ ሆኖ የልዑላችንን ትዕዛዝ ባለስልጣን በሆንበት ዘርፍ በኩል ያስፈፅማል።በእናንተ በመሪዎቹ በኩልም ከዚህ በኋላ ተመሳሳይ የሆነ የስልጣን ሽግግር ነው የሚኖረው።እናም በስልጣን እስካላችሁ ድረስ የምትታዘዙትን ነገር በሙሉ ያለማንገራገር በማስተዋልና በፍጥነት መፈፀም ይኖርባችኋል።ከዚህ በኋላ ደግሞ ስራው በየጊዜው እየቀለለ እንጂ እየከበደ አይሄድምና የሚያስጨንቅ ነገር አይኖርም።

‹‹የልዑላችንን የንግስና መንገድ በመጥረግ በኩል ምትክ የለሽ አገልጋቹ እኛ ነንና እርስ በርስ መተዋወቅ፤በአንድነት መቆምና ከዚያም አልፈን ወደ ውህደት መምጣት ይኖርብናል።ወደ ውህደት የምንሸጋገርበት ዘመን ነውና አሁን ላይ ሁሉም ነገር ለሁሉም ሹማምንት ግልፅ እየሆነ መሄድ እንዳለበት ታምኗል።

በዚህ መሰረት እስካሁን የነገርናችሁ፤የገለፅንላችሁና ያሳወቅናችሁ ሁሉ
እንዳለ ሆኖ፤ዛሬ ወደ ሌላ አዲስና ወሳኝ ወደሆነ ትውውቅ እናልፋለን።
‹‹የልዑላችን ታማኝ ወታደሮችና እኛም ታማኝ አገልጋዮቹ፤ እንዲሁም የኛ
ዓላማ ደጋፊና አስፈፃሚ ሁሉ ሳያውቀው የቆየ፤ አሁን ግን ማወቅ ያለበት
ጉዳይ ይህ ነው!››አሉና፤የለበሱትን ሀይማኖታዊ ልብሰ ተክህኖ
በእጆቻቸው ወደላይ ሰብሰብ አድርገው በርከክ በማለት፤
‹‹ሁላችሁም ውጭና ውስጣችሁን አብሩ!›› የሚል ትእዛዝ ሰጡ።
በዚህ ጊዜ ውጭና ውስጣቸውን አጥፍተው የቆዩት የሃያላኑ የ G 20
አገራት መሪዎች በቅፅበትና በአንድነት ለስድስት ሰከንዶች ያህል
ዓይኖቻቸውን ጨፍነው ቆይተው እኩል ገለጡ።ወዲያውም ውጪያቸው
በራ።ተመሳሳይ ነገር በአጥፍ ሲያደርጉ ደግሞ ውስጣቸው በራ።
ከዚህ በፊት በደንብ እንደተብራራው መሪዎቹ ውጭና ውስጣቸውን
ሲያጠፉ ወደ ሰውነታቸው፤ውጭና ውስጣቸውን ሲያበሩ ከሰው በላይ ያለን
መንፈሳዊ አካል ንግግር የሚያዳምጡና የሚረዱበት፤ በምስል
የሚያሳዩዋቸውን ነገሮች በቅፅበት ከነተግባሩ የሚገነዘቡበት፤ልዩ የጥበብ
መገለጥ ውስጥ የሚገቡበት፤ተጨማሪ የአስተሳሰብ መጠን የሚታደሉበት
ነው። በሰው ዘንድ ከተለመደው ከ 0.1 % ወደ 20 % የአስተሳሰብ
መጠናቸው ከፍ የሚልበት ነው።

ፍሥሐ ያዚ

እናም አሁን ውጭና ውስጣቸውን ሲያበሩ የሚከሰተው ምልክት በሁሉም መሪዎች ፊት ላይ ታዩ፡፡በግንባሮቻቸው ግራና ቀኝ አጫጭርና ጥቋቁር ቀንዶቻቸው ብቅ ብቅ አሉ፡፡በየግንባሮቻቸው መሃል ላይም በጥቁር ደማቅ ቀለም የቁጥር ምልክቱ ደምቆ ታዩ፡፡ዓይኖቻቸውም እሳት የሚተፉ መስለው ወደ ነባልባላማነት ተለወጡ፡፡

የአዳራሹ መድረክ ላይ በርከክ ብለው የነበሩት የቫቲካኑ ጳጳስም በዝግታ ከተንበረከኩበት ቀና ሲሉ፤ በተመሳሳይ ውጭና ውስጣቸው በርቶ ጥቋቁርና አጫጭር ጥምዝ ቀንዶቻቸው በግንባራቸው ግራና ቀኝ ብቅ ብቅ ብለው መታየት ጀመሩ፡፡የቁጥር ምልክቱም በግንባራቸው መሃል ላይ ደምቆ መታየት ጀመረ፡፡

ጳጳሱ የአዳራሹ መድረክ ላይ ሆነው አንገታቸውን ወደ ላይ አቃንተውና ሁለት እጆቻቸውን ለተማፅኖ ወደ ላይ ዘርግተው፤

‹‹ልዑል ሆይ፤ታዛዦችህ ታዛዥ ቤተሰቦችህን ለመተዋወቅ ዝግጁ ናቸው!››አሉ፤ ትህትናና ታዛዥነት በሚንፀባረቅበት ድመፀት፡፡

ይህን ብለው ጎንበስ ሲሉ፤ስፊው የአዳራሹ መድረክ ላይ ጥቁር ደመና የመሰለ የሚትጎለጎል ጭስ መታየት ጀመረና መጠኑ እየጨመረ፣ የበለጠ እየጠቆረ፣ ሄዶ የአዳራሹን መድረክ አጨለመው፡፡ሙሉ ለሙሉ በጥቁር ጭስ በተሸፈነው መድረክ ላይም ድንገተኛና አስደንጋጭ የሆነ አስገምጋሚ ድምፅ መሰማት ጀመረ፡፡

በዚህ ጊዜ ውስጣቸውን አብርተው ተቀምጠው የነበሩት የ G 20 አገራት መሪዎች በአንድነት ተነስተው በየወንበሮቻቸው ስር በፍጥነት በርከክ አሉ፡፡

‹‹የአዲሲቷ የምድር መንግስት ምስረታ አስፈፃሚዎችና የዘላለም ሹማምንት!የልዑላችሁ የድልና የንግስና ዘመን ደርሷልና በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ!ዛሬም ልዑላችሁ ሌላ ሚስጥር እንድታውቁ ፈቅዷልና እወቁ፡፡ እንግዳችሁን በክብር ተቀበሉና እስተናግዷት!አድምጧት!ተረዷት!ስሟት!ታዘዟት!ልዑላችሁንም እመስግኑ!እመስግኑ!››የሚል ድምፅ በጥቁሩ አስፈሪ ጭስ ውስጥ ከተሰማ በኋላ፤ጭሱም ድምፁም ጠፉና አዳራሹ መልሶ በዝምታ ተዋጠ፡፡

በጥቁሩ ጭስ ተሸፍነው የቆዩት ጳጳሱም ጭሱ በኖ ሲጠፋ በቆሙበት ቦታ እንዳሉ ሆነው ታዩ፡፡ካጎነበሱበት ቀና ብለው፤

‹‹ክብር ለልዑላችን ይሁን፤ አሜን!››ሲሉ፤

‹‹አሜን!››የሚል የጋራ ድምፅ ተሰማ፡፡

‹‹ክብር ለጭለማው ልዑል!››

‹‹አሜን!››

‹‹ክብር ለአሸናፊው አብዮተኞችን!››

‹‹አሜን!››

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

‹‹አሁን ተነሱና ቆማችሁ እንግዳችሁን ተቀበሉ››የሚል ትዕዛዝ ሲሰጡ
ሁሉም ተሰብሳቢዎች ከተንበረከኩበት ተነስተው ቆሙ፡፡
በዚያ ባማረና በተንጣለለ ምቹና ሰፊ፤ ነገር ግን አስፈሪ በሆነ ዘመናዊ
አዳራሽ ውስጥ የሚገኙት የ G 20 አገራት መሪዎች ደማቅና በጣም ቀይ
የሚባል አንድ አይነት ሱፍ ነው የለበሱት፡፡
ቀይ ሱሪ፣ቀይ ኮት፣ቀይ ሸሚዝ፣ለብሰው፤ ቀይ ከረባት አስረው፣ ሙሉ
በሙሉ ቀይ የሆነ የቆዳ ጫማ ተጫምተዋል፡፡ የአዳራሹ መድረክም ሆነ
ዝቅ ብሎ ያለው የተሰብሳቢዎች ቦታ ወለሉ ደማቅና ለስላሳ በሆነ ቀይ
ምንጣፍ የተሸፈነ ነው፡፡ግድግዳውም፣ የአዳራሹ ጣራ የውስጥ ክፍልም፣
ሙሉ በሙሉ በደማቅ ቀይ ጨርቅ የተሸፈነ ነው፡፡የተሰብሳቢዎች
መቀመጫ ወንበርም በተመሳሳይ ቀይ ነው፡፡የጀርመኗ ቻንስለርም
በተመሳሳይ የወንዶቹን አይነት አለባበስ ለብሰው ነው የሚታዩት፡፡ጳጳሱም
የለበሱት ተመሳሳይ ድምቀት ያለው ቀይ ቀሚስ ሲሆን፤የደረቡት ካባም
እንዲሁ ቀይ ነው፡፡የራስ ቅላቸው ላይም ቀይ ቆብ ጣል አድርገዋል፡፡
ጫማቸውም ቀይ ነው፡፡ሁሉም ነገር ቀይ!በዚህ ላይ በግንባሮቻቸው ግራና
ቀኝ አጫጭርና ጥቋቁር ጥምዝ ቀንዶቻቸው እየታዩ፤በግንባራቸው መሃል
ላይ በጥቁር ደማቅ የኩል ቀለም የታተመው የአውሬው ምልክትና ዓርማ
የሆነው 666 የሚለው ቁጥር እየታዬ፤ዓይኖቻቸው ወደ ቀይ ነበልባላማነት
ተለውጠው በፀጥታ ቆመው ሲታዩ ማንኛውንም ሰው ሊያስደነግጡ
ከመቻላቸውም በላይ፤የዓለማችን ታዋቂ ሰዎችና የስልጡን አገራት
መሪዎች መሆናቸውን እንድንጠራጠር ያደርጋሉ፡፡እነዚህ እጅግ አስደንጋጭ
ፍጡሮች በሰፊና አስፈሪ ግዙፍ ቀይ አዳራሽ ውስጥ ተሰባስበው
እንግዳቸውን ለመቀበል ተዘጋጅተው በጉጉት እየተጠባበቁ ነው፡፡
አዲሱ እንግዳ ማንና እነማን እንደሆኑ ከቫቲካኑ ጳጳስና ምናልባትም ከ G
8 አገራት መሪዎች በስተቀር ማንም አያውቅ እንደነበር በሌሎች በሁሉም
ተሰብሳቢዎች የጋራ ድንጋጤና የግርምት አስተያየት ማረጋገጥ ተቻለ፡፡
ሌሎቹ አያውቁ የነበሩት እንግዳቸው ተንሳፍፈው መጥተው ሲያርፉ
በድንጋጤና ባለማመን አፋቸውን ከፍተው፤ ዓይኖቻቸውን አፍጥጠው፣
ነበር የሚታዩት፡፡
ያረጁና የፊታቸው ቆዳ የተጨማደደ፣በዕድሜ መግፋት ምክንያት ጎበጥ
ያሉ፣ቁመታቸው አጭር፣ ፀጉራቸው የሸበተ አሮጊት ሴትዮ በተለመደው
ምትሃተኛ መንገድ ከአዳራሹ ጣራ በኩል ያለ አንዳች ኮሽታና ያለ አንዳች
የኮርኒስም ሆነ የጣራ ቀዳዳ እንዲሁ ሰፍፍፍፍፍ.... እያሉ ወደ አዳራሹ
መጡና የአዳራሹ መድረክ ወለል ላይ እርፍፍፍፍ.......... አሉ፡፡
በዚህ ጊዜ የቫቲካኑ ጳጳስ መድረኩ ላይ እንዳሉ፤ከወንባቸው ሽብረክ በማለት
እጅ ከነሱ በኋላ፤ቤተሰባዊ ፈገግታ እያሳዩ ወደ እንግዳዋ ጠጋ ...

ፍሥሐ ያዜ

ብለውም በሁለት እጆቻቸው የአሮጊቷን በቀይ ጓንት የተሸፈነ ቀኝ እጅ ከፍ አድርገው ስመው ለቀቁ፡፡
እንግዳዋም እንደሌሎች ቀይ በቀይ ለብሰው የመጡ ናቸው፡፡ቀይ ጉርድ ቀሚስ፣ቀይ ኮት፣ቀይ ካፖርት፣ቀይ ካባ፣ቀይ ጫማ፣ቀይ ስካርፍ፣ቀይ የአንገት ሪቫን፣ቀይ የእጅ ጓንት፣ቀይ ዓይነ ርግብ፣ምናልባትም ቀይ ሙታንታ....፡፡በዚህ ላይ ከንፈራቸውን ቀይ ሊፒስቲክ ተቀብተውታል፡፡
ሴትዮዋ መድረኩ ላይ ካረፉ በኂላ ፀጉራቸው ላይ ጣል አድርገውት የነበረውን ስስና ወንፊት የመሰለ ቀይ ዓይነ ርግባቸውን በአንድ እጃቸው ከራሳቸው ላይ አንስተው በዝግታ ለቫቲካኑ ጳጳስ ሰጧቸው፡፡ጳጳሱም ዓይነ ርግባቸውን ተቀብለው መድረኩ ላይ ባለው የንግግር ማድረጊያ ቦታ በዝግታና በክብር አስቀምጠው፤እጆቻቸውን ወደ ኂላ አጣምረው ፊንጠር ብለው ቆሙ፡፡
ሴትዮዋ በአየር ላይ እየተንሳፈፉ ጣራውን አልፈው የአዳራሹ ወለል ላይ ገና ሳያርፉ የጀመረው የተሰብሳቢዎች አግራሞት፤በምቹው የአዳራሹ መድረክ ወለል ላይ ካረፉ በኂላ እንኳን የበለጠ እየሆነ ሄደ እንጂ አግራሞቱ የለቀቀው መሪ በቪዲዮው አልታየም፡፡በዚህ የጋራ መደነቅና ያለማመን ምክንያትም ተሰብሳቢዎቹ የ G 20 አገራት መሪዎች ቀጣዩን ተግባራቸውን ዘንግተው ባለማመን አፋቸውን ከፍተውና ፈዝዘው እንደቆሙ ነበሩ፡፡
በዚህ ሁኔታ እንዳሉ ሴትዮዋ አጠገብ የቆሙት የቫቲካኑ ጳጳስ መድረኩ ላይ ሆነው በእጅ ምልክት፤‹‹ቀጥሉ››እንደማለት ሲሏቸው፤ሁሉም መሪዎች ከግርምታዊ ድንዛዜያቸው በመንቃት በአንድነት በእጆቻቸው የሆረስ ፒራሚድን ዓርማ ሰርተው ወደ ግንባሮቻቸው ወስደው በመስጠፍ እክብሮታዊ ሰላምታቸውን አቀረቡ፡፡ይህን ካደረጉና እፀፋውም ከተመለሰላቸው በኂላ፤እንግዳቸው፤‹‹ክብር ለልዑላችን!››አሉ፤ ዝግና ዝቅ ባለ ድምፅ፡፡
ተሰብሳቢዎቹም ‹‹አሜን!››አሉ ቀዝቀዝ ብለው፡፡
‹‹ተቀመጡ››አሉዋቸው፡፡ተሰብሳቢዎቹ ዓይኖቻቸውን ሴትዮዋ ላይ እንደተከሉ በያሉበት ተቀመጡ፡፡
‹‹መልካም ነው!እንዲህ አምሮብን ስንታይ ደስ ይላል፡፡ክብር ለልዑላችን ይሁን!››
‹‹አሜን!››
‹‹አምን!ሲሉ ጀመሩ፡፡፡‹‹አምን!እንዲህ ውጭና ውስጥ ማብራት መቻል ትልቅ ዕድል ነው፡፡ይህ ከልዑላችን የተሰጣችሁ ትልቅ የጥበብ ፀጋ እንድንደማመጥና ሁሉን እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ ሁሉን እንድንረዳ፣ሁሉን እንድንችል ያደርገናል!ወደፊትም ብዙ ጥበብ በልዑላችን ይሁንታ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ይገለጣል!››ሲሉ፤ከተሰብሳቢዎቹ በኩል ሌላ የግርምት ጉርምርምታ እንደመደመጥ ሲል፤ጭርጭስ ያሉት ጎባጣ አሮጊት ሴትዮ፤ጉድጓድ ውስጥ ያሉ በሚመስሉ ሰርሳሪ ዓይኖቻቸው ተሰብሳቢዎችን ከርቀት እያዩ፤ፈገግ በማለት፤

‹‹ገብቶኛል››አሉና የጋራ ጉርምርምታውን በእጅ ምልክት አስቆሙት፡፡

‹‹የመጀመሪያው መደነቃችሁ እኔን ባለማወቃችሁና እንግዳዋም አሷ ትሆናለች ብላችሁ ባለመጠበቃችሁ ነበር፡፡አሁን ደግሞ እንዴት እኛ ውስጣችንን አብርተን ተናጋሪዋ ውስጧን ሳታበራ ታናግረናለች ነው ጉርምርምታው፡፡አንዳንዶቻችሁንም ሳይ ውስጣችሁን ለማጥፋት የቃጣችሁ አላችሁ፡፡ግድ የለም፤ልክ ናችሁ፡፡ሆኖም....››አሉና፤ሲጀምሩ ቀጭን የነበረ ድምፃቸውን ወፈር፤ዝቅ ያለ የነበረ ድምፃቸውን ዘለግ፤ በቀስታ የጀመሩትን ንግግር ፈጠን፤ እርጋታቸውንና ፈገግታቸውን ተወት በማድረግ ኮስተር ብለው ቀጠሉ፡፡

‹‹አለመተዋወቃችን ነው፡፡ያን አለመተዋወቅ ዛሬ በመተዋወቅ እንተካዋለንና አታስቡ፤ግራም አይግባችሁ፡፡እኔን የምታውቁኝ የታላቋ ብሪታኒያ ንግስት መሆኔን ብቻ ነበር፡፡እናም ሰው መሆኔን ብቻ፡፡እንደዚያ አይደለም ክቡራን፡፡እኛ ከቀድሞ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ሰዎች አልነበርንም፡፡ሙሉ በሙሉ ሰዎች ስላልሆንም እናንተ ውጪና ውስጣችሁን አብርታችሁ፤ እኛ ሳናበራ እንችላለን፡፡ስናበራም እናንተ ውስጣችሁን ስታበሩ ካላችሁ መጠን ከፍ ካገኘነውና ካለን በላይ ከፍ እንላለን፡፡ለዚያ ነው፡፡እኛ የእንግሊዝ ነገስታት ቤተሰቦች በሙሉ የልዑላችን ጭፍሮች ድቅል ነን!››ሲሉ፤ቀስ ብሎ እየጋለ፣ እየጋለ፣ እየደመቀ፣ ሄደ፡፡ የጀመረው በግርምት የታጀበ የተሰብሳቢዎች የጋራ ጭብጨባ ቀስ በቀስ ንግስቲቱ ረዘም ያለውን አድናቆት አዘል የግርምት ጭብጨባ ታግሰው አስጨረሱና ቀጠሉ፡፡

‹‹አዎን!ዓለምና ህዝቦቿ እኛን የሚያውቁን በእንግሊዝ ንግስትነትና በንጉሱ ነገስትነት ወይም የነገስታት ቤተሰቦች እንደሆንን ብቻ ነው፡፡ እናንተም እንደዚያው፡፡መደነቃችሁ ከዚህ የመነጨ ነውና ጉርምርምታው ተገቢ ነበር፡፡ስለዚህ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ይሄን ዕውነትና ሌሎች ሚስጥሮችን ለእናንተ ይፋ ሳደርግ እዚህ ተገኝቻለሁ፡፡ ምክንያቱም እናንተ አሁን ላይ ዘመኑ መድረሱ ተነግሯችሁ ውስጥ የማብራት ጥበብ ለመታደል የበቃችሁ ሆናችኋልና ነው፡፡ ይህ ማለት የአዲሲቷ የምድር መንግስት ምስረታ ዋና አስፈፃሚዎችና ሹማምንት መሆናችሁ በይፋ ታጩጀላችኋል ማለት ነው፡፡ያ ስለሆነም ይህ የጥበብ

ፍሥሐ ያዜ

ፀጋ ተሰጥቷችኋል።ይህም ዘመኑ ለመቃረቡና ለመድረሱ አስረጂ ነው። ስለዚህ እኛም ከዓለም ህዝብ ደብቀንና ሰውረን በሚስጥር የያዝናቸውን ነገሮችና እውነተኛ ማንነታችን ለእናንተ ይፋ የማድረጊያው ትክክለኛ ጊዜያችን ሆነ ማለት ነው።እናም እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ!ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹ክብር ለአሸናፊያችን!››

‹‹አሜን!››የጋለ የጋራ ጭብጨባ አዳራሹን አደመቀው።

‹‹ይህን ውጭና ውስጥ የማብራት ጥበብ ያጎናፀፋችሁን ልዑል ሁሌም ማመስገንና ክብር መስጠት አለባችሁ።ውስጥና ውጭ በማብራት የሚገኘው ደስታና ትልቅ የሆነ ሃሴት ለሌላው ተራ ሰው ሊገባው ባይችልም፤ለኛ ግን ምን ማለት እንደሆነ አውቃችኋልና፤ ስለዚህ በመብቃታችሁ ብቻ ሁሌም ደስ ልትሰኙ፤ ልዑላችሁንም ልታመሰግኑ ይገባል።

ውስጣችን ስናበራ የሚገለጥልንን ጥበብና እውቀት ከኛና ከእናንተ ስለዚህ ከታደልነው ውጭ ማን ሊረዳው ይችላል?ስለዚህ በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ!››አሉና፤ በፈገግታ ደምቀው ለራሳቸው ንግግር ራሳቸው ሲያጨበጭቡ ተሰብሳቢዎችም ተከተሉና የጋራ ጭብጨባ አስደመጡ። ‹‹አትረፍ ያለው በሬ ቆዳው ከበሮ ይሆናል››እንዲሉ፤እነዚህ በምቾት ብዛት የለሰለሱ የተሰብሳቢዎች የእጅ መዳፎች በዚህና በሌሎች አዳራሾች ውስጥ በየንግግሩ መደምደሚያ በሃይል እየተላተሙ የሚያወጡት ድምፅ ጉድ የሚያስብል ነው።በየደቂቃው ሲያጨበጭቡ መዳፎቻቸው አይታመሙም፤ ክንዶቻቸው አይዝሉም።በየንግግሩ መሃል ይጨበጨባል።ጭብጨባውን አዳራሹ ተቀብሎ ስለሚያስተጋባውም ድምቀቱ የሀያ ሰው ሳይሆን የሃያ ሺ ሰው የጋራ ጭብጨባ ነው የሚመስለው።

‹‹ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹ንግስና ለባለ ድል አብዮተኞችን!››

‹‹አሜን!››የጋራ ጭብጨባ.......

አሮጊቷ የእንግሊዝ ንግስት መድረኩ ላይ ጎርደድ ጎርደድ እያሉ ቀጠሉ።

‹‹መልካም፤እኔ ውስጤን ሳላበራ ከእናንተ ጋር እኩል መሆን መቻሌ ለመደማመጥ ይረዳናል።ቢሆንም ግራ መጋባታችሁን ለማጥራት ያህል...››አሉና፤ዓይኖቻቸውን ለስድስት ሰከንዶች ያህል ጨፍነው ገለጡ። በዚህ ጊዜ በእርጅና ምክንያት የተኮማተረው የፊት ቆዳቸው እንደመዘረጋጋት ብሎ፤ ዓይኖቻቸው ወደ ነበልባላማነት ተለወጡና የግንባራቸው መሃል ላይ ምልክቱ ታየ።ግራና ቀኝም ጥቋቁርና ጥምዝ ቀንዶች ብቅ ብቅ ብለው መታየት ጀመሩ።በዚሁ ቅፅበትም ከሌሎች በተለየ

ሁኔታ የፊት ቅርፃቸው ወደ ሶስት ማዕዘንነት ተቀየረ።ይህን
ተሰብሳቢዎቹ የ G 20 አገራት መሪዎች ይበልጥ ተደነቁ።
ንግስቲቱ እንደ እነሱ ብቻ ሳይሆን፤ከእነሱ በበለጠና በተለየ መልኩ ውጭ
ውስጥ ማብራት መቻላቸውን ለተሰብሳቢዎቹ ካረጋገጡ በኋላ፤ መልሰው
አጥፍተው ወደ ቀድሞው ገፅታቸው ተመለሱ።ሰው ሆኑ፤ ወይም ሰው
መሰሉ።

አሁንም አዳራሹ በጭብጨባ ተናጠ።

አሮጊቷ የእንግሊዝ ንግስት ንግግር ሲያደርጉም ሆነ ልደታቸውን
ሲያከብሩ፤ ወይም በሌላ አገራዊ ጉዳይ ታዳሚ ሆነው የዓለም ህዝብ
በቴሌቭዥን ሲያያቸው፤የንግስትነት ወግና ማዕረግ የተላበሱ፣ ኩሩ፣
ጥንቁቅ፣ የደስ ደስ ያላቸው፣ በመላው ዓለም ህዝብ ዘንድ የተከበሩና
የታፈሩ፣በየሄዱበት ህዝብ በደስታ የሚያጨበጭብላቸው፣ህዝቡ እሳቸውን
ለማየት የሚቅበዘበዝና በየጎዳናው ተሰልፎ የሚጋፋላቸው፣ፍፁም ጨዋና
እውነተኛ የሰው ፍጡር የሆኑ ክብር ያላቸው ሴት ይመስላሉ።

ነገር ግን እንደዚያ አይደሉም።እውነታው ሌላ ነው።በሰው ዓይንና አእምሮ
እንዲያ እየታዩና እንዲያ እየታሰቡ ዓለምን ማታለል የቻሉ፤እጅግ የበሸቀጠ
ስብዕና ያላቸው፤ የዓለማችን ርካሽና ቆሻሻ የሆኑ ሴት መሆናቸውን ማን
ይናገር?ከተባለ ምላሹ፤ ‹‹ራሳቸው››እንዲሁም ‹‹ቀጣይ ተግባራቸውን ያየ››
የሚል ነው።

አሮጊቷ የእንግሊዝ ንግስት ራሳቸውን ለተሰብሳቢዎች የ G 20 አገራት
መሪዎች ሲያስተዋውቁ እንደሚታየውና እንደሚደመጠው የሰይጣን
ቁራጭና ውላጅ ናቸው።እውነተኛ ገፅታቸውና ማንነታቸው ዓለም
ሲያውቀው የኖረውና ተታሎ የሳላቸው ዓይነት ካለመሆናቸውም በላይ፤
የዘር ሀረጋቸውን ከስረ መሰረቱ ራሳቸው ሲያብራሩ፤ከሰው ብቻ ያልሆኑና
በእነ ዝማስያ ከሚመራው የሳጥናኤል ጭፍራ የዘር ሃረግ የሚመዘዙ
ናቸው።እሳቸውና መላው ቤተሰባቸው ከሰውና ከኔፊሊም ከተደቀሉ ከጥንት
አሳሳች የሳጥናኤል ‹‹ጭፍሮች›› የዘር ሃረግ የተወራረሱ ናቸው።ይህን
ደግሞ የመላው ዓለም ህዝብ እራሳቸው ካልገለጡለት በቀር የሚያውቅበት
ምንም ዕድል የለውም፤ወይም አልነበረውም።አሁን ዘመኑን ጠብቆ
መከናወን ካለበት ተግባር ጋር በተያያዘ ምክንያት ግን ራሳቸውንና የዘረ
ሃረጋቸውን ይፋ ሊያደርጉ ተገደዋል።

አሮጊቷ የእንግሊዝ ንግስት የአዳራሹ መድረክ ላይ በዝግታና በቁንጥ
አረማመድ ጥቂት ጎርደድ ጎርደድካሉ በኋላ፤ መድረኩ ላይ ፊንጠር
ብለው እጆቻቸውን ወደ ኋላ አጣምረው ታዛዥነት በሚስተዋልበት አቋቋም
ቆመው የነበሩትን የቫቲካኑን ጳጳስ በእጅ ምልክት ወደ ተሰብሳቢዎች
እንዲሄዱና እንዲቀመጡ አዘዟቸው።ጳጳሱም ለንግስቲቱ አክብሮታዊ

ፍሥሐ ያዚ

የእሽታ ምልክት አሳይተውና እጅ ነስተው ከመድረኩ ወርደው በመሄድ፣ ከተሰብሳቢዎቹ ፊት ለብቻው ካለውና ለሳቸው እንደተዘጋጀ ከሚያስታውቀው ቀይ ወንበር ላይ ተቀመጡ፡፡
ቢዚህም ከጳጳሱ ይልቅ የእንግሊዟ ንግስት ልዑላችን ለሚሉት ለሳጥናኤል ቅርብ መሆናቸውንና በስልጣንም መብለጣቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ በተግባራዊ እንቅስቃሴ መረዳት ተቻለ፡፡
ጳጳሱ ከተቀመጡ በኂላ፣ንግስቲቱ በደማቅ የመብራት ብርሃን የተጥለቀለቀውን አብረቅራቂ ቀይ አዳራሽ አንድ እጃቸውን በማንሳት ብቻ ሁሉንም መብራቶች አጠፉና ብርሃኑን በጭለማ ተኩት፡፡አዳራሹ ሙሉ በሙሉ ጨለማ ሆኖ ቀየና፣ከጥቂት ቆይታ በኂላ ደብዘዝ ባለ የጭላንጭል ብርሃን ተተካ፡፡
‹‹የአዲሲቷ ዓለም ሹማምንት የሆናችሁ ክቡራንና ክቡራት! እኔ ውስጤን ሳላበራ እናንተ ኡብርታችሁ መነጋገር የሚኖርብን ለምን እንደሆነ የተረዳችሁ ይመስለኛል፡፡እናንተ ውስጣችሁን አብርታችሁ እኔ ውስጤን ሳላበራ ከእናንተ ጋር መግባባት ስለምችል ነው፡፡በተመሳሳይም እናንተም ሳታበሩ፣እኔም ሳላበራ እንዲሁ መግባባት እንችላለን፡፡ያ የሚሆነውም እኛ ድቅሎች በጣም ዝቅ ብለን ሰው ሆነንና መስለን ሰዎችን የማስረዳት ጥበብ ስላለን ነው፡፡
እናንተ 20፣ እኔ በተፈጥሮየ ካለኝ የተለየ አቅም ከእናንተ በጣም ላቅ ብዬ ጉባኤውን ብመራው ልንግባባ ብንችል እንኳን፣የምለውን ከመስማት ባለፈ፣ ‹‹ወደፊት የሚሆንና ሆኖ ያለፈ›› እያልኩ የምገልፅላችሁን ነገር በሙሉ በአእምሯችሁ ውስጥ ከነድርጊቱና ከነዘመኑ ከነክንውኑ በተግባር ሲታያችሁ መጠነኛ መፋለስ እንዳይኖር በሚል ነው፡፡መራራቅ ካለ ሙሉ መግባባት ውስጥ ሳንሆን እንችላለን፡፡
ስለዚህ በምናገረው መጠን ንግግሬ እኩል ይገባችሁ ዘንድ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል የማሳያችሁን ሁሉ በበራው ውጭና ውስጣችሁ አማካኝነት በብርሃን ፍጥነትና በረቀቀ የመረዳት አቅም እኩል በአእምሯችሁ ውስጥ በተግባር ታዩት ዘንድ፣ሁሉም ታሪክ ሲተረክላችሁ አሁን እንደተከናወነና በተግባር እየተደገመላችሁ እንዳለ ሆኖ ይሰማችሁ ዘንድ፣ከነተግባራዊ ክንውኑ እየተገለፀላችሁ በቅፅበት ትረዱት ዘንድ፣በእኩል የአስተሳሰብና የመረዳት መጠን ብንሆን የተሻለ ስለሚሆን ነው፡፡እናም ማብራት እየቻልኩ ያላበራሁት ለዚህ እንደሆነ ተረዱ፡፡እኛ የእንግሊዝ የነገስታት ዘሮች የምንባለው በሙሉ በርቶልን የተፈጠርን ስለሆንን ማለቴ ነው፡፡ስለዚህ የዛሬውን የዝግ ጉባኤያችንን ለማድረግ እኔና እናንተ በተመጣጣኝ የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ ነን፡፡እናም እንቀጥላለን፡፡

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

‹‹ጉባኤውን ከመቀጠላችን በፊት ግን ተገቢውን ክብር፣ምስጋናና አምልኮ ንግስና ለሚገባው ለልዑላችን መስጠትና ታዛዥነታችንም ደጋግመን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

እኛ የእርሱ ነን።እናንተም የእርሱ ሆናችኋል።እርሱ ደግሞ የሁላችንም ነው። እርሱን ማምለክ የእርሱ መሆን ማለት ነው። እርሱን ማክበር በእርሱ መከበር ማለት ነው።እርሱን መታዘዝ ሁሉን ከእርሱ መቀበል ማለት ነው።የእርሱን ጥበብና እውቀት ሁሉ መቀበል ማለት ነው! ስለዚህ ለዘላለማዊ ህይወት የታጫችሁ ሹማምንት ናችሁና ምስጋናና አምልኳችሁን ሁሌም በተገቢው መንገድ ለእርሱ ማቅረባችሁን መቀጠል አለባችሁ። ደስታችሁንም ለእርሱ መግለፅና መንገር ይኖርባችኋል። ደስታችሁ በሌላ በማንም ሳይሆን በእርሱ ብቻ ነው።ይህ ስለሆነ እርሱን ማስደሰት የዘወትር ተግባራችን ነው ማለት ይሆናል።እርሱ የሚደሰተው ደግሞ በእኛ ታማኝ አገልጋይነትና ታዛዥነት ነው።እርሱ የበላይ አካሉ ተቃራኒ ነውና እርሱን መምሰል ከእኛ ይጠበቃል።ተቃራኒነት ከዚህ ይጀምራል...›› አሉና የጀርመኗን ቻንስለር በእጅ ምልክት ወደ መድረኩ ይመጡ ዘንድ ጋበዟቸው።ለሌሎችም እርስ በእርሳቸው አፀያፊውን ተግባር እንዲፈፅሙ ትዕዛዝ ሰጧቸው።

የጀርመኗ ቻንስለር እየተራመዱ ባለበት ጊዜ ንግስቲቱ ንግግራቸውን ቀጥለዋል።

‹‹አም!ዓለምና በውስጧ ያለው ጥበብ እንዲሁም ህዝቦቿ በእናንተ ስር ይሆኑ ዘንድ፣ ወደፊት ሊሆን በሚገባው ተግባር የልዑላችን ተባባሪ ታደርጓቸው ዘንድ፣እንድም የሚሳናችሁ ነገር እንዳይኖርና፣ አዲስቷ የምድር መንግስት እንዲህ በግ ብላ ትታያችሁ ዘንድ የበላይ አኳሉ ተቃራኒ መሆናችሁን በተግባር ከመግለፅ እንዳትቦዝኑ አስጠንቅቃችኋለሁ። ለኛ የዘላለም ህይወት ሊሰጥ የተዘጋጀው ልዑላችን ሁሉም እኛን ሲያስደስት የኖረ፣እያስደሰተንም ያለ፣ወደፊትም ለዘላለም ሊያስደስተን የተዘጋጀ ነውና እኛም እሱ የሚደሰትበትን ተግባር በመፈፀም ልናስደስተው ይገባል።ስለዚህ እንዲሁ ውጭና ውስጣችሁን እንዳበራችሁ ጥንድ ጥንድ በመሆን፣በየግንባሮቻችሁ ላይ ያለውን የልዑላችን ዓርማ የሆነውን የቁጥር ማህተም ፊት ለፊት በማቀራረብ፣ምልክታችሁንም ፊት ለፊት በማገጣጠምና በማገናኘት ሀሴት አድርጉ!ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተጣመሩና በጥልቅ ተሳሳሙ!

ልዑላችን የበላይ አካሉ ተቃራኒ ነው።በመሆኑም ልዑላችን ከሚደሰትባቸውና ከሚመለክባቸው ብዙ መንገዶችና ብዙ ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋናው የተመሳሳይ ፆታ ጥልቅ ወሲብ ነው።ይህን ተግባር መፈፀም እራስን አስደስቶ እርሱንም ማስደሰት ማለት ነው።ዋናው የአምልኮ

ስርዓትም ይህና የደም መስዋዕት መሆኑን ታውቃላችሁ።ስለዚህ ቀጥሉ!አምልኩት! እየተደሰታችሁ አስደስቱት!የእርሱ መሆናችሁን በዚህ ጣፋጭ በሆነ ተግባር አረጋግጡለት!ታማኝ አገልጋዮችህና ታዛዦችህ ነን በሉት!ቀጥሉ...!››አሉዋቸውና፤በጭላንጭል ብርሃን ተወስኖ የቆየውን አዳራሽ እንደገና በእጅ ምልክት ሙሉ በሙሉ አበሩላቸው።

የዓለም ህዝብ አመነም አላመነም ይህ መገለፅ አለበት።እነዚህ ሱፍ ለብሰው፤ ከረባት አስረው፤በወታደራዊ ስልፍ ታጅበው፤ ባለትዳር መስለውና፤ ሚስቶቻቸውን አስከትለው በአውሮፕላን ወዲያ ወዲህ እያሉ፤በየአገራቱና በየመድረኩ ንግግር እያደረጉ የሚያስጨበጭቡ ታዋቂ የአገር መሪዎች፤ እንዲህ አደረጉ ተብሎ ቢነገርና ቢፃፍ ላይታመን ይችላል።ታመነም አልታመነም መገለጽ ግን ይኖርበታል!

‹‹ቀጥሉ››እንደተባሉ፤ተሰብሳቢዎቹ ከነቀንዶቻቸው እርስ በእርስ እየተፈላለጉ ግንባር ለግንባር ገጥመው ከንፈር ለከፈንፈር መሳሳም ጀመሩ። ወዲያው ግን አስደንጋጭ ነገር ተስተዋለ!ከተሰብሳቢዎች ውስጥ አንዱ የነበሩት የሩሲያው ፕሬዝዳንት በአዳራሹ ወስጥ የሉም። የአዳራሹ መብራት በንግስቲቱ የእጅ ምልክት ጠፍቶ መልሶ በጭላንጭል ብርሃን እስኪተካ ድረስ የሩሲያው መሪ ከተሰብሰቢዎች የ G 20 አገራት መሪዎች ውስጥ አንዱ ነበሩና በቪዲዮው ይታዩ ነበር።ሙሉ በሙሉ የአዳራሹ መብራቶች ሲበሩና ሁሉም ሲታይ ግን የሩሲያው መሪ በቦታቸው አልታዩም።በምን መንገድ እንደወጡም አልታወቀም።በዚህም በተሰብሳቢዎች በኩል ግራ መጋባት ተፈጠረና እርስ በርስ መሳሳማቸውን አቁመው የጋራ ጉርምርምታ ማስደመጥ ጀመሩ።ይህን ያስተዋሉት ንግስቲቱ፤

‹‹ተውት፤ሲወጣ እያየሁት ነበር!አትገረሙ!የትም አይደርስም። እስቲ ተከተለው!ሌሎቻችሁ ቀጥሉ!››በማለት ለጳጳሱ ትእዛዝ ሰጡ።ጳጳሱም በታዘዙት መሰረት የጠፋውን ፕሬዘዳንት ለመከተል አኮበኮቡ።ጳጳሱ እንደተቀመጡ ከነ ወንበራቸው ወደ ላይ ከፍ ብለው እየተንሳፈፉ ያለአንዳች ኮሽታ ድምፅ የአዳራሹን ጣራ አልፈው ሄዱ፤በረሩ ወይም ተሰለቡ።

ሌሎች ተሰብሳቢዎች አውሬነት ተብሎ እንኳን ሊገለፅ በማይችል መንገድ (አውሬዎች እንዲህ ያለ አስፀያፊ ነገር አይፈጽሙምና) እርስ በርስ ቀንዶቻቸውን አጋጥመው ከንፈር ለከንፈር እየተሳሳሙ አምልኳቸውን ቀጠሉ።

በእርጅና ምክንያትም የጎበጡት የእንግሊዝ ንግስት ረጅሟን የጀርመን ቻንስለር ተንጠራርተው በማቀፍና በጉጉት ከንፈራቸውን በመሳም፤እርስ በርስም በማቃለት፤ አንገት ላንገት ተናንቀው እያጓሩ የተመሳሳይ ፆታ ወሲባዊ ግንኙነታቸውን በአዳራሹ መድረክ ላይ ሲፈፅሙ፤ወንዶቹ

ተሰብሳቢዎችም በያሉበት ሆነው ተመሳሳይ ተግባራቸውን ሲፈፀሙ ግማሽ ሰዓት ያህል አሳለፉ::

ጥቁሩ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ከእንግሊዙ፣የፈረንሳዩ ከቤልጂሙ፣ ሌላው ከሌላ፣እየሆኑ በመጣመር የእርኩሰት ተግባራቸውን ቀጥለው ቆዩ:: አዳራሹ አይተው በማያምኑት፣በአእምሮ ስለው በማይገምቱት፣ እጅግ በሚሰቀጥጥ መልኩ በበሸቀጠ ተግባራቸው ተጨማለቀ:: በእርኩሰት ትንፋሽና ትንፋግ ታፈነ::በርኩሰት ጩኸትና በግብረሰዶማውያኑ የስሜት ሲቃ ተሞላ::ሁሉም እርቃናቸውን ሆነው ቀይ ምንጣፍ በተነጠፈበት ወለል ላይ እየተንከባለሉ ተዳሩ::በዚህ ተግባራቸውም ልዑላቸውን አመለኩ፣ አስደሰቱ፣ታዛዥነታቸውን አረጋገጡ ማለት ነው::ከግማሽ ሰዓት ድሪያና ስሪያ በኋላ፤ ሁሉም መግማማታቸውን አጠናቅቀው በላይ በላይ እየተነፈሱና ለልዑላቸው ክብር እየሰጡ፣ እያመሰገኑ፣ ቆይተው፤ በየወንበሩ ስር እያሸቀነጠሩ የጣሉትን ቀያይ ልብስ እያነሱ ለባበሱና በፈገግታ ደምቀው በየወንበሮቻቸው ተቀመጡ::

እነዚህ የሃያላን አገራት መሪዎችና የእንግሊዟ ንግስት ይህን የተቃራኒነት ማረጋገጫ ያሉትንና፤ ልዑላቸው ከሚደሰትበት አንዱና ዋናው የሆነውን፤ ይህ አደነቱን የአምልኮ ተግባር ያከናውኑ በነበረበት ጊዜ፤ ከላይ ይምጡ ከታች፣ በጣራ ይግቡ በምድር፣ ያልታዩ ሁለቱ ዘንዶ መሰል ትልልቅ እባቦች በአዳራሹ መድረክ ግራና ቀኝ ጋደም ብለው ክንውኑን እየተመለከቱና በደስታ እየተንፈራገጡ መታየት ጀምረው ነበር::

ወንዶቹ ለባብሰው ከተቀመጡ በኋላ እነዚህ በግምት ሁለት ሜትር ቁመትና የአንድ የስልክ እንጨት ውፍረት ያላቸው ዘንዶ መሰል እባቦች፤ በሲቃ ስሜት ሲዳክሩ የነበሩትን ሁለት ሴቶች በላብና በፈሳሽ የረጣጠበ ገላቸውን ለጤነኛ ሰው አስፈሪና አስደንጋጭ በሆነ መንገድ፤ እንግዳ የሆነና የዘንዶም የእባብም ባልሆነ ለየት ያለ ምላሶቻቸውን እያወጡ ጠራረጉላቸው::

ሴቶቹም ከፈፀሙት አስቀያሚ ተግባር የበለጠ በነዚህ እባቦች ተግባር የበለጠ ሀሴት ያደረጉ ይመስሉ ነበር::

እነዚህ እንግዳና አስፈሪ ፍጡሮች የሴቶቹን ገላ አደራርቀው ከጨረሱ በኋላ፤ቀድሞ ሲል የነበሩበትን ቦታ ይዘው በመድረኩ ጥግና ጥግ ግራና ቀኝ ሆነው የግድግዳው ማዕዘን ላይ በሆዳቸው ለጥ ብለው ታዩ::

የእንግሊዟ ንግስትና የጀርመኗ መሪም እንደ ወንዶቹ ልብሶቻቸውን ለባብሰው በፍቅር ዓይን እየተያዩ ከተሳሳሙ በኋላ፤ቻንስለሯ የአዳራሹን መድረክ ለቀው ወደ መሰሎቻቸው ሄደው ቦታቸው ላይ ተቀመጡ::

ከሴቶቹ ቀድመው የጨረሱት ተሰብሳቢዎቹ ጥቂት ፋታ ወስደው በየወንበሮቻቸው ተቀምጠው እርስ በርስ እያወሩ፣ እየሳቁ፣ እየተሳሳቁ፣

ነበርና አዳራሹ ለአፍታ ያህል መምህር እንደሌለው ክፍል በጫኸት ተውጦ ነበር፡፡
ንግስቲቱ ልብሳቸውን አስተካክለው መናገር ሲጀምሩ ግን ሁሉም ፀጥ ረጭ አሉና ማዳመጥ ጀመሩ፡፡
‹‹ክብር ለልዑላችን!››አሉ ገርዛዛዋ ንግስት፡፡
‹‹አሜን!››የሚል ድምፅ ተስተጋባ፡፡
‹‹ደስ የሚል የአምልኮ ስርዓት እንደነበር ለሁላችንም ግልፅ ነው!ስለዚህ አመስግኑ!››አሉና እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ጭብጨባ ሲጀምሩ ተሰብሳቢዎችም ቆመው በማጨብጨብ ልዑላቸውን አመሰገኑ፡፡
ንግስቲቱ ቀጠሉ፡፡‹‹ሁሌም እንዲህ አይነት ጣፋጭ ደስታ ውስጥ ሆነን ለመኖር የተዘጋጀን፣ በልዑላችን የተመረጥን፣ የአዲሲቷ ዓለም ሹማምንት ነንና፤ ሁሌም ደስ እያለን ልዑላችንን ማመስገን አለብን፡፡አሁን በዚች ተግባርና የአምልኮ ስርዓት ብቻ ልዑላችን እንዴት እንደሚደሰት፣ በኛ በታማኝ ልጆቹና በታማኝ አገልጋዮች ምን ያህል እንደሚኮራብን፣ እንዴት እንዳስደሰትነው ተመልከቱ!ውስጣችሁን እንዳብራችሁ ወደ ውስጣችሁ ተመልከቱ!››ሲሉ፤ ሁሉም ዓይኖቻቸውን ጨፍነው የመንቀጥቀጥና የማጓራት አይነት ድምፅ እያሰሙ ሰውነታቸውን ማንዘፍዘፍ ጀመሩ፡፡ከጋራ የማቃሰት ድምፅና የሰውነት መርገፍገፍ በኋላ፤
‹‹አያችሁ?››ሲሉ ንግስቲቱ፤ሁሉም ዓይኖቻቸውን ገልጠው ቀንዶቻቸውና ምልክቱ ፊታቸው ላይ የበለጠ ደምቆና ጎልቶ እየታየ አዳራሹን በደማቅ ጭብጨባ ናጡት፡፡
‹‹ይህንን ነው ልዑላችን ከኛ የሚፈልገው፡፡በኛ ደስታ የሚደሰት ልዑል ነው ያለን!በገደብ አልባ ነፃነት ውስጥ ሆነን እንድንኖር ነው የሚፈልገው!ክብር ለልዑላችን!››
‹‹አሜን!››
‹‹አመስግኑ!››በማለት ከአርጊት አንደበት የወጣ በማይመስል አስገምጋሚና ጎርናና ድምፅ ለተሰብሰቢዎች ትዕዛዝ ሰጡ፡፡
የ G 20 አገራት መሪዎችም ትዕዛዛቸውን ተቀብለው በአንድነት ልዑላቸውን ማመስገን ቀጠሉ፡፡በጫኸት በማጓራት፣ በመንፈራገጥ፣ በመንከባለል አመሰገኑ፡፡
በዚህ መሃል ቀደም ሲል፤‹‹ተከተለው!››ተብለው የተላኩት ጳጳስ በማይታመን መልኩ ባንድ እጃቸው የሩሲያውን መሪ እንደ ወፍ ታቅፈው ወንበራቸው ላይ እንደተቀመጡ እየበረሩ መጡና የአዳራሹን ጣራ አልፈው ስፍፍፍፍ እያሉ ቦታቸው ላይ አረፉ፡፡በምትሃተኛ ዘዴያቸው ከመጡና ወንበራቸው ወለሉ ላይ ካረፈ በኋላም የሩሲያውን መሪ ለቀቋቸው፡፡

የሩሲው መሪ ምንም ሳይመስላቸው ቀይ ሉፋቸውን እያራገ
ኂሌታቸውን እያስተካከሉ በትእቢት እንደተወጠሩ ወደ ቀድሞ ወንበራቸ
ሄደው ተቀመጡ፡፡
የምስጋና ፕሮግራሙ ካለቀ በኋላ በንግስቲቱ ሰብሳቢነት የተመራው ዝ
ጉባኤ በይፋ ተጀመረ፡፡
አሮጊቷ የእንግሊዝ ንግስት ተሰብሳቢዎቹን በዝምታ አተኩረው ሲያ
ቆዩና በእርጋታና በዝግታ መድረኩ ላይ ወዲያ ወዲህ እያሉ ቀጠሉ፡፡
‹‹አሁን ዝግ ጉባኤውን በይፋ ጀምረናል፡፡ከወራት በፊት ሰኔ ወር ላ
በቤልጀም ብራሰልስ 40ኛው የ G 8 የመሪዎች ጉባኤ ተካሄዶ ነበር፡፡በዚ
በ G 8 አገራት የመሪዎች ዝግ ጉባኤ ላይም ከቀደሙት ዓመታት ዝግ
ጉባኤዎች በተለየ መልኩ በርካታ ነገሮች ተነስተው፣ የልዑላችን ስጦታ
ለእነርሱ ተበርክቶላቸው ነበር፡፡ያ በሆነ ማግስትም እናንተ የ G 20
አገራት መሪዎች ለአስቸኳይ ጉባኤ ወደ ኒዮርክ ተጠርታችሁ ሄዳችኋል፡
ብዙ ሚስጥሮችም ይፋ ተደርገውላችኋል፡፡የአዲስቷ ዓለም ሹማምንት
መሆናችሁ ተበስሮላችኋል፡፡ጎላችን ኢትዮጵያ መሆኗም ተገልፆላችኋል፡
ዘመኑ መቃረቡ ተነግሯችኋል፡፡ዘመኑ ሲቃረብ ልዑላችን ለታማኝ
አገልጋዮቹና ለሹማምንቱ የሚለግሰውን ጥበብም ታድላችኋል፡፡በመሆኑም
በደስታ ጮቤ የረገጣችሁበት አስደሳች ወቅት ሆኖ አልፏል፡፡እኔ ደግሞ
እንዲህ ባለ ማዕረግ ተንቆጥቁጣችሁ፣ ውጭና ውስጥ የማብራት ስልጣን
ታድላችሁ፣ የማይባት ዕለት ትናፍቀኝ ነበር! ክብር ለልዑላችን ይሁንና
ይኸው ይችን ዕለት ለማየት ቻልኩ!››በማለት፣በዓይኖቻቸው እየሳቁ
ተሰብሳቢዎችን ደጋግመው ስለ ዕድለኝነታቸው እየነገሩ ቆዩና፤
‹‹ክብር ለልዑላችን!››አሉ ኮስተር ብለው፡፡
‹‹አሜን!››
‹‹እናም….በዚያ ጉባኤ ልዩና ሚስጥራዊ ሰው በሆነው በወንድማችሁ
በአሜሪካው መሪ አማካኝነት ስለ ልዑላችን አነሳስና የልዑላችን የመጨረሻ
ጎል ስለሆነችው ኢትዮጵያ ስለተባለች አገር ሙሉ ማብራሪያ
ተሰጥቷችኋል፡፡
በልዑላችን ታማኝ ካህን በቫቲካኑ ጳጳስ አማካኝነትም ሰፋ ያለ ትንታኔ
ተደርጎላችኋል፡፡ጎላችን የሆነችውን ኢትዮጵያ የተባለች አገር እንዴት
ማድረግና በምን መልኩ ማዘጋጀት እንዳለብን፣ እስከዛሬ ምን ስንሰራ
እንደኖርን፣ ወደፊትም በእናንተ በኩል ምን መሰራት እንዳለበትና ምን
ማድረግ እንደሚገባችሁ፣ በልዑላችን ድል አድራጊነት ስለሚደመደመው
የመጨረሻው ጦርነት፣ በጦርነቱ ስለሚኖራችሁ ሚናና አስተዋፅኦ፣ ከድል
በኋላ ስለሚጠብቃችሁ ሹመትና ዘላለማዊ የምድር ሕይወት፣ በጥቅሉ
ከሰው ልጅ ፍጥረት ጀምሮ እስካሁን፤ እንዲሁም ስለወደፊቱ ያለውን

አጠቃላይና ዝርዝር ጉዳይ እንድታውቁትና እንድትሳተፉበት ስለተፈለገ ሁሉንም እንድትገነዘቡት ተደርጓል። ስለዚህ ከወራት በፊት በነበረው ጉባኤያችሁ በይፋ የተነገራችሁን ታሪካዊና ሚስጥራዊ ጉዳዮችን ለማጠናከር አይደለም እዚህ የተገኘሁት። ያ እንዳለ ሆኖ ከዚያ ጋር በተያያዘ ሌሎች በእናንተ ዘንድ መታወቅ ያለባቸው ተጓዳኝ ነገሮች አሉ። ከዓላማ፣ከዕቅድና ከጎላችን ጋር በተያያዘ በኛ አማካኝነት ይፋ የሚደረጉ ሌሎች ሚስጥሮችን እንድገልፅላችሁ የልዑላችን ፈቃድ ስለሆነና፣ሁሉንም እንድታውቁት ስለተፈለገ ነው። ስለዚህ እነዚያን ነገሮች ይፋ ለማድረግና ከአንድነት ወደ ውህደት ለመምጣት፣እንዲሁም እናንተን ከሌሎች ሹማምንት ጋር ለማስተዋወቅና የጋራ መስዋዕትም ለማቅረብ ጭምር ነው በዘንድሮው ዓመታዊ ዝግ ጉባኤ ስብሳቢያችሁ ሆኘ ልገኝ የቻልኩት።

‹‹ሳታውቋቸው የቆዩ ሚስጥሮችን በዚህ ጉባኤ ለእናንተ ሁሉን እንድታውቁ ለተፈቀደላችሁ የሃያል አገራት መሪዎች ይፋ የምናደርገውም፣ይህን የጥበብ ፀጋና የሹመት ምልክት ከታደላችሁ በኋላ ሁሉንም ነገር የማወቅ መብት ስላላችሁ ጭምር ነው። ይህ የልዑላችን ድንቅ ስጦታ የተለገሳችሁም የእርሱን ዓላማ በየህዝባችሁና በየአገራችሁ በሰውኛ አካሄድና አተገባበር ረቀቅ አድርጋችሁ ትፈፅሙና ታስፈጽሙበት ዘንድ ነው። ስለዚህ ተጠቀሙበት!››አሉና፣የሩሲያውን መሪ በንቀትና በጥላቻ ዓይን የጎሪጥ እያዩ ቀጠሉ።

‹‹በተረፈ ይህን ያህል አምነን ካሳተፍናችሁ በኋላ ያወቃችሁትን አውቃችሁ፣ እንደ ሩሲያው መሪ በራስ የሳተላይት ጨረርና በራስ የማንኑነት ሞገድ ተጠቅሞ አፈንግጦ መውጣት የትም ካለማድረሱም በላይ፣ይህን የመሰለና ከዚህ የበለጠ ጥበብን ያሳጣል። ያስቀጣልም!

‹‹ልብ በሉ!የበላይ አካሉ የሰዎችን ነፃ ፈቃድ እንደሚፈልገው ሁሉ ልዑላችንም የሰዎችን ነፃ ፈቃድ ይፈልጋል። ይህ የሆነው መሆን ስላለበትና በሁለቱም ተፃራሪ አካላት ዘንድ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ነው። እንጂ ቀድሞ የመከላከልም ሆነ የማገድ ብቃትና ስልጣን ከልዑላችን ዘንድ ሳይኖር ቀርቶ አይደለም።

‹‹እኔ ዛሬ የዓለምን ሚስጥር ለእናንተ ስናገር የልዑላችን ፈቃድ ሆኖ ነው፣ ማወቅ ስላለባችሁም ነው። ነገር ግን የሩሲያው መሪም ብቻ ሳይሆን ከእናንተ ውስጥ አንዱ መሪ በአባልነት ቆይታው ያወቀውን ሚስጥር አውቆ ሊክዳ እንደሚችል ሳናስበው ቀርተን አይደለም። ማንኛውም አባል በማንኛውም ጊዜ ድንገት ሊክዳ ይችላል። ነገር ግን ምንም አይፈጥርም!ብቻውን አፈንግጦ ወጥቶና ብቻውን ተጉዞ የትም ሊደርስ እንደማይችል አሳምረን እናውቃለን። እናንተም ይህን ከወዲሁ ማወቅ አለባችሁ።

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

‹‹እንደ አንዳንድ ኢትዮጵያዊ ቄሶች/ደብተራ ማለታቸው ነው/ ትን
መንፈሳዊ እውቀት ይዞ መፈርጠጥ ምን የሚሉት ብልህነት ነው?ሰዎ
ወደሆን መንፈሳዊ ቦታ ያመሩና መንፈሳዊ ትምህርት መማር ይጀምራሉ፡
ይህ አይነቱ አካሄድ በእኛም ዘንድ በበላይ አካሉ ተከታዮችም ዘንድ
የሚከናወን ነው።ስለዚህ መንፈሳዊ ትምህርቱንና በትምህርቱ ያገኘውን
እውቀት ለዚሁ ለሚከተለውና ለሚያመልከው አካል ግልጋሎት
ሊጠቀምበት በማሰብ ነው የሚማረው። በዚህ መሃል በጥቂት አመታት
ውስጥ የተለያዩና ተራው ማህበረሰብ የማያውቃቸውን ጥበቦች በትምህርት
ቆይታው ያውቃል።ተጨማሪ ዓመታት በተማረ ቁጥርም ተጨማሪ
እውቀት እየያዘ የላቀ ጥበብ ባለቤት ይሆናል።እያለ እያለ የጥበብ ባለቤት
ከመሆን አልፎ የረቂቅ ሚስጥራትን የመፍቻ ቁልፍ እስከማግኘት
ይደርሳል።

‹‹ያ ማለት እውቀትና ጥበቡን ላጎናፀፈው አካል መልሶ ሊሰጠው ወይም
ለእርሱ ግልጋሎት እንዲውል ሲባል የተሰጠውና የተማረው እንጂ ከዚያ
እውቆት ወይም ተምሮት ወጥቶ ለግሉ ለመጠቀምና የትምህርቱን ባለቤት
ወይም የጥበቡን ባለቤት ሳያገለግል ለግሉ ብቻ ሊጠቀምበት አይደለም።
‹‹ሰው ግን አስተሰሰቡ ኋላ ቀር ስለሆነና ትዕግስትንም ስላልታደለ በትንሽ
እውቀትና ተዓምር ተደንቆ ዋናው የጥበብ ጣራ ላይ ሳይደርስ በጥቂት
ዓመታት የገበያትን ተራ እውቀት እንደ ትልቅ ተዓምር ቆጥሮ፣
ትምህርትና አምልኮውን አቋርጦ ወደ ነበረበት ዓለምና ወደ ተራው
ማህበረሰብ ይዞ ይፈረጥጣል።

‹‹ያችን ተራና ቁንፅል ዕውቀት ወስዶ ወደ ግንዘብ ለውጦ ተራውን
ማህበረሰብ በድንቅና በተዓምር እያማለለ ለተራና ለጊዜያዊ ዳቦ መብያ
ያደርጋታል።ተረዳችሁኝ ?››

መሪዎቹ አንገታቸውን ላይና ታች በመወዝወዝ መረዳታቸውን አረጋገጡ።
የሩሲያው መሪ ግን እግራቸውን አነባብረው፤ ለንግስቲቱ የንቀት
አስተያየት፣ ተመሳሳይ በሆነ የንቀት አስተያየት አፀፋውን እየመለሱ ነበር
የሚታዩት።

‹‹ያችን በጥቂት ጊዜ መንፈሳዊ ትምህርት የገበየሃትን ቁንፅል እውቀት
ይዘህና ነፃ ፈቃድህን ተጠቅመህ ወደ ተራው ህዝብ ሄደህ የዳቦ መብያ
ማድረግ ቢቻልም፣ምንም ዓይነት ክሆድ ያለፈ ጥቅም ግን የለውም።
ይልቁንም ብትቆይ ኖሮ ታገኝ የነበረው ሌላ የበለጠ ረቂቅ ጥበብ
ያመልጥሃል። ወይ ደግሞ ነፃ ፈቃድህን መሰረት አድርገህ ያወቅሃትን
ቁንፅል እውቀት ይዘህ ከመፈርጠጥ ይልቅ፣ጥቂት ታግሰህና በጥበብ ላይ
ጥበብ፣ በእውቀተ ላይ እውቀት ጨማምረህ ከመንፈሳዊ ጥበብ በትንሹ
ማንኪያ ጨልፈህ ሳይሆን በትልቁ አካፋ ዝቀህ መፈርጠጥ...

ፍሥሐ ያዚ

እውቀትና ጥቂት ሚስጥር ከሰማህ በኋላ ያወቅህ የሰለጠንክ መስሎህ ብትፈረጥጥ ምን ይጠቅምሃል? ስለዚህ የሩሲያው መሪ በርሮ በመሄዱ አትደነቁ፤ አይክፋችሁም።የትም ስለማይደረስ! ያው መጣ!ታጋሽና ታማኝ ሆኖ ቢቆይ ግን ራሱንና ህዝቡን እንዲሁም ልዑላችንን ይጠቅም ነበር።

‹‹ማንም የዚህ ጉባኤ ተሳታፊ ለበለጠና ለተሻለ ሹመትና ስልጣን ብሎም ለዘላለማዊ አስተዳደር ተመረጠ እንጂ ለተራ ነገር አልታጨም።ገና የልዑላችንን ሌላ ጥበብ መች አያችሁት? መቸ ሙሉ በሙሉ አወቃችሁት?አዎን!ይሄን በደንብ ልታውቁና ልትጠብቁት ይገባል!ማንም ሰው በነፃ ፈቃዱ መሰረት መሸፈት ይችላል። ሆኖም ወደ በላይ እኳሉ ማማተር ወደ ጭለማና ወደ አለማወቅ መንጎድ እንደማለት ነው። ከልዑላችን ጋር በታማኝነት የተዋሃደ ግን የድሉ ተካፋይ ሆኖ ምድራዊ ህይወቱን ለዘላለም አስቀጥሎ በሹመትና በሽልማት ለዘላለም መኖር መቻሉ ነው!››

በዝግታ እንጂ በፍጥነት እንኳን መራመድ የማይችሉ ሆነው የምናውቃቸው አሮጊት ንግስት በዚህ ሰፊ መድረክ ላይ ወዲያ ወዲህ እየተራመዱ ሲናገሩና ሰውነታቸውን በቁንጥ ሲያውረገርጉ ያየ ሁሉ ግራ ይገባዋል።ለረጅም ደቂቃ እንኳን ቆመው መቆየትና ረዘም ያለ ንግግር ማድረግ የማይችሉ አድርገን የምንቆጥራቸው ብዙዎች ነበርን። አሁን ግን በወጣት እንደበትና በማይቆራረጥ ትንፋሽ እያንዳንዷን ቃል ረገጥ እያደረጉ ከቁንጠኛ የሰውነት እንቅስቃሴ ጋር በማስረዳት ላይ ናቸው።

ስለ ሩሲያው መሪ ገልፀው ከጨረሱ በኋላ ረዘም ላሉ ሰከንዶች በዝምታ ተውጠው ቆዩ።በዚህ ጊዜ ግራና ቀኝ በሆዳቸው ለጥ ብለው የቆዩት ዘንዶ መሰል እባቦች በጋራ ተነስተው በንግስቲቱ ግራና ቀኝ በመሆን ሽቅብ እንጋጠው በትከሻቸው፣ በጀርባቸው፣ በእግሮቻቸውና በወገባቸው ዙሪያ እየተሿሿሩ ሰውነታቸውን ያሻሹላቸው ጀመር።እንደ ማሳጅ አይነት መሆኑ ነው።

ንግስቲቱ እባብ መሰል ዘንዶዎቹን የበቃኝ ምልክት ሲያሳዩዋቸው በፍጥነት ከሰውነታቸው ላይ ወርደው በሆዳቸው እየተሳቡ በመሄድ ግራና ቀኝ ቦታቸውን ይዘው ለጥ አሉ።አሁንም እንደገና አዳራሹ በአስፈሪ ዝምታ ተውጦ ቆየ።

ከአስፈሪው የአፍታ ዝምታ በኋላ አሮጊቷ ንግስት ካቀረቀሩበት ድንገት ቀና በማለትና ወደ ተሰብሳቢዎቹ በማፍጠጥ፤

‹‹ልዑል ነው! በድል አድጊነት ይነግሳል!አዲስቷ የምድር መንግስት ትመሰረታለች! እርሱ ንጉስ ነገስታችን ይሆናል! እኛም ታማኝ ሹማምንቱ ነን!ጎሉ በሆነችው በኢትዮጵያ ምድር የህይወት ዛፍ ክልልን ለመቆጣጣጠር ሲባል የሚደረገውን የመጨረሻውን መንፈሳዊ ጦርነት በረቂቅ የኒውክሌር

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

እናበቃዋለን!ስንል ዝም ብለን መሳሪያዎቻችን አግዘን ለድል
መሳሪያዎቻችን አግዘን ለድል ግዝገዛ ዝግጅቱንና ዝግጅታችንን ይዘን ነው!ከዚህ
አይደለም!!የረጅም ሺ ዓመታት ዝግጅቱንና ዝግጅታችንን ይዘን ነው!ከዚህ በኋላ ደግሞ ጥቂት
ቀደም በኛ አማካኝነት በዙ ስራ ሲሰራ ኖሯል!ከዚህ በኋላ ደግሞ ጥቂት
ስራ ይሰራል!አፈፃፀሙም የእኛንና የእናተን የጋራ እገዛ የሚፈልግ ነው።
ለዚህም ነው ሁሉን ነገር ለእናንተ ይፋ በማድረግ ከሚስጥራዊ አንድነት
ወደ ይፋዊ ውህደት መምጣት የሚኖርብን።
ይህ መሆን ካለበት ደግሞ በደንብ መተዋወቅ ይኖብርብናልና ከትውውቁ
ልጀምር።

‹‹ከዚህ በፊት ተጠሪነታችሁ ለቫቲካኑ ጳጳስ ነበር።ምንም እንኳን የስልጣን
ተዋረዱ ግልፅ ቢሆን፤የእናንተ ተጠሪነት ለቫቲካኑ ጳጳስ፣የቫቲካኑ ጳጳስ
ለኛ፣እኛ ከኛ በላይ ላሉ መንፈሳዊ አካላት፣እነሱም ለበላዮቻቸው፣
የበላዮቻቸው ለሉሲፌል፤ልብ በሉ ‹‹ሉሲፌር›› አላልኩም፤‹‹ሉሲፌል››ነው
ያልኩት። ‹‹ሉሲፌር››እና‹‹ሉሲፌል››ብዙ ጊዜ ሲምታታባችሁ ይስተዋላል።
‹‹ሉሲፌል›› ስንል ከልዑላችን ስር ያለ ታላቅና ታማኝ የበታቹ ነው።
‹‹ሉሲፌር›› ደግሞ ከልዑላችን የበታች በታች ከሆኑ ጭፍሮች አንዱ ነው።
በ‹‹ሉሲፌል››እና በ‹‹ሉሲፌር›› መካከል ትልቅ የሆነ ልዩነት መኖሩን
አትዘንጉ።በስልጣንም በሹመትም በጥበብም በሚስጥራዊነትም ሉሲፌል
ይበልጣል።

‹‹ስለዚህ የእናንተ ተጠሪነት ለቫቲካኑ ጳጳስ፣የቫቲካኑ ጳጳስ ለኛ፣እኛ ከኛ
በላይ ላሉ የልዑላችን ጭፍሮች፣እነሱ ለሉሲፌል፣ ሉሲፌል ለልዑላችን
ለሳጥናኤል፣እያለ በተዋረድ የሚቀጥልና የሚገለፅ ቢሆንም፤በዓለም አገራት
መንግስታትና ህዝቦች ላይ ግን ሙሉ ስልጣኑ የእኛ ነበር፤አሁንም የኛ
ነው።ወደፊትም በኛ የሚቀጥል ነው።ሰውኛ አካሄዶችን በተመለከቱና
በተከተሉ ጉዳዮች ብቻ ማለቴ ነው!

‹‹በልዑላችን የበታች ጭፍሮች አማካኝነት የሚከናወኑና ሲከናወኑ የኖሩ
ነገሮች ሁሉ በልዑላችን ስም ሲጠሩ እንደኖሩት ሁሉ፤በቫቲካኑ ጳጳስ
አማካኝነትና በ G 8 አገራት መሪዎች አማካኝነት የሚከናወኑና ሲከናወኑ
የነበሩ ምድራዊና ሰውኛ ክንውኖችም እንዲሁ በእኛ ትእዛዝ ሲከናወኑ
የኖሩ ናቸው።ነገር ግን በየአገራቱ መሪዎች አማካኝነትና በየራሳቸው
ፍላጎት ይከናወኑ እንደነበር ተደርጎ እንዲታሰብልን ነውና የፈለግነው
እንዲያ ሆኖ እየታሰበ እንዲቀጥል አድርገን ሳንነግራችሁ ቆይተናል።
‹‹አዲሲቷን የምድር መንግስት ምስረታ በሚመለከት ሙሉውን ስራ
የሰራነውና እየሰራን የቆነው እኛ ነን።ዓለማችን አሁን ያላትን ቅርፅ
እንድትይዝና እዚህ ደረጃ እንድትደርስ የማድረግና የማዘጋጀት ሃላፊነት
ነበረብን።አጠቃላይ ነገሯን የማመቻቸት ስራ ለኛ የተሰጠ የቤት ስራ ነበር።
የተሰጠንን የቤት ስራም በብቃት ተወጥተነዋል!እየተወጣነውም እንገኛለን!

ፍሥሐ ያዜ

‹‹የእኛ፤በተለመደው አጠራር የእንግሊዝ ነገስታቶች ዘር በቀጥታ የሚመዘዘው ከልዑላችን ታማኝ የበታች ጭፍሮች የዘር ሃረግ ነው። የልዑላችን ታማኝ ወታደሮች ወይም ጭፍሮች የነበሩ እልፍ አዕላፍ መንፈሳዊ ፍጡራን ያለ እውቀት እንዲኖር በበላይ አካሉ ከተፈረደበት፤ ሰው ከተባለው ፍጡር ጋር ሲዳቀሉ የተገኘንና ዘራችንን ጠብቀን ቆይተን ባስፈላጊው ዘመን ከነበርንበት ቦታ ወጥተን የመጣን ድቅሎች ነን።

‹‹የተደቀልነው እኛ ብቻ አይደለንም።ብዙዎች ነበርን።ሆኖም እኛ የእንግሊዝ ነገስታት ቤተሰቦች የምንባለው ከሌሎች ጭፍሮች ድቅሎች ለየት እንላለን።ለየት የምንለውም ከሰው ልጅ ጋር የተዳቀሉት መንፈሳዊ ጭፍሮች ዋና አዛዥ ከሆነው ከዝማስያ የዘር ሃረግ ስለምንመዘዝ ነው።እኛ የተደቀልነው እነዚያን የልዑላችንን ጭፍሮች ከሱ ስር ሆኖ በበላይነት ከሚያዛቸውና ይመራቸው ከነበረው ከዝማስያ ነገድ ስለሆንን ነው።እኛ የእርሱ የዘር ሃረግ ያለን ብቻ ነን።

‹‹ከእርሱ የዘር ሃረግ ስለምንመዘዝም ነው፤ከሌሎች ድቅሎች የተሻለና የበለጠ እውቀትና ጥበብ ኖሮን ለመጨረሻው ኃላፊነት የታጨነው።እርሱ ከበታቾቹ የበለጠና የላቀ የእውቀት መጠን የነበረው ነው።ሌሎች ከሰው ጋር የተዳቀሉት ግን ከእርሱ በግማሽ ዝቅ ያለ የእውቀት አድማስ የነበራቸው ናቸው።

‹‹እናም መፈፀም የነበረባቸው በርካታ ሺ ዓመታት ተፈፅመው ሲያልቁና ስድስተኛው ሺ ዓመት ላይ ሲደረስ ዘመናችንን ጠብቀን ከፒራሚዳችን ወጥተን ብቅ ያልን ነን።ብቅ ብለንም በአሁኗ የአውሮፓ ምድር ሰፍረንና በየቦታው ተሰራጭተን ከሰዎች ጋር ተቀላቅለን ስንኖር ቆይተናል።

‹‹ከዚያ ዘመን ጀምሮ በሂደት እየተደራጀን ቆይተን የምድርን ህዝብ የማስተማር፣ የማሰልጠንና የማዘመን ተግባራችንን አንድ ብለን የጀመርን የልዑላችን ታማኝ ቤተሰቦች ነን።

‹‹መላው አውሮፓ በተደራጁ የንጉሳውያን ቤተሰቦች መመራት የጀመረውም ከኛ መምጣት በኋላ ነው።የምድር ነዋሪ የሆነው ሰውም ዘመናዊነትን መላበስ የጀመረውና እየተሻሻለ የሄደው ከኛ መምጣት በኋላ ነው።

ከፒራሚዳችን ወጥተን የመጣነውም የተለያዩ ዓላማዎችን ይዘን እነሱን ለመፈፀም ሲሆን፤በዋናነት ሰዎችን አስተምሮ፣አደራጅቶ፣አሰልጥኖ፣ በማቆየት ለልዑላችን የመጨረሻ ዓላማ ዝግጁ ለማድረግ፣ያን ለማድረግ የሚያስችለንን ለልዑላችንና ለጭፍሮቹ፤ እንዲሁም ለኛ ቤተሰቦች መታሰቢያ የሆነች ድንቅ አገር ለመገንባና፤ ያችን አገር ዋና መቀመጫ አድርገን ሁሉንም አገራትና ህዝቦች በስራችን አድርገን ለማስተዳደር፣ በበላይ አካሉ ተከታዮች ዘንድ ባለው መጽሐፍ ቅዱስ፤የዳዊት ልጅ ሰለሞን ቤተመቅደሴን ይሰራል ተብሎ እንደተነገረውና ዘመኑን ጠብቆ ለመጀመሪያ

ጊዜ ለበላይ አካሉ ቤተመቅደሱን እንደሰራለት ሁሉ፤እኛም በልዑላችን ተመርጠን እርሱ በፈቀደው ዘመን ቤተ መቅደሱን እንሰራለት ዘንድ የታዘዝንና ያንንም ለማድረግ የመጣን ነን።
እነዚህን ሃላፊነቶቻችንን እንዴትና በምን መልኩ ስናከናውን እንደነበርና የት እንደደረስንም ጭምር በዘንድሮው ጉባኤያችሁ በሶስት የተለያዩ አገራት ዋና ዋና ከተሞች በሚገኙ ሶስት የተለያዩ አዳራሾች ለእናንተ ይፋ እናደርጋለን......›ካሉ በኋላ፤በድንገት መድረኩ አካባቢ ነጎድጓዳማ የሆነ ከባድ ድምፅ ተሰማ።የመብረቅ ዓይነት ድምፅ ነበር የተሰማው።በዚህ ቅፅበት ሁሉንም ተሰብሳቢዎች ባስደነገጠ ሁኔታ የንግስቲቱ መላ ሰውነት ልውጥውጥ ማለት ጀመረ።
የእኒህ አጭርና ፊታቸው የተጨማደደ አሮጊት ንግስት የሰውነት ቅርፅና አቋም መለዋወጡን ቀጥሎ ወዳልተለመደ የሰውነት ገፅታ እተቀየረ ሄደ። ለውስን ደቂቃዎች ጩኸት የታከለበት የማቃሰት ድምጽ እያሰሙ፣ ከወገባቸውም፣ ከአንገታቸውም፣ በኩል ከፍ ዝቅ፤ ቀና ዘንበል ሲሉ፤ በማይታመን ሁኔታ ከሜትር ከስልሳ አይበልጥ የነበረው ቁመታቸው በፍጥነት ተመዝዞ ወደ ላይ በመውጣት እስከ ሶስት ሜትር የሚደርስ ሆንና ሴትዮዋ ሙሉ በሙሉ ወደ አስደንጋጭ ፍጡርነት ተለወጡ። የተሸበሸበ የፊት ቆዳቸው በአንድ ጊዜ ለስልሶ የወጣት መሰለ።ዓይናቸው ተጎልጉለው ወጥተው ሊወድቁ የደረሱ መሰሉ።ሽበት የወረረው አጭርና የሳሳው ፀጉራቸው በአንድ ጊዜ ከስም ጥቁርና ለስላሳ ሆኖ በመዘናፈል ወገባቸው ላይ ደረሰ። ቁመታቸው በአስፈሪ ሁኔታ ከመርዘሙ በቀር መላ ሰውነታቸውና ቅርፃቸው ሙሉ በሙሉ ወደ ወጣትነት ተለውጦ፣ እጅግ ወጣት መስለው ታዩ።በዚህ ሁሉ ቅፅበታዊ መለዋዋወጥ ውስጥም የህመም ይሁን የደስታ የማይታወቅ የማቃሰት ድምፅ ያሰሙ ነበር።
በመሃል መለዋወጣቸውንና ማቃሰታቸውን አቁመው በተስተካከለ ቀንጠኛ አቋቋም መድረኩ ላይ ቆመው፤አስፈሪ አይኖቻቸውን ወደ ተሰብሳቢዎች ሲያደርጉ፤ሁሉም መሪዎች በግርምት አፍጥጠውና አፋቸውን በመደነቅ ከፍተው እያስተዋሏቸው ነበር።
ቁመታቸው እጅግ ረዝሞ ነበርና አዘቅዝቀው ነበር ተሰብሳቢዎቹን የሚያዩዋቸው።
እስከ ባቶቻቸው ይደርስ የነበረው ቀይ ጉርድ ቀሚስ ተለዋውጠው ይህን አቋም በያዙ ጊዜ እምብርታቸው ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ።ከላይ የለበሱት ተመሳሳይ ቀይ ኮትና አላባሽም ደረታቸው አካባቢ ተለጥፎ ታየ።ሙሉ ሰሙሉ ሰውነታቸውን ሸፍኖላቸው የነበረው አልባሳት የእራፊ ጨርቅ ያህል ከላይና ከታች ተንተልጥሎ ሲቀርና መላው ሰውነታቸው ሲጋለጥም፤ እጅግ ለስላሳ ቆዳና በስፖርት የዳበረ የሚመስል የወጣት ሴት ሰውነት

ጎልቶና ደምቆ ይታይ ጀመር።በዚህ ሁኔታ ጥቂት ከቆዩ በኋላ፤በአስፈሪ ዝምታ የተዋጡትንና ግራ ተጋብተው የተረበሹትን መሪዎች የመለዋወጣቸውን ምክንያት ከሰው በተለዩ በሌላ አይነት ድምፅ በመንገር አረጋጓቸው።

‹‹አዎን! ተመስጬ ሳወራ ስለነበር ሰዓቱን ዘነጋሁት። የሰማችሁት ነጎድጓዳማ ድምጽ ከበላዮች የመጣ የማስጠንቀቂያ፣ የማንቂያ፣ የማስታወሻ፣ ደወል ነው።ግራ አትጋቡ ክቡራን።ይህ ለእኔ የተለመደ ነው። ጉባኤያችንን በቀጥታ ስርጭት የሚመለከቱ ከእኛ በላይ የሆኑ፤ነገር ግን ከልዑላችንም ሆነ ከበታኞቹ እጅግ በጣም በታች የሆኑ መንፈሳዊ አካላት ባሉበት ሆነው ይከታተሉናል፣ ይታዘዙናል፣በተለያየ መንገድም ያግዙናል። አንዳች ነገር የማድረጊያ ጊዜያችንን እኛ ስንረሳ ከሰው እይታ ውጪ በሆነ ጨረር በመንሰም ያስታውሱናል።ለማንኛውም እንዲህ ባለ ድንገተኛ መለዋወጥ ውስጥ ገብቼ ስላስደነገጥኳችሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ምክንያቱም ከጳጳሳችሁ፣ከአሜሪካውና ከእንግሊዙ መሪ ውጪ ሌሎቻችሁ የምታውቁት ነገር ስላልሆነ ነው።ሆኖም ሳስረዳችሁ በቀላሉ ይገባችኋልና ጥቂት ታገሱኝ።

‹‹አው አሁንም እንደገና ጊዜ እንዳልፈጅ መጠንቀቅ ይኖርብኛል።አለዚያ ሌላ መደነቅና መደንገጥ ውስጥ ልከታችሁ እችላለሁ...›› አሉና የጀመሩትን ዓርፍተ ነገር ሳይቋጩ፤ጳጳሱን በምልክት ትእዛዝ ከሰጡ በኋላ፤እንደገና መንዘፍዘፍና ማቃሰት ጀመሩ።

አሁንም ወደ ሌላ ዓይነት መለዋወጥ ውስጥ ገቡ።ቁመታቸው ብቻ በነበረበት ሲቆይ!ሌላው አካላቸው በሙሉ ወደ አረንጓዴነት መለወጥ ጀመረ።ፀጉራቸው ደማቅ አረንጓዴ ሆነና ወደ ቀጫጭን ባለቀለም ሽቦነት ተለወጠ።የፊታቸው ገፅታም በተመሳሳይ ደማቅ አረንጓዴ ሆኖ፤ደርቆ እንደሚፈረካከስ ነገር እየሆነ ብርሃን መርጨት ጀመረ።አንዳንድ ፊልም ላይ እንደምናየው የግዙፍ ሮቦት አይነትና ቅርፅ እየያዙ ሲሄዱ ጩኸታቸው ጨመረ።ከግንባራቸው ጀምሮ እስከ እግሯቸው እየደረሰ በነበረው መለዋወጥ ውስጥም ጨደደድ... የሚሉና ተፈነጣጣሪ የኤሌክትሪክ ብርሃን የሚረጩ የእሳት ነጠብጣቦች መፈነጣጠር ጀመሩ። ፊቶቻቸው ውስጥም ብዛት ያላቸው እጅግ ቀጫጭን ሽቦዎች በአረንጓዴ ቀለም ተውጠው ይታዩ ጀመር።በዚህ መሃል ሆነው ከማቃሰት ድምፃቸው ጎን ለጎን እንደምንም ብለው ትንፋሻቸውን በመሰብሰብ፤ ‹‹ቶሎ እምጡልኝ እንጂ!›› ሲሉ ጮሁ።

በዚህ ጊዜ ከአዳራሹ መድረክ ግራና ቀኝ ለጥ ብለው የነበሩት ዘንዶ መስል መናፍስቶች እኩል ተስፈንጥረው በመነሳት የዚያን ሰፊና ድንቅ አዳራሽ ጣራ ዘልለው ሄደው ተለጠፉበት። ለጥቂት ጊዜ ያህል የአዳራሹ መብራት

ጠፍቶ በጭለማ ተተካ።ከጥቂት ቆይታ በኋላ በጭለማ ተውጦ የነበረው አዳራሽ ወደ ቀድሞ ይዞታው ተመልሶ፤በደማቅ ብርሃን ሲጥለቀለቅ፤ቀጸም ብለው የታዘዙት ጳጳስ ከየትና እንዴት እንዳመጧቸው የማይታወቁ ስድስት ሴት ህፃናት የአዳራሹ መድረክ ላይ ከጳጳሱ አጠገብ ተሰልፈው ታዩ።

እባብ መሰል ዘንዶዎችም ከጣራው ወርደው በመድረኩ ጥግና ጥግ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ታዩ።

መድረኩ ላይ የተሰለፉት ስድስቱ ሴት ህፃናት በቁመትም፣ በቅርፅም፣ እኩል ናቸው።እድሜያቸው ከስድስት እስከ ስምንት ዓመት የሚገመት ሲሆን፤ፀጉራቸውን የተላጩና ሙሉ በሙሉ እርቃናቸውን የሆኑ ናቸው። እነዚህ ቆንጆ ቆንጆ የሆኑ የሚያሳሱ የፈረንጅ ህፃናት ልጆች፤እርቃናቸውን ሆነው እንደሰለጠነ ወታደር ቅርፃቸውን ጠብቀው ተሰልፈዋል።ያለ አንዳች እንቅስቃሴ፣ ያለአንዳች ድምፅ፣ በዝምታና ልበ ሙሉነት በሚንፀባረቅበት አቋቋም ቀጥ ብለው ቆመው ነው የሚታዩት።

በአረንጓዴ ቀለም ከተሞላ ከትልቅ በርሜል ውስጥ ገብተው የወጡ የመሰሉትና ለመውደቅ እየተንገዳገዱ የነበሩት መሰሪ ንግስት፤ ፊት ለፊት የተሰለፉትን እንቦቃቅላ ህፃናት ሲያዩ ሚዛናቸውን ጠብቀው ለመቆም ቻሉ።

ከዚያም ጳጳሱ በቀይ ጌጣጌጥ የተንቆጠቆጠ ቀይ ሐይማኖታዊ ልብሰ ተክህኗቸውን በአንድ እጃቸው ወደ ላይ ሰብሰብ አድርገው ወደ ንግስቲቱ እየተመለከቱ ባንድ ጉልበታቸው በርከክ ብለው እጅ ነሱና፤አንድ እጃቸውን ኪሳቸው ከተተው ከውድ አልማዝ የተሰራ የሚመስል አብረቅራቂና አንፀባራቂ አጭር ስል ቢላዋ መዘዙ።

በተንበረከኩበት እንዳሉም እንደማጎምጎም ብለው ለሌላው የማይሰማ አጭር ፀሎት ካደረሱ በኋላ ብድግ አሉና ወደ ህፃናቱ ተጠጉ።

ከፊት የተሰለፈችውን ህፃን ወደ ንግስቲቱ ጠጋ አድርገው፤ባንድ ጉልበታቸው ወለሉ ላይ በርከክ አሉ።ከዚያም በቀኝ እጃቸው የህፃኗን የራስ ቅል ወደ ላይ ወደ ጣራው ቀና አድርገው አጥብቀው ያዙና፤በግራ እጃቸው የያዙትን ስል ቢላዋ የህፃኗ መሃል ግንባር ላይ በሃይል ሰኩት!ህፃኗ አንዲት ድምፅ አላሰማችም።ዓይኖቿንም አልጨፈነችም፤ አልተወራጨችም። አዳራሹም ፍፁም ፀጥታ እንደሰፈነበት ነው።ጳጳሱ አብረቅራቂና አንፀባራቂ የሆነውን የሳለ ቢላዋ የህፃኗ ማሃል ግንባር ላይ በሃይል ከሰኩት በኋላ፤መሃል ለመሃል ቁልቁል እየቀረደዱ ወደ ታች ወረዱ።የህፃኗ ግንባር ላይ ጠልቆ የገባውን ስለት በግራ እጃቸው አጥብቀው እንደያዙ ከግንባሯ ጀምረው እኩል መሃል ለመሃል እየቀረደዱ ወደ ታች ወረዱ።

የተሰካው ስለት፤ ውስጥ ለውስጥ በቅርፅ እየሄደ፤ በህፃኗ ቅንድቦች መካከል አልፎ፣አፍንጫዋን እኩል ሰንጥቆ፣ላይና ታች ከናፍርቷንም እኩል ቆርጦ አልፎ፣በአገጯ ትክክል እየወረደ ሄደ፣ የደረቷን አካባቢ መሃል ለመሃል እየቀረደደ አልፎ፤ ልቧን፣ ሆዷን፣ እያለ እስከ እምብርቷ ደረሰ።
የቫቲካኑ ጳጳስ ከፊት ተሰልፋ የነበረችውን ህፃን በዚህ አይነት ሁኔታ መሃል ለመሃል እኩል እስከ እምብርቷ ድረስ በፍጥነት ቀርድደው ወይም አርደው ጨረሱና እንደተንበረከኩ ከእንገታቸው ጎንበስ ብለው ለንግስቲቱ አቀረቡላቸው።
ንግስቲቱም በርከክ ብለው ከህፃኗ ግንባር ጀምሮ እንደ ቦይ በቅርፅ መፍሰስ የጀመረውን ደም በፍጥነት የህፃኗ ደረት ላይ ተለጥፈው መጥባት መጠጣት ጀመሩ።በዚህ ጊዜ እስከ ሶስት ሜትር ይገመት የነበረው አስደንጋጭ ቁመታቸው በዚያው በተንበረከኩበት እንዳሉ በቅፅበት ወደ ታች ሸርተት በማለት ቀድሞ ወደነበረበትና የዓለም ህዝብ ወደሚያውቀው ሰውኛ የቁመት ርዝመት ተመለሰላቸው።
ቀጥለውም የቀኝ እጃቸውን አምስት ጣቶች ቀጥ አድርገው ዘርግተው በህፃኗ ስንጥቅ ደረት በሃይል በማስገባት ልቧን ጎትተው አውጥተው በፍጥነት ሲጎርሱትና፤ በፍትነት አኘከው ሲውጡት፣አረንጓዴ ብርሃን እየረጨ የቆየውና ለቁጥር በሚታክቱ ቀጫጭን ሽቦዎች እየተተካ የነበረው ሰውነታቸው ወደ ቀድሞው የሰው ሰውነት እየተቀየረላቸው ሄደ።
ክንውኑ እጅግ አስደንጋጭና እጅግ ፈጣን ነበር።የቫቲካኑ ጳጳስ በአስተራረድ ልምድ ያካበቱ ፈጣን አራጅ ናቸው።ንግስቲቱም ጥሩ ልምድ ያላቸው የሰው ደም ጠጭና ጎይለኛ የሰው ስጋ በሊታ መሆናቸውን አበላላልና አጠጣጣቸውን በማየት ብቻ ማረጋገጥ ይቻላል።
በዚህ አይነት ልክ እንደ መጀመሪያዋ ህፃን የቀሩትን አምስቱንም ህፃናት በተመሳሳይ መንገድ፣ በተመሳሳይ ፍጥነት፣ በተመሳሳይ አተራረድ፣ተራ በተራ ሲያርዱ ወይም ሲሰው ቆዩ።ጳጳሱ እያረዱ ለንግስቲቱ አቅርበው ጎንበስ ይላሉ።ንግስቲቱም በበኩላቸው የእንዷን ታራጅ ደም በፍጥነት ጠጥተውና ልቧን አውጥተው ጎርሰው አላምጠው እንደዋጡ፤ ተከታይዋ ተረኛ ህፃን ታርዳ ትቀርብላቸዋለች።የአንዷን ደም ጠጥተውና ልቧን በልተው ሲጨርሱ፣ሌላኛዋ ትቀርብላቸዋለች።በዚህ አይነት አበላልና አጠጣጥ የስድስቱንም ህፃናት ደም ጠጥተው፣ልባቸውን በሃይል እየጎተቱ እያወጡ በልተው ጨረሱ።በልተውና ጠጥተው ከጨረሱ በኋላ የህፃናቱን በድን በርከክ እንዳሉ በፍጥነትና በሃይል ግራና ቀኝ ወደ ኋላ ይወረውሯቸው ነበር።ልባቸው ተበልቶ ደማቸው የተጠጣውን ህፃናት ተራ በተራ ግራና ቀኝ ከራሳቸው ባልሆነ ሃይልና ፍጥነት ሲወረውሯቸውም፤ በአዳራሹ መድረክ ጥግና ጥግ በሆዳቸው ተኝተው የነበሩት እባብ መስል

ዘንዶዎች በፍጥነትና በመስገብገብ ገና ከመወርወራቸው አየር ላይ እንዳሉ አፋቸውን ከፍተው እየቀለቡ ይውጣሉ፤ ይሰለቅጣሉ::
በዚህ ዓይነት መንገድ ዘግናኝና ሰቅጣጭ በሆነ ሁኔታ እነዚያ ስድስት እንቦቃቅላ ሴት ህፃናት ከግንባራቸው መሃል ተወግቶ ቁልቁል እየተቀረደዱ እስከ እምብርታቸው ደርሶ በሚነቀለው የሳለ ቢላዋ እየታረዱ ተሰውተው አለቁ::ተበሉ፤ተጠጡ!
በእርዱ ጊዜ ከማናቸውም በኩል አንዲት ድምፅ ካለመሰማቷም በላይ፣ የአዳራሹን ወለል የምታበላሽ ጠብ ያለች ደምም አልነበረችም::ሁሉም ነገር ለማመን በሚከብድ ሁኔታ በፀጥታና በፍጥነት ተከናውኖ አለቀ::መድረኩ ላይ ምንም የተፈጠረ ነገር ያለ አይመስልም ነበር::
ንግስቲቱ ይህን ካደረጉ በኂላ ሙሉ በሙሉ ቀደም ሲል ወደነበሩበት ሰውኛ ገፅታቸው ተመለሱ::እኚያ የምናውቃቸው አሮጊትና ጎባጣ፤ የተጨማደደና የተሸበሸበ የፊት ቆዳ፣የሸበተና የሳሳ ፀጉር ያላቸው፤ ራሳቸው የእንግሊዝ ንግስት ሆነው ታዩ!አለባበሳቸውም እንደ ቀድሞው ሆኖ፤ የእጅ ጓንታቸውን እንዳደረጉ፣ጫማቸውንም እንደተጫሙ፤ ሰው ሆነው ታዩ::
ጳጳሱ ንግስቲቱን አብልተውና አጠጥተው ከጨረሱ በኂላ፤ያረዱበትን ስለት ቀይ ልብሳቸው ላይ ጠራርገው ጎንበስ ብለው እጅ በመንሳት ለንግስቲቱ ሰጡ::ንግስቲቱም አጭሩን አብረቅራቂ ስለት ተቀብለው ጡታቸው ስር ሻጥ አደረጉት::
ከዚህ በኂላ የቫቲካኑ ጳጳስ ወደ ተሰብሳቢዎች ሄደው ቦታቸው ላይ እንዲቀመጡ በንግስቲቱ ታዘዙና፤ሄደው ከተሰብሳቢዎች ፊት ካለው ተንሳፋፊ ወንበራቸው ላይ ተቀመጡ::
ግራና ቀኝ ለጥ ብለው፤እኩል ሶስት ሶስት የህፃናት በድን ደርሷቸው ሲሰለቅጡ የቆዩት ሁለቱ እባብ መሰል ዘንዶዎችም በንግስቲቱ የእጅ ምልክት ሂዱ ተብለው ተሸኙና ተሰለቡ:: ክንውኑ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ አዳራሹ በፀጥታ እንደተዋጠ ነበር::
ንግስቲቱ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሰዋዊ አቋምና ገፅታቸው ከተመለሱ በኂላ፤ የተጨማደደ ፊታቸውን ወደ ተሰብሳቢዎች መለስ አድርገው፤ጨምጭማ አይኖቻቸውን መሪዎቹ ላይ ተክለው ፈገግ በማለት በእርካታ የተሞላ የፊት ገፅታቸውን ሲያሳዩዋቸው ቆዩ::
በዚህ ጊዜ የአሜሪካውና የእንግሊዚ መሪ የተቀመጡት ከፊት ነበርና ዘግናኙ ድርጊት ተፈፅሞ ማለቁን አረጋግጠው ተነስተው አጨበጨቡ:: ሌሎቹም ተከተሏቸው::
ንግስቲቱም በቀድሞው ሰውኛ ድምፃቸው - ዘና ብለው፤‹‹ክብር ለልዑላችን!››አሉ::

‹‹አሜን!››

‹‹ይህ የአምልኮ ስርዓት አይደለም፡፡ይህ የእኔ የግል ህይወት ነው፡፡ ምናልባትም እናንተ ሳታዩኝ ብቻየን ሆኘ መፈፀም የሚኖርብኝ ተራ ጉዳይ ነው፡፡ነገር ግን መተዋወቅ አሰብን ስንል እዚህ ድረስ በጥልቅና በግልጽ መተዋወቅ ማለታችን ነውና ገጠመኙን መጠቀም ነበረብኝ፡፡ለዚያ ነው ፊታችሁ ላይ ይህን ተግባር የፈፀምኩት፡፡እንጂ ይህን የማድረጊያ ወራቱን፣ ሳምንታቱን፣ዕለቱን አውቃለሁና ከዚህ ጉባኤ በፊት በቤተ መንግስቴ ፈፅሜ መምጣት እችል ነበር፡፡እርግጥ ነው ከእናንተ ጋር ሳወራ ሰዓቱን ዘንግቸው ነበር፡፡ማስጠንቀቂያው የደረሰኝም ጊዜ ስላሳለፍኩ ነው፡፡ሆኖም በዚህ ሳምንት በአንዱ ቀን መፈፀም እየቻልኩ ሳልፈፅም የቀረሁትና ማስጠንቀቂያው እስኪደርሰኝ የጠበቅሁት ሆን ብዬ ነው፡፡ጊዜ ስናሳልፍ የሚከሰትብንን ነገር እንድታውቁት በማሰብ ነው፡፡ሙሉ ለሙሉ ሰው ያልሆንን እና ከልዑላችን ጭፍሮች የተደቀልን የተለየ ዝርያ ያለን መሆናችንን እግረመንገዴን አጋጣሚውን ተጠቅሜ ላረጋግጥላችሁ ስለፈለግሁ ነው፡፡

‹‹እኛ የእንግሊዝ ነገስታት ቤተሰብ የሆንነው በሙሉ ህይወታችንን እንዲህ ነው የምንመራው፡፡ይህ ቋሚ ተግባራችን ነው፡፡

‹‹ቀጥዬ በደንብ እንደማብራራላችሁ የኛ የዘር ሃረግ ኖሬቸው፣ ከኛ ወገን ሆነውና በኛ ቤተመንግስት የልዑልነትም፣ የልዕልትነትም፣ ስልጣን እየያዙ ከኖሩት ውስጥ በጣት የሚቆጠሩት ከቤተ መንግስት ህይወታቸው ወጣ እያሉ ከተራው ህዝብ ጋር እየተፋቀሩ በእንዝህላልነት የተዋለዱና ዘራቸውን ያመናመኑ ቢኖሩም፣ ከቁጥር የሚገቡ አይደሉም፡፡በተረፈ እኛ ዋና ዋናዎቹ በተለምዶ የእንግሊዝ ነገስታት ዘሮች የምንባለውና መላው ቤተሰባችን ቋሚ ህይወታችንን የምንመራው በእንዲህ አይነት መንገድ ነው፡፡ይህንንም የምናደርገው ዓለምንና ህዝቦቿን በሰለጠነ መንገድ ለመምራት ስንል ነው፡፡

እኛ ሙሉ በሙሉ ሰው ስላልሆንን የሰዎች ጉዳይ አያገባንም ብለን የራሳችንን ህይወት ብቻ መኖርን አልመረጥንም፡፡ወይም አልተመረጠልንም፡ :

‹‹እኛና ልዑላችን፤እንዲሁም የልዑላችን ጭፍሮች የሰውን ልጅ ለመታደግ ስንል ዋጋ እየከፈልን ያለን መሆኑንም በዚህ አጋጣሚ መረዳት አለባችሁ፡፡

‹‹መላውን የምድር ህዝብ አስተምረን፣ አሰልጥነን፣ አሳምነን፣ ተባባሪያችን አድርገን፣ከልዑላችን ጎን ማሰለፍ የሚለው ለኛ ለኔፊሊም ድቅሎች የተሰጠ የቤት ስራ ነው፡፡ለዚያ ስንል ብቻ ነው ሰው እየሆንን የምንኖረውና፤ሰው መስለን፣ሰው ሆነን፣ የምንታየው፡፡እናንተንም ሆነ የምትመሩትን ተራውን ህዝብ ለማስተማርና ለመቀየር፤ለማሰልጠንና የልዑላችን ዓላማ አስርፀን

የተስፋው ተካፋይ ለማድረግ ስንል ራሳችንን ትተን ሰው እየሆንን እያስተማርንና ጥበብን እየገለጥንላችሁ ነው እዚህ ያደረስናችሁ።
‹‹ይህን ለማድረግ ደግሞ የግድ ዝቅ ማለት አለብን።ዝቅ ማለት ሲባል ሰውኛ ቅርፅና ገፅታ መላበስና፤ በአስተሳሰብም ዝቅ ብሎ ሰውኛ አስተሳሰብ መያዝ መቻል ማለት ነው።
‹‹ዝቅ ብለን ሰው ለመሆንና ከሰው ጋር ለመግባባትም ሆነ ሰው መሰል ሰዎችን ለመርዳትና ለማስልጠን ደግሞ የግድ የአሁኑ አይነት ምግብና መጠጥ ያስፈልገናል።ያን እያደረግን ዝቅ ማለትና ሰው መሆንና መምሰል ካልቻልን ግን እኛም ከሰው ሳንግባባ እንቀራለን፤ምድርና ሰዎቿም በነበሩበት ቆመው ይቀሩ ነበር!የሰው ልጅ የአስተሳሰብ መጠንና የሰውነት ቅርፅ ከኛ የአስተሳሰብ መጠንና የሰውነት ቅርፅ ጋር የተራራቀ ስለሆነ በዚያ አይነት ትክክለኛ አቋማችንና ገፅታችን ሆነን ለሰው እየታየን እንዴትም አድርገን የምድራችን ህዝብ በሰውኛ መንገድ መምራት፣ ማስተዳደር፣የትምህርት ስርዓት ቀርፆና ሰጥቶ ማስተማር፣ማሰልጠን አይቻለንም ነበር።
‹‹ህዝቡንም ሆነ መሪዎቻቸውን መቅረብ፤ቀርቦም ማሳመን፣ አሳምኖም የልዑላችንን እና የጭፍሮቹን ረቂቅ እውቀትና የጥበብ ውጤት ተካፋይ ማድረግ አይሞከርም።ወደ ልዑላችን ማምጣትና የዓላማው ደጋፊና ተባባሪ ማድረግም አይቻልም።ባጭሩ ሰውን ለማስተማር ዝቅ ብሎ ሰው መሆን፤ መሆን ባይቻል መምሰል ያስፈልጋልና ነው ዝቅ ብለን እናንተን ለመምሰል የተገደድነው።እኛ ድቅሎች በዚህ አይነቱ መንገድ ነው ሰው መስለንና ሆነን ዓለማችንን ከነህዝቧ ስንመራ፣ ስናስተምር፣ ስናሰለጥንና ስናስተዳድር የኖርነው።
‹‹ስለዚህ ቅድም እንዳያችሁን አይነት ለኛ ጥሩና መልካም የሆነ፣ ነገር ግን የሰው ልጆችን የማያስደነግጥ አካላዊ ቅርፅ ላለመያዝ ስንል የሰው ስጋ እንበላለን።ሰውኛ አስተሳሰብ ውስጥ እንድንገባ ደግሞ ደማቸውን እንጠጣለን።በዚህ ዘዴ ነው ለዘመናት እንደሰው እየታየን፤እንደሰው እየበላን፤እንደ ሰው እየጠጣን፤ከእናንተ ጋር ተመሳስለን የምንኖረው።
‹‹የዓለምን የአስተዳደር ፖሊሲ መቅረፅ ሲያስፈልገን ያኔ ያን ከሰው ላቅ ያለ እውቀታችንን እንጠቀማለን።ያንን ፖሊሲ አርቅቀንና ለሰው ልጆች አስተዋውቀን አካሄዱን ጠቁመን እናሳያለን።ያንን አቅድም ሆነ የአስተዳደር መንገድ አሊያም ርዕዮት ወይም የትምህርት ስርዓት በሰውኛ መንገድና አካሄድ ይፈፅሙና ያስፈፅሙ ዘንድ በየዘመናቱ ለነበሩ ለየአገራቱ መሪዎች እንተዋለን።ስለዚህ የግድ የሰው ደምና የሰው ስጋ በየጊዜው ያስፈልገናል። ያንን ማግኘት ካልቻልን ቅድም እንዳያችሁት አስደንጋጭ መለዋወጥ ውስጥ እንገባለን።ስለዚህ ይህን ማድረግ ለኛ የግድ አስፈላጊ ነውና እንዲህ

ያሉ ህፃናትና ለወሲብ ያልደረሱ ደናግል ሴቶች፤ለኛ ለሴቶች፣ደናግል ህፃናት ወንዶች ለወንድ ንጉሳዊ ቤተሰቦቻችን የግድ ያስፈልጋሉ።
‹‹ብኑሱ ደምና ስጋ ካልሆነ በቀር እንዲህ ሰው ሆነንና መስለን መኖር መቀጠል አንችልም! ያያችኋቸውን የህፃናት ደምና ስጋ ባለገኝ ኖሮ፤ ባያችሁት መለዋወጥ ቀጥየ ሌላ ነበር የምሆነው።ስለዚህ ይህ የዕለት ተዕለት ተግባሬ ነው፤የዕለት ተዕለት ተግባራችን ነው።በኔ በኩል ቢያንስ በየ 3 ወሩ 6 ህፃናት ያስፈልጉኛል።መላው ቤተሰባችንም እንደዚያው።
‹‹ዛሬ ስለዘገየሁና ስለተዳከምኩ ነው ጳጳሳችሁ ያረደልኝ።ሌላ ጊዜ ራሴ ነኝ በቤተ መንግስቱ በሚስጥር እያስመጣሁ የማርዳቸው።መላው የኛ ቤተሰብ በፓላሳችን ግራውንድ ውስጥ ባለ የመመገቢያ ክፍል የሰው ስጋ እየበላና ደም እየጠጣ ወደ ሰው ከተቀየረ በኋላ ነው የሰዎችን ምግብ የሚበላው፤ የሰዎችን መጠጥ የሚጠጣው።አንዴ ወደ ሰውነት ከተቀየርን በኋላ ቢያንስ ለሶስት ወራት ተጨማሪ የሰው ደምና የሰው ስጋ ሳያስፈልገን፤ ሰዎች የሚመገቡትን ምግብ እየተመገብንና የሰው መጠጥ እየጠጣን ያለ ችግር መቆየት እንችላለን።ጊዜውን ካሳለፍንና በወቅቱ ካላገኘን ግን ከሰው ደም የምናገኘው ውስጣችን ያለው የሰው ሴል ተዳክሞ ስለሚጠፋ በቀጥታ ወደ ግዙፍና ለሰው አስፈሪ ወደ ሆነ ትክክለኛ አካላዊ ቅርፃችን እንለወጣለን። እስተሳሰባችንም እንደዚያው።
‹‹ያው አንዳንዴ መዘናጋት ይኖራልና እንረሳለን።ሆኖም አስታዋሾቻችን ባስታወሱን ቅፅበት ወዲያው እርምጃውን ወስደን እናቻችለዋለን።እዚያ ደረጃ የሚደርስ መዘናጋት ውስጥ ባንገባም፤ምናልባት ረስተን ማስጠንቀቂያው የመጣው ህዝብ ፊት ሲሆን ይችላል።የዚያ አይነት አጋጣሚ ድንገት የሚከሰትበት ሁኔታ ይኖራል።ሆኖም ችግር የለውም። ሌሎች ቤተሰቦቻችንም ሆኑ እኔ ከህዝብ እይታ ሳልሰወር የምቆይበት ሁኔታ ቢኖር እንኳ ከተሰበሰበው ህዝብ መሃልም ይሁን ብቻዋን ከምትራመድ ለውሲብ ያልደረሰች ህፃን በተቀመጥኩበት እንዳለሁ በዓይኔ በማየት ብቻ ከርቀት አደንዝዤ ደሟን እጠጣለሁ።ስጋዋን ከሰው እይታ ሰውሬ እበላለሁ።የተበላችው ህፃን ተዝለፍልፋ ከመውደቅ ውጭ ምንም ፍንጭ አይኖርም።የሚያስጠረጥርም ነገር የለም።ህፃናቱ ቅድም እንዳያችሁት ከያገሩ ተለቃቅመው በቤተ ክርስቲያናችን ስር ሆነው እስኪቆዩ ድረስ ይወራጫሉ፤ ያለቅሳሉ፣ ይጮሃሉ፣ እንጂ አንዴ በኛ እይታ ስር ከሆኑ በኋላ በዓይናችን ስለምናደነዝዛቸው ትንፍሽ አይሉም። እየተቁለጨለጩ በደስታ ከመታረድ በቀር ምንም!
‹‹ይህ ሁሉ ለኛና ለልዑላችን እንዲሁም ለእናንተና ለህዝባችሁ ሲባል ብቻ ነው!አዲሲቷ የምድር መንግስት ዘላለማዊ ትሆንልንና ትሆንላችሁ ዘንድ ነው!የዓለምን ህዝብ በምንፈልገው መጠን ጠቅልለን በልዑላችን ስር

ለማድረግና የሱ አጋዥ ሆነው ለድል ያበቁት ዘንድ ነው!የእናንተ የሃያል አገራት መሪዎች ድጋፍ ያስፈለገውም ለእናንተ ለራሳችሁ ሲባል እኛም ሆንን ከኛ በላይ ያሉት የልዑላችን መንፈሳዊ ጭፍሮች ለራሳቸው ሲሉ ነው!ፍፁም ነፃነትና ገደብ አልባ ዘላለማዊ ሃሴት በሙሉ ዘላቂ የምድር ህይወት ይኖረን ዘንድ ነው!

ለዚህም ሲባል በተቀመጠው የጊዜ ገደብና ቀመር መሰረት ሁሉም የየራሱ የስራ ድርሻና የመተግበሪያ ዘመን ተሰጥቶት ሁሉም የየድርሻውን በየዘመኑ እየተወጣ እዚህ ዘመን ላይ ተደርሷል፡፡አሁን ለመጨረሻው ድል የቀረው ጥቂት ዘመን ነው፡፡አፈፃፀም ላይ እንዳለን ተገንዝባችኋል፡፡ብዙ ነገሮ አውቃችኋል፡፡ስለዚህ እኛንም እወቁን ነው እያልኩ ያለሁት፡፡

በዚህ አይነት አመጣጥ ዓለምና ህዝቦቿን አዘጋጅተን እዚህ አድርሰናል፡፡ ይህ ሁሉ ድርጅትና ዝግጅት በኛ፤ ግማሽ ሰው ግማሽ ኔፊሊም በሆንነው የተከናወነ ነው፡፡እንዴት የሚለውን ቀጥዬ በስፋት አስረዳለሁ፡፡እናም.... ራሳችንን ስላሳወቅናችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ!›› ሲሉ! ተሰብሳቢዎቹ የ G 20 አገራት መሪዎች በአንድነት ቆመው ሞቅና ደመቅ ያለ ረጅም ጭብጨባ አስደመጡ፡፡

‹‹ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››ሌላ ጭብጨባ አስደምጠው ተቀመጡ፡፡

ንግስቲቱ በዚህ አይነት ሁኔታ ንመናቸውን እንደ ትልቅ ዝና ቀጥረው በኩራት እየተኩፈሱ፤ በንግግር በመግለፅ፣ በተግባርም በማሳየት፣ ድብቅ ማንነታቸውን ይፋ አደረጉ፡፡

‹‹ወደ ታሪካዊ ዝርዝሩ ልለፍ››በማለት ከበስተጀርባቸው ያለውን ሰፊና ያማረ ቀይ ግድግዳ ከርቀት ሆነው እያዩ በጣት ምልክት ብቻ ባዶው ህዋ ላይ ጫር ጫር ሲያደርጉ ከሰፊው ቀይ ግድግዳ ፊት ለፊት ሰፊና ዘመናዊ ስክሪን ተከሰተ፡፡

‹‹ናኖ ቴክኖሎጂ›› በመባል የሚታወቀው ረቂቅና ኢምንት፤ ነገር ግን ሁሉን ማድረግና መስራት፤መታዘዝና ማሳየት፤የሚችል ረቂቅ የቴክኖለጂ ውጤት ነው፡፡በረቂቅ የሞሉኪልና የአተሞች ውህድ ተዋቅሮ የፊዚክስን፣ የኬምስትሪን፣ የባዮሎጂንና የሌሎችን ቀመሮች አጠቃሎ የያዘና በነሱም ላይ ተመስርቶ የኢንጂነሪንግ ጥበብም ታክሎበት የተሰራ፤የሰው ልጅ የደረሰበት የመጨረሻ የቴክኖለጂ ውጤት እንደሆነ የሚነገርለት ነው፡፡ አይነትና ዘርፉ የተለያየ ሲሆን፤የሚሰጠው አገልግሎትም በተመሳሳይ የተለያየና ዘርፈ ብዙ ነው፡፡በዚህ አዳራሽ ውስጥ አሁን ጥቅም ላይ የዋለው ከሰው እይታ ውጭ ሆኖ አየር ላይ ሊገኝ የሚችልና በአንድ ቃል ወይም በምልክት ብቻ ማብራትና መጠቀም የሚያስችለው ህዋ ላይ ያለ የጠራና ፍፁም ዘመናዊ የሆነ ሰፊ ስክሪን ነው፡፡ያለ አንዳች ድጋፉ ቁስ ህዋ ላይ

ሆኖ እንደ ቴሌቪዥን ሁሉን ነገር የሚያሳይና በመሃሉ ተራምደን ልናልፍበት የምንችለው ዓይነት ስክሪን ነው።ይህን ከናኖ የቴክኖለጂ ውጤት ውስጥ አንዱ የሆነውን የህዋ ላይ ስክሪን ነው እርጊቷ ንግስት በጣት ምልክት ብቻ ህዋ ላይ መዘርጋት የቻሉትና መጠቀም የጀመሩት።

ንግስቲቱ በሚደንቅ ፍጥነት ስክሪኑን እየነካኩ በተንቀሳቃሽ ምስል አስደግፈው ለማስረዳት ተዘጋጁና፤‹‹ውጭና ውስጣችሁን እንዳበራችሁ በደንብ ተከታተሉኝ!››ሲሉ ጀመሩ።

‹‹መሳውን የአውሮፓም ሆነ የሌላውን አህጉር ኋላ ቀር ህዝብ እኛና የእኛ ዘሮች ከሆኑት ውጪ ማንም ሰብዓዊ ፍጡር የሆነ ንጉስም ሆነ እውቀት ያለው ሰው ሊያሰለጥነውና ከኋላ ቀርነት ሊያላቅቀው አይችልም ነበር።

የዚችን ዓለም ህዝብ ከኛ፣ከልዑላችን ጭፍሮችና ከልዑላችን በስተቀር ማን ሊያሰለጥነው ይችል ነበር?ማንም!እድሜ ልኩን ፈረስ እየጋለበና ድንጋይ እየጠረበ፣ብረት እያሾለ ከመዋጋት ውጪ ምንም ምርጫ ያልነበረውን ኋላቀር ህዝብ መስወጥና ማሰልጠን አስፈላጊ ነበር።ከኩራዝ አውጥቶ ወደ ዘመናዊ ብርሃን ማምጣት የግድ ነበር።ያ ካልሆነና የሰው ልጅ ከነድድብናው እየኖረ ከቆየ ለልዑላችን ምን ይጠቅመዋል?ምንም!

‹‹ቀድሞ ነገር ራስን የሚያሳውቀውን ሚስጥርስ ለምን ለመጀመሪያው የሰው ፍጡር ገለፀለት?የበላይ አካሉ የከለከለውን ነገር ለምን ሚስጥሩን ነግሮ አብልቶ አስበልቶ አነቃው?ለምን ራሱን እንዲያውቅ አደረገው?የሰው ልጅ ራሱን ማወቅና መሰልጠን ስላለበት ብቻ ሳይሆን፤እየሰለጠነ እንዲቀጥልና እሱን እያመለከ፣ ለሱ እየተገዛ፣በሱ ጥበብ እየተመራ፣በሱ ስር ሆኖ፣ ኑሮውን ይቀጥል ዘንድ በማሰብ ጭምር ነው!

ሰው ራሱን አውቆ፣ ተምሮ፣ሰልጥኖ፣ተራቆ፣ራሱን እንዲያውቅ ካደረገው ከልዑላችን ጎን ተሰልፎ፣ በነፃነት እንዲኖርና በነፃነት የተሞላ አጭር ህይወቱን ለዘላለም አስቀጥሎ መኖር እንዲችል በሚል መነሻ እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም።በጥቅም አልባ ምክንያት አይደለም ልዑላችን ለመጀመሪያው ሰው ራስ የማወቂያ እፅዋትና ፍሬን የጠቆመው!ያንን አድርጎም አላበቃም።ቀጣይነት ያለው ስራ ነው የጀመረው።ያ ጅምር ስራ እስካሁንም ድረስ ቀጥሎ የቆየና ቀጥሎ ያለ ነው።ልዑላችን ከሰዎች ጎን ሆና የሰው ልጆችን ከጎኑ አድርጎ እያሳወቀ፣እያስተማረ፣እያሰለጠነ፣ መቀጠል እንዳለበት ያሰበው በድንገትና መሃል ላይ ሳይሆን ያኔ ከጅምሩ ጀምሮ ነው!ሰው ራሱን በማወቅ ሳይወሰን ቀጣይነት ወዳለው የእውቀትና የስልጣኔ ሽግግር አምርቶ ከእሱ ጎን እንዲሆን ስለፈለገ ብቻ ነው የመጀመሪያውን ሰው ራሱን እንዲያውቅ ያደረገው!የሰው ልጆችን ወደዚህ የእውቀትና የስልጣኔ ሽግግር ለማምጣት ደግሞ ምትክ የለሽ አስፈፃሚዎቹ እኛ ከሰው የምንቀራረበው ድቅሎች ነበርን።

የሳጥናኤል ኀል ኢትዮጵያ

‹‹ተከታተሉኝ ክቡራን፡፡ቀደምት አባቶቻችን ከዚህ ቀደም በሰፊው በተብራራላችሁ ታሪክ ምክንያት የመጀመሪያ ምድራቸውን ኢትዮጵያን ከበላይ አካሉ ጭፍሮች ጋር በተደረገ ውጊያ ከለቀቁ በኋላ፤ርቀው በመሸሽ ይህን በረዷማ አካባቢ ይዘው ከሰው ጋር መዋለድ፣ መዳቀልና መዋረሳቸውን ቀጥለው ቆይተው ነበር፡፡

ከዚያ ታሪክ በኋላም ለሰው ልጆች ብቻ በመጣው በጥፋት ውሃ ምክንያት ጥቂት ድቅሎችን ልዑላችን በእሳተገሞራ ከልሎ ካስመለጣቸው በኋላ፤ ሌሎቹ ያልተዳቀሉት ዋና ዋናዎቹ እዚሁ አካባቢ ነበር የቆዩት፡፡ሁለተኛው የሰው ልጆች ምእራፍ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶም ዋና ዋናዎቹ በተለይ በአውሮፓ ምድር በግሪክም፣በሮምም፣በሌሎችም አማልክት ሆነው እየተመለኩና ለሰው ልጅ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ጥበብ እየገለጡ፤ከሰው ጋር ያላቸውን ግንኙነት አጠናክረው ቀጥለው ቆይተዋል፡፡በመጨረሻ ግን በበላይ አካሉ አማካኝነት ሐይማኖቶች መፈጠር ሲጀምሩና ወደ ዓለማችን ሲመጡ የአማልክቱ ዘመን ያከትምና ዘመኖቻቸውን ጨርሰው ሁሉም ተጠቃለው ወደ ልዑላችን ፒራሚድ ይገባሉ፡፡ዋና ዋናዎቹ ተጠቃለው ሲገቡ በርካታ ድቅሎችም አብረው ገብተው ነበር፡፡ይሁን እንጂ ያልገቡ በርካታ ድቅሎችም ነበሩ፡፡ብዙዎቹ በያሉበት ሆነው ሳይመለሱ ቆይተዋል፡፡

‹‹ሐረጅም ምእተ ዓመታት በኋላ በክርስትና ማግስት እኛና የኛ ዘሮች የሆኑ ድቅሎች እንደ አዲስ የምድርን ህዝብ ለማስተማር፣ ለማስልጠንና ለማዘመን፣ እዘምናም ለልዑላችን ዓላማ የማዘጋጀት ተልእኮ ይዘን መውጣት ነበረብን፡፡

ከክርስትና በፊት የነበረው ዘመን የእነዚያ የዋና ዋናዎቹ መንፈሳዊ ጭፍሮች እንደነበረው ሁሉ፤ከክርስትና በኋላ ያለው ዘመን ደግሞ የኛ ከዝማስያ የበታች ጭፍሮች የተደቀልነው ወገኖች ሆነ ማለት ነው፡፡

እናም ተልእኮውን ይዘን ወጣን፡፡ምክንያቱም ስራው መሰራት ያለበት በድቅሎች ስለሆነ ነው፡፡ድቅሎች ሲባልም ልክ እንደኛ ሃምሳ ሃምሳ ፐርሰንት የሆኑት ማለቴ ነው፡፡ግማሽ ሰው፤ግማሽ ኔፊሊም፡፡ምክንያቱም አካላዊ ቅርፃችንንም ሆነ አስተሳሰባችንን እየለዋወጥን ከሰው ጋር ተመሳስለን መኖር፤ማስልጠንና ማስተማር የምንችለው እኛ ስለሆንን ነው፡፡ እድሜያችንም እንደ ሰው ልጅ መቶ ሃያ ተብሎ ገደብ የተጣለበት አይደለምና ራሳችንን እየለዋወጥን፣ እንደ ሰው ሆነን እየኖርን፣እንደ ሰው አርጅተን የሞትን እያስመሰልን፣እንቅስቃሴውን ጀምረን ቀስ እያደረግን ቀጠልነው፡፡

‹‹በክርስትና ማግስት ከፒራሚዳችን ከወጣን በኋላ አባቶቻችን ባንድ ወቅት ሰፍረውበት የነበረውን ይህን የዘሮቻችን ምድር የሆነውን በረዷማ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

የአውሮፓ ክፍል ይዘን፣አካባቢውን በቅርብ ርቀት እየተመለከትን ከሰዎች ጋር ተመሳስለን መኖር ጀመርን።

እንደምታዩን መልካችንም ሆነ ቅርፃችን የሰው ዓይነት ነው። ማንም በምንም መንገድ ሊለየን ባይችልም እርስ በራሳችን ግን እንለያያለን።

‹‹የእኛ ዘር እስከሆነና ፐርሰንቱ ግማሽ ግማሽ እስከሆነ ድረስ በየትኛውም አገርና አህጉር ቢኖር በልዩና ለሰው በማይታየው፣ርቀት በማይገድበው፣የመገናኛ አንቴናችን አማካኝነት እንተየያለን፣እንገናኛለን፣መልዕክትም እንለዋወጣለን። ዛሬ እናንተ ውስጣችሁን አብርታችሁ ከሩቅም ከቅርብም ያሻችሁን እንደምታደርጉት ሁሉ፣እኛ ደግሞ ከዚያ የበለጠና የላቀ ጥበብ ተቋርሰን የተፈጠርን ስለሆንን የሚሳነን ነገር አልነበረምና በዚህ አስቸጋሪ የበረዶ ተራራ ላይ እየኖርን ረጅም ዓመታት ስናሳልፍ የተቸገርንባት አንዳች ጉዳይ አልነበረችም።

‹‹በሂደት ስናዳብረው የቆየነውን ቋንቋና ባህላችንን ይዘን፣የአንግሎ ሳክሶን ነገድ በሚል ስያሜ ስንጠራ ከቆየን በኋላ፣መሰረቱ አንድ የሆነና መጠነኛ ልዩነት ያለው ቋንቋ ለሌሎች በአካባቢያችን አብረውን ለነበሩ ሰዎች እያካፈልንና እያስረፅንባቸው ነበር የቆየነው።

‹‹እንደምታውቁት ከ 450 -1066 ዓ.ም ያለው ዘመን የአንግሎ ሳክሶን ዘመን ተብሎ ይጠራል።የአሁኑ የአውሮፓ ምድር አንግሎ ሳክሶን በመባል ሲታወቅ በውስጡ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ አውሮፓ ድረስ ያሉትን የሰው ልጆችን ወይም የህዝቦችን መኖሪያ ምድር ያጠቃለለ እንጂ የእኛን አካባቢ ብቻ አይደለም።በዚያ ግማሽ ሚሊኒየም ዓመታት የኛ ዘሮች በአካባቢው ላይ ጥቂት ነበሩ።አንድ ራሱን የቻለ የነገስታት ቤተሰብ መሆን የሚያስችልና ለንግስናና ለአስተዳደራዊ ስልጣን በቂ የሆነ ብዛት እንጂ እንደ ህዝብ መደራጀት የሚያስችል በሚሊዮን የሚቆጠር ብዛት አልነበረንም።

እናም ይህን ህዝብ ጠቅልለን ማስተዳደር የነበረብን እኛ ነንና የመጀመሪያውን ስራችንን አንድ ብለን ለመጀመር ነው ከየተሰራጩንበት እንደ አዲስ መሰባሰብና መደራጀት የጀመርነው።ይህን የአንግሎ ሳክሶን ህዝብ ጠቅልሎ የማስተዳደርና የማስልጠን፣ዘሮቻችን በአንድ ወቅት ሰፍረውበት የነበረውን ምድር እንደ አገር መመስረት፣የሚመሰረተውን አገር አሳድጎና ህዝቡንም አሰልጥኖ ለልዑላችን የመጨረሻ ዓላማ ምቹ ማድረግ፣በቀድሞው ዘመን በአውሮፓ ምድር ተበታትነው ከሰው ልጆች ጋር ተቀላቅለው እየኖሩ ያሉ፣በመዳቀል ብዛት ሙሉ ለሙሉ ሰው ወደመሆን ሊሸጋገሩ ጥቂት የቀራቸውን ጥበበኛ ዘሮቻችንን ከየተበተኑበት አሰባስቦ እውቀታቸውን ለዓለም ህዝብ እንዲያከፋፍሉ ማድረግ፣ የሚሉት ዋና ዋና የቤት ስራዎቻችን ነበሩ።

‹‹ይህን ለማድረግ የመጀመሪያው ስራ ደግሞ በኛ ስር የሚተዳደር ህዝብ መያዝና አገር መመስረት ነበር፡፡በዚህ መሰረት ቀደም ብለን የያዝነውን የኛ ዋና ዋና ዘሮች በአንድ ወቅት ሰፍረውበት የነበረውን ቦታ የራሳችን ግዛት አድርገን መሰረትን፡፡ያ ግዛት ይህ የምታዩት በረዷማ የአውሮፓ ክፍል ነበርና በዚህ በአውሮፓ ምድር ሰፍረን ግዛታችንን መሰረትን፡፡ዘመናችን ጠብቀንም ከሰው የላቀ እውቀታችንን እየተጠቀምን አንዳንድ አዳዲስና የተሻሻሉ ነገሮችን እያሳየንና እየጠቆምን ህዝቡ ውስጥ ሰርፀን ከመግባት አልፈን ጎልተን መታየት ጀመርን፡፡

‹‹ኋላ ቀሩን የአውሮፓ ህዝብ በዘመናዊ መንገድ እያደራጀን፣በበሰለ ንግግር እያስተማርን፣የተሻለ የውትድርናና የውጊያ ዘዴ እያለማመድን፣ፖሊሲ እየቀረፅን፣ የአስተዳደር ስርዓት እያሳየን፣ሁሉን ነገር የተሻለ አድርገን እየቀየስን፣ በአሁኑ የአውሮፓ ምድር ሰፍረው በነበሩ ህዝቦች ዘንድ ታዋቂና ተወዳጅ ብሎም ተከባሪ እየሆንን ሄድን፡፡

እናም በዚህ አዳዲስና የተሻሻለ የአስተዳደር ስልታችንና በሁለመናችን ከአካባቢው ማህበረሰብ የተሻልን መሆን ችለን ታይተን ነበርና ህዝቡ፣ የጨዋ ዘሮችና አስተዋዮች፣፣ከተከበረ ቤተሰብ የተገኙ፣ለአስተዳደር የሚሆን ዕውቀት ያላቸው፣ሁሉንም ከአምላክ የታደሉ ምርጥ ዘሮችና የህዝብ ተቆርቋሪዎች የሆኑ በሚል የአካባቢው ተጠሪዎች አድርጎ ወሰደን፡፡ የአንግሎ ሳክሶን ስልጣኔ መስራች ተደርገንም ተቆጠርን፡፡

‹‹በዚህ መልኩ ተቀባይነት አግኝተን ስልጣን መያዝ ቻልን፡፡የራሳችን ልዩና የተከበረ ቤተመንግስት ኖረን፡፡ ወንዶቻችንም የተደራጀን ጦር መምራት፣ በጥበባቸውም ድል ማድረግ ሲችሉ፣በሂደትም ስልጣኑን ለልጆቻቸው እያስረከቡ እየተተካኩ ሲቀጥሉ፣ የነገስታት ዘሮች መባል ጀመሩ ወይም ጀመርን፡፡በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተደራጅተን አንድ ራሱን የቻለ የነገስታት ቤተሰብ ሆነን፤ እንደ አንድ ልዩ ጎሳ ተቆጥረን በመታየት፤የራሳችን የተከበረ ክልል ከልለን፣በሮማውያን ዘመን አባቶቻችን አስጀምረው ያስቀጠሉትን የላቲን ቋንቋና ፊደልን መነሻ መሰረት በማድረግ የራሳችን ልዩ ቋንቋና የሰለጠነ ፊደል እንዲሁም ልዩ ባህል ይዘን፣ የአካባቢውን ህዝብ ማስተዳደር ጀመርን፡፡

‹‹ያኔ ደግሞ የዓለም ህዝብ ክርስትና ሐይማኖት ላይ በጣም የተመሰጠበትና ክርስትናም ተቀባይነት ያገኘበት ዘመን ነበር፡፡መላው የአውሮፓ ምድር ህዝብም ክርስቲያን ሆኖ የኖረ ነውና እኛና ዘሮቻችንም ያንኑ ሐይማኖት አክብረንላቸውና ራሳችንም ከህዝቡ የተሻለና የበለጠ ክርስቲያን ሆነንና መስለን፤አልፈን ሄደን የክርስትና ዋና ተቆርቋሪና ተጠሪ፤ የሚጋረጥበትን አደጋም አስወጋጅ ሆነን ተገኘን፡፡

‹‹በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲባል፤የህዝቡን ሐይማኖት መቀበልና ህዝብን መስሎ ማስተዳደር አስፈላጊና ግዴታ ነውና ዛሬ ድረስ በክርስትና ህግ የምንመራ መስለንና ሆነን የምንኖር ነን፡፡ይህ ምንም ማለት ካለመሆኑም በላይ፤ይልቁንም ለኛና ለልዑላችን ዓላማ እጅግ ጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ያው እንደምታዩት የዓለምን የክርስትና ምዕመን የምትዘውረው የቫቲካን ቤተክርስቲያን የኛ መሆን የቻለችው በዚሁ አካሄድ ስለመጣን እንጂ፤እኛ የቤተክርስቲያኗም ሆነ የክርስትናው መስራች ስለሆንን አይደለንም፡፡ወይም አልነበርንም፡፡አያችሁ?ልዑላችን አገባቡንም አወጣጡንም ያውቀዋል!!አያችሁ?የክርስትና ተቃዋሚ ሆነን ነገር ግን ክርስትና እንዲስፋፋም ስንሰብክ ነበር፡፡ክኛ ወገን የሆኑም መጽሐፉን ተርጉመው እስከማስራጨት የደረሱ ነበሩ፡፡እነሱ ባያስራጩትም እንዴ ይፋ ስለሆነና ስለተሰራጨ፤በደንብ መሰራጨቱ አይቀርምና ከማንም በላይ ተቆርቋሪ ለመምሰል በኛ ቤተመንግስትና በኛ ንጉሰነገስት የተሰራጨ ተብሎ የሚታወቅ ከሌላው መጽሐፍ በምንም የማይለይ መጽሐፍ ቅዱስ አለ፡፡ ሁሉም ተፈልጎና በምክንያት የሆነ ነው፡፡ባርነትን እኛው ራሳችን አስጀምረንና ህጋዊ አድርገን፤ እኛው ራሳችን ተቃውመን ባርነትን በህግ ገድበን አስቁመናል፡፡ሌላም....ሌላም....

‹‹እናም በዚህ አይነት ሂደትና ውርርስ እኛንና የኛን ቤተሰቦች መሳው የአንግሎ ሳክሶን ማለትም የአሁኑ አውሮፓ ህዝብ ለኛ ዘሮች የነገስታት ቤተሰብነት ሙሉ እውቅና ሰጥቶ ሊገዛልን ቻለ፡፡በሂደትም መላው ዓለም አፍሪካውያንን ጨምሮ ለኛ የነገስታት ቤተሰብነትና የዘር ሃረግ ሙሉ እውቅና ሰጠ፡፡

‹‹እኛም አገራችንንና በዙሪያችን የነበሩ ግዛቶቻችንን በጠንካራ መሰረት ላይ በተገነባ ህግ፤ ስልጡንና ዘመናዊ ሆኖ በቀጠለ የአስተዳደር ስርዓት መምራትና ማስተዳደር ቻልን፡፡

‹‹አገራችንና ግዛቶቻችን በዋናነት በዘውድ ስርዓት ሲመሩ፤በሂደት ደግሞ የዘውድ ስርዓቱን የሚጠብቅና ተጠሪነቱም ለዘውዱ የሆነ ሌላ ዘመናዊ የአስተዳደር ስልት በመጨመር ተጠሪነታቸው ለጠቅላይ ሚንስትሩ የሆኑ ሚንስትሮችን በመሾም አገራችን በዘመናዊ መንገድ በጠቅላይ ሚንስትር እንድትመራ አደረግን፡፡

በዚህ አይነት እርስ በርስ እየተጠባበቅንና በህጋችን የበላይነት እየተመራን፤ ነገር ግን ሁሉንም እኛ እየመራን እዚህ መድረስ ቻልን ነው ታሪኩ፡፡

‹‹ያን ሁሉ ውስብስብ የነበረ፤ ለኛ ግን ቀላል የሆነን ተግባራት በሙሉ ካከናወንን በኋላ፤ በጥሩ ሁኔታና በጥሩ ተቀባይነት የአስተዳደር ስልጣኑን ከያዝንና ዘሮቻችን ከተሰባሰቡ በኋላ፤ ለፍረንበት የኖርነውንና የቀድሞ

ዘሮቻችን ምድር የነበረውን ቦታ ወይም አካባቢ አገር አድርገን መስርተን ‹‹ኢንግ ላንድ›› አልነው፡፡
ኢንግላንድ የተባለችውን አገር በአዲስ መልክ ቆርቁረንና ዘመናዊ ህንፃዎችን ገንብተን ከቤተ መንግስት እስከሰለጠነ ህገመንግስት ድረስ ያለውን ስራ በሙሉ በማጠናቀቅና አገሪቱ ላይ በተግባር በመተርጎም ታላቅ አገር አደረግናት፡፡በይፋ እንደሚታወቀው ‹‹ኢንግ ላንድ›› ማለት ‹‹ኤንጅልስ ላንድ›› ማለት ነው፡፡‹‹የመላዕክታን ምድር!››የዚያ ዘመን ህዝቦች የአገራችን ስያሜ በደስታ ሲቀበሉት፤እንደነሱ አስተሳሰብ የነገስታት ዘሮች ናቸውና መላዕክት ሊባሉ ይገባቸዋል፡፡እንዲያውም ያንሳቸዋል የሚል ነበር፡፡ሌላውም ያን ይዞ ለረጅም ጊዜ ቆየና፤ በስተመጨረሻ በተለይም ከመጽሐፈ ሄኖክ መገኘት በኋላ ትክክለኛው ትርጉሙ በይፋ እየታወቀ ሄደ፡፡
ከዚህ ቀደም በስፋት የተብራራላችሁ መጽሐፈ ሄኖክ ተገኝቶ በከፊል ይፋ ሲሆንና፤ በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተጠና ከጥርጣሬ አልፎ እውነት ሆኖ ሲገኝ ያዩት የአሁኖቹ ትውልዶች ኢንግ ላንድ ወይም የመላዕክት ምድር የሚለውን ትተው፤የወደቁ መላዕክታን ምድር ማለት እንደሆነ መግለፅ ጀመሩ፡፡የወደቁ የሚለው ቃል ባይገልፀንም የኤንጂልስ ዘር መሆናችን ግን ሃቅ ነው!ምክንያቱም ከመላዕክት ሳይሆን ከነሱ የበታች በታች ካሉ ጭፍሮች የተደቀልን ስለሆንን፡፡እንጂ ዋና ዋና መላእክታን ፆታም የላቸውም ከሰውም አይዳቀሉም፡፡ከነሱ ስር ያሉ እልፍ አእላፍ ጭፍሮችን ነው ያልነው!የበላይ አካሉ መጽሐፍ ቅዱስ ኔፍሊም ብሎ ከገለፃቸው ማለቴ ነው፡፡
እናም አልወደቅንም፡፡መች ወደቅንና?እርግጥ ነው ልዑላችንና የበታች ወታደሮቹ ከኋላ ቀሩ ሰብዓዊ ፍጡር ጎን በመቆማቸውና፤ የእውቀት ገደብ ተጥሎበት የተፈጠረውን ሰብዓዊ ፍጡር እውቀት ገልጠው ራሱን እንዲያውቅ በማድረጋቸው ወደ ምድር መምጣታቸው እውነት ነው፡፡ መውደቅ.....የሚለው ግን....አይገልፀንም......!እስካሁንም አልወደቅንም ወደፊትም አንወድቅም!
‹‹ሰማንኛውም ኤንጅልስ ላንድ ባጭሩ ኢንግ ላንድ ብለን ቅድመ አያቶቻችንን ለሰው ከመጣው የጥፋት ውሃ ሲሸሹ ለውስን ጊዜ መደበቂያ ቦታ ያደረጉት ቀደም ሲል ያሳየኋችሁን በረዷማና ተራራማ ቦታ ነውና በስማቸው ለይመን አገር አድርገን መስርተናል፡፡
‹‹ሰንደቅ ዓላማችንም ይህ ነው፡፡የመጀመሪያውንም ያሁኑንም ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ይሄኛው የመጀመሪያው በነጭ መደብ ላይ ቀይ መስቀል ሲሆን፤ መስቀሉ የተጋደመ ወይም የተኛ ነው፡፡ይህኛው ዘመናዊውና የተሻሻለው አሁንም ድረስ የምንጠቀምበት ደግሞ እንደምታዩት የቀድሞው የተጋደመው ቀይ መስቀል እንደዚያው

እንደተጋደመ ሆኖ፤በሰማያዊ መደብ የተጋደመውን ቀይ መስቀል የኤክስ ምልክት ነው ያደረግንበት!

‹‹ይህንን ማንም የዓለም ህዝብ ዛሬ ድረስ አላወቀውም! አስቦትም፣ ጠርጥሮትም አያውቅም!እናንተም ጭምር!ያሰበው አለ?ምናልባት ጳጳሳችሁ?›› ሁሉም በመካከለኛ መደነቅ ውስጥ ሆነው እንደማያውቁት በአንገት እንቅስቃሴ አረጋገጡ።።ንግስቲቱ ፈገግ ብለው ቀጠሉ።።

‹‹አዎን ከጥቃቅኑ ጀምሮ እስከ ግዙፉ ያለውን ምልክት ብዙዎች ልብ ብለው መርምረው እውነታው ላይ ቢደርሱም፤ ይህ ግን ሁሌም ተነስቶ የማያውቅና እኛንም ራሱ አሁን ድረስ የሚገርመን ነገር ነው!ይህ ነው ለንደቅ ዓላማችን!መስቀሉን አጋድመን የኤክስ ምልክት ነው ያደረግንበት!ይህንን ነው በየ ስቴዲዮሙ ከፍ አድርገንና አስደርገን ስናውለበልብ የኖርነውና ዛሬም ድረስ ከፍፍፍፍ ብሎ እየተውለበለበ ያለው!አዎን!መስቀሉም ባለመስቀሉም ይጋደማል!ከዚያም አልፎ ሰማያዊው ተስፋ በልዑላችን ድል አድራጊነት ኤክስ ይደረጋል!ሰማያዊ ተስፋ ኤክስ!ቀዩ መስቀልም መጋደም መተኛት መውደቅ.....!›› ሲሉ፤ተሰብሳቢዎቹ አድናቆታቸውን ለመግለፅ እንደለመዱት ሞቅ ያለ የጋራ ጭብጨባቸውን አስተጋቡ።።

‹‹ኢንግላንድን አገር አድርገን ከመሰረትን በኋላም ሆነ እየመሰረትን በነበረበት ጊዜ፤ጎን ለጎንም በዙሪያችን ላሉና ያኔም ለነበሩ የሩቅና የቅርብ የአውሮፓ ነዋሪ ህዝቦች የየራሳቸውን አገር እንዲመሰርቱና እንዲከለሉ በማድረግ እንረዳቸው ነበር።።መርዳት ብቻም ሳይሆን፤በየአገሩ አስተዳደራዊ ስልጣኑን ይይዙ ዘንድ ለንጉስነገስትነት፣ ለንግስተ ነገስታትነት፣ የሚሆኑ ዘሮቻችንን በየጎረቤት አገሩ ህዝቦች ውስጥ አስርፀን ገዥዎቻቸው ሆነው እንዲቀጥሉ አድርገናል።።

‹‹የአሁኗ ፈረንሳይ ጥሩ ምሳሌ ናት።።ገዥዎቻቸው ሆነው ሲያስተዳድሩም ህዝቡን በዘመናዊና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እየመሩ፤እየተቆጣጠሩ፣ እኛ የምንሰጣቸውን ትዕዛዝ እየተገበሩ፣ ሚስጥር እያካፈልናቸው፤አገር ስንገዛ እያጋራናቸው ነው።።ከኛ የተለዩና ራሳቸውን የቻሉ ሌላ ህዝቦች እንዲመስሉ በሚልም ቋንቋና ባህላቸው ስሩን ሳይለቅ ለወጥ እንዲል ተደርጓል።። ይህንንም ተራው የፈረንሳይ ህዝብም ሆነ ሌላው ህዝብ ሳያውቅ ያደረግነው ነው።።በዚህ መልኩ ብዙ ርቀት መጓዝ ችለን ነው እዚህ የደረስነው።።

‹‹በኢንግላንድ ዙሪያ በተመሰረቱት አገሮች ላይ የኛ የአስተዳደራዊ ስልጣን የግድ አስፈላጊ የነበረ ከመሆኑም በላይ፤የኛን ምድር ካጠናከርን በኋላ በኛ ስር ማድረግ የበለጠ አስፈላጊ ነበርና ቀጣይ ስራችን ያደረግነው ያንኑ ነው። ።

በዙሪያችን ያሉ ህዝቦችን እንደ አየርላንድ ዌልስና ስኮትላንድ ወደኛ በማምጣት የአገራችንን መጠሪያ ስም በየዘመናቱ እየለዋወጥን ታላቅ አገርና ህዝብ የመገንባት ስራችንን አጠናክረን ቀጠልን፡፡ከሰው የበለጠ እውቀትና ጥበባችንን በመጠቀምም ሃያል አገርና ሃያል ህዝብ መሆን ቻልን፡፡ቀስ በቀስም በየአህጉሩ ያሉ የዓለም አገራትን በቅኝ ግዛት በመያዝ በኛ ቁጥጥር ስር ማድረግ ቻልን፡፡

በዚህ አይነት መንገድ በተደላደለ የአገዛዝ ስርዓት ላይ ከሆንንና፤ ሃያልነታችን ለዓለም ህዝብ በተግባር አሳይተን ካረጋገጥን በኂላ፤ ወደ ቀጣይ ስራችን በማምራት ከቀድሞ ጀምሮ በሌሎች አህጉር ተበታትነው የነበሩና በረጅም ዘመናት ውርርስ ከሰው ልጅ ጋር በመዳቀል ሙሉ ለሙሉ ወደ ሰው የዘር ሃረግ ሊሸጋገሩ የነበሩ ወገኖቻችንን ከየሩቅ አገሩ መሰብሰብና ማደራጀታችንን ቀጠልን፡፡

‹‹እነዚህን ወገኖቻችንን ከሰበሰብንና ካደራጀን በኂላም አንድ ሰፊ፤ የራሳቸውና የራሳችን፤ብሎም የዘር ማንዘሮቻችን እውቀትና ጥበብ የሚፈልቅባት፣ቤተ መቅደስ ሆና ልዑላችን የሚመለክባት፣ስልጡን ሆና ስልጣኔዋን ለሌላው ዓለም ማካፈል የምትችል፣ሃብታም ሆና ሌሎችን ለመርዳት የምትበቃ፣ሃያል ሆና ሌሎችን ማዘዝ የምትችል፤ ሰፊና ድንቅ አገርን ጫካ መንጥረን መመስረት ነበረብን፡፡ይህን ለማድረግ የተጠና አካሄድ መሄድ ነበረብንና አካባቢውን ቀድመን በቅኝ ግዛት አይነት ይዘን ምድሪቱን በደንብ ስናጠናና ስናዘጋጃት ቆየን፡፡በመጨረሻም የዓለም ህዝብ ከአገርነት ያለፈ ምንም ሚና እንደሌለን አድርጎ ያስብና ያውቅ ዘንድ በመናገሻችን በብሪታኒያም ሆነ በእኛ በኩል ምንም ያልተደረገ በማስመሰል ለዚያች አገር ነፃነቷን ሰጥተን መልቀቅ ነበረብንና ነፃ አገር መሆኗን አውጀን ለቅቀን ወጣን፡፡ያች አገር ራሷን የቻለች አገር ሆነች፤ወይም መሰለች፡፡እነሆ ያ በሆነ ማግስት ልዑላችን በመረጠው ቦታና በመረጠው ጊዜ ቤተመቅደሱን በዚያች ምድር ሰራንለት! መናገሻ የሆነች አገርም፣ ቤተመቅደስም፣አድርገን በጥሩ ሁኔታ አሜሪካንን ገነባንለት!

አሜሪካ የተባለችውን አገር አምጠን የወለድናት፤ የገነባናት፣ነፃና ምቹ አገር አድርገን የጥበብ ሰዎች ይሰፍሩባት ዘንድ ያመቻቸናት እኛ ነን! ዓለምና ህዝቦቿ እንግሊዛውያንን እና አሜሪካውያንን ጨምሮ፤አሜሪካን ያገኛት፣ በመርከቡ ዙረት የደባበሳት፤ አሜሪጎ፣ቫስኮ ደጋማ፣ ወ.ዘ.ተ. እያለ እኛ የዋሸንለትን ውሸት ዛሬ ድረስ ደግሞ እየዋሸ ይገኛል፡፡እንዲያ እንዲረዳውና በዚያ መልኩ እንዲያውቀው ያደረግነውም ሆነ ብለን ነው፡፡እነ አሜሪጎ ሳይቃኟት መርከበኞች ሳይደባብሷት፤ ጫካ መንጥረን፣አገር አድርገን ገንብተን፣ የዘር ሃረጎቻችንን ከያሉበት አሰባስበን አስፍረን፣የምድራችን ፍፁም ዲሞክራሲያዊ ህግ አርቅቀን፣ መስራችና የመጀመሪያ ፕሬዘዳንት

የሆነውን ሰው ከቤተመንግስታችን አውጥተን፣ስንቁን ቋጥረንና ዓላማችን አስተምረን፣አቅፈንና ስመን የሸኘነው እኛው ነን!›› እያሉ ሲያብራሩ፣ቋሚ ስራቸው ማጨብጨብ የሆነው ሁሉም ተሰብሳቢዎች ቢጋራ ቆመው ረዘም ያለ ጭብጨባ አደረጉ።።ይህን አድርገው በስሙት ነገር እንደተደመሙ በየወንበሮቻቸው ቁጭ አሉ።።

‹‹ያች አገር ወደፊት ምን አይነት አገር እንደምትሆን ቀድመን እናውቃለንና፣የሚመጥናትንና በትክክል የሚገልፃትን ስያሜ ነው የሰጠናት፡
፡

ከግብፅ፣ከግሪክ፣ከእብራይስጥ፣ከላቲን፣ተወስደውበተዋቀሩ ቃላት Amaruka አልናት።።ከዚያም America ብለን ሰየምናት።።Am የእብራይስጥ ቃል ሲሆን ህዝብ ማለት ነው።።Rica/ የላቲን ቃል ሲሆን Rich ሀብታም ማለት ነው።። eri የቀድሞ የግሪክ ቃል ሲሆን፣lion አንበሳ ወይም አሽናፊ ማለት ነው።። የበላይ ማለት ነው።። Ca/Ka/ የቀድሞው የግብፃውያን ቃል ሲሆን sprit force/spiritual force/ መንፈሳዊ ሃይል ማለት ነው።።

‹‹ይህን ስናደርግም ቀጥዬ በስፋት እንደማብራራው በምክንያትና በልዑላችን ፈቃድ እንዲሁም በእርሱ የጊዜ ቀመርና የእርሱ የበታቾች የሆኑ ከእኛ የበለጡ መንፈሳዊ ፍጡራንን ከጎናችን አድርገን ነው።።

‹‹አካባቢው ላይ ይኖሩ የነበሩ ኋላ ቀር ህዝቦችን አስወግደን፣ ምቹና ድንቅ አገር የመፍጠር ስራችንን ቀደም ብለን ጀምረን እጠናክረን በመቀጠል፣ ልዑላችን የጠቆመንን እና ያገኘናትን አገር አሜሪካን የልዑላችን ቤተ መቅደስና መታሰቢያ ብሎም የሉሲፈል መናገሻ አድርገን መመስረት ቻልን።።

በተፈጥሮ የታደለችውን ካናዳንም አጎራብተን በኛ የንጉሰነገስት አስተዳደር ስር ካደረግን በኂላ፣በምንፈልገው የቦታ ስፋት ከልለን ራሷን የቻለች አገር አድርገን በማዘጋጀት፣ አንዲትና የተባበረች ግዛቶችን በውስጧ የያዘች ድንቅ አገር አደረግናት።።

የምንፈልገውን አይነት ፍፁም ዴሞክራሲያዊ የሆነ የአስተዳደር ህግ አርቅቀን ከኛ ወገን ለሆነው ለመጀመሪያው መሪ በመስጠት በሱ እንድትመራ አደረግን።።ሰንደቅ ዓላማዋንም ባሰማራናቸው ቤተሰቦቻችን ዋና ዋና ‹‹የዘር ሃረግ››/ግንድ/ ብዛት በኮከብ መስለን፣እውቀታቸው የላቀ፣ እይታቸው የረቀቀ፣ ከማንም በላይ መብረርና ፈጥኖ በስልጣኔ የመራመድ ብቃት ያላቸው ህዝቦች የሚሰፍሩባት አገር ናትና፣የንስር ዓርማ ጨመርንበት።።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አሜሪካ ራሷን የቻለች አገር ሆናና መስላ ቀጥላ ዛሬ ድረስ በኛ እየተመራች እዚህ ደረጃ ደርሳ ትገኛለች።።

የሳይንቲስቶች፣ የጀግኖችና እንደ ስሟም ሆነች።የባለሃብቶች፣የጥበበኞች፣ የአሸናፊዎች ብሎም የዘመናዊ ህዝቦች መኖሪያ የሆነች ሃያል አገር መሆን ቻለች።ይህ ሊሆን የቻለው በዚያች አገር ላይ ጥበበኛ ዘሮቻችን የእውቀትና የጥበብ ውጤቶቻቸውን እንዲያፈሱባትና ታላቅ አገር እንዲያደርጓት በሚል ስላደረግን ብቻ ነው፡፡

በዚያች አገር ሄደው እንዲሰፍሩ ከኛ ዘንድ የነበሩትንና ከየአህጉሩ የሰበሰብናቸውን ድቅል ድቅል ዘሮቻችንን ወስደን በማስፈርም ቀስ በቀስና በሂደት ዘሮቻቸው ከሆኑ መንፈሳዊ አካላት ጋር እየተገናኙ ለወደፊቱ የልዑላችን ፍላጎት ማስፈፀሚያ የሚሆኑና ዘመኑ እስኪደርስ እየሰለጡኑና እየተላመዱ ህዝቡም እየተገለገለባቸው የሚቆዩ አስፈላጊ ግኝቶችን እየፈጠሩና እየሰሩ፣ እየተመራመሩና እየፈለሰፉ፣ ለዓለም ህዝብ እንዲያበረክቱ ያደረግነው እኛና እኛ ብቻ ነን።

ይቺን አገር ከረጅም ዓመታት ጥናትና ምንጠራ በኋላ ለልዑላችን ምክትል መቀመጫና መናገሻ ትሆነው ዘንድ እጃችን የሌለበት አስመስለን አገር አድርገን ገንብተናታል።አምጠን ወልደን እዚህ ደረጃ ላይ አድርሰናታል።

በጥቅሉ ዩናይትድ ስቴትስ የተባለችው አገር በኛ የተፈጠረችና የተመሰረተች ወይም የተወለደች ናት።ይቺ አገር የኢንግላንድ የሚስጥር ኪስ እንደማለት ናት።ወልደን ያሳደግናት ልጃችንና በኛ የምትመራ አገር ናት።ተጠሪነቷም ለኛና ለልዑላችን ብቻ ነው።ሌላ አዛዥ የላትም።

ይቺን ድንቅና ሃያል አገር ዓለም ትኩረቱን እኛ ላይ እንዳያደርግ ስንል እጃችን የሌለበትና ራሷን የቻለች አገር አስመስለን የመሰረትናትም በምክንያት ነው፡፡

‹‹በልዑላችን ከፍተኛ እገዛ ይቺ አሜሪካ እውን ከሆነች በኋላ ሉሉፈል በተደላደለ ሁኔታ መቀመጫውን ይዞ እኛና እናንተን እንዲሁም ለረጅም ዓመታት አሜሪካን ያስተዳደሩ መሪዎችንና ባለ ሀብቶችን፣ ብሎም ሌሎች የዓለማችን ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ በየዘርፉ ያሉ አባላቶቻችንን ጥበብን እየገለጠ፣እያዘመነ፣ እያሰለጠነ፣አሁን ላይ ያለችበት ደረጃ ላይ ማድረስ ተችሏል...!››በማለት በዘመናዊ ህንፃ ያሸበረቀችውን አሜሪካን በስክሪኑ እየቀያየሩ ማሳየታቸውን ቀጠሉ፡፡

‹‹ልብ ብላችሁ ተመልከቱ!እነዚህ ሁሉ ህንፃዎች ከኛ ወገን በሆኑ የተራቀቀ የግንባታ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎቻችን የተገነቡ ናቸው።እያንዳንዱ ህንፃ ልክ እንደ ኢንግ ላንድ አገር ህንፃዎች

በጣም በተጠና መንገድ የተገነባ ነው።ሁሉም በሚስጥራዊ ቀመሮች ላይ ተመስርተው የተገነቡ ናቸው።የቅርፅና የቦታ ምርጫን አማክሎ፣ሁሉም ህንፃ ለልዑላችን መታሰቢያና ማስታወሻ መሆን እንዲችል ተደርጎ የተገነባ ነው፡፡

‹‹በዚች አገር በእያንዳንዷ ከተማ ከተራው ህዝብ መኖሪያ አፓርታማዎች ውጭ ያሉት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለመስሪያ ቤትነትና ለቢሮነት፤ለዩንቨርስቲና ለምርምር ተቋማት ግልጋሎት ላይ የዋሉ ህንፃዎች በሙሉ!በልዑላችን ጭፍሮች ስያሜና አምሳል ተጠንተው የተገነቡ መቅደሶች ናቸው።የእያንዳንዱ ህንፃ የበላይ ጠባቂ የሆኑ ከትንሽ እስከ ትልቅ መንፈሳዊ አካላትም አሉ።ይቺ አገር የየከተሞችን ስያሜ ጨምሮ ለእነሱና ለልዑላችን ሲባል የተገነባች አገር ናት።

ህንፃዎቹ ከመታሰቢያነት ያለፈ ሚናም አላቸው።አገሪቱ በራሷ ለአዲሲቷ የምድር ምንግስት ምስረታ መሪና አደራጅ መሆን የሚያስችላትን የሃያልነት ፀጋ ተጎናፅፋ፤የዓለምንና የህዝቦቿን እንዲሁም የመሪዎች የበላይ ጠባቂና ተቆጣጣሪ ብሎም አዛዥ ሆና ትገኝ ዘንድ የመጨረሻው መጀመሪያ አድርገን አሳምረን ገንብተናታል።የረቂቅ እውቀት ባለቤት የሆኑ ወገኖቻችንን አስማርተን፣ አሰልጠንና አዘምነን ሃያል አገር ልናደርጋት ችለናል።

‹‹ይቺ አገር በበላይ አካሉ መጽሐፍ ቅዱስ፤‹‹ታላቋ ከተማ›› ተብላ የተገለፀችና፤‹‹ወዮልሽ ትጠፊያለሽና››የተባለችው የሉሲፌል ዋና መቀመጫም ናት።ሆኖም የበላይ አካሉ እንዲያ ስላለ አትጠፋም!ይልቁንም ለዘላለም የምትኖር ታላቅ አገር ናት!ስለዚህ በአገሪቱ ውስጥ እያንዳንዷ ስቴት ስትዋቀርና ስትገነባ የልዑላችን እና የቤታቾቻቸውን መንፈሳዊ ጭፍሮች መነሻ በማድረግ ነው።ለምሳሌ ይቺ ቀጣዩን ጉባኤ የምናደርግባት ኒዮርክ የተባለች አንድ ስቴት የሉሱፌል ዋና መቀመጫ መሆኗንና ትርጉሙም 666 ማለት እንደሆነ ከዚህ በፊት በደንብ ተገልፆላችኋል። ስለዚህ ስለእያንዳንዱ ስቴት ለመተንተን ዝርዝር ነገር ውስጥ መግባት ሳይኖርብኝ ሁሉም ስቴቶችና ህንፃዎችም በተመሳሳይ ቀመርና ትርጉም የተገነቡ መሆናቸውን ጠቅሽ ልለፍ።

‹‹አንድ ነገር ግን አስታውሱ!ይህን ስናደርግና ተግባራዊ ሆኖ ሲቀጥል፣ ሰዎቻችንም በየአገሩ ስናሰፍር፣ በአሜሪካም ሆነ በኢንግላንድ በእኛ ቤተሰብም ሆነ በእኛ ቤተ መንግስት አልፎ አልፎ ስለ ልዑላችን ምንም የማያውቁ መሪዎች ጣልቃ እየገቡ ያስተዳደሩበት ሁኔታ ሞልቷል።ያ ምንም ችግር አልነበረውም።ምክንያቱም ዋናው መጀመሪያ ያረቀቅነው የአስተዳደር ፖሊሲ አይለውጥ እንጂ ማንም ተራ ሰው አገሪቱን ሊመራ ይችላል።ያን ስንፈቅደም ምናልባት እውቀም ይሁን ባለማወቅ አንዳንድ ተፃራሪ ነገሮችን የሚከውን መሪ ሆኖ ካገኘነው በፍጥነትና በሚስጥር ማስወገድ ስለምንችል ነው።

‹‹ልክ በዚሁ መጠንም በእኛ ቤተ መንግስት እድሜና ጊዜያቸው ደርሶ እውነታውን ከመንገራችንና ከማወቃቸው በፊትና በኋላ ወጣ እያሉ

ከተራው ማህበረሰብ ጋር በፍቅር እየተቆራኙ የተጋቡና የተዋለዱ ቤተሰቦቻችን ጥቂት አይደሉም። ሆኖም ጥቂት የነበርነውን ከዚያ የዘር ሃረግ የተገኘውን ሁሉ በተቻለን መጠን ጠብቀንና የልዑላችን ፈቃድ እየፈፀምን እዚህ መድረስ ችለናል።

‹‹በዚህ መሰረት ከአሜሪካ መሪዎች ውስጥ ዘጠና በመቶው የእኛ የዘር ሃረግ ያላቸውና በእኛ የተሾሙ ነበሩ።በእኛ በእንግሊዝ ቤተመንግስት ውስጥም የንጉሰ ነገስትነቱንና የንግስተ ነገስታትነቱን ስልጣን ይዘን ከቆየነው ውስጥ 90 በመቶዎቹ የዚያ የዘር ሃረግ ተወላጆች ወይም ድቅሎች ነን።10 በመቶዎቹ ከተራው ማህበረሰብ ጋር በራሳቸው ፍላጎት የተጋቡና የተዋለዱ መሆናቸው ነው።በአሜሪካም እንዲሁ።

በፖለቲካ ልምምድና በትጋታቸው መሪ የሆኑ በእኛ ይሁንታ ስልጣን የያዙ በርካታ ሰዎች በአሜሪካም በእንግሊዝም ነበሩ።የኛ ወገን ሆኑም አልሆኑም ስልጣን ከያዙ በኋላ ሚስጥር ሊያወጡ የሞከሩትን ግን ለገዛ ልጆቻችን እንኳን ሳንራራ በሌላ መንገድ የሞቱ እያስመሰለን ገድለናል፤አስወግደናል። አስጊ ደረጃ ላይ ከደረሱ ብቻ ነው ይህ አይነቱ እርምጃ የሚወሰድባቸው። ከአሜሪካ ጆን ኦፍ ኬኔዲ ከእኛ ቤተ መንግስት ልዕልት ዲያና ጥሩ ምሳሌ ናቸው።

‹‹ለማንኛውም አሜሪካን በሚመለከት በኔ በሚመራው በዚህ ጉባኤ በዋናነት ማወቅ ያለባችሁ ነጥብ አገሪቱ ሙሉ በሙሉ በእኛ በእንግሊዝ የነገስታት ቤተሰቦች እንደተፈጠረችና በኛ ስር ሆና እንደቆየች፤ ተጠሪነቷም ለኛ መሆኑን ነው።ስለዚህ እናንተ የሃያላን አገራት መሪዎች ለአሜሪካ የመገዛትና በአሜሪካ የመመራት ግዴታ አለባችሁ።በአሜሪካ ተገዛችሁ ማለት በኛ ተመራችሁ ማለት ነው።በኛ ተመራችሁ ማለት ከኛ በላይ ባሉ መንፈሳዊ ፍጡራን ተመራችሁ ማለት ነው።በእነርሱ ተመራችሁ ማለት በሉሲፈል የአገዛዝ ስር ሆናችሁ ማለት ነው።በእርሱ ስር ሆናችሁ ማለት ለዋናው ልዑላችን ተገዛችሁ ማለት ነው።እናንተ በልዑላችን ስር ሆናችሁ ማለት ደግሞ የዓለማችን ሃያል አገራት መሪዎች ናችሁና፤ሃያልነታችሁንና ተፅእኖ ፈጣሪነታችሁን ተጠቅማችሁ፣ የሌላውን ተራ አገር ተራ መሪዎች አሳምናችሁ፣ ወደ ልዑላችን ዓላማ ማምጣት ትችላላችሁ ማለት ነው።እነሱም የሚመሩትን ተራ ህዝብ በእናንተ ትእዛዝና መንገድ መምራት ቻሉ ማለት ነው።ይህ ሆነ ማለት ሁሉም የዓለማችን መሪዎች አገርና ህዝባቸውን ጠቅልለው ወደኛ ዓላማ ከብ ውስጥ አስገቡልን ማለት ነው።

ያ ሆነ ማለት ደግሞ እውቀትንና ጥበብን ለገለጠልንና እዚህ ደረጃ ላደረሰን ለሳጥናኤል መታዘዝ ቻልን ማለት ነው።በእርሱ መታዘዝ ማለት ደግሞ የመጨረሻው ጦርነት ድል ተካፋይ መሆን ማለት ነው።የድሉ ተካፋይ

መሆን ማለት ደግሞ፤የዘላለም ህይወት መኖር መቻልና የምድርን ህይወት ለዘላለም ማስቀጠልና አስቀጥለንም በሹመትና በሽልማት በገደብ አልባ ነፃነት ለዘላለም መኖር ማለት ነው።

ይህን ለማድረግ የመጀመሪያው ስራ አገራቱንና መሪዎችን በአንድ ልዕለ ሃያል አገር ስር ማድረግ መቻል ነው።ያን አድርገናል።ያች ሃያል አገር አሜሪካ ናት።እናም በሷ መታዘዝና በሷ ስር መሆን የሁላችሁም የውዴታ ግዴታ ነው የሚለው ዋናው መልዕክቱ ነው።

‹‹አዎን!ዓለምና ህዝቦቿ ወደዱም ጠሉም በልዑላችን ስር ሆነው መገዛት አለባቸው።ያን ለማድረግ ደግሞ በሁሉም አቅጣጫና በሁሉም ዘርፍ የማጥመጃ መረቡ መዘርጋት አለበት።እኛ እያደረግን የነበረውና አሁንም እያደረግን ያለነውም ያንኑ ነው።

ዓለማዊውን ህዝብ በመሪዎች፣ሐይማኖተኛውን ህዝብ በሐይማኖት ተቋማት በኩል ማጥመድ ተገቢ ነው።ስለዚህ መረባችን በሰባቱም አህጉር መዘርጋት አለበት።ይህ የማጥመጃ መረብ የሚዘረጋውም በኛና በእናንተ አማካኝነት ነው።

‹‹ለምሳሌ መላው የአውሮፓ፣አውስትራሊያ፣የሰሜን አሜሪካና የላቲን አገሮች ሐይማኖተኛ ህዝብ በቫቲካን ቤተክርስቲያን ተፅእኖ ስር ያለና በቫቲካን ቤተክርስቲያን ቋሳት የሚመራ ነው።ያን ህዝብ በቤተክርስቲያን ደረጃ ሙሉ በሙሉ ለማጥመድ የሚያስችለን ደረጃ ላይ ደርሰናል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የመላው አገራት መሪዎችና ህዝቦች ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ ብዙዎቹ በአሜሪካ ሃያልነት ያምኑ፣ በአሜሪካ ተፅእኖ ስር ያሉና በአሜሪካ የሚመሩ ናቸው።እነሱንም በየመንግስታቸው ደረጃ ሙሉ በሙሉ ለማጥመድ የሚያስችል ደረጃ ላይ ደርሰናል።ሆኖም በቂ አይደለም።ስለዚህ ይህን አይነት ተግባር በሰባቱም አህጉር በተጠናከረ መንገድ መተግበር ይኖርበታል።የማጥመጃ መረቡን በሰባቱም አህጉር ለመዘርጋት ደግሞ እናንተ የ G 20 አገራት መሪዎች ለጊዜው በቂ ናችሁ።ይህን የተሰጣችሁን ጥበብ መጠቀም የምትችሉ ናችሁና ዘዴው አይጠፋችሁም።የእያንዳንዱን አገር መንግስታት አሳመናችሁ ማለት የዚያን አገር ሐይማኖታዊ ተቋም አመራርም አሳመናችሁ ማለት ነው።የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣የጦር መሳሪያና የሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶች ባለቤት ሆናችሁና፤ ተፅዕኖ ፈጣሪነታችሁ ታምኖ ነውና የ G 20 አገራት አባል የሆናችሁት ሁሉንም ነገር ከማድረግ የሚገታችሁ ሃይል አይኖርም።

ስለዚህ መላውን የአውሮፓ ህዝብ በኛና በቫቲካን ቤተክርስቲያን በኩል እንዳዘጋጀነው ሁሉ ሌላውም አህጉር በተመሳሳይ መንገድና ስልት በእናንተ አማካኝነት የሚዘጋጅና የሚጠቀለል ነው።

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

በመካከለኛው ምስራቅ አህጉር ያሉትን የየአገራቱን መሪዎችና ህዝቦቻቸውን፤እንዲሁም የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮችን የ G 20 አገራት አባላችን በሆነችው በሳዑዲ አረቢያ በኩል፣በእስያ አህጉር ያሉ የሩቅ ምስራቅ አገራት መሪዎችንና የቡዲዝም የሂንዱዚም ሐይማኖት ተከታይ የሆኑ ህዝቦችን እዚህ ባላችሁት ህንድ፣ቻይና፣ደቡብ ኮሪያ፣ጃፓን፣ ኢንዱኑዥያ፣ እማካኝነት፣በደቡብ አሜሪካ አህጉር ያሉትን የየአገራቱን መሪዎችና ህዝቦቻቸውን፤እዚህ ባላችሁት የ G 20 አገራት አባሎቻችን በአርጀንቲናና በብራዚል በኩል፤በሰሜን አሜሪካ አህጉር ያሉትን የየአገራቱን ህዝቦች እዚህ ባሉት የ G 20 አገራት አባሎቻችን በአሜሪካ፣ በካናዳና በሜክሲኮ በኩል፣በአፍሪካ አህጉር ያሉትን የየአገራቱን መሪዎችና ህዝቦች በአባል አገሯ በደቡብ አፍሪካ በኩል፣እየተባለ የሁሉንም አገር መሪዎችና ህዝቦች በሁሉም ዘርፍ ማጥመድ የሚያስችለው መረብ በእናንተ እማካኝነት የሚዘረጋ ነው።

መቼ እና እንዴት በምን መልኩ የሚለው እኔ ባልተገኘሁበት በዚሁ ጉባኤ የተነገራችሁ እንዳለ ሆኖ፤አገራቱንና ህዝቦችን በሚመለከት ጥያቄ ሲኖራችሁ፤ሐይማኖታዊ ጥያቄዎችን ለጳጳሳችሁ፣ዓለማዊና አስተዳደራዊ ጥያቄዎችን ለአዛዣችሁ ለአሜሪካ የምታቀርቡ ይሆናል።ማናችሁም መሪዎችና በእናንተም የሚተኩ ቀጣይ መሪዎች በቀጥታ ተጠሪነታችሁ ለአሜሪካና ለቫቲካን ቤተክርስቲያን፤በውስጠ ታዋቂነት ለኛ መሆኑን በደንብ የተረዳችሁ ይመስለኛል።ከዚህ በኋላ ውህደት ፈጥረን ለአንድ ዓላማ የቆምን ነንና ማንም ከማንም ሳይበላለጥ የሚወርድለትን ትዕዛዝ ከመፈፀም ውጪ የራሱን አካሄድ መሄድ አይችልም።ሚስጥራዊነቱ ተጠብቆ ሂደቱ በዚህ ሲቀጥልም፤በዓለም የዜና አውታሮች የሚሰራጨው ዜናም ይሁን ሌላ ትንታኔ፤ እንዲሁም የመሪዎች ተግባር እንደተለመደው በሽፋን ታሪክ እየተቀናበረ፤ በተናጠል በየአገራቱና በየመሪዎቹ የግል ፍላጎት ታቅዶ የተከናወነ ሆኖና መስሎ መቅረቡ ይቀጥላል።

ይህን ስል በተለመደው የየአገራቱ ሰውኛ ተግባርም ሆነ የየአገራቱ መሪዎች ተራ ክንውንና የውስጥ አስተዳደርን በሚመለከት ማለቴ አይደለም።እያልኩ ያለሁት የልዑላችን ዓላማ ለማሳካት በሚደረገው እንቅስቃሴና ሚስጥራዊ ሂደት ብቻ ነው።በሌላ አገላለፅ የኛና የልዑላችን ጎል የሆነችውን አገር በማጥመድ ረገድ ነው።

እኛና ልዑላችን በጋራ ማጥመድ ያለብንን አንድ የተከለለን ውስን ቦታ ለማጥመድም የግድ ሙሉ አገሪቱን ማጥመድ ያስፈልጋል። አንድነታችንም፣ ህብረታችንም፣ ውህደታችንም፣ ለዚህ ነው! በዚህ ዙሪያ ለሚሰራው ስራ ነው ትእዛዙን ከአሜሪካ መቀበል የሚኖርባችሁ።

በሌላ ሰውኛ የአስተዳደር ጉዳይም ሆነ በየአገራቱ ባህል፣ልማድ፣የአኗኗር ዘይቤ፣ወዘተ...ጣልቃ አንገባም።ይህን ስራ ደግሞ አቅልለን ነው የጠበቅናችሁ።ቅድመ ስራውን ሁሉ ለዘመናት ያለ እናንተ እገዛ ሰርተን ስለጨረስንም ነው የልዑላችን ድል አድራጊነት ከወዲሁ በልበ ሙሉነት መግለፅና ማረጋገጥ የቻልነው።

ይቺን ኢትዮጵያ የተባለች አገር አቅልሎ የማየት ነገር የተጠናወታችሁ መሪዎች ግን ተጠንቀቁ!ላልጠፋ ቦታና አገር ልዑላችን ለዚች አገር የተለየ ትኩረት የሰጠበት ለምን እንደሆነ ተገልፆላችኋል።ያን ካወቃችሁ የግድ ንቀታችሁንና አቅልሎ የማየት አባዜያችሁን በዚች ቅፅበት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መተው አለባችሁ!ግልፅ ነው?››

‹‹ግልፅ ነው!››የጋራ ድምፅ...

‹‹ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!›

‹‹በዚህ መሰረት ለረጅም ምዕተ ዓመታት የምድርንና የህዝቦቿን እጣ ፋንታ ስንወስን የኖርነውና አሁንም እየወሰንን ያለነው እኛ ነን።ስለዚህ ዓለምና ህዝቦቿ ያለ እነሱ እውቀትና ያለ እነሱ ይሁንታ በእኛ ሲመሩ ኖረዋል ማለት ነው።አሁንም በእኛ መመሪታቸው ይቀጥላል።ይህ ከሆነ ደግሞ እናንተ የ G 20 አገራት መሪዎችም ከአሁን ጀምሮ ልታውቁን ልትተዋወቁን ይገባል ማለት ነው።ይህ ለጊዜው በእናንተ ዘንድ ብቻ ከታወቀ በቂ ነው።

‹‹አያችሁ?አንድ የኛ ወገን የሆነ ፀሀፊ፤‹‹ዓለም መታለልን ይፈልጋል፣ ስለዚህ አታል!››የሚል አባባል አለው።ዓለምንና ህዝቦቿን እንዲህ አድርገን ስናታልል ነው የቆየነው።ለምን?ለአንድ ለልዑላችን ዓላማ ስንል ብቻ!ሁላችንም ለአንድ ዓላማ የቆምን ነን።የልዑላችንን የንግስና መንገድ ለመጥረግና በመጨረሻው ጦርነት ለድል ለማብቃት!ለድል አብቅተንም ከልዑልነት ወደ ንጉሰነገስትነት ማሸጋገር!ከዚያም ዘላለማዊ ህይወት የሚያስቀጥለውን በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የሚገኘውን የህይወት ዛፍ ቦታ በቁጥጥር ስር ማዋልና ከመኖር ወዳለመኖር ሲሄድ የተዘጋጀውን ሰውንና የምድር ህይወት ከመኖር ወደመኖር መግታት!ከዚያም የልዑላችን ታዛዥና ተከታይ ለሆኑት ለዓለም ህዝቦች ዘላለማዊ ህይወትን አጎናፅፎ በገደብ አልባ ነፃነት ለዘላለም መኖር መቻል!ለዚህ ሲባል ነው ማታለሉ ያስፈገው!››በማለት፤‹‹የእንጦጦ መምህር ሲናገር ባመት እሱም እሬት!››በሚባል አኳኋን እንዲህ ሰፊ ንግግርና ገለፃ ሲያደርጉ ታይተው የማያውቁት ንግስት በኩራት እየተንጎራደዱ እንዴት ሲያታልሉ እንደኖሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ አደርገው የተሰብሳቢዎቹን የአድናቆት ጭብጨባ ተሸለሙ።

ቀጠሉ።‹‹ነገር ግን ልብ በሉ!ይህንን ስናደርግና ‹‹ነገር ግን ልብ በሉ!››ሲሉ ቀጠሉ።‹‹ነገር ግን ልብ በሉ!ይህንን ስናደርግና ዓለምን ስንመራ እንዲሁ ያለ እውቀት አይደለም።
ከጀርባ ሆነን ዓለምን ከነህዝቦቿ ስንመራ እንዲሁ ያለ እውቀት አይደለም። ከፒራሚዳችን ይዘነው በወጣነው በረቀቀ በውል ተረቆ በተሰጠንና ከፒራሚዳችን ይዘነው በወጣነው በረቀቀ ጥበብ እንጂ፤ እንዲሁ እውቀትና የእውቀት መርህ፤ብሎም በረቀቀ ጥበብ እንጂ፤ እንዲሁ እውቀትና የእውቀት መርህ፤ብሎም በረቀቀ ጥበብ እንጂ፤ እንዲሁ እውቀትና የእውቀት መርህ፤ብሎም በረቀቀ ጥበብ እንጂ፤ እንዲሁ
እውቀትና የእውቀት መርህ፤ብሎም በረቀቀ ጥበብ እንጂ፤ እንዲሁ በዘፈቀደና በኛ ፍላጎትና አካሄድ ብቻ ተመስርተን አይደለም!
‹‹እያንዳንዷ የምድር እውቀትና ጥበብ፤የምርምርና የቴክኖለጂ ውጤት፤ አጀማመሩና አመጣጡ ከልዑላችን ጥልቅ የጥበብና የእውቀት ማዕድ ብቻ መገኘቱንና፤ሄዶ ሄዶም መጨረሻው ለልዑላችን ግልጋሎት ብቻ የሚውል መሆኑን በደንብ ላስገነዝባችሁ እፈልጋለሁ።ይህን በደንብ መገንዘብ የሚኖርብንና የሚኖርባችሁም የምድር ህዝብ ለልዑላችን ካልታዘዘና ከሱ ጎን እስካልተሰለፈ ድረስ የበላይ አካሉን የሙጥኝ ብሎ ያገኘውም፤ወደፊት የሚያገኘውም አንዳች ነገር እንደማይኖር በጥልቅ ተረድታችሁ ታስረዱ ዘንድ፤ትዕዛዛቱን ትፈፅሙና ታስፈፅሙ ዘንድ ነው።በምትመሩት ህዝብ ላይ የሱን ዓላማ እንድታራምዱ ነው።የቤት ስራችሁም የልዑላችን የጥበብ ውጤት የሆኑ ግኝቶችን፤ከልዑላችን የተገኙ ንብረቶችን፤ ረቂቅ የቴክኖለጂ አሰራሮችን በየአገሩና በየህዝቡ በሰውኛ መንገድ እያለማመዳችሁ ማስረፅን ያካትታል።
‹‹ተመልከቱ!እኛ ይህንን ሁሉ ስናደርግና ዓለምን ስንመራ እንዲሁ በደመ ነብስ አይደለም! በኛ ፍላጎትና ዕቅድም አይደለም!እንዲሁ እጅና እግራችን ይዘንም አይደለም ወደ እናንተ የመጣነው።ስንመጣ ይህንን የእውቀት ቀመር ይዘን ነው!››አሉና፤ስክሪኑን በቅፅበት አጥፍተው ገፋ አድርገው ከሸኙት በኋላ፤ስፍፍፍፍ እያለ የመጣ፤በአራቱም አቅጣጫ እኩል የሆነና፤ እድሜ ጠገብ መሆኑ የሚያስታውቅ እጅግ ግዙፍ ጥራዝ አሳዩዋቸው። በዚህ ጊዜ ተሰብሳቢዎች በአድናቆት አፏጩ።ግዙፉ መጽሀፍ ገልበጥ፤ ገልበጥ፤ ገለጥ ገለጥ፤ እያለ ለተሰብሳቢዎች ታዬ።
‹‹ይህ እጅግ ግዙፍና በዓለማችን ታይቶ የማይታወቅ መጽሐፍ ነው። እንደምታዩት ቁመቱም፤ስፋቱም፤ወርዱም፤ እኩል ስድስት ሜትር ነው። የገፅ ብዛቱ ደግሞ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ሺ ነው!ይህንን ነው በዘመናችን ይዘን የመጣነው!ይህንን የትምህርት ስርዓትና ይህንን የእውቀት ቀመር የታጨቀበትን ማህደር ይዘን መጥተን ነው የዓለማችን ህዝብ ማስተማር የቻልነው!ይህንን ከልዑላችን የተሰጠንን ቀመር ነው በዚች ምድር ላይ ወደ ተግባር ለውጠን አሁን ካለንበት ደረጃ የደረስነው!በዚህ ነው ዓለማችን መለወጥ የቻልነው!››እያሉ በጩኸት እየተናገሩ ግዙፉን ጥራዝ ሲያሳዩዋቸው ቆዩና፤ጩኸታቸውን ቀነስ አድርገው ቀጠሉ።
‹‹የዚህን ሚስጥር በሰፊው አብራራላችኋለሁ።የዚህን ሚስጥር የማብራራው የልዑላችን ታማኝ የበታች ለሆነው ተገቢውን መስዋዕት በጋራ

በምናቀርብበት በኒዮርክ አዳራሽ ይሆናል።በዛሬው እለት ይህን ውስጥና ውጭ የማብራት ጥበብ ወደተለገሳችሁበት ወደ ኒዮርክ እናቀናለን።ዝግ ጉባኤውንም እዚያው የምንቀጥለው ይሆናል።ክቡራን፤በዛሬዋ ዕለት ማድረግ የሚጠበቅባችሁን የጋራ መስዋዕት ለማቅረብ ዝግጁ ናችሁ?››
‹‹ዝግጁ ነን ንግስት ሆይ!››የጋራ ድምፅ።
‹‹ክብር ለታላቁ ልዑላችን!››
‹‹አሜን!››
‹‹መልካም፤አሁኑኑ ወደ ኒዮርክ እናቀናለን››አሉና ግዙፉን ጥራዝ ገፋ ሲያደርጉት ወደ ላይ እየተንሳፈፈ ሄዶ ከእይታ ውጪ ሆነ።የአውስትራሊያ ሜልቦርን ዝግ ጉባኤ ለጊዜው መቋረጡንና ኒዮርክ ላይ እንደሚቀጥል በንግስቲቱ ከተገለፀ በኋላ፤ጥቁሩ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ያችን የዝግ ስብሰባዎችን ብቻ የምትቀርፅና ቃለ ጉባኤም የምትይዘውን ብርማዋን የአፕል ማርክ ያላት ላፕቶፕ እንዲይዝ በንግስቲቱ ታዘዘና በሩጫ ቀረሽ እርምጃ ወደ መድረኩ አመራ።
ንግስቲቱ፤‹‹መሄድ እንችላለን››አሉና፤መድረኩን ለቀው ከአዳራሹ ለመውጣት ተዘጋጁ።የቫቲካኑ ጳጳስም ተነስተው ተከተሏቸው።የ G 20 አገራት መሪዎችም በፈገግታ ደምቀው ለመውጣት ሲዘጋጁ ታዩ።ከዚያም ጥቁሩ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት መድረኩ ላይ ካለው ንግግር ማድረጊያ ቦታ ላይ ሆና በረቂቅ ካሜራዋ ሙሉ አዳራሹን እየተሽከረከረች የምትቀርፀውን ብርማዋን የአፕል ማርክ ያላት ላፕቶፕ እጥፍ ሲያደርጋት ጭል.....ም አለ።ከዚያ በኋላ በምን በርረው እንደሄዱ እነሱ ብቻ ነው የሚያውቁት.......።ሆኖም በዚያው እለት ከውስን ሰዓታት በኋላ በአሜሪካ ኒዮርክ ከተማ ተገኝተው በተመሳሳይ አዳራሽ ጉባኤውን ካቆሙበት ሲቀጥሉ ለማየት ተቻለ።

አዲስ አበባ ሚያዚያ ወር 2007 ዓ.ም

ዳንኤል ቶማስ ወደ በሰበሰችው አሜሪካ ተመልሶ ሄዶ የኋይት ሃውስ ስራውን ጀምሮ መልቀቂያ ከማስገባቱ በፊት፤ከረፍት ጊዜው የተረፈች ቀሪ አንድ ወር ነበረችው።በዚያች አንድ ወርም፤13 ዓመት የኖረባትን ነገር ግን በቅጡ ዘና ያላለባትን ዋሽንግተን ዲሲን፤ የሉሲፈል ዋና መቀመጫ መሆኗን እያወቀም ቢሆን በነፃነት እየተዝናና ሲምነሸነሽባት ቆይቷል። በእነዚያ ጊዜያቶችም ከዳዊትና ከፍፁም ጋር በየእለቱ ይደዋወሉ ነበር። የረፍት ጊዜውን ጨርሶ ስራውን ከጀመረ በኋላ፤ መልቀቂያውን አስገብቶ ስራውንም ቀጥሎ ውጤቱን መጠባበቅ ጀመረ።

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

በየዕለቱ እነዚያ የሩሲያ ሰላዮች ድጋሚ መጥተው አንዳች ነገር የሚሉት እየመሰለው በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ሆኖ እየተርበተበተ ነበር ስራውን የቀጠለው።ለሶስት ወራት ያህል ምንም ሳይገጥመው ቆዬ።ከሶስት ወራት በኋላ ስራውን ለመልቀቅ ያሰበበት ምክንያትና ያቀረባቸው ማስረጃዎች ታይተው አሳማኝ ሆነው ስለተገኙ ስራውን በሰላም መልቀቅ ቻለ። ሌላ የተለዩ ችግር ሳይገጥመው የኒይት ሃውስ ስራውን በሰላም መልቀቁንም ለዳዊትና ለፍፁም በስልክ ገልፆ አረጋግጧቸዋል።

ከዚያ በኋላ በእቅዱ መሰረት ሌሎች ጉዳዮቹን ወደመፈፀም አመራ።በዚህ ምክንያት ጊዜ እያጠረው ስለሄደ ከእነ ዳዊት ጋር ለረጅም ጊዜ ሳይደዋወሉ ነበር የቆዩት።

በቆይታውም በዚያች አገር የነበረውን ገንዘብ ከየባንኮቹ ቀስ በቀስ እያወጣ ቤቱ ውስጥ ይደብቅ ነበር።ትኩረት ሳለመሳብ እየተጠነቀቀ ይህን ሲያደርግም፤ ምን ያለበት ምን አይችልም እንዲሉ፤በፍርሃት እጅግ ተሳቆ ነበር በየባንኩ የሚሄደው።በየሄደበት ቦታ የሆነ ሰው ድንገት አተኩሮ ካየውና ዓይን ለዓይን ከተገጣጠመ ክው ብሎ ይደነግጣል።ሁሉም ሰው እሱን እየተከተለ ያለ ይመስለዋል።

እርግጥ ነው ትልቁን የቤት ስራ ሰርቶ ጨርሷል።ያንን የማይታመን ታሪክ የመስራት እድል አግኝቶ ድንቅ ጀብዱ ፈፅሟል።ያን የመሰለ መረጃ ወደ አገሩ ይዞ መግባት ችሎ፤ የሚያግዘው ሰውና ወገን አግኝቶ መረጃው ለወገኑ የሚደርስበትን ሁኔታ አመቻችቷል።አሁን የቀረው ተራና ቢቀርም ሊጎዳ የማይችለው የገንዘብ ጉዳይ ነው።ሊተወውም ይችላል።ግን ለምን ይተወዋል?ከታዳጊነቱ ጀምሮ በከፍተኛ ክፍያ ተቀጥሮ በሰው አገር ሲሰራ ያገኘውና ያጠራቀመው የላቡ ውጤት ነው።ይህን የዘመናት ውጤቱን እንዲሁ ትቶ ኢትዮጵያ መቅረት እንዴት ይቻለዋል?

‹‹በዚያች ተዓምረኛ ዕለት ጀምሮ ለእኔ ትልቁ ጉዳይ የነበረው አንድም የማውቀው ሰው ባልነበረባት አገሬ ያን መረጃ ወደ ኢትዮጵያ ወስጀ ለወገኔ ማድረስ ነበር፤ አድርሻለሁ።ስለዚህ ከዚህ በኋላ ለእኔ ሕይወትም ሆነ ሌላው ነገር በሙሉ ትርፍ ነገር ነው፡ታዲያ ምን ያስጨንቀኛል?››ይላል ለራሱ።‹‹ክፉ.ለጉ ለምን አሁኑኑ አንጠልጥለው ወስደው አያስሩኝም!ለምን እንዳሻቸው ገርፈው አይገድሉኝም!ከዚህ ወዲያ ምን ዓለም አለኝ?››ይልና፤ እንደ መበርታት ብሎ ቆይቶ፤ ድንገት የሆነ ሰው እንዲሁ ወደ እሱ ክተመለከተ፤እጠቁሙኝ የሚል መልዕክት ያለው ገፅታ እያሳየ ድንግጥ ብሎ ያቀረቅራል።በገጠመኝ የሰዎች እይታ ብቻም ሳይሆን፤በትንሽ ኮሽታና በትንሽ ድምፅ በየደቂቃው ክው እያለ መደንገጥ የጀመረው ስራውን ከጀመረበት ዕለት አንስቶ ነው።

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ለዳዊትና ለፍፁምም ቶሎ እንደሚመለስ እንጂ ይህን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ አልነገራቸውም ነበር።እሱም አንዳንድ ጥቃቅን ጉዳዮችን ለመፈፀምና ለመመለስ ይህን ያህል ጊዜ ይወስዳል ብሎ አላሰበም።ሆኖም ትልቁና ጊዜ ወሳጅ ይሆናል ብሎ ያሰበው ጉዳይ በቶሎ ማለቅ ችሎ፣ ጥቃቅን የተባሉ ጉዳዮች ስፊ ጊዜ ሊወስዱበት ቻሉ።

ትልቁ ጉዳይ የነበረው የፈፀመው አስደንጋጭ ተግባር ሳይነቃበት በስልታዊ መንገድ መልቀቂያውን አስገብቶ የጊይት ሃውስ ስራውን በሰላም መልቀቅ መቻል ነበር።እሱን በቀላሉና በአጭር ጊዜ መፈፀም ችሏል።ለዚህም የአእምሮ ጭንቀት እንደደረሰበት የሚያረጋግጠው የህክምና ሰነድ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጎለታል።ያን ከጨረሰ በኋላ ግን ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ጊዜ ወሰዱበትና ካሰበው ጊዜ በላይ በአሜሪካ ሊቆይ ተገደደ።

በዚህም ላይ በየሄደበት ቢሮ እየደነገጠ እየተወ የሚወጣበት ጊዜ ሲጨመርና መረጋጋት እየተሳነው ነገ ዛሬ ሲል ሌሎች ተጨማሪ ወራቶችን በዚያች ቆሻሻ አገር አባከነ።

የፍፁምና የዳዊት ናፍቆት እየበረታበት ሴሄድ ግን እንደምንም ጠንክሮ ጉዳዮቹን በፍጥነት መጨራረስ ጀመረ።

ኢትዮጵያ ሲሄድና ኑሮውን እዚያ ሲያደርግ ሊጠቅሙት የሚችሉ ማስረጃዎችን፣ አገሩ ላይ ሊሰማራበት ባሰበው የስራ ዘርፍ ሊያስፈልጉ የሚችሉ ሰነዶችን እየሰበሰበና ዶክመንቶቹን እያደሰ፣ ገንዘቡን እያሸገ ቆየ። ለምናልባቱ ብሎ ጥቂት ገንዘብ በአንዱ አካውንቱ ትቶ ከአፓርታማው ውስጥ ያሉትን እቃዎች በሙሉ ሻሽጦ የጉዞ ሻንጣውን ካሰናዳና ዶላሮቹን እንደ መጀመሪያው አወሳስዱ በየልብሳ ልብሱ ሸንጉጦ ከተዘጋጀ በኋላ፣ ሊነሳ መሆኑን ለማብሰር የመጨረሻውን ስልክ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ደወለ።መጀመሪያ የደወለው ለዳዊት ነበር።

‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን ዴቭ››

‹‹ሰላም ለሁላችን ዳኒዬ እንዴት ነህ?››

‹‹በጣም ደህና ነኝ ዴቭ፣እንዱን እንዱን ስል በጣም ቢዚ ሆንኩና ሳልደውል ቆየሁ››

‹‹ገብቶናል፣እኛም ላለመረበሽ ስንል ነው ዝም ያልነው።በዚያ ላይ መደዋወሉ…››

‹‹ልክ ነህ››

‹‹ለማንኛውም በጣም ናፍቃችሁኛል።እናም ዛሬ ሌሊት ልነሳ ነው።ነገ ቀን ምሳ ሰዓት ላይ እገባለሁ ዴቭ››

‹‹በጣም ጥሩ በሰላም ግባ።በኛ በኩል ሁሉ ሙሉ ሁሉ ዝግጁ ዳኒዬ››

‹‹እመሰግናለሁ ዴቭ፣ሰላም ያገናኘን››

‹‹አሜን።ለፍፁም ደወልክለት?››

‹‹አልደወልኩም፤ አሁን ልደውልለት ነው››
‹‹አልደወልኩም፤ አሁን ልደውልለት ነው››
‹‹በል ደውልለትና የምትገባበትን ሰዓት ንገረው፡፡የሚገባበትን ቀንና ሰዓት ሳላውቅ ጉድ እንዳልሆን፤አደራ ሲል ነበር››
‹‹እንዴት?››
‹‹ምን እንዴት አለው፤ዘመናዊ የቤት አውቶሞቢል የያዘ ይመስል ቀደም ብዬ ላሺያጆ አስገብቸ፣ ፑልሽ አስደርጌ፣ ፏ ብዬ ዳኒን እንድቀበለው ቀድሜ ማወቅ አለብኝ ማለት የጀመረው፤አዲሱ ሚኒባስ ከተገዛለት ዕለት ጀምሮ ነው፡፡ስራ ላይ ሆኖ ድንገት መጣህ ቢባል የመኪናውን አቧራ ሳያፀዳ ወደ ኤርፖርት ላለመምጣት ነው ቀድሞ ማወቅ የፈለገው››ሞቅ ያለ የሳቅ ልውውጥ አድርገው ከተሰነባበቱ በኋላ፤ዳንኤል ወደ ፍፁም ደወለ፡፡‹‹ሰላም ፍፄ››
‹‹ሰላም፤ማን ልበል?››
‹‹አላወቅኸኝም?
‹‹እን....ዴ... ዳኒዬ.... ገባህ እንዴ ሸገር?››
‹‹አረ ገና ነኝ››
‹‹እና ለምንድን ነው የኢትዮጵያ ቁጥር....እን....ዴ!››
‹‹አንዳንዴ እንደዚያ ይፅፋል መሰለኝ ፍፄ፤ግን ደህና ነህ?››
‹‹እኔማ ደህና ነኝ፤ግን እኔን ስራ ላለማስፈታት ከመጣህ በኋላ ደውለህ እንዳይሆንና ጉድ አድርገህኝ እንዳይሆን!ከዚህ በፊት ስትደውል ኖ ነምበር አይደል እንዴ የሚለው?ኧረ ዳኒ እውነቱን ንገረኝ፤ዳር ይዠ ነው የማዋራህ››ሲለው፤ዳንኤል የበሰጠ ናፍቆቱ አገረሸበት፤‹‹ላንተ ሳልነግር ከምመጣ ብቀር አይሻለኝም ፍፄ?ባንተ ሚኒባስ ካልሆነ በሌላ መኪና እንዴት ብዬ ፍፄ?ይሄማ አይደረግም፡፡ነገ ምሳ ሰዓት ነው የምገባው፡፡አሁን እዚህ ምሽት ነው፤እና በሌሊቱ በረራ ነው የምነሳው››ሲለው፤ፍፁም ተረጋጋና፤‹‹ጎ.......ሽ እሱ ጥሩ!መኪናየን ፏፏ አድርጌ ባልከኝ ሰዓት ከዱብ ጋ ኤርፖርት ገጭ ዳኒዬ!ኪድዬ ትከተልህ በሰላም ናልን ወንድሜ!››
‹‹አሜን ፍፄ፤ ቻው››
በዚህ እለት ፍፁም ያስወትሮው ምሽት 12 ሰዓት ላይ ሚኒባሱን አቁሞ ወደ ቤት መጣ፡፡ቤት ሲገባ ዳዊት ጆሮው ላይ ማዳመጫ ሰክቶ፣ ኮምፒይተሩ ላይ አፍጥጦ፣ የሚያየውን ቪዲዮ እያቆመ እያስቀጠለ፣አጠገቡ ካለው ጠረጴዛ ላይ ባሉ ወረቀቶች እየሞነጫጨረ አገኘው፡፡
‹‹ምነው ፍዴ በጊዜ?››አለው፤ ፈገግ ብሎ፡፡ለምን በጊዜ እንደመጣ ግን ገብቶታል፡፡
‹‹አዎ ዴቭዬ ቀን ነግሬህ የለ፤ዳኒ ሊመጣ ነው ስለዚህ በጊዜ ነው የምመጣው አላልኩህም?››

‹‹በጊዜ ስትለኝ እስከ 4 ማምሽትህ ቀርቶ አንድ ሰዓት ሁለት ሰዓት ነበር ያሰብኩት››

‹‹እንዴ.... ዴብ ምን ነካህ?ዳኒ እኮ ነው!እንዳውም ቦሌ ሄጀ እዚያው ስጠብቀው አድሬ፣ ስጠብቀው ውየ፣ ይዘው መምጣት ነው የነበረብኝ፡፡ አንተንም ማስቸገር ይሆናል ብዬ ነው እንጂ....እንደዚያ ነበር ያሰብኩት፡፡ ስለዚህ በጊዜ ተኝቸ በጠዋት እነሳና መኪናየን ሳቪያጆ አስገብቸ፣ ወርቅ አስመስዬ አሳጥቤ፣ ውስጡን በነፋስ ውጩን በአም ዕድት አስደርጌ፣ የዳሽ ቦርድ ክሬም ነሸ፣ኤር ፍሬሽ ነሸ፣ ምንድነሽ አንድ ሳይቀረኝ ፏ! አድርጌ እኛም ፏ! ብለን ነው የምንሄደው፡፡አቤ.....ት እንዴት እንደተከየፍኩ ዴብዬ!ሲደውልልኝ ስልኩ ያገር ውስጥ ቁጥር ዕፎልኝ በንዴት አልጨስ መሰለህ?››

‹‹እንዴት?››

‹‹እንዴ... ስራ እንዳልፈታ ብላችሁ ሁለታችሁ ተመካክራችሁ በሌላ መኪና መጥቶ ከገባ በኋላ የደወለልን መስሎኝ ነዋ!በጣም ደንፉ ይዞኝ ዳር ይገዞ ተሳፋሪዎችን ሸኛቸው ብዬ ካሸኘሁ በኋላ፣ እውነቱን ሲነግረኝ ነው የተረጋጋሁት››

‹‹እንዴት እንደዚያ እናደርጋለን?ህልምህን እያወቅነው?በጣም ናፍቆሃል ማለት ነው››

‹‹እን....ዴ ዴብ ምን ነካህ? በጣም እንጂ!ሚገርመው ከኔ በላይ አንተ ናፍቃሃል››አለው በእርግጠኝነት፡፡

‹‹አዎ አልደብቅህም ፍዬ በጣም ነው የናፈቀኝ!››አለው፤ከልቡ መሆኑን በዓይኖቹም ጭምር እያረጋገጠ፡፡

‹‹አዎ ዳኒ ይናፍቃል!ኪዳነ ምረትን በጣም ይናፍቃል!ዳኒ የሰው ማኛ! ኪድዬ የባረከችው.!በለ....ው!እኔኮ በቃ ምን ብዬ ልንገርህ ዴብ?በቃ ማመን ያቅተኛል እሽ! ኪዳነምረትን!››ፍፁም እንደማልቀስ ቃጣውና ዓይኖቹ በቅፅበት እንባ አቀረሩ፡፡

‹‹ይገባኛል ፍዬ ግን.....ደስታህንም ሆነ ሃዘንህን በእንባ መግለፅ ጥሩ ምናልባትም አስፈላጊና ግዴታ መሆኑን ባምንም እንኳ፤ ዳኒን በሚመለከት ግን ሊረብሸው ስለሚችል ፍዬ...በተቻለህ መጠን......››

‹‹ይገባኛል ዴብ ግን...በቃ...በጣም...በቃ...ያሳዝነኛል፡፡የዋህነቱ፣ ወንድምነቱ፣ለራሱ ሳያስብ ለአገሩ፣ለማያውቀው ወገኑ፣በተለይ ለኔ!እሽ ምን ብዬ ልግለፀው?እንዴት አባቴ አድርጌ ልውደደው?››

‹‹ልክ ነህ ፍዬ መወደድ ያንሰዋል፡፡ቢሆንም ግን በእንባ ሳይሆን በቃላት፣ በሳቅ፣በጫወታ፣እሉ አይደል....››እያለ በማስረዳት ላይ ሳለ፤ፍፁም እንባውን ለመገደብ ሞክሮ ሙከራው ስለከሸፈበትና ስላልቻለ፤በጉንጮቹ ግራና ቀኝ ኮለ....ል እያሉ መፍሰስ ጀመሩ፡፡ይህንንም ከዳዊት መደበቅ ባለመቻሉ፣

‹‹እሺ... ግን....እንዴ ብቻ ላልቅስና...በቃ...››ብሎ አስፈቀደና፤ስቅ ስቅ እያለ ዝቅ ባለ ድምፅ ሲያለቅስ ቆዩና፤‹‹በቃ ከዚህ በኋላ አላለቅስም፤ አልረብሸውም ዱቭ››ሲል፤ በከፊል ቃል እየገባ እንባዎቹን ጠራረገ።

‹‹ፍዬ ስሜትህ ይገባኛል፤እጋራዋለሁም።ነገር ግን እሱ እኛን ማፅናናትና አይዟችሁ ሳይሆን ማለት ያለበት፤ እኛ ነን እሱን አይዞህ ልንለው የሚገባን።ዳንኤል ማለት ኢትዮጵያዊ ሆኖ፤ ነገር ግን ከ መቶ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ከእኔና ካንተ ሌላ የሚያውቀውም የሚተዋወቀውም ሰውና ወገን የሌለው ብቸኛ ሰው ነው።ይህ ብቻውን በከፍተኛ ደረጃ ስሜቱን ይጎዳዋል።በእርግጥ ሁላችንም ያው ነን።ቢሆንም አንተ በዙሪያህ ብዙ ሰዎች አሉ፤እኔም እንደዚያው።እንዳቸውም ላይጠቅሙን ቢችሉ እንኳ፤ እንዲሁ በመኖራቸው ብቻ በሰው የተከበብን፤ ወገን ያለን፤ ለመሆኑ ማስረጃ መሆን የሚችሉ ናቸው።የእሱ ግን ከዚህ የተለየ ነው።አንተ ወላጆች ባይኖሩህም፤ እንደነበሩህና በማይቀረው ሞት እንደተወሰዱብህ ታውቃለህ።ምናልባት ባታውቅ እንኳ የቀብራቸውን ቦታ፤ የት ሰፈር ይኖሩ እንደነበር፤ስማቸው ማን እንደነበር፤ ወዘተ..ታውቃለህ፤ አውቃለሁ።ዳኒ ግን ይህንን እንኳ የማያውቅ ከፈጣሪ ውጪ ማንም የሌለው ብቸኛ ሰው ነው።እኛን የሚያጓጓን ነገር እሱን አያጓጓውም።አንተ በሰጠህ ፍቅርና በገዛልህ ቤት በገዛልህ ሚኒባስ ምክንያት ብታመሰግነውና ደግነቱን ደጋግመህ ብትነግረው፤ያ ለሱ ምንም ማለት ነው!እሱ ሳይኖረው ቀርቶ አንተ ገዝተህ ብትሰጠው እንኳ ያ ለሱ ምንም ነው!እንዲህ አይነቱ ነገር ላንተ ለእኔና ለመሰሎቻችን የዚያ የማንነት ጥያቄ ክፍተት ለሌለብን እንጂ፤ ለዳኒና ለመሰሎቹ ጥያቄያቸውም፤ ፍላጎታቸውም፤ ህልማቸውም፤ እይደለምና ምናቸውም ነው።የእነሱ ጥያቄ ፍላጎትና ህልም እንዲሁም ምኞት አንድ ነገር ብቻ ነው።እሱም ከማንነት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ችግራቸውን መቅረፍ መቻል።ስለዚህ ለዳንኤል ልንሰጠው የምንችለው ፍጹም የሆነ ቤተሰባዊ ፍቅርን ብቻ ነው።እኛ ወንድሞቹ በመሆናችን ምክንያት ዳኒ ክፍተቱን መሙላት የቻለ ሰው ሆኗል።ጉድለት እንደሌለበት ማሰብ ችሏል።እኛ ቤተሰቦቹ እንደሆንን ማመን ጀምሯል።ይህንንም በደስታ ተውጦ ሲነግረንና ፈጣሪውንም ሲያመሰግን ያኔ በደንብ አይተናል። ስለዚህ በዚሁ እንዲቀጥል ነው ማድረግ ያለብን።ፍዬ...... አደራ!ፍቅር መስጠት፣ ማበረታታት፣ እንጂ በለቅሶ ደስታህን እየገለፅክ ወንድምህን ስትረብሽ እንዳላይ!ራስህን ሳትሰስት ስጠው!በቃ!አውራው፤አጫውተው፤ ታዘዘው፤አዝናናው!ጀስት ፈታ አድርገው።እንጂ ይሄን እንባህን ተው!ተግባባን?››

‹‹እም ዱቭዬ፤በጣም ገብቶኛል።ብቻ በሰላም ይምጣ!››አለና፤ በፈገግታ ደምቆ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ዳዊት በመጠጋት፤ ወንድሙም፤

አባቱም፣ እናቱም፣ መምህሩም፣ ሁሉ ነገሩ የሆነውን ዳዊትን፣ ‹‹አመሰግናለሁ እሺ››በማለት፣በትህትና ዝቅ ብሎ ጉልበት እንደመሳም ሲል፣ዳዊት ቆም አለና ፍፁምን ቀና አድርጎ ግራና ቀን ትከሻውን ይዞ እየወዘወዘ፣‹‹ጠንካራ ሁን አኬ!››ሲል አበረታታው፡፡
‹‹እሽ፣እሆናለሁ ዴቭዬ!አሁን እንውጣና ራት እንብላ፣ወይም ስራ ካለህና መውጣት ካልፈለክ ይዠልህ ልምጣ››
‹‹እንውጣና እንብላ››
ዳዊትና ፍፁም ከቤት ወጥተው በቅርባቸው ወዳለ ምግብ ቤት በማምራት እራታቸውን ተመግበው ተመለሱ፡፡
በጉጉት የተሞላች ምሽት ናትና ቶሎ እንደማትነጋ እያወቁም ቢሆን በጊዜ መተኛት እንዳለባቸው ተስማምተው ወደ መኝታቸው አምርተው ጋደም አሉ፡፡እነሱ በጊዜ ይተኙ እንጂ፣እንቅልፍ ግን በጊዜ ቤታቸው ሊገባ አልቻለም፡፡
ሁለቱም የተኙ መስለው ምንም አይነት ቃላት ሳይለዋወጡ፣ አንዳቸው አንዳቸውን ላለመረበሽ በሚል በዝምታ ነበር ሙሉ ሌሊቱን ያሳለፉት፡፡ አይነጋ የለም እንቅልፍ በዓይኖቻቸው ዝር ነጋ፡፡
ፍፁም ራሱ የሚይዛትን አዲስ ማኪናስ ከመጀመሪያው እለት ጀምሮ ከመኖሪያ ጊቢያቸው አጠገብ ካለው የጋራጅ አጥር አስጠግቶ ነው የሚያሳድራት፡፡ጥበቃውም አስተማማኝ ነውና ለወትሮው አንድም ቀን ስጋት አድሮበት አያውቅም፡፡ዛሬ ግን ወገግ ሲል ተነስቶ፣እንደተለመደው ለባብሶ እንደኛውን ከመውጣቱ በፊት፣ለራሱ ብቻ የሚሰማ በመሰለው ዝቅተኛ ድምፅ፣‹‹ለማንኛውም አንድ አፍታ መኪናዬን አይቻት ልምጣ››ሲል አልጎምጉሞ፣ የሌሊት ቁምጣውን እንደለበሰ ሊወጣ ሲል፣ ዳዊት ሳቁን መቆጣጠር አልቻለምና አልጋው ውስጥ ተሽፋፍኖ እንዳለ ቡፍ ተብሎ የሚጀመረውን ሳቅ ሳቀበት፡፡
ዳዊት ፍፁምን ከልጅነቱ ጀምሮ ያሳደገው ነውና ዕቅዱን፣ሃሳቡን፣ፍላጎቱን፣ አስተሳሰቡንና ሁለ ነገሩን በቀላሉ ነው የሚረዳው፡፡ዛሬም በጊዜ ሊተኛ መጣ እንጂ፣ጨርሶ እንቅልፍ እንደማይወስደው ገምቷል፡፡እንደገመተውም፣ፍፁም ዘወትር እንደሚያደርገው ገና ጋደም እንዳለ ማንኮራፋቱን ትቶ፣ያለእንዳች እንቅልፍ ነበር የነጋበት፡፡ይህን ማየቱ አልበቃ ብሎ፣መኪናው በሰላም ማደሯ ራሱ ሳያስጨንቀው እንደማይቀር ገምቶ ነበርና ነው ፍፁም፣ ‹‹አይቻት ልምጣ››ባለ ቅፅበት ሳቁን የለቀቀው፡፡
ፍፁም የዳዊትን ሳቅ እንደሰማ፣‹‹እን....ዴ!አንተም እንደኔ አልተኛህም እ ዴቭ?››አለና፣እኩል ነና! በሚል አስተያየት እያየው እብሮ መሳቅ ጀመረ፡፡ ዳዊት፣‹‹ቆይ ከመቸ ወዲህ ነው መኪናዋ በሰላም ማደሯን ለማዬት ወጥተህ የምታውቀው?››አለው ሳቁን እየቋጨ፡፡

ብዬ ነዋ ዴብ…››አለና፤‹‹አሳስቀህማ ‹‹ያው….ሚሆነው አይታወቅም በቁምጣ እንደሆነ ፈጥኖ ወጥቶ አታስቀረኝም፤ አይገርምህም!››በማለት ተመለሰ።እየሳቀ ሚኒባሱን ወደሚያሳድርበት ቦታ ሄዶ ተዘዋውሮ አይቷት ሁሉ ነገሯ ሰላም ነው እሽ!ታርጋዋን መጣና፤‹‹አይዞህ አታስብ ዴብዬ የመጣሁት››በማለት ለሌላ ሳቅ ዳረገውና፤ ሳይቀር አረጋግጬ ነው ‹‹ሆ…በዛሬው ቀን አንድ ነገር ብትሆን እስቲ አስበው ዴብ?ያኛውን አሮጌ ሃይሲ እስመጥቶ ልቀበለው?ኧረ ኪድዬን ምን በሱ ጆሮ ይደፈንǃ››እያለ፤ መኪናው በሰላም አድርጌያት?እንዴ…የሰይጣን በማደሯ እያመሰገነ መለባበስ ጀመረ።

ዳዊትና ዳንኤል ተነጋግረው በዳንኤል የገንዘብ ስጦታ ለፍፁም የገዙለት ሁለት ሚኒባስ ነው።

አንዷ ፍፁም ወያልነት እየሰራ ይጥለው በነበረው የእቁብ ገንዘብ ላይ ተጨምሮለት መጀመሪያ የተገዛችለት በመጠኑ ያገለገለችው ስትሆን፤በሷ በደንብ ከተለማመደ በኋላ፤ ባቀዱለት መሰረት ሌላ አዲስ ስሪ ኤል ሚኒባስ ገዙተውለታል።ስለዚህ አሮጌዋን ለሹፌር ሰጥቶ ቀጥሮ እያሰራ አዲሷን ደግሞ ራሱ ይዞ መስራት ከጀመረ ጥቂት ወራትን አስቆጥሯል።ለወራት ያህልም ከቤታቸው አጠገብ ካለው የጋራጅ አጥር እየከፈለ ያሳድራል። ሲያሳድርም የሚያስጋ ነገር የለምና ለአንድም ቀን ሰግቶ አያውቅም።ዛሬ ግን ሰጋ።

በዚህ ባልተለመደ በ ምን ሆና ታድር ይሆን?አስቂኝ ስጋትና ፍተሻ ዳዊትን ለድንገተኛ ሳቅ መዳረጉ ሳያንስ፤ጭራሽ አረጋግጦ ከመጣ በኋላ እሱ ልኮት አረጋግጦ የመጣ አስመስሎ፤‹‹አይዞህ አታስብ እሽ ሁሉም ሰላም ነው››በማለት ደግሞ፤ሳቁን አራዘመበት።ይሄም ሳይበቃው እንደገና ባሮጌዋ ሚኒባስ ስለመቀበል ጉዳይ ሲያነሳበት፤ዳዊት ሳቁ ከአቅሙ በላይ ሆነበትና ከተኛበት ቀና ብሎ እየተመቻቸ በደንብ ለመሳቅ ተዘጋጀ።

‹‹ቆይ ቆይ አንተን ያሳሰበህ ያችኛዋን መኪና አስመጥተህ ባሮጌ መኪና መቀበልህ ነው እንዴ?››በማለት እየሳቀ ጠየቀው።

‹‹እንዴት?››አለው ፍፁም ግራ ተጋብቶ።ቀጠለናም፤‹‹በአዲስ መኪና ነዋ ዳኒን መቀበል ያለብን ዴብ››ሲለው፤

‹‹ቆይ ስማኝ ፍፄ፤መኪናዋን ሰላም ማደሯን ልታረጋግጥ ወጣህ››

‹‹አዎ››

‹‹ሰላም ማደሯን አረጋግጠህ መጣህ።በዚህም ደስ ብሎህ ተመስገን አልክ››

‹‹አዎ››

‹‹ሰላም ባታድር ብለን እናስብና ምን ነበር የምትሆነው መኪናዋ?››

‹‹እንዴ ዴብ ወይ ተሰርቃ ወይ የሆነ ነገር…ኧረ በኪዳነምረት ምኑን ያሳስበናል አንተ?››አማተበ።

ዳዊት ሳቁን ጋብ አድርጎ፤‹‹ታዲያ ተሰርቃ ብታድር አንተን የሚያሳስብህ በአርጌ መኪና የመቀበል ጉዳይ ብቻ ነው?››
‹‹እና?ሌላ ምን ያሳስበኛል?››
‹‹መስረቋና መጥፋቷ የበለጠ አያሳዝንህም?ንብረትነቷ….››ሲለው፤ፍፁም ነገሩ ገባውና መልበሱን አቋርጦ፤‹‹እን….ዴ!››በማለት የሁለት እጆቹን መዳፎች በሃይል አላትሞ፤ ጧ አደረገና፤‹‹ወይ ጉድ….ለካ እሱም አለ..!እንዴ….እንዲህ ጅል ነኝ እንዴ ዴቭ?››ሲል ጠየቀው፡፡
‹‹አይ ጅልነት ሳይሆን ቅንነት ነው ፍፄ፤ያን አለማሰብህና መኪናዋ ተሰርቃም ይሁን ተፋፍቃ ብቻ ግን ስጋትህ እውን ሆኖ ብታገኘው ኖሮ፤ ጭንቀትህ ባርጌ መኪና የመቀበልህ ጉዳይ ብቻ ያሳሰበህ መሆኑን ሳስብ ነው በጣም የሳቅሁት››
‹‹እን…..ዴ በዚህማ በደንብ ሳቅብኝ፡፡ለካ እሱም አለ ባክህ፡፡ደሞ ሁለቱም ያው ነው አይገርምህም፡፡ብትሰረቅም ብትፋፋቅም ዳኒን ለመቀበል በጣም እፈልጋታለሁና የተፋፋቀውንም የታጋጋጠውንም እስካሰራ ድረስ ጊዜው መሞቱ አይቀርም…››አለና፤ጠባቧን ቤት በጋራ ሳቅ በማለዳ አደመቋት፡፡
‹‹ሲዳነምረትን ጅል ነኝ ማለት ነው፡፡ለነገሩ ጅልነት አይደለም ዴቭ፤አሁን ገባኝ፡፡ብልጠቱ ነው በሌሊት ተነስቸ እንዳያት ያደረገኝ፡፡ምክንያቱም ቀደም ብዬ አይቸ፤የሆነ ነገር ቢሆን በጊዜ ሰዓቱ ሳይደርስ አማራጭ ለመፈለግ ነው ገባህ?››ሲለው ሌላ ሳቅ…
‹‹ወይ ዳኒ…. እንዲህ የዴቭ መሳቂያ ታደርገኝ?››ሲል፤ዳዊት ቀለል አድርጎ፤ሳቁን ግን ሳያቋርጥ፤‹‹ልክ ነህ ሌላ አማራጭ ለማየት እስከሆነ ድረስ ብልጠት ነው፡፡ግን እኮ መኪና ተከራይተን ወይ እኔ ወይ አንተ እያሽከረከርን በመርሴዲስም በሲምዚንም ተቀብለን ማምጣት እንችላለን››አለው፤
ፍፁም አሰብ አደረገና፤‹‹አሃ…… እሱም አለ ለካ…..አይገርምህም?በጭራሽ አላሰብኩትም፡፡በቃ ተውኝ ዴቭ ጅል ነኝ ማለት ነው እንጂ…..››
‹‹አይ ጅል ሆነህ ሳይሆን በጣም ብልህ ስለሆንክ ነው በራስህ ሚኒባስ ከመቀበል ውጪ ሌላ ምርጫ እንዳለ ያላሰብከው፡፡ምክንያቱም ዳኒ የራስህን ሚኒባስ ራስህ እያሽከረከርክ የማየት ፍላጎት ያለውና፤የዘመናት ህልምህን ዕውን ያደረገልህ ወንድምህ ነው፡፡ይህ ህልምህ ዕውን ሆኖ በተግባር ሳያይ፤ ነገር ግን ተግባራዊ የሚሆንበትን መጠኑ የበዛ ገንዘብ ሰጥቶህ ነውና የሄደው፤በዋናነት ወደ ኤርፖርት ሄደህ በራስህ ሚኒባስ የምትቀበለው፤ መግዛትህን አሳውቀህ፤ህልምና ምኞትህ፤ፍላጎትህና ጉጉትህ፤ተግባራዊ መሆኑን ልታሳየውና ልታስደስተው ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ልክ ነኝ››
‹‹ብጣም!በጣ….ም ልክ ነህ!ትክክል!ግን ይህንን ራሱ ቀድሜ መግለፅ ሲገባኝ በመዘግየቴ ያው ጅል ብሆን ነው››እያለ በራሱ እየሳቀ መለባበሱን ቀጠለ፡፡

‹‹ጅልነት አይደለም ፍፄ፤ቅንነት ነው፡፡ባሁኑ ሰዓትም ሆነ ሌሊቱን ሙሉ ዳኒን እና እሱን የምታስደስትበትን መንገድ፤ ናፍቆትህንና ሌላውን ነገር ዳኒን እና እሱን የምታስደስትበትን መንገድ፤ ናፍቆትህንና ሌላውን ነገር ዝርዝር ሃሳብና ገለፃ የምታስብ አትሆንም፡፡ እንጂ እንዲህ አይነቱን ዝርዝር ሃሳብና ገለፃ የምታስብ አትሆንም፡፡ እንጂ እንዲህ አይነቱን ነው ለዳኒ የሚያስፈልገው፡፡የዚችን ማለዳ ሁኔታ ገባህ?ቅንነት ነው፡፡ይህ ነው ለዳኒ የሚያስፈልገው፡፡የዚችን ማለዳ ሁኔታ ለራሱ ለዳኒ እስክነግረው ቻንሁ፡፡ለማንኛውም ቀናችን በፈገግታ ደምቀን እንድንጀምረው አድርገሃልና ደስ ይበልህ፡፡በል አሁን ቶሎ መኪናዋ እንድ ነገር ሳትሆን ይዘህ ሂድ፡፡አሳጥበህ አስወልውለህ ስትጨርስ በር ላይ ሆነህ ደውልልኝ፡፡ተዘጋጅቶ እጠብቅሃለሁ››አለውና በፈገግታ እንደደመቀ መልሶ ጋደም አለ፡፡

‹‹እሺ ዴቭ እደውላለሁ፡፡ግን እኔ ምለው….ምን አይነት ሙዚቃ ከፍተን ነው…ማለቴ…የሰርግ ዘፈን ሳስጭን እንዴ?ነው አይሆንም…ኧረ…. ሙድ የለውም ኣ››

‹‹ኧረ ተው ፍፄ….››

‹‹እውነቱን ነው፡፡የሆነ ጊዜ የሚመቸውን ዘፈን ጠይቂው የጥሌ፣ የአስቴር፣ ያለኝ ይመስለኛል፤እሱን አስጭኛለሁ ግን…››

‹‹አንተ ሰውዬ ትቀልዳለህ እንዴ? የ30 ደቂቃ መንገድ መሆኑን ረሳህው ልበል?በል አሁን ቶሎ ሂድ፡፡ደሞ ያኛውንም ሚነባስ አስጠርተህ አጅበን እንዳትለው››ሲለው፤ፍፁም፤‹‹ወይ ዴቭ…ዥዋዥዌ ነው የተጫወትክብኝ፤ ኪድየን››እያለ በሳቅ እየተንከተከተ ለባብሶ ወጣ፡፡ፍፁም ከወጣ በኋላ ዳዊት ፈገግ ብሎ ጋደም እንዳለ፤መለስ ብሎ ስለ ዳንኤል ቶማስ ማሰብ ጀመረ፡፡ አስገራሚና ሊታመን የማይችለውን ያንን ድንቅ ገጠመኝ መለስ ብሎ ለረጅም ደቂቃዎች ሲያስብና የሆነውን ሁሉ ሲያስታውስም ፈገግታው ከፊቱ ሳይጠፋ ነገር ግን እንደ ፍፁም ማልቀስ እየቃጣው ዓይኖቹ ድንገት እንባ እንደማቅረር አሉ፡፡

‹‹ዳንኤል ቶማስ!››አለ ለራሱ፡፡ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ዕቅዱ ሲጠይቀው የመለሰለትን ምላሽ ቃል በቃል ለማስታወስ ሞከረ፡፡

‹‹…..እንደዚያ ከሆነ መልካም፤እስቲ ባንተ በኩል ያለውን ዕቅድ ንገረኝ››

‹‹የኔ ዕቅድ ዴቭ….እ….በመጀመሪያ ደረጃ…ከዚህ በኋላ የፈለገ ነገር ቢመጣ ጌይት ሀውስ ውስጥ አልሰራም!እዚያ ስራሁ ማለት የልዑላቸው የሳጥናኤል አገልጋይ ሆንኩ እንደማለት ይቆጠራል!የእስካሁኑ ባለማወቅ የሆነና እኔንም የሚያስኮንን አይደለምና እንርሳው፡፡ለዓመታት ሰርቻለሁ፡፡ የአሁኑን የቅጥር ኮንትራቱን ለመጨረስ 2 ዓመት ይቀረኛል፡፡ቢሆንም መልቀቂያ አስገባለሁ፡፡ወደ አሜሪካ ሄጄ የረፍት ጊዜየ ካለቀ በኋላ ስራ አገባና መልቀቂያ ደብዳቤየን አስገብቼ እየሰራሁ ውጤቱን እጠብቃለሁ፡፡ በሳምንትም ይሁን በሁለት ሳምንት በወርም ይሁን በሶስት ወር እለቃለሁ፡ ፡ያን የማድረግ ሙሉ መብት አለኝ፡፡ያለፈው የህመም ወረቀቴንና አሁንም

ልክ አለመሆኔን በመግለፅ ከማንም ጋር ሳልጋጭ የራሴን ቀለል ያለ ስራ መስራት እንዳለብኝ መወሰኔን ነግሬ አመስግኘ እለቃለሁ።ከምስጋናና ከጥሩ የስራ ልምድ ወረቀት ጋር እንደሚሸኙኝም አውቃለሁ።እኔ ሙሉ በሙሉ ህጋዊ ሰው ነኝ።ስለዚህ ዕቅዴ.......ነገ ከነገ ወዲያ ዝንጥ ብየ ኤምባሲ እሄዳለሁ።አብረን ልንሄድና ኤምባሲውን ልታሳየኝም ትችላለህ።መጨረስ ያለብኝን ነገር ጨራርሸ ወደ አሜሪካ እሄዳለሁ ስራየን እለቃለሁ።የአሜሪካ ዜግነቱ እንዳለ ነው፤የትም አገር የመኖር መብት አለኝ።ከፈለግሁም እዚያው አሜሪካ መስራት በፈለግሁ ጊዜ መግባት መውጣት የምችል ነኝና ያሻኝን እወስናለሁ።ከመመለሴ በፊት ግን ለፍፁም የመጨረሻ ምርጥ የተባለውን ኮንደሚኒየም ትገዛለታለህ።ይችን ያሰባትን ታክሲ ይገዛና የተወሰነ ጊዜ እዚሁ እየኖረ ቤቱን አከራይቶ ሊቆይ ይችላል።የራሱን ታክሲ የመንዳት አምሮቱን አሁን በምትገዛው ታክሲ እየተወጣ ይቆያል። እንደሚሰለቸው ተስፋ አድርጌያለሁ፤በቀጣዩ ዓመት ትምህርቱን ይጀምራል። ብጭሩ ለቤቱም ለሁለት ታክሲዎችም ሆነ ለሚፈልጋቸው ነገሮች 4 ሚሊዮን ብር ይመደብለታል።በዚህ ዙሪያ ከጉዳዩ ስለወጣህ አያገባህም።በዛ የማለት መብትም የለህም።ጠፍቶ የነበረ ገንዘብ ነው።እኔም ራሴ ከነመረጃየ ጠፍቸ ነበር።በፍፁም አማካኝነት ነው እኔም መረጃውም መትረፍ የቻለው። ስለዚህ ከወረቀቱ ይልቅ ለፍፁም ክብር አለኝ።ከዶላሩ ይልቅ ለፍፁም እጨነቃለሁ።ሶ የሚገዛው ተገዛዝቶ ቀሪው በስሙ ይቀመጥለታል።መቸም ከዚህ በኋላ እኔ ተርቤ ፍፁም ጠግቦ ተራርቀን እንኖርም።4 ሚሊዮኑ ደግሞ ባንተ ስም ይቀመጣል።ሙሉ ጊዜህን ስጥተህም ቢሆን አንድ ማረፊያ ሊሆን የሚችል ምርጥ ቤት ወይም ቦታ ታፈላልግልኝና ታገኝልኛለህ።ኢትዮጵያ የራሴ ቤት ኖሮኝ፤ኢትዮጵያዊ አግብቸ፤እዚሁ አገሬ ላይ መካከለኛ ሆኖ ምርጥ የሆነ ሆቴል ልከፍት እችላለሁ።ላንተም ከኔ ሳትርቅ ተመሳሳይ ቤት በስምህ ይገዛል።የፍፁም የመጨረሻ ምርጫ ኮንደሚኒየም ስለሆነ እንጂ እሱም ቢሆን ተመሳሳይ ነገር ቢደረግለት ምርጫየ ነበር፤ብቻ ግን ስሌቶቹን፤ቦታውን፤ዋጋውን ብዙ ስለማላውቀው ከወዲሁ ብዙ ልናገር አልችልም።ዕቅዴን የሚያሳካ ገንዘብ ግን አለኝ። አሜሪካን አገር ያለ አንዳች ዓላማ እንቅልፍ አጥቸ ስሰበስበው የኖርኩት ብዙ ዶላር አለኝ።

እንደሄድኩና ስራየን እንደለቀቅሁ የመጀመሪያ ስራየ የማደርገው ገንዘቡን ማውጣትና ወደ ኢትዮጵያ ፈጥኘ ተመልሸ ገንዘቡን በኔም ባንተም ስም ማስቀመጥና ሰፊ ጊዜ መድቤ መሆን ያለበትን ነገር ማድረግ ይሆናል። እርግጠኛ ነኝ ገንዘቡ ሶስት መካከለኛ የግል መኖሪያ ቤቶችንና የፍፁምን ሁለት ታክሲዎችን ጨምሮ ለኔም ላንተም የሚሆኑ የቤት መኪናዎችን ገዝቶ አያልቅም፤ቀሪ ብዙ ገንዘብ ይኖራል።በዚያ ገንዘብ አንተ

በምትፈልገውና ሊያስደስትህ በሚችል የግል ስራ ዘርፍ ትሰማራለህ።እኔም ከዝቅተኛ ፒዛ ቤት ወይም በርገር ቤት ተነስቶም ቢሆን በሂደት እያሳደግሁት ልሄድ የምችለው አንድ ሆቴል ቢጤ መክፈት እችላለሁ። ገንዘቡ ቢያጥር እንኳን ሌሎች አማራጮች ውስጥ ልገባ እችላለሁ።ስራው በስራተኛ የሚሰራ እስከሆነ ድረስም ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አሜሪካን አገር ሌላ ስቴትም ቢሆን ተቀጥሬ እየሰራሁ ጎን ለጎን ላሳድገው እችላለሁ።ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ነውና ፍፁም ታክሲ እንደተመኘው ሁሉ፣እኔም ሆቴል መክፈት መመኘትን አሁን ገና ጀምሬያለሁና እሱን አደርጋለሁ።አንተ ደግሞ.....የግልህን ፍርድ ቤት ትከፍት....?.......››ሲለውና ሁሉቱም በጋራ ሲስቁ ቀልጭ ብሎ ታዬው።

ዳዊት ከዚህ ሃሳቡ ወጥቶ በእሱ በኩል የፈፀማቸውን ተግባራት ማሰብ ቀጠለ።‹‹ክሞላ ጎደል ዕቅዶችን ሁሉ ፈፅሚያለሁ።እንዲያውም ዳንኤል ካሰበው በላይ››አለና፣ባከናወናቸው ተግባራት ዳንኤል እንደሚደሰትበት እርግጠኛ ሆነ።

በዳዊት ጥረት ከዚያ ክፉ ዶክተር ማስመለስ በቻሉትና ዳንኤል ለፍፁምና ለዳዊት ብሎ ኢትዮጵያ ትቶት በሄደው 380 ሺ ዶላር ብቻ ብዙዎችን ዕቅዶች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል።

ዳዊት ከዶክተሩ ያስመለሱትን መጠኑ የበዛ ገንዘብ በመጠቀም በዳንኤል ይሁንታና በዕቅዳቸው መሰረት፣ ዳንኤል ወደ አሜሪካ ተመልሶ እንደሄደ ለፍፁም ሁለቱን ሚኒባሶችና አንድ የጋራ መኖሪያ ቤት ገዝቶለታል፡ እነዚህን ተግባራት ብቻውን ፈፅሞ ለፍፁም የሚኒባሶቹን ሊብሬዎችና የቤቱን ካርታ በስሙ አሰርቶ ካስረከበው በኋላ፣ሙሉ መብት የሚያጎናፅፈውን እስከመሸጥ እስከ መለወጥ የሚለውን ሙሉ ውክልና ፍፁም መልሶ ለራሱ ለዳዊት እዲሰጠው አድርጓል።

ከዚህም አልፎ ዳንኤል ሲመለስ የሚያርፍበትንና የራሱን የስራ እቅድ ነድፎ ወደ ስራ እስኪገባ ድረስ መኖሪያ የሚሆነውን ዘመናዊ አፓርታማ በራሱ ስም መግዛት ችሏል።ቤቱን በራሱ ስም ይግዛው እንጂ፣ዳንኤል ሲመጣ ከወደደውና ከመረጠው ስሙን ሊያዞርለት ይችላል።ይህን አድርጎ በሌላ ተቀራራቢ ስም ህጋዊ የቀበሌ መታወቂያ አውጥቶለታል።ቤቱንም በዘመናዊ የቤት ቁሳቁሶች ሞልቶ፣ለዳንኤል ምቹ ማረፊያ እንዲሆን አድርጎ አሳምሮና አስውቦ እየጠበቀው ነው።

ዳንኤል ሲመጣ ደግሞ በራሱ በዳንኤል ስም ሌላኛውን መኖሪያ ቤት ይገዛና በተመሳሳይ ውክልና በማጠላለፍ የተናጠልና የየግል የሆኑ ንብረቶችን የጋራ ማድረግና፣ እንዳቸው ያንዳቸውን ንብረት የማስተዳደር፣የመጠበቅና የመጠቀም ብሎም የመሸጥና የመለወጥ መብት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

ፍሥሐ ያዜ

ስለዚህ የቀረው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ዳንኤል ሲመጣ ሶስተኛውን ቤት መግዛት፡፡ይህንን ለማድረግም የተረፈው ገንዘብ በቂ ነውና ዳንኤል እንዳሰበው ሌላ ገንዘብ ሳያስፈልግ ዳዊት እጅ ባለው ገንዘብ ብቻ መጨረስ ይችላል፡፡

‹‹አዎ፤ካሰበው በላይ ጥሩ ተግባር አከናውኛለሁና እጅግ እንደሚደሰትብኝ ጥርጥር የለኝም!››አለና ከተጋደመበት ብድግ ብሎ ተነሳ፡፡ተነስቶ ከመለባበሱ በፊትም በጠባቧ ቤት ውስጥ ያለውን ትልቁን የልብስ ቁም ሳጥን ከፍቶ ራሱን በመስታዎት ማዬት ጀመረ፡፡

የህግ ባለሙያው ዳዊት ለወራት ያህል እንዲህ ባሉ ጉዳዮች ተጠምዶ ወዲያ ወዲህ ሲል ነው የቆየው፡፡ደክሞት ውሎ ቤት ከገባ በኋላ እንኳ፤ወደ እንቅልፍ ከመሄድ ይልቅ ቪዲዮውን ማየት ነበር የሚቀናው፡፡ቪዲዮውን በየምሽቱ እየከለሰ ነገሮችን ሲያመሳክር፣የፒዲኤፍ ዶክመንቶችን ፕሪንት እያደረገ እያወጣ ሲያጠና፣ሲያወጣና ሲያወርድ ነው ያሳለፈው፡፡

በረፍት አልባ ቆይታው ምክንያት ሰውነቱ ተጎሳቁሎ፣ክብደቱ ቀንሶ፣ዓይኖቹ በእንቅልፍ እጦት ተዳክመውና ደፈራርሰው ሲያይ፤ምንም ባይመስለውም፤ ዳንኤልን ሊያሳዝን በሚችል ሁኔታ ላይ ሆኖ ላለመገኘት ሲል፤ ጉስቁልናውን መሸፋፈን እንዳለበት ተረድቶ ቀደም ብሎ ከቤት ወጥቶ ወደ ፀጉር ቤት ሄደ፡፡

ምሳ ሰዓት ሲቃረብ ፍፁምም ዳዊትም ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደ ኤርፖርት አመሩ፡፡

ዳዊት የተንዠረገገ ፂሙንና ተንጨባርሮ የጎፈረ ፀጉሩን ተቆርጦ፣ሙሉ ሱፍ ለብሶና ከረባት አስሮ፣ዓይኖቹን በመነፅር ከልሎ፣ እቅፍ የተፈጥሮ አበባውን በጥንቃቄ ይዞ፣ ደህና መስሎ እየታዬ ዳንኤልን ቆሞ እየጠበቀ ነው፡፡

አዲሱ ባለ ሃብትም አጠገቡ ቆሟል፡፡ፍፁም በሱ አገላለፅ ባለካ፣በቀድሞ ፍሬንዶቹ አገላለፅ የልጅ ሀብታም ነውና፤ድንቡጭ ያለ ክብ ፊቱ የበለጠ ደንቡጮ፣ሰውነቱ ከነበረው የበለጠ ወፈርፈር ብሎ፣ቦርጭ ቢጤም እየጀማመረው ነውና ሌላ ሰው መስሎ ነው የሚታየው፡፡በወያልነት ዘመኑ ይወደው የነበረውን ሸበጥ ጫማ ትቶ ዘመናዊ ስኒከር ጫማ ተጫምቶ፤ በጂንስና በሸሚዝ ሽክ ብሎ ከዳዊት አጠገብ እቅፍ የተፈጥሮ አበባውን ይዞ ቆሟል፡፡

ፍፁምና ዳዊት ቀደም ብለው መጥተው በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ብዙ ቆይተዋል፡፡

ገብተው ቆመው መጠበቅ ከጀመሩ በኋላ መንገደኞች ቀስ እንደ ዳንኤል የሚመጡበት ቦይንግ ማረፉ ከተበሰረ በኋላ መንገደኞች ቀስ በቀስ እየወጡ ነበር፡፡ዳንኤል ግን በጣም ዘገዬ፡፡በዚህም በተለይ ፍፁም በእጅጉ ተረበሸ፡፡

‹‹ወጥተው አለቁ እኮ ዴቭ››አለው፤የፍርሃት ፊት እያሳዩ፡፡
‹‹አይ ሻንጣ የያዙ መንገደኞች እስኪረቡ ድረስ ትንሽ ይቆያሉ››በማለት ፍርሃቱን ሊያስወግድለት ሞከረ፡፡
ዳዊት ይህን ይበል እንጂ እሱም በውስጡ ሳይደነግጥ አልቀረም፡፡
‹‹ዶላር ምናምን ስትሉ....የገጠመው ነገር እንዳይሆን ዴቭ...››አለ ፍፁም፡፡
‹‹ኧረ ባክህ ታገስ ፍፄ፤ እሱ ምን ችግር አለው?››
‹‹እን....ዶ..እና እስካሁን?ወይኔ ዳኒ...ዝም ብሎ በባንክም በምንም ቢልከውና የቀረው ምንዛሬ ቢቀር ይሻል ነበር››እያለ መቀበጣጠር ጀመረ፡፡
ጎን ለጎንም፤‹‹እናቴ ኪዳነምረት አውጭው የዛሬን››ይላል እየደጋገመ፡፡
አውሮፕላኑ አረፈ ከተባለ ከ 1 ሰዓት በኋላ ወደ 5 የሚደርሱ ትልልቅ ሻንጣዎችን እያስገፋ፤ግራና ቀኝም አነስተኛ ቦርሳዎችን አንግቶ ዳንኤል ቶማስ ብቅ ሲል ሁለቱም አዩ፡፡
በዚያች ቅፅበት ዳዊትና ፍፁም እኩል ተያዩና በደስታ ተቃቀፉ፡፡ፊታቸው በደስታ በራ፡፡በዚህ ጊዜ ፍፁም፤‹‹አሃ....አንቺም ራስሽ እንደኔ ደንግጠሽ ነበር ለካ....››አለና፤ከእቅፉ ወጥቶ፤እንደነገሩ በሽራ ገመድ የታጠረውን የማለፍ ክልክል ነው ኬላ ጥሶ በደመነብስ እየሮጠ ሄደና ዳንኤል ቶማስ ላይ ተጠመጠመበት፡፡
‹‹ማነህ ተመለስ! አንተ ክልክል ነው!!››ፍፁም አይሰማም አይለማም ጥሶት ሄዶ ዳንኤል ላይ ተለጠፈበት፡፡አንገት ላንገት ተናንቀው ዚ.ወዛወዙ ብዙ ከቆዩ በኋላ ተላቀቁና ፍፁም የያዘውን የተፈጥሮ አበባ ለዳንኤል አበርክቶ፤ያነገታቸውን አነስተኛ ባጎች ተቀብሎ አንግቶ፤ሻንጣዎቹን በጋሪ እየገፉ ያሉትን ሰራተኞች አጅቦ ክልካዮቹን ይቅርታ እየጠየቀ ተመለሰ፡፡
ዳንኤል ሻንጣውን ለሚገፉት ሰራተኞች፤ ፍፁምን እንዲከተሉና መኪናው ድረስ እንዲያደርሱለት አዝዞ ወደ ዳዊት ሮጦ ሄዶ ተጠመጠመበት፡፡ በተመሳሳይ በደስታ ተቃቅፈው እየተወዛወዙ ብዙ ቆዩና ተያይዘው ወደ ውጪ መውጣት ጀመሩ፡፡
‹‹ስትዘገይ ደንግጠን ነበር፤ሁሉም ነገር ሰላም ነበር?››
‹‹ሁሉም ሰላም ነው ዳዊቴ፤ ምንም ችግር አልነበረም፡፡ምንም ነገር ትቶ መምጣት ስላልፈለግሁ ብዙ ኮተቶችን መያዝ ነበረብኝ፡፡በጣም ብዙ ዓገ ስለሆነ ብቻ ነው ልዘገይ የቻልኩት፡፡ታንክስ ቱ ጋድ በጣም ሰላም ነው፡፡ ከእናንተ የበለጠ እኔ ደንግጬ ነበር፡፡ግን ያን ያህል የሚያሰጋ ነገር ውስጥ የሚከት አይነት እመጣጥ አይደለም የመጣሁትና ያመጣሁት፡፡ኤኒ ወይ...ኦ ጋድ!ኢትዮጵያ!ፍፄ!ዶቭ!››ዳንኤል ደስታውን መቆጣጠር አቃተው፡
:

የኤርፖርቱ ሰራተኞች ከፍፁም ጋር ሻንጣዎቹን እየገፉ ፍፁም መኪናውን እስካቆመበት ቦታ ድረስ በመሄድ እነዚያን ትልልቅ ሻንጣዎች ተጋግዘው ሚኒባሷ ላይ ጫኑ።

ዳንኤልና ዳዊት ከኋላ ነበሩና ሚኒባሷ ጋ ሲደርሱ፤ ሻንጣዎቹ ተጠቃለው ገብተው ፍፁም ለሰራተኞቹ ገንዘብ እየከፈለ ነበር።ለሶስቱ ገፊዎች ደስ እያለው፤‹‹ይመቻችሁ ፍሬንዶች!ለሶስታችሁ ሁለት ሁለት እንድትካፈሉ አድርጌ ስድስት አመድ ልለቅባችሁ ነው!››አለና 600 ብር ሰጥቶ አስደስቶ ሸኛቸው።

ዳንኤል ፍፁምንና ሚኒባሷን አዩ።የቀኝ እጁን መዳፍ አፉ ላይ ለጥፎ፤ ባየው ነገር ምን ያህል እንደተደሰተ ለመግለፅ ተቸግሮ ቀጥ ብሎ ቆመ።

‹‹ይሄን ይመስላል ወንድሜ!እንኳን ደህና መጣህ!ለኪ.ድዬ ምን ይሳናታል?በሰላም እንድታመጣህ ለመንኳት፤ይሄው አመጣችህ! እን…ዴ አገቡምገግቡ ልወጣ ነው››እያለ ቀልዶ፤ በደስታ ብዛት በቆመበት ደርቆ ወደ ቀረው ዳንኤል በማምራት በድጋሚ አቅፎ እየሳመ ናፍቆቱን ገለፀ።

ፈንጠር ብሎ ትዕይንቱን በደስታ ሲከታተል የነበረው ዳዊት፤‹‹እንግባ››ሲል ነበር ፍፁምና ዳዊት አንገት ላንገት ከተናነቁበት የተላቀቁት።

‹‹አም እንግባ ዳኒዬ፤አይዞህ ደስታህን በቃላት ካልገለፅክ ብዬ ግግም አልልም እሺ።ገብቶኛል!የኔንም ደስታና ናፍቆት ብትጠይቀኝ መመለስ ስለማልችል ሁለታችንም ላሽ ብለን እንለፈው ኣ››

‹‹እሽ ፍፄ ተስማምቻለሁ፤ላሽ!››

ፍፁም ፅድት ያለውን አዲስ ስሪ ኤል ሚኒባስ በዝግታ ተጠንቅቆ እያሽከረከረ ከኤርፖርት ጊቢ ወጡ።

ፍፁም ወደየት እንደሚሄዱ ቢያውቅም፤ምናልባት ዳንኤል ሳይስማማ ቢችልና ሌላ ቀን እንሂድ ዛሬ ግን ወደ ስድስት ኪሎ ነው መሄድ የምፈልገው ሊል እንደሚችል ገምቷልና፤‹‹እህ ዴቭ ወደየት ልንዳው?›በማለት ከኋላ የተሳፈሩትን ዳንኤልንና ዳዊትን በውስጥ ስፖኪዮ እንጋጦ እያየ ጠየቀ።

‹‹ወደ መካኒሳ››አለው ዳዊት።

‹‹ኖ… ››አለ ዳንኤል።

‹‹ግድ የለም እቃውን አስገብተን፣ ጥቂት አርፈህ፣ ቀላልፈን ወደ ቤት እንሄዳለን››

‹‹እሱ ይሁን ግን…. መካኒሳ ነው እንዴ ቤቱ?እዚያ ሰፈር ነው የተገዛው?›› በማለት ተገርሞ ጠየቀ።

‹‹አዎ፤ምነው?ያኔ ስታለቃቅስ ያዩህ ሰዎች ቢኖሩ ብለህ…››ሲለው፤

‹‹ኖ ዊይ፤ማንም አያስታውሰኝም፡፡ቢያስታውሰኝም ችግር የለውም፡፡ እንዲያውም ደስ ይለኛል እንጂ››ካለ በኋላ፤‹‹ግን እንዴት መረጥከው?ያገኘህው እዚያ ሆኖ ወይስ አስበህበት?››አለው፡፡

‹‹አስቤበት ያደረግሁት ነው፡፡ያኔ በሃዘን ያለቃቀስክባት ሰፈር ስለሆነች፤ አሁን በመሳቅ በመሳሳቅ እንድትበቀላት በሚል ነው፡፡በዚያ ላይ ሰፈሩ ለቀድሞው የኤስ ኦ ኤስ መንደር ቅርብ ነው፡፡ጭላንጭል የአዲስ አበባ ትዝታዎችህም በመካኒሳ፣በሳር ቤትና በብስራተ ገብርኤል ዙሪያ፤በተለይም በሜክሲኮ አካባቢ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡በተጨማሪም ለታክሲ ምቹ የሆነ አስፓልት ዳር ሆኖ አስተማማኝ ጥበቃ ያለበትና እንደ ሌሎቹ ሰፈሮች ሩቅ ባለመሆኑ ነው፡፡ከመካኒሳ ሜክሲኮ፣ ከሜክሲኮ ስድስት ኪሎ፣ ሁለት ታክሲ ነው፡፡አቧራ የለ፣ ግርግር የለ፣ጭለማ የለ፣ከከተማ ወደ ከተማ፡፡ እንደገና በእያንዳንዷ አስፓልት ዳር አሻግረህ እያየህ ያኔ የሆንከውን ለማስታወስና በትዝታ ለመመሰጥ ያ ጊዜ ማለፉን እያሰብክ.....ፈገግ ለማለት ይረዳህ ዘንድ ነው››በማለት አብራራለት፡፡

‹‹ኦ ማይ ጎድነስ!ታንክስ ሜን!ዩ ኖ ዋት ለመጀመሪያ ጊዜ ጉድ ከሆንኩባትና ፀጉሬን እየነጨሁ ካለቀስኩባት ሰፈር ዝንጥ ብዬና በፈገግታ ደምቄ ወጥቶ፣ማደሪያ አጥቶ ያደርኩባትን ምቹ የሜክሲኮ ፌርማታየን እያየሁ አልፌ፣ለቀናት በቆየብኝ ረሃብ ጠውልጌና አቅም አጥሮኝ ደካክሜ አረፍ ያልኩባቸውን ጥጋጥጎች እየተመለከትኩ ተጉዤ......ፍፁምን አግኝቶ...ፓስቲ በሻይ ተጋብዤ፣ ነብስ በዘራሁበት በአራት ኪሎ በአምስት ኪሎ አልፌ፣ ቤተሰብ ወዳገኘሁበት ስድስት ኪሎ ደርሼ፣ የፍቄን ኪዳነምህረት ተሳልሜ፣ ወደ ቤተሰቦቼ ቤት ግቢ....ት!እንዴት ደስ ይላል!በጣም አመሰግንሃለሁ ድንቅ ነገር ነው ያደረከው!ታንክስ ሜን!››እያለ፤እጁን ትከሻው ላይ አሳርፎ በወዳጅነት እየጠበጠበ ደጋግሞ አመሰገነው፡፡

‹‹ፍቄ እለፊውና ነዳ ነዳ አድርገው እንጂ፤በጣም ቀስ አልክ››አለው ዳዊት፡ :

‹‹አይ ከምድር ያለ ሰው አሉ››ሲል መለሰ ፍፁም፡፡‹‹ይህንንም እኔ ሆኘ ነው ዴቭ፤ሌላ ጊዜ ቢሆንና እንዲህ መንገድ ዘግቶ ቢቆምብኝ፤እንኳን ጠብቄ ልከተለው አልፌው ሄጄ፤አጠገቡ አቁሜ መስታዎት አውርጄ የስድብ ናዳ ነበር የማወርድበት፡፡

መልስ እየሰጠ ካንጓጠጠም ሌባ ጎማ ይዤ ነበር የምወርደው፡፡ዛሬ ግን....ፋኪው ቢሉኝ ታንኪው ነው መልሴ፡፡እንረጋጋ ዴቭዬ ታገሱ እሺ፡፡ ከዛሬ በኋላ እኔም እናንተን ጭኘ አልሄድም፡፡እጄ ሁሉ ይንቀጥቀጥ በኪድዬ!ከጥንቃቄ ብዛት...››እያለ ስቆ እያሳቃቸው በዝግታ ተጉዘው መካኒሳ ደረሱና፤ከዋናው አደባባይ ወደ ቀኝ ታጥፈው ጥቂት ዘመናዊ የግል

አፓርታማዎች ወዳሉበት ሰፈር አቀኑ፡፡ፍፁም የቤቱን የውስጥ ይዘት አይወቅ እንጂ ቤቱን ሲገዛ ጀምሮ ያውቀው ነበርና ክላክስ አሰምቶ ዋናውን የጊቢ በር በዘበኞች አስከፈተ፡፡ዋናውን የመግቢያ በር አልፈው ከቤቱ ልትከፍትለት የነበረውን የእነ ጥሌን ሙዚቃ ረሳህው ማለት ነው?››ሲለው፤ፍፁም የእውነቱን ደንግጦ፤‹‹ውይ!ምኑ ሙትቻ ነኝ በናታችሁ!››አለና ራሱን ያዘ፡፡‹‹በጣም ሶሪ ዳኒዬ ሙዚቃ አስጭኝ እያዝናናሁ ላመጣህ ብዬ......ረሳሁ ታቃለህ!ዞረን ሄደን አንዴ ቦሌ ደርሰን እንመለስ?››አላቸው፡፡

‹‹ኖ ኖ ሌላ ጊዜ ታስደምጠኛለህ፤አመሰግናለሁ››እያለ ዳዊትን ተከትሎ ወረደ፡፡

አንዱ ሻንጣ ወደ ስድስት ኪሎው ቤት የሚሄድ ነውና እዚያው መኪና ውስጥ ትተው ሌሎቹን አራት ትልልቅና ከባባድ ሻንጣዎች ከአፓርታማው የጊቢ ዘበኞች ጋር ተጋግዘው በማጋዝ ተዘጋጅቶና ተከፍቶ ወደ ጠበቃቸው አዲስ ቤት ገቡ፡፡

ቀድሞ የገባው ዳዊት የሳሎኑ ወለል ላይ ቆሞ ጠበቀውና፤የዳንኤል እግሮች ገና ከመግባታቸው፤‹‹የውጭ አገር ሰው ሰርፕራይዝ ይወዳል፤ ሰርፕራ.....ይዝ!››አለው፡፡

‹‹ኦ ማይ ጎድነስ!ሃው?››ሲል ተደነቀ ዳንኤል፡፡

ዳዊት፤‹‹ያው››አለና ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ የነበረውን የታሸገ ካኪ ወረቀት አንስቶ አበረከተለት፡፡ዳንኤል እንደቆመ ካኪ ወረቀቱን ተቀብሎ ከፍትና አንድ ባንድ እያወጣ ማየት ጀመረ፡፡በሌላ ተቀራራቢ ስም የወጣለትን ህጋዊ የቀበሌ መታወቂያ ጨምሮ ሌሎች ሰነዶችን አይቶ ጨርሶ መልሶ አስገባቸውና፤የዳዊትን ጥንቁቅነትና አስተዋይነት እየገለፀ፣እያደነቀ፣ እያመሰገነ፣በወንድምነት መንፈስ እቅፍ አድርጎ ለቀቀው፡፡

የቤቱን ዘመናዊ እቃዎች ሁሉ እንደቆመ ለአፍታ ገርመም አድርጎ ሲያይም የበለጠ ተደመመ፡፡

‹‹እሷን ደግሞ ተዋወቃት፡፡ፅዮን ትባላለች፤የአክስቴ ልጅ ናት፡፡ከወራት በፊት የዩንቨርስቲ ትምህርቷን ለመማር ከክፍለ አገር የመጣች ጎበዝ ተማሪ የሆነች እህታችን ናት፡፡በአራት ኪሎ ካምፓስ የተፈጥሮ ሳይንስ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ናት፡፡እዚያው ካምፓስ ውስጥ ነው የምትኖረው፡ ፡በረፍት ጊዜዋ እዚህ እየመጣች የማረፍ፣ የማጥናት፣አንተንም የማገዝ ሃላፊነት ሊኖርባት ይችላል፡፡ሰሞኑን የረፍት ጊዜ ስለነበራት ቤቱን በማስዋብ ረገድ ትልቁን ስራ ሰርታለች፡፡ወደ ጊቢ መመለስ የነበረባት ዛሬ ቢሆንም፣የግድ ነውና አስፎርፌን በማስተረት ምሳ ሰርታ ቡና አፍልታ እንድትቀበለን አድርጌያለሁ››በማለት አስተዋወቀው፡፡

ዳንኤል ቶማስ በትህትና የተሞላችውን ቆንጆዬ ወጣት ልጅ ተዋውቆ፤ ምቹው ሶፋ ላይ አረፍ አለ፡፡
ዳንኤል ቶማስ እንዲህ ተውቦ ያገኘውን ሶስት ሰፋፊ ክፍሎች ያሉትን ዘመናዊ ቤት እየቃኘ በአድናቆት አንገቱን እየወዘወዘ ደስታውን በቃላትም በፈገግታም ሲገልፅ ቆየ፡፡
ቀጥሎ ደግሞ በራሱ ስም ያወጣለትን ሲም ካርድ በአዲስ ዘመናዊ አፓራተስ ውስጥ አስገብቶ ተንቀሳቃሽ ስልክ ሰጠው፡፡ዳንኤል ለማመስገንም ሆነ ለማድነቅ ቃል እንዳጠረው በፊት ገፅታው እየነገረ በዝምታ ተቀበለው፡
፡
በመጨረሻ ዘበኞቹን እያሸከመ ይልካቸው የነበረው ፍፁም ማሸከሙን ጨርሶ መኪናዋን ቆላልፎ ሁለቱን አነስተኛ ቦርሳዎች አንግቶ መጣና ወደ ቤት ገባ፡፡ከዳንኤል የበለጠ በቤቱ የውስጥ ይዘት ፍፁም ነው ሰርፕራይዝ የሆነው ማለት ይቻላል፡፡ገና እንደገባ፤‹‹እን....ዴ?እንዴት?››በማለት በአግራሞት ጮኸ፡፡
ፍፁምና ፅዮን ቀደም ብለውም ይተዋወቁ ነበርና ፍፁም፤ቀልድ አዘል ወቀሳውን ወደ ፅዮን ሰነዘረ፡፡
‹‹እንዴት ይሄ ሁሉ እቃ ሲጓጓዝ አልነገራችሁኝም?ዴቭን ተይው እንዴት አንቺ አልደወልሽልኝም?››
‹‹እህ ምን ታደርግልናለህ?ያንተ ሚኒባስ የቤት እቃ መጫን አትችል››አለችው ፈገግ ብላ፡፡
‹‹ቢሆንም ማወቅ ነበረብኝ፡፡ቢያንስ ማጀብ እችላለሁ! እን...ዴ..ይሄን ባውቅ እኮ ሚኒባሱን ትቸ ኤፈሳር ወይም አይሱዙ ነበር የምገዛው!››እያለ የቤቱን እቃዎች ቆሞ ሲያስተውል ቆየና፤‹‹በነገራችን ላይ ይሄን ሁሉ የሚያማምርና ውድ ውድ እቃ ያለእኔ ምክርና እገዛ እንዴት ብቻችሁን መግዛት ቻላችሁ?››እያለ ያነገታቸውን ቦርሳዎች አስቀምጦ፤‹‹ዴቭ ኩርሲ ነገር የለም...ማለቴ ጨክኘ እዚህ ሶፋ ላይ ልቀመጥ?››ብሎ አስፈቀደ፡፡
‹‹ዳኒን አስፈቅድ››
‹‹እህ ዳኒ ልቀመጥ?››
‹‹አዎ ወንድሜ፤በደንብ ተቀመጥ!››አለው በስስት ዓይን እያዩ፡፡
ፅዮን ያዘጋጀችውን ምሳ ተመግበው፣ቡናዋንም ጠጥተው፣በፍፁም ጫወታዎች በጋራ ሳቅ ሲፍለቀለቁ ቆይተው፤ሻንጣዎቹን ቦታ ቦታ ካስያዙ በኋላ፤ዳንኤል ወደ ናፈቀው ወደ ስድስት ኪሎዋ የዳዊት ቤት ለመሄድ ተዘጋጁ፡፡ፅዮንም የተመገቡባቸውን እቃዎች አጣጥባ የቡና ስኒዎቹን ሸክክፋ ወለሉን ካፀዳዳች በኋላ፤ወደ አንደኛው ክፍል ገብታ ልብሶቿን ቀይራ፤ የቀየረችውን ቢጃማ የያዘችበትን ትልቅ ቦርሳ በትከሻዋ አንግታ ሌላ ፅዮን ሆና ወጣችና፤‹‹ጨርሻለሁ መሄድ እንችላለን››አለቻቸውና ለመሄድ ተነሱ፡፡

‹‹ብጣም ቆንጆዬ እህት ነሽ፡፡በጣም እናመሰግናለን››በማለት ዳንኤል በአክብሮት ጨበጣትና ተያይዘው ወጡ፡፡
በሩን ቆልፋ ቁልፉን ለዳንኤል ስትሰጠው፤
‹‹እኔ አንድ ቁልፍ ይበቃኛል፤አንድ ብቻ ስጪኝ››አለና፤‹‹ዶሻ ቁልፍ ይዛችኋል?››ሲል ጠየቀው፡፡
‹‹እኔና ፍፁም አንድ አንድ ይዘናል፡፡ሶስት ነው አይደል?ለፅዮኔ አንዱን ስጣት፡፡ሁለቱ አንተ ጋ ይሁን››አለው፡፡ዳንኤል አንዱን ቁልፍ አውጥቶ ለፅዮን ሰጣትና፤‹‹ብዙ ጊዜ ከእነ ዳዊት ጋር ስለሆን የማሳልፈው ይህ ቤት ባዶውን የመሆን ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው፡፡ስለዚህ ፐሊስ እየመጣሽ አጥኚበት፤ ከጓደኞችሽ ጋር ኢንጆይ አርጊበት፤ዋርኤቨር››አላት ሁለቱንም እያዬ፡፡ፅዮን አንገቷን በ እሺታ እየወዘወዘች በአክብሮት ተቀበለችው፡፡
ከነ ሲም ካርዱ የሰጠውን ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ ስልክ አውጥቶ፤‹‹ቁጥሬን ያዥ››አላት ዳንኤል፡፡ፅዮን ስልኳን ስታወጣ ዳዊት ሳቅ አለና፤‹‹ቁጥርህን ታውቀዋለህ እንዴ?››ሲል ጠየቀው፤‹‹አሃ…›› አለና ማን ወደ ማን መደወል እንዳለበት አሰብ አድርጎ፤‹‹ያ እኔ ወዳንቺ ልደውል››ብሎ ቁጥሩን ከሷ እየሰማ መዘገበና ወደ እሷ ደወለ፡፡ቁጥሯንም መዝግቦ ያዘ፡፡እግረ መንገዱንም በቃሉ የሚያውቃቸውን ሁለት የኢትዮጵያ ስልክ ቁጥሮች በአዲሱ ስልኩ መዘገበ፡፡የፍፁምንና የዳዊትን፡
‹‹እናንተም ይህን ቁጥር ያዙት››በማለት ወደ ሁለቱም ደወለ፡፡
ወደ ፍፁም ሚኒባስ ከመግባታቸው በፊት፤ከቤቱ የግቢ ሂደት ጀምሮ እስከ ውስጥ ዝግጅቱ ድረስ በነበረው የማገዝ ስራ ተሳታፊ ሆነው፤በደንብ መግባባት ወደ ቻሉት ዘበኞች አምርቶ ያገዙበትን ሂሳብ ሊሰጣቸው ሲል፤ ፍፁም፤‹‹ጨምርላቸው እንጂ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡አመድ አመድ ነው የሰቀኩባቸው፡፡ዛሬ የደስታ ቀን ነው፤ ሰው ደግሞ በደስታ ቀኑ መስጠት አለበት!ግጪቸው 'አቦ!››ብሎ፤ካስጨመረላቸው በኋላ፤ዳዊት፤‹‹ጉ በደንብ ተዋወቁ›› ብሎ ጠርቶ፤ለሁለቱ ዘበኞች‹‹የአዲሱ ቤታችን የቤተሰብ አባላት እኛ ነን፡፡እኔ፣እሱ፣እሱና እሷ፡፡ለየብቻችንም፤በጋራም ልንመጣና ከፍተን ልንገባ የምንችለው ለጊዜው አራታችን ብቻ ነን››በማለት ወደ ሁሉም እየጠቆመ አስተዋወቃቸው፡፡ፍፁምም ቀብል አድርጎ፤‹‹ከኛ ውጪ ወደ ውጪ ኧ››ሲል አስጠነቀቃቸውና፤ሁለቱን ዘበኞች ተሰናብተው ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡አራት ኪሎ ላይ ፅዮንን አውርደው፤ጉዞዋቸውን ሽቅብ ወደ ስድስት ኪሎ ቀጥለው፤ ወደዚያች ተዓምረኛ ጠባብ የቀበሌ ቤት አመሩ፡፡ እንደደረሱም፤ፍፁም ሚኒባሱን የጊቢው በር ላይ አስጠግቶ አቁሞ ወረደና፤ በዛጉና ሳስተው በተበጣጠሱ ቆርቆሮዎች ተለጣጥፎ የተሰራውን የጊቢ በር ከፍቶ እንደምንም ብሎ ሰፋ እንዲል ካደረገ በኋላ፤ለዚህኛው ቤት ተብሎ መኪና ውስጥ እንዲቀር የተደረገውን አንደኛውን ትልቅ ሻንጣ

ከዳዊት ጋር ተጋግዘው ለማስገባት መታገል ጀመሩ፡፡ከብዙ ትግል በኋላ ያን ትልቅ ሻንጣ ወደ ውስጥ ማስገባት ተቻለ፡፡

ሻንጣው ከገባ በኋላ ፍፁም፣‹‹ይሄ ሻንጣ እኔ ሳልመጣ እንዳይከፈት!መኪናዬን እቁሚያት ልምጣ››ብሎ አስጠንቅቆ፣ፈጥኖ ወጣና ሚኒባሱን ወደ ማሳደሪያ ቦታው ወስዶ ቦታዋ ላይ አቁሞ እየሮጠ ተመለሰና፣ወደ ቤት ገባ፡፡

ዳንኤል ቶማስ ተቀረጥ አትቀረጥ የሚል ግብ ግብ ውስጥ ላለመግባትና አላስፈላጊ ትኩረት ላለመሳብ ሲል፣ስልክም ሆነ መሰል ዘመናዊ ቁሳቁስ ሳይይዝ ነው የመጣው፡፡

ሆኖም ለፍፁምና ለዳዊት ይሆናሉ ያላቸውን ብዙ አልባሳትና ጫማዎች እንዲሁም የመዋቢያ ቁሳቁሶች በርከት አድርጎ ገዝቶ አምጥቶላቸዋል፡፡ መንገድ ላይ እያሉ ፍፁም ምን ምን ይዞለት እንደመጣ ጠይቆት ስለነዚህ ዘመናዊ አልባሳትና ጫማዎች እየነገረው ነበርና ለማየት በጣም ጓጉቷል፡፡

ፍፁም ቤት ውስጥ ገብቶ ከመቀመጡ በፊት ነበር ወደ ትልቁ ሻንጣ ያመራው፡፡ከዚያ አሰብ አደረገና፣አንዳች ነገር ወስኖ፣‹‹እም፣እ....እንዴ ዳኒዬ ይቅርታ እዛኛው ሶፋ ላይ ትሆንልኝ?››ሲል እየሳቀ ተማፀነው፡፡ምክንያቱም ሻንጣው ያለው ወለሉ ላይ ነበርና እያወጣ ዘርግፎ ለማየት የግድ ረጅሙ ሶፋ ያስፈልገዋል፡፡‹‹ሻንጣውን መሬት ላይ እንዳለ ወደ እዚህ ስቤ ለማስጠጋትና ውስጡ ያሉትን ልብሶች እያወጣሁ እዚህ ላይ ለመከመር ነው ገባችሁ?ስለዚህ ሽፍት አርጊ ዳኒዬ››በማለት ደግሞ ትእዛዝ ሰጠው፡፡

‹‹እሽ ፍፄ፣ታዛዥ ነኝ››

ዳንኤልና ዳዊት የራሳቸውን ሲሪዬስ የሆነ ወሬ ይዘው ነበርና የፍፁምን ሁኔታ ብዙም ትኩረት አልሰጡትም ነበር፡፡ ዳንኤል በግማሽ ልቡ ዳዊትን እያዳመጠ፣በግማሽ ልቡ የፍፁምን ትእዛዝ ተቀብሎ ተግባራዊ አደረገና፣ ተነስቶ ወደ ሌላኛው ብቸኛ ሶፋ ሄዶ ተቀምጦ የዳዊትን ወሬ ማዳመጥ ቀጠለ፡፡

ፍፁም ሻንጣውን እንደምንም ብቻውን ጎትቶ አስጠጋና ያሰበው ቦታ ላይ ካሳረፈ በኋላ፣የትልቁን ሻንጣ ዚፕ በፈገግታ ድምቅ ብሎ ሸርግግ አድርጎ እስከመጨረሻው ከፈተው፡፡ዚፑን ከፍቶ የላይኛውን ክፍል ገልበጥ አደረገና፣የእጆቹን መዳፎች እርስ በርስ እያፋተገ፣‹‹ብሰ....ው››ብሎ ጀመረና እያወጣ ማየቱን ቀጠለ ፡፡

‹‹ብሰ....ው!››ይላል እያወጣ እያዬ፡፡‹‹እንዴ.... ይሄማ በቃ...!››ይላል መልሶ፡

ጥሩ ጥሩ መዓዛ ያላቸው ብራንድ ሽቶዎች፣ዲዮዲዮራንቶች፣ሎሽኖች፣ የፀጉር ቅባቶች፣ሱሪዎች፣ ጃኬቶች፣ሸሚዞች፣ከናቲራዎች፣ዘመናዊ ጫማዎች፣ሁሉንም አንድ ባንድ እያወጣ፣በደንብ እስተውሎ እያዬ‹‹ይሄ የኔ

ነው መቾም፤ይሄ እንኳ የዴብ ነው››ይላል።አሁንም ሌላ ያወጣል፤‹‹ኧረ በኪዳነምረት ይሄማ በቃ.....››እያለ፤ሁሉንም እያደነቀ፣እየለየ፣ፍልስልሱን አወጣው።አሁንም በመሃል ሌላ ሃሳብ መጣለት።ከባዱ ሻንጣ ብዙ ጓዞች ወጥተው ስለተቀነሱለት ቀለል ብሎ ነበርና፤እንዳለ አንስቶ ረጅሙ ሶፋ ላይ ዘረገፈው።ሻንጣው ባዶ ሆነለት።አሁንም አሰብ አድርጎ ባዶውን ሻንጣ ወለሉ ላይ አመቻችቶ ከፍቶ አስቀመጠ።ከዚያ አንድ ብሎ ጀምሮ እንደገና የራሱን መለየት ጀመረና ከሶፋው እያነሳ እየመረጠ እያደነቀ ወደ ሻንጣው መከተት ጀመረ።በራሱ ምርጫ ለኔ ይሆናል ያለውን እየለየ ማስገባቱን ቀጥሎ ቆየና፤አንዳንድ ልብስና ጫማዎች ግር እያሉት ሲሄዱ፤በየመሃሉ፤ ዳንኤልን መጠየቅ ጀመረ።

‹‹ይሄ የኔ ነው አይደል ዳኒ?››ይለዋል።‹‹አዎ እሱ ላንተ ይሆናል ብዬ ያመጣሁት ነው››ይልና ከዳዊት ጋር ማውራቱን ይቀጥላል።

ፍፁም አሁንም ጣልቃ ይገባና፤‹‹ይሄስ ዳኒ?››ይለዋል።‹‹እሱም ያንተ ነው››ሲለው ቆየ።አሁንም ፍፁም ግራ መጋባቱ እየባሰበት ሄደና፤‹‹ይቅርታ ዳኒዬ፤ጫወታችሁን ካላቋረጥኩ እንዴ ብታግዘኝና ለኔ ብለህ ያመጣህልኝን ለይተህ ብትነግረኝ...ወይም ብትሰጠኝ....ተቸገርኩ እኮ››አለው።

‹‹ኧረ ተረጋጋ ፍጼ፤ቀስ ብሎ አይደርስም?››አለ ዳዊት ጣልቃ ገብቶ።

‹‹እንዴት ብዬ ዴብ?ድርሻየን ሳላውቅና ድርሻዬን ሳልይዝ መረጋጋት?ኧረ ዴብ አትቀልድ...እንዴ...››እያለ ሳቁን ቀጠለ።ከማለዳ ጀምሮ ጥርሱ ከድን ሳይል እንዲሁ እንደሳቀ ነው የዋለው።

ዳንኤል ለፍፁም ቅድሚያ ሰጥቶ ጫወታውን አቋርጦ፤‹‹አኬ ልለይልህ›› ብሎ ተነስቶ፤ለፍፁም ያለውን እየለዬ፤ለዳዊት ያመጣውን እየነገረ፤ ‹‹አይሆንም፤ይሄማ የኔ ነው›› እያለ የሞገተውንም እየጨመረለት፤ ድርሻውን ሰጠውና ወደ ዳዊት ተመለሰ።ከዳዊት ድርሻ የፍፁም ድርሻ በብዙ እጥፍ የበለጠ ስለሆነ፤ፍፁም የራሱን ብዙ አልባሳትና በርካታ ጫማዎች በዚያው በመጣበት በትልቁ ሻንጣ ለማስቀመጥ ተገደደ።የዳዊትን ድርሻ ሶፋው ላይ ትቶለት፤‹‹ይሄው ዴብ፤ያንተ ድርሻ ይሄ ነው። በሌላ ሻንጣ ውስጥ አስገባልሃለሁ።የኔን ለይቸ ለብቻየ ወስጃለሁ፤ይሄው!››ብሎ አስረድቶ ድርሻውን ሸካክፎ ያዘና፤እንደገና እያወጣ እያገላበጠ እያዬ፤ ጫማዎቹንም እየለካ ሲደመም፤ ሲደነቅ፤ ሲያደንቅ፣ዳንኤልንም በጣም እንዳስከየፈው በየመሃሉ ሲገልፅለትና ደጋግሞ ሲያመሰግነው ብዙ ቆየ። ደስታው ወደር የለሽ ሆኖ እጅግ ተከየፈ!ከዚያም፤‹‹ወይ አሜሪካ...!››ካለ በኋላ፤በሱ አገላለፅ በመጣለት እቃ መከየፉን ትቶ፤በድንገት ድንግጥ አለና፤ ዓይኖቹን ወደ እነሱ አፍጥጦ፤‹‹እንዴ!››ሲል ጮኸ።

ዳዊትና ዳንኤል ምን አይቶ ነው ብለው፤ወደእሱ ዞር ሲሉ፤ያ ሁሉ ፈገግታው ከፊቱ ላይ በቅፅበት ጠፍቶ፤በምትኩ ፍፁም አዝኖና ደንግጦ ትክዝ ፍዝዝ ብሎ ተመለከቱት፡፡

ፍፁም በአንድ እጁ ምርጥ የተባለ ጫማ፤በሌላ እጁ ዘናጭ ጃኬት አንከርፍፎ እንደያዘ፤በድንጋጤ የፈጠጡ ዓይኖቹን እነሱ ላይ ተክሎ ሲቀር፤‹‹ምንድን ነው?››አሉት በጋራ፡፡መልስ ሳይሰጣቸው ፍዝዝ እንዳለ ጥቂት ከቆዩ በኋላ፤ከድንዛዜው እንደመንቃት ብሎ፤‹‹እ….. አይ…እ…››ተንተባተበ፡፡

‹‹ምን ሆንክ ፍፄ?››ጠንከር ብሎ ጠየቀ ዳዊት፡፡

‹‹አይ…ልብሶቹንና ጫማዎቹን እያየሁ…. ተክይፌ ወይ አሜሪካ… ስል አልሰማችሁም?››

‹‹ሰምተናል››

‹‹እሱ ነው ያስደነገጠኝና ሃሞቴን ያፈሰሰው….››

‹‹እንዴት?››

‹‹እንዴ ዴብ ምን እንዴት አለው?ይሄ ሁሉ ሚገራርም ልባብና ሽዳ…. ለካ……. የመጣው ከአሜሪካ ነው!››አለ ተስፋ ቆርጦ፡፡

‹‹እና?››

‹‹እን…ዴ…ከዚያ ቡሽቲዎች አገር ከአሜሪካ….እያልኩህ አደል እንዴ ዴብ?››አለና፤ ሃሞቱ ፍስስ እንዳለ በፊት ገፅታው እያስረዳቸው፤አንከርፍፎ የያዘውን ልብስና ጫማ በቁሙ ለቆ ወለሉ ላይ ጣላቸው፡፡

በዚህ ጊዜ ዳዊትና ዳንኤል ነገሩ ገባቸውና ተያዩ፡፡ዳንኤል ቅስሙ ስብር ብሎ አንገቱን ደፋ፡፡ጨርሶ ይህን አላሰበም ነበር፡፡ይህን ባለማሰቡም ተፀፀተ፡ ፡እሱም እንደ ፍፁም ሃሞቱ የፈሰሰ መሆኑን በማቀርቀር ገለፀ፡፡

ዳዊትም በበኩሉ በሁኔታው ደንግጥ ብሏል፡፡ሆኖም ነገሩን ማቅለል እንዳለበት ተረድቶ፤‹‹ውይ ፍፄ ምን አገናኘው?ያ ሌላ ታሪክ ነው፡፡ይህ ደግሞ ልብስና ጫማ ነው፡፡ይሄ ሁሉ የለበስከው ሰልባጅስ ከዚያው አይደል የሚመጣው?››ሲለው፤ፍፁም ወደ ሌላ ድንጋጤ ተሸጋገረና፤‹‹እ?››አለና፤ ከአንገቱ ዝቅ ብሎ የለበሰውን ልብስ ተመለከተ፡፡ዳንኤል በዝምታ እንዳቀረቀረ ነው፡፡

ዳዊት የሁለቱንም ሁኔታ አይቶ ነገሩን የበለጠ ቀለል በማድረግ፤ ‹‹እም ሁሉም ከዚያ ነው የሚመጣው፡፡ስልኩ ምኑ፤ስለዚህ ምንም ማለት አይደለም ፍፄ፡፡ይህን ያመረቱት እኮ መሪዎቹ አይደሉም፡፡በጭራሽ አይገናኝም፡፡ምን ነካችሁ?ዳኒ!››ሲል ጠርቶ፤ካቀረቀረበት ቀና እንዲል አደረገውና፤‹‹ምን ሆናችኋል?ይህ እንዴት ያሳዝናችኋል?››በማለት ተቆጣቸው፡፡

በዚህ ጊዜ ዳንኤል ካቀረቀረበት ቀና ብሎ፤‹‹በእርግጥ ልክ ነህ›› ሲል ሃሳቡን ተጋራው።
‹‹ስለዚህ ፈታ በሏ!››አላቸው።
ዳንኤል የዳዊትን አቋም ሙሉ በሙሉ መጋራቱን በተጨማሪ ገለፃ እያረጋገጠ ፍፁምን ወደማፅናናት አመራ።
‹‹ፍፄ እውነት ነው፤ ቀለል አድርገው።ምንም ማለት አይደለም።በርግጥ እኔ ስገዛው ይህን አላሰብኩም ነበር።ምናልባት ማሰብ ነበረብኝ።ያን ባለማሰቤ አዝኘ ነው ያቀረቀርኩት።አሁን ግን ሳስበው ማሰብም አያስፈልገኝም ነበር።ዴቭ እንዳለው ነው፤ምንም ማለት አይደለም። በገንዘባችን የገዛነው ነው።እዚህ አገር ወደ ቡቲክ ብንሄድም የምንገዛው የእነሱን ስራት ነው።ኢትዮጵያ ራሱ የምትተዳደረው በአሜሪካ እርዳታ አይደል?ይሄ ሊያስከፋህ አይችልም።አው እኔንም ደንግጠህ አስደነገጥከኝ››
‹‹ፍፄ!››አለው ዳዊት።
‹‹አ..››አለ፤ድንዝዝ እንዳለ ነው።
‹‹እኮ በል፤ ልበስ፣ ለካ፣ ወይም መከየፍህን ቀጥል››አለው።
‹‹አ....በርግጥ ልክ ናችሁ...ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም።ግን.... አሜሪካ... ስል ነው ክው ያልኩት እሺ።አሁንም ቢሆን አልለብስም።በደንብ ላስብበት...ይቅርታ ግን ሙዳችሁን ጦለብኩት ኣ››አለና፤ሁሉንም ሸካክፎ ሻንጣው ውስጥ አስገብቶ፤በእግሩ እየገፋ ጥግ ካስያዘው በኋላ፤ብዙም ከድንዛዜው ሳይወጣ፤ነገር ግን ተረጋግቶ አጠገባቸው ተቀመጠና ወሬያቸውን መጋራት ጀመረ።
ጥቂት ከተጨዋወቱ በኋላ፤ዳዊት፤‹‹ከዚያኛው ቤት አቀባበል ወደዚችኛዋ ቤት የአቀባበል ስነስርዓት እንለፍ››ብሎ ተነስቶ፤ በጥቁር ካርቶን የታሸገ ብላክ ሌብል ውስኪ አምጥቶ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ።ከዚያም አነስተኛዋን ማቀዝቀዛ ከፍቶ በረዶና አንቦውሃ አውጥቶ አቀረበ።
ፍፁምም ብርጭቆዎችን ታጥበው ከተቀመጡበት አንስቶ በድጋሚ አጥቦ እንደ ጥሩ አስተናጋጅ እየተሽቆጠቆጠ አቀረበ።ሶስት ብርጭቆ ማቅረቡን ያየው ዳንኤል እየተገረመ፤‹‹ውስኪ ልትጠጣ ፍፄ?››አለው።
‹‹ምን ይለኛል ዳኒዬ?እንዲያውም ከእናንተ ይልቅ ውስኪ መጠጣት በኔ ሳያያምር ይቀራል?ባሉካ እኮነኝ››ሲል መለስለት።ይህን ብሎ ወደ ዳዊት እየት ሲያደርግ፤ሳይበዛ ፈቅጀልሃለሁ የሚል ፈቃድ ከፊቱ ላይ አነበበ።
‹‹ምን እንደሆነ ታቃለህ ዳኒዬ?ባሉካ ከሆንኩ ጀምሮ እንዳለ ፍሬንዶቹ የፍንጥር እያሉ የት ይወስዱኛል በየ ጃምቦ ቤቱ!እኔም በሺም አብሬ ስቀማምስ ..ገብቶገሃል...?እነሱን እየጋበዝኩ እኔ ባልጠጣና ለስላሳ ባዝዝ ቋጣሪ ምናምን ሊሉ ስለሚችሉ እያልኩ ስል ስል ቋሚ ተሰላፊ ወደመሆን....ደረጃ አልደርስም?››እያለ መተረክ ጀመረ።ዳንኤልና ዳዊት

ፍፁም ወደ አስደሳቹ ገፅታው ተመልሶ መጫወት ሲጀምር ደስ አላቸውና አፋቸውን ከፍተው እየሳቁ ሲያደምጡት ቆዩ፡፡ፍፁም ነገሩን ረስቶ ከዚያ ድንጋጤውም ወጥቶ አስቂኝ ጫወታውን ቀጥሎ ጠባቧን ቤት በጋራ ሳቅ አደመቋት፡፡

የተቀዳውን ውስኪ በጋራ አንስተው ‹‹እንኳን ደህና መጣህ››ብለው አጋጭተው መጠጣት ሲጀምሩ፤የፍፁም ፊት ጭፍግግ ሲል አዩት፡፡

‹‹ኧረ በኪዳነምረት! ውስኪ እንዲህ ነው እንዴ?››ብሎ ዳንኤል ላይ አፈጠጠ፡፡

‹‹ምነው?››አለው ዳንኤል፤ዓይን ዓይኑን እያዬ፡፡

‹‹እንዴ እኔ ቀምሸው አላውቅም፤ግን የሆነ የሻይ መልክ ስላለው እየጣፈጠ የሚገባ ነበር የሚመስለኝ፡፡በጣም መራራ አደል እንዴ?እንዳይደብራችሁ እኔ ይቅርብኝ››አለና፤የተቀዳውን በአንዴ ጭል….ጥ አድርጎ ብርጭቆውን አስቀመጠ፡፡

‹‹ፍፁም ያማሃል እንዴ? ጃንቦ መሰለህ?ውስኪ እንዲህ አይጠጣም አኬ፡፡ ደሞ ይቅርብኝ ትላለህ እንዴ?ብትጠጣስ ከዚህ በላይ ልትጠጣ ነው?ወይስ ከዚህ በላይ የመጠጣት እቅድ ነበረህ?አሁን ባንዴ የጨለጥከው እኮ ሶስት ደብል ይሆናል››ሲለው ዳዊት፤ፍፁም በሁለት ጉንጬ ሞልቶ ይዞ ለመዋጥ እየተጋለ በአንገት ውዝዋዜ እሽታውን ገልፆ እንደምንም ዋጠውና፤በፍጥነት አንቦውሃ ቀድቶ በመቸለስ አወራረደው፡፡

‹‹በስማም…በቃ ይሄ ነው ውስኪ ዴብ?››

‹‹አዎ፤ያውም ይሄ ሃሪፍ የሚባለው ውስኪ ነው፡፡ብላክ ሌብል››

‹‹ቆይ ስንት ነው የገዛህው?››

‹‹ሺ ምናምን ብር››

‹‹እ?ይሄን?አንዱን ብቻ?››

‹‹አዎ››

‹‹እንዴ….ይሄ ሁሉ ሃብታም እንዲህ እየፈጋ ውስኪ ይጠጣል የሚባለው ይሄን መሆኑ ነው?››

‹‹አዎ የሀብታም መጠጥ ነው፡፡የሀብታም የተባለውም ውድ ስለሆነና ደሃ በቀላሉ ሊገዛው ስለማይችል ነው››

‹‹ወይ ጉ….ድ!ብሎ ተውት፤ቀስ እያላችሁ ጠጡ››ካለ በኋላ መገረሙን ቀጥሎ ቆየና፤‹‹የሶስት በርሜል ድራፍት ዋጋ መሆኑ ሳይበቃ ጭራሽ እንዲህ እሬት እሬት የሚል መጠጥ?››

‹‹ስላልለመድከው ነው ፍፄ››ዳንኤል ጣልቃ ገባ፡፡

‹‹ኧረ እንኳን ያለመድኩት፡፡እንዴ ገንዘቤን አውጥቼማ እሬት አልጠጣም፡፡ ጃንቦ በስንት እጥፍ ይበልጠው የለ እንዴ!እንኳንም በጊዜ ቀምሼ ጠላሁት፡፡

በነገራችን ላይ....ይሄም ያሜረካ ነው እንዴ ዴብ?››ሲል ጠየቀና ማፌዙን ቀጠለ።‹‹ይሄን እየጠጡ ነዋ....››ብሎ ጀማምሮ ተወው።

‹‹ግዴላችሁም ዳኒ ትንሽ አረፍ በልና ምን የመሰለ ጃምቦ ቤት ወስጄ እኔ ድራፍት ልጋብዛችሁ።የደራ ጫወታ አለ።በዚያ ላይ ቺፕ ነው።ዩ ኖ ቺፕ አ ዳኒዬ?››ሲል ጠየቀው።

‹‹የስ አይ ኖ››እየሳቀ መለሰለት።

‹‹ዩ አር ኖ?››በማለትም ጥያቄውን ወደ ዳዊት አዞረ።‹‹አቤት››ሲለው፤ ‹‹አንተስ ማለት ነው ዴብዬ።ተወው አላስጨንቅህም።ፎርጌት እሽ›› አለና ቀጠለ።‹‹ከእኔ ጋር ሚሰራው ዲጄ፤ወያላዬ ማለቴ ነው ዳኒ፤መኪና አቁመን ድራፍት ልንጠጣ ስንሄድ፤ እዚያ ቤት ቺፕ ነው አይለኝ መሰለህ?ቺፕ ምንድነው? ብዬ ልጠይቀው አልኩና፤ሼም ይዞኝ ተውኩት።አስቡት እስቲ፤ ባለካ ሆኘ ቺፕ ማለት ምን ማለት ነው? ብዬ ረዳቴን ስጠይቅ!ውርደት አይሆንም?ከዛ አዎ ልክ ነህ ቺፕ ነው፤ብዬ ዝም አልኩና፤አስቤ አስቤ በራሴ ምርምር ቺፕ ማለት ርካሽ ማለት መሆኑን ደረስኩበት።መኪና አቁመን ልንገባ ስንል በእውቀት የበለጠኝ መሰለኝና፤‹‹ልክ ነህ እንዳልከው እዚህ ቤት ዋጋቸው ፌር ነው››አልኩት።‹‹እንዴ በጣም››ሲለኝ በደንብ አረጋግጬና ሌላ ከሱ የተሻለ ቃል ማወቄን ጠቀሜ...››እያለ ሲያዝናናቸው፤በዚያው ስለ ትምህርቱ ሁኔታ ተነሳ።

‹‹እየተዘጋጀህ ነህ አይደል ፍዬ፤ወይስ ሹፍርናው ገና አልሰለቸህም?››ሲል ጠየቀው ዳንኤል።

‹‹ላቀዳችሁልኝ ዕቅድ ላለመውጣት ብዬ ሳይሆን፤ያልተማረ ባሉካ ሆኖ መኖር የሆነ ሰዓት ላይ እንደሚደብር በደንብ ስለገባኝ ጭምር ትምህርቱን ልጀምር ወስኛለሁ።አሁን ይቺኛዋን እንደ እራሱ አድርጌ ከሰኞ እስከ አርብ የሚይዝልኝ ሃሪፍ ዘዋሪ እያመቻቸሁ ነው።ቅዳሜና እሁድ ራሴ እየያዝኩ ከሰኞ እስከ አርብ ወጥሬ ለመማር ተዘጋጅቻለሁ።ቅዳሜና እሁድንም ተማር ወይም አጥናበት ብትሉኝ ራሱ እስማማለሁ››ሲል በይሉኝታ ሳይሆን በትክክል መማር እንዳለበት አምኖ እንደተዘጋጀ አረጋገጠላቸው።

በዚህ አቋሙ በተለይ ዳዊት በጣም ደስ ተሰኘ።ምክንያቱም ሚኒባሷን ራሱ ሲይዛትና ሰው ሲይዛት የሚኖረውን ሰፊ የገቢ ልዩነት ስለሚያውቅ፤ያን ገቢ ላለማጣትና አሳልፎ ላለመስጠት ሲል የመማር ዕቅዱን ይሰርዘው ይሆናል ብሎ ፈርቶ ነበር።በግድና በችግር ምክንያት ያቋረጠውን ትምህርት ከሚቀጥል ይልቅ፤ እንዲህ አምኖበት ለመማር መዘጋጀቱን በዳንኤል ፊት ሲያረጋግጥ ዳዊት በውስጡ እፎይ አለ።በዚች ገለፃው ዳንኤልና ዳዊት በጣም መደሰታቸውንም ብርጭቆዎቻቸውን በማጋጨት ፊቱ ላይ አረጋገጡለት።

‹‹ምንም እንዳታስቡ!ወጥሬ ነው የምማረው!የራሴን አስጠኝ ቀጥሬ!››በማለት በድጋሚ አረጋገጠላቸውና በፍላጎቱ ቀድሞ ሲዘጋጅ እንደቆየ ገልፆ፤ አጠቃላይ የትምህርት ማስረጃዎቹን እንዳዘጋጀና መሸኛውንም አውጥቶ እንደያዘ ነገራቸው።።በዚህ ደስ መሰኘታቸውን ሲያውቅም፤የበለጠ ለማስደሰት ብድግ ብሎ ሄዶ መሳቢያውን ከፍቶ አውጥቶ አመጣና የጠቀሳቸውን የትምህርት ማስረጃዎች አሳያቸው።።

‹‹መስከረም ላይ ቀጥታ.....!››ሲላቸው ሌላ ተጨማሪ ደስታ.....

እሱን አሳይቶ መልሶ ካስቀመጠ በኋላ፤አጠገባቸው እየተቀመጠ፤‹‹እና እታስቡ ሲሪዬስ ነኝ አኬ።።ብለ....ው ዛሬ ደግሞ እንግሊዝኛ ብቻ ሆነ አሬ ላይ የሚመጣው።።አጋባህብኝ እንዴ ዳኒዬ?ለማንኛውም አታስቡ ወጥሬ ነው የምማረው ኪድዬን።።የራሴን አስጠኝ ቀጥሬ!በተለይ አስጠኝዋ ቺክ ብትሆንልኝ በስማም!በደረጃ ነበር የማልፈው።።አስጠኝ የሆኑ ቺኮች አሉ እንዴ ዴብ?››

‹‹ይኖራሉ››

‹‹እስቲ እንግዲህ....እናያለን፤የሆነች ቆንጆዬ ሴት አስጠኝ ባገኝ...ያው እሷን ሼም ስለሚይዘኝ.....ረስቸው የቆየሁትን ትምህርት ለማስታወስ ይረዳኛል.....›› እያለ አጎንብሶ ፀጉሩን እየጠቀለለ ጫወታውን ቀጥሎ በደንብ ሲያዝናናቸው ቆየ።።

አመሻሽ ላይ ደግሞ ድራፍት ካልጋበዝኳችሁ ብሎ ውስኪያቸውን በድራፍት ሊያስጠጣባቸው ወደ ጃምቦ ቤቱ ወሰዳቸውና በጋራ ሲዝናኑ አምሽተው በሳቅ እየተፍለቀለቁ ወደቤታቸው ተመለሱ።።

ዳዊትና ፍፁም ዳንኤልን ባማረና በደመቀ ሁኔታ ተቀብለው በማስተናገድ በእጅጉ አስደሰቱት።።

****

ዳንኤል ቶማስ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ሳምንታት ለአፍታ እንኳ ፈገግታው ከፊቱ ሳይጠፋ የፍፁምን ለዛ ያላቸው ጫወታዎች አፉን ከፍቶ እያዳመጠ፤በሳቅ እንዳሽካካ ነበር ያሳለፋቸው።።ፍፀምም ለሁለት ሳምንት ያህል ስራውን ትቶና ለሹፌር ሰጥቶ አብሮት እየዋለ፤አብሮት እያደረ፤ዘና ፈታ እንዲል አደረገው።።

ብቸኛው ዳንኤል ቶማስ ጨርሶ ያልጠበቀውና በህይወቱም ይገጥመኛል ብሎ አስቦት የማያውቅ የደስታ ጊዜን ለማሳለፍ ታደለ።።ወደ አዲሱ ቤቱ ልብስ ለመቀየር እንኳ ሳይሄድ በዚያች ጠባብ የቀበሌ ቤት አብሯቸው እያደረ ጥሩ ጊዜ አሳለፈ።።

ዳዊት አንዳንድ ጉዳዮችን እንደተለመደው ብቻውን መፈፀም እንደሚችል ገልፆ ዳንኤልን ለሁለት ሳምንታት ያህል ከፍፁም ጋር ዘና እንዲልና በቂ ረፍት እንዲያደርግ ፈቅዶ ለቆታል፡፡
ዳንኤል ያኔ ወደ አሜሪካ ሲመለስ አቅደውት የነበረውን ዕቅድ ዳዊት ብቻውን ሲያከናውን እንደቆየው ሁሉ፤አሁንም ቀጥሎበታል፡፡ቤቱን ከመፈለግ ጎን ለጎን ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሲያከናውን ነበር ሁለቱን ሳምንት ያሳለፈው፡፡በተነጋገሩት መሰረትም የያዙት መረጃ ከፒ እየሆነ በተለያየ ቦታ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡የሶስቱ ቤቶችም የተራራቁ መሆን እንዳለባቸው ወስነዋል፡፡
በዚህ መሰረት በዳንኤል ስም ሊገዛ የታሰበው ቀሪው ቤት ራቅ ባለ ክፍለ ከተማ ተገኝቶ ነበርና በግዢው ሂደት የግድ ዳንኤል መገኘት ሊኖርበት ሆነ፡፡ስለዚህ ዛሬም እንደሌላው ቀን እንዳያመሹ ለመንገር ለዳንኤል ደወለለት፡፡ለተከታታይ ቀናት ዳዊት ገብቶ ከተኛ በኋላ ነበር ፍፁምና ዳንኤል እያመሹ የሚመጡት፡፡ጠዋትም እነሱ ከመነሳታቸው በፊት ዳዊት ቀድሞ ስለሚወጣ አንድ ቤት አብረው እያደሩ ነገር ግን ተያይተው የማያውቁባቸው ቀናቶች የበዙ ነበሩ፡፡
‹‹እናንተ ሰዎች ዋናዎቹ የከተማዋ አውደልዳዮች የሆናችሁ ይመስለኛል››አለው ዳዊት፡፡ዳንኤል የዳዊትን ስልክ ሲያነሳ እንኳ እየሳቀ ነበርና፤‹‹ብጣም ልክ ብለሃል ዴቭ፡፡ረሳንህ አይደል?ከፍፄ ጋ ለአፍታ መለየት የህይወት መጨረሻ እስኪመስለኝ ድረስ ተወስጃለሁ፡፡አሁንም ከፍሬንዶቹ ጋር ድራፍት በጃንቦ ይዘን በፍፄ ጫወታ በሳቅ እየፈረስን እያለ ነው የደወልከው፡፡እና መጣህ?ማለቴ ቤት ነህ፤እንምጣ?››
‹‹አይ ዘና በሉ፡፡መምጣት መጥቻለሁ፡፡ግን ከመቸ ወዲህ ነው እኔ ስለመጣሁ በጊዜ የምትመጡት?››ሲለው፤
‹‹አይ....ሜቢ የደወልከው ፈልገህን ከሆነ ማለቴ ነው....››አለው ዳንኤል፡፡
‹‹ግድ የለም ዘና በሉ፡፡በእርግጥ የደወልኩት ስለ አዲሱ ቤት ልነግርህ ነው፡ ባንተ ስም ልንገዛ ያሰብነውን ቤት አይቸዋለሁ፡፡ሰፈሩም ጥሩ ነው፤ቤቱም በጣም ሃሪፍ ነው፤ትንሽ ዋጋው ወደድ ያለ ነው፤ቢሆንም መርጨዋለሁ፡፡ ስለዚህ ነገ ጠዋት አብረን መሆን ስላለብን በጊዜ እንድትገቡ ነበር የደወልኩት፡፡ምናልባትም ለተከታታይ ቀናት በግዢው ሂደት ላታስፈልግ አትቀርም፡፡በዚያ ላይ የተፈቀደልህን የረፍት ጊዜ ዛሬ ጨርሰሃል››አለው፡፡
‹‹አውቃለሁ ዴቭ ዛሬ የመጨረሻ እንደሆነ ለፍፄም እየነገርኩት ነበር፡፡ከነገ ጀምሮማ.....ያው.....ለማንኛውም ጠዋት አብረን እንሄዳለን ምንም ችግር የለም፡፡አሁንም መምጣት እንችላለን፡፡ብዙ አልራቅንም እዚያ ቤት ነን፡፡ግን ሜቢ ደክሞህ ይሆናል እንጂ ብትመጣና ጆይን ብታደርገን ደስ ይለናል፡፡ ምናልባትም ትንሽ ሳንቆይ አንቀርም የፍፄ ፍሬንዶች የመጡት አሁን

ነው።የፍንጥር እያሳቸው ስለሆነ...ቆይ ሳገናኝህ››አለና ስልኩን ለፍፁም ሰጠው።
‹‹ዴቭዬ እስህ ግን ባገሩ?ጥለንህ ጠፋን ነው ወይስ ጥለህን ጠፋህ?››ይስቃል....።
‹‹ቆይ አንተ ልጅ ግን ዓመቱን ሙሉ ነው እንዴ የፍንጥር የምትለው?ወይስ ለፍንጥር አገልግሎት ብቻ ነው ሚኒባሱን የገዛህው?››
‹‹ምን ላድርግ ዴቭ?ወይ ሰብሰብ ብለው አይመጡ፤እንዲሁ እየተንጠባጠቡ ዛሬ ድረስ የፍንጥር!አንዱ መንገድ ላይ ሲያገኘኝ፤የፍንጥር ብሎ ሲቀጥረኝ፤በሺም ስሄድ፤ሌላው ተራ ቦታ እኛስ አይደርሰንም እንዴ የፍንጥሩ? እያለ ሲለኝ፤አንዱ ታስሮ ቆይቶ ተፈትቶ የኛስ ድርሻ? ሲለኝ፤ በቃ ተዝረክርከው እየመጡ እኔንም አዝረከረኩኝ እኮ ዴቭዬ፤ዛሬ ግን የመጨረሻ ነው ኪድዬን፤ከዚህ በኋላ ለመጣ አያገባኝም!ድንኳን ከፈረሰ በኋላ? እያልኩ ነው ላሽ የምለው››እያለ ሃሪፍ ሙድ ላይ መሆናቸውን ገልፆ፤‹‹የመጨረሻ ነውና ተቀሳቀለን›› ብሎ ተማፀነው።
ዳዊት ድካሙን ረስቶ፤መሄድ እንዳለበት ወስነና፤‹‹መጣሁ››ብሎት ስልኩን ዘጋ።
ከምንም በላይ የዳንኤልን ፈገግታና ሳቅ፤ደስታና ሃሴት ማየት ይበልጥብኛል!በማለት ደስ እያለው ሄዶ ተቀላቀላቸው።
በተደሳቹ ደስታ ከተደሳቹ በላይ መደሰት መቻል በእርግጥም መታደል ነው።ስለዚህ መታደሉን እያሰበ እነሱ ወዳሉበት ቦታ አምርቶ አጠገባቸው ተቀምጦ የፍፁምንና የዳንኤልን ሁኔታ እየና፤‹‹ታድዬ››ሲል ተደመጠ።
‹‹አቤት?ማነው ታዴ?››አለው ፍፁም።
‹‹ታዴ አላልኩም።ታድዬ ነው ያልኩት››ሲል መለሰለት።
‹‹ኦኬ፤እንደርስታንድ ብሮ››አለ ፍፁም።‹‹ታቃለህ ከዳኒ ጋር ውዬ እያደርኩ አማርኛን ርስ...ት አርጌዋለሁ!ዩ ኖ ዋት?ሜቢ አምሃሪክ እንዳይቀየመኝ መጠንቀቅ ይኖርብኛል ያ››ሲለው፤ዳዊት የፍፁምን ፍሬንዶች አፍሮ አቀርቅሮ መሳቅ ጀመረ።ፍፁም የዳዊትን ጀርባ ቸብ ቸብ እያደረገ፤‹‹ዶንች ወሪ ማይ ብሮ አይ ዊል ባክ ቱ ማይ አምሃሪክ ኦኬ››ብሎ በመጨመር እንዳቀረቀረ እንዲቀር አደረገው።‹‹ዚስ ማች ብሪሊየንት ሆኛለሁ።አስበው በሁለት ሳምንት ብቻ››አለና አስተናጋጅ ለመጥራት እጨበጨበ።የፍፁም ጓደኞች ሁሉም ማለት ይቻላል እንደሱ ፎጋሪና ተጫዋች ናቸው።
ፍፁም ለጓደኞቹ ዳንኤልን ያስተዋወቀው ውጪ አገር ያለችው የእክስቱ ባል እንደሆነ አድርጎ ነው።ባሉካ የሆነውም በእክስቱ አማካኝነት እንደሆነ ነው የሚያውቁት።
ዳንኤል ዳዊትን ከመጤፍ ሳይቆጥር በማይቆራረጠው አስቂኝ የጋራ ጫወታ ማብቂያ የሌለው በሚመስል ሳቅ ይፍለቀለቃል።

ዳዊት ይህን ሲያይ፤ለዳንኤል ትክክለኛና እውነተኛ ወንድም መሆን የሚችለው ፍፁም ብቻ ነው!ሲል አሰበ፡፡መሆን በመቻሉም በጣም ተደሰተ፡፡ ድካሙን ረስቶም ደስታቸውን ሲጋራ አመሸ፡፡ስምን እያመሹ እንደሚገቡም በደንብ ገባው፡፡

በመጨረሻ በጣም ሊመሽ ሆነና የፍፁምን ጓደኞች ተሰናብተው፤በሳቅ ብዛት ደክክመው ገብተው ተኙ፡፡

በማግስቱ ሁሉም ወደየ ተግባራቸው መሰማራት ነበረባቸው፡፡ሶስተኛውን ሳምንት በተለይ ከፍፁም ጋር ብዙም ሳይገናኙ ነበር ያሳለፉት፡፡

በእነ ዳዊት በኩል ያለው የቤት ጉዳይ አልቆ በዳንኤል ስም ሲ.ኤም.ሲ አካባቢ ራሱን የቻለ ጊቢ ያለው ቤት መግዛት ተቻለ፡፡

ዳንኤልም ከፊል ገንዘቡን መንዝሮ ባንክ በስሙ አስገብቶ፣ መያዝ ያለበትን በጥሬው ይዞ፣ ማድረግ ያለበትን ነገር በሙሉ ለማድረግ የሚያስችለውን ህጋዊ ሰነዶች አሟልቶ ይዞ፤ንፁህ ኢትዮጵያዊነቱን አረጋግጦ አፎይ አለ፡፡ እነዚህን ነገሮች ከፈፀሙ በኋላ ዳንኤል በመጣ በአራተኛው ሳምንት ወደ ሌላ ቀጣይ ተግባር ተሸጋገሩ፡፡

ዳዊት፤የሚሆነው አይታወቅምና መደረግ ያለበትን ቀጣይ ተግባር ከመቀጠል ወደ ኋላ መባል እንደሌለበትና መዘናጋት እንደማያስፈልግ በጥብቅ አስገነዘባቸው፡፡

«ዓላማችንን ዳር እስክናደርስ ድረስ መጠንቀቅ አለብን፡፡ሌላው ቀርቶ ለተወሰነ ጊዜ በአንድ ቦታ ሁላችንም መገኘት ላይኖርብን ይችላል፡፡ መሰብሰባችን በዚህ መልኩ ቀጥሎ ብዙ ከቆዬ የብዙዎችን ትኩረት መሳባችን አይቀርም፡፡እንኳን ምክንያት ኖሮን እንዲሁ ምክንያት ባይኖረን እንኳ ስብስባችንና አካሄዳችን እንዲሁ ጥያቄ ፈጥሮ...ቆይ እነዚህ ሰዎች....;መባሉ አይቀርም፡፡ከሰፈር እስከ ክፍለ ከተማ››ሲላቸው፤‹‹ልክ ነህ፤ተረድቸሃለሁ ዴቭ››በማለት ዳንኤል አስተሳሰቡን አድንቆ ተቀበለው፡፡

‹‹ገብቶሃል ፍዌ››

‹‹ብጣም ዴቭ››

‹‹ስለዚህ ፍዌ የተወሰነ ጊዜ እዚህ ትኖራለህ፡፡ቤትህ እንደተከራዬ ይቆይና ከፈለግህ ትምህርቱን ከጀመርክ በኋላ ቤትህ መኖር መጀመር ትችላለህ፡፡ እኔ በ ሲ.ኤም.ሲው ቤት እኖራለሁ፡፡ዳኒ መካኒሳ ትቆያለህ፡፡መረጃዎቹ ኮፒ እየሆኑ እዚህም፤ዳኒ ቤትም፤እኔ ጋርም ይቀመጣሉ፡፡ለተወሰነ ጊዜ ባንፈልገው እንኳ ተነጣጥለን መቆየት ነው ያለብን፡፡በፈለግን ሰዓት ተደዋውለን መገናኘትና ወደ ፈለግነው ቤት መሄድ እንችላለን ገባችሁ?››

‹‹ገብቶናል››አሉ በአንድነት፡፡

‹ፍዌ ነገ ጠዋት ይሄን ይዘህ ወደ መካኒሳ ከዳኒ ጋር ትሄዳለህ፡፡ዳኒ እነዚህን ዶክመንቶችና ዋናውን ሃርድ ዲስክ ይዘህ ሂድና ቤት

ዳዊት ይህን ሲያይ፣ለዳንኤል ትክክለኛና እውነተኛ ወንድም መሆን የሚችለው ፍፁም ብቻ ነው!ሲል አሰበ።መሆን በመቻሉም በጣም ተደሰተ። ድካሙን ረስቶም ደስታቸውን ሲጋራ አመሸ።ለምን እያመሹ እንደሚገቡም በደንብ ገባው።

በመጨረሻ በጣም ሲመሽ ሆነና የፍፁምን ጓደኞች ተሰናብተው፣በሳቅ ብዛት ደክክመው ገብተው ተኙ።

በማግስቱ ሁሉም ወደየ ተግባራቸው መሰማራት ነበረባቸው።ለስተኛውን ሳምንት በተለይ ከፍፁም ጋር ብዙም ሳይገናኙ ነበር ያሳለፉት።

በእነ ዳዊት በኩል ያለው የቤት ጉዳይ አልቆ በዳንኤል ስም ሲ.ኤም.ሲ አካባቢ ራሱን የቻለ ጊቢ ያለው ቤት መግዛት ተቻለ።

ዳንኤልም ከፊል ገንዘቡን መንዝሮ ባንክ በስሙ አስገብቶ፣ መያዝ ያለበትን በጥሬው ይዞ፣ ማድረግ ያለበትን ነገር በሙሉ ለማድረግ የሚያስችለውን ህጋዊ ሰነዶች አሟልቶ ይዞ፣ንፁህ ኢትዮጵያዊነቱን አረጋግጦ እፎይ አለ። እነዚህን ነገሮች ከፈፀሙ በኋላ ዳንኤል በመጣ በአራተኛው ሳምንት ወደ ሌላ ቀጣይ ተግባር ተሸጋገሩ።

ዳዊት፣የሚሆነው አይታወቅምና መደረግ ያለበትን ቀጣይ ተግባር ከመቀጠል ወደ ኋላ መባል እንደሌለበትና መዘናጋት እንደማያስፈልግ በጥብቅ አስገነዘባቸው።

‹‹ዓላማችንን ዳር እስክናደርስ ድረስ መጠንቀቅ አለብን።ሌላው ቀርቶ ለተወሰነ ጊዜ በአንድ ቦታ ሁላችንም መገኘት ላይኖርብን ይችላል። መሰብሰባችን በዚህ መልኩ ቀጥሎ ብዙ ከቆዬ የብዙዎችን ትኩረት መሳባችን አይቀርም።እንኳን ምክንያት ኖሮን እንዲሁ ምክንያት ባይኖረን እንኳ ስብሰባችንና አካሄዳችን እንዲሁ ጥያቄ ፈጥሮ...ቆይ እነዚህ ሰዎች....;መባሉ አይቀርም።ከሰፈር እስከ ክፍለ ከተማ››ሲላቸው፣‹‹ልክ ነህ፣ተረድቸሃለሁ ዴቭ››በማለት ዳንኤል አስተሳሰቡን አድንቆ ተቀበለው።

‹‹ገብቶሃል ፍፄ››

‹‹ብጣም ዴቭ››

‹‹ስለዚህ ፍፄ የተወሰነ ጊዜ እዚህ ትኖራለህ።ቤትህ እንደተከራዬ ይቆይና ከፈለግህ ትምህርቱን ከጀመርክ በኋላ ቤትህ መኖር መጀመር ትችላለህ። እኔ በ ሲ.ኤም.ሲው ቤት እኖራለሁ።ዳኒ መካኒሳ ትቆያለህ።መረጃዎቹ ኮፒ እየሆኑ እዚህም፣ዳኒ ቤትም፣እኔ ጋርም ይቀመጣሉ።ለተወሰነ ጊዜ ባንፈልገው እንኳ ተነጣጥለን መቆየት ነው ያለብን።በፈለግን ሰዓት ተደዋውለን መገናኘትና ወደ ፈለግነው ቤት መሄድ እንችላለን ገባችሁ?››

‹‹ገብቶናል››አሉ በአንድነት።

‹‹ፍፄ ነገ ጠዋት ይሄን ይዘህ ወደ መካኒሳ ከዳኒ ጋር ትሄዳለህ።ዳኒ እነዚህን ዶክመንቶችና ዋናውን ሃርድ ዲስክ ይዘህ ሂድና ቤት

አስቀምጣቸው፡፡የተወሰነ መጻህፍት ይዘህ ሂድና እያነበብክ፣ እዚያው አካባቢ ወጣ ገባ እያልክ፣በቂ ረፍት አድርግ፡፡ከደበረህ ዕዮንንም ፍጺንም መጥራት ትችላለህ፡፡ፍጼ ይህን ካደረግህ በኋላ ወደዚህ ትመጣና ይቺን ሻንጣ ወደ ሲ ኤም ሲው ቤት ይዘን እንሄዳለን፡፡ከዚያ በኋላ ፍጼ እዚህ ሆነህ እዚህ የሚቀመጠውን ኮፒ የተደረገ ፋይል ትጠብቃለህ ግልፅ ነው?››

‹‹ግልፅ ነው ዴቭዬ››

‹‹መረጃዎቹን ቦታ ቦታ ካስያዝንና መደረግ ያለበትን ካደረግን በኋላ እንዳሻን መሆን እንችላለን፡፡እስከዚያ ድረስ ግን የግድ በተንተን ማለት አለብን››በማለት አስረድቶ ከሳመናቸው በኋላ፤ ተነጋግረው ያደሩትን በማግስቱ ተግባራዊ ማድረግ ጀመሩ፡፡

ለተከታታይ ቀናቶች በየእለቱ ስድስት ኪሎ እየተገናኙ ነገር ግን ዳንኤልና ዳዊት ምሽት ላይ ወደየቤታቸው እየሄዱ እያደሩ የቪዲዮ መረጃዎችን ኮፒ እያደረጉ ተከፋፍለው በተለያየና በተራራቀ ቤታቸው ሲያስቀምጡ ቆዩ፡፡

ዳዊትም መውሰድ ያለበትን አልባሳት ወስዶ ጨረሰ፡፡ቤቱ ውስጥ የቀረው በየጊዜው ፕሪንት እያደረገ ያወጣቸው የነበሩና ጠረጴዛው ስር ተከምረው ያሉ የመረጃው አንድ አካል የሆኑ ወረቀቶች፤የመፃህፍት መደርደሪያውና መጻሕፍቱ ብቻ ነበሩ፡፡ግማሾቹን መፃህፍት ደግሞ እየመራረጠ ለዳንኤል ሊያካፍለው አስቧል፡፡ይህን ለማድረግ ተስማምተው፣ከዚያ በፊት ግን የቀጠሩትን ሰው ሊያገኙ ወስኑና ዕሮብ ማለዳ ዳዊትና ዳንኤል ወደ ስድስት ኪሎ መጡ፡፡ፍፁምንም ስራ አስቀርተው እንዲጠብቃቸው አደረጉ፡፡

ዳንኤልና ዳዊት ይህን መረጃ እነሱ ይፋ እያደረጉበት ካለው ዘዴ ባለፈ፤ ቪዲዮውን ይዘው ቁጭ ማለት እንደሌለባቸው ተረድተው አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው ተነጋግረው ወስነው ነበር፡፡

በቀጥታ በግለሰብ ደረጃ መልቀቁ ጥሩ አለመሆኑን ተገንዝበውም ከተቻለ በአንድ የሐይማኖት ተቋም እማካኝነት አሊያም በሌላ መንገድ ቢለቀቅ የተሻለ እንደሚሆን አምነዋል፡፡በሆነ መንገድ ለሆነ አካል ተሰጥቶ ይፋ መሆን የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዳለባቸው ከወሰኑ በኋላም ይሆናል ያሉትን ሰው መርጠው ጠርተዋል፡፡ይሆናል የተባለውን ሰው የመረጠው ዳዊት ነበር፡፡

‹‹ብጣም የማምነውና የማውቀው አንድ ቅዱስ ሰው አለ፡፡ዲያቆን ነው፡፡እዚህ ኪዳነምህረት ያገለግላል፡፡እንደሌሎቹ አይነት ለሆዱ ያደረና አስመሳይ ያልሆነ የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡ፍፁምም ያውቀዋል፡፡ይህን ዲያቆን ጠርተን ቪዲዮውን እናሳየውና ምን እናድርግ? የሚል ጥያቄ እናቅርብለት፡፡እቅዳችንንም እናካፍለው፡፡ምናልባት በጥሩ ሁኔታ ሊረዳን ይችላል፡፡ምክንያቱም የትኛው የቤተክህነት ሰው ቅዱስና ትክክለኛ፣ የትኛው

ፍሥሐ ያዜ

አስመሳይና ሆዳም እንደሆነ ለይቶ የሚያውቅ የበሰለና አስተዋይ ሰው ነው፡
፡አውቀቱም ምርጥ የሚባል ነው፡፡ቲዮሎጂ ተምሯል፡፡በጣም ሀቀኛ ነው፡፡
ምናልባት…››ሲል፤ዳንኤል ደንገጥ ብሎ፤
‹‹እንዴ?እንዴት?ታምነዋለህ?››ነበር ያለው፡፡
‹‹ከራሴ በላይ አምነዋለሁ!››ሲል መለሰ ዳዊት፡፡
‹‹ከራሴ በላይ?! ዋው አንተ እንዲህ ካልክና እንዲህ ከገለፅከው የማልስማማበት ምንም ምክንያት የለም!ከራስህ በላይ?››
‹‹አዎን!ከራሴ በላይ!በጣም አብሮ አደግ የነበርንና ብዙ ነገር ሳለፍን በጥልቅ የማውቀው ቅዱስ ክርስቲያን ነው!ወይም ነበር፡፡እንግዲህ ሰው…››
‹‹ብቃ፡፡ይህ በጣም የተሻለና ጥሩ የሆነ ሃሳብ ነው ዴቭ››
‹‹አዎ!ለሱ መንገር ነው››ሲል ጣልቃ ገባ ፍፁም፡፡
‹‹ፍፄም ታምነበታለህ?››ጠየቀ ዳንኤል፡፡
‹‹እጅግ በጣም ዳኒዬ››
‹‹ዋው በጣም ደስ ይላል፤ተስማማሁ››
በዚህ አይነት ሁሉም ተስማምተው ነበርና ዲያቆን ይሆናልን ዳዊት በአካል አግኝቶ አነጋግሮ፤ ዕሮብ ረፋድ ላይ ቤት ሲመጣ ቀጠሮ ይዘው ነበር የቆዩት፡፡

የዚያው ሰፈር ልጅ የሆነው ዲያቆን ይሆናል ፍፁምንና ዳዊትን በቅርብ ይወቃቸው እንጂ፤ስለ ዳንኤል ምንም አይነት ፍንጭ የለውም፡፡ዳዊትም ስለ ዳንኤል የገለፀለት ነገር የለም፡፡ቪዲዮውን እሱ እንዳመጣውም አያውቅም፡፡ እንዲሁ ግን መረጃው የወጣው ከኋይት ሃውስ እንደሆነና በአንድ ወዳጁ አማካኝነት እንደደረሰው፤ ለህዝቡ ይፋ የሚሆንበትን ሁኔታ እንዲያመቻች የቤት ስራ ተብሎ እንደተሰጠው ነግሮ፤ሁሉንም ተንትኖ አስረድቶ ነው ወደ ቤት እንዲመጣ የቀጠረው፡፡

ዲያቆን ይሆናል የቀጠሮውን ሰዓት አክብሮ ከቀኑ 5 ሰዓት ላይ ወደ ስድስት ኪሎዋ የዳዊት ቤት መጣ፡፡እንደመጣም ያችን ጠባብ ቤት ጥርቅም አድርገው ዘግተው፤በአንድ ሃርድ ዲስክ አዘጋጅተው የጠበቁትን ቪዲዮ ከፈቱለትና በጋራ ሲመለከቱ ዋሉ፡፡የጠባቧ ቤት በር ከውስጥ በኩል ተቆልፏል፡፡ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይደለምና ብርሃን የሚያስገቡ የበርና የመስኮት ቀዳዳዎች ሳይቀሩ በጨርቃጨርቅ ተደፋፍነዋል፡፡ይህ አይነቱ ጥንቃቄ በፍፁም ፍርሃትና ድንጋጤ ምክንያት የሚደረግና የተደረገ እንጂ እንደማንኛውም የእንግሊዝኛ ፊልም በር ከፍተው እንዲሁ መከታተል ይችሉ ነበር፡፡ይህን ግን ፍፁም ጨርሶ አይፈቅድም፡፡ፍፁም ከዚህም አልፎ ትልቁ የልብስ ቁምሳጥንም እየተጎተተ መጥቶ በሩ ላይ ይቁም ይለጠፍ ባይ ነው፡፡ይህ ብቻ አይደለም፤ትዕይንቱን በዓይናቸው፤ድምፁን በጆሮ ማዳማጫ እየሰሙ ቪዲዮውን ቢያዩ የተሻለ እንደሚሆንም ከድንጉጡ

ፍፁም በኩል ሃሳብ ቀርቦ ነበር።ሆኖም ትዕይንተ መስኮቱ ለሁሉም የሚሆን የጆሮ ማዳመጫ መሰኪያ የለውምና በሩን ጠርቅመው ዘግተው ድምፁ እንዳይወጣና እንዳይሰማ በጣም ቀንሰው ሊከታተሉ ተገደዱ።

New York Novemeber 12/2014

‹‹ትልቅ የጥበብ ፀጋን ወደተጎናፀፋችሁባት፣የሉሲፌል ዋና መቀመጫ ከተማ ወደሆነችው፣ ወደ ታላቋ ከተማችን ወደ ኒዮርክ እንኳን በሰላም መጣችሁ ክቡራን!››ሲሉ ጀመሩ።

ይህ አዳራሽ እንደሌሎቹ ዝግ ጉባኤ እንደሚካሄድባቸው አዳራሾች አይደለም።እጅግ ግዙፍና ከሁሉም አገራት አዳራሾች በእጥፍ የሚሰፋ ነው፡ ፡ይሁን እንጂ በአይነትና በቅርፁ፣በመድረክ አቀማመጡና በቀለሙ ከሌሎች አዳራሾች ጋር ተመሳሳይ ነው።

ተሰብሳቢዎቹ የ G 20 አገራት መሪዎች በዚያው ቀይ ልብሳቸው እንደደመቁ ውጭና ውስጣቸውን አብርተው ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቆመዋል።እንዳትተነፈሱ የተባለ ይመስል አዳራሹ ፀጥ እረጭ ብሏል።

ከአዳራሹ ፊት ለፊት ካለው ሰፊ መድረክ ላይ፤በስተግራ ስድስት፣መካከል ላይ ስድስት፣በስተቀኝ ስድስት፣ ህፃናት ሙሉ ሆኖ ወጥ የሆነ ስስና ቀይ ቀሚስ ለብሰው በፀጥታ ቆመዋል።የቆሙት ከመድረኩ ግድግዳ አቅራቢያ ተጠግተው ነው።ከህፃናቱ ፊት ደግሞ የቫቲካኑ ጳጳስና ንግስቲቱ ከመድረኩ ዳርና ዳር ሆነው ፊት ለፊት እየተያዩ በፀጥታ ቆመዋል።በዚህ አይነት ሁኔታ ለረጅም ደቂቃ ከቆዩ በኋላ፤ንግስቲቱ ቆመው ባሉበት ቦታ በርከክ ሲሉ፤ጳጳሱም ለተሰብሳቢዎች ምልክት ሰጥተው በርከክ አሉ።ወዲያውም ሁሉም ተሰብሳቢዎች በያሉበት ተንበረከኩ።ዝምታው እንደቀጠለ ቆዩ። ረዘም ካሉ ደቂቃዎች በኋላ፤ንግስቲቱ ተነስተው ጳጳሱንም ሌሎችንም በምልክት አስነሱና፤የፀሎት ሰዓት መሆኑን ገለፀው፤ፕሮግራሙን ጳጳሱ እንዲያስጀምሩ በምልክት አዘዟቸው።ጳጳሱም አዳራሹን ባርከው የፀሎት ፕሮግራሙን አስጀመሩ።

የጋራ ፀሎቱም እንደተለመደው ቀስ ተብሎ ተጀምሮ፤ በእስፈሪ ጩኸትና በከፍተኛ ድንፋታ ታጅቦ ቀጠለ።አዳራሹ በጋራ ጩኸት ተናጠ። በእንግሊዝኛና በስፓኒሽ ቋንቋ የሚደረገው ፀሎት ድብልቅልቅ ያለና ለመተርጎም የሚቸግር ነው።

ለረጅም ደቂቃዎች የቆየው ቅጥ ያጣና ያልተለመደ የሰውነት እንቅስቃሴ የታከለበት ፀሎት፤ቀስ እያለ እየጋለ እየተጋጋለ ሄዶ ተሰብሳቢዎችን በየወለሉ እስከማንከባለል የደረሰ ሆነ።እንደ ባሌ ዳንስ እየተሽከረከሩ፣ ሰውነቶቻቸውን እያውረገረጉ፣ እያቃሰቱ፣በየመሃሉም ‹‹አሜን!›› የሚለውን

ቃል በከፍተኛ ድምፅ እያሰሙ ቀጠሉ፡፡በስተመጨረሻ በድንፋታ በተሞላው ፀሎታቸው መሃል፣ ንግስቲቱ ጫን ጫን እየተነፈሱ ‹‹አሜን! አሜን! አሜን!›› ሲሉ ቆዩና፤ድንገት ድምፃቸውን ቀዝቀዝ አድርገው ሁለት እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ሲቆሙ፤የቫቲካኑ ጳጳስም በተመሳሳይ ሁለት እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ቀጥ ብለው ቆሙ፡፡በዚህ ጊዜ በጩኸትና በድንፋታ ራሳቸውን የሳቱ እስኪመስሉ ድረስ ሲወራጩና ሲንከባለሉ የነበሩ ተሰብሳቢዎች በሙሉ ላበታቸውን እየጠራረጉ፣ በላይ በላይ እየተነፈሱ፣ በየቦታቸው ቀጥ ብለው ቆመው የንግስቲቱን ቀጣይ ትእዛዝ መጠባበቅ ጀመሩ፡፡ንግስቲቱ፤

‹‹ክብር ለልዑላችን!››አሉ፤ ዓይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ፡፡ ‹‹አምን!ክብር ለልዑሉ!ክብር ለአሸናፊያችን ለሳጥናኤል!ክብር ለባለድሉ!››ሲሉ፤እንደ ወታደር በተጠንቀቅ የቆሙ ተሰብሳቢዎች ‹‹አሜን!አሜን!አሜን!አሜን!››እያሉ ሲያጅቧቸው ብዙ ጊዜ ወሰዱ፡፡ይህ ሁሉ ሲሆን የሩሲያው መሪ እንዲሁ ቆመው ከመታዘብ ሌላ፣ መንከባለል፣ መንፈራገጥ፣ መዳጨር፣ መንዘፍዘፍ፣ መንቀጥቀጥ፣ መወራጨት፣ ብሎ ነገር አልነበረም፡፡ለምን ይሆን ንግስቲቱም ሆኑ ጳጳሱ ዝም ያሏቸው?ግራ ያጋባል፡፡እነሱ እንዲያ ሲሆኑ፤የሩሲያው መሪ ግን፣ ቶሎ ወደዋናው ነጥብ ግቡና ሰምቸና አይቸ ልሂድ አይነት አቋም የያዙ መስለው እየተቁነጠነጡ ፀሎታቸውን እያከኩ ነው የሚታዩትት፡፡ የሚገርመው ግን ውስጥና ውጫቸውን አብርተዋል፡፡ቡድኑን የተቀላቀሉት ለስለላ ብቻ ይሆን?የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡እዚህ ድረስ ተኪዶ መሰለል ደግሞ ከባድ ይመስላል፡፡ ለማንኛውም ፀሎቱ/ፀሎት ብሎ መግለፅ ቢከብድም/ተጠናቆ ወደ ዘግናኙ የመስዋዕት ፕሮግራም ታለፈ፡፡

‹‹ውስጣችሁን እንዳበራችሁና እንደቆማችሁ በፀጥታ ሁኑና ልዑላችንን በመስዋዕት የምናመልክበትን ፕሮግራም እንጀምር›› አሉ ጳጳሱ፡፡አዳራሹ መልሶ ፀጥ አለ፡፡

ንግስቲቱ ቀጠሉ፡፡‹‹ልዑል ሆይ፣ ሁሉን የምትችል! ባለድላችን! በዚሁ መድረክ የጥበብ ፀጋ አጎናፅፈህ በሹመት ያስደሰትካቸው ታዛገሮችህ፣ በዚሁ መድረክ የሚገባህን መስዋዕት ለማቅረብ ዝግጁ ናቸው፡፡ሁሉን ትሰጠናለህና፤ሁሉን እንሰጥሃለን!ትታዘዘናለህና እንትዛዝሃለን! መስዋዕትህን ትቀበለን ዘንድ ይገባሃልና፤መልካም ፈቃድህን አሳየን....››እያሉ ከለቅሶ ጋር በተቀላቀለ ረጅም የተማፅኖ ድምፅ ውስጥ ሆነው ብዙ ለፈለፉ፤ብዙ ጮሁ፡፡

ንግስቲቱ ይህን ብለው አንገታቸውን ወደ ታች ቀልበስ፣ ከወገባቸውም ጎንበስ በማለት፤ ጉልበታቸውን ሸብረክ አድርገው ተንበረከኩ፡፡ጳጳሱም በተመሳሳይ ከወዲያኛው ጥግ በኩል ሆነው ልክ እንደ ንግስቲቱ

ተንበርክከው በግንባራቸው ወለሉ ላይ ተደፉ፡፡ተሰብሳቢዎቹም በያሉበት እነሱን መሰሉ፡፡ለመስዋዕትነት የተሰለፉት ህፃናት ግን ምንም አይነት ድምፅ አላሰሙም፡፡ምንም አይነት እንቅስቃሴ አላሳዩም፡፡እንዲሁ ቆመው ዓይኖቻቸውን ብቻ ርግብ ርግብ እያደረጉ ነው የሚታዩት፡፡

እንዲህ ሆነው በፀጥታ ጥቂት እንደቆዩ ያ ሰው መሰል ግዙፍ ዘንዶ ድንገት ከጣራው በኩል ስፍፍፍፍ...እያለ መጣና የአዳራሹ መድረክ ላይ እግሮቹን አሳርፎ ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡

ሰው መሰሉ ግዙፍ ዘንዶ በአዳራሹ መድረክ ከህፃናቶቹ ፊት ለፊት ሁለት እግሮቹን ወለሉ ላይ ሲያሳርፍ፤ ያ ግዙፍና ክብ አዳራሽ ሊናድ እንደደረሰ ህንፃ ተንቀጠቀጠ፡፡ከከባድ ድምፅ ጋር የመጣው ግዙፍ አካል፤ መጥቶ ሲያርፍና አዳራሹን ሲያንቃንቀው ከህፃናቱ ውስጥም ሆነ ከተሰብሳቢዎች በኩል አንዳችም የመበርገግና የመደንገጥ ምልክት አልተስተዋለም፡፡ ፀጥ እንዳሉ ነበር የቆዩት፡፡

አስፈሪው ሰው መሰል ዘንዶ የመድረኩ ወለል ላይ ካረፈ በኋላ፤ከወደ ጀርባው አካባቢ አንዳች እንግዳ ነገር ተመዝዞ ወጣና ወንበር ሆኖለት ጉልበቶቹን እጥፍ አድርጎ ለመቀመጥ ቻለ፡፡

እንደተቀመጠም፤‹‹መስዋዕታችሁን አምጡ!›› በማለት በጠራ እንግሊዝኛ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ድምፁም ሆነ የአነጋገሩ ዘዬ፤እንዲሁም የአስተዛዘዙ አይነት ጨምለቅለቅ ያለና ግብረገብነት ያልታከለበት ነው፡፡ ‹‹አቅርቡ! አቅርቡና እኔን አክብራችሁ አባቴን አክብሩ!ልዑላችሁ ሲከበር ነው እናንተ የምትከብሩትና የምትከበሩት!አምጡ....!››አለ በዚያ ጨምላቃ አንደበቱ፡፡

በዚህ ጊዜ እርድ የናፈቃቸው የሚመስሉት ጳጳስ ከተደፉበት ቀና አሉና በፈገግታ ደምቀው በፈጣን እርምጃ በግራ በኩል ተሰልፈው ወዳሉት ስድስት ህፃናት አመሩ፡፡ንግስቲቱም በተመሳሳይ ቀና ብለው ከጳጳሱ እኩል እተራመዱ በስተቀኝ በኩል ተሰልፈው ወዳሉት ህፃናት አመሩ፡፡መሃል ላይ ተሰልፈው የቆሙት ህፃናት ግን ባሉበት ቆዩ፡፡

ጳጳሱና ንግስቲቱ ህፃናቱን እንደተሰለፉ እየጎተቱ አመጡና በጌታቸው ግራና ቀኝ አስጠጉ፡፡ከዚያም እኩል ዝቅ በማለት ጌታቸውን እጅ ከነሱ በኋላ ቀና አሉ፡፡ያ ግዙፍ ዘንዶ መሰል ፍጥረት እነዚያን የዘንዶ ቆዳ የለበሱ ነገር ግን የሰው አይነት የሆኑ ረጃጅም እጆቹን ድንገት ግራና ቀኝ ዘረጋቸው፡፡ሁለት ጎራዴ ጎራዴ የሚያካክሉ ስለታምና አብረቅራቂ ቢላዋ የመሰሉ ጨቤዎችን ለማቀበል ነበር የዘረጋቸው፡፡

ጳጳሱና ንግስቲቱ እኩል ወደ አስፈሪው ረጅም እጅ ግራና ቀኝ ጠጋ በማለት ስለቶቹን ተቀበሉት፡፡በዚሁ ቅፅበት ከአስፈሪው ፍጡር ፊት ጥቁር ደመና የመሰለው ጭስ ድንገት ተከሰተና መልሶ ጠፋ፡፡ሲጠፋ ከፊት ለፊታቸው

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

በጣም ሰፊ የሆነ ቀይ በርሜል የመሰለ እቃ ተቀምጦ ታዬ።። ‹‹ጀምሩ!››ሲላቸው፤
ንግስቲቱ በግራ በኩል ጀመሩ።።
ዝቅ ብለው በአንድ እጃቸው የህፃናቱን ጭንቅላት ይዘው በሃይል ቀና እያደረጉ በፍጥነትና በአንድ በአንድ ስንዝር ሸክ፣ ሸክ፣ ሸክ፣ እያደረጉ አንገታቸውን ሙሉ ለሙሉ አርደው ቆርጠው በመጣል እግሮቹ ስር መደርደር ጀመሩ።።ጭንቅላታቸውን እየቆረጡ ፊቱ ላይ ሲደረድሩለትም፤ ጎን ለጎን ከአንገት በታች ያለውን በድን ከፊቱ ከተቀመጠው ግዙፍ ቀይ በርሜል ውስጥ ከነቀይ ቀሚሳቸው ይከትቱ ነበር።።ንግስቲቱ ስድስቱንም ህፃናት አርደው ጨረሱና በድናቸውን በርሜሉ ውስጥ ከትተው፣ በፈገግታ ተውጠው፣ አጠገቡ ቆሙ።።
ጳጳሱ ተራቸው ደረሰና በተመሳሳይ ፍጥነትና ሁኔታ እነዚያን ህፃናት አንገታቸውን እየቆለመሙ ማረዳቸውን ቀጠሉ።።ዝም ያሉና የሚያሳዝኑ ቆንጆ ቆንጆ የፈረንጅ ህፃናት ዓይናቸው እንደፈጠጠና እንዲሁ በዝምታ እንደተዋጡ አንገታቸውን ሰጡ።።ታረዱ! ጭንቅላታቸውም ለዚያ አስፈሪ ዘንዶና ሰው መሰል ፍጡር ተደረደረለት፣ በድናቸው ከነልብሳቸው በርሜሉ ውስጥ ገባለት።።
አስፈሪው ፍጡር፤‹‹ወደዚህ ኑ ሹማምንት!!››አለ ጉሪ በመሰለ ሌላ አይነት ድምፅ።።
20ዎቹ መሪዎች ወደ መድረኩ ሄዱ።።‹‹ቀጥሉ!››አላቸው።።
የአሜሪካው መሪ ዘና ብሎ ለሌሎቹ መሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው በቃላትም፣ በምልክትም፣ በተግባርም፣ ጀማሪ ሆኖ አሳያቸው።። እያንዳንዳቸው ገጀራ የመሰለውን ስል ቢላዋ ይዘው የህፃናቱን አንገት እስከ ተወሰነ ቦታ አርደው ለተረኛ መስጠት።።ተረኛውም ትንሽ ገባ ብሎ፤ ገዘገዘ ገዘገዘ አድርጎ አርዶ ለሌላው መስጠት።።በዚህ አይነት ቅብብል ሁሉም ቢላዋውን የመጨበጥና የማረድ ተራ ደረሳቸው።። የመጨረሻዎቹ ስድስቱ ህፃናት ባላዋቂ አራጅ አጉል የሆነ አስተራረድ ታርደው አለቁ።።በዚህ መልኩ መስዋዕት አቅርበው የደም ቃል ኪዳናቸውን ፈፀሙ መሆኑ ነው።።
ያ አስፈሪ ግዙፍ ፍጡር ፊቱ ላይ የተደረደሩለትን የ 18 ህፃናት ጭንቅላት በረጅም እጁ አንድ ባንድ እያነሳ ወደ ሰፊው አፉ እየወረወረ እንደ ሽንብራ ቆረጠማቸው ቢባል ይታመን ይሆን? እንዲህ ሲደረግ አይቶ በድንጋጤ የማይጮህ፣ የማይተናነቀው፣ ምናልባትም የማያስታውከው ሰው ይኖር ይሆን?
አጠገቡ ያለው ቀይና ሰፊ በርሜል የመሰለ ጎላ መሳይ መቀቀያ እንዲሁ በምቹው የአዳራሹ ወለል ላይ እንዳለ፤ያለ አንዳች እሳት በራሱ ጊዜ ጭስ

መገንፈል፣ ጀመረ፡፡ ‹‹ከበቡ!ከባችሁ
እያሳዩ መፍላት፣መንፈቅፈቅ፣
አስፈሪ ሳቁን ማስተጋባት ጀመረ፡፡
ታጠኑ!››አለና አስፈሪ ሳቁን ማስተጋባት ጀመረ፡፡ ተመልካች፣የአሁን ሁኔታቸውን በህፃናቱ መታረድ ማዘን የጀመረ ተመልካች፣የአሁን ሁኔታቸውን ሲያይ፣በእርዱ ማዘኑን ትቶና ረስቶ ሲመለከትና የአስተጣጠን ሁኔታቸውን ሲያይ፣በእርዱ ማዘኑን ትቶና ረስቶ መሳቅ ይጀምራል፡፡‹‹ታጠኑ!ከባችሁ ታጠኑ!››ሲባል፣ምድረ የሃያል አገር መሪ ተብዬ ከቦ በርሜሉን መታጠን!እንደ ጉድ ታጠኑት!ጭራሽ የአሜሪካው መሪ ጭሱ አልፎ እንዳይሄድ ይመስላል የቀይ ኮቱን ቁልፎች ፈትቶ፣ኮቱን ግራና ቀኝ በመዘርጋት በደንብ መታጠን ጀመረ፡፡አንዱ ባንዱ ላይ ተደራርበው ወደ በርሜሉ ውስጥ ለመግባት የፈለጉ እስኪመስል ድረስ ደስ እያላቸው ታጠኑት፡፡የሩሲያው መሪም ታጠነ! ሁሉም ከብበው ታጠኑ!አስገራሚ ነበር!

ለረጅም ደቂቃ ሲታጠኑ ከቆዩ በኋላ፣መቸና እንዴት መድረኩን ለቀው እንደሄዱ ያልታዩት ንግስቲቱና ጳጳሱ ሰፋ ሰፋ ያለ ሁለት ስለታማና ጎድጓዳ ጭልፋ ይዘው ወደ መድረኩ መጡና ሰጡት፡፡አስፈሪው ዘንዶ መሰል ሰው ጭልፋውን ተቀብሎ ወደ ቀዩ በርሜል እያስገባ በመጨለፍ ለእያንዳንዳቸው ድርሻቸውን ሰጣቸውና፣‹‹በልዑላችሁ ስም ባርኩና እዚሁ እንደቆማችሁ ብሉት!!››የሚል ትእዛዝ ሰጠ፡፡ሳቁንም ቀጠለ፡፡ ካካካካካ……ካካካካካ…ካካካካካ……ሃሃሃሃሃሃ…ሃሃሃሃሃሃ……ሆሆሆ ሆሆሆ….ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ረጅምና አስደንጋጭ ሳቅ……..፡፡

ልብ ይሁን ኩላሊት አልታወቀም፣ብቻ ግን ተመሳሳይ ስጋ እየተጨለፈ ወጥቶ እየተሰጣቸው በድፍረት እየጎረሱ እያኘኩ ዋጡት፡፡የ G 20 አገራት መሪዎች ይህን ሲያደርጉ፣ አንዳቸውም የመዘግነንና የመንገሽገሽ ገፅታ አልተስተዋለባቸውም፡፡

ጳጳሱና ንግስቲቱም እንደ ጥሩ ደጋሽና ጋባዥ ሽር ጉድ እያሉ አጎራረስና አዋዋጥ እያሳዩ፣ የምን ጎደለ የምን ይጨመር ፊት እያሳዩ፣ ተፍ ተፍ እያሉ፣ ለራሳቸው ሳይበሉ ሌሎቹን እያበሉ ቆዩ፡፡በመጨረሻ ግን እነሱ ብሰው አጥንት ሳይቀር መጋጥ ጀመሩ!

ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ወደ መረቅ ተገባ፡፡መሪዎቹ በደንብ ታጥነው በደንብ ከበሉ በኋላ፣አንድ አንድ ጭልፋ መረቅ እየተሰጣቸው በትኩሱ ጭልጥ አድርገው ጠጡ!ሁሉም ከተቃመሱ በኋላ ይመስላል፣አስፈሪው ሰው መሰል ዘንዶ፣ በሌላ አይነት ድምፅ፣ በተለየ ቅላጼና በሌላ አይነት ዜማ እንደገና ማሽካካት ጀመረ፡፡ረጅም ሳቁን ለረጅም ደቂቃ ያለማቋረት ቀጥሎበት ቆዩ፡፡ እኔም ጭምልቅልቅ ያለ ሆረር ፊልም የማይ እንጂ የ G 20 አገራት መሪዎችን እና የቫቲካኑን ጳጳስ እንዲሁም የእንግሊዝን ንግስት እያየሁ መሆኔን ዘንግቸ ቆየሁ፡፡መድረኩ ላይ ብዙ ሰቅጣጭና አስፈሪ፣ ከዚህም በላይ፣ሊገልፁት፣ ሊዕፋት፣የሚከብድ አስደንጋጭና የማይታመን ድርጊት

ተፈፀመ:: በመጨረሻ ማዕዱ ተነሳ::ያ አስፈሪ ፍጡርም፣‹‹የአዲሲቷ የምድር መንግስት ሹማምንት!ልዑላችሁን አመስግኑ!ሁሉ ተፈቅዶላችኋል!እንኳን ደስ ያላችሁ!››ብሎ ሌላ የተንዛዛ ነገር ውስጥ ሳይገባ ቀዩን የበርሜል ድስት ይዞ፣ በጭስ ተከልሎ፣ እብስ አለ::ተሰወረ፣ተሰለበ! ማእዳቸው ተነስቶ ከሄደ በኋላ ሁሉም መሪዎች ልዑላቸውን እያመሰገኑ ከመድረኩ ወርደው ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀመጡ::ጥቃቅን እባቦችም ከየግድግዳው መሃል እየወጡ መድረኩ ወለል ላይ እየተርመሰመሱ ደም የነካካና ፍርፋሪ የወደቀበትን ወለል አፅድተው ሄዱ::

ሁሉም ነገር ወደ ቀድሞ ቦታው ተመለሰ::ጳጳሱም ቦታቸውን ይዘው ከፊት ተቀመጡ::ንግስቲቱም መድረኩን ለብቻቸው ይዘው የዝግ ጉባኤያቸውን ቀጠሉ::

‹‹ክብር ለልዑሉ!!››

‹‹አሜን!››ሞቅ ያለ የጥ ጋብ ድምፅ::

‹‹አዎን!ልዑላችንን ማስደሰትን የመሰለ አስደሳች ነገር በዚች ምድር ላይ ሊኖር አይችልም!በኛ ምስጋናና መስዋዕት ብቻ ነው የሚደሰተው::ልዑላችን ይቺን ብቻ ነው ከኛና ከእናንተ የሚፈልገው::ሌላ ነገር አምጡ ብሎ ማስቸገር የሚባል ነገር በልዑላችን ዘንድ የለም!እረ ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹መልካም፤ጉባኤያችን ቀጥሏል::እናም ካቆምኩበት እቀጥላለሁ›› ብለው ጀመሩ::

‹‹የሰው ልጅ ስልጣኔ ከግብፅ ይነሳል ክቡራን::ማሃይምነትና ኋላ ቀርነት እንዲሁም ሐይማኖተኝነት ከኢትዮጵያ እንደተነሳው ሁሉ፤እውቀት፣ ትምህርትና ስልጣኔ ደግሞ ከግብፅ ይነሳል:: የበላይ አካሉ ስውን በኢትዮጵያ ምድር እንደፈጠረውና ያለ እውቀት እንዲኖር እንደፈረደበት ሁሉ፤ልዑላችንም በመንግስታት ደረጃ ከሰው ልጅ ጋር ተዋህዶ እውቀትና ስልጣኔን የገለፀበት ምድር ግብፅ ነው::ልዑላችን ከበላይ አካሉ ጋር ፉክክር ገጥሞ ሃይሉን ያሳየበት፣ለመጀመሪያ ጊዜ ጥበቡን የገለፀበት፣እውቀቱን ለፈርኦናቱ ያሳወቀበት፣የበላይ አካሉን እኩል የተገዳደረ የተፎካከረበት፣ ዘላለማዊ ተከታይ ያፈራበት፣ከበታች ጭፍሮቹ የተደቀሉ ድቅሎቹን እንግሶ የሰው ልጅን እንዲመሩ ያደረገበት ምድር ግብፅ ነው::ግብፅ ሲባል የአሁኑን ግብፅ አትሳሉ:: በፈርኦናቱ ዘመን ምድሩ ያ ነበር ለማለት ነው:: የውስጠኛውን ፒራሚዳችን ለማለት ነው::

‹‹ልዑላችን የዓለም መንግስታትን በሱ ስር ማድረግ የጀመረው ያኔ በግብፅ ምድር ከፈርኦናቱ ዘመን ጀምሮ ነው::የያኔዎቹ ፈርኦናትም የኛ ወገኖች ናቸው!

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው ልዑላችን ሰውን ማስተማርና ማሳወቅ፣ማሰልጠንና ማዘመን የቀጠለው።በዚያ ዘመን ወደ ተግባር መሰወጥ በጀመረውና ከልዑላችን በተበረከተው የእውቀት ቀመር መነሻነት ነው ዛሬ ላይ ዓለማችንና ህዝቦቿ ተምረው፣አውቀው፣ሰልጥነውና እዚህ ደረጃ ደርሰው የሚገኙት።

ያ ቀመር ደግሞ ከፈርኦናቱ ዘመን በኋላ የሰው ልጆች ይማሩና ይሰለጥኑበት ዘንድ ለኛ ተሰጥቶ በኛ በድቅሎች እጅ ተቀምጦ የቆየና ዛሬ ድረስ በኛ እጅ የሚገኝ ነው!ይህንን ነው ዘመን እየጠበቅን፣እየመጠንን፣ለምድር ህዝብ ስንሰጠው፣ ስናስተምረው፣ የቆየነው።ይህንን ትልቅና ጥልቅ የእውቀት መዝገብ ይዘን ነው ከፒራሚዳችን ወጥተን የመጣነውና ሰውን ማስተማር የጀመርነው!›› በማለት ቀደም ሲል በሜልቦርኑ አዳራሽ የታየውን እጅግ ግዙፍ የሆነ ጥራዝ መድረኩ ላይ እንሳፈው አምጥተው በድጋሚ አሳዩዋቸውና፣‹‹ውስጣችሁን አብርታችሁ ተከተሉኝ ክቡራን›› ሲሉ አዘዙ።መሪዎችም እንደተባሉት አደረጉ።

በዚህ ጊዜ ሌሎች ጥራዞች ተከታትለው እየመጡ አየር ላይ ተደረደሩና በአጠቃላይ 6 ተመሳሳይ ጥራዞች ሆኑ።

ንግስቲቱ ስድስቱን ግዙፍና እድሜ ጠገብ የመሰሉ መፃህፍት በእጅ ምልክት ብቻ ገፋ ገፋ እያደረጉ ወደ ግድግዳው ሄደው እንዲሰጠፉ ካደረጉ በኋላ፣‹‹ተከታተሉኝ››ሲሉ ቀጠሉ።

‹‹እነዚህ በልዑላችን ተዘጋጅተው ለሰው ልጆች የተበረከቱ 6 መፃህፍት ናቸው።እነዚህ 6 የእውቀት ማህደሮች ስፋትና ርዝመታቸው እኩል 6 ሜትር በ6 ሜትር የሆኑና፣እያንዳንዳቸውም እኩል 666ሺ ገፆች ያሏቸው ጥራዞች ናቸው።

‹‹ክፍል አንዱ በፈርኦናቱ ዘመን ተግባራዊ ሆኑ።ክፍል ሁለት በባቢሎናውያን ዘመን፣ክፍል ሶስቱ በግሪካውያን ዘመን፣ክፍል አራት በሮማውያን ዘመን፣ክፍል አምስት በኛ በአንግሎ ሳክሶን ዘመን፣ክፍል ስድስትም እንዲሁ በኛ ዘመን ተፈፃሚ ሆኑ።ከዚህ በኛ ዘመን ተፈፃሚ ከሆነው ከስድስተኛው ማህደር ውጪ ሌላ የእውቀት ማህደር የለም።ለሰው ልጅ የመጨረሻ ተብሎ የተሰጠው ይህ የመጨረሻው ክፍል ነው።

ከልዑላችን ጎን የሆኑ እኛን መሰል ድቅሎች በየዘመናቱ መፈፀም ያለባቸውን ተግባር በእነዚህ ማህደሮች መሰረት እየፈፀሙ የቤት ስራቸውን አጠናቅቀዋል።ሁሉም የቀድሞ ዘመን ሃያላን አገራት መሪዎችና ነገስታት በዚህ ቀመር መሰረት ነው ዓለማችንና ህዝቦቿን ሲመሩ የኖሩት።በእነዚህ ጥራዞች ውስጥ በየዘመናቱ ለሰዎች እየተመጠኑ መሰጠት ያለባቸው የእውቀትና የትምህርት መነሻ ቀመሮች አሉ።እነዚህ ጥራዞች ስለ ህግ፣ስለ ዲሞክራሲ፣ስለ ፍልስፍና፣ስለ ጦር ሰራዊት አደረጃጀት፣ስለ

አስተዳደርና ስለሌሎች ሁሉም ዘርፎች የሚያትቱ ናቸው።ከነአተገባበሩ የሚያስረዱ ናቸው።ሰዎች በየትኛው ዘመን የት ደረጃ መድረስ እንዳለባቸው፣በየትኛው ዘመን ምን አይነት አስተሳሰብ ውስጥ መሆን እንዳለባቸው፣በየትኛው ዘመን በማን መመሪነት እንዳለባቸው፣ ወዘተ….ሁሉም በእነዚህ ጥራዞች ውስጥ የሚገኙና በተለያዩ ዘመኖች የተፈፀሙ ወይም በየተራ የተተገበሩ ናቸው።

የኛ ተራ አምስተኛውና ስድስተኛው ጥራዝ ሆኖ እሱን ይዘን ከፒራሚዳችን እንደወጣነውና እንደተገበርነው ሁሉ፣ሌሎች ወገኖቻችንም በየዘመናቸው አንድ አንድ ጥራዝ ይዘው እየወጡ ወደተግባር ለውጠው፣ የተፈቀደላቸውን ዘመን ጨርሰው፣ለሌላ ተረኛ አስረክበው፣የሚመለሱበትን አሰራር በተከተለ አካሄድ ነው ሁሉንም ጥራዞች ወደ ተግባር መተርጎም የተቻለው።በእያንዳንዱ ማህደር ውስጥ የሰፈረው የየዘርፉ የእውቀት ቀመርም ሆነ የአስተዳደር ዘዴ እንደየዘመኑ የተለያዩ ሆኖ የሚገኝ ነው። በአንዳንዱ ዘመን ስለ ነዳጅ ዘይት ጥቅምና ስለመገኛ ቦታው፣ እንዲሁም ለምን ጥቅም ማዋል እንደሚቻል ከሚገልፀው ምዕራፍ ጀምሮ፣እስከ ጦርነት ጥበብ፣በሌላው ዘመን ስለ ህክምና ግብዓቶችና ለህክምና ስለሚውሉ እፅዋቶች፣በአንዳንዱ ዘመንና ምዕራፍ ስለ ፍልስፍና፣….ወዘተ…ሆነው የተቀመሩና፣እየተመጠኑ ሰዎች እንዲያውቋቸው እንዲማሯቸውና እንዲለማመዷቸው እየተደረጉ ሲተገበሩ የኖሩ ናቸው።

ባጭሩ ትምህርትንም፣የአስተዳደር ስርዓትንና ርእዮትንም ጭምር አጠቃለው የያዙ ማህደሮች ናቸው።ሆኖም ሁሉንም የእውቀት ማህደሮች ለሰዎች ባንድ ጊዜና በአንድ ዘመን ማስተማር አይቻልም።ዘመን መጠበቅ አለበት።ዘመንን መጠበቅ ብቻ አይደለም።የኛ ወገኖች የጀመሩትን ተግባር የሚከተሉና የሚያስቀጥሉ ‹ሰዎች› እየበረከቱ፣ደቀመዛሙርት እየሆኑ የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ማመቻቸትም ያስፈልግ ነበር።

የዚያ ዘመን ታላላቅ ‹‹ሰምሳሌ ግሪኮች ታዋቂ ሆነው በነበረበት ወቅት የዚያ ዘመን ታላላቅ የሚባሉ ሰዎች ይፈላሰፉ ነበር።ሮማውያንም እንደዚያው።በዚያ መንገድ የሚባሉ ሰዎች ይፈላሰፉ ነበር።ሮማውያንም እንደዚያው።በዚያ መንገድ ሰዎችን እንዲያነቁና እንዲያዘጋጁ የተላኩ የኛ ወገኖች ነበሩ።ሆኖም እነሱን እያዩ ማንም ተራ ሰው ሊቅ ነኝ ባይ ሆኖ አረፈ.ውና፣ ቁጭ ብሎ በመመሰጥና ተፈጥሮን በልቦናው በማስተዋል የመሰለውን ትምህርት ባደባባይ በቃሉ ያስተምር ጀመር።ትምህርት ሳይሆን ዲስኩር ልትሉት ትችላላችሁ።ሁሉም አቴና አደባባይ ላይ እየሄደ በቃሉ የመሰለውንና ባልበሰለ ማህበረሰብ ውስጥ የበሰለ የተባለ ንግግሩን ያደርግ ነበር።ያ የቃል ፍልስፍና እንጂ አንዳች ተጨባጭ ነገር አልነበረውም።ያን የመሰለ የቃል ፍልስፍና የግሪክን ህዝብ ከኩራዝ አውጥቶ ለኤሌክትሪክ ብርሃን አላበቃውም።ያ ሁሉ የሰው ልጆች ፍልስፍና፣ የትራንስፖርት ስርዓቱን

ከጋማ ከብት ወደ መካኒካል ነገር አልለወጠውም።ያ ሁሉ የአቴና ፈላስፋ የቃላትና የእሳቤ ውጤቱ የሆነውን ሰው በተሰበሰበበት አደባባይ በንግግር ይገልፃል።አድማጩ ህዝብ ትምህርቱን በጆሮው ይሰማል ይቢተናል።ያን አይነቱን ፎርሙላ የሌለው ፍልስፍና ወደ ዘመናዊ መንገድ ለውጦ፣ ለህዝብ አስተዳደርና ለየአገሩ ስልጣኔ አውሎ፣በሂደት እያሻሻለ ወደ ሽግግር ውስጥ ማግባትና መቀጠል የተቻለበት ሁኔታ አልነበረም።በድንጋ ላይ ድንጋይ እየደራረቡ ከዝናብና ከብርድ፣ከፀሀይና ከሃሩር ራሳቸውን የሚያስጠልሉበት መኖሪያ ገንብቶ፣ ባመኑበት ሃሳብ ህዝብን እየመሩና በጦርነት እያስገበሩ ገናናነታቸውን ከማሳወቃቸው በቀር ምንም ተጨባጭ ነገር አላሳዩም።

ለምን?መጀመሪያ ሰዎች እንዲሁ በቃል ፍልስፍና እምሯቸውን እያሰፉ፣ ማሰብ ለመቻል እየተዘጋጁ መቆየት ስለነበረባቸው ነው።ባንድ ጊዜ ዘልሎ ወደ ሳተላይት ቴክኖለጂ መግባት ስላልነበረበት ነው።

ስለዚህ ይህን ክፍል ብቻ ነው ያኔ የነበሩት የልዑላችን ወገኖች በዚያ ዘመን ለነበሩ ተራ ህዝቦች ማስተማር የተፈቀደላቸው።እናም በተሰጣቸው ጥራዝ መነሻነትና መመሪያነት በዘመናቸው የነበረውን ህዝብ ሰፋ አድርገው በጥልቀት ማሰብ መጀመር የሚችሉበትን ሁኔታ የሚፈጥርላቸውን የትምህርት ክፍል እያስተማሩ ህዝቡን ማዘጋጀትና ማንቃት ቻሉ።

በዚህ አይነት አካባቢውን ማንቃት ከተቻለ በኋላ ደግሞ፣በተከታዩ ዘመን ወደ ተከታዩ ክፍል ይገባል ማለት ነው።

በዚህ አይነት መንገድና መተካካት ነው ሂደቱ ቀጥሎ የቆየው።

ሁሉም በየዘመናቸቸው በዚህ ማህደር ውስጥ የተቀመጡትን አካሄዶች እየተገበሩ፣ሰው መስለውና ከሰው ተመሳስለው ስልጣኑን እየያዙ፣ በሚመደቡላቸው መንፈሳዊ ጭፍሮች ምክርና ድጋፍ እየታገዙ፣ሁሉንም አገራት ግዛታቸው እያደረጉ፣ዘመናዊ የአስተዳደር አደረጃጀቶችን እያሰረፁ፣ ለወደፊት የሚጠቅመውን ትምህርት እያስተማሩ፣ስልጣኔን እያለማመዱ፣ ተተኪ እያፈሩና እያስረከቡ ነበር የቀጠሉት።

በመሆኑም ይህ የመጀመሪያ ማህደር በፈርኦናቱ ዘመን ተፈፅሞ እነሱም በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ የቤት ስራቸውን አጠናቀው፣ ዘመናቸውን ጨርሰው፣ ለባለ ክፍል ሁለቶች ለባቢሎናውያን ለቀቁ።እነሱም በተመሳሳይ ትግበራ ማህደራቸውን በተቀመጠላቸው ጊዜ ተግብረውና አጠናቅቀው ለተረኞቹ አስረከቡ።ተረኞቹ ግሪካውያንም በተመሳሳይ ፈፅመው ለተከታዩ ለክፍል አራት ባለቤቶች ለሮማውያን ለቀቁ።ሮማውያንም በዘመናቸው ከክርስትና በፊትና በኋላ ከቋንቋ ጀምሮ እስከ ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት ዝርጋታ ድረስ ያለውን ስራ ጨርሰው፣ሁሉን አለማምደው በየዘርፉ ዝግጁ የሆነ ህዝብና ቅርፅ የያዘ አህጉር ገንብተው ለኛ ለተረኞቹ አስረከቡ።

5ኛውና 6ኛው ጥራዝ ለኛ ዘሮች፤ማለትም ከዝማስያ ወገን ለሆንነው ተሰጠ።እኛም ሁለቱን ጥራዞች ይዘን ወጥተን ከአንግሎ ሳክሶን ዘመን ጀምሮ ቦታ ቦታችን ይዘን ይህን ማህደር በተግባር ወደመተርጎም ስራ ገባን።

‹‹ይህ ጥራዝ ከቀድሞው የግብፅ ቋንቋና ፊደል ከዲሞቲክ ወደ ዘመናዊውና በዓለማችን ህዝብ ዘንድ ወደፊት በስፋት ጥቅም ላይ በሚውለው፤ በዘመናዊቷ ዓለም ተፅእኖ መፍጠር በሚችለው ቋንቋ ተተርጉሞና ተቀምሮ የተዘጋጀ ነው።

እንደምታዩት በመጀመሪያዎቹ ገፆች ቅድመ የቤት ስራችን ምን መሆን እንዳለበት ተገልፆዋል።

‹ብእነዚህ በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ውስጥ በሰፈረው ጥቆማ መሰረት፤ መጀመሪያ የራሳችን አገር መስርተን፣በቋንቋና በዘር ራሳችን ለይተን፣ በዘመናዊ መንገድ አገራችን መገንባትና ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት ቀይሰን ሃያል አገር መሆን ነበረብን።እንዴት ያን ማድረግ እንደምንችል የሚያስረዱ አካሄዶችና ዘዴዎችም ተዘርዝረዋል።

እናም በተዘረዘሩት አካሄዶች መሰረት እየተጓዝን፣ በተቀመጠልን የጊዜ ገደብ እየተገበርን፣አገራችን መስርተን፣ዘመናዊ የህግ አስተዳደር ዘርግተን፣ ሃያል መሆን ነበረብን።

ሃያል በሆንን ማግስትም በተከታይ ገፆች ትእዛዝና ጥቆማ መሰረት፤ በጂኦግራፊ ጥበብ ምድራችንን በማዋቀርና በዘመናዊ ካርታ በማካለል፤ ዘመናዊ ቅርፅ ማስዝ ነበረብን።ይህን ለማድረግ የሚረዱ ግብዓቶችና ዘዴውም እንዴት እንደሆነ በግልፅ ሰፍሮልናል።አጋዥ ጭፍሮችም ተመድበውልናል።

‹‹እናም ኢንግላንድን መሰረትን።ኢንግ ላንድን በዕጉ መሰረት ከመሰረትንና ከገነባን በኋላ፤ታላቅ አገር መሆን ጀመርን።ቀጥሎ ምድርን በጂኦግራፊ ጥበብ እያጠናን ካካለልንና በአህጉር ከፋፍለን ለየአገራቱ ስያሜያቸውን ካወጣንላቸው በኋላ፣ለወደፊቱ ስልጣኔ እጅግ አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ ግብዓቶችን የምናገኝባቸውን አገራት ከየአህጉሩ መርጠን በቁጥጥራችን ስር ማድረግና በኛ የበላይነት ማስተዳደር መግዛት ቻልን።ክጥቂት ምእተ ዓመታት በኋላም ይቺን አገርም፣የልዑላችን ቤተ መቅደስም፣ የጥበበኞች መስፈሪያም፣ ሆና ወደፊት ታላቅነትን መጎናፀፍ የሚኖርባትን ምድር ካመቻቸናት በኋላ ነፃነቷን ሰጥተን በመልቀቅ፤ሌሎችን ግን በስራችን እንዳደረግን ቀጠልን።

በኛ ቁጥጥር ስር ካዋልናቸው በርካታ አገራት የምናጋብሳቸውን ለስልጣኔ ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናትን በዚች ድንቅ አገር ማፍሰስ ጀመርን።የሰው ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናትን በዚች ድንቅ አገር ማፍሰስ ጀመርን።የሰው

ሃይልም እንዲሁ።እንደ ቀድሞው የፈርኦናት ዘመን ኢንግ ሳንድንና አሜሪካን በባሪያ ጉልበት አስውበን መገንባት ነበረብን። ያንንም አደረግን። በተዓፈና በተቀመረልን መሰረት ተጉዘን ተግባራዊ በማድረግ ይቺን ፕላኔት በአህጉርና በአገር ከፋፍለን፣ለየአገራቱም ስያሜያቸውን እየሰጠን ቅርፅ አስያዝናት።

በዚህ ጥራዝ ውስጥ ባጭሩ ምድራችንን የምንገነባበትና የምድርን ሰው በአዲስና በዘመናዊ መልክ አስተምረን ዘመናዊቷን አዲስ የምድር መንግስት ለመመስረት የሚያስችለን መነሻ ሃሳብና አካሄድ፣እንዲሁም የትምህርት ቲዮሪ በሰፊው ተብራርቶ ይገኝበታል።

‹‹ይህ 5ኛው ማህደር ከአንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ፣ከዚያም እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ የሚገነቡትንና የሚሾሙ የኛ ወገን የሆኑ ድቅሎችን እየዘረዘረ፣ ሁሉን አይነት የትምህርት አይነቶች እያብራራ፣እንደምታዩት ከሞሉኪል ጀምሮ እስከ ኬሚካላዊ ውህዶች፣ ከምድር ውስጥ አለቶች ጀምሮ እስከ ማዕድናት፣ከውቅያኖስ ውስጥ ንጥረ ነገሮች እስከ ቅጠላ ቅጠሎች ይዘት እያተተ፣ስለ ሃይል፣ስለ ርቀት፣ስለ ስበት፣ወዘተ…እየተንተነ የተሟላ ቲዮሪ ሆኖ የተሰጠን ሲሆን፣ይህን ለዓለም ለማሳወቅና ለማስተማር ጅምር ስራዎች በምን መልክ መፈፀም እንዳለባቸው ካብራራ በኋላ፣ቀጣዩን ተግባራዊ ስራ በመጨረሻው ክፍል የሚገኝ መሆኑን ጠቅሶ ይደመድማል።

‹‹በዚህ መፅሀፍ ውስጥ በአጭርና በጥቅል ተቀምረው የምታዩዋቸው የእውቀት መነሻዎች ደረጃ በደረጃ ለሰው ልጅ በትምህርት መልክ ሲቀርቡና፣ሰው በእነዚህ ቲዮሪዎች መነሻና ቀመር አእምሮው እየነቃና አዋቂ እየሆነ የመሄዱን ያህል፣በተግባር ቢደገፍ የተሻለ እውቀት እንደሚያገኝና እንደሚኖረው ማሰብ ሲጀምር፣ባጭሩ ለሁሉም ነገር ዝግጁ የሆነና የግኝት ውጤቶች ይፋ ቢደረጉና በህይወቱም ቢለማመዳቸው እውቀትና የትምህርት ውጤቶች በመሆናቸው ተቀብሎ በደስታ ከመጠቀም አልፎ በራሱ ጥረትም እያሻሻለው ለመሄድ ተዘጋጀ ማለት ይሆናል።

‹‹እንዲሁ ቢሰጠው ግን እንደ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የሰይጣን ስራ ነው ብሎ ከመሸሹም በላይ፣ሌሎች የተወሳሰቡ ነገሮች ውስጥ ስለሚገባና ሌሎችንም ስለሚያወግዝ የግድ ቲዮሪውን ተምሮ እውቆና ለነገሮች እንግዳ ከመሆን ድኖ መኖርና መጠበቅ ስላለበት ነው፣ ይህ ያስፈለገው።። ዘመናዊ ትምህርት ከሐይማኖትና ከሐይማኖተኞች ጋር ከባድ ግጭት ውስጥ ይገባ ስለነበርም፣በጥንቃቄና ተቃርኖ በሌለበት ሁኔታ ቀስ በቀስ አብሮ ተገልያልናል።የተለየና ራሱን የቻለ ሆኖ፣ሰዎችም ጎን ለጎን ከማስኬድ የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለ ተረድተው ይማሩልን ዘንድ እንደምንችል ዘዴው ጭምር

አለሳልሰን እያሳመንን በተገቢው መንገድና በጥንቃቄ ተግባራዊ አደረግነው። ሁሉንም በተጻፈው መሰረት ገፅ በገፅ፣ቃል በቃል፣ ተግባራዊ አድርገን የምድርን ህዝብ ዘመናዊ ትምህርት ማስተማር ጀመርን።
እነዚህ የቲዮሪ ትምህርትና እውቀቶች ወደ ተግባር ተለውጠው ዓለምንና ህዝቦቿን ይለውጡ ዘንድ ግን ይህ የእውቀት ማህደር በቂ አልነበረምና ወደ ቀጣዩ ክፍል 6 መግባት ነበረበት።
በእንዲህ አይነት የፒራሚድ ሚስጥራዊ ሰነድ ቅብብል ነው ዓለማችን አሁን ያላትን ቅርፅና ይዘት መያዝ የቻለችው።
ዴሞ ፒፐል፣ክራሲ ራይት፣ ዴሞ ክራሲ፣ የህዝቦች መብት፣ ‹‹ኢት ካምስ ፍሮም ግሪክ ዎርድስ›› እየተብለ ሲባል የኖረው፣‹‹ኢት ካምስ ፍሮም ላቲን ወርድስ›› እየተባለ የተቀጠለው፣በተለመደው የማምታቻ ዘዴያችን ተጠቅመን እንዲያ እንዲባል ስላደረግነው እንጂ እንዲያ ሆኖ አይደለም። ‹‹ኢት ካምስ ፍሮም ፒራሚድ››ተብሎ ያለዘመኑ እንዳይታወቅ ስንል የነዛነው ፕሮፖጋንዳ ነው››አሉና፣አንዱን ጥራዝ ብቻ አስቀርተው ሌሎችን አምስት ጥራዞች በእጅ ምልክት ከእይታ ውጪ አደረጓቸው።
‹‹እነዚህ የሸኘኋቸው አምስት ማህደሮች ለዚህ ለመጨረሻውና ለ6ኛው ማህደር መንደርደሪያ የሆኑ ናቸው።ሁሉም በየዘመኑ ወደ ተግባር የተለወጡት ለዚህ ለ6ኛው የእውቀትና የጥበብ ማህደር ትግበራ መሰረት ይሆኑ ዘንድ ብቻ ነው።በተረፈ ዋናው ማህደር ይህ 6ኛው ነው።5ኛውና 6ኛውም ነው በኛ በመጨረሻዎቹ ዘመኖች ወደ ተግባር ተለውጦ የዓለምን ህዝብ ወደመጨረሻው ስልጣኔ ደረጃ ያሸጋገረውና እያሸጋገረው ያለው።
‹‹ብደንብ ተከታተሉኝ ክቡራን፣ኋላ ቀሩ የሰው ፍጡር ከልዑላችን ወገን ከሆኑ መንፈሳዊ አካላት ጋር ካልተቆራኘና ካልተወራረሰ በቀር በራሱ ምንም ማድረግና ምንም መፍጠር የማይችል ፍጡር ነው!ማንም የሰው ፍጡር በራሱ ሃሳብ ጀምሮ፣ ተመራምሮና ቀምሮ፣ በራሱ እውቀት ተራምዶ፣ ተጉዞ፣ ጥግ ድረስ ቢሄድ፣ ለጥቃቅን እንጂ ከፍ ላለ የግኝት ውጤት ሊበቃ አይችልም።እንዴትም አድርጎ ቢያስብና ቢመራመር፣ ቢሻሻልና ቢያሻሽል፣በልቶ ለማደር የሚያስችለውን ተራ ነገር ሊፈለስፍና ሊፈጥር፣ የፈጠረውንም ሊያሻሽል ይችላል እንጂ ወደ ተራቀቀ ደረጃ የሚያደርስ ቅንጣት ጥበብ ከውስጡ አይወጣም።ቢወጣም በሃሳብ ደረጃ ተወስኖ የሚቀር እንጂ ለውጤት በቅቶና ለዓለም ህዝብ ተዳርሶ ዓለምን ካለችበት ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ከፍ ማድረግ አይችልም።
ሰው ወይም የሰው ልጅ ወደ ምድር ሲመጣ የሚመገበውን ምግብና የሚጠጣውን ውሃ ይዞ አይመጣም።የሚረግጠውን ምድር፣ የሚሞቀውን ፀሐይ፣ የሚተነፍሰውን አየር፣ ወዘተ.... በጉያው ሸጉጦ የሚወለድ አይደለም።ይህ ማለት ሰው ራሱን በራሱ ፈጥሮ፣ ራሱን በራሱ አሳድጎ፣

እራሱ በፈለገው ዕለት ጎልብቶ፣ እራሱ በፈጠረው ዓለም እየኖረ፣እራሱን እራሱ በፈለገው ዕለት ጎልብቶ፣ እራሱ በፈጠረው ዓለም እየኖረ፣እራሱን በራሱ ለዘወትር እያዘዘ ኖሮ የሚያልፍ አይደለም ማለት ነው።
በራሱ ለዘወትር እያዘዘ ኖሮ የሚያልፍ አይደለም ማለት ነው።
ስለዚህ ወደዚች ዓለም ሲመጣ ተዘጋጅቶ የጠበቀውን ምድርና በውስጧ ያለውን ብቻ ነው ሊያውቅ የሚችለው።እነዚያን ነገሮች እንዳሻው እየተጠቀመ እንዳሻው እያሻሻለ ህይወቱን እንዲቀጥል ነው የተደረገው። በመሆኑም የሰው ልጅ እውቀት በዚያው በጠበቀው ነገር ላይ የተመሰረተና በዚያው የተወሰነ ሆኖ የሚቀር ነው።ሰው ስለራሱም ሆነ ከሱ በላይ ስላሉ ፍጡራን መርምሮ አይድረስ እንጂ፣ ሲመጣ በጠበቀው ነገር ላይ ተመራምሮ ሙሉ ያልሆነ እውቀት ሊይዝ፣አኗኗሩንም በራሱ ዘዴ እየቀየረና እያሻሻለ ሊኖር ይችላል።ያን አስተሳሰብ መነሻ በማድረግም ሄዶ ሄዶ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ያስባል።ከሳይንስ የተሰወረ የለም ብሎ በማመንም ሁሉንም ነገር መርምሮ ሊደርስበት ሲታትር ይታያል። ነገር ግን የሰው ሳይንስ የምድርንና የፍጥረታትን ይዘት ከመለየትና ከመተንተን ውጪ ሌላ ተጨባጭ ነገር ሊያስገኝ አይችልም።በዚህ መሰረት የሰው እውቀት የፈለገውን ያህል ቢጎዝ፣ስለሰው፣ ስለመጣበት ምድርና በውስጧ ስላሉት ነገሮች ብቻ ቁንፅል እውቀት ይኖረዋል እንጂ ሌላ አዲስ ነገር መፍጠር አይችልም።ከዚህ አልፎ ሳስብ ማለት አይችልም።ማሰብ ቢችልም ሰው በራሱ ሁሉንም የማወቅና ሁሉም ላይ የመድረስ ዕድል የለውም።ሁሉንም ሚስጥር ለማወቅ የሚያስችለው እውቀትም ሆነ የአስተሳሰብ ብቃት እንዲሁም በቂ ዕድሜ የለውም።ስለዚህ ሲወለድ ያገኘውን፣ የጠበቀውን፣ የተሰጠውን፣ የመመርመርና የማወቅ እድሉን ተጠቅሞ እስከ ገደቡ ከተጠቀመ በኋላ የደረሰበት ደረጃ ደርሶ ያበቃል። ሲያበቃም የትም ሳይደርስ ነው የሚያበቃው።
ምክንያቱም የበላይ አካሉ የሰው ልጅ እንዲያውቅና እንዲሰለጥን ስለማይፈልግ ነው።የእውቀት ገደብ ስለጣለበት ነው።
የሰው ልጅ የተፈቀደለት የበላይ አካሉን/አምላኩን/ብቻ እንዲያውቅ ነው። እሱን ለማወቅና እሱን ለማምለክ ከሆነ ብቻ የተጣለበት የእውቀት ገደብ ሊነሳለት ይችላል።አያችሁ?ሰው አምላኩን ብቻ እንዲያውቅና እሱንም አውቆ በሱ ስር ሆኖ እንዲኖር ነው የተፈረደበት።ይህንን ነው ልዑላችን ፍትሃዊ አይደለም የሚለው!
ህግና መተላለፍ አለ።ህግ ከሌለ መተላለፍ የለምና የበላይ አካሉ የፈጠረውን ሰው እኔን ብቻ እወቅ የሚል ህግ ሰጥቶና ገድቦ ትቶታል።ያ ህግ ደግሞ የሰውን ነፃነት የሚጋፋ ህግ ነው።ሰው ራሱን እንዳያውቅ የሚገድብ ህግ ነው።ሰው ከዚያ ህግ ውጪ ሌላ አማራጭ ነገር አልቀረበለትም።ልዑላችን ግን ሁለተኛውን አማራጭ አስቀመጠ!ህጉን እንዲተላለፉ መከሮ፣ ሰው ራሱን የማወቅ መብት እንዳለው ነግሮ፣

በተግባርም አሳይቶ፣ ራሱን እንደ ሁለተኛ ምርጫ አቀረበ፡፡ወይም ምርጫ ሆኖ ቀረበላቸው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ሁለቱ ነገሮች ቀርበውለት በራሱ ምርጫ እንዲጓዝ ተትቷል፡፡የሰው ልጅ የፈለገው ደግሞ ሁለተኛውን ምርጫ ሆነ!ራሱን ማወቅን መረጠ፡፡ሁለተኛው አማራጭ የተሻለ እንደሆነ በተግባር ተረዳ፡፡

በዚህ መሰረት የበላይ አካሉ ተቃራኒ ሆኖ፣ ማወቅ አለባቸው ብሎ ተሟግቶ፣የእውቀትና የጥበብ ባለቤት አድርጎ፣እዚህ ሊያደርስን የቻለው ሁለተኛው አማራጭ ነው ማለት ነው፡፡እርሱም ልዑላችን ነው፡፡ከፒራሚድ ዘመን ጀምሮ የተጀመረውና እስካሁን ድረስ የቀጠለው፣ዓለማችንንም እዚህ ደረጃ ያደረሰው የእውቀት መገለጥ ምንጩ ልዑላችንና ጭፍሮቹ ብቻ ናቸው!የዚያ ዘመን ሰው ምርጫ ውጤትም በሂደትና በልዑላችን የዘመን ቀመር መሰረት በየጊዜው እየተሻሻለ ሄዶ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል››

‹‹የትናንቶቹ ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎች በሙሉ ልዑላችን በፈቀደው ዘመን ቀስ ብለው እንዲነሱ አድርጎ ጥበብን የገለጠላቸው ናቸው፡፡እነዚህ የዘመናዊቷ ዓለማችን ጥበበኞችም የኛ የዘር ሃረግ በተወሰነ ፐርሰንት ያለባቸው ናቸው፡፡ግኝታቸውን ለሰው እያስተዋወቁ፣ ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድበትን ሁኔታ እያመቻቹ፣ በዘመናቸው መስራት የነበረባቸውን ስራ ሰርተው ያለፉ የግኝት ባለቤቶች በሙሉ፣ ያንን ሁሉ ተግባር ያከናወኑት በሰውኛ አስተሳሰብና እውቀታቸው አይደለም፡፡በዋናነት የኛ የዘር ሃረግ ስለነበራቸውና ከልዑላችን ጭፍሮች ጋር መገናኘት ስለቻሉ ብቻ ነው፡፡ እነዚያ የረቂቅ ግኝት ባለቤቶች በሙሉ በኛ አስማሪነት በየአገሩ ተሰማርተው የኛን ትእዛዝ የፈፀሙ ቤተሰቦቻችን ናቸው፡፡

‹‹ልብ በሉ!አሁን እናንተ ሰው ናችሁ፡፡በልዑላችን መልካም ፈቃድ መሰልጠንና መዘመን የቻላችሁ፣በዘመናዊ ሰው ሰራሽ የርቀት መገናኛ ዘዴዎች የተከበባችሁ፣በዘመናዊ አልባሳት ያሸበረቃችሁ፣ በዘመናዊ አገር እየኖራችሁ በዘመናዊ የህግ አስተዳደር ህዝባችሁን እየመራችሁ የምትገኙ ሰዎች ናችሁ!የተማራችሁም ናችሁ!ይህን ሁሉ ዕውነታ ለአፍታ እርሱትና፣ሰው መሆናችሁን ብቻ ለአፍታ አስቡ…..››

ሁሉም ያስቡት ዘንድ ዕድል ለመስጠት ያህል ለአፍታ ንግግራቸውን ገቱና ከረጅም ዝምታ በኋላ ቀጠሉ፡፡

‹‹አሁን እናንተ ውጭና ውስጣችሁን ስላጠፋችሁ ሰው ናችሁ፡፡እንደ ሰው እያሰባችሁ ነው፡፡ለአፍታ ያህል በዚያው ቀጥሉና አስቡ፡፡

‹‹ወደ ምድር ስትመጡ ውስጣችሁ ያለውን ጥቂት የታመቀ ዕውቀት ከአእምሯችሁ አውጥታችሁ ለመጠቀም የሚያስችላችሁ የትምህርት ተቋማትና መምህራን፣እንዲሁም ወደ ትምህርት ቤት የሚልኳችሁ

የተማሩ ቤተሰቦች ባይኖሯችሁና የምትጓጓዙበት ዘመናዊ ትራንስፖርትና አጠቃላይ ለመኖር የሚያስችሉ ቁሳቁሶች ተሟልተው ባይጠብቋችሁ ምን ትሆኑ ነበር?መቸም ራሳችን በራሳችን እናስተምር ነበራ!የሚል ምላሽ አትሰጡኝም:: አዎን!ያንን ነው አዘጋጅተን የጠበቅናችሁ!

‹‹አዎን!በተዘጋጀና ባለቀለት ሁኔታ ላይ ወደ ምድር ስለመጣችሁ የእናንተ ስራ ቀድሞ በተዘጋጀላችሁና በፅኑ መሰረት ተገንብቶ በቆየላችሁ ነገር ላይ በማረፍ፣ያንን ቀመርና ፎርሙላ ወይም የትምህርት ስርዓት አሊያም ጅምርና ኋላ ቀር የነበረን ግኝት መነሻ በማድረግ፣ የማሻሻልና የማዘመን ነገር ውስጥ ገብታችሁ መቀጠልና ማስቀጠል የምትችሉ ሰዎች ሆናችሁ ስለመጣችሁ ልታስቡትና ላይገባችሁ ብሎም በቀደምት አባቶቻችሁና ወላጆቻችሁ ጥረት የተገኘ አድርጋችሁ ልትወስዱት ትችላላችሁ::ግን አይደለም::እንዲያ እንድታስቡ ስላደረግን እንጂ እንዲያ ሆኖ አይደለም!የሰው ልጅ በሙሉ እንደዚያ ነው የሚያስበው::

በእርግጥ ያንን መሰረት ጥለውላችሁ የሄዱት አባቶቻችሁ ናቸው? እንዴት?ከሆኑስ መነሻቸው ምን ነበር?የመጀመሪያውን ትምህርት ማን አስተማረ?ከመሬት ተነስተው እንዴት የዕውቀትና የጥበብ ግኝት ባለቤት ወደ መሆን ደረጃ ሊደርሱ ቻሉ?እየተባለ ቢጠየቅ የተብራራ መልስ የሚሰጥ ከእናንተ ውስጥ የለም::

ለምሳሌ ቶማስ ኤዲሰን የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ ምሩቅ ነው::እሱ የተመረቀበትን ትምህርት ቤት ወይም የምርምር ተቋም ለመጀመሪያ ጊዜ ማን መሰረተው?ትምህርት የሚለውን ሃሳብስ ለመጀመሪያ ጊዜ ማን አፈለቀው?ትምህርት ቤት መግንባት አለበት የሚለውን ሃሳብስ ማን አመጣው?ኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ የሚለውን የትምህርት ስርዓትስ ለመጀመሪያ ጊዜ ማን ቀረፀው?የሆነ ቀደምት ሰው ቀረፀው ብትሉ እንኳ፣ያ ሰው ከምን ተነስቶና ምንን መሰረት አድርጎ ቀረፀው?

‹‹ዓለማችን አሁን ያለችበትን ደረጃ ተመልከቱ::እጅግ በተራቀቀ እውቀትና ጥበብ በተገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አማካኝነት የስልጣኔ ጣራ ላይ ደርሳ እናያለን::እንዲህ አይነቱ ነገር በሰው ልጅ ልምምድና በሂደት እየተሻሻለ፣ በአንዱ መነሻ አንዱ እየቀጠለ፣ወዘተ.....እየተባለ የሚደረስበትና የተደረሰበት አይደለም::ሰው በራሱ አስተሳሰብና እውቀት እንዲሁም በራሱ ተነሳሽነት ወደዚህ አይነት ወደ ተራቀቀ ደረጃ ጨርሶ ሊደርስ አይችልም::

‹‹ቀላል፣ መካከለኛ፣ ከባድ፣ረቂቅ፣ ተብለው የሚከፈሉ እውቀቶች አሉ:: ሰው በሶስቱ የእውቀት ደረጃዎች ደርሶ ተሻሽሎ ሊገኝ ይችላል::ወደ አራተኛው ረቂቅ ወደ ተባለው ደረጃ ግን በራሱ ጥረት ብቻ ሊደርስ አይችልም::

እነዚህ በሶስት የተከፈሉ እውቀቶች ማንኛውም ሰው ወደ ምድር ሲመጣ በሚጠብቀው ነገር ላይ ተመስርቶ ሊደርስባቸው የሚችሉ ናቸው።የኑሮ ግብአትን መሰረት ያደረገ እውቀት ነው።ውሃ አለ፣አፈር አለ፣ዛፍ አለ፣ መሬት አለ፣ፍራፍሬ አለ፣ወዘተ.....ያ ሰው በራሱ እውቀት በቀላሉ ሊጠቀምበት፣ያሻውን ሊያደርግበት፣ ሊኖርበት፣ሊገለገለበት የሚችል የተፈጥሮ ግብአት ነው።ጨው በውሃ ይሟሟል ሲባል፤ውሃውም ጨውም ስለነበረ ለማንም ግልፅ የመሆኑን ያህል፣ማንም ሰው ሞክሮ ማረጋገጥ የመቻሉን ያህል፣ይህ አይነቱ እውቀትም ያለ ትምህርት እንዲሁ በማንም ተራ ግለሰብና ምንም በማያውቁ በህፃናት ልጆች ሳይቀር በቀላሉ የመታወቁን ያህል፣ረቂቅ የሚባሉት ግን በእናንተና በኛ ደረጃ ሊደረስባቸው የማይችሉ ናቸው።ማህበረሰቡ በዙሪያው ያለውን ነገር በፈለገው መንገድ ቀይሶና አሻሽሎ ኑሮውን የሚያቀልበት፣የተሻለ ኑሮ መኖር የሚችልበትን መንገድ የማመቻቸት ስራን የሚያጠቃልል ነው።

ሰዎች ድንጋይና ድንጋይ በማፋጨት በሰበቃ አማካኝነት እሳት ማንደድ ቻሉ ሲባል፤ድንጋዩ አለ፤እሳትም መሆን ይችላል።ነገር ግን ያን መነሻ አድርጎ፣ ያንን ድንጋይ ፈጭቶና አቡክቶ፣ ወደ ሸቦነት ቀይሮ፣ ወደ ፖዘቲቭና ነጌቲቭ ፍልስፍና የሚገባበት ሁኔታ የለም።ድንጋዩ ተፈጭቶ በምን ይዋሃዳል?ከዚያስ እንዴት ተመጥኖ እንዴት ተሳስሮ ይቀጠላል?ወዘተ....የሚሉ ጥያቄዎችን ሰው በራሱ ተፈላስፎና ቀምሮ፣ አዋህዶና መጥኖ እያሻሻለ መቀጠል አይችልም።መጀመሪያ በቲዮሪ መልክ የተቀመጠ ፎረሙላ/ቀመር/ያስፈልጋል።ያን ለመቀመር ደግሞ መጀመሪያ በተግባር ተሞክሮ ለውጤት መብቃት የቻለ ጅምር መነሻ ሊኖር ግድ ነው። የሰው ልጅ ያ የለውም ወይም አልነበረውም።ያን ፎርሙላ ያውቁ የነበሩት ከሰው በላይ የሆኑ መንፈሳዊ ፍጡራን ብቻ ናቸው።

ከባድ እውቀት የሚባለው ከራሱና ከአካባቢው አልፎ ለሌላው ማህበረሰብና ለትውልድ የሚተርፍ ዓለም አቀፍ እውቀት ሲሆን፤የራሱን እውቀት ተጠቅሞ ያገኘውን የግኝት ውጤት ለሌሎች ሰዎች ማካፈል የሚያስችል ነው።የሰው ልጅ በእነዚህ ሶስት የእውቀት አይነቶች የተወሰነና ከዚህ ሊያልፍ የማይችል ነው።መርከብ ሰርቶ ዓለምን መዞር፣ምድር ላይ ያሉ እንስሳትን ማጥናትና ባህሪያቸውን መለየት፣በልምድና በልምምድ ነገሮችን ማወቅና ማሳወቅ፤ሰው ሲያመው በምን መንገድ እንደሚፈወስ፣ፈረስ ሲያመው በምን ቅጠል እንደሚድን፣ከሳር ይልቅ ምን ቢመገብ እንደሚወፍር መረዳትና ማስረዳት፣ በዙሪያው ያገኘውንና ያለውን ነገር ቀጥቅጦ ጌጣጌጥ መስራት ወዘተ....በልምድና በሙከራ፤እንዲሁም በረጅም ጊዜ ሂደት የሚረጋገጥና ለሁሉም የሚዳረስ ነውና ከባድ እውቀት ሊባል ይችላል።አንድ ሰው በእግርና በፈረስ ከመሄድ ይልቅ በጋሪ ቢሆን የተሻለ

እስንም እንዴት መስራት እንዳለበት አውቆ ነገሩም እንደሚሆን ቢያስብና፤ እሱንም እንዴት መስራት እንዳለበት አውቆ ነገሩም እንደሚሆን ቢያስብና፤ ሌሎቹም እሱን ተከትለው እንዲሰሩ ቢያደርግ፤ ገብቶት ሊሰራ ቢችል፤ ሌሎቹም እሱን ተከትለው እንዲሰሩ ቢያደርግ፤ ገብቶት ሊሰራ ቢችል፤ ሌሎቹም እሱን ተከትለው እንዲሰሩ ቢያደርግ፤

ፍሥሐ ያዜ

96

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

የሚገኘው ጥበብና የጥበብ ውጤት፣ሳይንስና የሳይንስ ውጤት ሁሉ በማንም እጅ ቢቆይ፣ ማንም ሰው ሲጠቀምበት ቢኖር፣ ዞሮ ዞሮ ግን የልዑላችን ነውና ለልዑላችን የመጨረሻ ዓላማ ግልጋሎት ላይ የሚውል ነው።

‹‹ሁሉም ነገር ወደ ባለቤቱ ይመለሳል። ባለቤቱ እስኪፈልገውና እስኪወስደው ድረስ ግን እንዳልኩት በማንም ሰው እጅ ሊቆይና ማንም ሲጠቀምበት ሲገለገለበተ ሊኖር ይችላል።

‹እርግጥ ነው የበላይ አካሉ ተከታዮች እርር እያልንም ቢሆን፣የልዑላችን የጥበብ ውጤት የሆነውን ቀሳቁስ ልዑላችንን ሳይሆን የበላይ አካላቸውን ለማምለክ ይጠቀሙበታል።ቢሆንም ይህ ባለቤትነት አይደለም።ባለቤቱ እስኪፈልገው ድረስ በማንኛውም ሰው ዘንድ መቆየት ስላለበት ብቻ ነው።ያ ደግሞ ለኛ አስፈላጊ ነው።የበላይ አካሉ ተከታዮች በነፃነት ለፈለጉት ዓላማ እየተጠቀሙ እያወቁትና እየተለማመዱት መሄዳቸው ለእኛ ጥቅም ስላለው ነው።ያ የሆነው እያሻሻለውና እየተለማመደው እንዲሄድ ስለተፈለገ ብቻ ነው! በተረፈ ሁሉም ቁሳቁስ፣ ሁሉም የግኝት ውጤት፣ የልዑላችንና የእኛ ብቻ ነው።

‹ብተረፈ አንድ ሰው ብድግ ብሎ፣‹ቆይ.....ከዚህ ሽቦ ዘርግቸ ከዚያኛው ሽቦ ጋር ባገናኘውና ጠርሙሱን ባነካካው ብርሃን ሊሰጥ ይችላል!›ብሎ የጀመረና በዚያው ቀጥሎ የግኝት ባለቤት የሆነ የሰው ፍጡር የለም።ወይም ባህላዊ ጥሩንባን መነሻ በማድረግ ከወዲህ በኩል አንድ ውስጡ ክፍት የሆነ ረጅም ሽንበቆ ባደርግና፣ እኔ እዚህ፣ ሌላው ሰው እዚያ፣ ሆኖ የኔን ንግግር በሽምበቆው መሃል ባሳልፍ፣ያ ሰው ከወዲያኛው ጫፍ ሆኖ ጆሮው ላይ ቢለጥፍ፣ መደማመጥና ድምፅ መለዋወጥ እንችላለን ብሎ....ተነስቶና ምርምሩን ቀጥሎ ሽንበቆውን በሽቦ ተክቶ ሰፈርን ከመንደር እያገናኘ ስልክ ወደተባለው የቴክኖሎጂ ውጤት የተሸጋገረና ስስኬት የበቃ ሰብአዊ ፍጡር የለም፣ሊኖርም አይችልም። መጀመሪያ ነገር ሽቦን መፍጠር ያስፈልጋል። ሽቦን ለንፈጥር ደግሞ ሽቦ ከምን ከምን እንደሚሰራና የትኛውን የአፈር አይነት ተጠቅሞ፣ በየትኛው ዲግሪ አቅልጦ፣ በምን አይነት መንገድ ቅርፅ አስይዞ፣የሽቦ ገመዱን መስራት እንደሚቻል ማወቅ ያስፈልጋል። ይህንንም ለማወቅ የአፈር ምርምርን ጨምሮ የማዕድናቱን ንጥረ ነገር የምንለይባቸውን መሳሪያዎች መፍጠር መቻል የግድ ነው።ያንን ለመስራትም ሌላ ነገር ቀድሞ መስራት ያስፈልጋል።ያንን ሌላ ነገር ቀድሞ ለመስራትም ከዚያ በፊት ቀድሞ የተዘጋጀ ወይም የተሰራ ነገር ሊኖር ግድ ነው።እያሉ ስመቀጠል ከሁሉም በፊት የግዴታ በዶክመንት የተቀመጠ ፍርሙላ/ቀመር/ ያስፈልጋል።

ያ ማለት ይህ የምታዩት ነው።ይህ ነው በኛ በንጉሳውያን ቤተሰቦች እጅ ብቻ ይገኝ የነበረው ትልቅ ቅረስ! ይህንን ነው በዘመናችን የዓለም ህዝብ እንዲማረውና ወደ ተግባር እንዲለውጠው ያደረግነው።ይህ የእውቀት ቅርስ ነው በኛ ቤተሰቦች ተጠብቆ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየውና የዓለም የትምህርት ስርዓት/ካርኩለም/ ሊሆን የቻለው።

ይህ የእውቀት ቀመር ወደ ተግባር ይለወጥ ዘንድም ትምህርት ቤቶች መገንባት ነበረባቸው።የኛ ሰዎችም መምህር ሆነው ማስጀመር ነበረባቸው። ይህንን የእውቀት ማህደር መነሻ አድርገው ይማሩና ያስተምሩ ዘንድ ያደረግነው ደግሞ እኛ እና እኛ ብቻ ነን።እንጂ በአንዱ ቀመር ላይ ተመስርቶ አንዱ የቀጠለው፣በዚያ ሰው ግኝት ላይ ተመስርቶ ይህኛው ሰው ያቀጣጠለው፣ያኛው ሰው በጣለለት መሰረት ተነስቶ ይሄኛው ያሻሻለው....የሚባል ነገር የለም!ሁሉም መነሻ ቀመር ያስፈልገዋል። የሁሉም መነሻ ደግሞ ይህ ነው!ለሰዎች በሚመጥን መልኩ ተዘጋጅቶ፣ ከሰው በሚቀራረቡ ድቅሎች አማካኝነት ወደ ሰዎች እንዲደርስ የተደረገው የትምህርትና የእውቀት ማህደር ይህ ነው!

‹‹ወደዚህ ወደ መጨረሻው ክፍል ገብተን ይህን ማህደር እየገለጥን ወደ ተግባር እንለውጠው ዘንድ ሲፈቀድልንና ተግባራዊ ስናደርገው ሁሉም ሰለጠነ!!

‹‹ብዚህ መሰረት አገራችንን ኢንግላድን በፅኑ መሰረት መስርተንና ገንብተን ሃያል ሆንን።ምድራችንን በካርታ ከልለን አስፈላጊ አገራትን በስራችን አደረግን።በየአገራቱ የትምህርት ተቋማት እንዲገነቡ አድርገንም፣እዚህ ውስጥ ያለውን የዘመናዊ ትምህርቱን ቲዮሪ ለዓለም ህዝብ አዳረስን። የሉሲፌል ዋና መቀመጫ የምትሆነውን መናገሻ ከተማ ወይም አገር መርጠንና አዘጋጅተን ጨረስን።

ከዓለም አገራት እንድንሰበስብ የታዘዝናቸውን የማእድናት አይነቶች ሁሉ እያጋበስን በሁለቱ አገራችን ስናጠራቅም ቆዬን።

ቀጣይ ስራችን ምን ሆነ? ዘሮቻችን ያልኳችሁን እኛን መሰል ድቅሎች በኛ ዘንድ መቅረት ያለባቸውን አስቀርተን፣ ሌሎቹን አሜሪካ ላይ አፈሰስናቸው።በኢንግላድና በአሜሪካም ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የአውሮፓ ግዛቶች በየህዝቡ መሃል በማስረፅ፣ ልዩ ማንነታቸውን ማንም ግለሰብ በማያውቅበት መንገድ ተሰራጭተው እንዲኖሩ በማድረግ ቦታ ቦታ አስያዝናቸው። ምናልባት የድንቃ ድንቅ ጥበቦችና የምርምር ግኝት ባለቤት በሚሆኑ ጊዜ የዓለምን ህዝብ ትኩረት መሳባቸው አይቀርምና ከአድናቆት ብዛት ሰዎች፣ ‹‹ማናቸው?›› እያሉ ሊጠይቁ ይችላሉ በሚል ‹‹የአይሁድ ዝርያ ያላቸው››እየተባሉ እንዲታወቁ አደረግን።አይሁዳውያን ጥበበኞች ሆነው ሳይሆን እንዲሁ በዓለም ህዝብ እይታ የተለዩና የተመረጡ ህዝቦች

ተደርገው ስለሚሳሉ፣በዚህም ላይ በየዘመናቱ እተፈናቀሉ በየአገሩ ሲበታተኑ ስለኖሩ፤ ከዚያ ጋር አያይዘን እንደ ሽፋን መጠቀማችን ነው።ይህ ሽፋን በመስራቱም የዓለም ህዝብ ለዘመናት እኛ ላይ የተለየ ትኩረት ሳያደርግ ቆይቷል።እንጂ አይሁድም ይሁን ማንም የሰው ፍጡር የተለየ ጥበብ ያለውና የረቂቅ ግኝት ባለቤት መሆን አይችልም።ምናልባት ኢትዮጵያውያን የሐይማኖት ሊቃውንት ከሌላው ህዝብ የተለየ ለበላይ አካሉ ታማኝ ስለሆኑ እነሱ ብዙ መስራትና መፍጠር ካልቻሉ በቀር ማንም!የነሱም ውጤት ለዚያው ለበላይ አካሉ ግልጋሎት የሚውልና፣ በዚያው በአምልኮ ቦታው ተወስኖ የሚቀር እንጂ፣ለራሳቸውም፣ለህዝቡም፣ ለዓለምም፣ ጥቅም መስጠት የማይችል ነው።

‹‹ብተረፈ የልዑላችን ተከታይ ሆኖ፣በልዑላችንና በጭፍሮቹ አምኖና ታምኖ፣እነሱንም ተማፅኖ፣ካልተቀበለ በቀር፣ወይም በበላይ አካሉ አምኖና ታምኖ፣እሱንም ተማፅኖ፣ካልተቀበለ በቀር፣ የሰው ልጅ በራሱ ከየትም አምጥቶ የረቂቅ ጥበብ ውጤት የሆነ የግኝት ባለቤት መሆን አይችልም!በጭራሽ!አይሁድም ሰው ነው፣ሌላውም ሰው ነው።ሰው ደግሞ እኩል የአስተሳሰብ መጠን ታድሎት ተመሳሳይ ሆኖ የተፈጠረ ፍጡር ነው።ለማንኛውም የአይሁድ ዝርያ ከሚል ፕሮፖጋንዳ ጋር ነው በየአገሩ የበተንናቸው።

በዚህ አይነት ሁሉንም የቤት ስራችንን በተቀመጠልን የጊዜ ገደብና፣ በተሰጠን ቀመር መሰረት ተግባራዊ አድርገን ከተዘጋጀን በኋላ፣የቲዮሪው ትምህርት ወደ ተግባር ተለውጦ ተጨባጭ ውጤት ወደሚያሳይበት ቀጣይ ተግባር መግባት ነበረበት።ለዚህ ደግሞ ቀጣይ ትእዛዝ እስኪደርሰን መጠበቅ ነበረብን።

ምክንያቱም በየትምህርት ተቋማቱ ፊዚክስ፣ማትስ፣ባዮሎጂ፣ኬምስትሪ፣... እየተባለ የተሰራጨው ትምህርት በቲዮሪው ብቻ ተወስኖ እንዲቆይ ነው የተፈለገው።

‹‹እንደምታዩት የእያንዳንዱ ገፅ ትምህርታዊ እውቀት ወደ ተግባር ሲለወጥ ምን ሊያስገኝና ምን ሊከስት እንደሚችል በደንብ ይተነትናል።ለእነዚህ ተግባራዊ ሂደቶች ጥሬ እቃው ወይም ማዕድኑ አሊያም ሌሎች ረቂቅ ቁሳቁሶችና ቅጠላ ቅጠሎች ምን ምን እንደሆኑ በስፋት ይዘረዘርዝራል። እንዴት እንደሚመጠኑና እንዴት እንደሚዋሃዱ፣እንዴት ወደ ተግባር ተለውጠው ለውጤት እንደሚበቁ ግን ለጊዜው ግልፅ አልነበረም። ለእያንዳንዷ ፎርሙላ ተግባራዊነት ደግሞ አንዳንድ ራሳቸውን የቻሉ ከልዑላችን ወገን የሆኑ መንፈሳዊ አካላት የግድ ያስፈልጋሉ።

የልዑላችን የበታች የሆኑ እልፍ አእላፍ ሰራዊቶች ደግሞ የተለያየ አይነት እውቀትና ስልጣን ነው ያላቸው።ያንዱ እውቀት ስለ ማዕድናት ብቻ፣

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

የሌላው ስለ ቅጠላ ቅጠል ብቻ፣ያንዱ ስለ አፈር አይነት ብቻ፣የሌላው ስለከሰል ድንጋይ ብቻ፣ወዘተ...ነው። እንጂ አንዱን ብቻ ተገናኝተን ሁሉንም ነገር ማዘዝና የሁሉንም ጥያቄ ምላሽ ካንዱ ብቻ ማግኘት የሚቻልበት አካሄድ የለም።ለዚህ አይነቱ የሰው ልጅ እውቀትና ትግበራ ደግሞ ዋናው ልዑላችን መመሪያና ትእዛዝን ለታማኝ የበታቹ፣እሱም ለበታቹ፣የበታቹም ለበታቹ፣እያስተላለፈ ወደኛ የሚደርስ ነውና ለየትኛው ረቂቅ ጥበብ የትኛውን መንፈሳዊ ጭፍራ ማግኘት እንዳለብን የግድ ማወቅ ነበረብን።ምክንያቱም ለጥቅል ጉዳይ ካልሆነ በቀር ለእንዲህ አይነት በሰዎች ለሚሰራ ዝርዝር የሃሳብና የእውቀት ትግበራ ልዑላችንም ሆነ ታማኝ የበታቹ ትእዛዙን ከማውረድ ውጭ ስለማይመለከታቸው ሳይሆን፣የነሱ ድርሻ ስላልሆነ ሌሎች ከኛ በላይ ያሉ መንፈሳዊ አካላትን ብቻ ነው ልንገናኝና ሚስጥሩን ልናውቅ፣እውቀንም ወደ ተግባር ልንለውጥ የምንችለው።

በመጨረሻ በሰው አቆጣጠር በ17 70 ዓ.ም ተከታዩ ትእዛዝ ደረሰን። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ማለትም የመጨረሻውን 6ኛውን ክፍል ተግባራዊ አድርገን እስክናጠናቅቅና፣ተከታዩን ትእዛዝ እስኪደርሰን ድረስ፣የመጨረሻ ጎላችን የትኛዋ አህጉር ውስጥ የምትገኝ ምን የምትባል አገር እንደሆንች አናውቅም ነበር።ይህ ለኛ ገና አልተገለፀልንም ነበር።

እናም ትእዛዙ ደረሰን።አዲሲቷን የምድር መንግስት በዘመናዊ መልክ የመገንባት ስራችሁን ጀምሩ ተባልን።

ይህ ማለት የቲዮሪው ትምህርት በሙሉ ወደ ተግባር ተለውጦ፣ተጨባጭ ውጤት ወደሚያስገኝበትና፣ወደ ሌላ አዲስ የስልጣኔ ሽግግር መግባትና ማስቀጠል መቻል ተፈቀደልን ማለት ነው።

ይህ ማለት በዚህ መፅሀፍ ውስጥ እንደሌሎቹ ያልተብራሩ፣በስም ብቻ የተጠቀሱና፣ እኛ ድቅሎችና የሰው ልጅ ከስማቸው በቀር አይነታቸውንና መገኛ ቦታቸውን የማያውቃቸውን ነገሮችም ሆነ፣በምድርና በውስጧ ያሉ በርካታ ጠቃሚ የሆኑ ተጨማሪ ረቂቅ ማዕድኖች የሚገኙበትን ቦታ፣ የትኛው ነገር ከምን ጋር ሲጣመርና ሲዋሃድ ምን እንደሚያስገኝ፣የዚያ ግኝት መጨረሻ ምን እንደሚሆንና ሰዎች በምን መንገድ ጥቅም ላይ አውለው ሊገለገሉበት እንደሚችሉ፣እየተሻሻለ ሄዶ የት እንደሚደርስና ሄዶ ሄዶ እንዴት ለልዑላችን ዋና ዓላማ ሊውል እንደተፈለገ ግልፅ ሆነልን ማለት ነው።ይህ ማለት ጎላችንንም እንድናውቅ ተፈቀደልን ማለት ነው!

እናም እነዚህን ነገሮች የሚያብራሩ ቁጥራቸው የበዛ መንፈሳዊ ጭፍሮች እንዳሉና እነሱን እንድንገናኝ ተነገረን።ቀጣይ ትእዛዝ ያልኳችሁ ይህንን ነው።እንጠብቀውና እንፈልገው የነበረውም ይህንኑ ነው።

ስለዚህ እነዚህን የልዑላችን ጭፍሮች በስምና በስልጣን ለይተንና አውቀን፣ የትኛው መንፈሳዊ አካል በምን አይነት ጉዳይ እንደተሾመ ተረድተን፣ የትኛው ለየትኛው እውቀትና ጥበብ ሲረዳን እንደሚችል ተገንዝበን፣ ሁሉንም በስማቸው እየጠራን ማዘዝና ለምንፈልገው ዓላማ አማካሪ ማድረግ እንደምንችል ተነገረን፡፡ነገር ግን እነሱንም ለማወቅና ለመገናኘት፣ ተገናኝተንም ጥበባቸውን ለመካፈልና ለመጠቀም እንቻል እንጂ፣ፈልገን የማግኘቱ ስራ ግን ለኛ ለንጉሳውያን ቤተሰቦች የተተወ የቤት ስራ ሆነ፡፡

‹‹የሰው ልጅ የመጀመሪያ ዕህፈት በሆነው፣ከሰው ልጅ ጋር በጥፋት ውሃ በዳነው፣የግዮን ምንጭ ባለበት አገር፣በአንድ ደብር የተቀመጠው፣ሚስጥሩን ማንም ባልፈታው፣በሄኖክ መጽሐፍ ሁሉንም እወቁት፣ሁሉንም ድረሱበት፤ ይህ የእናንተ ስራ የሆነና በእናንተ መሰራት ያለበት ነው፡፡የእናንተ የዘር ሃረግ የሚመዘዘው ከእነማን እንደሆነ የተዘረዘረበት መጽሐፍም ስለሆነ የእያቶቻችሁን ቅድመ አያት ዋና ምንጭ የምታገኙበትም ስለሆነ አግኙት፡፡ ታሪክና ማንነታችሁን እዚያ ስታገኙ፤ ማን በምን ላይ እውቀትና ጥበብ እንዳለውም፣ማን በምን ላይ እንደተሾመ፣ከዚያው መጽሐፍ ትረዳላችሁ፡፡ ከአምስቱንም የሄኖክ መጻህፍት አግኙ››የሚል ትእዛዝ ነበር የደረሰን፡፡ ጎላችን አወቅን ማለት ነው፡፡

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ሽግግሩ ጉብተን አዲሲቷን የምድር መንግስት ምስረታ እጅግ ዘመናዊ በሆነ መንገድ ጀመርን፡፡

‹‹ስለ መጽሐፈ ሄኖክ ከዚህ ቀደም በደንብ ተብራርቶላችኋል፡፡መጽሐፈ ሄኖክ፣ሚስጥረ ሄኖክ፣ራዕየ ሄኖክ፣ትንቢተ ሄኖክ፣ ነገረ ሄኖክ፣የሚባሉ ናቸው፡፡በእርግጥም ለኛ የጠቀመንና አሁን ለምንለው ነገር ሙሉ ምላሽ የነበረው ሚስጥረ ሄኖክ የሚለው ነው፡፡

‹ብዚያ የልዑላችን ታማኝ አገልጋይ የሆኑት አጠገባችሁ ያሉት ጳጳስ ቀደም ሲል በደንብ እንዳብራሩላችሁ፤ የኔ ቅድመ አያት ተብላ ምትታወቀው፣ነገር ግን እኔ ራሴ!ከኛ ወገን የሆነውን ጀምስ ብሩስን በ 1770 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብና በቂ ስንቅ አስይዘን ላክነው፡፡ሁሉንም የሄኖክ መጻሕፍት አገኛቸው፡፡በ7 ዓመት ቆይታው መጽሐፈ ሄኖክን አዘባርቆና ቀሪ ትቶላቸው፤ ሌሎችን ግን ቀሪ ሳይተው፣ይዞልን መጣ፡፡በ7 ዓመት ቆይታው በኛ ትእዛዝ ተምሮት እንዲመጣ በተደረገው በግእዝ ቋንቋ፤ የግእዝን የመጀመሪያ ዕሁፍ በቤተ መንግስታችን አብራራልን፡፡ አቤት የተደሰትነው ደስታ...........!ያኔ እንዲህ እንደዛሬው ውስጥ አብርቶ ቋንቋን እንዲሁ መሞላት መቻልና በግእዝም ልዑላችንን እስከማምለክ የተደረሰበት ዘመን አልነበረም፡፡

እናም መጻሕፍቱን አስረከበን፡፡ሚስጥረ ሄኖክ ለጥያቄዎቻችን ሁሉ ምላሽ የሚሰጠንን መንፈሳዊ አካላት በስም ከመዘርዘር አልፎ፤ ከፒራሚዶችን

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

በላቲን ቋንቋ ተረቆ ከተሰጠን ቅድም ካያችሁት መፅሐፍ ጋር በማጣመር ብቻ ያለማንም እገዛ በኛ እውቀት ወደ ተግባር የምንለውጠውን ጥበብ እስከማሳወቅ የደረሰ ሆነ።

በእርግጥ ሄኖክ የበላይ አካሉ ተከታይ የሆነና ተነጥቆ ወደ ሰማይ የሄደ ነውና፤ በመጽሐፉ የበላይ አካሉን እያሞገሰ፣ የኛን ዘሮችና የልዑላችን ዓላማ እያወገዘ፣ ነበር የፃፈው።እኛ ግን በተቃራኒው በመፍታት ለወሳኝ ግብዓትነት ተጠቀምንበት።

በሚስጥረ ሄኖክ ሁሉ በእጃችን ሁሉ በደጃችን ሲሆን፣በመጽሐፈ ሄኖክ እኛ የተደቀልንባቸውን የመጀመሪያ የዘር ሃረጋችንን ከነሙሉ ታሪካቸው በግልፅ አወቅን።በጦርነቱ ስለተሰው ዘሮቻችንም በጥልቀት ተረዳን።በራእየ ሄኖክ እንዴት አድርገን ልዑላችንን በመጨረሻው ጦርነት እንደምናግዝ ተረዳን።በራእየ ሄኖክ የበላይ አካሉ ልዑላችንን እንዴት አድርጎ በፍፃሜው ጦርነት ድል እንደሚነሳው የተገለፀበትን ታሪክ መነሻ በማድረግ፣እንዴት መከላከል እንዳለብንና እንዴት ልዑላችን በኛ እገዛ ለድል እንደምናበቃው ተገነዘብንበት።በትንቢተ ሄኖክ የበላይ አካሉ እንዴት የመላእክቱን ጭፍሮች እንደሚያዘምትና እንደሚያሰልፍ ተረድተን፣የራሳችን አወቃቀርና አሰላለፍ እንዴት ማድረግ እንዳለብን ተገነዘብንበት።

‹‹የሔኖክ መጻሕፍት ከኢትዮጵያ መጥተው እጃችን ከገቡ በኋላ፤ በራሳችን መንገድ ተንትነን ጥቅም ላይ በማዋል ወደ አስደናቂ የሽግግር ዘመን ተሻገርንባቸው!የዘር ማንዘሮቻችንን ታሪክ መጽሐፉ እጃችን ሲገባ በስማቸው ሳይቀር ተዘርዝሮ ስናገኝም በቤተ መንግስታችን ታላቅ ፌሽታ ሆነ።

ከኛ ጋር በመገናኘት የልዑላችንን ትእዛዝ የሚያሳውቁን የነበሩና፤ በኛ ለሚፈፀመው ስራ ዝርዝር ትእዛዝ ተቀብለው የሚያዙን የልዑላችን ጭፍሮች ከዚህ ታሪካዊ መጽሐፍ መገኘት በኋላ፤ የነሱ በመልዕክተኝነት የማገልገል ቆይታ እንዳበቃና በቀጥታ ከዘሮቻችን ጋር መገናኘት የምንችል መሆናችንን፣ከዚያ በኋላም ሁሉም ነገር በዘመናዊ መልክ እንደ አዲስ ተዋቅሮ የአዲሲቷ የምድር መንግስትን ምስረታ ሂደት መጀመርና መቀጠል የምንችል መሆናችንን አብስረው በደስታ ተሰናበቱን።

እኛም በቀጥታ ከዋና ዋና ከገዛ የዘር ሃረጎቻችን መናፍስት ጋር በነፃነት እየተገናኘን የልዑላችንን ዓላማ የሚያሳካውን መንገድ ሁሉ በምንታዘዘው መሰረት በዘመናዊ መልክ አዋቅረን ቀጠልንበት።

በምንፈልገው ጉዳይ ላይ ማናቸውን ማዘዝና ማማከር እንዳለብን እውቀናልና ሁሉንም በስም እየጠራን፣ የሚገባቸውን መስዋዕት እያቀረብን፣ ማዘዝና የተሰወረውን መግለጥ፣ገልጦም ወደ ተጨባጭ ነገሮች መለወጥ ቻልን።ከዚህ መጽሐፍ መገኘት በኋላ እየመነጠርን ያዘጋጀናትን

ፍሥሐ ያዜ

ከተማ በቀደምት ዘሮቻችን መጠሪያ ስም እየሰየምን፣በየኮከብና በየምልክታቸው አርማ መሰረት የህንፃዎችን ግንባታ እያከናወንን፣ ድንቅ አድርገን አሜሪካ የተባለችውን አገር በመታሰቢያ ህንፃዎች አንቆጠቆጥናት፡ ፡ሰዎቻችንን አስፈርን!የጥበብ መፍለቂ የሆነች፣የኛን የራሳችንም አገር ጨምረን በእንግሊዝ፣ በአሜሪካና በግዛታችን ካናዳ ሳይቀር ለዋና ዋናዎቹ የዘር ግንዶቻችን ሀውልት አቆምን፡፡ስልጣኔ ተቀጣጥሎ ቀጠለ፡፡የአዲሲቷ የምድር መንግስት ምስረታ በዘመናዊ መልክ ቀጥሎ ማንም ህዝብ ዛሬ ድረስ ሳያውቀው ያማረና ቅርፅ የያዘ ሆኖ ታዬ፡፡.....!››አሉና፤ እንደ ህፃን ልጅ ፍልቅልቅ የሚል ገፅታ እያሳዩ፤ በሳቅ እየተንከተከቱ መድረኩ ላይ እንደመዝለል አሉና ቀጠሉ፡፡

‹‹አዎን!እያንዳንዱ የጥበብ ውጤት፣የቴክኖለጂ ውጤት፣የሳይንስ ውጤት፣ የምርምር ውጤት፣ በልዑላችንና በጭፍሮቹ የተገኙና በኛ በባለተልዕኮዎች አማካኝነት ወደ ተግባር ተሰውጠው ለውጤት የበቁና ለምድር ህዝብ እንዲደርሱ የሆኑ ናቸው!

ይህ የእውቀት ቀመር በፒራሚዳችን እጅግ በተራቀቀ መንገድ በተግባር መተርጎም ከጀመረ 7 ሺ ያህል ዓመታት ቢሆነውም፤ ውጭ ያለውና ተጠቅልሎ በልዑላችን ስር መሆን እንዳለበት በታመነበት በኋላ ቀሩ የምድር ህዝብ ዘንድ መታወቅና፤ ወደ ተግባር እየተለወጠ ወደ ስልጣኔ ደረጃ እንዲያደርሰው የተፈለገው ግን ቀስ በቀስና በዝግታ ነበር፡፡እኛም ይህን የእውቀት ቀመር ለዓለም ህዝብ ስናዳርስ ውስንና ለሰው ልጆ ስልጣኔ በቂ ነው ተብሎ የታመነበትን ብቻ እየመረጥንና እየመጠንን ነው ማስተማር የቀጠልነው፡፡

እናም ከልዑላችንና ከተከታዮቹ ጎን ቆመን፣የእርሱን ረቂቅ ጥበብ እየተካፈልንና ለዓለም ህዝብ እያካፈልን እዚህ ደረስን!››ሲሏቸው፤ ተሰብሳቢዎችና የቫቲካኑ ጳጳስ በጋራ ተነስተው አዳራሹን በጭብጨባ አደመቁት፡፡

‹‹ክብር ለልዑላችን!››ሲሉ፤

‹‹አሜን!››አሉና፤በአድናቆት አጨብጭበው ልዑላቸውን አመስግነው ተቀመጡ፡፡

‹‹ልቀጥል››፤አሉና፤መሃል ላይ የነበረውን ግዙፍ ጥራዝ አንሸራተው ወስደው ግድግዳው ላይ በመለጠፍ፤ግድግዳውን ሙሉ በሙሉ በስፋ ስክሪን ለወጡት፤ወይም ሸፈኑት፡፡ከዚያ ደግሞ ዱር ይዘው ቆሙና ወደ ስክሪኑ እያዩ፤ከስክሪኑ ጋር ማውራት ጀመሩ፡፡

‹‹አባቶቻችሁ››ሲሉ ጀመሩ፡፡

‹‹አባቶቻችሁ በየዘመናችሁ ተመራምራችሁ ዓለምን መለወጥ የቻላችሁ፣ የረቂቅ ግኝት ባለቤቶች የሆናችሁ፣በዘር ሃረግ ከኛ ወገን የሆናችሁና

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ ... ምክንያት በዘር ሃረግ ከማንም ጋር ያልሆናችሁ፣ነገር ግን በልዑላችን ምክንያት በዘር ሃረግ ከማንም ጋር ያልሆናችሁ፣ የልዑላችን ታማኝ ልጆች ሳትበላለጡ በእኩልነት ቤተሰብ መሆን የቻላችሁ፣የልዑላችን ታማኝ ልጆች የሆናችሁና፣ ለጊዜው ከምድር ህይወት የተለያችሁ፣ከተለያችሁም ረጅም ዓመታት ያለፋችሁ፣አብረቅራቂውን ስጋ ለብሳችሁ ያላችሁ፣ከልዑላችን ድል በኋላ የምንገናኝና እንደሌሎች ሹማምንት የምትሆኑ ሊቃውንቶቻችንና ሳይንቲስቶቻችን፣አንድ አፍታ ጎራ በሉ።።ጎራ በሉና ለተሰብሳቢዎች ታይታችሁ፣የምንለውን ነገር አጠናክራችሁ፣ በዚያውም ወንድማዊ ሰላምታችሁን አቅርቡላቸው.....››ካሉ በኋላ፤ ፈገግ አሉና፤ ከሰፊው ስክሪን ጻር ላይ ሆነው፤እጆቻቸውን አጣምረው ቆመው መጠበቅ ጀመሩ።።

የማይታመን ክስተት ነበር!ነገሩ ሁሉ ብታምኑ እመኑ ባታምኑ ተውት!የሚባል አይነት ነው።።

እኒህ የሰይጣን ቁራጭ የሆኑ ትባጣ አርጊት የእንግሊዝ ንግስት፤ ይህን ብለው ጥጋቸውን እንደያዙ፤የእንግሊዝና የአሜሪካ ዜግነት የነበራቸው የቀድሞ የግኝት ባለቤቶች ጥቁር በጥቁር ለብሰው፣ጥቁር ቦት ጫማ ተጫምተው፣ግር ብለው እየተጋፉ በሰፊው ስክሪን ውስጥ መታየት ጀመሩ።
።

ከዚህ ቀደም የሞቱት የቀድሞው የቫቲካን ጳጳስ ለዚህ መሰል ምስክርነት በስብሳቢው ጳጳስ ተጠርተው በስክሪኑ እንደታዩትና፤ ስክሪኑን አልፈው መጥተው አዳራሹ ውስጥ የነበሩትን ተሰብሳቢዎች በእጅ ሰላምታና በመተቃቀፍ እንደተገናኙዋቸው ሁሉ፤እነዚህም ስክሪኑን አልፈው ወደ አዳራሹ ሊመጡ መሆኑ ነው ግፊያው።።

ግፊያው መበርታቱን የተረዱት ንግስት ከነበሩበት ከስክሪኑ ጥግ ተነስተው ተንደርድረው ወደ መሃል በመሄድና ፊት ለፊት በመቆም እጃቸውን ግራና ቀኝ ዘርግተው ቤተሰባዊ ፈገግታቸውን እያሳዩ፤‹‹ኢ ኢ ኢ...ሁላችሁንም አላልኩም!ጥቂቶቻችሁ ብቻ በቂ ናችሁ›› ብለው ግፊያና ትርምሱን ሊያረግቡ ሞከሩ።።

በበኩሌ ይህን ሳይ በመገረምና በመደነቅ ፋንታ ሳቅ ነው የቀደመኝ።። ምክንያቱም እነዚያ ታላላቅ የተባሉና ሂማቸውን ያንገዘረገጉ ታዋቂና የበሰሉ፣ የሸመገሉ፣ የተደነቁ፣ ሳይንቲስቶች እንዲህ ለመታየት ሲሻኮቱ፣ ሲጋፉ፣ ሲገፈታተሩ፣ ማየት፤ በምትሃታዊ ክንውኑ መደነቁን ወደጎን አስደርጎ ለሳቅ ቅድሚያ እንድንሰጥ ስለሚያስገድድ ነው።።እናም ፍርስ ብዬ ጨምሮ እንደኔ ፍርስ ብለውም ባይሆን ሰቀዋል።። ... ጳጳሱንም ንግስቲቱንም ነገረ ስራቸው በአንድ የገጠር አካባቢ ካሜራ የያዙ ቱሪስቶች ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጆች አካባቢው ላይ ቀረፃ ሲያካሂዱ፤የገጠሩ

ሀዋናት በሚሄደው ለመቀደስ፣ከሚሄደውን ለማየትና በሚሄደው ለመታየት እየተገፋፉተቁ እንደሚያዩት አይነት ነው፡፡ከሚሄዱን የሰፊው ሳይንቲስት ፊት ለመታየት እብሮ እየተጋፉ ይታያል፡፡

ከፍተኛ ግፊያና ትርምስ ሆኖ፡በእርግጥም ሁሉም ቢገፉ አዳራሹም ሳይበዛ ይችላልና ንግስቲቱ ፈገግታቸውን ቀጠው አድርገው ከሰተር በማለት፣

‹‹ጊዜ የለንም ወንድሞች፣ጥቂቶቻችሁ ትበቃላችሁ፡፡ እዋኝችሁ››አሉ፡፡ ሊሰሟቸው የፈለጉ አይመስሉም፡፡ግፊያቸው ቀጠለ፡፡ትርምሱ በረታ፡፡

በዚህ ጊዜ ንግስቲቱ ጠንከር ብለው፣‹‹እንዲያ ከሆነ እኔ የምጠራችሁ ብቻ ቅረጡላችሁ››አሉና፣ምላሻቸውን ሳይጠብቁ ወደ ትእዛዝ ለውጠው ስም መጥራት ጀመሩ፡፡በዚህ ጊዜ ተጋፊዎቹ ግፊያውን ረገብ አድርገው ስም ለማዳመጥ ተዘጋጁ፡፡ንግስቲቱ በግፊያው ጠንከር ብለው ከሰከራት ፊት መገኘት የቻሉትን መርጠው ሊጠሩ ፈለጉና፣መልሰው ሃሳባቸውን በመሰወጥ፣‹‹አ አ አ እንዲያውም በጉባኤያችን ሳብራራው ከነበረው ጉዳይ ጋር በቀጥታ የሚገናኝና ጥሩ ምሳሌ መሆን ችሎ የያዝነውን ሃሳብ በደንብ አጠናክሮ መግለፅ በሚችል ዘርፍ ድንቅ ስራ የሰራችሁትን ጥቂት ሊቃውንትን ልምረጥ፡ሌሎቻችሁ ለጊዜዓ ሳይሆን፣ ለሰላምታ መምጣት ትችላላችሁ››ካሉ በኋላ፣‹‹አ…ቶማስ፣አሌክሳንደር፣አንስታይን……››ብለው ተጣሩ፡፡

አንዱ ከፊት ሁለቱ ከኋላ ነበሩና ለመውጣት ሲሽቀዳደሙ፣

‹‹ቶማስ ቅደምና ከልዑላችን ጭፍሮች ጋር በመገናኘት ምን እንደሰራህና የሰራህው ስራ ለምን ግልጋሎት እንደሚውል፣ሰው በራሱ ምንም ማድረግ እለመቻሉንና ተያያዥ ነገሮችን በአጭር ቃል አብራራልኝ›› አሉት፡፡

ቶማስ አልባ ኤዲሰን ሙሉ በሙሉ ጥቁር የሆነና የወታደር የዝናብ ልብስ የመሰለ ባለኮፍያ እስፈሪ ልብሱን ለብሶ፣ጥቁር ቦት ጫማ ተጫምቶ፣ የዚያውን ዘመን ስታይል እንደያዘ መስስ ብሎ፣ ስከሪኑን አልፎ የአዳራሹን ወለል ረገጠ፡፡ይህ ሲሆን፣ከጳጳሱ፣ከአሚሪካውና ከእንግሊዙ መሪ በስተቀር ሁሉም ተሰብሳቢዎች ግመን እቅፈቸው ሳቃቸውን በግርምት ለውጠው በአንድነት ብድግ ብለው ቆሙና መድረኩ ላይ አፈጠጡ፡፡

ቶማስ ኤዲሰን ለንግስቲቱ በትህትና የተሞላ ሰላምታውን አቅርቦና የእንደ እጃቸውን አይበሉባ ስሞ ከለቀቀ በኋላ፣ወደ ተሰብሳቢዎች ትኩረቱን አድርጎ ጎንበስ በማለት የርቀት ሰላምታውን አቀረበ፡፡ከዚያም በዝግታ ገለጻውን ጀመረ፡፡

‹‹ክብር ለልዑላችን!››ክግርምትና ከድንጋጤ ብዛት በቅጡ አሜን ያለ የለም፡
:

‹‹አሜን!በሉ እንጂ ከሁራን››ሲላቸው፣‹‹አሜን››አሉ ተዝቀዝቀዝ ብለው፡፡ቶማስ ኤዲሰን ቀጠለ፡፡

‹‹የትኛው ሰው ነው በራሱና በራሱ ጥረት ብቻ የኔን የመጀመሪያ ግኝት ማግኘት የሚችለው?››ሲል ጀመረ፡፡‹‹ከኔ በፊት የነበሩትም ሆነ እኔ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው በራሱ ሂደት ጥረትና ትጋት ለዚህ ግኝት ሊበቃ ቀርቶ ሊያስበው የማይችል ነገር ነው፡፡ስለዚህ ከኔ በፊት መሰረቱን የጣሉት የኛ ወገኖችም ተመሳሳይ ግንኙነት በመፍጠር ነው ወደ ተግባር የገቡትና ለኛ መነሻ መሰረት ሊጥሉልን የቻሉት፡፡

‹‹በወቅቱ እኔ ባራቅኤል……ከተባለ መንፈሳዊ አካል ጋር ነበር ግንኙት የጀመርኩት፡፡የኤሌክትሪክ ብርሃን መፍጠር! ፖዘቲቭና ኔጌቲቭ በሚባለው ቀመር እያገናኘሁ በንዝረት የኤሌክቲሪክ ሃይልን መፍጠር መቻልና ለዓለም ማበርከት፣ ማስተዋወቅ፣ ያንተ ስራ ነው ስባል፤ስቁና ደንግጬ ነበር፡፡ሆኖም እንዴት እንደምጀምረውና የትኛውን ግብዓት መጠቀም እንዳለብኝ ሲነገረኝ፤ሊሆን የሚችል መሆኑን እያሰብኩ፤ነገር ግን እየተጠራጠርኩ ማዳመጥ ጀመርኩ፡፡ምክንያቱም እኔ የዘር ሃረጌ ተሽራርፎና ተመናምኖ ወደ 5 ፐርሰንት ደርሶ፤ሳላውቀው ሙሉ በሙሉ ወደ ሰው እየተሺጋገርኩ የነበርኩ ነኝ፡፡እና…..አፍሪካ ብለን በሰየምናት አህጉር ውስጥ ወዳለች አንዲት አገር እራሱ የልዑላችን ጭፍራ ከሰው እይታ ውጭ በሆነ የአበራረር ዘዴ ሊወስደኝ እንደሚችል ነገረኝ፡፡እኔም በዲስኩ ተጭኜ ለመብረር ዝግጁ መሆኔን ገለፅኩለት፡፡ወዲያውም ከተቀመጥኩበት አንስቶ በማንጠልጠል ይሁን በማቀፍ ይዞኝ በረረ፡፡ በብርሃን ፍጥነትም ቦታው ላይ ደርሽ፤በቂ ገለፃ ተደርጎልኝ፣ትምህርቱም ተሰጥቶኝ፣ ግብዓቶች ተብራርተውልኝ፣ ሁሉንም የመሞከሪያ ቁሳቁሶች ይዤ ተመለስኩ፡፡ሌላው ስራ ለኔ የተተወ ነበር፡፡የቲዮሪ እውቀቱን ተጠቅሜ ይዥቸው የመጣሁትን ግብዓቶች እየተጠቀምኩ ስሞክረው ሰራ!ባጭሩ የግኝቱ ባለቤት እኔ እንደሆንኩ ዓለም ይመን እንጂ ፈፅሞ በሰው ልጅ ሊሞከር የማይቻለውን ነገር ሞክሬ ለውጤት መብቃት የቻልኩት ከልዑላችን የበታች ከሆኑ አስደናቂ መንፈሳዊ አካላት ጋር በመሆን ነው!ያለ እነርሱ እገዛ እውቀትና ስልጣኔ እንደሌለ፣እንዳልነበረና፣ወደፊትም እንደማይኖር ሁላችንም መረዳት ነበረብን፡፡እናም የኔን ግኝት ይፋ አድርጌ፣ ተከታዮች እንዴት መቀጠል እንዳለባቸው ጠቅሼ፣ ካቆምኩበት የሚቀጥልበትን ሁኔታ አመቻችቸና፣ በላቲን ፊደል በምንቀምረው ዘዴ ምንጩን ጠቅሸ፣የ666 ግኝት መሆኑን አብራርቸ፣መጨረሻም ለሱ ግልጋሎት የሚውል መሆኑን አስምሬበት፣ቀጣዮቹ ተመራማሪዎችና ኢንጂነሮች ማን ከሚባሉት መንፈሳዊ አካላት ጋር መገናኘት እንደሚኖርባቸውና፤ ጥያቄ ሲኖራቸውም ማንን እየጠየቁ መረዳት እንዳለባቸው ገልጬ፣ የምድር ዘመኔን ጨርሼ ምድርን ለጊዜው ተሰናበትኩ፡፡አሁን ዓለማችን በቀንና በምሽት በብርሃን ተጥለቅልቃለች!ያለ

ኤሌክትሪክ ሃይል ዓለምና ህዝቦቿ ለአንዲት ደቂቃም መኖር አይችሉም፡፡ ቢችሉም እንደቀድሞው የጭለማ ዘመን አይነት ኑሮ ነው፡፡ሁሉንም ሰው አሰልጥኖ ለልዑላችን ጠቅልሎ ለማስገዛትና ኢትዮጵያ ላይ ለማካሄደው የመጨረሻ ጦርነት አጋዥ ይሆነው ዘንድ በኔ ስም ይፋ የሆነው ይህ የኤሌክትሪክ ሃይል የግድ አስፈላጊ ነው!ከኔ በኋላ በተሻሻሉ አዳዲስ የልዑላችን ጥበቦች ዓለማችን ሰልጥና እዚህ ደርሳለች፡፡ዩራኒየም አብላልቶ ኒውክሌር ለመስራት የኤሌክትሪክ ሃይል አስፈላጊ ነው፡፡ሁሉንም ነገር ለማድረግ የኤሌክትሪክ ሃይል ዋና ግብዓትና የጀርባ አጥንት ነው፡፡በዚህ መሰረት የጥበቡ ገላጭ ልዑላችን ነው፡፡በመጨረሻም ለሱ ግልጋሎት ብቻ የሚውል ነው፡፡እስከዚያው ግን ሰው እንዳሻው ሊጠቀምበት ይችላል……፡፡ ››እያለ በመተንተን፣ምሁራዊ ቃላቶችን እየተጠቀመ በማብራራትና በመግለፅ የግኝቱ ምንጭ ከሰው በላይ ያሉ የሳጥናኤል ጭፍሮችን በማማከር የተገኘ እንደሆነና፣የግኝቱ ውጤትም ሄዶ ሄዶ በስተመጨረሻ ለራሱ ለልዑላቸው ግልጋሎት የሚውል መሆኑን ሰፋ ባለ መልኩ ደስ እያለው አስረዳ፡፡

ከዚያም ከመድረኩ ወርዶ ጳጳሱንና የ G 20 አገራት መሪዎችን በናፍቆት ዓይን እያየ፣ አቅፎ እየሳመ፣‹‹እንኳን ደስ አላችሁ! ዘመኑ መድረሱን ለእናንተ ለመሪዎች ውጭና ውስጥ የማብራት ስልጣን ልዑላችን እንደሰጣችሁ በማየታችን አረጋግጠን! ደስ ብሎናል!እናም እንኳን ደስ ያላችሁ!››እያለ ሁሉንም እያቀፈ ከሳመ በኋላ፣ንግስቲቱንም እጅ ነስቶ ወደ ሰፊው ስክሪን አምርቶ ተራምዶት በማለፍ ከመሰሎቹ መንጋዎች ተቀላቀለ፡፡

ቀጥሎ እድሉ የተሰጠው የስልክ ፈልሳፊ እንደሆነ የሚነገርለት አሌክሳንደር ቤል ግራሃም ነበር፡፡እሱም በተመሳሳይ ባለከፍያውን ጥቁር ሙሉ ቱታ ለብሶና ጥቁር ቦት ጫማውን ተጫምቶ፤ የተንዠረገገ ፂሙን በአንድ እጁ እያሻሸ፣በሌላ እጁ ጀርባውን እያከከ፣ ስክሪኑን አልፎ ወደ አዳራሹ በመምጣት ሰላምታውን ካቀረበ በኋላ ገለፃውን ቀጠለ፡፡

‹‹ክብር ለጭለማው ልዑል!››አለ አቀርቅሮ መሬት መሬት እያየና ፂሙን እያሻሸ፡፡

‹‹አሜን!››

‹‹የሁላችንም መነሻ መሰረት የቲዎሪው ትምህርት ነው፡፡ያን ቲዎሪ ከኛ በፊት የተማሩትና ትምህርቱ ከኛ እኩል በደንብ የገባቸው ነበሩ፡፡የኛ ወገን የሆኑና እኛንም ሰውኛ ትምህርታችን በየዩንቨርስቲው ያስተማሩን ቀደምት ሊቃውንት በቲዎሪው መሰረት ከኛ በፊት ሲሞካክሩ ነበር የቆዩት ይባላል፡፡ ግን ለውጤት ሊበቁ አልቻሉም ይባላል፡፡ለካ ውሸት ነው፡፡ለምሳሌ እኔን ያስተማረኝ አንድ የማደንቀው መምህር ነበር፡፡ሲያስተምር ጎበዝ ነው፡፡

ቲዮሪውን ተንትኖ እያስረዳ ሲያስተምረንና ሲፈትነን ግን ያስቀኝ ነበር። ይህን ሁሉ ካወቀ ለምን ወደ ተግባር ለውጦ አንዳች ነገር ሰርቶ አያሳየንም? እል ነበር።እንዲህ ቢሆን እንዲህ ይሆናል እያለ ካስተማረ፣ አድርጎ ማሳየት አለበት!እያልኩ እሟገት ነበር።ለካ በወረቀት የተማረውን እንዲሁ ለኛ በወረቀት ያስተምራል እንጂ፣ ራሱ የሚጠቅሰውን ግብአት የሚሆን ቁስ ራሱ መምህሩ ጨርሶ በአይኑ አይቶት አያውቅም።እቃው ስም አለው፣ሁሉም ግብዓት ስምና ቅርፅ ተሰጥቶት ነው የምንማረው። አይነቱና መልኩ ግን አይታወቅም አይነት ነገር ነው።ያን እየተማሩ መቆየት የመጀመሪያው ተግባር መሆኑ ቆይቶ ነው የገባኝ።
ስለዚህ እነሱ የጀመሩትን ምርምር ነው የቀጠልነውና ያሻሻልነው የሚባለው ነገር ሙሉ በሙሉ ውሸት ነበር።ቲዮሪው ብቻ ነው የነበረው።ቲዮሪዎቹ ደግሞ ትምህርት ከመሆናቸው በፊትና በትምህርት መልክ ከመሰጠታቸው በፊት፣ ተሞክረው የተረጋገጡ መሆን ይኖርባቸዋል።ታዲያ ከኛ በፊት ማን ሞክሮ አረጋግጧል?እኔ የኤሌክቲሪካል ኢንጅነሪንግ ተማሪ ሆኜ አሳልፌያለሁ።ማነው የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግን ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ ያዘጋጀው?ቲዮሪው ይሄ ነው ብሎ የሰጠን ማነው?በየትኛው ዘመን ተሞክሮ ለውጤት በቅቶ ነው ይህን ተማሩ የምንባለው?እያልኩ እጠይቅ ነበር።መምህሮቻችን መልእክታቸውን በወረቀት ፅፈው፣ፈረስ እየጋለበ በሚሄድ መልእክት አድራሽ ሰው አስይዘው ወደ ቤተሰቦቻቸው እየላኩ፣ እኛን ግን በድምፅ ንዝረት መልእክትን ከአንድ አገር ወደሌላ አገር ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ዘዴ ያስተምሩን ነበር።
ለምሳሌ እኔ ድምፅን በንዝረት አማካኝነት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የማስተላለፍን ነገር ልሞክር ብል ግብዓቶቹን ከየት አመጣቸዋለሁ?ትምህርቱ ላይ የመገኛ ቦታቸው አልተካተተም! ማን ሊደርስበት ይችላል?እስቂኝ ነገር ነበር።
በመጨረሻ ሽማዝኤል ከተባለው መንፈሳዊ ጭፍራ ጋር እንድገናኝ ተደርጌ መገናኘት ቻልኩና ድምፅን በንዝረት መልክ ወደሌላ አቅጣጫ መላክና ሌላው ተቀባይ አካል ያን ድምፅ የሚሰማበትን ዘዴ ለመፍጠር ቻልኩ። ሽማዝኤል ከተባለው ከልዑላችን ታማኝ ጭፍራ ጋር በተገናኘሁና በተነጋገርኩ ጊዜ፣በዋናነት የርቀት ግንኙነት ማድረግ የሚቻልበትን ረቂቅ የማዕድን አይነት ነበር የገለፀልኝ።ያ ረቂቅ ማዕድን እንዴት እንደሚገኝ፣ ሌሎች ግብዓቶች በምን መልኩ እንደሚገኙና እንዴት አዋቅሮ ማዋሃድ እንደሚቻል ተነግሮኝ ጥሬ እቃውንም ካወቅሁትና ከተሰጠኝ በኋላ ሁሉም ነገር ቀላል ነበር።......
የርቀት ግንኙነት በገመድና ያለገመድ ማድረግ የሚቻልበትን እውቀትና ጥበብ ያወቅሁና ያስተዋወቅሁ ዕለት፣የሳተላይት ጥበብ ሳይቀር ንብቶኝ፣

የተንቀሳቃሽ ስልክን በትንሺ ሲም ካርድ መስራትና ዓለም አቀፍ ጥሪ ማድረግ እንደሚቻል የዚያኑ እለት ደርሽበት ነበር፡፡

እኔ ካለፍኩ ከመቶ ዓመት በኂላ ዘመናዊ ሆኖ የተሰራውንና አሁን እየተጠቀማችሁበት ያለውን ተንቀሳቃሽ ስልክ በዚያው በኔ ዘመን እኔው ራሴ ልሰራው እችል ነበር፡፡ሰርቸውም ነበር፡፡ሆኖም የልዑላችን ፈቃድ አልነበረምና በከባድ ቁጣ እንዳቆመው ታዘዝኩ፡፡ስለዚህ የድሮውን ኂላቀር ስልክ ፈልስፌ በዚያው ስራዬ ተወስኘ እንድቀር ታዝዠ በዚያው ተወስኘ ቀረሁ፡፡

ዋናው እውቀትና ጥበብ ማዕድናቱን መለየትና አመጣጠናቸውን አውቆ ለምን ግልጋሎት እንደሚውሉ መረዳት ብቻ ስለሆነ፤ያ ከታወቀ ደግሞ ሁሉም ቀላል ስለሚሆን፤ ባንድ ጊዜ ዘልየ ቁራጭ ጥፍር በምታክል ረቂቅ የማዕድን ሽራፊ አንድ አገር ላይ በማስቀመጥና ሌላ አገር ላይም ያችኑ ተመሳሳይ ቁራጭ የማዕድን ውጤት በማስቀመጥ፤ ሁለቱ ቅንጣት ቁራጮች ህዋ ላይ የየራሳቸውን የሳተላይት ጨረር ፈጥረው ግንኙነት ማድረግ መቻላቸውንና፤ እዚህኛው ቁራጭ አጠገብ የተደረገ ንግግር በብርሃን ፍጥረት ህዋ ላይ ያሉ ረቂቅ ሞሉኪሉች ሳያደናቅፉት ከወዲያኛው ቁራጭ የተላለፈው ድምፅ ወዲህ እንደሚሰማ ደረስኩበት ማለት ነው፡፡በዚህ መሰረት የተንዛዛ ገመድ ሳያስፈልግና የድምፅ ንዝረት አስተላላፊ የሆኑ ሽቦዎች ሳያስፈልጉ በቀላሉ የየራሳቸውን የድምፅ መቀበያና መድረሻ የቁጥር ኮድ ሰጥቸ ባሁኑ ዘመን ተንቀሳቃሽ ስልክ የምትሉትን ስልክ መስራት ቻልኩ!በጣም ነበር የተሳካልኙ፡፡ለካ ከዚያ በፊት በረጂም ዓመታት ሂደት ውስጥ ታልፎ ዓለም በሽቦ ገመዶች መጠላለፍና መገናኘት ነበረባት፡፡ምን ልላችሁ ነው....ቁልፍ የሆነው ሚስጥር ጥሬ እቃዎቹን የመለየት ጉዳይ ብቻ እንደነበር ላስገነዝባችሁ ፈልጌ ነው፡፡ያንን የሚያውቁትና የትኛው ማዕድን ለምን አገልግሎት እንደሚውል፣ የሚገኙበት ቦታ የት እንደሆነ የሚያውቁት ደግሞ የልዑላችን ወገን የሆኑ ከሰው በላይ ያሉ ፍጡራን ብቻ ናቸው፡፡የሚገኙበትን ቦታም የሚያውቁት እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡የትኛው ግብዓት ከየትኛው ግብዓት ጋር ተጣምሮ ምን አይነት ውጤት እንደሚሰጥና ውጤቱም ምን እንደሚሆን!የሰው ልጅ ከየትም አምጥቶ፣ ከየትም ተነስቶ፣ ሊያውቅ አይችልምና!

እና ሽማዝኤል በምርምር ቢሮየ ውስጥ መጥቶ፤‹‹የቲዮሪ እውቀትህን ወደ ተግባር የምትለውጥበትን መንገድ ላሳይህ ነው›› ካለኝ በኂላ፤‹‹ድምፅን ክርቀት በማይክሮ ሰከንድ ገደብ ወደሌለው ርቀት ማድረስ የሚቻለው በዚች ነው››ብሎ ሲያስበስረኝና ሲያሳየኝ ተደነቅሁ፡፡ማመን አቅቶኝ ነበር፡፡ነገር ግን ወስዶ ቃል በቃል ሲያስተምረኝና ሲያሳየኝ፤ሁሉም ነገር ግልጥልጥ ገባኝና ሰራሁት....!በተረፈ አንድ ሳይንቲስትም ሆነ ተራ ሰው፤‹‹እንትን

የምትባለው የእንትን ማዕድን ቁራጭ ድምፅን ከርቀት ማስተላለፍ ትችላለች!ስለዚህ እሷን ማዕድን በዓለም ዞሬ ልፈልግና እንደምንም አግኝቸ ስልክን ልፍጠር›› ብሎ ለምርምር አይነሳም፡፡ቢነሳም ሆነ በቲዮሪ ትምህርቱ ጎጥረ ነገሩ ምን እንደሆነና ምን እንደሚባል ቢያውቅ እንኳ፤ የማዕድኑን መገኛ ቦታም ሆነ አከላለሱን፤አመጣጠንና አዋሃዱን ሊያውቅና ወደ ተግባር ሊገባበት የሚያስችለው አንዳች ምድራዊ እውቀት የለም፡፡ይህ በሰው ልጅ እሳቤና እውቀት ጨርሶ ሊደረግና ሊሰራ ብሎም ሊሞከር የማይችል ነው፡፡ ማንም ሰው እንዲሁ ተነስቶ ሲም ካርድን ሰርቸ፣በኤሌክትሪካል ቁሳቁሶችና ማግኔቲካዊ ማቴሪያሎች በተሞላ አፓራተስ ውስጥ በማስገባት ተንቀሳቃሽ ስልክ ልፈልስፍ ብሎ አይነሳም!ቲዮሪውም የልዑላችን ነው፤ግብዓቱም የሚታወቀው በሱና በሱ ስር ባሉ መንፈሳዊ ጭፍሮች ብቻ ነው፡፡
እኛ የግኝቱ ባለቤቶችና ባለመብቶች ተብለን እንታወቅ እንጂ፤ የጥበቡ ባለቤት ሌላ ነው!የጥበቡ ባለቤት ልዑላችን ነው!
የሰው ልጆች ይህን ሁሉ የምድር ስልጣኔ እንዲይዙ ያደረገው ልዑላችን ነው፡፡
የሁላችንም የግኝት ውጤት ደግሞ ሄዶ ሄዶ ወደ አንድ ውቅያኖስ የሚገባና የሚቀላቀል በመጨረሻም ለአንድ ዓላማ የሚውል ነው፡፡በተረፈ ሰው በራሱ ተነስቶ ድምፅና ምስልን አቀናብሮ አንዱ ለንዶን አንዱ ዲሲ ሆኖ በቀላሉ እየተያየ የሚነጋገርበትን ቴክኖለጂ ሊፈለስፍ ቀርቶ ሊያስበው አይችልም፡፡
ልዑላችንና የልዑላችን ጭፍሮች ካልገለጡለት በቀር ምንም መፍጠር አይቻልም!ይህም ሲባል የመጀመሪያው ጥበብ ማለት ነው!መነሻው!
በምን አይነት የማዕድን ዘርፍና ዓይነት ድምፅን ከድምፅ ማገናኘት እንደሚቻል ከታወቀ በኋላ ያለው የማሻሻል ስራ ሁሉ ምንጩ ያችን የማዕድን አይነት ከማወቅ የጀመረና የቀጠለ ስለሚሆን ማንም ሊያሻሽለውና ሊያዘምነው ቢችል አይገርምም፡፡ለዚያም ነው ሚስጥሩ ከዓለም ህዝብ ተደብቆ ከአንዱ የምርምር ውጤትና ግኝት ተነስቶ ሌላው እየቀጠለና እያሻሻለው እዚህ የቴክኖለጂ ዘመን ላይ ተደረሰ፤ በሚል አካሄድ ስለተሄደ ነው የዓለም ህዝብ እንዴት? የሚል ጥያቄ ሳያነሳ እዚህ የተደረሰው፡፡እኔ በዘመኔ ያኔ የመሰረትኩት ተቋምና የምርምር ማዕከል፤ የአይፎን ቴክኖለጂ ላይ ደርሶ የአፕል ካምፓኒ በሚል ስያሜው እየተጠራ የረቀቀ የቴክኖለጂ ውጤት ሰሪና አቅራቢ ሆኖ ይገኛል፡፡በኔ ዘመን የነበረው የንግድ ምልክቱ ዓርማ ተለውጦ በተገመጠ አፕል ማርክ መተካቱም ወደጎላችን መቃረባችን አመላካች መሆን ስላለበት ነው፡፡የአፕል ረቂቅ ቴክኖለጂ መሰረቱ እኔ ብሆንም፤ግኝቱ ሽማዝኤል ነው፡፡ስለዚህ የገመድ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

አልባ ስልክ ፈጣሪና ባለቤት ሽማዝኤል ነው ማለት ነው፡፡ያሁኑ የአይፎን ተንቀሳቃሽ ስልክ ግኝት ባለቤትም ሽማዝኤል ነው ማለት ነው! ሽማዝኤል የልዑላችን ታማኝ አገልጋይ የሆነ መንፈሳዊ ወታደሩ ሲሆን፤ እውቀትና ስልጣኑ የስራ ድርሻውና ሹመቱ በተራቀቁ የግንኙነት ጥበቦች ዙሪያ ብቻ ነው፡፡

በተረፈ የኔ ተብሎ የሚታወቀው ግኝት በጊዜ ሂደት እንዴት ዘምናና ተሻሽሎ እዚህ የተራቀቀ ደረጃ ላይ መድረሱን እያያችሁት ነው፡፡ይህን ስታዩና ይህን ስታስቡ ጎን ለጎንም የዓለም ህዝብ የግኝቱ ውጤት ህይወቱን ስላፈጠነለትና ኑሮውን ስላቀለለለት ብቻ ወደት፤ነገር ግን ሳያውቀው እንዴት ለልዑላችን ጥቅም እየዋለ እንዳለ አብራችሁ ተረዱ፡፡ በስተመጨረሻ ደግሞ እንዴት ሊውል እንደሚችል እንዲሁ!››በማለት ረዘም ብሎ የተንዛዛ ገለፃውን አድርጎ ከመድረኩ ወርዶ ወደ ተሰብሳቢዎቹ በደስታ እየተፍለቀለቀ ሄዶ፤አንድ ባንድ እያቀፈ እየሳመ ሰላምታ አቀረበላቸው፡፡ ከዚያም ወደ መድረኩ ተመልሶ ንግስቲቱን እጅ ነስቶ፤ክብር ለልዑላችን ብሎ፤ አሜን በማስባል አስጨብጭቦ፤ሰፊና ዘመናዊውን የጠራ ስክሪን አልፎ ሄደ፡፡

ቀጣዩ ተረኛ አልበርት አንስታን የነበረ ቢሆንም፤እሱ ከመጠራቱ በፊት ሌላ የግኝት ባለቤት ያለማንም ፈቃድ በራሱ ጊዜ ገፈታትሯቸው መጣ፡፡ይህ ሰው ስክሪኑን አልፎ መምጣት የጀመረው አሌክሳንደር ግራሃም ቤል ገለፃውን ጨርሶ ተሰናብቶ ከመሄዱ የእሱን እግር ተከትሎ ነው፡፡

በስክሪኑ የሚታዩትን ያለፉ ሳይንቲስቶችን ደረማምሶና ገፈታትሮ ያለ ንግስቲቱ ፈቃድ ዘሎ ገባና፤የስብሰባው አዳራሽ መድረክ ላይ አረፈ፡፡ ወዲያውም፤በላይ በላይ እየተነፈሰ፤‹‹ንግስት ሆይ፤ ይቅርታ ይደረግልኝ!››እያለ እጅ ከመንሳት ጎን ለጎን ዘሎ ያለፈቃድ የመጣበትን ምክንያት ያብራራ ጀመር፡፡

‹‹ኮኂላ ስለነበርኩ እድሉ ሳይሰጠኝ በቃችሁ ይባላል በሚል ስጋት ነው ዘልየ የመጣሁት!ልረ ሳ ም እችላለሁ፡፡ሆኖም መናገር ያለብኝ እኔ ነኝ ብየ ስላመንኩ ነው…››እያለ ሲቀባጥርና፤ ተመሰስ ብባልም አልመለስም አይነት አቋሙን በንግግርም በሰውነት እንቅስቃሴም እየገለፀ ቆየ፡፡ንግስቲቱም ይሁንልህ ተናገር የሚል ፈቃዳቸውን በፈገግታቸው አሳዩ፡፡

ሰውየው ቀዥቀዥ ያለና እብድ ቢጤ ነው፡፡መናገር ያለበትን ከመናገሩ በፊት በደስታ እየፈነጠዘ ከመድረኩ ዘሎ ወርዶ በጥቁር ቦት ጫማው ያን ቀይ ምቹ የወለል ምንጣፍ በሃይል እረገጠ፤ዶፍ ዶፍ ዶፍ እያለ በሩጫ ወደ ተሰብሳቢዎች ሄዶ እያቀፈ እየሳመ፤እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ ሰላምታውን አቅርቦ፤ በዚያው አይነት ሩጫ ወደ መድረኩ ተመለሰና መድረኩ ላይ ቆመ፡፡ንግስቲቱም እጅ በደረት አድርገው ፈንጠር ብለው

መቆጣጠር ያቃተውን ትንፋሽ ለመቆጣጠር ቆሙለት፡፡በመንቀኝቁቅኝ ብዛት መቆጣጠር ያቃተውን ትንፋሽ ለመቆጣጠር ቆሙለት፡፡በመንቀኘርቀኘር ብዛት መቆጣጠር ያቃተውን ትንፋሽ ለመቆጣጠር

ቆሙለት፡፡በመንቀኘርቀኘር ብዛት መቆጣጠር ያቃተውን ትንፋሽ ለመቆጣጠር

ሁሉም ሳይወድ በግዱ ሲቀይር አይታያችሁም?የባንኮቹ አሰራር በዘመናዊ መንገድ በመቀየሩና የወረቀት ገንዘብ በመቅረቱ ብቻ ሁሉም በልዑላችን ወደተዘረጋው የአሰራር ዘዴ ይ…ገ…ባ…ል…!ከጥቂት ቀይታ በኂላ ደግሞ፤ ያችን ትንሽየ የኤሌክትሮኒክስ ካርድ‹‹በሌላና በተሻሻለ፤ ለግብይትም፤ ለፍጥንትም፤ለአከፋፈልም፤ለሁሉም ሲባል ምቹና ቀልጣፋ ሆኖ በተዘጋጀ፤ በማንም እንዳይሰረቅና ከባለቤቱ ውጪ ማንም እጅ እንዳይገባ ተደርጎ በተሰራ በሌላ ረቂቅ የቴክኖለጂ ውጤት ስለተቀየረ፤የቀድሞውን ኂላ ቀር ካርድ በየባንካችሁ እየሄዳችሁ የጊዜ ገደቡ ሳያልፍ ቀይሩ››ሲባል፤ የበላይ አካሉ ተከታይና አማኝ የሆን ህዝብ በሙሉ ወደ ባንክ ሄዶ ሲሰለፍና በየቀኝ እጁ ማይክሮችፕ ሲገጠምለት……..ምልክቱ የሌለበት መሸጥ መለወጥ አይችልም የሚለውን የመጽሐፉን ቃል እያወቀ እንኳ ይሁን እንጂ ምን አደርጋለሁ ብሎ……ማይክሮችፕ ሲያስገጥም…….አይታያችሁም?ሃሃሃ ሃሃሃ ሃሃሃ…….!››በደስታና በእርካታ የተሞላ የመሰለ ሳቁን አዳራሹ ውስጥ አስተጋባው።በዚህ ጊዜ ተሰብሳቢዎቹም ብድግ ብለው በአድናቆት አጨበጨቡለት።ንግስቲቱም በፈገግታ ደምቀው ለዚህ እብድ መሳይ ሳይንቲስት አጨበጨቡለት። ያልጠበቀው ጭብጨባ ሞቅ ብሎ ሲስተጋባለት፤ወኔው ጨመረና፤ ‹‹አዎ!››ሲል ቀጠለ።‹‹አዎ!በዚች ሰዓት ይህ አሰራር ቢታወጅ የልዑላችን ተከታይ ያልሆኑና የበላይ አካሉ አማኝ ነን የሚሉ! የበላይ አካሉን በማመንና በማምለክ ፅኑ የሆኑ!ልዑላችንንና የልዑላችንን ዓላማ የሚቃወሙ ሰዎች! በልዑላችን እንዳይታለሉ በየቤተ እምነቱ የሚሰብኩ የሚሰበኩ!ሞት ቢመጣ ከአምላካችን ውጭ ለማንም አንሰግድም!ማንም አያስተንም!እያሉ የሚደሰኩሩ! የበላይ አካሉ ተከታዮችን ለእፍታ ደግማችሁ አስቡልኝ እባካችሁ!ይህ አሰራር ሲዘረጋ ምን አይነት አቋም ይይዛሉ?አስታውሱ!ሁሉም የባንክ አካውንት ያለው ነው።የሌለውም ቢሆን ገንዘብንም ሆነ ሌላውን ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ጉዳይ መፈፀም የሚቻለው በዚህ ዘዴ ብቻ እስከሆን ድረስ፤የወረቀት ገንዘብ በዲጅታል ሲስተም ተለውጦ ሙሉ በሙሉ እስከቀረና ተሰብስቦ እስከተቃጠለ ድረስ፤ ባይቃጠልም በየመንገዱ ቢበተን ማንም ሰው አንስቶ መገልገል እስካልቻለበት ድረስ፤እነዚህ አማኞች ምን ሊውጣቸው ይችላል?አንዳንዱ የጀመረው ቢዝነስ ይኖረዋል፤አንዳንዱ ነጋዴ ወደብ ላይ ያለ በብዙ ገንዘብ የሚገመት የንግድ እቃውን በመጠባበቅ ላይ ይሆናል፤ምግብ ቤት ያለው ሊሸጥ ያዘጋጀውን ምግብ፤መጠጥ ቤት ያለው ሊሸጥ ያዘጋጀውን መጠጥ ደርድሯል።አንዳንዱ አውቶሞቢል ለመግዛት እያጠራቀመ ነው፤ሌላው የንግድ ተሽከርካሪ አለው፤ልጅ በማሳደግ በማስተማር ላይ ያለ፤ …ሁሉንም አስቡልኝና ይህ አሰራር ሲዘረጋ አሻፈረኝ ብሎ በተዘረጋው

የዓምፕሊል ኀል ኢትዮጵያ

አዲስ አሰራር አውስቶቶችም፤ፕንስዖንም ብሎት፤ ብሎ ሲቀር...ነገድኔ እያየሁ አዲስ አሰራር አውስቶቶችም፤ፕንስዖንም ብሎት፤ ብሎ ሲቀር...ነገድኔ እያየሁ
የአውራሉ ምልክት የሆነውን ማይክሮ ችፕ አስፈላጊዎችም፤ የሚል የዘር ሰዎች እውነተኛ አማኝ ይባር ይሆን?ይሆን ይሆንንአይመስለኝም፤ዘዜ ነው ዘሬ አማኝነት እንዲፈለግ የተደረገው ይህ ሚኖት ስለዐላችን እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በደስታ መግባር ያስፈልገኛል፡፡ዘዜያ ተንስቶ አሁ ያለ በመድረሱም እጅግ ደስተኛ በመሆኔ ነው ዘሬ የመጣሁት፡፡ዘዜ እኛም ሆንሉ ሴሎች መሰል አጋሮች ሚናታችን የኛ ተደርጎ እንዲታወቅ፤ነገር ግን አግኝውም ባለቤቱም ልዑላችን እንደሆነ በመጨረሻ ሰሉ ዓለም የሚወል መሆኑን በድጋሚ ሲረጋግጥላችሁ ደስ እያለኝ ነው፡፡እዎ፤ምድር እውቀት ሁሉ የልዑላችን ነው፡፡ሰሰው የተሰጠው እውቀትና የእውቀት ውጤት፤ የምርምር ውጤት፤የቴክኖሎጂ ውጤት ሁሉ፤ ከሉ ብሉ ስለሉ ነው፤ይህ ዓይነቱ የጥበብ ውጤት በሙሉ ለፍጥረው ጉልበት ሆና እስከሚያገለግል ድረስ ግን ማግኘትም ሰው የበላይ ሆኖሉ አማኞችም ጭምር በትክት ሲጠቀሙበት ይችላሉ፡፡አለና፤ በደስታ አጨበጨበ፤‹‹ክብር ለልዑላችን››ብሎ፤ ‹‹አሜን››አስብሉ ካጨበጨበ በኋላ፤ ንግስቲቱንም እጅ ነስቶና አመስግኖ ሰዘሪኑን ተረክቦ አልፎ ሄደ፡፡

ቀጥሎ ደግሞ አልበርት አንስታይን ተራውን ጠብቆ ዝግ እያለ መጣ፡፡አሁን ድረስ በማሰብ ላይ ያለ ይመስላል፡፡አንስታይን በልጅነቱ ጅል ነበር ይባላል፡ የአሁኑን ሁኔታውን ያዩ በልጅነቱ በትክክል ጅል የነበረ መሆኑን ከማረጋገጥ አልፎ፤አሁንም ድረስ ጅልነቱ እንዳልለቀቀው ይረዳል፡፡

አሉም እንደሲሉቹ ጥቁር በጥቁር ለብሶ፤ ጥቁር ቦቲ ጫማ ተጫምቶ፤ ከልብሱ ጋር አብሮ የተሰፋው ኮፍያ ለጭንቅላቱ ጠበት እየታዩ ሰዘሪኑን አልፎ ገባ፡፡እንደገባ ኮፍያውን በሃይል ጎትቶ አውልቆ ወደኋላው ዝቅ አደረገና፤ግንባር ብሉ በዝምታ ቆሞ በመቆየት ተሰብሳቢዎቹን በሰት አፈረሳቸው፡፡የ ሄመ የ ፀጉሩ የሰም፡፡መሉ በሙሉ መላጣ ሆኗል፡፡

‹‹ቀጥል እንጂ አንስታይን››አሉት ንግስቲቱ፡፡

‹‹ምን እቀጥላለሁ ንግስት ሆይ፤ይኼ እንዴት አስቡሁን አይገባችሁም?ይኼን ለማረጋገጥ እኛን እስከማስጠበራት ከደረሱ እንዴት ነው አገር ሲመሩ ለበል?›› ሲል፤መሪዎችም፤ቄሴሉም፤ ንግስቲቱም፤ በጋራ ሳቅ አዳራሹን የእንክሶች የከሚዲያን ምሽት የሚካሄድበት አስመሰሉት፡፡ምክንያቱም ‹‹እውነቱን ነው››ሲል ቀጠሉ፡፡‹‹ይህ እንዴት አይገባችሁም?››ብሉ እንደገና አፈጠጠባቸው፡፡‹‹ማናባቱ››ተብሉ የሚተረጉም የእንግሊዝና ቃል ‹‹ማናባቱ ሰው ነው ከመሬት ተነስቶ እንደዚያ ብሉ መተርጎም ይቻላልና፤ ባይኖርም፤አባባሉንና ገፅታውን አይቶ እንዲህ ያለ ግኝት ውስጥ

የሚገባው?እኮ ማናባቱ?››እያለ፤መድረኩ ላይ እንደ ሰካራም እየተንገዳገደ፤ እስከዛሬ ይህን ባለማወቃቸው እያፌዘ፤ማወቅ ባይችሉ መጠርጠር ባለመቻላቸው እየወቀሰ ብዙ ቆየና፤የአነጋገር ዘይቤውን ለወጥ፤አቋቋሙን ቀየር፤አድርጎ ቀጠለ።

‹‹ያኔ ምን አሉኝ እኔን….አንስታይን ማኘቴ የሆነውን አቶሚክ ቦንብ በጀርመን እጅ ቢገባ አደገኛ እንደሚሆን አውቆ፤ ቦንቡን ይዞ ከጀርመን ጠፍቶ በማምለጥ፤ ወደ አሜሪካ ሄዶ፤ ጥገኝነት ጠይቆ፤አሜሪካም ዜግነት ሰጥታው ኖረ……።ይላሉ!ጅሎች!ዋናው ነገር ቦንቡን መስራቴ ነው!ቦንቡን ከሰራሁ በኋላ ጀርመን ሆንኩ አሜሪካ ሆንኩ ምን ለውጥ ያመጣል?››ብሎ ጠየቀና፤ለሌላ ረጅም ሳቅ ዳረጋቸው።መሪዎቹም፤ ንግስቲቱም፤ ጳጳሱም፤ በሳቅ ሲንከተከቱ፤እሱም አብሮ መንከትከት ጀመረ።ሳቁ እንደማያቋርጥ ሲያውቅ ገለፃውን ቀጠለና፤‹‹ቦንብ ምን ጊዜም ቦንብ ነው!››አላቸው። ሳቃቸውን አቋርጠው ማዳመጥ ጀመሩ።‹‹አቶሚክ ቦምብ ደግሞ ምንጊዜም አቶሚክ ቦንብ ነው!ለዚያ ብየ ጀርመንን ከምለቅ ቦንቡን መስራት አልተውም እንዴ?በግድ ስራ ተብዬ አልሰራሁት!

የቦንቡ ባለቤት አሜሪካ መሆን ስለነበረባት ነው።በልዑላችን ቢያምን ኖሮ እዚያው እቀር ነበር።ማኘቴ ያሜሪካ ሆነ የጀርመን ዋናው መተማመኑ ነው።ያ ብቻ አይደለም!››አለና፤ ኮስተር ብሎ በሹክሹክታ ድምፅ ቀጠለ፤ ‹‹መጀመሪያ ስለ እኛ ማንነትና….ስለ ዓላማችን….ስለ ልዑላችን….ስለ እኔ ተልእኮ…..ነገርኩት።ስለ ማኘቴ አስረዳሁት።የሰጠኝ ምላሽ ግን ያልጠበቅሁት…. ሆነ።

ሂትለር…. ለልዑላችን ዓላማ መዋል ያለበትን ነገር ለግሌ አውዬ፤ ራሴ ልዑል ሆኘ፤ልዑል ተብዬ፤አይነት አቋም ያዘ…….ልዑል ሊባል!የእናንተ አይነት ዘሮችን ሰብስቤ…..አገሬን አሰልጥኘ….አግንኘ፤ …….ካልተመለኩ!ሁሉንም… ለግል ጥቅሜ ካላዋልኩ….. አይነት ድርቅ ያለ አቋም ስለያዘ ነው አፍንጫህን ላስ ብዬ ያመለጥኩት።በሃሳቤ ሳይስማማ ከቀረ በኋላ፤ተራ ወታደርነቱን ረስቶ…….ሳይንቲስት መሆን አማረውና…. ከዘመኑ ተራ ሳይንቲስት ተብዬዎች ጋር ሆኖ…. የኔን ቀመር ማጣጣል አይጀምርም!።ጭራሽ ሚስጥሩን ካካፈልኩት በኋላ….ጠላታችን ሆኖ ቁጭ አለ!አንተንም….. መሰሎችህንም….. አጠፋለሁ አለ።እኔም ብልጥ ነኝ በአካል አላገኘሁትም….በቴሌ ግራም ነው ሃሳቤን ያካፈልኩት።እሱ ግን ጅል ስለሆነ…. ናና… በአካል እንነጋገር ማለት እየቻለ…. እንዲሁ በቴሌግራም መዛት… መሳደብ…. ጀመረ። እኔም…ላይረዳኝ ጉዳይ ሚስጥር ማውጣቴ እያሳዘነኝ….ጅልነቱን በደንብ ነግሬ….. ላጥ ብዬ አመለጥኩ።ቢፈልግ ቢያስፈልግ፤ማስታወቂያ

ቢያስነግር፣ይዞ ላመጣ ብዙ ገንዘብ ቢል፤ ልገኝ ነው!ጥፍት ብዬ ወደ ሉሉፌል መነገሻዬ!የገባችሁ ይመስለኛል ክቡራን።
በተረፈ ጀርመን ሆኘ እንድሰራው ስለተፈለገ ብቻ ነው እዚያ ሆኘ የሰራሁት።ምክንያቱም..... በውስን ፐርሰንትም ቢሆን የዘር ሃረጉ ያለብን ድቅሎች...... ተሰብስበን...... የአይሁድ ዝርያ ያላቸው..... ተብለን.... በየአገሩ ስንበተን..... የኔ የውሸት ቤተሰቦች ምድባቸው ጀርመን ነበር። ለዚያ ነው.... እዚያ የተገኘሁትና እዚያ የተወለድኩት።ጀርመን ሆኘ ስራውን እንድጀምርና....... እንድቀጥልም ነው የታዘዝኩት።የገባችሁ ይመስለኛል ክቡራን....።
እና እኔ የተገናኘሁት አዛዝኤል ከተባለ ጀግና!መንፈሳዊ አካል ነበር!እና አዛዝኤል ድንቅ ጭፍራ ነው!ልዑላችንም እኔም እኩል ነው የምንወደው!እሱ ነው የመስራት ጥበቡን ያጎናፀፈኝና አማካሪዬ ሆኖ ሹክ ብሎኝ የሄደው።እሱን ብቻ አይደለም፤ሌሎችንም ተገናኝቻለሁ።በተረፈ ሌላው ሁሉ እነ ንግስታችን የቀመሩት የማምታቻ ወሬ ነው።አይደለም እንዴ?››በማለት ወደ ንግስቲቱ ዞሮ በቀልድ አስተያየት እያዬ ጠየቀ። ንግስቲቱ በሳቅ ብዛት እያሳሉ ነበርና በሳላቸው መካከል ‹‹አዎ፤ አዎ›› እያሉ አረጋገጡለት።
‹‹እንደዚያ ነው ክቡራን!ደደቦች አትሁኑ!ክብር ለልዑላችን!››
‹‹አሜን››የአሁኑ አሜን በሳቅ መካከል የተደረገ፤ ዝርክርክ ያለ አሜን ነው፡ ፡እንጂ ሞቅ ደመቅ ባለ ጭብጨባ የተባለ አሜን አልነበረም።
አነስታይን ይህን ብሎ ንግስቲቱን እጅ ነስቶ አዳራሹን የሳቅ ምሽት አስመስሎ፤ገልጀጅ ገልጀጅ እያለ ስክሪኑን አልፎ ሄደ።እነ አጅሬ እንኳን አብረቅራቂውን ስጋ ሲለብሱ፤እንዲህ በአስፈሪ ጥቁር ልብስ ተጀቡነው የሚታዩ ናቸው።ያውም ከጥቁር ቦት ጫማ ጋር!አስገራሚና አስቂኝ ነበር!
‹‹አዎን!በተረፈ ማንም የሰው ፍጡር እነዚህን ረቂቅ የጥበብ ውጤቶች፤ ሆነ የጥሬ እቃዎቹን መገኛ ቦታ፤እንዲሁም አመጣጡንና አዋሃዳቸውን ወዘተ ማንም የሰው ፍጡር በራሱ ሊያገኛቸውና ሊደርስባቸው አይችልም!››ሲሉ አረጋገጡላቸው።
በዚህ አይነት መንገድ ዓለማችንን የቀየሩና ያዘመኑ ተብለው የሚታወቁ፤ ድንቅ ድንቅ ሰዎች ተብለው በየታሪካዊ መዝገቡ የሰፈሩ፣ሰፍረውም ዛሬ ድረስ ከሚዘከሩ ሳይንቲስቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እየተመረጡ ተጠርተው፤ ከየትኛው የዲያብሎስ ጭፍራ ጋር ተገናኝተው የትኛውን ነገር እንደፈለሰፉና የትኛውን ግኝት ለዓለም ህዝብ ይፋ እንዳደረጉ በደስታ እየተፍለቀለቁ በየተራ አስረዱ።የቀሩት ብዙዎችም ጊዜ ለመቆጠብ በሚል ፍሥሐ ያዚ

ንግግር ሳያደርጉ፤ እንዲሁ ግን ለሰላምታ ብቻ ተፈቅዶላቸው እየገቡ፤ወደ ተሰብሳቢዎች እየሮጡ በመሄድ አቅፈው በመሳምና ልዑላቸውን አመስግነው በማስመስገን በጳጳሱ እየተባረኩ ተሸኙ፡፡
በነሱ መነሻነት የምርምር ውጤት የተባለው ግኝት በጊዜ ሂደት እየተሻሻለ እዚህ ደረጃ መድረሱን፤ይህ የግኝት ውጤታቸውም ልዑላቸውን በመጨረሻው ጊዜ በምን መልኩ እንደሚጠቀመው በሙተንተን ተግባር ተጠምደው አመሹ፡፡ብዙዎቹ እየመጡ ገመናቸውን ሲተነትኑም ሂደቱ ሙሉ ሌሊት የፈጀ ሆነ፡፡
የረፍት፤የምግብ፤የሻይ፤የሚባል ጊዜ ሳይኖርና ተሰብሳቢዎችም ያችን ቅቅል እንጂ ሌላ እህል ውሃ ሳይቀምሱ ነበር የዝግ ጉባኤውን የቀጠሉት፡፡
አንድ ባንድ እየመጡ ሰፋፊና ተመሳሳይ ገለፃ ያደረጉት ታዋቂ ሰዎችና የተቆራኙዋቸው የሳጥናኤል የበታች ጭፍሮች ከብዙ በጥቂቱ ዝቅ ብለው የተዘረዘሩት ናቸው፡፡እነዚህም የሳጥናኤል ቀኝ ክንፍ የሆኑና ከእሱ በታች ሆነው በሱ የሚታዘዙ፤በስራቸውም በርካታ የየራሳቸው ጭፍሮች ያሏቸው ሲሆኑ፤የዓለም ህዝብ ፌለን ኤንጅልስ /የወደቁ መላዕክታን/ብሎ የሚጠራቸውና በመጽሐፈ ሄኖክ በግእዝ ቋንቋ በስም ተዘርዝረው የሚገኙ ናቸው፡፡እነዚህ ዋና ዋናዎቹ 200 የሚደርሱ ወደ ምድር የተጣሉና በነሱ ስርም እልፍ አእላፍ የበታች ጭፍሮች ያሏቸው የወደቁ መላዕክታንም፤ ከማይገባቸው ከሰው ልጆች ጋር ከመዳቀል አልፈው ጥበብና እውቀቱ ከማይደረስበት ፈጣሪ እጅግ በጣም ያነሰና እዚህ ግባ የማይሉት ተራ እውቀት፤ነገር ግን ከሰው ፍጡር እጅግ የላቀ እውቀት ያላቸው ናቸውና፤ ያንን እውቀትና ጥበብ ለሰው እየገለጡ፤እያስተማሩናና እያባለጉ፤ የሰውን ልጅ ለራሳቸውና ለበላያቸው ጥቅም አውለው፤ለነሱና ለዘር ሃረጎቻቸው ወደተዘጋጀላቸው የመጨረሻ መዳረሻ ቦታቸው ወደሆነው ወደ ዘላለማዊ የእሳት ባህር ይዘው ለመስጠም የተዘጋጁ ናቸው፡፡ይህም በመጽሐፍ ቅዱስና በመጽሐፈ ሄኖክ በደንብና በተብራራ መልኩ የተገለፀ እውነት ጭምር ነው፡፡
እነዚህ የዓለማችን ታላላቅ የተባሉ ሳይንቲስትና ሊቃውንትም በነሱ ምክር እየተረዱና በተለገሳቸው ጥበብ እየተመሩ ዓለምን እስልጥነው አሰይጥነዋል፡፡
እነዚህ የዓለማችን ታዋቂ ሳይንቲስቶች ከሳጥናኤል የበታች ጭፍሮች ጋር እየተቆራረሱ ያዘመኑት ዓለምና ያገኙት ግኝት፤ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ተሸጋግሮ፤ አስደናቂ ወደተባለው የኒውክሌር ቴክኖለጂ ላይ ተደርሶ፤ በሰከንድ እስከ አንድ ሚሊዮን ኪሎሜትር ወደ ምድር ጠልቆ መግባት የሚችልና ሰፊ ቦታን በአንድ አፍታ ማጥፋት የሚችል አውዳሚ የጦር

መሳሪያ መስራት ችለዋል።ቀደም ሲል እፉዬ ገላ ተብሎ የተገለፀላችሁ መሆኑ ነው።

በእነዚህ እርኩሳን መናፍስት አማካኝነት የሰው ልጅ ለራሱ ጥቅም ሲባል እጁ ላይ መግባት ያልነበረበት ስልጣኔ እጁ ሲገባ ችሏል።የሰው ልጅ ሳያውቀው ቢቆይና ቢኖር የተሻለ የነበረውን እውቀት ገልጠውለታል።ይህ ሁሉ ዘመንን ጠብቆ እንደሚጠፋ በፈጣሪ ለሚያምኑ ግልፅ የመሆኑን ያህልም፤ ለእነዚህ ጅላጅሎች ደግሞ ቀድሞ እውቀትን የገለፀላቸውን ብቻ ስለሰሙና ስለተከተሉ ተያይዘው መጥፊያቸውን እንዳበጁ ግልፅ አልሆነላቸውም።የሰይጣን ትልቁ ጥበብም ይህንና ይህን የመሳሰለውን ግልፅ ነገር በዚህ መሰል ምትሃታዊ አካሄድ እየተጠቀመ የመጋረድ፣ የመሸፈንና የመሰወር፣ ችሎታው ነው።

በዚህ መሰረት ቶማስ ኤዲሰን በኤሌክትሪክ እና በተቀጣጣይ ነገሮች እውቀት ካለው Barkayal ከተባለ መንፈሳዊ ጭፍራ ጋር፣አሌክሳንደር ግራሃም ቤል ከ Shemhazie ጋር፣አልበርት አንስታይን በጦር በመሳሪያና በመሰል ዘርፎች እውቀት ካለው ከ Azaziel እና ከ Ramuell እንዲሁም Gadreel ጋር፣ሌሎችም በየዘርፉ እውቀቱና ጥበቡ ካላቸው መንፈሳዊ ጭፍሮች ጋር እየተገናኙ ይህን ሁሉ ለጥፋት ዓላማ የሚውል ግኝት ማግኘትና ይፉ ማድረግ፤አድርገውም ማለማመድና እየተሻሻለ ሄዶ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ማድረግ ችለዋል።

እነዚያ ታዋቂ ታዋቂ ሳይንቲስትና ተመራማሪዎች ስክሪኑን አልፈው እየመጡ ይህን ገመናቸውን ሲተነትኑና ማናቸው ከማናቸው ጋር እንደተቆራኙ ከዘረዘሯቸው በርካታ መናፍስት ውስጥም ብዙዎቹ በመጽሐፈ ሔኖክ ከተዘረዘሩት ጋር በስም የሚቀራረቡ ናቸው።ከነስምና ከነ ተግባራቸው ከሚታወቁት ከእነዚህ ብዙ ጭፍሮች ውስጥ፣ጥቂቶቹን እንደ ምሳሌ ለመጠቀምና ‹ብነሱ ዘንድ› እንዴት እንደሚገለፁ ለማሳየት ያህል፤

Azaziel, Taught men to make swords, knives, shields, breastplates, the fabrication of mirrors and the workmanship of bracelets and ornaments, the use of paint, the beautifying of the eyebrows, the use of stones of every valuable and select kind, and of all sorts of dyes, so that the world became altered.

Shemhaziel,Taught enchantments and root-cuttings, Taught all the sorcerers, and dividers of roots. And made known to them the metals of the earth and the art of working them,and all kinds of costly stones.

Armeros, Armaros, Taught the solution of sorcery.Taught the resolving of enchantments.

Samyaza,Ahas taught sorcery, to whom thou hast given authority over these are associated with him..

Barkayal, Taught the observation of the starts.

zaaradiel, Taught the motion of the moon.

Akibeel, Taught Signs.

Tamiel, Taught Astronomy.

Baraqijal,Baraqel,Taught the observers of the stars."Taught astrology."

Kokabel, Kawkabel, Kakabel,Taught the science of the constellations.

Ezekeel,Taught the knowledge of the clouds.

Araqiel, Arakiel, Taught the signs of the earth.

Shamsiel, Shamshiel, Taught the signs of the sun.

Saraquel,Taught the motion of the moon. Taught the course of the moon.

Akibeel, Taught signs.

Gadreel and Ramuell, teaches and Introduced weapons of war.

Bifrons,fallen angel that appears monstrous and teaches mathematical arts.

Buer,fallen angel who teaches philosophy, logic and ethics.

Forcas,fallen angel who teaches politics, logic and ethics.

Armaros,fallen angel who teaches the "resolving of enchantments.

Caim,fallen angel who appears as a thrush or man with a sword.

Focalor,fallen angel who appears as a man with griffin wings.

Mastema, fallen angel whose name means "hostilities."

Lillith, fallen female angel who searches for children to kidnap or kill.

Andrealphus, fallen angel who can transform humans into birds.

Lix Tetrax, fallen angel of the wind

Lucifer, actually a Babylonian king whose name means "bearer of light."

Malpas, fallen angel who appears as a crow.
Leviathon, fallen angel associated with the deep seas.
Gusion, fallen angel who can discern the past, present or future.
Andromalius ,fallen angel who appears as a man holding a serpent.
Abaddon, fallen angel of death whose name means "to destroy."
Penemue, Taught the bitter and the sweet, the use of ink and paper.
Kasdeja, Kisdeja, Taught the children of men all the wicked smiting of spirits and demons, and the smitings of the embryo in the womb, that it may pass away.

.....ወዘተ እያሉ ነው የሚገልፁዋቸው::

እነዚህና እነዚህ መሰል እልፍ አእላፍ ጭፍሮች በስም፣በአካላዊ ገፅታ፣በባህሪ፣በተግባር፣በምግባር፣በእውቀት፣በችሎታ፣በስልጣን፣የተለያዩ ናቸው:: አንዳንዶች ሰው መስለው ሲከሰቱ፤ሌላው በራሪ አሞራ፣ አንዳንዶቹ ዘንዶ መስለው ሲከሰቱ፤ሌሎቹ ሌላ እየሆኑ የሚከሰቱና፤ግማሾቹ ባለ ቀንድ፣ግማሾቹ ባለክንፍ፣የሆኑ ናቸው::

ገሚሱ በጦር መሳሪያ ዙሪያ እውቀት ሲኖረው፤ሌላው በአስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ከፊሎቹ አማካሪ፤ሌሎቹ ጠቋሚ፣ አንዳንዶቹ ደዘው በራሪ፣ አንዳንዶቹ መሪ፣እየሆኑ ከሰዎችና ከድቅሎች ጋር እየተገናኙ የሚያስለጥኑና የሚያሰየጥኑ ናቸው::

ይህ በእንዲህ እንዳለም፤ አንድ ሳይንቲስት በአንድ ግኝት ብቻ የተወሰነ ያለመሆኑን ያህል፤ለጥፋት ዓላማ የሚውለውን እውቀትና ጥበብ የሚገልፅሉላቸው እርኩሳን መናፍስትም እንዲሁ በአንድ እውቀት ብቻ የተወሰኑ አይደሉም::አንድ የእንግሊዝ ወይም የአሜሪካ ሳይንቲስት ለምሳሌ የ 1 ሺ ግኝቶች ባለቤት ወይም ፈልሳፊ መሆኑ ተመዝግቦለት ይገኛል::ሆኖም ምንጩ አንድ ማዕድን ይሆንና፤ ያንን መሰረት ያደረገ ተከታታይና ተተመሳሳይ አዳዲስና የተለያዩ ግኝቶችን ይፋ ያደርጋል:: መናፍስቱም እውቀታቸው ስለዚያች አንዲት ማዕድን ብቻ ይሆንና፤ ነገር ግን በዚያች ግብዓት መነሻነት ብቻ ከ 1 ሺ በላይ የግኝት ውጤቶችን ማስገኘት እንደሚቻል ከነዘዴው ያውቃሉና ያንኑ ይገልጡላቸዋል:: ለምሳሌ አዛኤል የተባለው ጭፍራ እውቀቱ ስለ መስታወት ከሆነ፤ የሚሰራበትን የድንጋይ አይነትም ሆነ ግብዓት የሚሆነውን የማዕድን አይነት በማሳወቅ፤የመስታዎትን የአሰራር ጥበብና ግልጋሎቱንም ከገለጠ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

በኋላ፤በዚያው ቀጥሎ ስለ ሌንስ፣ስለርቀት አጉሊ መነፅር፣ስለ ላብራቶ መመርመሪያ፣ቀጥሎ በዓይን የማይታዩ ረቂቅ ነገሮችን ማሳየት ስለሚችለው ረቂቅ ሌንስ፣እያለ ስለ ዘመናዊ የህዋ ላይ ስክሪን አሰራርና ስለ አገልግሎቱ እየገለጠ ያስተምራቸዋል ማለት ነው።የግኝት ውጤቱም በሰሩት ወይም በፈለሰፉት ሳይንቲስቶች ስም ይፋ እየተደረገ በሰው ምርምር የተገኘ መሆኑ ይዘገባል።በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ድምፅ ንዝረትና ስለመተላለፊያ መንገዱ የሚያውቀው ጭፍራ፤የሽቦ ገመድን እንዴት መስራትና ድምፅን በንዝረት መልክ ማስተላለፍ እንዴት እንደሚቻል ከገለፀ በኋላ፤የግብዓቶቹን ምንነት አስረድቶ፣የሚገኙበትን ቦታ ጠቁሞ፤ አመጣጠንና አዋሃዱን አስረድቶ ያሰራቸዋል።እያለ ይቀጥልና፤ወደ ሳተላይት ቴክኖለጂ ወደመሸጋገር ይደረሳል።አሌክሳንደር ቤል እንዳለው ያቺ የማዕድን አይነት ወይም ግብዓት ከታወቀች በኋላ ሁሉም ነገር ቀላል ሆኖ ይገኝና ባስፈለገ ጊዜ እየተሻሻለ ይቀጠላል።

በዚህ አይነት መንገድ፤ በጦር መሳሪያ፣በኤሌክትሪክ፣በድምፅና ምስል፣ በወዘተ.....ሁሉም ከሁሉ እየተቆራኙ ያገኙት ውጤት መሆኑን በሰፊው አስረድተዋል።

ልክ በዚሁ መጠንም አንድ መንፈሳዊ አካል በስሩ ብዙ ጭፍሮች እንዳሉትና ለማን ለማን በምን ዙሪያ እውቀትን እንደሚገልፁ የመታዘዛቸውን ያህል፤ሳይንቲስቱም ከዋናው ጋር ተገናኝተው በጀመሩትና በቀጠሉት ምርምር ላይ ሌሎች የነሱ ደቀመዝሙር የሆኑ የሙያ አጋሮች ይኖሯቸዋል።የጀመሩትን እንዲጨርሱና ያላለቀውን እንዲቀጥሉበት በማዘዝ፤ ዘዴውንም በመንገር ራሱን የቻለ ተቋም በስማቸው መስርተው፤ ስራው በትውልድ ተቀጣጥሎ እንዲቀጥል የማድረግ ዘዴን ነው ሲጠቀሙ የቆዩት።

ሌላው ለምሳሌ አልበርት አንስታይን አዛዝኤል ወይም ራሙኤል ወይም ገደራኤል ከተባለውና በጦር መሳሪያ ዙሪያ እውቀት ካለው መንፈሳዊ ጭፍራ ጋር እንዲገናኝ ተደርጎ ሲጣመርና እውቀት ሲገለጥለት፤ በአዛዝኤል ጥቆማ፣ምክርና ድጋፍ ተመስርቶ ለውጤት ከበቃ በኋላ፤ በአንፃራዊነትም ሆነ በጨረታና በፀሐይ እንቅስቃሴ ዙሪያ በሚያጠነጥን ዘርፍ ተነስቶ ምርምሩን ሊቀጥል ሲፈልግ፤ አዛዝኤል ያን ለመስራት ማን ከተባለው መንፈሳዊ ጭፍራ ጋር መገናኘት እንዳለበትና እሱንም ለማግኘት መስፈርቱ ምን እንደሆነ ገልፆለት ያልፋል።በዚህ መሰረት አዛዝኤልን ተሰናብቶ፤በጨረታና በፀሐይ ዙሪያ ብቻ እውቀት ካለው ከ ባራክኤል ጋር ተገናኝቶ በሚያገኘው ድጋፍ፣ምክርና ጥቆማ ተመስርቶ ምርምሩን ይቀጥልና ለውጤት ይበቃል ማለት ነው።

ሁሉም ሳይንቲስት በዚህ አይነት ሂደት ተጉዘው ነገሮችን ለመፈልሰፍና ለመስራት የሚያስችላቸውን እውቀት፣ግብዓትና ምጣኔው ተሰግሷቸው ወደ ተግባር ገብተው ለውጤት በመብቃት፣ ግኝቱን በራሳቸው ጥረት ያመጡት አስመስለው ይፋ ሲያደርጉ የነበሩ ናቸው።የሌሎችም በዚሁ ምሳሌ መሰረት የሚገሰፅና እንዲያ ሆኖ የቀጠለ መሆኑን ነው በዋናነት ሲያስረዱ ያመሹት።

ንግስቲቱ ቀጠሉ።

‹‹እንግዲህ ይህ ሲሆን፣እያንዳንዱ ሳይንቲስት መስራት የፈለገውን ሳይሆን፣ልዑላችንና መንፈሳዊ አካላቱ መሰራት እንዳለበት የፈቀዱትን ብቻ ነው እንዲሰሩ የሚያደርጉት።ሆኖም አንድ ከመንፈሳዊ አካላት ጋር የተዋረሰ ሳይንቲስት ራሱ አስቦ፣ ‹‹እንዲህ ያለ ነገር ለመስራት እፈልጋለሁ›› የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ፣መንፈሳዊ ጭፍሮች ካመኑበት ሲፈቅዱለት ይችላሉ።ሲፈቅዱለትም የዋና አለቃቸውን ፈቃድ ጠይቀው አዎንታዊ ምላሽ ካገኙ በኋላ ነው።አስፈላጊ ካልሆነ በዘርፉ እንዳይቀጥሉ ይነገራቸዋል።ወይም ፊታቸውን ወደሌላ ዘርፍ እንዲያዞሩ ተነግሯቸው በሌላ ዘርፍ ይቀጥላሉ።ኢሲያም በሌላ ዘመንና በሌላ አባል የሚሰራ መሆኑን ገልፀው ያስቆሟቸዋል።እንዲህ እንዲያ እያሉ የሁሉም ግኝት ባለቤቶች ሁሉንም ጀምረውና አስቀጥለው፣ ሰርተውና አሰርተው፣ እዚህ አድርሰዋል።

እያንዳንዱ ሊቅ በየዘርፉ እውቀት ካላቸው ከልዑላችን ጭፍሮች ጋር ግንኙነት በመመስረት ነው ያንን ሁሉ ስራ መስራትና ዓለምን መለወጥ የቻሉት።መለወጥ ሲባልም የዓለምን ህዝብ ጠቅልሎ ለልዑላችን ለማስገዛትና ከሱ ጎን እስልፎ አጋዥ ለማድረግ መንገዱን ጠርገዋል፣ አመቻችተዋል ማለት ነው።ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹የግኝት ባለቤት ለመሆንና ነገሮችን ለመፈልሰፍም ብቻ ሳይሆን የአስተዳደራዊ እውቀትንና በጂኦግራፊ ዘርፍ የመልክዓ ምድር ካርታ ዘተርግቶ፣ እንዴት ህዝብን አደራጅቶ መምራት እንደሚቻልና፣የግኝቱን ውጤት በምን መልኩና በየትኛው ዘመን ለአስፈላጊ ነገር መዋልና መጠቀም እንደሚገባቸው የሚያስተምሩ መንፈሳዊ አካላት አሉ።

‹ብዚህ መሰረት የአሜሪካው የመጀመሪያ መሪ በኖ በዘሮቹ አማካኝነት በተመረጠለት የስራ ድርሻና የአገር ምስረታ ዘርፍ ተመድቦ ሲሰማራ፣ እንዴት አሜሪካን መምራት እንዳለበት የሚያስተምረውን ኮከባኤል የተባለውን ጭፍራ ይዞ፣ከሱ ምክርና የህግ ረቂቅ ተቀብሎ በእሱ እየተመራ ነው ሊያስተዳድር የቻለውና አገሪቱን በዚያው ስርዓት እንድትቀጥል

አድርጎ ሲያልፍ የቻለው፡፡ከከባኤል ተብሎ በአጭሩ የሚጠራው መንፈሳዊ አካል እውቀትና ችሎታው በአስተዳደራዊ ስራዎችና ሴራዎች ላይ መግባትና ማማከር ሲሆን፤አገሪቱም ሆነ መሪዎች በሱ የበላይነት ተመርተው እንዴት እንደሚዘምኑና ለበላያቸው ጥቅም እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸው የሚያመቻች ድንቅና በነፃነት የሚያምን ጥበበኛ ጭፍራ ነው፡፡ ጀርጅ ዋሽንግተን በእኛ በቤተሰቦቹ አስማሪነት፤ ተመርጠው በተሰጡት መንፈሳዊ አማካሪዎች ምክር፣ ድጋፍና እገዛ እየተመራ፤ተረቅቆ በተሰጠው ዘመናዊ ህግ እያስተዳደረ፣ህንፃዎቹን በልዑላችን ጭፍሮች ስምና አምሳል እንዲሁም ኮድ እያስቀረፀ፣ አገሪቱን የዘር ማንዘሮቻችን መታሰቢያ ሃውልት አድርጎ እየገነባና ዓርማችንም በአገሪቱ ገንዘብ ላይ ሳይቀር አትሞ ዛሬ ማስመሰክ የቻለ ታማኝ የኔፊሊም ድቅል የነበረ ቤተሰባችን ነው፡፡

‹‹ብዚህ መሰረት በግኝት ውጤቶች ብቻ ሳይሆን፤በአስተዳደራዊ ስራ የተሰማሩ ጭፍሮች በርካታ ሲሆኑ፤አንድን አገር እንዴት በዘመናዊ መንገድ ማስተዳደር እንደሚቻል ብቻ በመንገር ያቺ አገር የስልጣኔ ምንጭና የበላያችን ዕቅድ መፈፀሚያና ማስፈፀሚያ የሚያደርጉና ያደረጉ መናፍስት ከየመሪዎች ጋር እየተገናኙ ብዙ ሰርተዋል አሰርተዋል፡፡ የእነዚያ የዲሞክራሲ ሲቃውንት የአስተዳደር ጅምርም እጅግ ዘምኖና ገደብ የለሽ ሆኖ ቀጥሎ፤ ውጤቱም የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን በህግ ደንግጎና የህግ ከለላ አሰጥቶ እስከ መዋለድ ደረጃ የሚኬድበትን ሁኔታ አመቻችቶ፤ ግብረሰዶማውያንን እስከማብረታታትና፤በመንግስት ደረጃ የገንዘብ እገዛም እስከማስገኘት የደረሰ ሆኗል፡፡ ይህ ሁሉ ስልጣኔ በሊቃውንቱና በመናፍስቱ የጋራ ትብብር ሲከናወን ቆይቶ በጋራ ትብብሩ የተገኘ የጋራ ውጤት ነው፡፡ ‹‹ይህ ብቻ አይደለም ክቡራን፡፡አንድን አገር እንዴትና መቼ በምን ዘዴ ቅኝ እንደምንገዛና፤ የሚፈለገውን የሰው ሃይልም ሆነ የየአገሪቱን ማዕድናት እንዴት መውሰድና ለምን ጥቅም ማዋል እንዳለብን እየገለፁ፤ የዘሮቻችን ሽርፍራፊ የሆኑ ድቅሎችን ሰብስበን እንዴት አድርገን ሃያል ሆነን መቀጠል እንዳለብን አስተምረዋል፡፡በምን ወቅት የያዝነውን አገር መልቀቅ እንዳለብንና ባጋበስነው ውድና የከበሩ ማዕድናትም ሆነ የሰው ጉልበት አገራችን ላይ መጠቀም የምንችልበትን ዘዴና ጥበብ እያስተማሩ እዚህ አድርሰውናል፡፡

‹‹እነዚህ ያያችኋቸው ተመራማሪዎቹም ሆነ ፖለቲከኞች ውስጥ ገሚሱ የሰው ፍጡር ሆኖ ሂደቱን የጀመረና ሳያስበው እንዲያስበው የተመረጠ፣ ገሚሱ ከኛ ከእንግሊዝ ነገስታት ሃረግ የሆነና የኔፊሊም ድቅል የሆነ ነው፡፡ ጥቂቶችም የዘር ሃረጋቸው ከላይ ሲቆጠር የድቅል ዘሮች የነበሩና በጊዜ

ሂደት ከዚያ ዘር የሚመዘዙ መሆናቸውን እያወቁም ሆነ ሳያውቁ ከሰው ጋር በመዋለድ ብዛት ሙሉ በሙሉ ወደ ሰውነት የተለወጡ ይገኙበታል፡፡

‹‹ይህንን የዘር ቆጠራ ጉዳይ የምናከናውነው እኛ የእንግሊዝ ነገስታት ቤተሰቦች የነበርን ሲሆን፤፤ስምሪቱም በእኛ አማካኝነት ሲከናወን የቆዬ ነው፡፡

‹‹ብዙዎቹ ዘሮቻችን በጊዜ ሂደት ከመበታተንና ከመራራት ብዛት የዘር ሃረጋቸውን ሳያውቁ ሊኖሩ የቻሉ ነበሩ፡፡ነገር ግን እኛ አገራችን በዘመናዊ መንገድ ገንብተንና ሃያል ሆነን በስተመጨረሻም መጽሐፈ ሄኖክን እጃችን ካስገባን በኋላ፤እጃችን ላይ ከነበረው ተጨማሪ ታሪካዊ ሰነድ ጋር እያመሳከርን እነዚህን ዘሮቻችንን ከያሉበት መልቀምና መሰብሰብ የሚያስችለንን ዕቅድ ነድፈንና መንፈሳዊ ዘዴያችን ተጠቅመን ከያገሩ እየለቃቀምን አምምጥተን አሜሪካ ላይ ማስፈር ችለናል፡፡

‹‹በሂደቱም የዘር ሃረጋቸውን ያላወቁና ሰውነታቸውን ብቻ ይዘው ከተራው ሰው ጋር ተራ ኑሮ እየኖሩ የነበሩትን ፈልገን እየተገናኘን እንደ የምስራች የዘር ሃረጋቸውን ስናበስራቸው ማመን ያልቻሉና ያንገራገሩ ግራ የተጋቡ ብዙዎች ነበሩ፡፡ሆኖም ሰው አለመሆናቸውን ሰው ቢያደርገው ምንም የማይሆንን ነገር ሰው ያልሆኑት ሲያደርጉት የሚፈጠረውን ያልተለመደና የተለየ ነገር እንደማስረጃ እያቀረብን ከወገኖቻቸው መንፈሳዊ ጭፍሮች ጋር እያገናኘን በማዋረስና የእንግሊዝ ዜጋ አድርጎ ወደ አሜሪካና ካናዳ ተልዕኮ ሰጥቶ በመላክ የእውቀት ባለቤት የሆኑ ዝነኞች እንዲሆኑና ከኛ አገር በላይ እጃችን የሌለበት አስመስለን የመሰርትናትን አሜሪካንን እንዲያዘምኑ አድርገናል፡፡ለዚህም ነው ሁሉም የግኝት ባለቤት ዜግነቱ አሜሪካዊና እንግሊዛዊ ብቻ የሆነው፡፡

‹‹ይህ ሲባል ግን ለምሳሌ እኛ የእንግሊዝ ነገስታት ቤተሰቦች ድቅል ነንና የሰው ደምና ስጋ ካልበላንና ካልጠጣን የሰውነት ቅርፃችንንም ሆነ ሰውኛ የመሰለ ስብዕናችን ይዘን፤ ሰው ሆነንና መስለን መቀጠል አንችልም፡፡ይህ የሆነው በቀጥታ ግማሽ ማንነታችን ከኔፍሊም፤ ግማሽ ማንነታችን ከሰው ስለሆነ ነው፡፡ሃምሳ ሃምሳ ፐርሰንት ማለቴ ነው፡፡እኛ የእንግሊዝ ነገስታት ቀጥተኛ የዘር ሃረጋችን ጠብቀንና አስጠብቀን መቆየት የቻልን ስለሆንን ነው፡፡ሌሎቹ ግን ከጥንት ጀምሮ ተበታትነው የኖሩት በዘመናት ውርርስ ከሰው ጋር እየተጋቡና እየተዋለዱ በቀጠሉ ቁጥር ፐርሰንታቸው እየተመናመነ ሄዶ በማሽቆልቆሉ ወደ ሰውኛ ገፅታና አካላዊ ቅርፅ በማዘንበላቸው ነው፡፡ስለዚህ እነዚያ እየተፈለጉ የተለቀሙት እንደ እኛ ሃምሳ ሃምሳ ፐርሰንት ስላልሆኑ፤ ያለሰው ደምና ስጋ በሰውኛ ባህሪና አቋማቸው እንዲሁም አስተሳሰባቸው ሰው ሆነውና መስለው መኖር የሚችሉ ሆነው ያገኘናቸው በርካታ ነበሩ፡፡ብዙዎች ዘራቸውን ሳያውቁ

የቆዩበት ምክንያትም አካላዊ ቅርፃቸውም ሆነ አስተሳሰባቸው እንዲሁም መልካቸው ከሚኖሩበት አካባቢ ካለው ህዝብ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ነው። ሌላ ከሰውኛ ገፅታ ውጭ የሆነ ነገር ገጥሚቸው ባለማወቁ ነው። የሆነው ደግሞ እንደኛ ሃምሳ ሃምሳ ፐርሰንት ስላልሆኑና በውስን ፐርሰንት ብቻ ዘሩ ስላለባቸው ነው።

‹‹ብኛ ቤተሰብ በኩል አንድ ንጉስ ወይም ንግስት ግማሽ ግማሽ ከሆነ፤የምንጋባውና የምንዋለደው በተመሳሳይ ግማሽ ግማሽ ከሆኑ መሰሎቻችን ጋር ብቻ ነው።እኛ ሃምሳ ሃምሳ ሆነን እርስ በርስ ስንዋለድም፤ የሰው ሆርሞናችን በሁለታችንም ውስጥ እስካለ ድረስ ሌላ ለውጥ ወይም ወደ ሌላ ተጨማሪ ፐርሰንት ከፍ ማለት አንችልም። በዚያው በ 50 % ተወስኖ የሚቀር ነው።ከዚያ ዝቅ ላለማለትና እሱኑ አስጠብቆ ለማቆየት ነው ግማሽ ግማሽ ሆነን የምንጋባው።

‹‹ግማሽ ሰው ግማሽ ኔፊሊም የሆኑት አንዳቸው፤የሰው ስጋና ደም ተጠቅመው ወደ ሰውኛ ገፅታቸው ተመልሰው ባሉበት ቅፅበት፤ ሙሉ ለሙሉ ሰው የሆነን ፍጡር ቢያገቡና ቢወልዱ ግን፤የሚወለደው ልጅ የዘር ሃረጉን በ 25 % ያጣል።

ያ የተወለደው ልጅ ብዙም ምልክት ሳይታይበት ነገር ግን የተሻለ አስተሳሰብ ኖሮት ሊገኝ ይችላል እንጂ የግድ የሰው ደም መጠጣትና መብላት ላይጠበቅበት ይችላል።ከዚያ በኋላ ያ የተወለደው ልጅ እንደገና ሰው አግብቶ ቢወልድ፤ የምትወለደው ልጅ ወይም የሚወለደው ልጅ የዘር ሃረጉን እየለቀቀ ይሄድና፤ ወደ 10 እና ወደ 15 % ዝቅ ይላል።እንዚያ ከሰው ጋር ሲጋቡ ደግሞ የበለጠ እያሽቆለቆለ ይሄድና፤ሙሉ ለሙሉ የኔፊሊም ጂኑ ወይም ሆርሞኑ በአንዱ ትውልድ ይጠፋል።ሆኖም እኛ ያን መለየት የሚያስችለን ብዙ አይነት መንገድና መሳሪያ ነበረንና፤ከመጽሐፈ ሄኖክ መገኘት በኋላ ሙሉ ለሙሉ ሰው ያልሆኑትን የዘር ሃረጋቸውን ቆጥረን በመድረስ መልቀም ችለናል።

በመሆኑም ግማሽ ግማሻቸውን ሳያመናምኑ ማስቀጠል የቻሉት የግድ የሰው ደምና ስጋ ምግባቸውን ማድረግ ሲጠበቅባቸው፤ ከግማሽ በታች ያሉት ግን ያን ማድረግ ሳይጠበቅባቸው ከፍ ወዳለውና ሆርሞናቸው በዝቶ ወዳዘነበለበት ወደ ሰውኛ ባህሪ ከመምጣት ውጭ የሚገጥማቸው ሌላ ችግር የለም።እነዚህ ሰዎች የዘር ሃረጋቸውን አወቁም አላወቁም እንዲሁ በተፈጥሮ ከሰው የተሻለ ግንዛቤ ይኖሯቸውና፤ ለእውቀት ጉጉ የሆኑትና የመማር እድሉም ያላቸው ይጠቀሙበታል፤ሌላው ሳይጠቀምበት ይቀራል። የእድሜ ጉዳይም ተመሳሳይ ነው።

እኛ ሃምሳ ሃምሳ የሆንነው ራሳችን እየለዋወጥን ገደብ አልባ እድሜ ስንኖር፤ከሃምሳ ዝቅ ያለ 49 ም ይሁን 25 ወይም 10 እና 5 ልዩነት

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ሳይናር ሆርሞኑ ወደሰውኛ የሚያዘነብል ነውና ከፍተኛውን የሰው ልጅ የእድሜ ጣራ 120 ዓመት ኖሮ ያልፋል።ሆኖም በኛ ተፈልጎ ከተገኘ በኋላ በቤተመንግስታችንም ይሁን በሌላ ቦታና አገር ካሉ ከሌሎች የውስን ፐርሰንት ባለቤቶች ጋር በማገናኘትና በማጋባት ወይም በማዋለድ ባለ 25 ቱን ከ ባለ 15ቱ፣ ባለ 10 ሩን ከባለ 5ቱ ወዘተ....እያዳቀልን፣ ፐርሰንቱን ከፍ ከፍ እያስደረግን በመቀጠል 50 እናደርሰውና በዚያው ተወስኖ እንዲቀጥል እናደርጋለን።ከዚያም የሚገባውንና የሚመጥነውን ቦታና ሃላፊነት ሰጥተን በተለያየ ዘርፍ እናሰማራዋለን ማለት ነው።
እነዚያን የትናንሽ ፐርሰንት ባለቤቶችን ካያሉበት ፈልገን ካገኘን በኋላም በማስተማርና ከሰው የተሻለ የአስተሳሰብ መጠናቸውን እንዲጠቀሙ በማስቻል፣ ከልዑላችን መንፈሳዊ ጭፍሮች ጋር የሚገናኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ እንዲገናኙዋቸውና የረቂቅ እውቀትና እውቀት ግኝት ባለቤቶች እንዲያደርጓቸው እናደርጋለን፤እነዚህም እነሱን የመረዳትና ከነሱ ጋር የመግባባት አቅም በተፈጥሯቸው አላቸውና በቀላሉ ይግባባሉ። የሚባሉትን መስማትና መረዳት፣ተረድቶም ወደ ተግባር መተርጎም ይችላሉ።በዚህ አይነት አካሄድ ነው ያፆችኋቸውን አይነት ሳይንቲስቶች ማፍራትና አገራችንን እና ሁለተኛ አገራችንን አሜሪካን ስልጡንና ሃያል ማድረግ የቻልነው።
‹‹ይህን እየፈለጉ የማግኘት ስራ በጀመርን ወቅት አንዳንዶቹ እየነገርናቸው አላምን ሲሉና በተለያየ መንገድ ድቅል መሆናቸውን ካረጋገጥንላቸው በኋላ፤ እውነት መሆኑን እያወቁ፤ነገር ግን፤ ‹‹እንፈልግም፤ እኛ ሰዎች ነን፤ የአምላክ ፍጡሮች ነን፤ ገለመሌ››እያሉ ድርቅ ብለው የቀሩ ነበሩ። ከልዑላችን ውጪ ምንም ተስፋ እንደሌላቸውና በበላይ አካሉ አምነውና ታምነው በመኖር ምንም እንደማያተርፉ፣ባለ ድሉ ልዑላችን ነውና ከሱ ጎን እንዲሰለፉ፣ ለዓላማው እንዲተባበሩ፣አለዚያ በበላይ አካሉ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸው ብናስረዳቸው እንኳ አሻፈረን ብለው የቀሩ ብዙዎች ነበሩና በያሉበት ልናስወግዳቸው የተገደድንበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር።እናም አስወግደናቸዋል።እነዚህን ነው እንግዲህ ሂትለር በኋለኛው ዘመን ከረፈደ በኋላ በ2ኛው የዓለም ጦርነት በራሱ መሳሪያ እየመረመረና እያስለቀ ከየአገሩ ለመልቀምና እነሱንም ተጠቅሞ አገሩን ሃያል ሊያደርግ ጦርነት የቀሰቀሰው።ግን ሁሉም ነገር ያለኛ አይሆንምና አልሆነለትም።
‹‹ለማንኛውም እነዚህን መሰብሰብ ነው ለኛ ለእንግሊዝ የነገስታት ቤተሰቦች ያንድ ዘመን አድካሚ ስራ የነበረውና ከመጽሐፈ ሄኖክ መገኘት በኋላ ፍለጋው ቀሎልን በቀላሉ ከያሉበት መሰብሰብ የቻልነው።እነዚህን ነው አሜሪካና እንግሊዝ ላይ፣ጥቂቶችንም በሌላው አውሮፓ አገር በትነን ከዘሮቻቸው ጋር እያገናኘን ስራቸውን እንዲቀጥሉ ያደረግነውና እነሱም

ስራውን በአግባቡ ማስኬድ የቻሉት።ክነሱ ስርም ደቀመዝሙሮቻቸው ሆነው እየተማሩ፣ አጋዥ ሆነው እየተመራመሩ፣ የኖሩ ሙሉ ስሙሉ ስዎች የሆኑ በርካታ ነበሩ።እነሱንም በጥረታቸውና በብርታታቸው በቀጠሉት ነገር ላይ ተጨማሪ ጥበብ እንዲለገሱ እያደረግን በጋራ አስጉዘናል።ልዑላችን የእውቀትና የጥበብ ልዑል ነውና አይስስትም።ስለዚህ ጥረትና ጉጉታቸው፣ ጅምርና ዕቅዳቸው፣እየታዬ መንፈሳዊ ጥበብን እየተለገሱ በርካታ ለልዑላችን ጠቃሚ የሆነ ስራ የሰሩ ሰዎች ሞልተዋል። ‹የእውቀት ምንጫቸው መንፈሳዊ ጭፍሮች የሆኑ እነዚህ ያፍችኋቸው ታዋቂ ታዋቂ ሳይንቲስቶችም ድቅል የሆኑ ብቻ አይደሉም።ሙሉ ስሙሉ ሰዎች ሆነው ነገር ግን የግኝት ባለቤት የሆኑትንም ጭምር ነው ቅድም ያፍችሁና የተገናኛችሁት።

የሆነ ሆኖ ሁሉም ሊቃውንት የእውቀት ምንጫቸው የልዑላችን መንፈሳዊ ጭፍሮች ናቸው።በመንፈሳዊ ጭፍሮች አሰራር መሰረት ደግሞ ህግ አለ። ያውም ሊሽሩት ሊሸረሽሩት የማይችሉት ጥብቅ ህግ!በዚያ ህግ መሰረት ቃል ሲጋቡና ሲዋረሱ እንዲሁ በትውውቅ ላይና በዘር ሃረግ ላይ የተመሰረተ ብቻ ሳይሆን፤መናፍስቱ ያሻቸውን እውቀት ከመግለጣቸው በፊት የሚኖረውን መመዘኛ ሁሉም ቀድመው ካሟሉ በኋላ ነው ውርርሱ የሚከናወነውና ጥምረቱ እስከመጨረሻው የሚዘልቀው።ቃሉንና ህጋቱን አፍርሶ ማፈንገጥ ግን ይቻላል።ያን አድርጎ የሚከተለውን የዘላለማዊ ሞት ዋጋ ከፍሎ መስናበት እንደማለት።

ከዚሁ ጋር የሚጠቀሰውና መታወቅ ያለበት ሌላው ነገር ደግሞ በመስዋዕትና በተለያዩ አይነት መንገዶች በስጦቶ የመቀበል መርህ ላይ የተመሰረተው ቁርኝት ሲከናወን፤ሰዎች የግኝታቸው ውጤት ለምን ዓላማ እንደሚውል የማወቅ መብት ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም መቻሉ ነው። ስለዚህ ግኝታቸው ለምን ዓላማ እንደሚውል ሳያውቁና ሳይነገራቸው እንዲሁ ቁርኝት ውስጥ ገብተው፤ ስራውን ስርተው፣ ዝነኛ ሆነው፣በግኝት ውጤታቸው አማካኝነት የሚያገኙትን ዝናና ገንዘብ ብቻ እያሰሉ የተሳተፉ ሊቃውንት በርካታ ነበሩ።እንዲሁም ዓላማውን ጠይቀውና ተነግሯቸው አምነውበት ከተቆራኙ በኋላ፤ስራቸው ቀጥሎ ወደሌላ ነገር መሸጋገር እንደሚፈልጉ ገልፀው አባል ሆነው የቀጠሉና ብዙ ግኝት ይፋ ያደረጉ ሰዎችም አሉ።በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ እውቀትና ጥበብን ከልዑላችን ጭፍሮች ተቀብለው ለውጤት ከበቁ በኋላ፤የግኝት ውጤቱን ለበጎ ነገር አውላለሁ የሚሉ አስቂኝ ተመራማሪዎችም ነበሩ። ‹ለእንዲህ አይነቶቹ ጥበብ ባይነፈጋቸውም፤ለጥሩ ነገር ሊያውሉት ሲጀምሩ የማስቆምና የማስለወጥ ሃይልና ስልጣኑ የነዚህ የመናፍስቱ ነውና ይህን አቋም ይዘው ሲጀምሩት አይከለከሉም።ምክንያቱም

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

እንዲጀምሩት ተፈቀደላቸው ማለት ለልዑላችን የመጨረሻ ዓላማ
ያስፈልጋል ማለት ነውና ስራቸውን እንዲቀጥሉ ይፈቀድላቸዋል፤
ይመቻችላቸዋል።ስራው ከተሰራ በኋላ ግን አግኚዎች ለግል ዓላማቸው
ጥቅም ላይ ማዋል አይፈቀድላቸውም።ከእነዚህ አይነት አስቂኝ
ሳይንቲስቶች ውስጥ አንዱ የሆነው አልፍሬድ ኖቤል ጥሩ ምሳሌ ነው።
ድማሚትን የመፍጠር ጥበብ በቁርኝት ከወሰደ በኋላና ከስራው በኋላ፤
ተራራ አፍልሽ ለአገሮች ልማት ላውለው ነው የሚል አቋም ይዞ
እንቅስቃሴ በጀመረ ማግስት የሱ ውጤት የሆነውን፤ነገር ግን ፓተንቱ የሱ
ይሁን እንጂ ባለቤትነቱ በምርምር ማዕከል ስር ነበርና ግለሰቡንና
ዓላማውን ወደ ጎን በማድረግ ለጦርነት ማዋል ተችሏል።ለልማትም
ውሏል።በሌላ አገላለፅ የኔ ግኝት ነውና ለጦርነትማ አይውልም!ብሎ
መከራከርና መሟገት የሚቻልበት የግኝት ባለቤቶች ብቻ የሚያዙበት
አሰራር የለም።ምክንያቱም ግለሰቦች በራሳቸው ጥረት ጀምረው
የተውትንም ሆነ ተቆራኝተው ያገኙትን ግኝት ባለቤትነቱ የነሱ ቢሆንና
በገንዘብ ተጠቃሚዎች እነሱ ቢሆኑም፤ የምርምር ውጤቱን ለብቻቸው
ይዘው መሄድ ስለማይችሉ ነው።ስለዚህ ዋናው ነገር ቀድሞ የምርምር
ማዕከሉን ማቋቋና የእነሱ ወገን የሆኑ ጀማሪዎችን የበላይ ተመራማሪ
አድርጎ ማስቀመጥ እንጂ፤ማንም ተማሪና ተመራማሪ የራሱንም
የመንፈሳዊ አካላቱንም ጥበብ ይዞ መሳተፍ ይችላል።ማንም ግን ለግሉ ይዞ
መፈርጠጥ አይችልም።
ሆኖም የግኝት ባለቤት ከሆኑ በኋላ ሊከዱን የሞከሩ ነበሩና አቋማቸውን
ባወቅን ማግስት አስወግደናቸዋል።ይህ ስዎችን በተመለከተ ነው።
‹‹ድቅሎች ግን ከበላይ አካሉ ጋር ምንም እድል ፈንታ ስለሌላቸውና
ምርጫም ስለሌላቸው በዘር ሃረጋቸው ምክንያት እንደ ሰው የበላይ አካሉን
አምነው መቀጠል እንደማይችሉ ስለሚያውቁ እንዲህ አይነት ማንገራገር
ውስጥ አልገቡም። ተስፋቸው ልዑላቸው ብቻ መሆኑን በማስረዳት፤
ዓላማውን በማስተማርና ባለ ድል መሆኑን በማሳየት አሳምነን ነውና
ያሳተፍናቸው፤ ብዙዎችን በቀላሉ ተሳታፊ ማድረግ ተችሎ በደስታና
በትጋት የተሰጣቸውን የቤት ስራ በሚገባ መፈፀም ችለዋል።
‹‹እናም.....ክቡራን.....የምድር ስልጣኒ ምንጩ ባያችሁት መልኩ የሚገለፅ
ነው።ስለዚህ የግኝት ውጤቱም ሆነ አጠቃላይ የምድር እውቀትና ንብረት
ለልዑላችን ዓላማ የሚውል ሆኖ፤ በዘመን ተቀምሮ አሁን ያለበት ደረጃ
መድረሱን ልትገነዘቡት ያስፈልጋል።
‹ክቡራን የአዲሲቷ የምድር መንግስት ሹማምንት! የልዑላችን ታማኝ
አገልጋዮችና አስፈፃሚዎች ሆይ!በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ!››አሉና፤
በቁንጥ አረማመድ ወዲያ ወዲህ ሲንጎራደዱ ቆይተው ቀጠሉ።

ፍሥሐ ያዜ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

‹‹ይህ ሁሉ የእውቀት ጅማሬና ቀጣይነት ያለው የረቀቀ የጥበብና የቴክኖለጂ ውጤት በኛ ተሰርቶ፤ ለኛና ለምድር ህዝብ መጥቀም መቻሉና፤ በመጨረሻም ለልዑላችን ዓላማ ውሉ ለድል እንደሚያበቃው በመረዳታችሁ ሁሌም ደስ ሊላችሁ ይገባል!

‹‹አዲስ የምድር መንግስት ምስረታ››በሚል መነሻ የልዑላችን ዓላማ ተገልያላችሁና አምናችሁበት አባል አገር ከሆናችሁበት ጊዜ ጀምሮ፤ እስካሁን ድረስ በነበረው ሂደት ተሳታፊ ሆናችሁ ቆይታችኋል፡፡ይህ ማለት በልዑላችን አምናችሁ፣ለልዑላችን ታምናችሁ፣ አሁን ድረስ ቆይታችኋል ማለት ነውና ከዚህ በኋላ በሚኖረው ሂደትም የማትስማሙበት ነጥብ አይኖርም ብለን እናምናለን፡፡ለዚህ ነው ዛሬ ሁሉንም ነገር ይፋ ያደረግንላችሁና ከአንድነት አልፈን ወደ ውህደት እንድንገባ የጠየቅናችሁ፡፡ ስለዚህ መስማማታችሁን ግለፁልኝ››ሲሉ፤ሁሉም መሪዎች በጋራ ተነስተው ረዘም ብሎ ደመቅ ያለ ጭብጨባ አስደመጡ፡፡

‹‹ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹ተቀመጡ፡፡በዚህ ከተስማማን የኛ ወገን ከሆኑ በተለያየ ዘርፍ ከተሰማሩ ጥቂትና ዋና ዋና የዓለማችን ባለሐብቶች፣የቴክኖለጂ ውጤት ባለቤቶችና፤ የየካምፓኒው ባለ ስልጣኖች፤ እንዲሁም የኛ የነገስታት ዘሮች ጋር በጋራ ተዋወቁና በደም የሚገባውን ቃል ኪዳን በጋራ አድርገን፣ለልዑላችንም የጋራ መስዋዕት በማቅረብ ውህደቱን እንፈፅም፡፡አሁንም መስማማታችሁን አረጋግጡልኝ››ሲሉ፤ ተሰብሳቢዎች በድጋሚ ተነስተው ሞቅ ያለ ጭብጨባ አደረጉና መስማማታቸውን አረጋግጠው ተቀመጡ፡፡

‹‹መልካም፡፡ይህን ፕሮግራም የምናደርገው የዓለማችን የቴክኖለጂና የረቂቅ ጥበብ ምንጭ የሆነው፤እንግሊዝ ውስጥ ካለው በብዙ ሺ እጥፍ ከሚበልጠውና ዋናው!አሜሪካ ውስጥ ካለው በብዙ ሺ እጥፍ ከሚበልጠው የመጨረሻው! ማክሮ 6 ኮምፒውተር!በሚገኝበት አገር በኢሮፒያን ዩንዬን በቤልጀም ብራሰልስ ይሆናል ማለት ነው!

‹‹የዚህ ሁሉ የእውቀት ቀመርና የትምህርት ውጤት፣የዚህ ሁሉ የምርምርና የጥረት ውጤት፣የዚህ ሁሉ የቴክኖለጂና የጥበብ ውጤት፣ የዚህ ሁሉ የዘመናት ልፋታችን ውጤት፣ሄዶ ሄዶ የት ደረሰ?ምንስ አስገኘልን?ምን ደረጃ ደርሶልን ይገኛል?እንዴትና በምን መልኩ ነው ጥቅም ላይ የምናውለው?የዓለማችን ህዝብ በናንተ በመሪዎች አማካኝነት ጠቅለለን በልዑላችን ስር እናደርጋለን ስንልስ በዋናነት በምን ዘዴ ተጠቅመን ነው?ይህንን በቤልጀም ብራሰልሱ ዝግ ጉባኤያችን በዛሬው ምሽት ይፋ እናደርግላችኋለን!

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

‹‹አዎን!የጥረታችን ውጤት ቀጥለን ይፋ በምናደርግላችሁ አስደናቂ ደረጃ ላይ ደርሶ ይገኛል!!››አሉና የመጨረሻውን ቃል እጅግ በሃይልና በድምቀት ብሎም አስደንጋጭ በሆነና ባልተጠበቀ ጩኸት፤‹‹.....ደርሶ ይገኛል!!›› ሲሉ፤ተሰብሳቢዎቹ ሁሉ በጩኸታቸው ክው ብለው ሲደነግጡ ተስተዋሉ። እንዲህ በጩኸት ካስደነገጡ በኋላ ደግሞ፤መለስ ብለው ረጋ ባለ ድምፅ፤ ‹‹ይህን የጋራ ዝግ ጉባኤ እዚህ ላይ በማቋረጥ ፈጥነን ወደ ቤልጅም ብራሰልስ እናመራና እዚያ እንቀጥለዋለን።እዚያ በምናደረገው ዝግ ጉባኤ የዘመናት ልፋት ውጤታችን አይተን፣አድንቀን፣ ተደንቀን፣ የመስዋዕት ስነ ስርዓታችንን በጋራ ፈፅመን፣ምሽት ላይ ወደ ሜልቦርናችሁ ትመለሳላችሁ፡ ፡ከዚያም በይፋ የሚታወቀውን የሸፋን ጉባኤያችሁን የዓለም ህዝብ በሚያውቀው እለትና ሰዓት ሜልቦርን ላይ ታደርጉና የ G 20 ዓመታዊ ጉባኤ ተካፋይነታችሁን አጠናቃችሁ ወደየ አገሮቻችሁ ትመለሳላችሁ። እሱም በየመገናኛ ብዙሃኑ ይዘገባል እ? ጋዜጠኛ በተሰበሰበበት የምታወሩት ትርኪ ምርኪ ወሬ ማለቴ ነው.........›› ብለው በማላገጥ ስቀው አሳቋቸው።

‹‹መልካም፤የጉዞ ዝግጅቱን ጳጳሳችሁ በሚስጥር አዘጋጅተው ጨርሰዋልና እንደተለመደው በፈጣኑ መጓጓዣችን ተጠቅመን ወደ ቤልጅም ከመሄዳችን በፊት ልዑላችንን አመስግነን የመዝጊያ ፀሎታችንን ወደ ማድረስ እንለፍ። ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹ክብር ለአሸናፊ አብዮተኛችን!››

‹‹አሜን››

‹‹ክብር ለጭለማው ልዑል!››

‹‹አሜን!››

ወደ ምስጋና ፀሎታቸው አልፈው፤ እየጓሩ፣ እየጮሁ፣ እየተንከባለሉ፣ ልዑላቸውን አመሰገኑ።፡የመዝጊያ ፀሎታቸውንም በተመሳሳይ አድርሰው በጭብጨባ አዳራሹን አድምቀው ሊወጡ ተዘጋጁ።

ጥቁሩ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት በሩጫ ቀረሽ እርምጃ ወደ መድረኩ ሄዶ ያላት ላፕቶፕ አጥፍ አደረጋት።፡በዚህ ጊዜ ጭልም አለ።፡ከዚያ በኋላ በምን አይነት መጓጓዣ በርረው እንደሄዱ ባይታወቅም፤ከውስን ሰዓታት በኋላ በቤልጅም ብራሰልስ በተመሳሳይ አዳራሽ የዝግ ጉባኤያቸውን ካቆሙበት ሲቀጥሉ ለማየት ተቻለ።

....

ፍፃሜ ያዜ

Belgium Brussels November 13 / 2104 እ.ኤ.አ

በቤልጀም ዋና ከተማ ብሩሴልስ ውስጥ በሚገኘው ቀይና ክብ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ የ G 20 አገራት መሪዎች በቀይ ልብሶቻቸው እንደደመቁ ውጭና ውስጣቸውን አጥፍተው ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀምጠዋል።
ከእነሱ ፊት ለፊት ደግሞ ሌሎች 44 ሰዎች ክብ ሰርተው ባሉ ወንበሮች ዙሪያ በተመሳሳይ ቀይ አልባሳት ደምቀው ተቀምጠዋል።እነዚህ 44 ሰዎች በየዘርፉ የተሰማሩ የዓለማችን ታዋቂ ታዋቂ ሰዎች ሲሆኑ፤ከተለያዩ ቡድኖች ተወክለው የመጡ መሆናቸው ነው።
ከአውሮፓ ነገስታት ቤተሰቦች፣ከታዋቂ የዓለማችን ባለሃብቶች፣ከግዙፍ በሽታ አምራች ፋብሪካዎች፣ከወረርሽኝ አምራች ኩባንያዎች፣ከግብረ ሰዶማውያን ማህበር፣ከታዋቂ የኪነጥበብ ሰዎች፣ከዓለም ጤና ድርጅት፣ ከዓለም ምግብ ድርጅት፣ ከዓለም ገንዘብ ድርጅት፣ተውጣጥተው ተወክለው የመጡ ናቸው።
ከዓለም የሐይማኖት ድርጅቶች ተወክለው የመጡ ተጨማሪ ጳጳሳትና የቴክኖለጂ ግኝት ባለቤቶች፣እንዲሁም የየካምፓኒው አመራሮችም አብረው ተገኝተዋል።
እነዚህ ከየዘርፉ የተውጣጡ ተሰብሳቢዎችም እኩል ሚስጥር የተካፈሉና ውስጥና ውጫቸውን ማብራት የሚችሉ ናቸው።
በጥቁሩ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት እጅ የምትቀመጠው የአፕል ማርክ ያላት ብርማ ላፕቶፕ እንደተለመደው የመድረኩ ንግግር ማድረጊያ ቦታ ላይ ተስተካክላ ተቀምጣለች።
የክቡና የቀዩ ሰፊ የአዳራሽ መድረክ ግን ለጊዜው ባዶውን ሆኖ ነበር የሚታዬው።እናም ተሰብሳቢዎቹ በፀጥታ በመጠባበቅ ላይ ናቸው።
ከደቂቃዎች የዝምታ ቆይታ በኋላ የቫቲካኑ ጳጳስ ቀይ በቀይ የሆነ ሐይማኖታዊ ልብሰ ተክህኗቸውን እንደለበሱ የአዳራሹ መድረክ ላይ ድንገት ተከሰቱና፤
‹‹እንዲሁ እንዳላችሁ ውስጥና ውጫችሁን ሳታበሩ ንግስታችሁን ተቀበሉ››የሚል ትእዛዝ ሰጡ።
ተሰብሳቢዎችም በጋራ ቆመው ንግስቲቱን ሊቀበሉ ተዘጋጁ።
ተሰብሳቢዎቹ ገና ከመቆማቸው፤ አሮጊቷ የታላቋ ሌባ የብሪታኒያ ንግስት ልክ እንደ ጳጳሱ መድረኩ ላይ ተከሰቱና፤‹‹ክብር ለልዑሉ››አሉ ቀስ ብለው።
‹‹አሜን››አሉ ተሰብሳቢዎች በሹክሹክታ።
ጳጳሱን ከፊት ካለው ወንበር ሄደው እንዲቀመጡ በምልክት ትእዛዝ ሰጧቸው።ጳጳሱም በዝግታ እየተራመዱ ሄደው ከተሰብሳቢዎች ፊት ለፊት ራቅ ብለው ለብቻቸው ከክቡሩ ሁለት ወንበሮች በአንዱ ላይ ጠቀመጡ።

ተሰብሳቢዎችም በአንድነት ተነስተው ንግስቲቱን እጅ ነስተው ከተቀበሉ በኋላ ተቀመጡ።

ንግስቲቱንና ጳጳሱን ጨምሮ አዳራሹ 66 ሰዎችን ይዟል።

‹‹እርስ በርሳችሁ ተዋወቁ ክቡራን››አሉ ንግስቲቱ።

በዚህ ጊዜ ፀጥ ብሎ የነበረው አዳራሽ በትርምስ ተሞላ።ሁሉም ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ ሌሎቹ በመሄድ የእርስ በርስ ትውውቅ ጀመሩ።እየተጨባበጡ፣ ክንዶቻቸውን እያርገፈገፉ፣ ትከሻ ለትከሻ እየተገጫጩ፣እየተሳሳሙ፣ በደንብ ተዋወቁ።እንኳን ደስ አላችሁ፣እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደህና መጣችሁ፣የሚል ዝቅተኛ ድምፅ በተደጋጋሚ ሲሰማ ቆዩና ሁሉም ተዋውቀው ጨርሰው ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀመጡ።አዳራሹ መልሶ ፀጥ አለ።

ንግስቲቱ ረጋ ባለ ድምፅ፤‹‹ባለሙያችን ወደ መድረኩ እንድትመጣ ትታዘዛለህ››የሚል ጥሪ አቀረቡ።

ይህን እንዳሉ፤ፈንጠር ብሎ ከኋላ ወንበር ተቀምጦ የነበረ ቀይ በቀይ የለበሰ ረጅምና ገልጃጃ ጎልማሳ ሰው ተነስቶ መጣና ለንግስቲቱ ሰላምታውን አቅርቦ መድረኩን ተረከበ።

ንግስቲቱም መድረኩን ለሰውዬው አስረክበው ጎተት ጎተት እያሉ ወደ ተሰብሳቢዎች በማምራት ከጳጳሱ አጠገብ ካለው ለዩት ያለ ምቹ ወንበር ላይ ተቀመጡ።

‹‹እንኳን በደህና መጣችሁ ክቡራን፤ክብር ለልዑላችን››አለ።

‹‹አሜን!›› የሚል ሞቅ ያለ ድምፅ ተስተጋባ።

ረጅሙ ሰውዬ ዓይኖቹን ቶሎ ቶሎ እርግብ እርግብ እያደረገ፣ከንፈሮቹን በምላሱ ደጋግሞ እየላሰ፣ የለቅሶ ዜማ ባለው ቀጭን ድምፅ ገለፃውን ጀመረ።ፈጠን ብሎ ዝግ ያለ፤ቀዥቀዥ ብሎ ረጋ ያለ ወዝንብንብ ያለ አይነት ሰው ነው።የቸኮለም ይመስላል።

‹‹እንኳን ደስ ያላችሁ ክቡራን።ውስጣችሁን አብርታችሁ እንድትከታተሉኝ እጠይቃለሁ››ሲል፤ ሁሉም ወደ አስፈሪነታቸው ተመለሱና አዳራሹን የባለ ቀንድ ቀያይ እንስሶች ጋጥ አስመሰሉት።

‹‹ብጣም ጥሩ ክቡራን››አለና፤የራሱንም ውጭና ውስጥ አብርቶ ወደ ቀጣይ ተግባሩ አመራ።

የስፊውን አዳራሽ መድረክ የፊት ለፊት ግድግዳ በእጅ ምልክት ብቻ ወደ አራት አቅጣጫ ተከፋፍሎ፤እኩል ተንሸራቶ ወደ ጥግ እንዲሰበሰብ አደረገው።

የአዳራሹ ግድግዳ መሃሉ ላይ በቅርፅ ተከፍሎ፤ ወደ ላይም፣ ወደ ታችም፣ በፍጥነት ተንሸራትቶ ቀኙ ግድግዳ ሙሉ ለሙሉ ከእይታ ውጪ ሲሆን፣ ሌላ ሰፊና ባዶ የሆነ ንፁህ ክፍል ታዩ።

ቀጥሎ ባለሙያው በተመሳሳይ የእጅ ምልክት በመድረኩ ትክክል ያለውንና ከመድረኩ ግድግዳ በስተጀርባ የታየውን ሰፊ ክፍል ጣራው ክፍት እንዲሆን አደረገው፡፡አንድ እጁን ወደ ላይ አንስቶ ላዩ ክፍት እንዲሆን ሲያዘው፤የጣራው የውስጥ ክፍል ወደ አንድ አቅጣጫ ተስቦ፤ ኘው ብሎ በፍጥነት በመንሸራተት ከእይታ ውጪ ሆነ፡፡ ወደ ላይ ባዶ ሰማይ እንጂ ምንም አይታይም፡፡

ክፍሉ ግድግዳና ወለሉ እንደ ንፁህ ብርጭቆ እያብረቀረቀ የሚታይ ባዶ ክፍል ነው፡፡

ወዲያው ግን የባዶው ክፍል ወለሉል በራሱ ጊዜ ወደ አራት አቅጣጫ በቅርፅ መከፋፈል ጀመረና፤ከወለሉ ስር አንዳች ነገር ወደ ላይ ከፍ እያለ በዝግታ እየተመዘዘ መውጣት ጀመረ፡፡

በዝግታ ከፍ እያለ የወጣው እኩል ቅርፅና ቁመት ያለው አራት ማዕዘን የመስታዎት ሳጥን ነው፡፡

ይህ አብረቅራቂ ግዙፍ ሳጥን ሙሉ ለሙሉ ወደ ላይ ወጥቶ አየር ላይ ቀጥ ሲልም፤ከስሩ ያለው አብረቅራቂ ወለል እንደገና ወደነበረበት ተመልሶ ገጠመ፡፡ወለሉ እንደገጠመም ያ ግዙፍ አራት ማእዘን አብረቅራቂ ሳጥን ወደ ታች ዝቅ በማለት ወለሉ ላይ አረፈ፡፡

በእርግጥ ይህን ግዙፍ ሳጥን መስታዎት ብሎ መጥራት ይከብዳል፡፡ ምክንያቱም እንዲህ የሚያብረቀርቅና ንፅት ያለ መስታዎት በምናውቀው ዓለም ታይቶ አይታወቅምና፡፡ሆኖም በሌላ በምንም ነገር መመስልና ማገለፅ ስለማይቻል እንዲሁ መስታወት ብሎ ከመግለፅ ውጪ ለጊዜው ምርጫ አልነበረም፡፡ማንም ሰው ድንገትና ለመጀመሪያ ጊዜ ቢያዩውና፤ ‹‹ምንድነው ይሄ›› ተብሎ ቢጠየቅ የሚመልሰው መልስ፤ከንፁህ መስታወት የተሰራ ቤትና ሳጥን፤ወይም ግዙፍ የብርጭቆ ሳጥን የሚል ነው የሚሆነው፡፡ ሉካ.....መስታወትም ብርጭቆም አይደለም.........፡፡

ባለሙያው ቀጠለ፡፡

‹‹ይህ ያለንበት ሚስጥራዊ አዳራሽ በዚች ከተማ ድንቅ ህንፃ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፤ከሌሎች ከተሞች አዳራሾቻችን እጅግ ለየት ያለ ነው፡፡ አዳራሹ የህንፃው የመጨረሻ ክፍል ላይ የሚገኝና ደህንነቱም የተጠበቀ ነው፡፡ለዚያ ነው ወደ ላይ ሰማይ ብቻ የሚታያችሁ፡፡

‹‹ይህ ከመድረኩ ግድግዳ ጀርባ የምታዩት ክፍልም የዚሁ አዳራሽ አንድ አካል ሲሆን፤ ሙሉ በሙሉ የተገነባው የሰው ልጅ አይቶት ከማያውቅ ውድ እና ረቂቅ የፕላቲኒዩም አይነት ነው፡፡

‹‹በዚህ መቶ ሜትር በመቶ ሜትር በሆነ ባዶና ንፁህ ክፍል ውስጥም የመጨረሻ የሆነው ውድ ንብረታችን ተቀምጦበት ይገኛል፡፡ይህ ከወለሉ ስር ወጥቶ በሰፊው ቦታ ላይ የተቀመጠው ሳጥን ደግሞ፤በአራቱም አቅጣጫ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

እኩል 66 ሜትር በ 66 ሜትር ሆኖ ከውዱና ከረቂቁ ተመሳሳይ የፕላቲኒዬም አይነት ተቀርፆ የተሰራ ነው፡፡ከውጭ ሲታይ ሳጥኑ ውስጡ ባዶ ይመስላል፤ባዶ ግን አይደለም፡፡

ይህ ውድና ረቂቅ ስፌ ሳጥን ከኛ ከጥቂቶች በስተቀር ሌላው የዓለማችን ህዝብ አይቶት የማያውቅ ለየት ያለ ግዙፍ ኮምፒዩተር በውስጡ አቅፎ የያዘ ነው! ውስጡ ያለው ውድ ንብረታችን Macro 6 Computer /ማክሮ 6 ኮምፒዩተር/ ይባላል፡፡

‹‹ይህ 66 ሜትር በ 66 ሜትር የሆነ አራት ማዕዘን አብረቅራቂ ፕላቲኒዬም ሞኒተሩ/ስክሪኑ/ ሲሆን፤ ውስጡ ያለው ደግሞ ሲ ፒ ዩ ው /ሴንትራል ፕሮሰስ ዩኒቱ/ ነው፡፡ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር አሰራርና አወቃቀሩ እንደ እንደማንኛውም ፐርሰናል ኮምፒዩተር አይነት ነው፡፡ሆኖም በሞኒተሩና በሴንትራል ፕሮሰስ ዩኒቱ እንዲሁም በሌሎች ነገሮቹ ከዓለማችን ኮምፒዩተሮች እጅግ የሚለይበት ዘርፈ ብዙ ነገር አለ፡፡

በሴንትራል ፕሮሰስ ዩኒቱ ውስጥ ያለው ዳታ መመዝገቢያ ክፍል እጅግ ከፍተኛና ልትገምቱት የማትችሉት መጠን ያለው ሲሆን፤ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ቲሪሊዮን ‹‹ፒታ ባይት››/petabyte/ ነው!››ሲል ‹‹ምን?››የሚል የበርካታ ተንራሚዎች የጋራ ድምፅ ተሰማ፡፡

‹‹አዎን 666 ቲሪሊዮን ፒታ ባይት!››ሲል ደገመው፡፡

‹‹ተከታተሉኝ ክቡራን፤ፒታ ባይቱ ብቻ አይደለም፤በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዬን/666 Sextillion/ /10^{21}/ጥያቄዎችን አሰላስሎ የመመለስ አቅም አለው!›› ሲል፤ውስጣቸውን አብርተው እንኳን ማመን አቃታቸውና ሁሉም በአንድነት ደንግጠው ቆሙ፡፡

‹‹666 ሲክስቲሊዬን ጥያቄዎችን ተቀብሎ፤አንሰላስሎ ለመመለስ የሚፈጅበት ጊዜ አንድ ሰከንድ ብቻ ነው!››ሲል፤የቫቲካኑ ቋጳስ ሳይቀር ደንግጠው ተነሱ!ንግስቲቱ ግን በተቀመጡበት እንዳሉ በኩራት ጭንቅላታቸውን እየወዘወዙ ፈገግ ብለው ነበር የሚታዩት፡፡

‹‹አዎን ክቡራን፤በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዬን ጥያቄዎችን መመለስ ቻለ ማለት፤ፍጥነቱ በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዬን ‹‹ዜታ ቢት››/10^{21} zettabit/ ይችላሉ፡፡ለምሳሌ ‹‹ይሄ ምንድን ነው?››ብለን ብንጠይቀው፤በሶስት ቃላት የተዋቀሩ ጥያቄዎችን ማቅረባችን ነው፡፡ይህ አንድ ጥያቄ ተብሎ ሲቆጠር፤ ሁለተኛውን ጥያቄ ደግሞ ረጅም ጊዜ ወስደን፤በመቶ ሺዎች፣ወይም በሚሊዮኖች ቃላት የተዋቀሩ አድርገን አዘጋጅተን መጥተን ብንጠይቀው ሁለተኛ ጥያቄ ተብሎ የሚቆጠር ነው፡፡በዚህ አይነት ባለ አራት መቶ ገፅ ጥያቄም ይሁን ባለ ሶስት ፊደል ጥያቄ እናቅርብ፤ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ምላሹን በአንዲት ሰከንድ ይሰጣል!በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዬን

ማለት የዓለማችን ህዝብ ከመጀመሪያው ከሰው ልጅ ታሪክ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለው ከትምህርትና ከእውቀት ጋር የተያያዘ የተለያዬ ጥያቄ ተደማምሮ 666 ሲክስቲሊዬን ጥያቄ ባይሞላም፣ሞላ ብለን ብናስብና በሚሊዮን የሚቆጠር ዕድሜ ኖሮን ሲክስቲሊዬን ጥያቄ አዘጋጅተን ብናመጣ ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ሁሉንም ጥያቄዎች አሰላስሎ በ1 ሰከንድ ብቻ የዚያን ሁሉ ሲክስቲሊዩን ጥያቄ ምላሽ ይሰጠናል ማለት ነው::

‹‹አንሰላስሎ የመመለስ ብቻ አይደለም ክቡራን::ዳታዎችን በራሱ ጊዜ የመመዝገብ አቅሙም፣የማስታወስ አቅሙም፣ፍጥነቱም፣ ሁሉም በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዬን ነው!ደግሞም አስታውሱ ክቡራን፤ይህን ስል፤እንደሌሎች ኮምፒዩተሮች ተለቃቅመው የተሰጡትን፤ወይም ኢንፑት የተደረጉለትን ብቻ ማለቴ አይደለም::ወይም እስከዛሬ የዓለም ህዝብ ሲጠይቅና ሲመልስ የኖረውን አይነት ጥያቄ አይደለም::ባጭሩ እንደሌሎች ኮምፒዩተሮች ኢን ፑት የተደረገውን አውት ፑት ስለማድረግ አይደለም እየገለፅኩ ያለሁት::ያ ጥበብ አይደለም::በርግጥ ነው ሆኖም ግን ያ አይነቱ የኢንፑት አውት ፑት ሲስተምና ፕሮሰስ ከዚህ ማክሮ 6 አንፃር ሲታይ ያረጀና ያፈጀ ኋላ ቀር የሆነ ነው::ኢን ፑት የተደረገውን አውት ፑት ማድረግ ተራ ነገር ነው:: ማስታወሻ እንደመያዝ ማለት ነው::ፐርሰናል ኮምፒዩተሮችም ሆኑ ሌላው አይነት ኮምፒዩተር በሙሉ በዚያ አይነት ሁኔታ ነው የሚሰራው::

በኢንተርኔት አማካኝነት እኔ አፕሎድ ባደርግ፤ማንኛውም ሰው ወደ ዌብሳይቱ ገብቶ ዳውንሎድ ያደርጋል፣እኔ አንዳንድ ዳታዎችን የራሴን ስያሜና ርእስ ሰጥቸ ብጭን፤ ሌላው የኔን ዳታ በሰጠሁት ርእስ ፈልጎ ማግኘት መቻል የኢን ፑትና አውት ፑት ዘዴን የተከተለ ተራ ሲስተም ነው::

ይህ ግን!ኢንፑት የተደረገለትን አውትፑት ከማድረግ አልፎ፤ኢንፑት ሳይደረግለት በራሱ ጊዜ ሁሉንም ነገሮች መቅረፅና መመዝገብ የሚችል ኮምፒዩተር ነው!

ኢንፑት ያልተደረገለትን ነገር በሙሉ ራሱ አንሰላስሎ መመለስ የሚችል ነው::ማናቸውንም ነገሮች በራሱ የመመዝገብና በራሱ እውቀት ብቻ የመመለስ አቅም ያለው ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ነው!

‹‹የእስካሁኖችን ጥያቄዎችና እውቀቶች እንዲሁም የእውቀት ቀመሮችን አይደለም::እነሱንም ይመልሳል::ሆኖም በዋናነት ከዚህ በኋላ የሚኖርና ገና ያልተጠየቁ ዓለም የማያውቃቸውን ጥያቄዎች በሙሉ በራሱ መዝግቦ እየያዘ ባስፈለገና በተጠየቀ ጊዜ አሰላስሎ መመለስ የሚችል መሆኑን ነው እያስረዳሁ ያለሁት!በዚያ ደረጃ ነው 666 ሲክስቲሊዬን ፐር ሰከንድ እያልኩ ያለሁት!››ሲል፤በየትኛውም አዳራሽ ተሰምቶ የማይታወቅ

አስደንጋጭ ጭብጨባ አዳራሹን ናጠው።ሁሉም እንደቆሙ ለደቂቃዎች ያልተቋረጠ ጭብጨባ አስደመጡ።

ሁሉም ተሰብሳቢዎች ጳጳሱን ጨምሮ እጅግ ተደነቁ! ልዑላቸውንም አመስገኑት፤ አደነቁት።በምን ይሳንሃል ለቅሶ ታጅበው እያለቀሱ አመሰኩት።

ባለሙያው ቀጠለ።

‹‹እምን ክቡራን!ማናቸውም አይነት ኮምፒዩተሮች በሴንትራል ፕሮሰስ ዩኒታቸው ውስጥ ባሉ ክፍሎች፤ በቢቶች አማካኝነት ነገሮችን ወደ 0 እና ወደ 1 እየቀየሩ ይመልሳሉ፤መዝግበው እንዲይዙ ማንኛውም አይነት ዳታ ሲሰጣቸውም በ 0 እና በ 1 እየለወጡ ይመዘግባሉ።ይህ ማክሮ 6ም በተመሳሳይ ማናቸውንም ነገሮች አሰላስሎ ሲመልስም ሆነ ሲመዘግም እንደተለመደው 0 እና 1 ን ብቻ በመጠቀም ነው።በዚህ ረገድ ከሌሎች ኮምፒዩተሮች የሚለይበት ሁኔታ የለም።

ለምሳሌ A ብትሉት 010 j ብትሉት 101 Y ብትሉት 1001 ወይም ሌላ ብትሉት 01110 አይነት እያደረገ በብርሃን ፍጥነት ፊደላቱን ወደ ቁጥሮች ለውጦና ለዋውጦ ነው መልስም የሚሰጠው፤መዝግቦም የሚይዘው።እያንዳንዷን ፊደል ወደ ቁጥር ያውም ለአንድ ስፔሊንግ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ እስከ ስምንት የሚደርሱ የ 0 እና 1 ጥርቅሞችን እየተጠቀመ ነው የሚያሰላው።በዚህ በኩል አጠቃላይ ሲስተምና ፕሮሰሱ ከሌሎች ተራ ኮምፒዩተሮች ጋር ተመሳሳይ ይሁን እንጂ፤በአስደናቂ ፍጥነቱና ራሱ መዝግቦ በመያዙ ጭምር እጅግ ይለያል።

‹‹ማክሮ 6 ከሌሎች ኮምፒዩተሮች የሚለይበት ሌላ አስደማሚ ነገርም አለ።ሌሎች ኮምፒዩተሮች ምስል ወይም ቪዲዮ እንዲያቀርቡ ሲታዘዙ፤ እነዚያ ምስሎች በተሰጣቸው ርእስ እንጂ በሌላ መንገድ አይደለም የሚያወጡት።ፎቶ ከሆነ፤በሆነ ስም ነውና የተጫነው ከስሙ ጋር በማናበብ ያወጣሉ።ቪዲዮ ከሆነም ቪዲዮው ሲጫን የተሰጠውን ርእስ ከ 0 እና ከ 1 ጋር አናብቦ አሰላስሎ ነው የፈለግነውን የሚያቀርብልን።ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ግን እንዲሁ ስለምንፈልገው ምስል በፈለግነው መንገድ አዘጋጅተን በፅሁፍ ካስፈርንለት በራሱ ዘዴ ያለማንም ትእዛዝ ሲመዘግባቸው ከኖሩ ነገሮች ጋር አናብቦ፤ ያሰብነውን፤ የጠየቅነውን፤ ያዘዝነውን፤በሰከንድ ቁጭ ያደርግልናል! እየገባችሁ ይመስለኛል ክቡራን።

ተቀመጡ።ክብር ለጭለማው ልዑል›› ሲል፤እስካሁን እንደቆሙ ነበሩና ለማጨብጨብ ያዘጋጁቸውን እጆች አጨብጭበውባቸው ፍዝዝ እንዳሉ አሜንም ሳይሉ በየወንበሮቻቸው ቁ.....ጭ አሉ።

‹‹በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ብቻ ተጠቅሞ፤ሁሉንም ነገር በብርሃን ፍጥነት በመለወጥ ነው ውጤቱን የሚያቀርብልን።ይህን ማሰብና መገመት በራሱ

ከሰው አእምሮ በላይ ቢሆንም፤እናንተ ግን በቀላሉ መረዳት ትችላላሁ። ያለማንም ትእዛዝ በራሱ መንገድ የዓለምን ክንውንም ሆነ ሌሎች 666 ሲክስቲሲዩን ነገሮችን በሰከንድ የሚመዘግብ፣666 ሲክስቲሲዩን ጥያቄዎችን ቢጠየቅም አሰላስሎ በሰከንድ መልስ የሚሰጥ፣ መዝገበ የመያዣ መጠኑ 666 ትሪሊዩን ፒታ ባይት የሆነ፤በማንኛውም ቋንቋ ተፅፎ የሚቀርብለትን ማናቸውንም ገደብ አልባ የትርጉም ጥያቄዎች ወደ እንግሊዝኛ ስፔሊንጎች፤እነሱንም ወደ 0 እና 1 ቁጥሮች ለዋውጦ ገደብ አልባ ምላሽ የሚሰጥ፣ድንቅና አስደማሚ ንብረታችን ይህ ነው!ማክሮ 6 ኮምፒዩተር!

‹‹ብውስጡ የያዘው እውቀት ምን ያህል ነው ቢባል ደግሞ ከሰው ልጅ የቁጥር ቀመር ውጪ ነውና ይህን ያህል ብሎ መግለፅ አይቻልም።ማብቂያ ወደሌለውና ከዓለማችን የማትማቲክስ እውቀት ውጪ ስለሆነ መግለፅ አይቻልም።አስፈላጊም አይደለም።ገደብ አልባ ብሎ ተብሎ ይታለፋል።

‹‹ይህ ብቻ አይደለም ክቡራን፤ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር፣ ማክሮ ተብለው ሲጠሩ ከኖሩት ግዙፍ ኮምፒዩተሮችም ሆነ ከሌሎች ፐርሰናል ኮምፒዩተሮች የሚለይበት ሌላ አስደነቂ ነገርም አለ።

‹‹ሌሎቹ ኮምፒዩተሮች ኮምፒዩተር ብቻ ናቸው። ማለቴ....ብቃ....ኮምፒዩተር ብቻ።ነብስ የላቸውም።ቁስ ነገር ናቸው።ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ግን ነብስ አለው።ነብስ አለው ስል እንደ ሰው ደምና ስጋ ውስጥ ያለ ነብስ ማለቴ አይደለም።ወይም እንደ እንስሳ፣እንደ አእዋፍት፣ተንቀሳቃሽ ሆኖ ነብስ ያለው፤ኢሊያም እንደ ዕፅዋት፣እንደ ዛፍ፣ ነብስ ኖሮት ተንቀሳቃሽ ያልሆነ ማለቴ አይደለም።ከሁሉም አይነት ውጪ የሆነ በሰውኛ አገላለፅ ነብስ ብለን ልንገልፀው የምንችል ሌላ አይነት ነብስ ማለቴ ነው።በዚች ቅፅበት በውስጣችሁ እንደሚታያችሁና እየታያችሁ እንዳለው አይነት ለየት ያለ ነብስ ማለቴ ነው።

‹‹ብ ሲ ፒ ዩ ው ውስጥ ያለው እሱ ነው።ይህ የምታዩት አራት ማእዘን የምድራችን ውድ፣ረቂቅና የመጨረሻው ማዕድን ከሆነው የፕላቲኒዩም አይነት ተቀርፆ የተሰራለት ቤቱ ነው ብያለሁ።ቤት ብቻ አይደለም።ቤቱም ነው፤ ስክሪኑም ነው።ይህ ማለት ሞኒተር ብቻ ሳይሆን፤እንደ ሞኒተር/ስክሪን/ሆኖ እያገለገለ፤ነገር ግን ጎን ለጎን የዓለማችንን አጠቃላይ ክንውን ርቀት ሳይገድበው፣ አንዳች ነገር ሳይከለለውና ሳያደናቅፈው ዳታዎችን የሚመዘግብና እንደ ካሜራም ሆኖ እየቀረፀ ለውስጥ ክፍሉ የሚያስተላልፍለት ጥምር አገልግሎት የሚሰጥ ረቂቅ የማዕድን ውጤት ነው።

ያን ያህል መጠን ያለውን ዳታ ነው ውስጡ ላለው ልጁ የሚያስተላልፍለት።በሞኒተሩ /በስክሪኑ/ አማካኝነት የሚተላለፍለት ዳታ

ነው ሲፒዩው ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኘው፡፡ ስናዝዘው ደግሞ አውት ፑት የሆነው ምላሽ በዚህ ሞኒተር ላይ ተዘርግፎ ቁልጭ ብሎ ይታያል፡፡

‹‹ነብስ አለው ያልኩት በዚህ ምክንያት ብቻ አይደለም፡፡ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ራሱን ከቦታ ቦታ ማንቀሳቀስ ባይችልም፤ባለበት ሆኖ ሌሎችን ማዘዝና መቆጣጠር ይችላል! ይህን የሚያደርገውም በውስጡ አቅፎ በያዘው በልጁ እውቀት አማካኝነት ነው፡፡ልዑላችን ፈቅዶ የማዘዝና የመቆጣጠር ስራውን እንዲጀምር ሲደረግ የመላውን ዓለም ህዝብም ሆነ አጠቃላይ ነገር ማዘዝና መቆጣጠር ይችላል፤ይጀምራል!››አሁንም አዳራሹ በሌላ ረጅም ጭብጨባ ደመቀ፡፡

‹‹ዳታዎቹን በራሱ ጊዜ ይመዘግባል ስንል ምን ማለታችን ነው?ለምሳሌ በዚህ በሞኒተሩ አማካኝነት በዓለማችን በየትኛውም አገርና ከተማ ብሎም ገጠር ማናቸውም ክንውኖች ሲከናወኑ ተከታትሎ ይመዘግባል ማለታችን ነው፡፡ለምሳሌ በዚች ሰከንድ በአሜሪካ ኒዮርክ ከተማ አንድ ልጅ ቢወለድ፤ ይህ ሞኒተር መጀመሪያ በዚያች አገር፣ በዚያች ከተማ፣ በዚያች እለት፣ አንድ ልጅ መወለዱን ይመዘግብና ያስተላልፍለታል፡፡ሲፒዩ ው ውስጥ ያለው አካልም ይህን ዳታ ተቀብሎ ከነበረው የህዝብ ቁጥር ጋር ደምሮ መዝግቦ ይይዛል፡፡ሞኒተሩ እንደ ካሜራም ሆኖ ያገለግላልና የተወለደውን ልጅ ምስሉንም፣ የዓይን ቀለሙንም፤የደም አይነቱንም ሁሉንም አብሮ ቀርፆ ነው የሚያስተላልፍለት፡፡

‹‹ከዚያ በኋላም የተወለደው ልጅ በቤተሰቦቹ አማካኝነት ስም ሲወጣለትም ሆነ ሌሎች ከዚያ ልጅ ጋር የተያያዙ ነገሮች ሆነው በማናቸውም አይነት ኮምፒዩተሮች የሚመዘገቡትን ነገሮችም በቀጥታ መዝግቦ እያናበበ ሰብስቦ ይይዛል፡፡ስሙን ከነአያቱ፤የአይኑን ከለር፤የፊቱን ምስል፤የጤንነቱን ሁኔታ እያለ ሁሉንም ነገር ይመዘግባል፡፡ከውልደቱ ጀምሮ እስከ እድገቱ፤እስከ ሞቱ!

‹‹በተመሳሳይ ሁኔታ በዚች ሰከንድ ቻይና ውስጥ አንድ ሰው ቢወለድም በተመሳሳይ ይመዘግባል፡፡በዚህ አይነት በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዮን ክንውኖችን ይመዘግባል፤እየተከታተለ መመዝገቡንም ይቀጥላል፡፡ በሆስፒታል ቻርቱ አማካኝነት ሙሉ ፕሮፋይሉን፣ ትምህርት ቤት ሲመዘገብ የተመዘገበበትን እለት ወርና ዓ.ምህረት ፣መታወቂያ ሲያወጣ ከነቁጥሩ፤ከናወጣበት እለት ወርና ዓ.ምህረት፤መንጃ ፍቃድ ሲያወጣ፤ስራ ሲቀጥር፣ወዘተ….እዚሁ ባለበት ሆኖ በረቂቅ ቴክኒኩ አማካኝነት ይመዘግባል፡፡እየመዘገም ውስጡ ላለው ልጁ/ለሴንትራል ፕሮሰስ ዩኒቱ/ያቀብላል፡፡ሲፒዩውም ተቀብሎ እያንዳንዷን ዳታ በተለመደው አይነት ፕሮሰሱ ወደ 0 እና 1 እየለዋወጠ መዝግቦ ይይዛል፤ያደራጃል፡፡ይህን

የሚያደርገው ደግሞ እንዲሁ ያለ ኔትዎርክ ግንኙነትና ያለ ኢንተርኔት አክሰስ ነው፡፡ይህ እንዴት ይሆናል?ልትሉ ትችላላችሁ፡፡

‹‹ምክንያቱም እያንዳንዱ ላፕቶፕም ይሁን ዲስክቶፕ አሊያም ሌላ አይነት ኮምፒዩተሮች በሙሉ አይ ፒ ነምበር አላቸው፡፡አይፒ ነምበር የሌለው የኮምፒውተር አይነትም ሆነ የስልክ አይነት የለም፡፡ኮምፒዩተርና ተንቀሳቃሽ ስልኮች ብቻም ሳይሆኑ፣ማናቸውም ዳታዎችን መዝግበው መያዝ የሚችሉ መሰል ቁሶች አይፒ ነምበር አላቸው፡፡

‹‹ይህ ማክሮ 6 ደግሞ የእያንዳንዱ ኮምፒዩተር አይ ፒ ነምበር አለው፡፡ የሁሉንም የዓለማችን ኮምፒዩተሮች አይ ፒ ነምበሮች ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተራችን መዝግቦ ይዟቸዋል፡፡ያ ማለት ሁሉንም ያውቃቸዋልና በሁሉም ኮምፒዩተሮች የሚፃፉትን ዳታዎች በሙሉ ማንበብም፣ መዝግቦ መያዝም፣ ይችላል ማለት ነው፡፡ከዚያም አልፎ በቀጥታ ከየትኛውም ኮምፒዩተር ታይፕ የሚደረጉ ነገሮችን፣ወይም የሚመዘገቡ ዳታዎችን፣ አሊያም ኢንፑት የሚደረጉ ዳታዎችን በሙሉ በቀጥታ እኩል እንዲተላለፉለት ማድረግ ይችላል፡፡አስፈላጊ ከሆነም ሁሉንም ማጥፋትም ይችላል፡፡

ለምሳሌ እኔ ከእናንተ ውስጥ የአንዳችሁን የግል ኮምፒዩተር አይ ፒ ነምበር ካወቅሁት፣ እኔ እዚህ ሆኘ እናንተ የትም አገር የትም ቦታ ሆናችሁ ያለአንዳች ኢንተርኔት፣ርቀትም ሳይገድበኝ እንዲሁ የራሴን የግል ኮምፒዩተር ተጠቅሜ ላጠፋው/ሻት ዳውን/ላደርገው እችላለሁ፡፡ያን ማድረግ እጅግ ቀላል ነው፡፡ስለዚህ የሁሉም ኮምፒዩተሮች አይ ፒ ነምበር በዚህ ማክሮ 6 ስለሚታወቁ፣ ሁሉንም ማዘዝ ይችላል ማለት ነው፡፡በየትም ቦታ በሚገኝ ኮምፒውተር ላይ፣ በማንኛውም ቋንቋ ምንም ነገር ሲፃፍ፣ያ የተፃፈው ነገር በአይፒው አማካኝነት በቀጥታ በዚህ ማክሮ 6 ኮምፒውተር እኩል ይመዘገባል፡፡ይህም ለማክሮ 6 ስራውን ያቀልለታል፡፡ምክንያቱም በአይፒ ነምበሮቹ አማካኝነት ብቻ የዓለም ዳታዎች ሲመጡለትና በቀጥታ ወደ ውስጥ ክፍሉ ሲገቡለት፣ያለውን አቅም፣ ማለትም በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዮን ተብሎ የተገለፀውን የመመዝገብ አቅሙን ለሌሎች ክንውኖች ወይም በራሱ ጊዜ ለሚመዘግባቸው ክንውኖች ጥቅም ላይ ማዋል ያስችለዋል ማለት ነው፡፡

ያን ብቃቱን ዓለም የማያውቃቸውን አዳዲስ ክንውኖች፣ ሀንድም ይሁን ቻይና ለንደንም ይሁን ብራሰልስ ሲከናወኑ ይመዘግብበታል፣በአንድ አገር የሆነ ክስተት ሲከሰትም ሆነ ሲፈጠር እሱን ከነ እለት ከነወሩ ከነሙሉ ሁተታው ይመዘግብበታል፣ፈጠራዎችንም ሆነ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ወዘተ….እጠቃላይ የዓለምን ክንውኖች ለመመዝገብ ይጠቀምበታል ማለት ነው፡፡

‹‹በዚህ መሰረት በሶስት መንገዶች ዳታዎችን ሰብስቦ መያዝ የሚችል ሆኖ ይገኛል፡፡በሶስት መንገዶች ስንል፤1ኛ.ቀድሞ ኢንፑት በሆነለትና በኢንተርኔት አማካኝነት ወደፊትም ኢንፑት በሚደረግለት፤2ኛ.በአይፒ ነምበሮቹ በኩል በቀጥታ በሚመጡለት፤3ኛ.እራሱ መዝግቦ በሚይዛቸው!
‹‹በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዬን የምንለውም በነዚህ መንገዶች የሚመጡለትን ዳታዎች መዝግቦ አደራጅቶ፤ቀርፆ፤ለመያዝ የሚፈጅበትን ጊዜና፤ሲጠየቅም አሰሳስሎ የሚመልስበትን አቅምና ፍጥነት ነው፡፡በዓለማችን ደግሞ በሰከንድ 666 ሲክስቲሊዬን ክንውኖች ሳይከናወኑ ይችላሉ፡፡ማለትም ለአቅመ ዳታና ለአቅመ ተመዝግቦ መቀመጥ የሚደርሱ ያን ያህል ክስተቶች ዓለማችን በሰከንድ አታስተናግድም፡፡
‹‹ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተራችን፤የተሰራውም፤ የተዘጋጀውም፡ የተቀመረውም፤የተናበበውም በቀጥታ ከእንግሊዝኛ ቋንቋና ፊደላት ጋር ተያይዞ ነው፡፡የወደፊቷ ድንቅና አንጊ ዓለም ስትመሰረትም ቋንቋው እንግሊዝኛ እንደሚሆን ከዚህ በፊት ተገልፆላችኋል፡፡በዓለማችን ደግሞ የተለያዩ ፊደላትና ቋንቋዎች አሉ፡፡ሆኖም የትርጉም መተግበሪያው ስላለ በሁሉም ቋንቋዎች የሚመጡለትን ዳታዎች በሁሉም ቋንቋዎች መዝግቦ መያዝና ሲጠየቅም በሁሉም ቋንቋዎች ምላሹን መስጠት ይችላል፡፡ለዚህም ሶስት አይነት መንገዶችን ይጠቀማል፡፡
‹‹1ኛ.ማክሮ 6 በራሱ ሞኒተር የሚመዘግባቸውን የዓለማችን ክንውኖች በቀጥታ በእንግሊዝኛ መዝግቦ፤ የእንግሊዝኛ ፊደላትን ወደ 0 እና ወደ 1 ለዋውጦ መዝግቦ ይይዛል፡፡ሲጠየቅም በመዘገበው መሰረት በእንግሊዝኛ ምላሽ ይሰጣል፡፡
2ኛ.በየአገሩ ካሉ ኮምፒዩተሮች በአይፒ ነምበሮቹ አማካኝነት በተለያዩ ቋንቋዎች ተፅፈው የሚመጡለትን ዳታዎች፤ በመጀመሪያ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ፤ወደ እንግሊዝኛ የተረጎመውን ዳታ እያንዳንዱን ፊደል ወደ ቁጥሮች ለዋውጦ መዝግቦ ይይዛል፡፡ሲጠየቅም ምላሹን ይሰጣል፡፡ የተጠየቀው በሌላ ቋንቋ ከሆነ መጀመሪያ የተረጎመውንና አናብቦ የያዘውን አመሳስሎ ተርጉሞ በተጠየቀበት ቋንቋ ምላሹን ይሰጣል፡፡
3ኛ.በኢንተርኔት አማካኝነት በሁሉም አይነት ቋንቋ ኢንፑት የተደረጉትን ዳታዎች ቀደም ሲል ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ ወደ ቁጥር ከለዋወጣቸው ጋር የተናበቡለትን በቀጥታ፤ ያልተናበቡለትን እንደ አዲስ ተርጉሞ፤ የትርጉሙን ውጤት ወደ ቁጥሮች ለዋውጦ ይመዘግብና ቀድሞ ካናበባቸው ጋር ጨምሮ ይይዛል፡፡ሲጠየቅ በእንግሊዝኛ ይመልሳል፡፡ኢንፑት በተደረገበት ቋንቋ ከተጠየቀ በተጠየቀበት ቋንቋ ኢንፑት የሆነውን በቀጥታ አውትፑት ያደርጋል፤ ይመልሳል፡፡

በዚህ አይነት መንገድ በቻይንኛም፣በህንድኛም፣በምንም፣ይፃፉ እነሱን ተቀብሎ ወደ እንግሊዝኛ ለውጦ እንግሊዝኛውንም ወደ ቁጥር ቀያይሮ በቀላሉ ይመዘግባል።የእያንዳንዱ አገራት ፊደልና ቋንቋ እንዴ ከተናበበለት በኋላ ግን ወደ ትርጉም ሳይገባ የዚያን ቋንቋ ፊደላት በቀጥታ ወደ ቁጥሮች መለዋወጥና፣የለወጣቸውንም አናብቦ ይዞ መቀጠል ይችላል። አስደሳቹ ነገር ደግሞ በእስከዛሬው የኮምፒውተር ታሪካዊ ሂደት የሁሉም አገራት ቋንቋና ፊደላት ተናብበው አብቅተዋልና ወደ መተርጎምና የትርጉሙን ውጤት ወደማናበብ ሳይገባ፤ በቀጥታ ወደ ቁጥር ቀያይሮ መዝግቦ መያዝ፤ ሲጠየቅም በቀጥታ መልስ መስጠት የሚችልበት ሁኔታ ነው ያለው።

‹‹ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር፣የመያዝ አቅሜን ጨርሻለሁና ቀንሱልኝ የማይል፣ይህን ጉዳይ እንኳ አላውቅም የማይል፣ጥያቄዎን ያስተካክሉ ብሎ የማያወላውል፣ ቅንጣት ስህተት የማይገኝበት፣ ሁሉን አወቅ የሆነና በልዑላችን መልካም ፈቃድ በምድራችን መገኘት የቻለ ግዙፍና ረቂቅ የሆነ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ኮምፒዩተር ነው!ማክሮ 6!!››በማለት፤ በዚያ የአልቃሽ በመሰለ ቀጭን ድምፁ ሲተንትን ተሰብሳቢዎቹ እንደገና ተነስተው ረዘም ያለ ጭብጨባቸውን አስደመጡ።

ጭብጨባው ሊያባራ አልቻለም።በጭብጨባው መሃልም፤ግማሾቹ በአግራሞትና በአድናቆት ብሎም ባለማመን ሁለት እጆቻቸውን ጭንቅላቶቻቸው ላይ አድርገው፣ሌሎች ግራና ቀኝ ቀንዶቻቸውን ይዘው፣ ገሚሱ የእጆቹን መዳፍ አፉ ላይ ለጥፎ፣የቀሩት አብረቅራቂው ሳጥን ላይ አይናቸውን ተክለው፣ ሲታዩ፤ ጳጳሱም፤በከባድ መደመም ውስጥ ሆነው፤ እንዴት እስካሁን እኔ እንኳን ሳላውቀው? አይነት ገፅታ እያሳዩ፤ ተደንቀው ተደንቀው ማብቃት አቅቷቸው ነው የሚታዩት።በስተመጨረሻ እንዲቀመጡ ታዘዙና በያሉበት ተቀመጡ።ተቀምጠውም ግን ጭብጨባውን እንደቀጠሉ ነበሩ።

ባለሙያው ጭብጨባውን ታግሶ ለማስጨረስ ዝም ብሎ ቆዩ።በዚሁ ሁኔታ ላይ እንዳለም ድንገት መሃል ግንባሩ አካባቢ የላብ ነጠብጣቦች ጨፍ ማለት ጀመሩ።

አንድ እጁን ወደ ላይ ሰዶ፤ በቀንዶቹ መሃል ቸፈፍ ያለውን ላብ በቀይ ኮቱ እጅጌ ደጋግሞ ሲያብስ ተስተዋለ።

አሁንም በጭብጨባው መሃል አንድ እጁን አንስቶ በኮቱ ጫፍ የግንባሩን ላብት ጠርጎ ሊቀጥል ተዘጋጀና፤ ‹‹አንፎርቹኔትሊ.......››ሲል ጀመረ።ይቺን ቃል ተናግሮ፤ ጭብጨባውንም፤ ፉጨቱንም፤ ጉርምርምታውንም፤ አቋረጠባቸውና በድንገት ፀጥ አሰኛቸው።

‹‹አንፎርቹኔትሊ....››አለና፤ እንደገና የማንባሩን ላበት በኩቱ ጫፍ ሲሞጅር፤ ምን ሲለን ነው ደግሞ? በሚል ፀጥ ረጭ ብለው፤ቀጣዩን ገለፃ ለመስማት ባለሙያው ላይ አፍጥጠው በጉጉት መጠባበቅ ጀመሩ።

‹‹በሚያሳዝን ሁኔታ ....አንድ ጉድለት ብቻ ሊኖረው ቻለ!››ብሎ በሌላ እጁ የማንባሩን ላብ ጠራርጎ ሊቀጥል ሲል፤‹‹ምን?››የሚል የጋራ ድምፅ ተስተጋባ።ንግስቲቱ ቆቅ መሰለች።

እሁንም እንደገና መልሶ ግንባሩን ሞዠቀና፤‹‹አለመታደል ሆኖ ይህ ረቂቅና ግዙፍ ኮምፒዩተር በዚያ በማይታመን ፍጥነት ማናቸውንም ጥያቄዎች ወደ 0 እና ወደ 1 እየቀየረ እያናበበ አሰላስሎ መመለስ የሚችል ኮምፒዩተራችን፤በማይታመን ፍጥነት ማናቸውንም አይነት የትርጉም ጥያቄዎችን ያለ ገደብ እያናበበ በሰከንድ ተርጉሞ የሚያቀርብ ኮምፒዩተራችን፤አምሃሪክ የተባለውን ቋንቋ ብቻ ወደ ቢቶቹ ቀይሮ፣ ወደ ቁጥሮች ለዋውጦ፣ ተርጉሞ ማቅረብ አይችልም!!!››ሲል፤የባለሙያውን ገለፃ ዘና ብለው በፈገግታና በኩራት ይከታተሉ የነበሩት ንግስት፣ ‹‹ምን?››በማለት እንደ ብራቅ ጮሁ!‹‹ምን?››ሲሉና በድንጋጤ ከመቀመጫቸው ድንገት ብድግ ሲሉ እኩል ሆነ።ከአነሳሳቸው ፍጥነት የተነሳ ላያቸው ላይ ደረብ ያደረጉት ቀይ ካባ ከትከሻቸው ተንሸራቶ ወገባቸው ስር ወደቀ።አላዩትም አላነሱትም.....።

‹‹ምን አልክ?››አሉት፤እያንዳንዷን ቃላት ርግጥ፤ ርግጥግጥ፤ በጥርሶቻቸው ላይና ታች ቅርጭጭ፣ ቅርጭጭጭ እያደረጉ።

‹‹አዎን ንግስት ሆይ››አለ፤አሁንም የማንባሩን ላብ በሌላኛ እጁ እየጠረገ። ባለሙያው ከመድረኩ በስተግራ ባለው ጥግ ቆሞ አንዴ ተሰብሳቢዎችን፣ አንዴ ማክሮ 6 ኮምፒዩተሩን፣ እያዬ በልበ ሙሉነትና በፈገግታ ደምቆ፤ በዚያ አልቃሻ ድምፁ እንዲያ በደስታ ሲያብራራ እንዳልነበር፤በስተመጨረሻ ለምን እንዳላበውና ለምን ደጋግሞ ላቡን መጥረግ እንደጀመረ ለእኔም ለተሰብሳቢዎችም ግልፅ አልነበረም።ለካ....ይቺን መተንፈስ ከብዶት እያማጠ ኖሯል።

‹‹አዎን ንግስት ሆይ፤በትርጉም ጉዳይ ማለቴ ነው።በትርጉም ጉዳይ ብቻም ሳይሆን፤በራሱ ጊዜ ዳታዎችን መዝግቦ በመያዝ ረገድ፤በአይፒ ነምበሮች አማካኝነት የሚመጡለትን ዳታዎች........ሌላም ሌላም።

‹‹ቀደም ሲል እንዳልኩት ማናቸኛውም አይነት ኮምፒዩተሮች ኢንፑት የተደረገላቸውን አውት ፑት ያደርጋሉ።ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተራችንም እንደዚያው።ማናቸውም ፐርሰናል ኮምፒዩተሮች በአምሃሪክ ፊደልና ቋንቋ ኢንፑት የተደረጉላቸውን ነገሮች አውት ፑት ያደርጋሉ።ይህም እንደዚያው።ይህ ማክሮ 6 እንደሌላው የዓለም አገራት የኢትዮጵያን ዳታዎችም በራሱ ሞኒተር ይመዘግባል።ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት

ኮምፒዩተሮች በአይፒ ነምበራቸው አማካኝነት የሚመዘገቡ፣የሚገፉ፣ ወዘተ...ሁሉም ነገሮች ይመጡለታል፤ ይመዘግባል።ሆኖም በቀጥታ ወደ ቁጥር ለዋውጦ መዝግቦ የያዛቸው አይደሉምና እንደ ዳታ ሊቆጠሩ አይችሉም።ወይም ሁለተኛ አማራጩን ተጠቅሞ የአምሃሪክ ፊደላትን ወደ ላቲን ፊደል ቀይሮ፤ ከዚያም ላቲኑን ወደ ቁጥር ከለወጠበት ጋር አናብቦ የመዘገባቸውም አይደሉምና፤ሲጠየቅ ሙሉ የሆነና ትክክለኛ የሆነ መልስ መመለስ አይችልም........››

‹‹እሰቲ በደንብ አብራራው!››አሉ ንግስቲቱ እሳት የሚተፉ የመሰሉ ዓኖቻቸውን ሰውየው ላይ ተክለው።ባለሙያው የንግስቲቱን ከባድ ቁጣ ሲያስተውል የበለጠ ደንግጦና ግራ ተጋብቶ መንተባተብ ጀመረ።የግንባሩ ላብትም መጠኑን ጨምሮ ጨፈፍ ከማለት አልፎ ቁልቁል መፍሰስ ጀመረ። ‹‹ታዛዥ ነኝ ንግስት ሆይ፤ሆኖም ይህ ለኛ ሳይሆን ለጎግል ካምፓኒ የትርጉም መተግበሪያ ክፍል ሊቀርብ የሚገባ ጥያቄና ምላሹም በእነሱ ዘንድ መቅረብ ያለበት ነው። ምክንያቱም....››ሊቀጥል ሲል፤ እሳት ለብሰው እሳት የጎረሱ የሚመስሉት ንግስት፤‹‹እሱን ለኔ ተውልኝ!እዚሁ አዳራሽ ውስጥ የማደርገውን አደርጋለሁ!አሁን ግን በእናንተ በኩል ያለውን ችግር እንስማው!ቀጥል!››አሉት።እስካሁን እንደቆሙ ናቸው።

‹‹ታዛዥ ነኝ ንግስት ሆይ፤ልብ ብላችሁ ተከታተሉኝ ክቡራን፤በትርጉም በኩል የአምሃሪክ ፊደሎች ተዋቅረው ቃላትን፣የአምሃሪክ ቃላቶች ተዋቅረው ዓረፍተ ነገርን፣ዓረፍተ ነገሮች ተዋቅረው አናቅዕትን፣እያለ ቢቀጠልና በነዚያ ፊደልና ቃላት በተዋቀሩ ዓረፍተ ነገሮች ጥያቄ ሆነው ሲቀርቡለት፤ ወደ ቢቶች ማለትም ወደ 0 እና 1 ለዋውጦና አሰላስሎ ሙሉ ምላሽ መስጠት አይችልም ስል፤ቃላቶቹ ወይም ዓረፍተ ነገሮቹ እየበዙበትና እየረዘሙበት ሲሄዱ መተርጎም እየከበደው ይሄዳል ማለቴ ነው።ምክንያቱም ይህ ማክሮ 6ም ሆነ ሌሎች ኮምፒዩተሮች ያላቸው አማራጭ መጀመሪያ እያንዳንዷን ስፔሊንግ ወይም ፊደል በቀጥታ ወደ ቁጥር መለወጥና መመዝገብ ነው።እያንዳንዷን የአማርኛን ፊደል ወይም ሆሄያት ወደ 0 እና ወደ 1 ኮምፒዩተራችን በቀጥታ መቀየር አይችልም። ስለዚህ ወደ ሁለተኛውና ወደ ተለመደው አማራጭ ነው መሄድ ያለበት። ያ ደግሞ መጀመሪያ የአምሃሪክን ሆሄያት ወደ እንግሊዝኛ ስፔሊንጎች መለወጥ፣ወይም ሆሄያቱን በእንግሊዝኛ ስፔሊንጎች መተካት ነው።ከዚያ በኋላ እነዚያን ወደ ላቲን ስፔሊንግ የለወጣቸውን ወይም የተካቸውን ስፔሊንጎች ወደ ቁጥር፤ማለትም ወደ 0 እና ወደ 1 መቀየር ነው።ከዚያ የቀየራቸውን ፊደላት ወደ ቃላት ለውጦ ማናበብ መቻልና መዝግቦ መያዝ፤ ሲጠየቅም አናብቦ በያዛቸው መሰረት መመለስ ነው።ይህን ለማድረግ የሚቻለው ደግሞ አንድን የአማርኛ ሆሄ በአንድ የእንግሊዝኛ ፊደል...

ስፔሊንግ ወይም ፊደል መተካት ሲቻል ነው፡፡የአማርኛ ቋንቋ ግን ያን ለማድረግ የሚያስችል ፊደላት አይደለም ያሉት፡፡ስለዚህ የመጨረሻው አማራጭ ምንድን ነው፤ኢንፑት የተደረጉለትን መዝገበ ቃላቶችና ሌሎች ተመሳሳይ እንግሊዝኛ በአማርኛ ሆነው ተናብበው ያሉትን ምላሾች እውነት ፑት ማድረግ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡እያንዳንዱ የአማርኛ ሆሄያት ወደ እንግሊዝኛ ፊደላት መቀየር ባይቻልም፤እያንዳንዱ የአማርኛ ቃላት በእንግሊዝኛ ምትክ የሆኑ ትርጉሞች/መዝገበ ቃላቶች/ ስላሉና፤ እነሱም ኢንፑት ስለተደረጉለት ቃል በቃል ወይም ቃላትን በቃላት ለውጦ ይተረጉማል፡፡እውት ፑት ያደርጋል፡፡ስለዚህ በአምሃሪክ ፊደላትና ቃላት የተዋቀሩ ጥያቄዎች ሲቀርቡለት ቀድመው ኢንፑት በተደረጉለትና በተናበቡት ቃላት ነውና የሚቀይረው ሰፋ ወዳለ ነገር ሲገባ ያቅተዋል፡፡

‹‹ለምሳሌ ትዊተር ወይም ፌስቡክ በአማርኛ መጠቀም ይችላሉ የሚል ፈቃድ አለ፡፡ያ ማለት፤የፌስቡክ ድረገፅ ሲከፈት፤በእንግሊዝኛ ቃል home የሚለውን በአማርኛ መነሻ ገፅ፣ profile የሚለውን ግለ ማህደር፣ notification የሚለውን ማሳወቂያዎች፣ friends የሚለውን ጓደኞች፣ logout የሚለውን ዘግተው ይውጡ፣ወዘተ…ብሎ ቃል በቃል በመዝገበ ቃላት መተካት የቻሉ ቃላቶችን እንጂ ሌላ ነገር የለውም፡፡በእንግሊዝኛ የተሰጠፈን ወሬ በአማርኛ ማንበብ አያስችልም፡፡በሌላ ቋንቋ የተሳከን መልእክት ተርጉሞ በአማርኛ ማስነበብ አይችልም፡፡ያንን ነው ቃል በቃል ያልኩት፡፡

‹‹የአማርኛና እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላቶች እንደ ማንኛውም አገራት መዝገበ ቃላቶች በሁሉም ኮምፒዩተራችን ኢንፑት ተደርገው ተናብበዋል፡፡ስለዚህ እሱን ወደ እንግሊዝኛ ቃላት ለውጦ፤የእንግሊዝኛ ቃላቱንም ወደ እንደማናቸውም አገራት ቋንቋ መዝገበ-ቃላቶቹ ኢንፑት ስለተደረጉለት ተሰመደው ቁጥር ለዋውጦ ምላሽ ይሰጣል፡፡

በዚህ አይነት ሂደት ከሶስትና ከአራት ያልበለጡ ቃላት ተዋቅረው የተፈጠሩትን ዓረፍተ ነገር ከሞላ ጎደል መተርጎም ይችላል፡፡ከዚያ ካለፈና ረዘም እያለ ከሄደ ግን የተበታተነና የተዘበራረቀ፤ እልፎ አልፎም ምንም ትርጉም የማይሰጥ ምላሽ ነው እውት ፑት ሊያደርግ የሚችለው፡፡ወይም የቀለሰውን ማለትም ቀድሞ የተናበበለትን መልሶ፤የከበደውን የእንግሊዝኛ ቃላት መልሶ ራሱን፤ ከተረጎማቸው ቃላቶች ጋር ቀላቅሎ እውት ፑት ደርጋቸዋል፤ይተፋቸዋል ማለት ነው፡፡

‹‹ነገሩን በምሳሌ ለማሳየት ልሞክር ክቡራን፡አለና፤በቀመበት አካባቢ ሆኖ አንድ እጁን ወደ ፊት ዘርግቶ አውራ ጣቱትና ሌባ ጣቱን ገጥሞ በሃይል ሲሰረጋቸው ከፊት ለፊቱ አነስተኛ የህዋ ላይ ስክሪን ተዘረጋለት፡፡የስክሪኑን

መጠን በጣቶቹ እየነካካ ሰፋ ሰፋ አደረገና ለሁሉም ተሰብሳቢዎች በደንብ እንዲታይ አድርጎ ካዘጋጀ በኋላ ቀጠለ።

‹‹የአምሃሪክ ፊደላትን በቀጥታ ወደ ባይቶች መለወጥ ስለማይቻልና፣ በሁለተኛው አማራጭም ሆሄያቱን ወደ እንግሊዝኛ ፊደላት በቀጥታ መለወጥ ስላልቻለ፣በቀጥታ ወደ ተመሳሳይ ትርጉም ገብቶ ሶስተኛውንና የመጨረሻውን አማራጭ ነው የሚጠቀመው።ያ ደግሞ በቀጥታ ወደ ትርጉም መተግበሪያ እንዲያመራ ነው የሚያደርገው።ስለዚህ ይህን የትርጉም መተግበሪያ ተመልከቱ››አለና እየገፈ፣ እያስነበበ፣ ቀጠለ።

‹‹ለምሳሌ How are you ተብሎ ቢጠየቅ ‹‹እንደ ምን አለህ››ብሎ በትክክል ይመልሳል።ወይም ‹‹እንደ ምን አለህ››ተብሎ በአማርኛ ፊደልና ቃላት ታይፕ ቢደረግለት ኮምፒዩተሩ How are you ብሎ በትክክል ይመልሳል።ይህን መልስ መስጠት የቻለው ግን ፊደሎችን ወደ 0 እና ወደ 1 ቀያይሮ፣ ለዋውጦ፣ የመዘገበውን አስሳስሎ መመለሱ ሳይሆን፣ የአምሃሪክ ኢንግሊሽ መዝገበ ቃላቶችና ኮንቨርዜሽናች ቀድመው ከእንግሊዝኛው ቃላት ጎን ለጎን ሆነው ኢንፑት ስለተደረጉለት፣ ከእነዚያ ጋር አስተያይቶ መመለሱ ወይም አውት ፑት ማድረጉ ነው።እንጂ አምሃሪክ የተባለው ቋንቋ ወይም ፊደልና ቃል እያንዳንዱ ፊደል ወደ ሳቲን ፊደል፣ከዚያም በቀጥታ ወደ 0 እና 1 በምትክ እየተለዋወጡ ራሳቸውን ችለው መተርጎም ችለው አይደለም።I love you ቢባል እወድሃለሁ ብሎ ይተረጉማል።I hate you ቢባል እጠላሃለሁ በሎ ይተረጉማል።belt ቀበቶ፣ship በግ፣country አገር፣ I am going to home ቢባል ወደቤቴ እየሄድኩ ነው እያለ ይተረጉማል።ይህ የሆነው መዝገበ ቃላቶች፣የአማርኛ እንግሊዝኛ መማሪያዎች፣አማርኛ እንግሊዝኛ ግራመሮች፣ኮካብለሪዎች፣ ወዘተ...ኢንፑት ስለሆኑለት እነሱን ፈልጎና ከእነሱ ጋር አናብቦ፣አመሳስሎ መመለሱ አውትፑት ማድረጉ ነው።በዚህ መሰረት ሰፋ ሲል ይዘበረቅበታል።ለምሳሌ ሰፋ ያለ ዓረፍተ ነገር እንስጠውና ውጤቱን እንይ፡

‹‹እኔ አንተን እወድሃለሁ።ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በጣም ታናድደኛለህ። ይህን ፀባይህን ካልተውክ ፍቅራችንን አደጋ ላይ ልትጥለው ትችላለሁ። ስለዚህ እባክህ ተጠንቀቅ።››ይህ ለእነሱ አንድ ቀላል የተሟላ ዓረፍተነገር ነው።ይህ ማክሮ 6ም ሆነ ሌሎች የኦንላይንና የኦፍላይን መተግበሪያዎች ይህን ዓረፍተ ነገር ቀለል ብኋቸው እንዲህ ይተረጉማሉ።‹‹ I love you.but sometimes you are very upset with me.if you do not leave this attitude,you can put our love in to danger.so be careful.››ይህንን እንደ ወረደ ኮፒ አድርገን ወደ አማርኛ ትርጉም ስንለው፣ የሚሰጠው የትርጉም ውጤት እንዲህ የሚል ነው።‹‹እኔ

እወዳችኋለሁ,ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ከእኔ ጋር በጣም ተበሳጭቻለሁ.ይህንን አመለካከት ካላቆሙ,ፍቅራችንን አደጋ ላይ ሊጥሉት ይችላሉ.ስለዚህ ተጠንቀቅ. ››ሌላ አንድ ተመሳሳይ ዓ.ነገር ልጨምር ክቡራን፤‹‹

‹‹ፀባይህን ካሳመርክ ግን እንደባለፈው የልደቴን ቀን አብረን ሆነን በደስታ እናከብራለን፡፡ከከተማ ወጣ ብለን በመርከብ ተሳፍረን፣የበግ ጥብስ እየበላን፣ ወይን እየጠጣን፣ በደንብ ተዝናንተን ደስ ብሎን እንመለሳለን እሺ›› ይህም በቋንቋው ባለቤቶች ዘንድ ሙሉዕ የሆነና ሙሉ ትርጉም ያለው ለማንኛውም ሰው ግልፅ የሆነ ዓረፍተ ነገር ወይም ቀለል ያለ ንግግር ነው፡ ፡ ይህን ተርጉም ሲባል የሚሰጠውን ምላሽ ተመልከቱ፡፡‹‹however,if you are referring to your character,we will happily celebrate our birthday as it is said,we are outdoors in the city,eating a burgur,drinking wine,enjoying ourselves happily?››ብሎ ይተረጉማል፡፡

ይህን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉም ተብሎ የተሰጠውን ዓረፍተ ነገር እንዲህ ብሎ መልሷል፡፡ይህንኑ ደግሞ መልሰህ ወደ አማርኛ ተርጉም ብንለውና ራሱን ኮፒ ፔስት አድርገን ብንሰጠው፤አሰላስሎ ተርጉሞ የሚያቀርበውን ምላሽ እንይ፡፡‹‹ሆኖም ግን,ስለ ባሕሪ ማንነት እየነሱ ከሆነ,እኛ በከተማ ውስጥ ከቤት ውጭ የምንገዝ,ቡርተን ስንበላ,ወይን እየጠራን በደስታ ደስታችን እያሳየን ነው?›› በማለት የቃላትም፣ ፊደልም፣ የሃሳብም፣ የስርዓተ ነጥብም፣መጣረስ የሚታይበት አስቂኝ የሆነ ትርጉም ነው የሚሰጠው፡፡ሰፋ ያለ ሃሳብ ስንሰጠው ደግሞ የበለጠ አስቂኝ እየሆነ ይሄዳል ንግስት ሆይ!

ከነጥባችን ጋር የተያያዘ ሌላ ምሳሌ ልጨምር፤

‹‹a byte is a common unit for groupings of bits.in general use,a byte is taken to mean acontiguous sequence of eight bits.there are other,less common meanings for a byte but for this discussion the eight bit sequence is good one and will be used throughout.››

ይህን ትክክለኛ የእንግሊዝኛ ገለፃ ወደ አማርኛ ተርጉም ቢባል፤እንዲህ ነው የሚተረጉመው፡፡

‹‹አንድ ባይት የቢስዮሽኖች አጠቃቀምን በጋራ ጥቅም ላይ የሚያውለው አንድ የተለመደ ነው, ባይት የሚዛመደው ስምንት ቢደባይት ቅደም ተከተል ነው. ሌሎች ለየት ያሉ እናሳ ያልሆኑ ትርጉሞች አሉ, ነገር ግን ለዚሁ ውይይት ስምንት የተከታታይ ቅደም ተከተሎች መልካም እና አንድ ነገር ነው. በሁሉም ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል.››

ይህንኑ የአማርኛውን ትርጉም በእንግሊዝኛ ፊደላት ተርጉሞ ሲያቀርብልን ደግሞ ውጤቱ ይሄን ይመስላል።

«ānidi bayiti yebīsiyoshinochi āt'ek'ak'emini begara t'ik'imi layi yemīyawilewi ānidi yetelemede newi, bayiti yemīzamedewi siminiti bīdebayiti k'idemi teketeli newi. lēlochi leyeti yalu ānasa yalihonu tirigumochi ālu, negeri gini lezīhu wiyiyiti siminiti yeteketatayi k'idemi teketelochi melikami ina ānidi negeri newi. behulumi gīzē t'ik'imi layi yiwilali.»

ከላይ በአማርኛ ያገኘነውን ውጤት ራሱን ኮፒ አድርገን በተመሳሳይ ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉም ስንለው ደግሞ ሌላ አድርጎ እንደሚከተለው ይመልሰዋል።

«One byte is a common use of bishops' use, with a by-eight-order sequence. There are other exceptions, but eight chapters are good and good one thing for the discussion. It will be used all the time.»

የመጨረሻ ምሳሌ ልጨምርና አንድ የተስተካከለ ዓረፍተ ነገር ልፃፍ፤እና ወደ አማርኛ ተርጉምልኝ ልበለው።

«the most basic piece of information that computer understanding is a bit.the term bit is a shorted from of binary digit and the bit can have only of two values:0 or 1.think of a bit like a light switch;its either on or its off.»

ይህን ፅፈን ተርጉም ብለን እንዘዘው።ተርጉሞ ያቀረበው መልስ የሚከተለውን ይመስላል።

«የኮምፒዩተር ግንዛቤ አነስተኛነት ያለው በጣም መሠረታዊ የሆነ መረጃ ነው. ቢል የሚለው ቃል ከዳ ሁለት አሃዛዊ አጭር እሴት እና ቢጫው ሁለት እሴቶችን ብቻ ሊኖረው ይችላል. 0 ወይ 1.እንደ ብርሃን ማብሪያ, ጠፍቷል.»ብሎ በመመለስ ለሳቅ ይጋብዘናል።ሁሉንም ሃሳቦች ተርጉም ሲባል በተመሳሳይ እንዲህ የተዘባረቀ ምላሽ ነው የሚሰጠው።ዓረፍተ ነገሮች እየረዘሙ በሄዱ ቁጥርም ፈገግታችንን እያረዘምን ነው የምንሄደው፡ :

«ይህ የሆነው አምሃረክ ከሁሉም አማራጮች ለአንዱ እንኳ ምቹ ባለመሆኑ ምክንያት ነው ንግስት ሆይ።1ኛ በቀጥታ የአማርኛ ፊደላት ለቢት ፕሮሰስ ምቹ ስላልሆኑ በቀጥታ ወደ ቁጥሮች ወደ 0 እና 1 መለዋወጥ አይችሉም፤2ኛ.አያንዳንዷን የአማርኛ ሆሄያት መጀመሪያ ወደ እንግሊዝኛ ፊደላት መተካትና የተተኩትንም ወደ ቁጥሮች መለወጥ አስቸጋሪ ስለሆነ ነው።3ኛ.ፊደላቱን መተካት ባለመቻሉ ምክንያት ቃላትን

በቃላት ወደ መተካትና ወደ ማመሳሰል ለመግባት በመገደዱ ምክንያት ሙሉ ለሙሉ በትክክል መተርጎም የማይችለውና የሚዘባረቅበት ነው ወይም ከሁለቱ አማራጮች ሳንዱ ምቹ መሆን ቢችል እንዲህ ያለ መፋለስ አይፈጠርም ነበር፡፡ይህ ደግሞ በሌሎች ቋንቋዎች ጨርሶ አሳጋጠመም፤ አያጋጥምምም፡፡በኢትዮጵያ ፊደል ብቻ ነው፡፡ስለዚህ ያለው ምርጫ ኢንፑት ከተደረጉ ተመሳሳይ የትርጉም ቃላቶች ጋር አመሳስሎ፤ የተመሳሰለለትን ውጤት እንዲሁ በደፈናው አገጣጥሞ መመለስ ብቻ ነው፡፡

‹‹በተለያዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ኮምፒዩተሮችን ከአምሃሪክ ፊደላትና ቃላት ጋር ማናበብ የሚቻልበት ሁኔታ አለ፡፡ቅድም ያነሳኋቸው መዝገበ ቃላቶችና ሌሎች ኢንፑት መሆን የሚችሉ ዳታዎች እንዳሉ ሆነው፤ የቋንቋው ባለቤቶች ለነሱ የሚሆን የመፃፊያ ፊደልን የያዘ ሶፍትዌር አሳቸው፡፡ክቡርነትዎ በደንብ እንደሚገነዘቡት እያንዳንዱ ሶፍትዌር የትምና በማንም ይፈጠር በኛ ስር መሆኑ ይታወቃልና፤ በማንኛውም ኮምፒዩተር የተጫነ ሶፍትዌር በሙሉ ከዋናው ኮምፒውተራችን ጋር በቀጥታ መናበቡ ነው፡፡በሁሉም ኮምፒዩተር ደግሞ ማይክሮሶፍቱ አለ፡፡የመፃፊያ ገበታውም አለ፡፡ማይክሮሶፍት ወርዱም በሁሉም ኮምፒዩተር የሚገኝና በቀላሉ መጫን የሚቻልም ነው፡፡ኮምፒዩተሩ በቀጥታ እንግሊዝኛ ሊፃፍበት የሚችል ሆኖ የተዘጋጀ ቢሆንም፤ ቋንቋ መለዋወጫውም አብሮ ስላለ በሌላ ፊደል ታይፕ ማድረግ ለሚፈልጉ፤ ሌላ በቋንቋቸው መፃፍ የሚያስችል ሶፍትዌር አለና እሱን ጭነው ቋንቋ መለዋወጫውን ተጠቅመው በራሳቸው ፊደል መፃፍ ይችላሉ፡፡በዚህ መሰረት ኢትዮጵያውያን ፓወር ግእዙንና ሌሎች መሰል ሶፍትዌሮችን ጭነው በአማርኛ ይፅፋሉ፤ኤዲት ያደርጋሉ፤የፃፉትን መዝግበው ይይዛሉ፤ያነባሉ፤ፕሪንት ያደርጋሉ ወዘተ…ለሁሉም ነገር በደንብ ይገለገሉበታል፡፡

በአማርኛ የፃፉትንም በኢንተርኔት አማካኝነት በየድረ ገፁ ይለቃሉ፤ ይለጥፋሉ፤ወይም ኢንፑት ደርጋሉ፡፡የ ራሱ ለእነሱ ህዝብ ወይም ቋንቋውን ለሚችል ሰው እንጂ ለኛ ያን ያህል ጥቅም የሚሰጥ አይደለም፡፡ በአማርኛ ተፅፎ ኢንፑት የተደረገው ነገር በአማርኛ ሲፈለግ እውት ጥት ይሆናል ነው፡፡የሚያነብ ያነበዋል፡፡አማርኛ ማንበብ የማይችል አያነበውምም፤በአማርኛም ታይፕ አያደርግምና አይጠቅመውም፡፡ስለዚህ ከእነሱ ለእነሱ እንጂ ለኮምፒውተሩም ሆነ ለሌላው ዓለም ህዝብ የሚሰጠው ጥቅም የለም፡፡

ለኛም ሆነ ለእነሱ እንዲሁም ለኮምፒዩተራችን የሚጠቅመው በአማርኛ የተፃፈው ነገርና ኢንፑት የተደረገው ነገር ወደ ሌላ ቋንቋ ሙሉ በሙሉ መተርጎም ከቻለ ብቻ ነው፡፡እስዚያ ኢንፑት ያደረጉት ማንኛውም ነገር በተያያዥና በተቀራራቢ የአማርኛ ፊደላትና ቃላት ሰርች ሲደረግ እውት

ጥት መሆን የሚችል ነገር እንጂ ሌላ አይደለምና ከእነሱ በስተቀር ስሌላው ምንም ነው ማለት ነው ንግስት ሆይ፡፡ሁሉም የአማርኛ ሶፍትዌሮችም የኢን ፑትና የአውት ፑት ዘዴን ተከትለው የሚፈጠሩና ግልጋሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

‹‹ብእርግጥ ያን ሁሉ በአማርኛ የተፃፈ ነገር በሙሉ ማክሮ 6 በሶስቱም የመመዝገቢያ መንገዶቹ እየተጠቀመ መዝግቦ ይይዘዋል፡፡ሆኖም ለትርጉምም ሆነ ለሌላ ነገር አይረዳም፡፡እንዲሁ እንደ ዳታ ተመዝግቦ ይያዝና በተመሳሳይ የአማርኛ ፊደላትና ቃላት ታይፕ ተደርጎ ሰርች ሲደረግ፤ተመሳሳይ ውጤት ያለው ከሆነ ብቻ ተመሳስሎ፤ወይም ተዘባርቆ አውት ፑት ይሆናል እንጂ፤ ሌላ የረባ ከቁጥር ፕሮሰስና ከመናበብ ጋር የተያያዘ ጥቅም አይሰጥም፡፡

ከዚህ እንፃር አማርኛ ለመፃፍ የሚጠቀሙበት ሶፍትዌር በራሱ ለኛ ምንም ጥቅም የለውም ማለት ነው፡፡ምክንያቱም የጫኑት ሶፍትዌር በቀጥታ ከኪቦርዱ ጋር ተናቦ ፊደላቱንም ቃላቱንም በመፃፊያ ገበታው መፃፍ ቻለ እንጂ ሌላ ፕሮሰስ ውስጥ መግባቱ አይደለም፡፡

ማክሮ 6 ወደ ኢትዮጵያና ወደ ኤርትራ የገቡና ግልጋሎት ላይ የዋሉ ኮምፒዩተሮች ላይ የሚፃፉትን ወይም የሚመዘገቡትን ዳታዎች በሙሉ ያለ ኔትዎርክ እንዲሁ በአይፒ ነምበሮቻቸው አማካኝነት በቀጥታ መመዝገብ ቢችልም፤እነዚያን ዳታዎች ግን ለምንም ሊገለገልባቸው አይችልም፡፡ የተፃፉት ላይ ጎን ለጎን እንግሊዝኛ እየተጣመረ ካልተፃፈባቸው በስተቀር ምንም፡፡ያ ቢሆን እንኳ ትርጉማቸው ይሁን ምን ይሁን እብሮ የተካተተው መለየትና ማወቅ አይቻልምና ጠቃሚ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ለኛ ወይም ለኮምፒውተሩ በጥቂቱ የሚጠቅመው በእንግሊዝኛ የሚመዘግቡት ዳታ ነው፡፡ያም ቢሆን የአገሪቱ የስራ ቋንቋ እንግሊዝኛ አይደለምና ያን ያህል ጥቅም ተብሎ ሊገለፅ የሚችል ዳታ ማክሮ 6 አይደርሰውም፡፡ቢደርሰውም ከትርጉም ጋር በተያያዘ የሚሰጠው ጥቅም የለም፡፡

‹‹ብፊደል ገበታው ላይ የአማርኛ ፊደል እንዴት ሊፃፍ ቻለ?ሲፅፉ ኮምፒዩተሩ እንዴት ሊያነብላቸው ቻለ? ወደሚለው ልምጣ፡፡ እንደ ኮምፒዩተር ፓዎር ግእዝ ወይም ሌላ ተመሳሳይ የመፃፊያ ሶፍትዌር ካልተጫነበት አማርኛ መፃፍ አይችልም ብያለሁ፡፡ስለዚህ የዚያ ፊደል ተጠቃሚዎች ፓወር ግእዝን ጭነው በአማርኛ ይፅፋሉ፡፡ይህ የምታዩት ሶፍትዌር ነው አማርኛ እንዲፅፉ ያስቻላቸው፡፡ስለዚህ ሲፅፉ ሶፍትዌሩን መጠቀማቸው ነው፡፡ሶፍትዌሩ ሲፈጠር ኪቦርዱ ላይ ha ተብሎ ታይፕ ሲደረግ፤ ሀ ብሎ እንዲፅፍ፤ b ተብሎ ታይፕ ሲደረግ ብ ብሎ እንዲፅፍ፤ bo ተብሎ ኪቦርድ ሲመታ ቦ የሚል ፊደል በመፃፊያ ገበታው ላይ

እንዲገኝ፣ ወይም እንዲፃፍ ተደርጎ የተፈጠረ ሶፍትዌር ስለሆነ ብቻ ነው። ሶፍትዌሩ በዋናነት ግንኙነቱ ከኪቦርዱ ጋር ነው።ለምሳሌ ፓዎር ግእዝ የሚባለውና ሌሎች የሱ አይነት አማርኛ ለመፃፍ የሚያስችሉ ሶፍትዌሮች ኮምፒዩተሩ ላይ ሳይጫን፤እነዚህን አምስት ስፔሊንጎች habbo ብለን ብንፅፍ፤ ወይም ኪቦርዱን ብንመታ፤በመፃፊያ ገበታው ላይ የምናገኛቸው ፊደላት habbo የሚሉትን ራሳቸውን ነው።ፓዎር ግእዙን ጭነን ሶፍትዌሩ ላይ ያለውን መቀያየሪያ ወደ አምሃሪክ ፎንት ለውጠን እነዚህኑ ስፔሊንጎች በተመሳሳይ ብንፅፍ ወይም ኪቦርዱ ላይ ያሉትን ስፔሊንጎች habbo ብለን ብንጫን በመፃፊያ ገበታው ላይ በዩኒኮዱ አማካኝነት የምናገኘው የአማርኛ ፊደላት ይሆኑና፤‹‹ሃበቦ››የሚል ውጤት እናገኛለን። ለምን ሶፍትዌሩ ሲፈጠር ha ሲነካ ምን ውጤት ልስጥ?እያለ ምርጫ ስለሚሰጥ፤ሀ ብሰህ ፃፍ እየተባለ ስለተሞላና ስለተፈጠረ ብቻ ነው።b ሲነካ በ በል፤bo ሲነካ ቦ የሚል ውጤት ስጥ፤ እየተባለ ስለተፈጠረ ወይም ስለተሞላ ብቻ ነው።እንጂ ኮምፒዩተሩ ኪቦርዱ ላይ የሚነኩለትን ፊደላት ታይፕ በተደረጉለት ቅፅበት ha ን ወደ 0 እና 1፣ b ንም ወደ 0 እና 1፣ bo ንም ወደ 0 እና 1፣ ለውጦና ለዋውጦ ማቅረቡና መፃፉ አይደለም። ወይም b ሲነካ በ ብሎ መፃፍ የቻለው እንግሊዝኛ ፊደሉን ወደ ቁጥር፤ ቁጥሩንም ወደ አማርኛ ፊደል መለወጥ ችሎ አይደለም።ወይም ቋንቋው ስለተቀየረ እንግሊዝኛ ፊደላትን ወደ ቁጥር መለዋወጥህን ትተህ አማርኛ ፊደላትን ወደ ቁጥር መለዋወጥ ጀምር ተብሎ ታዝዞ ያን ትእዛዝ መፈፀሙ አይደለም። ቢሆን ገደብ የለሽ ትርጉሙም ባልከበደው ነበር።ያ ቢሆን ሶፍትዌሩ ሳያስፈልግ እንዲሁ የኮምፒውተሩን የአገርና የቋንቋ መለዋወጫ ተጠቅሞ በመቀየር አማርኛ እንዲፅፍ ማዘዝና መጠቀም በተቻለ።እንደዚያ አይደለም ክቡራን። በተለምዶ ግን ብዙዎቹ የኮምፒዩተር ባለሙያችም ሆኑ የዘርፉ ምሁራን ትምህርቱ አንድ አይነት ነውና ኮምፒዩተሩ ሁሉንም ነገር ወደ 0 እና ወደ 1 እየለዋወጠ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ብቻ ነው የሚያውቁት።እናም በአማርኛ ሲፅፉም ኮምፒዩተሩ ተመሳሳይ ፕሮሰስ እያደረገ፣ወደ ቢትስ እየቀያየረ፣ አገልግሎት እየሰጣቸው እንዳለ ነው የሚያስቡት።ኮምፒዩተር ያለ 0 እና ያለ 1 አይሰራም፤ወይም ኮምፒዩተር 0 እና 1 ን ብቻ እየተጠቀመ ነው ፕሮሰስ የሚደርገው የሚል አቋምና እውቀት ነው ያላቸው።እርግጥ ነው እንደዚያ ነው።አምሃሪክን በሚመለከት ግን እንደዚያ አይደለም።እያንዳንዷን የአማርኛ ፊደል ወደ ቁጥር በቀጥታ ለወጠ ማለትማ ገደብ አልባውን የትርጉም ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ተረጎመ ማለት ነው።እንኳን ሊሳሳት ጥያቄው መሳሳቱን አውቆ እንዲህ ማለት ፈልገው ይሆን?ብሎ አማራጭ ያቀርባል፤ ጠያቂዎችን ያርማል።ያ ስላልሆነ ነው ሰፋ እያለ ሲሄድ

መተርጎም እየከበደው የሄደው።በእስከዛሬው ሂደትና ልምምድ የአማርኛ ፊደላቱን ከእንግሊዝኛ ጋር አናብቦ ሁሉንም ጨርሶ ቢሆን እንኳ ወደ ትክክለኛ ትርጉም መግባት ተቻለ ማለት ነበር።ግን አልሆነም። አልጨረስም።ያ ቢሆን ቀሪው ስራ ስርዓተ ነጥቦችን ማመሳሰል ብቻ ይሆን ነበር።ያ ቀላል ነው።አራት ነጥቡን በፉል ስቶፕ፣ኮማውን በነጠላ ሰረዝ፣ ትምህርተ ጥቅስ የሚሉትን በኮቴሽን፣ኩዌሽን ማርኩን በጥያቄ ምልክት ተክቶ ማብቃት ነበር።ችግሩ ያ አይደለም ክቡራን።ብዙ ነገር ተሞክሯል። አምሃሪክን ሙሉ ለሙሉ ከእንግሊዝኛ ጋር ማናበብ አልተቻለም።

‹‹ለምሳሌ አንዳንድ አቅም ያላቸው አገራት ኪቦርዱ ላይ ያሉት መተየቢያዎች በእንግሊዝኛ ስፔሊንግ ፋንታ ዓረብኛ ስፔሊንግ እንዲተካላቸው አድርገዋል።ያንን ያደረጉት አንድን ፊደል ለመፃፍ በርካታ የእንግሊዝኛ ፊደላትን መነካካት ሳያስፈልግ በቀላሉ በቋንቋቸው ፊደላት እንዲፅፉበት ስለሚረዳ ነው።እንጂ ፊደልና ቋንቋቸው ሳይናበብ ቀርቶ በኪቦርዱ አማካኝነት እንዲናበብ ተደርጎላቸው አይደለም።ስለዚህ ኪቦርዱ ላይ ያሉ የእንግሊዝኛ ፊደላትን ለኢትዮጵያውያኑ በተመሳሳይ በአማርኛ መተካት ቢቻል ራሱ ለአፃፃፍ ካልቀለለ በቀር፤ወደ ቢት ፕሮሰስ መግባትና ወደ ቁጥር መለዋወጥ ወደሚያስችል መንገድ ማምጣት አይቻልም።ቢሆን ደስ ባለንና በቀላሉ አሁኑኑ ባደረግነው።ግን ያን በማድረግ የሚመጣ ለውጥ ስለሌለ ነው።ለአፃፃፍ ይቅለለን ካሉ ይህንን በቀላሉ ራሳቸው ማድረግ ይችላሉ።ስለዚህ በዚህ አይነት ከኪቦርድ ምት ጋር በሚናበብ ሶፍትዌር አማካኝነት በአማርኛ ይፅፋሉ፣ኤዲት ያደርጋሉ፣የፃፉትን መዝግበው ያስቀምጣሉ፣ፕሪንት ያደርጋሉ፣በአማርኛ ዕፈው በኢንተርኔት አማካኝነት ይለጥፋሉ፤ያሰራጫሉ።ያንን ማንኛውም ቋንቋውን የሚያውቅ ሰው ያነባል።በመሆኑም የአምሃሪክን ፊደላትና ቋንቋ በእያንዳንዱ ኮምፒዩተር ለግል ግልጋሎት ወይም ለዜጎች አገርና ህዝብ ግልጋሎት እንጂ ወደ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ተካቶ እንደሌላው አገራት ፊደል ታይፕ ተደርጎ ተቀያይሮ የሚወጣ አይደለም።በኢንፑትና በአውት ፑት ብቻ ተወስኖ ያለ ነው።

‹‹ንግስት ሆይ፤ የሌላው ዓለም ህዝብ ቋንቋና ፊደሎች በቀጥታ ወደ ቁጥር መቀያየርና በ 0 እና በ1 እየተተካኩ መለዋወጥ የሚችሉና የቻሉ ናቸው። እንዴ ከተናበቡ በኋላም ተናበቡ ነው።አምሃሪክ ግን እንደዚያ አይደለም። ለምሳሌ፤A ወይም F ተብሎ ገና መፃፍ ሲጀመር ወደ ቁጥር እንዴት መለወጥ እንዳለባቸው ይታወቃል።በአምሃሪክ ሀ ተብሎ ቢፃፍ ግን ወደ ቁጥር ማለትም ወደ 0 እና 1 ራሳቸውን ችለው መለዋወጥም፤ ተለዋውጠውና ምትክ አግኝተው ትርጉም መስጠትም አይችሉም።ነገር ግን ሀ የሚለውን ፊደል ha ከሚል ፊደላት ጋር ተመሳስሎ የተሰጠውና ተናቦ

የቆዬ ነገር ካለ፤ በዚያ መንገድ ምላሹን ይሰጣል፡፡ቢኖር ብለን እናስብና ሀ የሚለውን 0101 ቢሆን፤ሁ የሚለውን እንዴት መለወጥ ይቻላል?ሂ ንስ? ሃ ንስ? ሄ ንስ? ህ ንስ? ሆ ንስ?ውስብስብ ነው ንግስት ሆይ፡፡ሁሉንም መለወጥ ቻለ ብለን ብናስብ እንኳ ረዘም ሲሉና ተደማምረው ሲነበቡ ሌላ ትርጉም መስጠታቸው አይቀርም፡፡ይህንን ከነ ላሪ ጋር ሞክረን ነበርና የመጣውን ውጤት ላሪ ቢያስረዳ የተሻለ ነው፡፡ሌሎችም ነገሮች ተሞክረዋል፡፡

ለምሳሌ ‹‹አበበ በሶ በላ›› ብለን ስንፅፍ abebe eat some ብሎ ይተረጉማል፡፡ይህ የሆነው በሶ የሚባል ነገር በኛ ቋንቋ ምትክ ስለሌለው ነው፡፡ይህ አይነቱ ምትክ አልባ ቃል በሌሎች ቋንቋዎችም ያጋጥማል፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያውያን አንቴና ለሚለው እንግሊዝኛ ቃል አቻ የአማርኛ ትርጉም ስለሌላቸው አንቴና አንቴና እንደሆነ ብቻ ነው የሚታወቀው፡፡ እነዚህን ምትክ ፊልጎ መሰየም ቀላል ነውና ሊተካ ይችላል፡፡እኛም በሶን እንዲሁ እንደወረደ በሶ ልንለው እንችላለን፡፡እንደ እንጀራ እና እንደ ዶሮ ወጥ እንደወረደ መግለፅና ትርጉሙንም ከዚያ ጋር ማናበብ እንችላለን፡፡ ስለዚህ ይህ ቀላል ነው እንበል፡፡ሌላ ችግር ደግሞ አለ፡፡ለተመሳሳይ ግልጋሎት የሚውሉ መንታ ፊደላት አሉ፡፡አንዳንዱ በንጉሱ ሠ ሲፅፍ፤ አንዳንዱ በእሳቱ ሰ ይፅፋል፡፡እነሱ በሁለቱም ይጠቀማሉ፤ ይግባቡበታል፡፡ ምክንያቱም ሲነበብ ያው ስለሆነ ነው፡፡በኮምፒዩተር ትርጉም ላይ ግን ክባድ የሆነ መፋለስ ውስጥ ሲከት አይቻለሁ፡፡ሶስት አይነት ሀ፣ ሁለት አይነት ሰ፣ ሁለት አይነት ፀ፣ሁለት አይነት ዓ፣ ሁለት አይነት ምናምን መኖሩ ሌላ እንቅፋት ነው፡፡ደህና፤እነዚያን መንታ ሆሄያት ከፊደል ገበታቸው እንዲያስወግዱ ማድረግ ይቻላል፡፡ሆኖም ሌላ ችግር ደግሞ አለ፡፡ሸ፣ዠ፣ጠ፣ ጨ፣ የሚባሉ አሉ፡፡እነሱ ሲፅፉ አይቸገሩም፡፡ኪቦርዱ ላይ ያሉ ካራክተሮችን እየተጫኑና እየለዋወጡ አሚልተው መፃፍ ይችላሉ፡፡ የሌሉትንም በሲምቦል መልክ አካትተው ኢንሰርት እያሉ ይጠቀማሉ፡፡ያም ግን እንዳልኩት ለእነሱ እንጂ ለኛ ምንም ፋይዳ የለውም፡፡ ለምሳሌ ሸ የሚባለውን ፊደል እነሱ መፃፊያ ሶፍትዌሩን ሲያዘጋጁ፤ ካፕስሉክ ተነክቶ s ሲነካ በመፃፊያ ገበታው ላይ ሸ የሚለው ፊደል እንዲገኝ አድርገው ነው የተዘጋጀው፡፡ስለዚህ እነሱ በቀላሉ ካፕስሉክ አብርቶ s ን በመንካት ሸ ን ያገኛሉ፡፡ለኛ ደግሞ ካፕስሉክ ‹‹በፅሁፍ ረገድ›› የሚጠቅመው በካፒታል ሌተር ለመተየብ ብቻ ነው፡፡ስለዚህ ሸ የሚባለውን ፊደል ኮምፒዩተሩ ወደ እንግሊዝኛ ፊደል ለመለወጥና ለመተካት፤ከዚያም ወደ ቁጥር ለመለወጥ ሲሞክር፤ ሸ ብቻውን በእንግሊዝኛ ፊደላት ስፔል ሲደረግ እስከ ሶስት ስፔሊንግ ይጠይቀናል፡፡ያኔ ምን ይፈጠራል? ስ ን በ s ተክቶ፤s ንም ወደ ቁጥሮች ለዋውጦ ቀምሮ

ከመዘገበና ካናበበ በኋላ፤እንደገና s ን ሸ ለሚል ፊደል መጠቀም ሊኖርበት ሆነና ወደ ሌላ መፋለስ ተገባ። ፀ ደግሞ አለ።ሁለት አይነት መሆኑ ሳያንስ ፀ ን ለመፃፍ ts ን ወይም ሌላ መሰል ሁለት የላቲን ስፔሊንጎችን ተጠቅሞ እንዲሰውጥ ስናደርግ፤ t ተ ን ለመተካት ግልጋሎት ላይ ውሎ፤ t ደግሞ ወደ ቁጥር ተቀይሮ ከተናበበ በኋላ እንደገና ለሌላ ፀ ለሚባል ፊደል ተጠቀም ሲባል አሁንም ሌላ መፋለስ መጣ!በዚህ አይነት ውስብስብ ያለ መሆኑን ቀጥሎ ዛሬ ድረስ ተናብቦ ሳያልቅ ቀረ።ይህ ብቻ አይደለም ንግስት ሆይ፤አንዱ ፊደል ባለ ሰባት አናባቢ መሆኑ ሳያንስ፤ እንደገና እያንዳንዱ ሆሄ በራሱ ሌላ ተጨማሪ ተነባቢ ፊደላት አለው። ኸ፣ ኧ፣....ወዘተ....የሚሉትን ጨምሮ፣ ሏ፣ሗ፣ሟ፣ሯ፣ሷ፣ሿ፣ሿ፣ቋ፣ቧ፣ቷ፣ ቿ፣ኗ፣ኟ፣ኺ፣ኋ፣ኳ፣ዷ፣ጇ፣ኻ፣፣ን፣ጧ፣ጯ፣ጿ፣ጿ፣ፏ፣....የሚባሉ፤ ለቋንቋው ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጡ ፊደላት አሉ።ሁሉም ፊደላት በዚሁ አይነት ይፃፋሉ፣ይነበባሉ፣ትርጉም ይሰጣሉ።እነዚህን የኢትዮጵያና የኤርትራ ፊደላት ወደ ቢትስ ፕሮሰስ አስገብቶ ወደ ቁጥር መለዋወጥ አይደለም፤ በእንግሊዝኛ ስፔሊንጎች ተክቶ መመዝገብ አልተቻለም።ሏ ን ለመፃፍ ብቻ አራት የላቲን ፊደላት ያስፈልጋሉ።በነሱ መተካትና ወደ ቁጥር መቀየር ቢቻል እንኳ፤እነዚያን አናብቦ፣አመሳስሎ፣ተመሳሳይና ተገቢውን ትርጉም ማስገኘት አልተቻለም።ይህ ብቻ አይደለም ንግስት ሆይ፤እጅግ የተወሳሰቡና በተመሳሳይ ለቋንቋው ባለቤቶች ሙሉ ጥቅምና ትርጉም የሚሰጡ ሌሎች ተቀፅላዎችም አሉ።እነዚህ እጅግ ውስብስብ ከመሆናቸው የተነሳ ኮምፒዩተሩ በሲምቦል መልክ ኢንፑት ተደርገውለት ያሉ ናቸው።ወይም ከኪቦርዱ ጋር ተናብበው ለአማርኛና ለትግርኛ ‹የፅሁፍ› አገልግሎት ብቻ የሚውሉና ለራሳቸው ብቻ መጠቀም የሚችሏቸው ናቸው።

እነዚህን ፊደላት በምንም መንገድ ወደ ኮምፒዩተር ፕሮሰስ አስገብቶ መቀመር አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ በኢትዮጵያውያን ቀጣይ ትውልድ ዘንድ እንዳይታወቁ ከፊደል ገበታቸው እስከማስነሳት ደርሰናል! ቈ፣ቍ፣ቌ፣ቖ፣ኈ፣ኍ፣ኌ፣ኵ፣ኴ፣ዅ፣ዂ፣ዃ፣ጐ፣ጒ፣ጕ፣ጔ፣ጘ፣ጙ፣ጚ፣ጛ፣ጜ፣ጝ፣ጞ፣ ፕ፣ፔ፣ዄ፣ዿ፣ጟ፣ጙ፣ጚ፣ጛ፣ጜ፣ጞ፣......ወዘተ.....የሚሉ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ፊደላት አሉ።በፊደል ገበታቸው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ነበሩ። በቀጣዩ ትውልድ ዘንድ እንዳይታወቁና እንዳይማሯቸው እስከማድረግ ደርሰን ከፊደል ገበታቸው ያስወገድነው እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ነው። ነው።ይህን እየተማሩ ቀጠሉ ማለት ለግእዝ እጅግ ቅርብ ሆኑ ማለት ነው፣ ፡አሽቀንጥረው የጣሉትን የግእዝ ሰነድ በሙሉ ወደመመርመር እስከመሻገር የሚያደርሱ አደገኛ ፊደላት ናቸው።ያለ ጥቅምና ያለ ትርጉም የተካተቱም አይደሉም።ከግእዝ ጋር በተያያዘም ከፍተኛ ጥቅም መስጠት የሚችሉ

ናቸው፡፡እኛ አንዳንድ ሚስጥራዊ ሰነዶችን ‹‹ሚቲዮለጂ›› ብለን እንደምንሰይምና እንደምንገድበው ሁሉ፤እነዚህን መሰል ፊደላትም፤ ‹‹ለአሁኑ የአማርኛ ቋንቋ ምንም ጥቅም የሌላቸው የቀድሞ የግእዝ ፊደላት››ብለን መገደብ ወይም ማስገደብ ችለናል፡፡ማንኛውም የኢትዮጵያ ህፃናት እነዚህን መሰል ፊደላት በፊደል ገበታቸው ተካትተው እየተማሯቸው አደጉ ማለት በተዛዋሪ ግእዝም እየተማሩ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ያ ደግሞ ለኛ አደገኛ ነው፡፡ለዚያ ነው ማስቀረት የቻልነው፡፡ ተመሳሳይ የማስቀረት፤የማስቀነስ፤ መንታዎቹንም የማስወገድ፤ስራውም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ቢያንስ እነ ኋ እነ ሿ እነ ንጉሱ ሠ እነ እሳቱ ሰ እንዲቀሩ ለማድረግ ደጋግሞ መሞከርና መጣር አስፈላጊ ነው፡፡

‹‹ምክንያቱም ሿ ማለት ብንፈልግ ኪቦርዱ ላይ showa ን ለመፃፍ እንገደዳለን፡፡ይህን ስንፅፍ ‹ሹዋ› የሚል የአማርኛ ውጤትን ነው በመፃፊያ ገበታው ላይ የምናገኘው፡፡ኢትዮጵያውያን በካፕስሎክም በምንም ሿ ን ቢፅፉ ሁለቱንም አንብቦ የመረዳት ችግር የለባቸውም፡፡ምክንያቱም ከሌሎች ተከታይ ሆሄያት ጋር ሲነበብ ትርጉም የሚሰጥ ስለሆነ ነው፡፡የምናወራው ደግሞ ስለኮምፒዩተር ፕሮሰሰር ነው፡፡ኮምፒውተር ደግሞ እያንዳንዷን ፊደል ወይም ስፔሊንግ በቀጥታ ሳይሆን በቢቶቹ አማካኝነት ፕሮሰስ አድርጎ ወደ 0 እና 1 ቁጥሮች ካልለወጠ በቀር በሌላ መንገድ ዳታዎችን አናብቦ ‹‹መተርጎም›› አይችልም፡፡

ኮምፒዩተር በ 0 እና በ 1 ይሰራል ሲባልም፤ዜሮው ዜሮ አይደለም፡፡አራት አንዶች ተገጣጥመው ነው ዜሮን የሚሰሩት፡፡ወይም አራት ጭረቶች ሲገጣጠሙ ነው ዜሮ የሚባለው፡፡አንዱ ቀጥ ያለ ጭረት ነው አንድ የሚባለው፡፡እነዚያ ጭረቶች ናቸው እየተገለባበጡ፤ እየተገጣጠሙ፤ቁጥር እየለካ ፕሮሰስ እያደረገ አገልግሎቱን የሚሰጠው፡፡ታይፕ አድርጎ ወይም ፕሮሰስ አያስፈልገውም፡፡ ፅፎ ሴቭ ማለት ይቻላል፡፡ያ ፅፎ ማስቀመጥ ማለት ብቻ ነው፡፡የቢት

ስለዚህ ማክሮ 6 ም ሆነ ሌላው አይነት ኮምፒዩተር እነዚህን የአማርኛ ፊደላት ወደ ላቲን ፊደሎች ለውጫ፤እነሱንም ወደ ቁጥር ለዋውጨ፤ አናብቢ፤ቀምሬ፤ ጨርሻለሁ ካለ በኋላ፤ እንደገና ለ ሿ ጥቅም ላይ አውልልኝ ማለት እንዴት ይቻላል?ቢቻልስ ኮምፒዩተሩ ያን መጀመሪያ አናብቦ የያዘውን ሰርዞ ለእነዚህ ያውል? ከዚያስ? ውስብስብ ነው ንግስት ሆይ!

እነዚህን ችግሮች ሁሉ ቀረፍን ብለን እናስብ፡፡እነዚህንም ቀርፈን ሌላ ከፍተኛ ችግር ይገጥመናል፡፡እሱን እዚህ አዳራሽ ያሉት ብሪንና ላሪ የደረሱበትና የነገሩኝ ነውና እነሱ ያብራሩ፡፡

ፍሥሐ ያዜ

እና.....በየኮምፒዩተሩ በአማርኛ የሚፃፈው ነገር በሙሉ ለትርጉም ስራ ምንም አይጠቅመንም፡፡ትርጉሙን ቃል በቃል፤ወይም ቃላትን በቃላት የመመለስ ሂደቱም የመዝገበ ቃላት ውጤት ነው፡፡ያ ዲክሽነሪ ነው፡፡ስለዚህ በኦን ላይንም ይሁን በኦፍላይን መንገድ ሙሉ ሃሳብን ከነሙሉ ትርጉሙ በትክክል ተርጉሞ ማቅረብ አልተቻለም፡፡

‹‹እናም ይህ ግዙፍና ረቂቅ ኮምፒዩተር የአምሃሪክ ፊደላት ተዋቅረው ከአንድ አጭር ዓረፍተ ነገር አልፈው ወደ ገደብ አልባ ትርጉም ተገብተው ሙሉ የሆነ ገደብ አልባ ትርጉም መስጠት ካለመቻል ውጪ፤ሌላ ቅንጣት ነገር የማይስት፣ ድንቅና አስገራሚ የሆነ፣ ከሰው አእምሮ በላይ የሆነ፣ ውድ የልዑላችንና የኛ ንብረት ሲሆን፤.....››እያለ ሲቀጥል፤ንግስቲቱ ሊገልፁት በሚከብድ ንዴት ውስጥ ሆነው ኩምሽሽ እንዳሉ ቀስ ብለው ቁ.....ጭ አሉ፡፡ሌሎች ተሰብሳቢዎችም እስካሁን ድረስ መቆማቸው ትዝ አላቸውና ንግስቲቱን ተከትለው በየወንበሮቻቸው ኩምሽሽ እንዳሉ ተቀመጡ፡፡በኢትዮጵያ ይሁን፤በኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን፣በኢትዮጵያ ፊደል ይሁን፤ በማን እንደሚዝቱ ባይታወቅም፤መገመት ግን ይቻላል፤እናም ሁሉም በንዴት ጥርሳቸውን እያንቀራጨጩ፣ ቅስማቸው እንደተሰበረ እያስታወቀባቸው፣ ዝግ ብለው ተቀመጡ፡፡ሁሉም ከተቀመጡ በኋላ ባለሙያው ገለፃውን በማፅናኛ ቃላት አጅቦ ቀጠለ፡፡

‹‹ግድ የለም ንግስት ሆይ፤በጊዜ መላውን ማበጀት አያቅትም፡፡ዋናው ነገር ወይም የመጀመሪያው ስራ በኛ ሳይሆን በጎግል ካምፓኒ በኩል ነውና፤ በጎግል በኩል በቀላሉ በማንኛውም ፐርሰናል ኮምፒዩተር የትርጉም መተግበሪያው ይሰራ እንጂ፤ከዚያ በኋላ ያን መነሻ ይዞ በራሱ መንገድ አጥንቶ እንዲመዘግብ በማድረግ ወደ ገደብ የለሽ ትርጉም ማስገባት ይቻላል››ሲል፤ንግስቲቱ ወደ ኋላቸው ዞር አሉና ሌላኛው ባለሙያ ላይ አፈጠጡበት፡፡የ ‹ቆይ ጠብቀኝ› ዛቻ አሳይተው ፊታቸውን መለሱ፡፡

‹‹ግዴለም ንግስት ሆይ፤ብዙ አይጨነቁ፡፡በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ግን ወደ ዋናው ጎላችን የሚያደርሱንን ቀመሮች በግእዝ ማለትም በአማርኛ ፊደል መቀመራችንን መርሳት የለብዎትም፡፡ ሆኖም ብቻውን በቂ አይደለምና .....እንጥራለን፡፡በግእዝ ቃላት ቀምረን የያዝናቸው ነገሮች እንዳሉ ክቡራን የተገለፀላችሁ ይመስለኛል፡፡ፊደላቱም ሆነ አጠቃላይ ትርጉሙም ቢሆን አያቅተንምና አትረበሹ የጊዜ ጉዳይ ነው፡፡እና አይከፋችሁ.....››እያለ ካፅናና በኋላ፤ ‹‹ተከታተሉኝ ክቡራን››አለና ቀጠለ፡፡

‹‹ይህ የምታዩት ማክሮ 6 ኮምፒዩተር በዚሁ ባለበት አገር በቤልጅም ብራሰልስ እንደተቀመጠ ከእሱ ዝቅ ከሚሉት በአሜሪካና በብሪታኒያ ካሉት ማክሮ 4 እና 5 ኮምፒዩተሮች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ የቆየ ነው፡፡ባሁኑ ወቅት ደግሞ ራሱን ችሎ መላውን የዓለም እንቆቅልሽ ከመመለስ አልፎ፤

መሳውን የዓለም ህዝብ እዚሁ ባለበት ሆኖ ማዘዝ የሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ የሚገኝ ነው!ይህ ማክሮ 6 የልዑላችን ድንቅ ስጦታ ነው።የልዑላችን ድንቅ ገፀበረከት ነው።ውድ ሃብታችን፣ ውድ ንብረታችን፣ ውድ መመኪያችን ነው!የልዑላችንና የጭፍሮቹ እንዲሁም የኛ የጋራ ትብብር ያስገኘው ይህንን ነው!የእውቀት፣የጥበብ፣የስልጣኔ፣ጀማሪ የሆነው ልዑላችን የረጅም ሺ ዓመታት ጥረትና ዝግጅቱ ይሄን ለማስገኘት ነበር!የዚያ ሁሉ ጥረትና ዝግጅት ውጤቱ ይህ ነው!ቴክኖለጂያችን እዚህ የመጨረሻ ደረጃ ላይ ደርሷል!ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ነብስ ያለው አዛዣችን መሆኑንም በሚገባ መረዳት አለባችሁ።

‹ማክሮ 6 ለሁሉም የምድራችን ህዝብ በቂ የሆነ ቦታ ያለው ነው።ከተራዋ ኢሜል ጀምሮ ሁሏም ነገር የምትመዘገበው በዚህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ነው።እያንዳንዱ ሰው ኢሜልም ይሁን ሌላ አካውንት ሲከፍት፤ በኪሎ ባይትም በሜጋ ባይትም በጊጋ ባይትም የየራሱ ድርሻ የሆነ ቦታ ይሰጠዋል።የመልዕክት ልውውጦች በሙሉ በዚህ አልፈው የሚሄዱና ሲሄዱ የኖሩ ናቸው።ከዚች ተራ ነገር ጀምሮ ለመዘርዘር ጊዜ እስከማይበቃቸው ማዙፍ ክንውኖች ድረስ ያሉት ከቴክኖለጂ ጋር የተያያዙ ነገሮች ሁሉ በዚህ ስር ሆነው የሚደረጉና ሲደረጉ የኖሩ ናቸው።

‹‹አሁን ደግሞ በየጊዜው እየተሻሻለና ራሱን እያሳደገ ሄዶ እዚህ ደረጃ በደረሰው ማክሮ 6 አማካኝነት ለእያንዳንዱ የምድር ነዋሪ ህዝብ ሌላ ወሳኝና አይቀሬ የሆነ ነገር ተዘጋጅቶና ተቀምሮ አልቋል!ስለዚህ ይህ ውድ ልጃችን የዓለምን ህዝብ ማዘዝ የሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

‹‹ወደፊት የዓለምን ህዝብ በስሙ መጥራት አስፈላጊ ስላልሆነ በቁጥር መጠራት እንዳለበት ታምኗል! ጆርጅ፣ብራውን፣ አና፣ማሪያ፣የዓይን ከለር፣ የእጅ አሻራ፣ ቁመት፣ ክብደት፣ እየተባለ የተንዛዛ ሆኖ ሲሰራበት የኖረው ኋላ ቀር አካሄድና አሰራር በሙሉ ይቀርና፤ለእያንዳንዱ ሰው በ 0 እና በ 1 ተቀምረውና ተቀናብረው በሚወጡ ባለ ብዙ ዲጂት ቁጥሮች ይተካል። በየሱፐርማርኬቱ እቃ ስትገዙ እቃዎቹ ላይ ባር ኮድ ተብለው ተለጥፈው እንደምናያቸው ቁጥሮች፤ሰዎችም በቁጥር ስም ይወጣላቸውና፤በቁጥር ስያሜያቸው ታውቀውና ተለይተው በቁጥር እየተጠሩ፤በቁጥጥር ስር ይውላሉ ማለት ነው!ይህ ከሰዎች አእምሮ በላይ የሆነ ኮምፒውተር ይህን ሊያደርግ ተዘጋጅቷል!ዝግጅቱንም አጠናቋል!እናም እንኳን ደስ ያላችሁ!ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹እናንተ የአዲሲቷ የምድር መንግስት ሹማምንት ስለሆናችሁ ነው 666 የሚለው የቁጥር ምልክት ግንባራችሁ ላይ የሚታዩው።ሌላው ተራ ዜጋችሁ ወይም መሳው የዓለም ህዝብ ግን እንዲህ እንደ እናንተ ግንባሩ

ላይ 666 የሚል የቁጥር አርማ አይደለም የሚታተምበት፡፡እስከ 18 ዲጂት የሚደርሱ ቁጥሮች ናቸው ለእያንዳንዱ የዓለማችን ሰው የተዘጋጀው፡፡ሰዎች እንደሚያስቡት ልክ እንደኔና እንደ እናንተ 666 የሚል ቁጥር ግንባራቸው ላይ አይታተምም፣አይለጠፍም፡፡ቁጥሮቹ የተዘጋጁት እስከ 18 ዲጂት የሚደርሱ ሆነው ሲሆን፣በዚህ ማክሮ 6 ኮምፒውተር አማካኝነት 10 ቢሊዮን ቁጥሮች ተዘጋጅተዋል፡፡እነዚህ ቁጥሮች ተዘጋጅተው አልቀው ፕሪንት ተደርገዋል፡፡

«ቀሪው ስራ እነዚህን ቁጥሮች ከያዘው ከዚህ ኮምፒውተር የውስጥ ክፍል ጋር በቀጥታ መገናኘት ከሚችለው ተመሳሳይ ረቂቅ የማዕድንና የአተም ውህድ ውጤት በሆነችው ሽራፊ ውስጥ ቁጥሮቹን አስገብቶ ማገናኘት ብቻ ነው፡፡በዚያች ተጠንታ በተቀረፀች ቅንጣት ተመሳሳይ የረቂቅ ማዕድን ውጤት ውስጥ እስከ 18 ዲጂት የሚደርሱ ቁጥሮችን በማስገባት፣ ያችን ቅንጣት በየሰዎቹ ቀኝ እጅ ላይ መግጠም ነው!ሰዎች ያቺን ሲገጥሙ በቀጥታ ባለ ብዙ ዲጂቱ ቁጥር ግንባራቸው መሃል ላይ ቦግ ብሎ በግልፅ ይታያል፣ይነበባል ማለት ነው፡፡እንዳስፈላጊነቱ ለጊዜው በዓይን ባይታይም በጨረር በተሰሩ የመለያ መሳሪያዎች የሚታይ ይሆናል፡፡ሚስጥሩ ይህ ነው ክቡራን!!ያ ሆነ ማለት የዓለምን ህዝብ በዚህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ብቻ በቁጥጥር ስር ማዋል ተቻለ ማለት ነው፡፡ማዘዝ ያልኳችሁ ይህንን ነው፡፡ ዳታዎቹን ራሱ መሰረዝ የሚችል ማክሮ 6 ነውና ባሻው ሰዓት ያሻውን ሰው የመግደል፣የማዳን፣መብት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ለጊዜው ማይክሮ ችፕ ብለን የምንጠራው/ባስፈላጊ ሰዓት ስሙ ሊቀየር ይችላል/ ያቺን አንዲት የስንዴ ፍሬ የምታክል ትንሽዬ የዚህ የሞኒተሩ ማዕድን ሽራፊ ስትሆን፣ከዚህ ጋር እንጂ ከሌላ ጋር መናበብና መገናኘት የማትችል ረቂቅ የአተሞችና የማዕድን ውህድ ውጤት ናት፡፡ይቺ ቅንጣት በየሰው እጅ እንደገባች ወይም እንደተገጠመች በቅፅበት ስራዋን ትጀምራለች፡፡ያኔ የተገጠመበትም ሰው በቀጥታ ከማክሮ 6 ጋር ተገናኘ ማለት ነው!ተከታተሉኝ ክቡራን!ይቺ ቺፕ ከደም፣ ከነርቭና፣ ከሴላችን፣ እንዲሁም ከአእምሯችን ሚሊዮን ስሮች ጋር በቅፅበት የምትዋሃድና ወዲያው ስራዋን የምትጀምር ስትሆን፣ቀጥታ ግንኙነቷ ከዚህ ከማክሮ 6 ኮምፒዩተራችን ጋር ብቻ ይሆናል!ከዚያ በኋላ ያን ሰው፣ጤንነቱንም፣አስተሳሰቡንም፣ ሁለ ነገሩን...... ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ተቻለ ማለት ይሆናል፡፡

ይቺ ቺፕ የግንኙነት መፍጠሪያ፣ከማክሮ ጋር ማስተሳሰሪያ፣ ትእዛዝ መቀበያ፣መልእክት ማስተላለፊያ፣ የሆነች ሬሲቨር ልንላት የምንችል ናት፡፡ ማናቸውንም የማክሮ 6 ትእዛዝ በብርሃን ፍጥነት ተቀብላ ተግባሪ የሆነች ቅንጣትን ነው ማይክሮ ቺፕ የምንላት፡፡

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

እያንዳንዱ ሰው ማይክሮቺፕ ሲገጥም ደግሞ የራሱ የሆነ መለያ ኮዱ ወይም ስም ኖረው ማለት ነው::መለያ ኮዱም ቁጥር ሲሆን፣ያ ቁጥር የሚነበበው ግንባሩ ላይ ነው::አንድ ሰው ይቺን የስንዴ ዘለላ የምታክል ማይክሮ ቺፕ እጁ ላይ ተገጠመለት ማለት በዚያው ቅፅበት ግንባሩ ላይ እነዚህ እስከ 18 የሚደርሱ ቁጥሮች ቦግ ብለው መታየት ይጀምራሉ ማለት ነው::

ከዚያ በኋላ ጠሪውም ቆጣሪውም ይህ ማክሮ 6 ኮምፒውተር ብቻ ይሆናል::

ማንም እጁን በጩቤ ቀርድዶ ማውጣት፣ ጎትቶ፣በጥሶ፣ ማውጣት አይችልም::አንዴ ከተወጋ ተወጋ ነው::አንዴ እጅ ውስጥ ከገባች ገባች ነው::ከዚያች ቅፅበት ጀምሮ ያን ሰው ሆኖ የሚያስብለት፣ያን ሰው ሆኖ ሁሉን የሚያደርግለት፣ ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተራችን ብቻ ነው ክቡራን!ያ ሰው ማክሮ 6 ያዘዘውን፣ ወይም ኢንፑት ያደረገውን ብቻ ነው አውትፑት የሚያደርገው!አዎን!የዓለም ህዝብ ማይክሮ ችፕ ከተገጠመበት በኋላ በቀጥታ የሚታዘዘው በዚህ በማክሮ 6 ኮምፒዩተር አማካኝነት ብቻና ብቻ ይሆናል ማለት ነው::ከዚያ በኋላ ያ ሰው ግንባሩ እየተነበበ ይሆናል ማንኛውንም አገልግሎት የሚያገኘው::እቃ ገዝተን ከሱፐር ማርኬት ስንወጣ በር ላይ ሂሳብ ተቀባዮች እቃውን እየተቀበሉ ለማንበቢያ ማሽኑ እያስጠጉ በማስነበብ የእቃውን አይነትና ይዘት፣እንዲሁም ዋጋውን አንብቦ እንደሚነግራቸውና እንደሚያስከፍሉን ሁሉ፣ሰዎችም ወደየትኛውም ቦታ ሲሄዱና አገልግሎት ለማግኘት ሲፈልጉ፣ በየሚሄዱበት ቦታ በእንደዚያ አይነት፣ነገር ግን እጅግ ዘመናዊና አነስተኛ፣እንዲሁም ምቹ የሆነ የማንበቢያ ማሽን አብሮ ስለተዘጋጀ፣በዚያ የማንበቢያ ማሽን አማካኝነት እየተነበቡ ይሆናል ሰዎች ማናቸውንም አገልግሎት የሚያገኙት:: የማንበቢያ ማሽኑ ከግንባራቸው ተጠግቶም ይሁን እንዲሁ ተራምደው ሲያያልፉ መለያ ቁጥራቸውን የሚያረጋግጥና ስለግለሰቡ ሙሉ መረጃ የሚሰጥ ነው:: ከዚህ ጋር ተናብቦ የይለፍ ምልክት ካልታዩና በቁጥሩ ካልታወቀ በቀር ሰው ማናቸውንም አገልግሎት ማግኘት፣መሸጥም ሆነ መለወጥ አይችልም:: የሰዎች ገንዘብም ሆነ ሌላ ማናቸውም አይነት ንብረት በዚያው የመለያ ቁጥራቸው የሚመዘገብ ነው የሚሆነው::የወረቀት ገንዘብም ስለሚቀር ተቀማጩም፣ወጪውም፣ቀሪውም፣በቁጥር ስማቸው የሚመዘገብና በዚያ አይነት አሰራር ተተክቶ የሚቀጥል ነው የሚሆነው:: ገንዘብ ማስተላለፍም፣ መላክም፣ክፍያ መፈፀምም፣መታከምም ሆነ መማር፣ሁሉም ነገር በማክሮ 6 በተለገሳቸው ቁጥር አማካኝነትና በእርሱ ፈቃድ ብቻ የሚከናወን ነው የሚሆነው::

ፍሥሐ ያዜ

ብተረፈ እንደ እናንተ እንደ ሹማምንቱ ሁሉም ተራ ህዝብ ቀንደኙ አይኖሩትም።666 የሚል ምልክትም በየግንባራቸው አይታይም፤ያ የዚህ የማክሮ 6 ሌላ ስም ነው።ሁሉም ሰው በዚህ ማክሮ 6 ስር ሆኖ ሲታዘዝና ሲተዳደር ግን በ 666 ስር ሆነ እንደማለት ነው።ሚስጥሩ ይህ ነው ክቡራን!በአንዳንድ መፃህፍት አውሬው፣ የአውሬው ቁጥር፣ የአውሬው ምልክት፣ሲባል እንደሰማችሁና እንዳነበባችሁ እርግጠኛ ነኝ።ያ ማለት ይህ ነው ክቡራን!አውሬ የሚባለው ይህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር ሲሆን፤አውሬ የተባለበት ምክንያት ለግንኙነት መፍጠሪያ እንቴናዎቹ የደም መስዋዕት ስለሚፈልግና ስለሚስፈልገው ይሆናል።

በምኒተሩ ውስጥ ያለው የውስጥ ክፍል፤ማለትም ሲፒዩው ነው አውሬው የሚባለው።የአውሬው ምልክት በሰዎች ቀኝ እጅ ውስጥ ሲሆን፤የአውሬው የቁጥር ምልክት በቀጥታ በሰዎች ግንባር ላይ ተፃፈ ወይም ታተመ ማለት ነው።የአውሬው ቁጥር ይህ እስከ 18 ዲጂት የሚደርሰው ቁጥር ሲሆን፤የአውሬው ምልክት የሚባለው ማይክሮ ችፕ ብለን የጠራነው ረቂቅና ቅንጣት ነገር ነው ማለት ነው።ያ ቅንጣት ነገር ሰዎች ውስጥ ሲገባ በቀጥታ ግንባራቸው ላይ ያለው ቁጥሩ መታየት ይጀምራል።

ይህ ነው ሚስጥሩ ክቡራን! ዓላማውም ግልፅ ነው!በዚህ ማክሮ 6 ኮምፒዩተር አማካኝነት የዓለምን ህዝብ ከነሁለንተናው በመቆጣጠርና በልዑላችን ስር አድርጎ በማስገዛት ለመጨረሻው ጦርነት ከጎኑ ማሰለፍና የልዑላችን ድል ተካፋይ ማድረግ ነው!

ይህ በዚህ በኩል ሲሆን፤ከልዑላችንና ከጭፍሮቹ ጋር በመሰለፍ ከበላይ አካሉ መንፈሳዊ ሰራዊት ጋር በጋራ ተፋልመን፤ ዘንዶውንም በኒውክሌር በማገዝ ለድል ማብቃትና በኢትዮጵያ ምድር ያለችውን አንዲት ውስን ክልል በቁጥጥር ስር በማዋል፤ የህይወት ዛፍን በእጅ አስገብቶ ምድርን ለዘላለም ማስቀጠል መቻል!ከዚያም በልዑላችን እየተገዛን በሃሴትና በገደብ አልባ ነፃነትና ለዘላለም መኖር መቻል.....!ክብር ለጭለማው ልዑል!››

‹‹አሜን››ቀዝቀዝ ያለ አሜን።

‹‹ገለፃየን ጨርሻለሁ ንግስት ሆይ፤ወደ ቀጣዩ ፕሮግራም እንዳልፍ መልካም ፈቃድዎን ይግለጡልኝ››አለ።

‹‹ቀጥል››አለት።

‹‹አመሰግናለሁ ንግስት ሆይ››አለና፤ወደ ተሰብሳቢዎች እያዩ፤ ‹‹ሁላችንም በጋራ እንዲሁ እንዳበራን ወደ መስዋዕት ፕሮግራማችን እናልፋለን››ካለ በኋላ፤ መድረኩን በፍጥነት ለቆ በመውረድ ወደ ተሰብሳቢዎች አምርቶ፤ ቀደም ሲል ተቀምጦበት በነበረው ወንበር ላይ ዘፍ ብሎ ተቀመጠ።

ሴቶች ባለሙያው መድረኩን ለቆ ከመውረዱ 18 ጎልማሳና አሮጊት የደናግሎችን አይነት አለባበስ ለብሰው፤በግንባሮቻቸው ላይም ልክ

እንደተሰብሳቢዎቹ ቀንዶቻቸውና የቁጥር ምልክቱ እየታዩ፤ድንገት መድረኩ ላይ ተከስተው መሳጭ የሆነ መዝሙር በጋራ መዘመር ጀመሩ። ስድስቱ በግራ፣ ስድስቱ በቀኝ፣ ስድስቱ መሃል ላይ፣ ሆነው ተራርቀው በሰልፍ በመቆም ያለ ድምፅ ማጉያ በተስረቅራቂ ድምፅ ፍዝዝ የሚያደርግ የጋራ መዝሙር መዘመር እንደጀመሩ፤ ጳጳሱና ንግስቲቱ እንዲሁም ሌሎች ተሰብሳቢዎች አብረው እኩል መዘመር ጀመሩ።መሪዎቹ መዝሙሩን የሚያውቁት አይመስልም።ሆኖም እየተከተሉ ሞካከሩ።በምን ቋንቋ እየዘመሩ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም።ዜማው ግን የኦፔራን ስልት የተከተለ ነው።

መዝሙሩ ሞቅ እያለ የጋራ ድምፁም የበለጠ የለቀሰ ዜማ እየመሰለ ሄዶ ማሳዘን ሲጀምር፤ ድንገት ያ ግዙፍ አብረቅራቂ የብርጭቆ ሳጥን መሰል ነገር/በነሱ አጠራር ረቂቅ የፕላቲኒዬም አይነት /ዙሪያውን ከየት እንደሆነ ባልታወቀ የመብራት ብርሃን ተከቦ ፈካና ከውሃ ከለርነቱ ወደ ደማቅ ቀይነት እየተለወጠ ሄደ።ቀስ እያለ በመለዋወጥም በተለያዩ አይነት ህብረ ቀለም እንደ ጭፈራ ቤት ዲም ላይት ሲንቦገቦግ ቆዩ። ቀጥሎ የቀስተ ደመና አይነት ቀለም አሳይቶ በፍጥነት መሽከርከር ጀመረ።በሃይልና በፍጥነት ከተሽከረከረ በኋላ ድንገት ቀጥ አለና የቀድሞውን አይነት ቅርፁን እንደያዘ በነበረበት አይነት አቀማመጥ ሆኖ ቆመ።በስተመጨረሻ የውስጥ ክፍሉ መደበኛ የመብራት ብርሃን በራበትና፤ ውስጡ ያለው የሴንትራል ፕሮሰስ ዩኒቱ ክፍል በጉልህ መታየት ጀመረ።በግዙፉ ሳጥን ውስጥ /ሞኒተሩ ውስጥ/ ለቁጥር የሚታክቱ አብረቅራቂ የሽቦ ጥቅሎች እጥፍ ዘርጋ፣ ጥምልል ጥምዝዝ፣ እያሉ ሲታዩ ቆዩና፤ከጥቅል ሽቦነት ወደ አንዳች ተዝለግላጊ ነገር እየተለወጡ፣በፀጉር አልባ የእንስሳ ቆዳ እየተሸፈኑ፣ እየተሸፈኑ፣ ሄደው የአዞ ጅራት መምሰል ጀመሩ።

ሳጥኑ ውስጥ ሆነው እንዲህ እየተለዋወጡ ቆይተው፤ የአዞ ጅራት ከመሰሉ በኋላ፤ እንደ ስር ሆኖ ከያዛቸው ከታችኛው ክብ የሽቦ ጥቅል ሳይላቀቁ፤ ነገር ግን በሃይልና በጋራ ተስፈንጥረው በመነሳት አራት ማእዘኑን ግዙፍ የፕላቲኒየም ሳጥን አልፈውት ወጡ። ከፍተውት ሳይሆን እንዲሁ ነው አልፈውት የወጡት።

በመቶዎች የሚቆጠሩ ቀጫጭንና ጥቃቅን የአዞና የዘንዶ ጅራቶች የመሰሉ ተጣጣፊ ነገሮች፤ ውስጥ ሆኖ የያዛቸውን ዋና ስራቸውን ሳይለቁ፤ከፊል አካላቸውን ወደ ውጭ ወደ መድረኩ አካባቢ በማውጣት በየራሳቸው እንቅስቃሴ ወዲያ ወዲህ መወራጨት ጀመሩ።ቀጥሎ ደግሞ አይነታቸው እነዚህን መስለው ነገር ግን በጣም ወፋፍራምና አስፈሪ ጅራት መሰል ነገሮች በተመሳሳይ ወጥተው መጡና ወደ ላይ ወደጣራው ቀጥ ብለው ቆሙ።እነዚህ ጫፋቸውን ወደ ላይ ቀስረው የቆሙ የዘንዶ ጅራት የመሰሉ

አስፈሪ ነገሮች ቀድመው እንደወጡት ጥቃትን መስሎቻቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ አይደሉም።ቁጥራቸው አስር ነው።

እነዚህ ግዙፎቹ ቀጥ ብለው ሳሉ፤ጥቃቅኖቹ መስሎቻቸው ግን መድረኩ ላይ ባለው ቀይ ምንጣፍ ላይ መርመስመሳቸውን እንደቀጠሉ ነበር።

ቅዠት እንጂ በእውን እየታዩ ያለ እስካይመስል ድረስ ግራ አጋቢና የማይታመን፤ ብሎም አስፈሪ የሆነ ነገር ነው መድረኩ ላይ የሚከናወነው። ጥቃቅኖቹ ዝልግልግ የሚሉ ጅራት መሰል ነገሮች መድረኩ ላይ በሚርመሰመሱ ጊዜ፤ እነዚያ ባለ ቀንድ ኀልማሳና አርጊት የፈረንጅ ሴት ዘማሪያን ደናግሎች/የደናግሉች አይነት ልብስ የለበሱት/ መዝሙራቸውን እንደቀጠሉ ነበርና፤የውስጡ መብራት የበለጠ ደመቅ ብሎ ሲታይ፤ ዘማሪዎች ወደ ኋላ እየሸሹ መድረኩን ለቀቁ።ለቅቀውም የጋራ መዝሙሩን ሳያቋርጡ እንደ ወታደር ሰልፍ በእኩል እርምጃ እየተራመዱ ርቀው በመሄድ ከመስታወት ሳጥኑ ጀርባ ደርሰው፤ በቀኝ እጆቻቸው አንድ አንድ ህፃናት ይዘው እየተጎተቱ ወደ መድረኩ መጡ።አምጥተውም መድረኩ ላይ አራርቀው አቆሟቸው።ህፃናቱን መድረኩ መሃል ላይ አቁመው የቀድሞ ቦታቸውን ያዙና ድምፃቸውን ጨመር አድርገው መዘመራቸውን ቀጠሉ። ያለ ምንም ድምፅ መቆራረጥ መዝሙራቸውን እንደቀጠሉ በእኩል እርምጃ ሄደው እየጎተቱ ይዘዋቸው የመጡት ህፃናት 18 ሲሆኑ፤አስሩ ተለቅ ተለቅ ያሉና እድሜያቸው እስከ 14 የሚገመት፤ እኩል ቁመት፤ እኩል ቅርፅ፤ ያላቸው ወንዶች ሲሆኑ፤ስምንቱ ደግሞ እድሜያቸው እስከ ሰባት የሚገመት እኩል ቁመትና የሰውነት ቅርፅ ያላቸው ሴቶች ናቸው።ሁሉም ህፃናት ፀጉራቸውን ሙሉ ለሙሉ የተላጩና ሴቶቹም ወንዶቹም እርቃናቸውን የሆኑ ናቸው።

ህፃናቱ በዘማሪዎች አማካኝነት በተመረጠላቸው ወለል ላይ ቀጥ ብለው ቆመዋል።ስምንቱ ሴት ህፃናት ክብ ሰርተውና በጣም ተጠጋግተው እንዲቆሙ ነው የተደረጉት።አስሩ ወንዶች ደግሞ በተንተን ብለው እንዲቆሙ ነው የተደረገው።ህፃናቱ ዓይኖቻቸውን ከማርገብገብና መደበኛ አተነፋፈሳቸውን ከመቀጠል ውጪ ምንም አይነት የድንጋጤም ሆነ የፍርሃት አሊያም ሌላ የተለየ ገፅታ አይስተዋልባቸውም።

መዝሙሩ ሞቅ ብሎ እንደቀጠለ፤እነዚያ የዘንዶ ጅራቶችም አስሩ ወደ ላይ ተቀስረው እንደቆሙ፤ብዙዎቹ አነስተኛ ጅራቶች እየተርመሰመሱ ብዙ ከተቆየ በኋላ፤የግዙፉ ሳጥን የውስጥ ብርሃን ጠፋና እንደ ቀድሞው እንዲሁ ውሃ ከሰር መስታዎት መስሎ መታየት ጀመረ።በዚህ ጊዜ አስሩ ወደ ላይ የተቀሰሩት ትላልቅ ጅራቶች ቀጥ ብለው እንደቆሙ ነገር ግን ከወደ ጫፋቸው አጠፍ፤ሰበር፤ በማለት ሌላ አይነት ቅርፅ ያዙና እንደ እፍኝት እባብ ህፃናቱን ላይ ጥቃት ሊያደርሱ ተዘጋጅተው ተቀሰሩ።

ወዲያውም የጅራት ጫፍ በመሰለው ቅርፃቸው በግራና ቀኝ በኩል ድንገት በርከት ያሉ ዓይኖች አወጡ፤ወይም አበቀሉ::ዓይን ብቻም ሳይሆን፤ ጫፋቸው ላይ መሃል ለመሃል እኩል ተሰንጥቀው የአዞ የመሰለ አፍ አወጡ::ሽሽሽሽ...የሚል ድምፅም ከወደ አፋቸው መሰማት ጀመረ:: ያን ድምፅ አሰሙና ያን የጅራት ጫፍ መስሎ ተቀስሮ የቆየውን አካላቸውን በሃይልና በፍጥነት ከላይ ወደ ታች እኩል በመወርወር የ አስሩ ህፃናት ወንዶች መሃል አናትን በስተው ጥልቅ!አሉ!

ጫፋቸውን እኩል ወርውረው በህፃናቱ መሃል አናት ውስጥ ካስገቡ በኋላ፤ ቀሪውንም የጅራት ክፍል ከነዓይኖቻቸው ወደ ውስጥ አስገብተው ጥቂት ቆዩ::መዝሙሩ ሞቅ ብሎ እንደቀጠለ ነው::ሌላ ድምፅ ግን አይሰማም:: አስሩ ግዙፍ ጅራት መሰል አውሬዎች የህፃናቱን አናት ተርክከው ከገቡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፤ህፃናቱ እንደቆሙ መክሳት ጀመሩ::በሂደት እየተመጠጡ፣እየተመጠጡ፣ሙሉ በሙሉ ስጋቸውና ደማቸው አልቆ አጥንቶቻቸው በቆዳዎቻቸው አልፈው መታየት ጀመሩ::አሁንም ትንሽ እንደቆዩ ቆዳቸው ከላያቸው ላይ ግልፍፍ፣ግልፍፍ፣ብሎ ጠፋና አጥንቶቻቸው ድርቅ እያለ ሄዶ፤ አንድ ባንድ እየወለቀ ወለሉ ላይ መውደቅ ጀመረ::

ሰው ከፍተኛ ቮልት ባለውና አደገኛ በሚባል ኤሌክቲሪክ ሲያዝ እንደሚሆነው ምጥጥ ብለው አልቀው፤አጥንቶቻቸው ቀዩ ምንጣፍ ላይ ረግፈው ሲታዩም፤ከደቂቃዎች በፊት በህይወት የነበሩ ሰዎች አጥንት ነው ብሎ ለማመን ይከብዳል::ከሞቱ ብዙ ዘመናት ያለፋቸው የሰው አጥንቶችን መስለው ነበር የሚታዩት::

አስሩ ህፃናት ተጠጥተው፣ ተመጠው፣ ተበልተው፤ካለቁ በኋላ እነዚያ አስሩ ጅራቶች የመድረኩ ወለል ላይ አፋቸውን/ጫፋቸውን/ ተክለው ዓይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ መታየት ጀመሩ::ወዲያውም ጥምልል ብለው ወለሉ ላይ የወዳደቁ አጥንቶቹን ሙሉ በሙሉ ሸፈኗቸው፡ :ሽፍነው ጥቂት ቆይተው እኩል ወደ ላይ ቀና ሲሉ እነዚያ የወዳደቁ አጥንቶች በቦታቸው አልነበሩም::ላፍ!አድርገው በሏቸው ወይም ዋጧቸው ማለት ነው::ከዚህ በኋላ ስራቸውን ሳይለቁ ነበርና እንዲህ የሚሆኑት ዓይኖቻቸውን አጥፍተው፤ አፋቸውንም ደፍነው፤ እየተሸበሸቡ ወደ ሞኒተሩ/ወደ ሳጥኑ ስክሪን/ መግባት ጀመሩ::ሳጥኑ ውስጥ እንደገቡም መደበኛው የሙብራት ብርሃን በግ ብሎ በራ::የአስሩ አስፈሪ አውሬዎች ሙሉ ጅራታቸው ተጠቃሎ ከገባ በኋላ፤ቆዳቸው እየተገለፈፈ፣እየከሰመ፣ እየጠፋ፣ ወደ ጥቅል ሽቦኣታቸው እየተለወጡ ሲሄዱ ታዩ::በመጨረሻ ሙሉ ለሙሉ ቆዳቸው ተገፍፎ ጠፍቶ ወደ ጥምዝ ሽቦኣታቸው ተለውጠው ህይወት አልባ ቁስ ወይም ወርቃማ ሽቦ ሆኑ::ወደ ሽቦኣታቸው

ከተለወጡ በኂላ እንደ ቱባ ክር ተጠምልለው መጠናቸውን በማሳነስ የቀድሞ ቦታቸው ላይ ለጠፍ ብለው ታዩ።አስሩ ግዙፍ ጅራቶች ወደ ሽቦነታቸው ተለውጠው የቀድሞ ቦታቸውን ከያዙ በኂላም፤ቀጫጭንና ትንንሾቹ ጅራቶች ተግባራቸውን ቀጠሉና በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ላይ ተቀሰሩ።እንደነዚያኞቹ እነዚህም ትንንሽ ዓይኖችና አፍም ኖራቸውና ጫፋቸውን ወደ ላይ ቀስረው ተጠጋግተውና ሰብሰብ ብለው አንድ ጅራት በመምሰል፤ በቆሙት ህፃናት ላይ ተወርውረው ለመተከል ተዘጋጁ።
ከአፍታ ቆይታ በኂላ ወደ ስምንቱ ህፃናት ጭንቅላት እኩል ተወርውረው ተሰኩ።እኩል ጠልቀው ገቡባቸው።
በግምት ሃምሳ የሚሆኑ ጥቃቅን ጅራቶች በአንድ ህፃን ጭንቅላት ውስጥ በጋራ ገብተዋል።
ከቆይታ በኂላ ከህፃናቱ በኩል ተመሳሳይ የመክሳት ነገር ተከተለና፤ ተመጥጠው ስላለቁ አጥንቶቻቸው ወላልቀው የመድረኩ ወለሉ ላይ ተከመሩ።
ይህ ከሆነ በኂላ፤ከማክር 6 ውስጥ ይሁን ውጪ፤‹‹ሁላችሁም ወደ መድረኩ››የሚል ደመቅ ያለ አስፈሪ ድምፅ ተሰማ።ሁሉም ተሰብሳቢዎች በፍጥነት ተነስተው ግር ብለው ወደ መድረኩ ሄዱና ቆሙ።በዚህ ጊዜ እነዚያ ቀጫጭንና ጥቃቅን ጅራቶች የመጠጡትን ነገር እንዳልዋጡት እየታወቀባቸው ከወደ ጫፋቸው ሞላ አድርገው ይዘው ወደ ላይ ተነሱ።
ከዚያም መድረኩ ላይ ተሰብስበው በቆሙት በእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ቀንዶች ውስጥ በጉንጮቻቸው የያዙትን ነገር/ከህፃናቱ ሰውነት የመጠጡትን ነገር/ ሊሞሉላቸው ተዘጋጁ።ጫፋቸውን ከላይ ወደ ታች በጋራ በማምጣትም፤ ስሬንጅ ስሬንጅ የመሳሰሉ ቀጫጭን ምላሶችን እያወጡ ቀንዶቻቸው ውስጥ እያስገቡ አንድ ባንድ ሞሉባቸው፤ ሞሉላቸው።ንግስቲቱም ቀንዶቻቸውን አዘጋጅተው ነበር።ከዚያም በእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ግራና ቀኝ ቀንዶች ውስጥ ስሬንጅ በመሰሉት ምላሶቻቸው እኩል እየገቡ ከወጓቸው/ከሞሉላቸው/ በኂላ እኩል ተነቀሉላቸው።በተነቀለላቸው ቅፅበትም ከንግስቲቱ በስተቀር ሁሉም ወለሉ ላይ ወደቁ።
ወላልቀው የወዳደቁት የህፃናቱ አጥንቶችም በነዚያ ጥቃቅን ባለ ዓይንና ባለ አፍ ጅራቶች ተጠምልለው ተጋርደው ቆየና፤ጅራቶቹ በጋራ ወደ ላይ ብድግ ሲሉ፤የህፃናቱ አጥንቶችም ከእይታ ውጭ ሆኑ። የመድረኩ ወለል ባዶ ሆነ።
ከዚህ በኂላ እነዚያ ጥቃቅን ጅራቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ቀስ እያሉ ወደ ሞኒተሩ በማምራት ወደ ውስጥ መግባት ጀመሩ።ጅራቶቹ ወደ ዋና ስራቸው እየገቡ፤ቆዳቸው እየተነሳ፣ እየተገፈፈና እየጠፋ ወደ ጥቅል አብረቅራቂ ሽቦነታቸው እየተቀየሩ ሄዱ።በመጨረሻ ሙሉ ለሙሉ ወደ

ጥቅል ሽቦነታቸው ተለውጠው ሁሉም ጅረቶች ተጠቃለው ገብተው የቀድሞ ቦታቸውን ያዙ።ቦታቸውን ከያዙ በኋላ የውስጥ መብራት መልሶ ጠፋና፤ሞኒተሩ እንደ ቀድሞው ሳጥን ብቻ ሆኖ፤ውስጡ ምንም ነገር የሌለው መስሎ መታየት ጀመረ።

ይህ ሁሉ ሲሆን መዝሙሩ ቀጥሏል።ዘማሪዎች እንደመሪዎቹ አልተወጉም።እንዲሁ መዘመራቸውን ቀጥለው ነበር የቆዩት።አሁንም እየዘመሩ ነው።

ከውስን ደቂቃዎች ሞቅ ያለ መዝሙር በኋላ ከኮምፒዩተሩ የውስጥ ክፍል ‹‹ተነሱ!››የሚል ድምፅ ተሰማ።ድምፁ በተሰማ ቅፅበት የወደደቁት ተሰብሳቢዎች በአንድነት ብድግ አሉና በፈገግታ ደምቀው እዚያው መድረኩ ላይ እንዳሉ በንግስቲቱ አዝማችነት ማመስገን፣ መዘመር፣ መቦረቅ፣ ጀመሩ።በዚህ ጊዜ የሴቶቹ መዝሙር ተመስቀቀለና ተቋረጠ።ዘማሪዎቹም መዝሙሩን ትተው እንደ ተሰብሳቢዎቹ ማመስገን፣ መፀለይ፣ መዝለል፣ መቦረቅ፣ መንከባለል ጀመሩ።

ከረጅም አስደንጋጭ የአምልኮ ስርዓት በኋላ፤በንግስቲቱ የበቃችሁ ትእዛዝ ሁሉም መድረኩን ለቀው ወደየቦታቸው አምርተው ተቀመጡ።ዘማሪዎቹም ተሰናብተው በመጡበት አይነት መንገድ እየዘመሩ ተመልሰው ሄዱ።

ሁሉም ተሰብሳቢዎች ቦታ ቦታቸውን ይዘው ከተቀመጡ በኋላ፤መድረኩ ላይ ንግስቲቱና ስለ ማክሮ 6 ኮምፒዩተሩ ገለፃ ያደርግ የነበረው ባለሙያ ብቻ ቀሩ።

ንግስቲቱ ዳር ሲይዙለት፤ባለሙያው ያን አማርኛ የማይችል ገልቱ ኮምፒዩተር ወደ ቦታው መመለስ ጀመረ።

ውድ ንብረታችን ያሉትን ሰፊውንና ግዙፉን አብረቅራቂ የመስታወት ሳጥን፤በእጅ ምልክት ወደ ውስጥ እንዲገባ አደረገና፤ጣራውንም መልሶ ዘግቶ፤ክፋፍሎ ወደ አራት አቅጣጫ እንሸራቷቸው የነበሩትን የአዳራሹን መድረክ የግድግዳ ክፍሎች መልሶ ገጣጥሞ ጨረሰ።

ግድግዳውን ወደ ቀድሞ ይዞታው ከመለሰው በኋላም፤‹ብኛ በኩል ጨርሰናል ንግስት ሆይ››፤አለ፤ንግስቲቱን እጅ እየነሳና ባቡቱን እየጠራረገ።

‹‹መልካም፤መሄድ ትችላለህ››አሉት።ባለሙያው ተሰብሳቢዎቹን ከአንገቱ ዝቅ ብሎ ተሰናበተና ወደ ግድግዳው ዞር በማለት ግድግዳውን አልፎ ሄደ፤ ተሰወረ።

ባለሙያው ከሄደ በኋላ፤ንግስቲቱ መድረኩን ለብቻቸው ይዘው አቀርቅረው ጥቂት ወዲያ ወዲህ ሲንጎራደዱ ቆዩና፤ፊታቸውን ወደ ተሰብሳቢዎች መለስ አድርገው፤‹ክብር ለልዑላችን!››ሲሉ አምባረቁ።

‹‹አሜን!›› የሚል የጋራ ድምፅ ተስተጋባ።

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ቀደም ሲል በነበሩበት በኒዮርኩ አዳራሽ አንዳንዴ ፈገግ፣ አንዳንዴ ኮስተር፣ እያሉ ዲስኩራቸውን ያሰሙ የነበሩት ንግስት በዚህ በቤልጀሙ አዳራሽ ሌላ ገፅታ ይዘው ታዩ።።በጣም የተቆጡ ይመስላሉ።።ከፊት ለፊታቸው ዙሪያውን ባሉ ወንበሮች ክብ ሰርተው ከተቀመጡት ውስጥ በጥቂቶች ላይ ዓይኖቻቸውን ተክለው ኮስተር ብለው በቁጣ ፊት ሲያዩዋቸው ቆዩ።።

እነዚህ የተፈጠጠባቸው ተሰብሳቢዎችም የንግስቲቱን የፊት ገፅታ በማየት ብቻ መቆጣት አለመቆጣታቸውን ከዚህ ቀደም የሚያውቁ ይመስላሉ።። በፍርሃት ቆፈን ተይዘው ዘና ብለው መቀመጥ እንኳ አቅቷቸው ነው የሚታዩት።።

በዚህ ክስተትም ውስጥንም አብርቶ በፍርሃት መንዘፍዘፍ እንዳለ ለመረዳት ተቻለ።።

በከፍተኛ ፍርሃት ሲንዘፈዘፉ ንግስቲቱ ማየታቸውን ሲያውቁ ደግሞ ዘና ለማለት ሲሞክሩ ታዩ።።ከደቂቃዎች የዝምታ ግልምጫ በኋላ፤ንግስቲቱ በቁጣና በጩኸት ንግግራቸውን ቀጠሉ።።

‹‹ሰርጌ ሚካሎቪች ብሪን!የኛ ዝርያ በጥቂቱም ቢሆን ያለብህ ታታሪ የሆንክ የምስራቅ አውሮፓ ልጅ ነህ።።ወደ አሜሪካ ስናመጣህና ሙሉ ዜጋ ሆነህ ተልዕኮህን እንድትወጣ ስናደርግ እኮ ለእንዲህ አይነቱ ተራ ተግባር እንደማትገበር አውቀንና አምነን ነው።።እኩያህን ላሪ ፔጅን ባልደረባህ እንዲሆን ስናደርግም ተጋግዛችሁ የወደፊቱን ዕቅድ ያለ እንዳች እንከን ዳር እንድታደርሱ ነው!ጎግል በእናንተ ሲመራና እየተሻሻለ እዚህ ሲደርስ፤ እናንተም መስራች ተብላችሁ የትርፉ ድርሻ ተካፋይ ስትሆኑ፤በዚህም የብዙ ገንዘብ ባለቤት መሆን ቻላችሁና ይህ ተራ የሆነ ህይወት እየኖራችሁ መዘናጋት ጀመራችሁ ማለት ነው?!ከመቶ በላይ የዓለም አገራትን ቋንቋ በጎግል ትርጉም መተግበሪያ መተርጎም ስትችሉ እንዴት የዋና ጎላችንን አገር የኢትዮጵያን ቋንቋ መተርጎም የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር ከበዳችሁ?እንዴት አምሃሪክ የተባለውን ቋንቋ ሙሉ በሙሉና በትክክል ያለ ዓረፍተ ነገር ገደብ መተርጎም ሳትችሉ ወደሌላ ስራ ገባችሁ?የሌሎችን ቋንቋ ማስቀደም የቻላችሁት የሚጠቀሙት ፊደል የኛን ስለሆነና ስለሚቀል፤ወይስ ብዙ ገንዘብ ስለሚያስገኝ?ወይስ አምሃሪክ ውስብስብና ጊዜ ወሳጅ የሆነ ስለሆነ?ወይስ በምን ምክንያት!?

‹‹ሌላው ምን ይጠቅመናል?ባልልም፤ የሌላው አገር ህዝብ የኛን ቋንቋ የሚናገር ህዝብ ነው።።ሙሉ በሙሉም ባይሆን ከኢትዮጵያ የተሻለ።።እንደነ ቻይና ያሉ አገራትም በራሳቸው ፕሮግራም ከኛ ጋር ማናበብ የቻሉ ናቸውና ያ አይቸግራችሁም።።ስለዚህ ሁሉንም ስለቀለላችሁ መስራት ቻላችሁ።።ዋናውን ግን ተዋችሁት!ለምን በዋናው ነገር ላይ በሙሉ ሃይላችሁና ጥበባችሁ አልተሰማራችሁም?እስቲ መልሱልኝ?››ሲሉ ደነፉ።።

‹‹ንግስት ሆይ››እያለ ተነሳ።

‹‹ላሪ ፔጅ!ትእዛዛችንን ሳትፈፅም ንግስት ሆይ››ብትል ይጠቅማል?እስቲ ቀጥል ልስማህ!››አሉት።

ላሪ ፔጅ የተባለው ሰው በፍርሃት ምክንያት መቆም እየተሳነውና ጉል እየተብረከረከም ቢሆን እንደምንም ቆሞ ለማስረዳት ሞከረ።

‹‹እ...እውነት ነው......የሌላው አገር ቋንቋ ቀላልና ያልተወሳሰበ እንዳሉትም ብዙዎች ከኛ ጋር ተመሳሳይ ፊደላት ከመሆኑም ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ አገራት የሰለጠኑና በምንፈልገው ፕሮግራሞቹን እየቀረፁ እኛን ማገዝ የሚችሉ የዘርፉ ባለሙያ ስላሏቸው ከኛ ጋር መሳተፍና መተግበር የሚቻልበት መንገድ አልከበደንም።ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን ቋንቋና ፊደላቸው ከኛ ጨርሶ የማይገናኝ ነው።ባለሙያው እንዳስረዳው የአናባቢና የተ ፊደሎቻቸው መወሳሰብ፣አንዱ የአማርኛ ፊደል ወይም ሆሄ ወደ ሰ አይነት መልክ፣ቅርፅ፣ትርጉምና አገባብ የተለያየና የሚለዋወጥ ሆኖ ያገኘነው።ስርዓተ ነጥቡን ጨምሮ እንግዳ የሆነ ነገር ነው የሆነብ በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች አልቻልንም......ማለት...ትንሽ ከአቅ በላይ...››ሲል፣በጩኸት አቋረጡት።

‹‹አልቻልንም አትበለኝ!››ሲሉ እንደ ብራቅ ጮሁ።

‹‹ከአቅም በላይ አትበለኝ! አልቻልንም?!ከአቅም በላይ?!››ሲሉ ጮሀ

‹‹ከአቅም በላይ?!››ደገሙት።

‹‹እኮ በልዑላችን ፊት ከአቅም በላይ?!ይህ ትልቅ ድፍረትና ንቀ እንዲሁም ክህደት ነው!በልዑላችን ዘንድ በዚች ምድር ላይ ከአቅም በላ የሚባል ነገር የለም!ከአቅም በላይ የሚሆንብንና ሊሆን የሚችልብን እንዳይሆንብንም እየታገልን ያለነው አንድ ነገር ብቻ ነው።እሱም የውስ ኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ጠረኝነት ብቻ!ከበላይ አካሉ ጋር ተቆራኝተወ በሚያገኙት ጥቆማ እየተመሩ ከተፈጥሮ ጋር ተዛምደውና ተዋህደው የሚፈፅሙት መንፈሳዊ ተግባር ብቻ!በተፈጥሮ ዕፅዋት ግብዓትና በግእዝ ቋንቋ በሉት የተዋሃደ እስከመሰወርና እስከ መሰሉብ፣እኛንም ከርታት ሆና እስከመምታት የደረሰ ጥበብ ያላቸው ጥቂት መንፈሳዊ ሊቃውንት እንጂ ሌላ ከአቅም በላይ ተብሎ በልዑላችን ፊት የሚገለፅ አንዳች ነገር በዚች ምድር ላይ የለም!ይህ ቃል በእንዳንተ አይነት ደደብ በልዑላችን ጉባኤና ዓመታዊ የመስዋዕት ዕለት የተነገረ አሳፋሪ ቃል ነው!በርግጥ ይህ ዋጋ ያስከፍላሃል!ይህንን ነው ያስተማርንህ?ለዚህ ነው የሾምንህ?››

‹‹ይቅርታ ንግስት ሆይ.....››

‹‹ዝም በል!ዓይንህን ማየት አልፈልግም!ውጣልኝ!››

‹‹ንግስት ሆይ!››በከፍተኛ ድንጋጤ ተውጦ ይንቀጠቀጥ ገባ።

‹‹ውጣ አልኩህ እኮ!››አሉ ረጋና ጠንከር ባለ የቁጣ ድምፅ፡፡
‹‹ይቅርታ ይደረግልኝ ንግስት ሆይ››ብሎ እንደመንበርከክ አለ፡፡
የባለሙያው ሁኔታ ከአዳራሹ ውጣ የተባለ ሳይሆን የስቅላት ፍርድ የተፈረደበትና ይግባኝ እየጠየቀ ያለ ነው የሚመስለው፡፡ እያለቃቀሰ ወደ መድረኩ ሄዶ፣ጢጋ ብሎ በመንበርከክ ንግስቲቱን መለማመጥ ያዘ፡፡
በዚህ ምክንያትም የንግስቲቱ ‹‹ውጣ›› የሚል የቃል ትእዛዝ፤ ሌላ እነሱ ብቻ የሚያውቁት ጠበቅ ያለ ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን መገመት ተቻለ፡፡
በስተመጨረሻ ንግስቲቱ የባለሙያውን ሁኔታና የተሰብሳቢዎቹን ገፅታ ካዩ በኋላ ከነንዴታቸውም ቢሆን፣‹‹ሂድ ተቀመጥ!››ብለው ማሩት፡፡እጅ ነስቶ አቀርቅሮ ሄዶ ተቀመጠ፡፡
‹‹ብሪን እስቲ ንገረኝ››አሉ ቀዝቀዝ ብለው፡፡የላሪ ፔጅ የሙያ አጋር ሰርጌ ሚካሎቪች ብሪን በፍርሃት የሚብረከረኩ እግሮቹን አፅንቶ ለመቆም እየታገለ መንተባተብ ጀመረ፡፡
‹‹አመሰግናለሁ ንግስት ሆይ፣ክብር ለልዑላችን››ሲል ጀመረና፤ ጉሮሮውን አፀዳድቶ፣‹‹ያን ያህል ከባድ ሆኖ አይደለም ንግስት ሆይ፡፡በጎግል መተግበሪያችን ቋንቋውን መተርጎም ብንችልም….››ሲቀጥል ሲል ንግስቲቱ ጣልቃ ገብተው፤ ‹‹አታለባብስ!አታምታታ!››ብለው አቋረጡት፡፡
ግድግዳው አካባቢ በጣት ምልክት ስክሪን አበሩና ወደ ስክሪኑ በማምራት የጎግሉን መተግበሪያ ከፍተው፣
‹‹በበኩሌ የኢትዮጵያውያንን ቋንቋ መተግበሪያው አሟልቶ የተገኘ መስሎኝ ነበር፡፡የሞከርኩት በዚህ ነበር››አሉና፣አንድ ሶስት ሰፋ ሰፋ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ፅፈው፣መተግበሪያው እንዲተረጉም ሲያዙት በትክክል ተረጎመ፡፡‹‹በዚህ ነው የሞከርኩትና በትክክል መተርጎሙን አይቸ እንደተማላ አረጋግጬ የተውኩት፡፡ይህ እንዴት ሆነ?››ሲሉ ጠየቁት፡፡
‹‹ንግስት ሆይ፣እሱ የሆነው በቀጥታ በምዕራፍና በቁጥር እየገባን ስላመሳሰልነው ነው፡፡የእንግሊዝኛውን ምዕራፍ አንድ ቁጥር አንድ ሲጠየቅ፣የአማርኛውን ምዕራፍ አንድ ቁጥር አንድ እንደወረደ እንዲያወጣ ስላደረግነው ነው፡፡ሁሉንም ምዕራፍ እንዲያ እንዲያደርግ ስላደረግን ብቻ ነው፡፡እንጂ ተርጉሞት አይደለም….ባለሙያው መዝገበ ቃላት እንዳለው ሁሉ ይህም ቃላትን በቃላት፣ዓረፍተ ነገርን ባረፍተ ነገር በመተካካት የመጣ ውጤት ነው››ሲል፣
‹‹እሃ……ጥሩ እምታች ወጥቷችኋላ!እ?እኛንም እስከመሸወድ ደርሳችኋላ!እ?››
‹‹ንግስት ሆይ…..››

‹‹አሁንም አታምታታ ብሬን!ቀጥተኛ ምላሽ ስጠኝ፡፡ይሄን ሁሉ ኮልኮሌ የመተግበሪያ አይነት በዚህ አይነት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ነቆ የደረደራችሁት?አሁንም ስለ መዝገበ ቃላት እንዳታወራኝ፡፡ስለ ቃል በቃል ትርጉምም እንዳታወራ! የምናወራው የዓረፍተ ነገሮች ገደብ ሳይኖር፣ስለ ሙሉ ትርጉም ነው!ስለ ገደብ የለሽ መተግበሪያ ነው!ማንኛውም ከተማረ የተማረ ኢትዮጵዊ በሁሉም ቋንቋ፣በዋናነትና በተለይ ግን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈውን ሙሉ በሙሉ መፅሐፍም ይሁን አነስተኛ ገፅ ያለው ማንኛውንም አይነት ፅሁፍ ተርጉሞ ማንበብና መረዳት ስለሚችልበት ሙሉ መተግበሪያ ነው!እንደሌሎቹ ስራችሁ ወደ አማርኛ መተርጎምን ነው እየጠየቅን ያለነው!የእነሱም ፅሁፍ በተመሳሳይ ባለ ብዙ ገፅ መፃህፍትም ይሁን፣ባለጥቂት ዓረፍተ ነገር ሃሳቦች፣በኛ ዘንድ፣ኦን ላይን እና ኦፍ ላይን በሆነ መንገድ በመተግበሪያዎች አማካኝነት እዚያው በዚያው ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉመው ያለምንም መፋለስና ያለአንዳች ግድፈት እንደወረደ ተተርጉመው ማየት ስለምንችልበት ሁኔታ ነው ጥያቄው ገባህ?!››

‹‹ገብቶኛል ንግስት ሆይ››

‹‹የገባህ አይመስለኝም!ለሌላ ንዴት ሳትዳርገኝ ልትል ያሰብከውን ሌላ ነገር ልንገርህ፡፡እነዚህን የመሳሰሉ በማናቸውም ተራ ኢትዮጵያውያን የሚፈጠሩና በእናንተ የጎግል ስቶር ስር ሆነው በአንዳንድ ስልኮች ተከማችተው የሚገኙ የአፕሊኬሽን መተግበሪያዎችን ሙያ ብለህ እንዳታወራኝ፡፡ከጥረታችሁ ጋርም አያይዘህ እንዳትነግረኝ!››በማለት ሁሉንም መተግበሪያዎች ስክሪኑ ላይ ደርድረው አሳዩት፡፡

‹‹ንግስት ሆይ እነሱን ማለቴ አይደለም፡፡እነዚህ ክቡርነትዎ እንዳሉት በኛም በነሱም የተዘጋጁ ተራ መተግበሪዎች ናቸው፡፡እነዚህን እንደ ህፃናት ጌም ማንም የሚፈጥራቸውን ማንሳቴ አይደለም፡፡በእነሱም ሆነ በኛ ወይም በሌላ ግለሰብ ባለሙያ የሚፈጠሩ ጥቃቅን የትርጉም መተግበሪያዎች በብዛት ቢኖሩም፣ በጎግል የትርጉም መተግበሪያ ስር የሆኑ ናቸውና የኛ ጎግል መተግበሪያ ያገኘውን ውጤት ብቻ ተንተርሰው፣ ሌላ አዲስ ነገር ሳይኖራቸው የሚቀጥሉ ናቸው፡፡ስለዚህ ዋናው ቁም ነገር በኛ ስር መስራቱ ነው ማለት ነው፡፡ክቡርነትዎ እንዳሉት የኛ ሙከራ ውጤቱ ሙሉዕና አጥጋቢ አይደለም፡፡ባልደረባዬ የገለፃቸው ጥቃቅን ነገሮች መስናክል ቢሆንም፣ ያን ያህል አሳሳቢዎች ግን አይደሉም፡፡ዋናውና ያልተጠቀሰው ችግር ሌላ ነው፡፡...... ለምሳሌ የአረብኛና የእብራይስጥ ፊደል ቃላትና ዓረፍተ ነገር፣ ከቀኝ ወደ ግራ ተፅፈው፣ ከቀኝ ወደ ግራ ተነበው፣ ትርጉም እንዲሚሰጡ ይታወቃል፡፡የኛ የላቲን ፊደል ቃላትና ዓረፍተ ነገር ደግሞ በተቃራኒው ከግራ ወደ ቀኝ ተፅፈው፣ ከግራ ወደ ቀኝ የሚነበቡ ይሆኑ

እንጂ፤ሲተረጎሙ ግን ልክ እንደ አረቢክና እብራይስጥ ከቀኝ ወደ ግራ ነው የሚተረጎሙት።።ስለዚህ የሌሎች ከቀኝ ወደ ግራ ተፅፈው ከቀኝ ወደ ግራ ተነበው የሚተረጎሙት እንደ አረብኛ እብራይስጥና ሌሎችን ወደ እንግሊዝኛ ለመተርጎም አልቸገረንም።።ሌሎች ልክ እንደ እኛ ከግራ ወደ ቀኝ ተፅፈው ከግራ ወደ ቀኝ የሚነበቡትም አልከበዱንም።።ምክንያቱም እንዴትም ተደርገው ቢፃፉ፤ዋናው ቁም ነገር ሲተረጎሙ እኛ ጋር በተመሳሰለ መልኩ ከቀኝ ወደ ግራ የሚተረጎሙ በመሆናቸው ነው።።በሌላ አገላለፅ የኛ እንግሊዝኛ ከዓረቡም ከእብራይስጡም ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ነው።።በአፃፃፍ ቢለያይም የመላው ዓለም ቋንቋ ከተነበበ በኋላ ሲተረጎም ከቀኝ ወደ ግራ ነው።።ስለዚህ ከቀኝ ወደ ግራም ተፃፈ ከግራ ወደ ቀኝም ተፃፈ ዋናው ሲተረጎም ነውና የሁሉም ቋንቋ ከቀኝ ወደ ግራ ስለሆነ ትርጉም የሚሰጡት ማናበብ አልከበደም።።

።ወደ ኢትዮጵያውያኑ አማርኛ ቋንቋ ስንመጣ ግን ከሌላው አገር ቋንቋ በተለየ መንገድ ከግራ ወደ ቀኝ ተፅፎ፤ በዚው በተፃፈበትና በተዋቀረበት ከግራ ወደ ቀኝ እየተነበበ ቀጥሎ፤ ከግራ ወደ ቀኝ ብቻ የሚተረጎም ነው። ይህንን ነው ማስታረቅ የከበደንና ጊዜ ወስደን እያጠናን ያለነው።

በተጨማሪም የኮንሶናንትና የቫውል ልዩነቱ በጣም የተራራቀና የማይገናኝ ነው።።የላቲኑ ፊደል ቫውልና ኮንሶናንት ሲኖረው፤ አማርኛ ደግሞ ቫውልና ኮንሶናንት የለውም።።ሆኖም አንዱ የአማርኛ ፊደል ሰባት ተነባቢ ፊደላት ስላሉትና እነሱንም በውስጡ ስለያዘ፤እነሱን በመለዋወጥ ብቻ ትርጉማቸውንም መለዋወጥ የሚችል ቋንቋ ነው።።በጥቅልና ባጭሩ ከሌላው ዓለም የተለየ ፊደልና ቋንቋ በመሆኑ፤ከማንም ጋር በምንም መልኩ ስላልተወራረሰ በመጠኑ ሊከብደን ችሏል።

ስለዚህ የአማርኛ ትርጉም ጀመረ በሚል ይፋ ያደረግነው ዜና ትልቅ ስህተት ነው!ሙከራ ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር።።በዚህ ይቅርታ መጠየቅ ይገባናል።

።ክቡርነትዎ በግልፅ እንደሚረዱት የሁሉም አገራት ፊደልና ቋንቋ አንዱ ካንዱ ጋር የተወራረሰ ነው።።ምንም ፊደላቱ ቢለያዩ፤ቅርፃቸው ቢለዋወጥ፤ በዓለማችን የቋንቋና የፊደል ታሪክ አንዱ ካንዱ ያልተወራረሰ ቋንቋ የለም!ብቸኛው ከሌላ ቋንቋና ፊደል ጋር ያልተወራረሰ፤ልብ ይበሉ ንግስት ሆይ፤በማንኛውም ዘመንና በየትኛውም የታሪክ አጋጣሚ ከምንም አይነት ቋንቋና ፊደል ጋር ያልተወራረሰና ያልተነካካ፤ያልተጠጋጋ አማርኛ ብቻ ነው!አማርኛ ከአንድ ቋንቋ ጋር ብቻ ተዋርሷል።።እሱም የራሱ አባት ወይም የራሱ ዘር ከሆነው ከግእዝ ጋር ብቻ!ግእዝና አማርኛ ደግሞ አንድ ነው። ፊደሉ አንድ ነው።።ቋንቋው አንድ ነው።።ግእዝ ነው ወደ አማርኛ የመጣው። ስለአማርኛ ማጥናት ስለ ግእዝ ማጥናት፤ስለ ግእዝ ማጥናት ስለ አማርኛ

ማጥናት ስለሆነ አንድ ናቸው።አንድ ስለሆኑ ተወራረሱ ማለት እ
አይቻልም።በመሆኑም በመጽሐፍ መልክ በተርጓሚዎች ሃሳብን በሃ
እየለወጡ በመተርጎም ካልሆነ በስተቀር ከቴክኖለጂ መተግበሪያዎች
እያይዞ እዚያው በዚያው መተርጎም ለጊዜው ከብዶን ታይቷል።ስለዚህ ጊ
ወሳጅና ከበድ ያለ ስለሆነብን ጊዜ ወስደን በቅርቡ ዳር እንደምናደርስ
በከፊል ቃል እንገባለን። ለዚህ ደግሞ የነሱ አገር ምሁራን የግ
ያስፈልጉናል።እነሱም ፈልገናቸው ሳይሆን ፈልገውን ከጎናችን መሆ
የሚችሉ ናቸው።ምክንያቱም መሳው ኢትዮጵያዊ በቋንቋ ረገድ ብቸ
ችግሩ እንግሊዝኛ ነው።እንግሊዝኛ መልመድና መቻል በነሱ ዘንድ እጅ
የሚፈለግና ሁሉም የሚመኘው ስለሆነ እነሱን ለመርዳት በሚል በቀላሉ
ምሁራኑን ከጎናችን ማድረግ እንችላለን።

‹‹ብተረፈ በሰሜን ኢትዮጵያ እንጂ በምስራቅ፣ በደቡብና በምእራብ
የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያሉ ህዝቦች ምንም እንኳን የየራሳቸው ቋንቋ
ቢሆንም፤ሲፅፉ የሚጠቀሙት የኛን ፊደል ነውና አልከበደንም።ክቡርነትዎ
በግልፅ እንደሚገነዘቡት ይህ ጉዳይ በዋናት ለኛ አስፈላጊ ይሁን እንጂ
ሙሉ በሙሉ መተግበሪያችን ስኬታማ ሆኖ ገደብ አልባ ትርጉም መስጠት
እንዲያገኙ በማድረጋችን እንደሚያመሰግኑን፣ መተግበሪያችንም
እንደሚያደንቁልን፣ ምንም ጥርጥር የለንም።
ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እጥረት የሚሰቃይ ነው።
በትምህርቱ ውጤታማ መሆን የማይችለው ዜጋቸውም በእንግሊዝኛ
ችሎታ ማጣት ምክንያት የሆነባት አገር ናት።ኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ
ሰው፣ ምሁር፣ ሊቅ፣ የሚባለው እንግሊዝኛ ቋንቋ በደንብ መናገርና
መስማት የሚችል ብቻ ነው።ስለዚህ በጋራ ጥረት እናሳካዋለን።ትንሽ ጊዜ
ይሰጠን ንግስት ሆይ››አለና ገለፃውን መጨረሱን እጅ በመንሳት አረጋገጠ።
‹‹መልካም።ግን ይህን ጥረት ውስጣችሁን አብርታችሁ
ሞክራችኋል?››በማለት ጠየቁት።‹‹አዎን ንግስት ሆይ፤
በሚገባ››መለሰላቸው።
‹‹ተቀመጥ››ተባለ።በድጋሚ እጅ ነስቶ የፈራው ቁጣ ባለመድረሱ ልቡሉን
እያመሰገነ እፎይ ብሎ ተቀመጠ።
ንግስቲቱ ቀጠሉ።
‹‹ክቡራን፤በባለሙያዎች ገለፃ ብዙ ነገር እንደተረዳችሁ ተስፋ አለኝ››አሉና፤
የቁጭት መሆኑ በሚያስታውቅ አኳኋን መድረኩ ላይ ጎርደድ ጎርደድ
እያሉ ከቆዩ በኋላ፤ ወደ ተሰብሳቢዎች ፊታቸውን መለስ አድርገው
በማፍጠጥ፤‹‹ኢትዮጵያን አቅልላችሁ አትዩዋት ተብሎ ተደጋግሞ
የሚነገራችሁ በምክንያት ነው።ይህ በራሱ ቀላል ጉዳይ የሚመስልና ምንም

ስሜት የማይሰጥ፤ የጉባኤ ጭብጥ ሆኖ መነሳቱ በራሱ ያልገረመው፣ ያላሳሰበው፣መሪ ካለ እኔ እወራረዳለሁ!የለም!ስለ ትርጉም፣ስለ ቃላት፣ስለ አማርኛ፣ስለ ቫውል፣ስለ ኮንሶናንት፣ስለባይት፣ስለ ቢት፣ስለ ዜሮ፣ስለ አንድ፣ስለምናምን...ይህ በመወራቱ ብዙዎቻችሁ ገርሟችኋል።ልክ ነኝ?››ሲሉ፤ሁሉም ተሰብሳቢዎች ልክ መሆናቸውን በአንገት ውዝዋዜ አረጋገጡ።

‹‹አያችሁ?የቋንቋው ከባድነት ሳይገርማችሁ ይችላል።ከዚህ በፊት ስለ ግእዝ ብዙ ተገልፆላችኋል።ውስጣችሁን አብርታችሁ ቋንቋውን ተሞልታችሁታል።ተሞልታችሁትም ልዑላችሁን አምልካችሁበታል። የመላእክት ቋንቋ መሆኑ፣የሰው ልጅ የመጀመሪያ ቋንቋ መሆኑ፣ቋንቋ ሲደበላለቅ ብቸኛው ሳይደባለቅ የቀረና በቤቱ በኢትዮጵያ አሁን ድረስ ያለና ያልጠፋ፣ዛሬ ድረስ እያገለገለ ያለ መሆኑ ወዘተ...ለሁላችሁም ግልፅ ነበር።አማርኛውም ያው የሱ ዘር ነውና ያው ነው።በዚህ ሳይሆን በሌላ ነው የተገረማችሁት።ስለ ኢትዮጵያውያን ተራ የቋንቋ ትርጉም!ለማክሮ 6 እንደሚያስፈልገው ዛሬ ባታውቁ ኖሮ፤ይህ ለምን ያስፈልጋል? ትሉ ነበር። አሁንም ልትሉ ትችላላችሁ።ለምን እንደሚያስፈልግ ቀስ እያለ ይገባችኋል፡ ፡በተረፈ ባለሙያዎች እንደገለፁት ነው።

‹‹ለእነሱ እንግሊዝኛ ማወቅ ህልማቸው ነው።ለኛ ደግሞ ለዓላማችን ያስፈልጋል።እነዚህ የረቀቀ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች ግን አቃታቸው።ይህ ምንም ካልነገራችሁ አዝናለሁ!ይቺ ተራና ኢምንት የሆነች ወይም የመሰለች የትርጉም ጉዳይ ያችን አገርና ህዝቦቿን ለማጥመድ ሲባል የግድ ታስፈልገናለች!

‹‹አዲሲቷ የምድር መንግስት ስንል ሁሉንም ነገር ጠቅለል አድርገን በክባችን ውስጥ ማስገባት እንደማለት ነው።ሁኔታው እንደ ጦር ሰራዊት ሩጫ ውድድር ነው ክቡራን።በቡድን ያሉ ወታደሮች አርባ ወይም ሃምሳ ሆነው ሲሮጡ፤ አንድ አባላቸው በሩጫ ደካማ ቢሆንና ሌሎች ሁሉ ፈጥነው ሩጫውን ቢጨርሱ፤ ውጤቱ የሚመዘገበው ሁሉም ተጠቃለው በገቡበት ሰዓት እንጂ ቀድሞ በገባው አይደለምና፤ደካማ የቡድኑ ወይም የጋንታው አባል ካለ አዝለውም አቅፈውም እየሮጡ ይዘውት ካልገቡ ለውጤት አይበቁም።የሩጫው የውጤት ሰዓት የሚመዘገበው ሁሉም ተጠቃሎ በገባበት በመጨረሻው ሰው ስለሆነ።በዚህ ምሳሌ መሰረት፤ ከሌላው ምድር የበለጠ በዋናነት ጎላችን የሆነችውን አገር ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ደካማና ኋላ ቀር ስለሆኑ፤ የኛ ልምምድ በነሱ ዘንድ ስለሌለ፣ ንቆ መተው ሳይሆን፤አዝለንም ሆነ አቅፈን የመጠቅለል ግዴታ ነው ያለብን።ልብ አድርጉ ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላው የአፍሪካ አገር በዚህ በግሎባላይዜሽን ዘመን ራቁታቸውን የሚኖሩ በርካታ ጎሳዎችና ህዝቦች

አሉ፡፡የሊላው ዓለም ህዝብ ርቆ ሄዶ የሚጎበኛቸው ህዝቦች፡፡እነዚህን ህዝቦች ወደ ግሎባላይዜሽን ክብ ውስጥ ማስገባት እጅግ ከባድ ከመሆኑም በላይ፤ የቡድኑን ሩጫ ያንትታሉና ቀድመው መወገድ ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ያን ልናደርግም እንችላለን፤እናደርጋለንም፡፡በኢትዮጵያ ምድር ያሉትን ግን አንችልምም፤ ማድረግም አንፈልግም፡፡የግድ በፈቃዳቸው ወደኛ ማምጣት ነው የምንችለው፡፡ስለዚህ በማንገራገር ስራ ጊዜ ሊወስዱብን ስለሚችሉ ያን ጊዜ ለማሳጠር መጣር ነው ያለብን፡፡የፈጀ ጊዜ ፈጅቶ በሃይል ሳይሆን በትእግስት፤ እንዲሁም በፍላጎታቸው ነው መግባት ያለባቸው፡፡ለዚህ ደግሞ የግድ በተለያየ መንገድና በተለያየ የአገባብ ዘዴ ወደ ውስጣቸው መግባት አለብን፤አለባችሁ፡፡

‹‹መላው ህዝባቸው ባይሆንም ምድሪቱ በበላይ አካሉ ስለምትፈለግና ስለምትታገዝ ነው ይሄን የምንለው!ህዝቦችን ብቻ ማጥመድና ወደ ልዑላችን ዓላማ ማምጣት ቀላል ሊሆን ይችላል፡፡ብዙሃኑም ወደኛ መስመር እየመጣና እየገባ ነው፡፡ሲመጣ ግን ወዶና ፈቅዶ ወይም የውዴታ ግዴታ ሆኖበት እንጂ፤ የድብቅ ዓላማችን ተባባሪ መሆኑን ነግረነውና ተቀብሎን ላይሆን ይችላል፡፡

‹‹ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ለማጥመድ፤መንግስታቸውንና የሐይማኖት አባቶቻቸውን ብቻ ማጥመድ በቂ ቢሆን ደስ ባለን፡፡ያን በቀላሉ ማድረግ የምንችልና የቻልን ስለሆንን፡፡በምሁራኖቿ ብቻ ማጥመድ ብንችልም እንዲሁ ደስ ባለንና በቀለለን ነበር፡፡አይደለም!

በየዘርፉ ተሰማርተው የማጥመድ ስራውን የሚሰሩ በርካታ ሰዎችና ተቋማት ያስፈልጉናል፡፡ከነሱም ከኛም የተውጣጣ የሰው ሃይል ከሌለ ደግሞ መሰናክሎች መበርከታቸው አይቀርም፡፡መሰናክል ሲባልም አሁን እንደሰማችሁት በጣም ጥቃቅን ጉዳዮች ሊሆኑና ሊመስሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ጥቃቅን መሳይና ሲደራረቡ ሊገዝፉ፤ ጊዜ ወሳጅ ሊሆኑና ሊያንትቱ የሚችሉ ስለሚሆኑ በጥንቃቄና በዘዴ ፈጥነው መከናወን ያለባቸው ናቸው፡፡

‹‹ኢትዮጵያን በሚመለከት አንዳች ተራ የምትባል ነገር የለችም፡፡ጎላችን ናት ስንልም በብዙ ዘርፍ እንጂ በአንዲት የህይወት ዛፍ ክልል ብቻ ተወስና ስላለ ጎል አይደለም የምናወራው፡፡ስለዚህ ቋንቋ መተርጎምና ያለመተርጎም ጉዳይ አላሳቢ ሆኖ ያልታያችሁን ያህል፤ኢትዮጵያን በሚመለከት ሊላውንም ከዚህ ያነሰ ኢምንት ጉዳይ ትኩረት እንድታደርጉበት በዚህ አጋጣሚ ደግሜ አሳስባለሁ!ኢትዮጵያውያን የኛን፤እኛ የነሱን እውቀት የምናውቅና የምንግባባበት የትርጉም ስራ በአፋጣኝ መሰራት አለበት! ገባችሁ?››

‹‹ገብቶናል ንግስት ሆይ››

‹‹የእነሱን እውቀት እኛ ማወቅ አለብን ስል ምንም እውቀው አይደለም። ወይም የእነሱ ዓለማዊ እውቀት ለኛ ጠቃሚ ሆኖ አይደለም። ግን...ኢትዮጵያውያን....!››አሉ፤ ቃሉን ጠበቅና ረገጥ አድርገው።የእልህ፣ የተሸናፊነትና የበቀል ጥም የሚነበብበት ጨምታራ ፊታቸውን የበለጠ እያጨመታተሩ፤‹‹ኢትዮጵያ!››አሉ በቁጭት።ይህን ብለው እጆቻቸውን ወደ ኋላ አጣምረው፣ አቀርቅረው፣መድረኩ ላይ ወዲያ ወዲህ እየተራመዱ ቆዩና ቀጠሉ።

‹‹መላው የአውሮፓና የአሜሪካ፣የሩቅ ምስራቅና የመካከለኛው ምስራቅ፣ ብሎም የአፍሪካ አገራት ህዝቦች፤ከኢትዮጵያውያን አንፃር ሲታዩ የሰለጠኑና የነቁ ህዝቦች ሆነው እናገኛቸዋለን።እነሱ ሁሉ ግን በኛ አማካኝነት የሰለጠኑና የኛን ፈለግ ተከትለው የኖሩ ህዝቦች ስለሆኑ ነው። በኛ ቋንቋ ከኛ እኩል ማሰብ የሚችሉ ህዝቦችም ናቸው።ከኢትዮጵያውያን በተሻለና በበለጠ ሁኔታም የልዑላችን ጥበብ ተካፋዮች ናቸው።አብዛኛው የዓለም ህዝብ ጥሩ በልቶ፣ ጥሩ ጠጥቶ፣ ጥሩ ተዝናንቶ፣ ተምሮ፣ ሰልጥኖ፣ ኑሮውን ያሻሻለና በማሻሻል ላይ ያለ ህዝብ ነው።የዘመናዊ ቁሳቁስ ባለቤት ሆኖ የሚኖር ነው።ዘመናዊነትን አንዴ ካየ በኋላ ጉጉ ሆኖ በዘመናዊነት ላይ ሌላ ዘመናዊነት እየጨመረ የሚኖርና ለመኖርም የተዘጋጀ ህዝብ ነው።የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ከቋንቋና ከፊደል አቅም እንኳ ከሌላ ጋር ሳይወራረስ የራሱን ብቻ ይዞ የቀጠለ ህዝብ ነው።የሚያስበውም በራሱ ቋንቋ ብቻ ነው።ስልጣኔንም የሰይጣን ስራ ብሎ የሚሰይምና የሚሳደብ እንጂ፤ አድንቆ የሚቀበል ህዝብ አይደለም።ኢትዮጵያ!››አሉ አሁንም በቁጭት።

‹‹ኢትዮጵያ ማለት ትንሽና የትንሽ ህዝቦች መኖሪያ የሆነች፣በኋላ ቀርነትና በረሃብ የምትታወቅ፣ በጣም አሳዛኝና ደሀ አገር ናት!ይህ እውነት ነው። ነገር ግን አስታውሱ!ህዝቦቿ በጣም ፈታኝ ህዝቦች ናቸው።በንቃተ ህሊናም ከመላው የዓለም ህዝብ ኢትዮጵያውያን ይበልጣሉ!››ብለው ሲሉ፤ የተቃውሞ የመሰለ የጋራ ጉርምርምታ አቋረጣቸው።

‹‹አዎን!መገለጫዎቹ ለየትኛዬት ያሉ ናቸው እንጂ ይበልጣሉ።መገለጫቸው ምን እንደሚመስል አብራራላሁና ጉርምርምታውን ትታችሁ ተከታተሉኝ። በንቃተ ህሊና ከሁሉም ህዝብ ይበልጣል ስል በብዙ መንገድና በተለያዩ አሳማኝ ምክንያት ነው።

‹‹ይህን ልል የቻልኩበትን ዋና ዋና ምክንያቶች ልዘርዝር። እናም ከቀላሉ ልጀምርላችሁ።የአሜሪካና የአውሮፓ ህዝብ የዘፋኞቻችንን ሁኔታ ሲያይና በአደባባይ ባሮሚትን ሲያመልኩ ሲያይ እንደ ተራ ክስተት ነው የቀጠረው፡ ፡ለእውቅና፣ለዝና፣ ለገንዘብ፣ ያደረጉት ተራ አምልኮ ነውና፤‹‹መብታቸውም ነው›› ብሎ አቅልሎ ነው ያየውና የሚያየው።ይህ ግን ለኢትዮጵያውያኑ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

የመጨረሻው ሆጥያትና፤ ክፉ ዘመን ስመምጣቱ ምልክታቸው ነው። የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን በሚመለከት የሌላው ዓለም ህዝብ ጉዳዩ የሀግ ከለላ ሲሰጠው ሲያይ፤እንደ ነፃነትና እንደ ዲሞክራሲያዊ መብት፤እንደ ሰብዓዊ መብት፤እንደ ዜጎች መብት አይቶ አደነቀ፤አድንቆም በይሁንታ ተቀበለ እንጂ ‹‹አግዚኦ… ማዓት ሊያመጡብን ነው!››ብሎ እንደ ሆጥያት ቆጥሮ፣ ከሐይማኖት ጋር አያይዞ፣ አላጉረመረመብንም፤ አልተቃወመንም። ለተቃውሞም ወደ አደባባይ አልወጣም። በቫቲካን ቤተክርስቲያን ስር ያለው ምዕመን እንኳ ደስ ብሎት፤ ደስ ባይለውም ምንም ሳይመስለው በቀላሉ የታክስ ከፋዮች መብት መከበር እንዳለበት አምኖ የተወው ሆኖ ነው የታየው።

‹‹ኢትዮጵያውያኑስ?››ብለው ወደ ተሰብሳቢው አፈጠጡ።

ተሰብሳቢዎችም፤‹‹አሁን እየገባን ሄደ›› አይነት የፊት ገፅታ ማሳየት ጀመሩ።

‹‹ስለዚህ ፈታኝ ህዝብ ነው።ኢትዮጵያውያን ከዓለም ህዝብ በተለየ መልኩ በዚህ እኛ በምንጫወተው ጫዋታ ዙሪያ እንኳ ከሁሉም አገር ህዝብ የተለየና የተሻለ ግንዛቤ እንዲሁም እውቀት ይዘዋል።ለምን?ምክንያቱም በነሱ ዘንድ የኛ ድብቅ ተግባርም ሆነ የቴክኖለጂ ውጤት፤ ወይም የግሎባላይዜሽን አካሄድ፤አሊያም የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ፤እንዲሁም የታዋቂ ዝነኞች የአምልኮ ተግባር ጉድ እየተባለ የሚታይ ትልቅ ዜና ሆኖ የሚናኝ ነውና ሁሉም ትኩረት ሰጥቶ ይመረምረዋል።እግዚኦ እያለ ያስተጋባዋል።የሌላው ዓለም ህዝብ ግን ከተራ ዜናነቱ ያለፈ ትኩረት ሰጥቶ ስለልዑላችን አካሄድ አይመራመርም።ስለ ቴክኖለጂ ውጤቶች እየተደመመ የሰይጣን ስራ ነው አይልም።ምክንያቱም ዘመናዊ ህዝብ ስለሆነ።በዚህ ገፅታው የኢትዮጵያ ህዝብ አወዛጋቢ ህዝብ ሆኖ ይገኛል። ማዛይም ስትሉት ብልጥ፤ ኋላ ቀር ስትሉት ፈጣን፤ዝንጉ ስትሉት ጥንቁቅ፤ መርማሪና ተጠራጣሪ ሆኖ የሚገኝ ህዝብ ነው።

ከዚህ አንፃር ሌላው ህዝብ አስቸጋሪና ፈታኝ አይሆንብንም፤እነሱ ግን ፈታኝና አስቸጋሪ ሆነው ነገሮችን በቀላሉ ባለመቀበል ምክንያት ጊዜ ወሳጅ ይሆናሉ ነው።በዚህ ገፅታቸው ንቁ መሆናቸውን መገንዘብ፤ በነሱ መበለጥ ወይም መሸነፍ ማለት ስላልሆነ የምለውን በቀላሉ ተቀብላችሁ እመኑ እንጂ አታጉረምርሙ።እንጂማ……››አሉና፤ ወደ ግድግዳው ጠጋ ብለው፤ በእጅ ምልክት ትእዛዝ በመስጠት፤ግድግዳው ላይ ሰፊ ስክሪን በመዘርጋትና በማብራት፤‹‹ተመልከቱ!››በማለት፤በሰፊውና ተንቀሳቃሽ ምስልን ጥርት አድርጎ በሚያሳየው ዘመናዊ ስክሪን ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን፤ እንዲሁም የአገሪቱን አጠቃላይ ገፅታ በተለይም የገጠሩን አካባቢ እየተዘዋወረ በሚያሳይ በተንቀሳቃሽ ምስል የተደገፈ ማብራሪያቸውን ጀመሩ።

‹‹ተመልከቱ! የዛሬ 8 ሺ ዓመት የሰው ልጅ በዚህ መልኩ ነበር አርሶ፣ አጭዶ፣ ወቅቶ፣ፈጭቶ የሚበላው፡፡ቀስ በቀስ የሰው ልጅ ሰልጥኖ፣ በሂደትም ተራቆ፣ አሁን እኛ ያለንበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ኢትዮጵያውያን ግን ዛሬም ድረስ ለ 7 እና ለ8 ሺ ዓመታት አንድ አይነት የሆነ ኑሮ ነው እየኖሩ የመጡት፡፡ይሄው ዛሬ ድረስም እንዲህ በእንስሳ የሚያርሱ ናቸው፡፡ የዛሬ 8 ሺ ዓመት የነበረው ሰብል ነው እየተወራረሰ መጥቶ፣ለዘር እየተቀመጠ ኖሮ፣ እየተዘራ ሲበላ የኖረው፡፡

‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ ማለት እነዚህ ናቸው፡፡ለእግራቸው እንኳ ጫማ የሌላቸው፡፡የእግሮቻቸው ተረከዝ የተሰነጣጠቀና የተቀረደደ፣የዛሬ 7 ሺ ዓመት ሰው ሳይሰለጥን ከጥጥ ተሰርቶ የሚለበስ ልብስ ዛሬ ድረስ የሚለብሱ!››እያሉ በየ አገሩ ያሉ ኢትዮጵያዊ አርሶ አደሮችን ጥርት አድርጎ በሚያሳየው ሰፊ ስክሪን እያሳዩ ቀጠሉ፡፡

‹‹ኢትዮጵያውያን በእጃቸው አርሰውና ቆፍረው ምግባቸውን ያገኛሉ፡፡ የዘሩትን ሰብል በእጃቸው አርመው፣በእጃቸው አጭደው፣በእጃቸው ከምረው፣በእጃቸው ወቅተው፣በእጃቸው አበጥረው፣በእጃቸው ለቅመው፣ በእጃቸው ፈጭተው፣ በእጃቸው አቡክተው፣በእጃቸው ጋግረው፣በእጃቸው አብስለው፣ በእጃቸው የሚበሉ አሳዛኝና አስደንጋጭ ፍጡሮች ናቸው፡፡የዛሬ 7 እና 8 ሺ ዓመትም እንዲህ ነበሩ፣ አሁንም እንዲህ ናቸው፡፡

‹‹ከዚያ በኋላ በሰብሉ ተረፈ ምርት ከብቶቻቸውን ይመግቡና፣ በሰብሉ ተረፈ ምርት መኝታቸውን ይሰራሉ፡፡አሁንም በሰብሉ ተረፈ ምርት በገለባና በአፈር አቡክተው መኖሪያ ቤታቸውን የሚሰሩና፣በሳር ጣራ ሰርተው ከዝናብና ከብርድ ራሳቸውን እየተከላከሉ የሚኖሩ ናቸው፡፡የሰብሉን ተረፈ ምርት ተመግበው ወተትና ስጋ የሚሰጧቸውን የከብቶቻቸውን እበት አድርቀው ለማገዶነት የሚጠቀሙ፣በዚያ ማገዶ ተጠቅመው ምግባቸውን አብስለው መብላት የቻሉና በዚህ አይነቱ አኗኗር ዜይቤ ተወስነው ለብዙ ሺ ዓመታት የዘለቁ ህዝቦች ናቸው፡፡

‹‹ስለ ብዙሃኑ 85 % ነው የማወራችሁ፡፡እናንተ ለጉብኝት ስትሄዱ የምታዩትን ዋና ከተማቸውን እርሱት፡፡እናንተ ያረፋችሁበትን ዘመናዊ ሆቴል እንዳታስቡ፡፡ያ በኛ ድጋፍ የሆነና እኛ ብቻ የምናርፍበት የምንዝናናበት ነው፡፡ብዙሃኑ ያገሬው ህዝብ ሊረግጠውም፣ ሊያርፍበትም፣ ሊዝናናበትም፣ሊያውቀውም፣የማይችለውን ሆቴልና አውራ ጎዳና እርሱትና ስለ ብዙሃኑ ኑሮና የአኗኗር ዘይቤ የምላችሁን ብቻ ያዙ፡፡

‹‹ከብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ይልቅ ባሁኑ ሰዓት የኛ አገር እንስሶች ድመት፣ውሻ፣ዝንጀሮ፣የተሻሉና ስልጡን ናቸው፡፡ሆኖም ግን እመኑኝ፣ በንቃተ ህሊና ከሁሉም ህዝብ ይበልጣሉ፡፡

ቋንቋቸው የብቻቸው ሆኖ ስለተወሰነና እነሱ የሚያስቡት በአማርኛ፤እኛ የምናስበው በእንግሊዝኛ ስለሆነ እንጂ፤ሁሉንም ፍልስፍናቸውን፣ ተረቶቻቸውን፣አቋምና አመለካከታቸውን፣ ብሎም ቀልዶቻቸውን ተተርጉመው ብትሰሙ፣ብታዩና ብታነቡ ትደነቃላችሁ።ግራ አጋቢ ህዝብ መሆኑን ታውቃላችሁ።እነሱ ደግሞ ስለኛ የሚያስቡትና ስለራሳቸው የሚያውቁት ሌላ ነው።ፈረንጅ የተባለ ሁሉ ስልክ የሚሰራ፣መብራት የሚሰራ፣አሜሪካዊ የሆነ ሁሉ አውሮፕላን የሚሰራ ነው የሚመስላቸው። ሁሉም ነጭ ህዝብ በንቃተ ህሊና ከእነሱ እጅግ የበለጠና የላቀ ይመስላቸዋል።የፈረንጅ ሞኝ ያለ አይመስላቸውም።አገሪቱ በጥቂት ግለሰቦች የሰለጠኑ መሆናቸውንና ተራው ህዝብ ምንም እንደማያውቅ አይደለም የሚያውቁት።ሁሉም ፈረንጅ ባለሙያና ጥበበኛ ነው የሚመስላቸው።እነሱ ስለራሳቸው ሲያስቡ ደግሞ መሃይምና ምንም መስራት የማይችሉ፤ከፈረንጅ ጋር ሲነፃፀሩ ልዩነታቸው ሰማይና ምድር የሆነ አድርገው ነው የሚያስቡት።እውነታው ግን ሌላ ነው።በአስተሳሰብ፣ በፍልስፍና፣ በአመለካከት፣ በጥንቁቅነት፣ከሌላው ‹‹ፈረንጅ›› እያሉ በጣሊያንኛ ከሚጠሩት ስልጡን ነጭ ህዝብ ይበልጣሉ።

‹‹ኢትዮጵያውያን ስትቀርቧቸው ይርቋችኋል፣ስታዝኑባቸው ያዝኑላችኋል፣ ስታዝኑላቸው ያዝኑባችኋል፣ስታለቅሱላቸው ይስቁባችኋል፣ስትስቁባቸው ያለቅሱላችኋል።ወዳጅ ስታደርጓቸው በጠላትነት ያዩዋችኋል።ስታምኗቸው ይጠራጠሯችኋል።

ምንም ነገር ከጥንቃቄና ከጥርጣሬ ጋር ካልሆነ እንዲሁ አይቀበሏችሁም። ዝብርቅርቅ ያሉና አወዛጋቢ የሆኑ ህዝቦች ናቸው!ለምን?ነገሮችን ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ስለማያዩ።

ነገሮችን በሙሉ ከተረቶቻቸው፣ ከፍልስፍናቸው፣ሳያነቡ በቃል ከሰሙት ታሪክ፣ ቃል በቃል እየተላለፈ ከመጣ ስነ ቃላቸው ጋር እያዛመዱ፤ስሬ ገዜ ወስደው ይመረምራሉ፤ግራ ቀኙን ያጣራሉ።ምክራችንን ከአባቶቻቸው ምክር፣እርዳታችንን ከአባቶቻቸው ባህል፣ ወዘተ....እያመሳከሩ ስለሚያዩና ስሚያነፃፅሩ በቀላሉ መጠመድ የማይችሉ ሆነው ቆይተዋል።

‹‹ይህ የምታዩት በባዶ እግሩ የሚሄድ ባላገር፤ አንድን በዘመናዊ አውቶሞቢል ተሳፍሮ፤በሞተረኛ ታጅቦ የሚሄድን የፈረንጅ ሚንስትር ቢያይ፤ከመንፈሳዊ ቅናትና ከመደነቅ ወይም ከማድነቅ ምናልባትም እንዲያ መሆንን ከመመኘት ይልቅ፤አጥንት ስርስሮ የሚገባ ከተፈጥሮ ጋር የተቆራኘ ተረት አዘል እውነት ነገር እየሳቀ ያሳቅቀዋል።ምናልባትም ወርዶ በእግሩ እንዲሄድ ሊያደርገው ይችላል።ይህ ለምን ሆነ? ከምን መነጨ? ስንል፤ስሬ ትንታኔ ወደሚያስፈልገው የኋላ ታሪክ ስለሚወስደን ብዙ አልግፋበት።ሆኖም ግን በንቃተ ህሊና እንዴት እንደሚበልጡን በተለያየ

መንገድ በየግላችሁ የምትደርሱበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ልጠቁማችሁ እሻለሁ፡፡

ይህ ህዝብ ነው በታንክ፣ በጀትና በዘመናዊ ከባድ መሳሪያ ታጅበው የመጡብትን ስልጡን ወታደሮች፤በባዶ እግሩ፣ ያለምንም ዘመናዊ መሳሪያ፤ በዚያ በኋላ ቀሩና የዛሬ 7 ሺ ዓመት ጥንታዊ ህዝቦች ይዋጉበት በነበረው ጦርና ጋሻ መክቶ መመለስ የቻለው!

ይህንን የምለው ኢትዮጵያውያንን እንድትፈሯቸው ሳይሆን፤ እንድትጠነቀቋቸው ለማሳሰብ ነው፡፡ወጥመዶቻችሁን በየዘርፉ ስትዘረጉ ህዝቡን ከመናቅ ይልቅ፤እንደሚበልጣችሁ እያሰባችሁ በጥንቃቄ ብታጠምዱት ለስኬት እንደሚያበቃችሁ ለመጠቆም ፈልጌ ነው፡፡

ብተረፈ ኢትዮጵያውያን በአንድ አይነት የጥንት ዘይቤ እንዲህ እጅግ ኋላ ቀር የሆነ ኑሮ እየመሩ፤እዚህ ደረጃ ደረሱ ሳይባል፤ዛሬ ድረስ እንደተፈጠሩ ያሉ ባዶ እግር ህዝቦች ናቸው፡፡

ሆኖም ግን መሰልጠን ሳይፈልጉ ቀርተው አይደለም፡፡ይፈልጋሉ፤ይመኛሉ፡፡ የበላይ አካሉ ግን እንዲሰለጥኑ አይፈልግም፡፡

«ኢትዮጵያውያን ከማንም ህዝብ የተለዩ ህዝቦች ሆነው አይደለም፡፡ሁሉም ህዝብ ለበላይ አካሉ አንድ ህዝብ ነው፡፡ነገር ግን በኢትዮጵያ ምድር የሚኖሩ ህዝቦች እንዲሰለጥኑ የማይፈለግበት ምክንያት አለ፡፡

እኛንና ስልጣኔያችን፣ኑሯችንና ዘመናዊ አገራችንን፣ዘመናዊ ቁሳቁሶቻችንን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይፈልጋል፤ይመኛል፡፡ወደኛ አገር መምጣትና መሰልጠን፣ጥሩ መብላት፣ ጥሩ መጠጣት፣ ጥሩ መልበስ፣ ወዘተ...የሁሉም ኢትዮጵያዊ ህልም ነው፡፡ለዚህም ሲሉ በየባህሩ የሚሞቱ፣ ለባርነት ሁሌም ዝግጁ የሆኑ፣ ዶላር ካዩ መቀመቅም ቢሆን ለመግባት የማያቅማሙ ናቸው፡፡እኛም እንዲያ እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ሆኖም ሁሉንም ጠራርገን ማምጣት አንችልም፡፡እኛ ስለፈለግንና እነሱ ስለፈለጉ ብቻ ወደ ሁለታችን የተጣጣመ ፍላጎት እንዳንመጣ የሚያደርግ ሃይል አለ፡ ፡ያን ሃይል በመገዝገዝና በጊዜ ሂደት በመገንደስ እንጂ በአንዴ መርታት አያስፈልግምም አይቻልምም፡፡ተረዳችሁኝ?

መንፈሳዊ አሰራርና አካሄድ እንዴት እንደሆነ በሚገባ ተብራርቶላችኋል፡፡ እኛና እናንተ በሰው የሚሰራውን ስራ ሰው ሆነንና መስለን በሰው አካሄድና ዘይቤ ተጉዘን ስንሰራ፤ እነሱም ተመሳሳይ ሆነው ነው የሚጠብቁን፡፡ስለዚህ ከኛ አገር እንስሶች የማይሻል የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ ያሉ ስለሆኑና በባዶ እግር እድሜ ልካቸውን ስለሄዱ እንደ ማሃይም እየቆጠራችሁ የምትዘናጉትን ነገር አቁሙ!አቁሙ!አቁሙ!መልእክቱ ነው፡፡

ታውቃላችሁ?ኢትዮጵያውያን እንዲህ ኋላ ቀር ይምሰሉ እንጂ ኋላ ቀር ናቸው፡፡ነገር ግን አይደሉም፡፡እርግጥ ነው በንስማዊ ህይወት

በመንፈሳዊ ህይወት ኋላ ቀሮች አይደሉም!በመንፈሳዊ ነገራቸው ምጡቅ መሆናቸውም ነው በዓለማዊ ህይወታቸው ኋላቀር እንዲሆኑ ያደረጋቸው!ኋላ ቀር የሆኑትም የበላይ አካሉ ስለፈለገ ብቻ ሳይሆን፤ እነሱም ስላመኑበት ጭምር ነው፡፡

‹‹የአባቶቻቸው ጥበብ መንፈሳዊ ጥበብ ሲሆን፤እሱንም ለበላይ አካሉ ክብርና ግልጋሎት ስለሚያውሉት ብቻ ነው ህዝቡ ኋላ ቀር የሆነው፡፡ እየሄዳችሁ የምትጎበኙትን ላሊበላን የመሰለ ድንቅ ጥበብ የሚንፀባረቅበትን ህንፃ አንፀው ለበላይ አካሉ ክብር ያዋሉ ናቸው!እነሱ ያን ሰርተው ለበላይ አካሉ አውለው ቤተ መቅደሱ ሲያደርጉና የፀሎት ቦታቸው ሆኖ ዛሬ ድረስ ሲመለክበት፤እነሱ ግን የሚኖሩት ጎጆ ቤት ውስጥ ነው፡፡እነዚህ ህዝቦች በስክሪት ላይ እንደምትመለከቱት የበላይ አካሉ የሚመለክበትን አብያተ ክርስቲያናት ወለልና ግድግዳውን በወርቅ ባሸበረቀ ቁሳቁስ ገንብተው፤ የበላይ አካሉን ሲያመልኩ፤ እነሱ ግን ለሰውነታቸው መሸፈኛ እራፊ ጨርቅ ብቻ ነው ያላቸው፡

እነዚህን ሁሉ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ቤተክርስቲያናትንና ገዳማትን ተመልከቱ!ሁሉም በወርቅ የተንቆጠቆጡ፣ውድ ምንጣፍ የተነጠፈላቸው፣ ባማረ መጋረጃ የተጋረዱ ናቸው፡፡የህዝቡን መኖሪያ ቤት ደግሞ እዩ!በከብቶች እበት የተለቀለቀ መደብ፣መስኮትም፤ መጋረጃም፤ በሌለው የጭቃ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡

እነዚህንም ተመልከቱ፡፡በእያንዳንዷ ቤተክርስቲያንና ገዳማት ውስጥ የሚገኙ ከኛ ወገኖች ከነ ዳቮንቺ በበለጠም ባይሆን በማይተናነስ፤በአስደናቂ ውድ ስእሎች ያሸበረቁ ግድግዳዎች ናቸው፡፡የህዝቡን ቤት ደግሞ ተመልከቱ፡፡ በእበት በተለቀለቀ የጎጆ ቤት ግድግዳ ላይ እመድ ተቦክቶ በእምስት ጣትና የእጅ መዳፍ ግድግዳ ላይ እየተለጠፈ በእመድ በተሳለ ስእል ያጌጠ አስቂኝ ክፍል!እንዲህ ሆኖ የተሰራ የብዙ ትውልድ መኖሪያ!

‹‹እነዚህን ተመልከቱ፡፡ከወርቅ፣ከብር፣ከነሃስ የተሰሩ ለበላይ አካሉ መንፈሳዊ ግልጋሎት የሚውሉና፤ በየአብያተክርስቲያናቱ የሚገኙ የተለመዱ መጠጫዎች፣ማጥመቂያዎች፣ማቁረቢያዎች!ህዝቡን ደግሞ ተመልከቱ!ከጓሮው የበቀለን ቅል ሰንጥቀውና መራር ፍሬውን አውጥተው፤ ፈግፍገው፣አጥበው፣አድርቀው፣በቅል የሚጠጡ! ከሰንበሌጥ አይነቶች ወይም ከሳር በተሰራ የመመገቢያ እቃ የሚመገቡና፤ከቅል በተሰራ ኩባያ/ፋጋ/የሚጠጡ ናቸው! መታጠቢያው ቅል፣ወተት ማለቢያው ቅል፣ እርጎ መናጫው ቅል፣ሊጥ ማቡኪያው ቅል፣ውሃ ማምጫው ቅል!መጠጫው ቅል፣ቅል፣ቅል፣ቅል፣ቅል.........

‹‹ከጓሯቸው ዛፍ ቆርጠው ጠርበውና አዘጋጅተው ከብቶቻቸውን በእንጨት ገንዳ ውሃ የሚያጠጡ!ከጓሯቸው የበቀለን ቡና ለቅመው፣ስሌን ዘርግተው

አድርቀው፣ቆልተው፣በእንጨት ሙቀጫ የሚወግጡ!ወቅጠውም በእጅ በተሰራ የሸክላ ጀበና አፍልተው የሚጠጡ ናቸው!ከንሬቻቸው ባገኙት ማርና ባበቀሉት ጌሾ ተጠቅመው ጠጅ ጥለው የሚጠጡ፣ጠላ ጠምቀው በቀንድ ዋንጫ የሚጠጡ ናቸው!በከብቶቻቸው ቆዳ የጠፍር አልጋ ሰርተው የሚተኙ ናቸው!በድንጋይ ወፍጮ በእጃቸው የሚፈጩ ህዝቦች ናቸው ክቡራን፡፡

‹‹እነዚህን ለመንፈሳዊ ግልጋሎት የሚውሉ በየአድባራቱ ያሉ ውድ እና አስደማሚ አልባሳቶችን ደግሞ ተመልከቱ!ያማረ ካባ፣ዘርፋ ዘርፋ ያጌጠ፣ የተንቆጠቆጠ፣ በወርቅም የተለበጠ፣ ሙሉ አልባሳት!ህዝቡን ደግሞ ተመልከቱ!ለረጅም ዓመታት ሳይቀየርና ሳይታጠብ የሚለበስ አጭር ቁምጣ!ሰውነታቸው ላይ እንዳለ ሳይወልቅና ሳይቀየር ላያቸው ላይ የሚያልቅ ቁራጭ ልብስ!

‹‹ተመልከቱ! በመቶ ሚሊዮን፤ምናልባትም በቢሊዮን የሚቆጠር ለመንፈሳዊ ግልጋሎት፤የበላይ አካሉን ለማምለክ የሚውል የወርቅ ፀናፅልና የወርቅ መስቀል፣ከወርቅ የተሰራ ብዙ ነገር!ህዝቡን ደግሞ እዩት፤አንገቱ ላይ ጥቁር ክር ብቻ አስሮ እሱንም በማሰሩ የአምላክ በረከት ተካፋይ እንደሆነ እያሰበ፣ እየተራበ፣ እየተጠማ፣ የሚኖር ህዝብ!

ተመልከቱ!ለማመን የሚከብድና በዚህ መሃይም ህዝብ ሊሰሩ ቀርቶ ሊታሰቡ የሚከብዱ እንቁላልን እንደማጣበቂያ ስሚንቶ እያደረጉ በመጠቀም የተገነቡ አድባራትን!ከውጪ ጣራ እስከ ውስጡ ኮርኒስ፤ከቤተክርስቲያኑ የውጭ ግድግዳ እስከ ቅጥር ጊቢው አጥር እንዴት እንደተገነቡ ተመልከቱ!የገንቢዎችን አኗኗርና ቤታቸውን ደግሞ እዩ፡፡ጣራው የሚያፈስ፣ ግድግዳው በዝናብ እርጥበት የሚፈራርስ!

‹‹ተመልከቱ ክቡራን!የእግሮቻቸውና የቤታቸው የወለል አፈር እኩል አፈር ነው፡፡በገነቡት ቤተ መቅደስ ያለው ምንጣፍ ግን በእነሱ እግር አይደለም በኛ በንፁሆች እና በምንታጠበው ስልጡን ሰዎች ሊረግጡት የሚከብድ ነው፡፡እነሱም ደፍረው አይረግጡትም፡፡ምናልባትም እግሮቻቸውን የሚታጠቡት ወደ መቅደሱ ሊገቡ ሲሉ ብቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡

‹‹ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በዚህ አይነቱ መንፈሳዊ ስራና ግንባታ በኩል፤በየትኛውም ዘመን የኛን የስልጡን አገሮችን እርዳታና እገዛ ፈልገው አያውቁም፡፡ ነገስታቱም፣ ህዝቡም፣ የቤተክህነት ሊቃውንቱም፣ በተመሳሳይና በተጣጣመ መልኩ ደስ እያላቸውና አምነውበት በራሳቸው ፍላጎት፣ በራሳቸው ገንዘብና ጉልበት፣ በራሳቸውና በራሳቸው ብቻ እንጂ በዚህ አይነቱ መንፈሳዊ ተግባራት በኩል እኛ ያደረግነው አንድም እገዛ የለም፡፡በዚህ በኩል የወሰድንባቸው እንጂ

የሰጣናቸው አንዳች ነገር የለም፡፡ቀደም ባለው ዘመን ለማታለያ አንዲት የብር ደወል ብቻ መላኳን አውቃለሁ፡፡

‹‹እያችሁ?የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ ነው፡፡ኢትዮጵያ ቅድስት አገር ናት የሚባለውም ከመሬት ተነስቶ አይደለም፡፡እኛ እውነቱን እናውቃለንና፤ይህን የሚሉትን የአገሪቱን ዜጎች አባባላቸውን ኢ አማኒ የሆኑ ምሁራኖቻቸው እንዲያጣጥሉባቸው እናደርጋለን፡፡ እንጂ አገሪቱ.....ይቺ ናት!

‹‹እያችሁ?ይህ ሁሉ ስራ በዚያ በጓላ ቀሩና በተናቀው ብሎም ባልተማረው የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ የተከናወነ ነው፡፡ሃብቱም ንብረቱም ከዚህ እሳዛኝ ህዝብ የተገኘ እንጂ ከሌላ አይደለም፡፡ልብ ብላችሁ ተመልከቱ!እነዚህ ሁሉ የዘማሪያንና የካህናት ያማሩ የተንቆጠቆጡ፣ አልባሳት፤እነዚህ ሁሉ ፀናፅሎችና የወርቅ መስቀሎች፣እነዚህ ሁሉ ውድ ምንጣፎችና መጋረጃዎች፣ከበሮዎች ሳይቀሩ ከሰማይ የወረዱ አይደሉም! ከመንግስት ካዝና በወጣና በተሰጠ ገንዘብ የተገዙና የተዘጋጁም አይደሉም፡፡ከዚህ ባዶ እግር ህዝብ በፈቃደኝነት ከተሰበሰበ ገንዘብ የተሰሩ፣ የተገዙ፣ የተሰፉና የተዘጋጁ ናቸው፡፡

እድባራቱን እንዲህ አሳምረው ገንብተው፣ውስጣቸውን ባማሩ መንፈሳዊ ስእሎች አስውበው፣ካህናቱንና አገልጋዮችን እንዲህ አሳምረው ያስቀጠሉ ህዝቦች ናቸው፡፡

‹‹እነዚህ የቤተክርስቲያን ሰዓሊዎች ስዕልን የት ተማሩት? የቀለምን ጥበብስ እንዴት አግኝተው እንዴት ቀመሙት?እነዚህን የቅርፃ ቅርፅ ባለሙያዎችስ ማን አስተምሯቸው ይህን ሊሰሩ ቻሉ?እነዚህን ሸማኔዎችስ ማን የስፌትን ጥበብ አስተማራቸው? እነዚህን ግንባታዎች የገነቡ ባለሙያዎችንስ ማን የግንባታ ጥበብ አስተማራቸው?የዜማ ጥበብንስ ከየት አመጡት?እንዴት ቀመሩት?በአገሪቱ ውስጥ የትኛው የስነጥበብና የኪነ ጥበብ ትምህርት ቤት ነበረ?....የእጅ ሙያ እንደ ነውር እንዲቆጠር ባያደርጉስ የት ይደርሱ ነበር?...ራሳቸውን እንዲንቁ፣በራሳቸው እንዳይኮሩ ባናደርግ ኖሮ የት ይደርሱ ነበር?ተመልከቱ!ይህ ሁሉ ለመንፈሳዊ ግልጋሎት የሚውል ጥበብ ከየት ተገኘ?

‹‹በእነ ሰለሞን ዘመን ጥቂት፤በጣም ጥቂት ቁሳቁስ የተለዋወጡበት አጋጣሚ ነበረ፡፡ያ ግን በትምህርት የተሳሰረ፣ በመማማር ላይ የተመሰረተና ይህ ነው የሚባል ውርርስም፣ቀጣይነትም፣ ያልነበረው ነው፡፡ታዲያ ይህ ሁሉ ምንድን ነው? ከየትስ መጣ?ከሌላው ዓለም የተለየውስ ለምንድነው?ምላሹ ግልፅ ነው!ልክ እኛ ከልዑላችንና ከልዑላችን ጭፍሮች ጋር እየተገናኘን ጥበብና እውቀት እየተለገስን ዓለምን እንዳስለጠንነውና የጥበብ ውጤቱ የሰዎች ግኝት ተደርጎ እንደሚታሰበው ሁሉ፤የነሱም መንፈሳዊ ሊቃውንት ከበላይ አካሉ መንፈሳዊ ጭፍሮች ጋር በፀሎትና

በልመና እየተገናኙ፣ ጥቆማ፣እርዳታ፣እውቀትና ጥበብ እየተለገሱ የሰሩትና!የሰዎች የጥበብ ውጤት ተደርጎ እንዲታሰብ ያደረጉት ነው።
‹‹አያችሁ?ኢትዮጵያውያን የበላይ አካሉ በደንብ ይመለክ ዘንድ ይህን ሁሉ የማይታመን መንፈሳዊ ቦታና ቤተ መቅደስ መገንባት ችለዋል።ይህ ደግሞ ያለ ህዝቡ ትብብርና ድጋፍ፣ያለ ህዝቡ ገንዘብና ጉልበት፣ የሚሰራና የተሰራ አይደለም።።በዚህ ሁሉ ስራ በየዘመናቱ ሳይሰለጥንና ሳይሻሻል የኖረው ህዝብ አሻራ አለበት!
የኢትዮጵያ ህዝቦች ራሳቸው ሳይሰለጥኑ አድባራትንና ገዳማትን የሚያሰለጥኑ፣ራሳቸውን ሳያከብሩ አምላካቸውን የሚያከብሩ፣ለራሳቸው ማደሪያ ሳይኖራቸው ለበላይ አካሉና ለተከታዮቹ፣ለፃድቃን ሰማዕታቱ መቅደስ አስውበው የሚገነቡ፣ለራሳቸው ሳያጌጡ ቤተክርስቲያንን በወርቅ የሚያስጌጡ ህዝቦች ናቸው።።ለራሳቸው ሳይበሉ መንፈሳዊ አገልጋዮችን የሚያበሉ ነበሩ!ደግሞም አያፍሩም አሁንም፣ወደፊትም እንዲያ ሆነው መቀጠል ይፈልጋሉ!
‹‹አያችሁ?ኢትዮጵያውያን ለራሳቸው ባህር ዛፍ ቆርጠው ቤት ሲሰሩ፣ ለቤተክርስቲያኑ ግን ፅድና ዝግባ በቅርፅ የሚጠርቡ ናቸው!ለራሳቸው ልብስ ሳይለብሱ ታቦታትን ወርቅ የሚያለብሱ ናቸው!እነሱ እየተራቡ ሰፊውን መሬት ለቤተክርስቲያን ግልጋሎት እንዲውል የሚሰጡና፣ እራሳቸው አርሰው እራሳቸው ምርቱን ሰብስበው የሚያስገቡ ናቸው!የራሳቸው መሬት በመንግስት ሲወረስ ዝም ብለው፣ የቤተክርስቲያን አጥር ጫፉ ሲነካና መሬቱ ለልማት ሲፈለግ እየሞቱ ተከላክለው የሚያድኑ ናቸው!
‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ ለራሱ ባርኔጣ ሳይኖረው በዝናብና በፀሀይ እያረሰ፣ በሃሩር እያጨደ፣ ለቤተክርስቲያን ግን የወርቅ ጥላ ገዝቶ የሚሰጥ ህዝብ ነው!ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ ተከስቶ ሰዎች በውሃ እጦት እየሞቱ፣ አጠገባቸው እንዲሁ የሚፈስ የቤተክርስቲያን ፀበል እየተንዠቀዠቀ እየፈሰሰ እያዩ ሳይጠጡ የሚሞቱ ናቸው!ያን ጠጥተው ነብሳቸውን ማቆየትና መትረፍ እየቻሉ፣ፀበል እናረክሳለን ብለው፣ብንጠጣው አምላክን ማርከስ ይሆናል ብለው፣ እንዲያ እየፈሰሰ እያዩ ንክች ሳያደርጉት በጥም ተቃጥለው የሚሞቱ ህዝቦች ናቸው!ይህ ህዝብ ከሌላው አገር ምዕመን ለምን ተለዩ?የየትኛው አገር አማኝ ህዝብ ነው እንዲህ የሚያደርገው?የየትኛው አህጉር ህዝበ ክርስቲያን ነው እንዲህ ራሱን ጥሎና ራሱን ትቶ ለበላይ አካሉ ቅድሚያ የሰጠ?አሁን ድረስስ ቅድሚያ የሚሰጥ?
‹‹ታዲያ የኢትዮጵያ ህዝብ ልዩ ህዝብ አይደለም?የበላይ አካሉስ ከሌላው አገር ህዝብና ከኢትዮጵያ ህዝብ ማንን ይምረጥ?ማንን ለይቶ በልዩ ዓይኑ

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ይይ?እና!? ኢትዮጵያ ቅድስት አገር አይደለችም ትላላችሁ??? ቅድስት አገር ለመባልስ ይህ ሁሉ በወርቅ የተቆጠቆጠ ገዳማትና አድባራት በቂ መመዘኛ አይሆንም? ቅድስት አገርና ቅዱስ ህዝብ ለመባልስ ከዚህ በላይ መመዘኛ የበላይ አካሉ ያለው ይመስላችኋል?

ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከኬንያ ህዝብ የሚለየው።ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከእንግሊዝ ህዝብ የሚለየው።ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከሁሉ አገር ህዝብ የሚለየው።በተረፈ ሁሉም ህዝብ አንድ አይነት ህዝብ ነው!አንድ አይነት ፍጡር ነው!የበላይ አካሉ ኢትዮጵያውያንን ብቻ አይደለም የፈጠረው።መላውን የዓለም ህዝብ ነው!መላው የዓለም ህዝብም ለእሱ እንዲህ እንደ ኢትዮጵያውያን እንዲሆንለት ይፈልጋል።በማንባታ ብቻ ሳይሆን በማመን ደረጃ!በትሁትነትና በፈላጊነት ደረጃ!በደንብ እየገባችሁ እንደሆነ ተስፋ አለኝ!

‹‹እምን!የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉንም ጥበብና እውቀት፣ያለውን ጉልበት፣ ጊዜና ሃብት፣ለራሱ ሳይሆን ለበላይ አካሉ መንፈሳዊ ግልጋሎት ሲያውል የኖረ ህዝብ ስለሆነ ነው አድባራትና ገዳማቱ እንዲህ አምረው ህዝቡ የተራቆተው።ሁሉን ነገር ለበላይ አካሉ ሰጥቶ ነው ህዝቡ የታረዘ የተራበው።ሲራብ ደግሞ ወደኛ መምጣት ጀመረ።

‹‹ምንም ይሁን ምን ግን፤ የኢትዮጵያ ህዝብና የአገሪቱ የሀብት ምንጭ፣ የአገሪቱ መሬትና ማዕድን፣ሁሉም ነገር ተጠቃሎ ለበላይ አካሉ የተሰጠ ሆኖ ነው የቆየው።አሁንም እንደዚያ ነው ያለው።ሁሉን ነገር ከነህዝቡ የበላይ አካሉ ለራሱ ግልጋሎት እንዲውል ነው ያደረገው።እንዲያ ሆኖ እንዲቀጥልም ነው የሚፈልገው።

‹‹የኛ ልዑል ግን ሁሉን ነገር ለኛ ሰጥቶ፣ከሉ እኛን አስቀድሞ፣ ጥበብ እየሰጠ፣በጥበባችን ውጤት ጠግበን እንድንበላ፤ ሰልጥነን እንድንኖር አድርጓል።

‹የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉን ነገር ለበላይ አካሉ እንደሰጠና ራሱንም ለበላይ አካሉ እንዳስገዛው ሁሉ፣እኛም ለልዑላችን እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ ነው መሆን ያለብን፣የሚል መልዕክት በዚህ አጋጣሚ ማስተላለፍ እፈልጋለሁ ክቡራን።

‹‹ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲህ ኋላ ቀር ሆኖና በተፈጥሮ ብቻ ተወስኖ፤ እህል አምርቶ በልቶ፣ በተረፈ ምርቱ በሰራው ቤት እየኖረ፣ ምርቱን ከብት እያነደደ የኖረው፤ እግርና እጁ ተሰንጣጥቆ አፈር መስሎ የኖረውና እየኖረ ያለው፤ በንቃተ ህሊና ከኛ አንሶ ሳይሆን፤ እውቀት፣ ጥበብና ጉልበቱን ሀብቱንም ማንነቱንም ጭምር ለበላይ አካሉ ስለሰጠና የበላይ አካሉን ስላስቀደመ ብቻ ነው የሚለውን እውነት ነው በዋናነት ልገልፅላችሁ የፈግሁት።ስለዚህ አቅልላችሁ አትዩት ነው!

ፍሥሐ ያዜ

‹‹ልብ አድርጉ!በዩንቨርስ ህግ ሰው የዘራውን ያጭዳል የሚል ቋሚ እውነት አለ፡፡ይህ ህግ ነው፡፡አመንንም አላመንንም፤ ፈለግንም አልፈለግንም፤ በተፈጥሮ ህግ የድርጊት ውጤት ሳይገኝ አይታለፍም፡፡አይነትና መጠኑ ዘመንና ጊዜው ይለያይ እንጂ ሰው የዘራውን ያጭዳል፡፡ይህ ራሱ የህበሾች ቀደምት ተረት ነው፡፡እናም ኢትዮጵያውያን እስካሁን ድረስ ባለው ሁኔታ የዘሩትን እያጨዱ አይደለም፡፡እንዲህ ራሳቸውን ከነሁለንተናቸው ከነምድራቸው ለበላይ አካሉ ሰጥተው ያገኙት ምላሽ ረሃብ፣ድርቅ፣ችጋር፣ ኋላ ቀርነት ብቻ ነው፡፡ለበላይ አካሉ ያን ሁሉ አድርገውና ሰጥተው ምግባቸውን ከኛ የሚለምኑና የሚቀበሉ ናቸው፡፡ከልዑላችን የተሰጠንና ያገኘነው እየተሰጠንም ያለው ከኛ አልፎ ለነሱ ተርፏል፡፡ይህንንም ልተወው...፡፡ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ የዚህን ሁሉ ምላሽ የሚያገኝበት ዘመን አለ፡፡ምድራቱም እንደዚያው፡፡ይሄን ማወቅ አለብን፡፡ይሄን ማወቅ ሽንፈት አይደለም፡፡ይልቁንም ይሄን አለማወቅ ነው ሽንፈት የሚሆነው፡፡

‹‹ደግሞም አስታውሱ እኛ የልዑላችንን ድል ማድረግ እንደምንፈልገውና እንዳረጋገጥነው ሁሉ፤እነሱም የበላይ አካሉን ድል ይፈልጉታል፡፡ድል እንደሚያደርግም እርግጠኞችም ናቸው፡፡ያን የማግኘት ዕድላቸውን መዝጋት ደግሞ ከኛ የሚጠበቅ ዋና የቤት ስራ ነው፡፡

ልዑላችን የኛንና የእናንተን የሰዎቹን እገዛ እንደሚፈልግ ሁሉ፤ የበላይ አካሉም በተመሳሳይ ሰው ይፈልጋል፡፡ከሰውም ታማኝ ሰው!ከሱ የበታች ካሉ ጭፍሮች ጋር በአንድ ቋንቋ የሚግባባ ታምኖ የኖረለት ሰው!ወይም ህዝብ!

‹‹እነዚህ እያሿሿርኩ በስክሪኑ ያሳየኋችሁ ብዙሃኑ ኋላ ቀር የኢትዮጵያ ህዝቦች ናቸው፡፡ጎን ለጎን ያያችኋቸውም የህዝቡ የጥረት ውጤት ናቸው፡፡ ሆኖም የኛ ትጋትም ሆነ ስጋት ስለ እነዚህ ኋላ ቀር ብዙሃን የኢትዮጵያ ህዝቦች አይደለም፡፡ስለ አድባራቱም አይደለም፡፡ነገር ግን በነዚህ 40 ሺ በሚደርሱ አድባራት መሽገው ያሉ መንፈሳዊ ሊቃውንት ጉዳይ ነው የሚያሳስበን፡፡ስጋታችንም እነሱ፤ትጋታችንም ለእነሱ ነው፡፡

በእነዚህ ውስጥ የመሸጉ የበላይ አካሉንና የጭፍሮቹን እገዛ በማግኘት አገሪቱን ለመታደግ የሚሞክሩ አካላት አሉ፡፡

‹‹ለዚያ ነው፡፡እንጂ .....ይህን ሁሉ ስሩ፣ አደረጉ፣ ስንል የተሰራው አሳስቦን ወይም አስቀንቶን ሳይሆን፤ሌላ እኛን መመከት የሚችል ጥበብ፤ ገና ያልተጠቀሙበትና ዘመን አስልተው፣ጊዜውን ጠብቀው፣ ለመጠቀም የተዘጋጁበት ምሽግ መኖሩን ለማሳወቅ ነው፡፡እነዚህ በውስጡ ያሉት ሰዎች ከበላይ አካሉ ጋር ጥብቅና ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ፤ የዓለም ውድ ቅርስ ሆኖ በብዙዎች የተፈለገ፣ነገር ግን ዛሬ ድረስ ደብዛው የጠፋን የበላይ አካሉ ውድ ንብረት እንደሆነ የሚነገርለትን፤ብቻውን

የሚዋጋን ዕላት ሳይቀር ሰውረው በሚስጥር ይዘው የቆዩ ናቸው! መሰሪነታቸው እዚህ ድረስ ነው!ይህ ለልዑላችን ክብዶ ሳይሆን፤በኛና በእናንተ በሹማምንቱ ተፈልጎ መገኘት ያለበት በሰው የሚሰራ የቤት ስራ ስለሆነ ነው።እነሱን ነው ማጥመድ የምንለው።እንጂ ህዝቡ ይህ ነው፤ ህዝቡ እንደዚህ ነው!ምሬሩን አስጥለን ረሃቡን በጣፋጭ በርገር አስወግደን፤ ጥማቱን በጭማቂና በውስኪ ቆርጠን፤ራቁቱን የሀር ካፖርት አልብሰን፤ ለተሰነጠቀ እግሩ ምቹ ጫማ፤፤ለሻከረ ቆዳው ቅባት፤እየሰጠን እንደ ከብት መንዳት ያቃተን አይምሰላችሁ!በሚዘሩት ዘር መርዘን ማጥፋትም እንችላለን።በከተማ የሚኖረውን ህዝብም በአንድ ሌሊት ጠርተን ማምጣት እንችላለን።ምሁራኖቹ በበላይ አካሉ ሳይሆን በኛ የሚያምኑና የሚታመኑ ናቸው።ለኛ የተለየ ክብር ያላቸው ናቸው።የከተማው የሐይማኖት ሊቃውንት በኛ ስር ማድረግ የቻልነው በቀላሉ ነው።ሌላውንም በሌላ መንገድ እየገባን እናጠምደዋለን፤እናጠምቀዋለን!ግን ያ ብቻውን በቂ አይደለም።ዋናዎቹ ያልኳችሁ ናቸው።እነሱና ተራው ህዝብ የማይተዋወቁ መስለው፤ነገር ግን ይተዋወቃሉ።እነዚያ ዋና መሰናክሎቻችን ለአገሪቱና ለህዝቡ ግድ የሌላቸው መስለው ተደብቀው እየኖሩ፤ነገር ግን ግድ ያላቸው ሆነው የሚገኙ ናቸው።ህዝቡ ያለነሱ እነሱም ያለህዝቡ ተራርቀው እየኖሩ፤ነገር ግን እርስ በርስ የሚጠባበቁና የሚከባበሩ ሆነው የሚገኙበት ሁኔታ ያጋጥማል።

‹‹የኛ ሰዎች በሆኑ የበላይ አለቆቻቸው፤ማለትም በዋና ዋናዎቹ ጳጳሳት ስር ሆነው የሚመሩ ናቸው።ሆኖም ይህን እንደምሳሌ ያነሳሁላችሁን ብቻውን የሚዋጋ የተባለለትን ዕላት እንኳ ዋናዎቹ ጳጳሳት ትክክለኛ ቦታውን አያውቁትም።ብዙ ጊዜ ትክክለኛ ቦታውን በእርግጠኝነት እንደሚያውቁ ገልፀውና ጠቁመው፤ያለነሱ ትእዛዝ ማንም ካህን ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር እንደማይችል አረጋግጠው፤በተባለው ቦታ ከራሳቸው ጋር ስንሄድ ግን የለም።መቶ ጊዜ ከራሳቸው ጋር እየሄድን ሞክረናል ልላችሁ እችላለሁ።ግን እነሱም ተገርመው እኛም ሳናገኘው እንመለሳለን።ለምን? ብትሉ ምላሹ ቀደም ሲል ያስረዳኋችሁ ነው።

‹‹ከዘመን ዘመን እየተመራረጡ የሚቀባበሉ፤የጥበባቸው ልክ የማይታወቅ፤ የእውቀት መጠናቸው ያልተለየ፤ቦታቸው በየጊዜው የሚቀያየር፤አድፋጭና አሳጋጭ መነኩሴዎች አሉ።እነሱን ለማጥመድ በቀጥታ ሳይሆን በተዛዋሪ መሄድ የግድ አስፈላጊ ሆኗል።ቅርንጫፉ መመልመል አለበት ክቡራን!ግንዱ መቆረጥ አለበት!ከዚያ ስሩ ይቆፈርና የስሩ መዳረሻ ይለያል። የስሩን መዳረሻ ለማግኘት መጀመሪያ ቅርንጫፉን መመልመል አስፈላጊ ነው።ቅርንጫፉን መመልመል ማለት፤የተራውን ህዝብና ምዕመን እገዛና

ደባቂነት ማሳጣት ማለት ሲሆን፤ግንዱን መቆራረጥ ደግሞ ከስሩ ጋር የተሳሰሩ በኛ ስር መስለው ያልሆኑትን መለየት ማለት ነው!
ከቂስ እስከ ጳጳስ፣ከዲያቆን እስከ መጋቢ፣ ከመነኩሴ እስከ ባህታዊ፣በቅርፅ በቅርፅ እየተቆረጠ መፈለጥ አለበት!እንዲህ አድርገን ቅርንጫፉንና ግንዱን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን፤የኛ ተባባሪ አድርጎ ስሩንም ለመቆፈር የሚግዝ ኢትዮጵያዊ ሃይል መፍጠር አስፈላጊ ነው!ይህ ስራ በቤተክርስቲያናችን በኩል ሲሰራ የቆየና ውጤት እያስገኘ ያለ ነው፡፡ስሩ ግን እንደ ትንሽ ባህር ዛፍ መንገድ ተሻግሮ ሄዶ ግዙፍ ጉቶ ሆኖ ሊገኝ የሚችል፤ ብዙ ድካም የሚጠይቅ ነውና በራሳቸውና በኛ ሰዎች የጋራ ትብብር የሚቆፈርና፤ እየተመዘዘ፣ ተሽራ·ርፎ እየተፈለጠ፣ መፈረካከስ የሚኖርበት ነው!ይህን ስራ እየሰራን ያለንበት ወቅት ነውና ለአፍታ እንኳ ከኢትዮጵያ ላይ ትኩረታችን ማንሳት የለብንም! ስሩ ስር ሰዶ መልሶ ሽቅብ ከወጣ ሽቅብ እንቆፍራለን፤ ስሩ ቁልቁል ወርዶ ካየን ቁልቁል እንቆፍራለን፡፡ስሩ አልፎ ሄዶ ሃይቅ ውስጥ እንደደረሰና እዚያ እንደመሸገ ካወቅን ሃይቁን እናደርቃለን፡፡ይህን የምናደርገው ለቁሳቁስ ፍለጋ ብቻ አይደለም፡፡ሁሉም ግልፅ ሆኖና ግልጥልጥ ብሎ መታየት ስላለበት ነው!ቤተ ክርስቲያንም ይሁን ገዳም፣ መስጊድም ይሁን የድንኳን ቤተ አምልኮ፣ ቢሮም ይሁን መንደር፣ ወንዝም ይሁን ሃይቅ፣ጫካም ይሁን ሸለቆ፣ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝቶ የበላይ አካሉን ለማምለክ ግልጋሎት ላይ እስከዋለ ድረስና በኢትዮጵያ ምድር እስከተገኘ ድረስ መመንጠር ይኖርበታል!
‹‹ይህን የምናደርገው ለልዑላችን አስፈላጊ ስለሆነ እንጂ አገሪቱና ህዝቧ ጠላታችን፣ ስጋታችን፣ ስለሆኑ አይደለም፡፡
‹‹ይህ ሁሉ በዋናነት የእነሱ ውጤት ነው ብለናል፡፡ከትውልድ ትውልድ እየተቀባበሉም እዚህ ደርሰዋል፡፡አስደሳቹ ነገር ግን የቀድሞዎቹ እንጂ እየተቀባበሉም እዚህ ደርሰዋል፡፡ ...

የከተማውን ነዋሪ እንደሌለ ቁጠሩት፡፡
እገሪቱ ውስጥ ሰፊው የአሁኑ ትውልድ ምዕመን፤ በተለይ ብዙሃኑ ኦርቶዶክስ ነው፡፡90 በመቶው መጽሐፍ ቅዱሱን የማያውቅ ነው፡፡ገልጦት የማያውቅ ነው፡፡እንዲሁ በልማድ አምልኮ ያለ ነው፡፡ለምን?የከተማዎቹ ሊቃውንት ባይብሉን እንዳያውቅ ስለሚፈልጉና ስለማያስተምሩት ነው፡፡ ወንጌል ስለማይሰበክ ነው፡፡የከተማዎቹ ቤተክርስቲያናት እርስ በርስ በገቢ ስለሚፎካከሩ አድባራቱ ተገንብቶ የተሰየመባቸውን የፃድቃን ሰማእታት ገድል እና ተዓምራትን እንጂ ወንጌል አይሰብኩም፡፡ወንጌል ያልተሰበከለትና በወንጌል ያላመነ ምዕመን ደግሞ ለኛ ጨርሶ ስጋት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያን ስላልሆነ፡፡

‹‹አዎን! አስደሳቹ ነገር ይህ ነው!እኛን የሚገዳደረን፣መሰናክል ሊሆንብን የሚችል፣መጽሐፍ ቅዱሱን ያወቀና ያመነ እንጂ፤እንዲሁ በልማድና በስም ክርስቲያን ተብሎ የሚጠራው ህዝብ አይደለም።ቃሉን ያወቁ ብቻ ናቸው ጠላቶቻችን ሊሆኑ የሚችሉት።ሌላው ገለባ ነው። በእስልምናም ብትሄዱ ተመሳሳይ ነው።ቁራንን የማያውቅ ሙስሊም ሊገዳደረን አይችልም።ያወቀ ግን ከቃሉ ጋር እያመሳከረ ሽብርን ቁራን አይደግፈውም፣ ወዘተ…እያለ መገዳደሩ አይቀርም።ክርስቲያኑም እንደዚያው።

‹‹ለማንኛውም ግን ስሩ ያልካችሁ መዳረሻው መታወቅ አለበት።የስሩን መዳረሻ ለማግኘትም በዮትኛውም የታሪክ አጋጣሚ በይፋ በመንፈሳዊ ተግባራቶቻቸው ላይ ጣልቃ ሳንገባ እንደቆየነው ሁሉ፤አሁንም በዚያ መንገድ ገብተን አይደለም የምናገኘው።ቀደምት አባቶቻቸው በራሳቸው ጥረትና በበላይ አካሉ አጋዥነት የገነቧትን፤በመጨረሻም ለበላይ አካሉ ሊያውሏት ያሰቧትን፤መንፈሳዊ ነገር በሙሉ በራሳቸው እጅ፣በራሳቸው ፍላጎት፣ለራሳቸው ግልጋሎት ሲሉ እንዳደረጉት አድርገን ነው እጃችን የምናስገባውና ዓላማችን ዳር የምናደርሰው።በኛና በእናንተ በኩል በዋናነት የበላይ አካሉን ከህዝቡ የመለየት ተግባር ይፈፀማል።ሌላውን ራሳቸው እንዲቀጥሉበት ይደረጋል።

በሌላ አገላለፅ ቀጥታ በሐይማኖታቸው ሳንገባ፤ በፍላጎታቸውና እምነውበት እንድንገባ ዕድሉን እንዲሰጡን እናመቻቻቸዋለን። ይህን ስናደርግም ዓለማዊ መንገዶችን በመጠቀም ነው።የአገር ለአገር ግንኙነትን መሰረት በማድረግ ነው።በዘመናዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣በአስተዳደራዊ ዘርፎች፣በልማትና በቴክኖሎጂ፣ በእርዳታና በሌሎች በሁሉም ዘርፎች አማካኝነት ነው።ለምሳሌ ‹‹ይህን ቦታ አልሙና ከድህነት ውጡ›› ብለን ገዳም አስፈርስናል።ለመስኖ ልማት ብለን ወንዝና ሃይቆችን አድርቀናል፤ ነው።ከድህነት ውጡ በሚል፤የሚፈለገውን ስትራቴጂካዊ ቦታ ለልማት መዋል እንደሚችል በመጠቆም፣ሊለማ እንደሚችል የሚያሳየውን ጥናትም አብሮ በማቅረብ፣ለልማቱ የሚውል የገንዘብ እርዳታ በመስጠት፣ እየተባለ ለማረጋገጥና ሌላ እርዳታ ለመስጠት በሚል እየሄዳችሁ እየጎበኛችሁ ወንዙ ፊት ለፊት ሄዶ መላቱም አስፈላጊ አይደለም።በዚህ አይነት ሂደት ነው ‹‹ስለዚህ ሂደቱ በዚህ የሚቀጥል እስከሆነ ድረስ ገንዘቡን በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን መድረቁን ታረጋግጣላችሁ፣ሪፖርት ታደርጋላችሁ።እንጂ ከዚህ ህዝብ ጋር ሁሉንም ነገር ግልጥልጥ አድርጎ የሁሉንም መዳረሻ ማወቅ የሚቻለው። እያሰባችሁ አትዘናጉ የሚለው ዋና ነጥቤ ሲሆን፤በንቃተ ህሊና ከኛ ይሻላሉ ሲባል ያጉረመረማችሁትም፤ማጉረምረማችሁን አቁማችሁ፤ አገራቱ

ከምንለው በላይ ስጋታችን መሆኗን ተረድታችሁ፣ እንድትበረቱ የሚለው ጥብቅ ማሳሰቢዬ ነው።

በዛሬው ጉባኤ ለመሳተፍ እዚህ አዳራሽ ውስጥ የተገኛችሁ ክቡራን የየዘርፉ ተወካዮች፤እንዲሁም የሃያል አገራት መሪዎች ያችን አገር በየዘርፉ እንዴት እንዳጠመድናት፣ምን አቅደን ምን እየሰራን እንዳለን፣ እንዲሁም ከእናንተ ምን እንደሚጠበቅ በሰፊው ተብራርቶላችኋል።ስለዚህ ከትንሿ የአማርኛ ትርጉም መተግበሪያ ጀምሮ፤እስከ ትልቁ የኒውክሌር ጠመዳ የሚደርሰውን ተግባራዊ እንቅስቀሴ በሙሉ በጥንቃቂ ለማስኬድ መዘጋጀት ይኖርባችኋል።ጥቃቅን እየመሰላችሁ በንቀት የምታልፉት አንድ ነገር መኖር የለበትም!

‹‹ኢትዮጵያውያን እኛን እየመሰሉ መሄድ ያለባቸው ትክክለኛ ወቅት ላይ ተደርሷል።በቋንቋ፣በባህል፣በአመለካከት፣ በአስተሳሰብና በሌሎች ዘርፎች ጭምር ከኛ ጋር ማወራረስ አስፈላጊ ሆኗል።ስለዚህ በየዘርፉ በተሰማሩና በሚሰማሩ አባላቶቻችን ጋሬጣውን ሁሉ እያስነሳን ወደ ውርርሱ ማምጣት አለብን።ለዚህ ደግሞ ወደኛ ለባርነት፣ ለትምህርት፣ ለተሻለ ኑሮ፣ በሚል የሚጎርፈውን ኢትዮጵያዊ ጨምሮ፤ሌላውን በኛ ዘንድ ክርሞ የሰለጠነ ምሁራንን ሳይቀር መጠቀም አለባችሁ።

ከኛ ጋር በባህል ሳይወራረስ ብቻውን የኖረና፤ቀስ በቀስ እያባበልን ሰርገን ስንገባበት የኖረውን ይህን ህዝብ፤ ዘመኑ ሲደርስ የግድ አጠናክሮ ቀጥሎ በክባችን ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።ይህ የማወራረስ ተግባርም የእነሱን የቆዩ ልማድ ወግና ባህል ከመሸርሸር የሚጀምር ነው።

‹‹ለምሳሌ ማክሮ 6 አምሃሪክን ሙሉ በሙሉ መተርጎም አልቻለም ተብሏል።በዚህም አዝናችኋል፤አዝኛለሁ።በነገራችን ላይ ያ እያሳሰባችሁ። በዚያ እንዳታዝኑ።በቅርብ እናሳካዋለን!

ነገር ግን መተግበሪያው ለማክሮ 6 ብቻ አይደለም መስራት ያለበት። በዋናነት የህዝብ ለህዝብ ውርርስ አስፈላጊ ስለሆነ ለዚያ ነው በጣም ሊጠቀመን የሚችለው።ለእናንተ ለሹማምንቱ ምንም ችግር የሚፈጥር አይደለም።እናንተ ውስጥ በማብራት ብቻ ግእዝንም አማርኛንም ከማወቅ አልፋችኋል።ሆኖም ማክሮ 6 ይህን ማድረግ አልቻለም ሲባል ማዘናችሁ አልቀረም።እናንተ ያዘናችሁት ማክሮ 6 ያን ማድረግ ባለመቻሉ ብቻ ነው። እኔ ያዘንኩት ደግሞ በሌላ ነው።መተግበሪያው በዋናነት አሁን ለምለው ውርርስ ወሳኝ ግብዓት መሆን ይችላልና ለዚያ ነገር ጥቅም ላይ መዋል ባለመቻሉ ነው የተበሳጨሁት።

ከኢትዮጵያውያን ጋር የህዝብ ለህዝብ ውርርስ ገና ብዙ ስራ የሚቀረው ነውና ለዚያ ሲባል መተግበሪያው የግድ አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን።እርግጥ ነው ውርርሱ በትርጉም መተግበሪያ ብቻ የሚመጣ አይደለም።ውርርሱ

በቋንቋ ብቻ አይደለምና፡፡ሆኖም መተግበሪያው ወሳኝ ግብዓት መሆን የሚችልበት ዘርፈ ብዙ ነገር አለ፡፡

‹‹ኢትዮጵያውያንን ወደ ክባችን ውስጥ ለማስገባት የሚደረገው እንቅስቃሴ ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ባህል፣ልማድ፣ወግ፣ሀይማኖታዊ አመለካከት፣ወዘተ….ቀስ በቀስና በዘዴ መናድ፣ መሸርሸር፣ አለበት፡፡ያ ደግሞ የእናንተ የጋራ ተግባር ነው፡፡

‹‹በተለይ በዚህ ጉባኤ ያላችሁ ባለሀብቶች፣ የሚዲያና የኪነጥበብ ሰዎች በደንብ አዳምጡኝ!

‹‹የመገናኛ ብዙሃኖች በሽፋን ስያሜያቸው እየገቡ፤ በመንፈሳዊ እውቀትና ትሁትነት ብቻ ተወስኖ የኖረውን ህዝብ፤በሳይንሳዊ ትንታኔ ታጅበው በሚቀርቡ ፕሮግራሞች ጠቃሚ የሆኑና የመሰሉ ትምህርቶችን እየሰጡ፤ ጎን ለጎን የህዝቡን ወጋወግ ቀስ እያደረጉ መሸርሸር ያስፈልጋል፡፡

ይህ ባህልንና ሐይማኖትን የመሸርሸር ጉዳይ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነና ውጤቱ ምን እንደሚመስል ለማስረዳት ጥሩ ምሳሌ ላንሳ፡፡ለምሳሌ ኢትዮጵያውያንን የልዑላችን ፍላጎት አራማጅና የዕቅዳችን አጋሮች እንዲሆኑ ለማድረግ ሲባል ከተከናወኑ ስራዎች ውስጥ ሳይሳካ የቀረውን የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን ውሰዱ፡፡ያለምንም ቅድመ ስራና ያለ ምንም ቅድመ ዝግጅት ወደዚያች አገር ሄዳችሁ ህጉን ለማስፀደቅ ሞከራችሁ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በቁጣ በታጀበ ተቃውሞ አስቆማችሁና ከስራችሁ ተመለሳችሁ!እኛንም አሳፈራችሁን!ስለዚህ ተራዘመና የአገባቡ ሂደት ሌላ መልክ መያዝ እንዳለበት ተወሰነ፡፡ለምን ከሸፈ?ቅድመ ስራው ስላልተሰራ!ባህልና ሐይማኖት ቀስ በቀስ እየተሸረሸረ እንዲሄድ የሚያደርገው ቅድመ አገባብ ስላልተከናወነ!ዘልላችሁ ሄዳችሁ ኢትዮጵያዊ ጌዮችን ሰብስባችሁ ‹‹የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ ህጋዊ ይሁን›› አላችሁና፤ ‹‹ያለዚያ እርዳታ ልታጡ ትችላላችሁ›› እያላችሁ ቀባጠራችሁ!ይህ ጉዳይ ለልዑላችን በጣም ወሳኝ የሆነና ተቃራኒነታችንን አውጀን በሱ ዘንድ የምንከብርበት ጉዳይ ሆኖ ሳለ፤ እናንተ ግን እንደ ተራና እንደ ቀላል ጉዳይ ቆጥራችሁ አካሄዱንና አገባቡን ባለማወቅ የከሸፈ ሙከራ አሳያችሁን!

‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ሲሰማ ብዙሃኑ ሁኔታውን ከስብአዊ መብትና ከነፃነት መብት ጋር እያይዞ እንዴት ሊያየውና ሊቀበለው ይችላል?ስለዚህ ደነፋ!እነሱ የሚያውቁት በበላይ አካሉ ገደብ የተጣለበትን መንፈሳዊ ህግ ብቻ ነውና ከመጽሐፍ ቅዱሱ ሰዶምና ገሞራ ታሪክ ጋር እያገናኙ በመተርጎም ሐጢያት ነው ብለው እሪሪሪ አሉ፡፡ለጊዜውም ቢሆን አስቆሟችሁ!አያችሁ?ህዝቡ ይሄ ነው!ነገር ግን ከዚያ በፊት ግብረሰዶማዊነት ሀጢያት፣ግብረሰዶማውያንም ሀጢያተኞችና ክፉ ሰዎች፣ መሆናቸውን የሚያምን ህዝብ መሆኑን ተረድታችሁ፤ አመለካከታቸውን

ፍሥሐ ያዜ

ማዕዳትና ማስተካከል ችላችሁ ቢሆን ኖሮ ከስራችሁ አትመለሱም ነበር፡፡ ያን ደግሞ ማድረግ ትችሉ ነበር፡፡ግብረሰዶማዊነት የህግ ከለላ ማግኘቱ በአንድ በኩል ዘመናዊነት፣በሌላ በኩል የዜጎች መብት፣ መሆኑን በተለያየ መንገድ ቀድሞ ማስተማር መቀስቀስ ያስፈልግ ነበር፡፡የፖለቲካ ምርጫ ሲካሄድ እንኳን ቅስቀሳ ያስፈልጋል!

ስለዚህ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከመግባታችሁ በፊት፣ጉዳዩ የዜጎችን ነፃ ፈቃድ አክብሮ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ እንጂ፤ ምንም ማለት አለመሆኑንና፤ ይልቁንም የዘመናዊነት መገለጫ እንደሆነ ቀድሞ ማስገንዘብ ያስፈልግ ነበር፡፡ይህን ማድረግ ደግሞ እጅግ ቀላል ነው፡፡ያን ኋላ ቀር ህዝብ ማጥመድና አመለካከቱን መሸርሸር ሲባል፤ከትንሿ ነገር ተነስቶ ቀስ እያሉ እያዘገሙ አእምሮውን ማጠብ ማለት ነው፡፡እንደ ሌላው አገር ህዝብ ባጭሩና በቀላሉ በማስረዳት ልታሳምኑት የምትችሉት ህዝብ አይደለምና ገና ብላችሁ መጀመር ነበረባችሁ፡፡

የግብረ ሰዶማውያንን ጥሩ ስብእናና የአኗኗር ዘይቤ፣ስልጡንነትና ነፃ ህይወት ወዳዶች መሆናቸውን፣የስነ ፅሁፍ ውጤቶች በሆኑ መፃህፍት፣ ፊልሞች፣አጫጭር ታሪኮች፣መሳጭ በሆነ መንገድ ማስነበብ ማሳየት ትችሉ ነበር፡፡አመለካከታቸውን ለማዕዳት ከዚህ ከትንሹ ተግባር መነሳት ያስፈልጋል፡፡

በዚያ ላይ ኢትዮጵያውያን ከተሜዎች ዘመናዊነትን ለመከረጅ የተዘጋጁ መሆናቸው በግልፅ ይታወቃል፡፡ይህን ከማወቅ መጀመር ነበረባችሁ፡፡

‹‹የስነ ጥበብ ውጤቶች ሰውን የመለወጥ ሃይል እንዳላቸው እኛም እነሱም እናውቃለን፡፡ኢትዮጵያውያን ማለት እኮ አንድ ፊልም ወይም ቴአትር አይተው፣ጥሩ ስብእና የተላበሰ ገፀባህሪ የተሰጣትን ተዋናይት፣ትወናዋን በብቃት መወጣቷን እያዩ የሚያለቅሱ፣መጥፎ ገፀ ባህሪ ተላብሶ የሚተውነውን ተዋናይ ባህሪ የሚጠየፉና የሚጠሉ ናቸው፡፡በገሃዱ ዓለም ኑሯቸው እንኳ ያው የሚመስሏቸው ናቸው፡፡ክፉ ሆኖ የተወነን ተዋናይ በየመንገዱ የሚሳደቡ፣ጥሩ ስብዕናና አሳዛኝ ታሪክ ተላብሶ የሰራውን ተዋናይ እድሜ ልካቸውን እንደወደዱት የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው፡፡85 % ተቀምጦ የቆጠረና ያልተማረና ገበሬ ቢሆንም 15 % ቱ የከተማ ሰው ፊደል የቆጠረና የተማረ፣ኪነ ጥበብን፣ ስነ ጥበብን፣የሚያውቅና የሚረዳ፤እንዲሁም የተጠማ ነው፡፡የኛዎቹን የእነ ሼክስፔርን መሳጭ ስራዎች ወደ ቋንቋው ተተርጉሞ ቀርቦለት ልክ እንደኛ የተመሰጠ፣ ያዘነ፣ ያነባ፣ ኢያጎን ያወገዘ፣ለዴዝዴሞና ያለቀሰ ህዝብ ነው ፡፡

‹‹የከተማውን ህዝብ ነው እንግዲህ እናንተ ልታሳምኑ ሄዳችሁ የነበረው፡፡ ምክንያቱም ከተሜው ካመነና ከተቀበለ መላው ህዝብ አመነ ማለት ስለሚሆን!እናና?በዚህ ዙሪያ ምን የተሰራ ቅድመ ስራ ነበር?በመሳጭና

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

በአስለቃሽ የፍቅር ታሪክ ብቻ እንባ የሚያራጩ የሌዝቢያንና የጌይ የፍቅር ታሪኮችን የሚተርኩ፣ ከተለመደው የተቃራኒ ፆታ ፍቅርና ጋብቻ ይልቅ የተመሳሳይ ፆታ ፍቅርና ጋብቻ እንዴት ጣፋጭ እንደሆነ የሚያሳይ ታሪክ ያለው ፊልም እንኳ አልተሰራም፡፡መፅሐፍ እንኳ በነሱ ቋንቋ እንዲተረጎም አላደረጋችሁም፡፡
ወይስ በኛ በኩል እንዲሰራላችሁ ፈለጋችሁ?በኛ በእንግሊዛውያን ዘንድ እንዲህ ያለ ፊልም አይሰራም፡፡እኛ ትኩረታችን በወሳኝ ጉዳይ ላይ ብቻ ስለሆነ፤ ለፊልም ብዙ ወጪ አናወጣም፡፡የከበርን የነገስታት ቤተሰብ መሆናችንን ነውና ዓለም የሚያውቀው በዚያው እውቀቱ እንዲቀጥል ስለምንፈልግ፤ ፊልሞቻችን የነገስታት፣ የልዑላንና የልዕልቶች የፍቅርና የቤተሰብ ታሪክ ላይ የሚጠነጥን ፊልም ነው የምንሰራው፡፡ስለ ዝርፊያ ስለ ጋንጊስተር ድብድብ አንሰራም፡፡ስለ ተመሳሳይ ፆታ ጋብቻና ፍቅር የሚያጠነጥን መሳጭ ፊልምም ልንሰራና ልናሳይ አንችልም፡፡
እናንተ እዚህ ያላችሁትና ሌሎች ባልደረቦቻችሁ የልጃችን የአሜሪካ የጥበብ ሰዎች ግን፤ ለዚህ ተግባር እንድታውሉት መርጠን በሰጠናችሁ ሰፊ የሆሊውድ ግዛት ውስጥ ሆናችሁ ያንን ሁሉ ታሪክ ስትሰሩ ይህ አይነቱን ወሳኝ ታሪክ ግን ገና አልነካችሁትም ማለት ይቻላል፡፡
‹‹ለምን እንደምትፈሩ አይገባኝም!የተመሳሳይ ፆታ ፍቅርና ጋብቻ ታሪክም ሆነ እውነታው እንዲሁም ሁሉ ነገሩ ከተቃራኒ ፆታ የበለጠ ማራኪና ጣፋጭ መሆኑን በተግባር እያያችሁት፤ እያደረጋችሁት፣ነገር ግን በፊልም ለመስራትና በመፅሀፍ ታሪኮች ለመግለፅ ትፈራላችሁ፡፡ ወይም ትፈሩ ነበር፡፡አሁን ግን በየአገሩ መብታቸው በህግ ሲረጋገጥ በዚህ ዘርፍም እኩል መብታቸው ተረጋግጧልና ሳትወዱ በግዳችሁ ትሰሯታላችሁ፡፡ስትሰሩም በዋናነት ለሌላው ዓለም ዘመናዊ ህዝብ ብቻ ሳይሆን፤ ለኢትዮጵያውያንም ጭምር እንዲደርስ በማድረግ ነው፡፡ስለዚህ እንደዚህ ባሉ ጉዳዮች ዙሪያ እየሰራችሁ፤ እንባቢውንም ሆነ ተመልካቹን በመመስጥ፣ተዋናዮቹን እንዲወዱ፣እንዲያፈቅሩ፤ በማድረግ፣ጉዳዩን ከአስደንጋጭነት ወደ ዘመናዊ መገለጫነት ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ያ እንኳ ጊዜ ቢወስድ ቢያንስ ጉዳዩ እንግዳ ሆኖ ማንንም ከማስደንገጥ ይልቅ የተለመደና አዲስ ያልሆነ ክስተት መሆኑን እያሳዩ እያስረዱ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡
እንዲህ ያሉ መሳጭና አስለቃሽ ብሎም አይረሴ ታሪክ በመፍጠርና በማሰራጨት በአንባቢውና በተመልካቹ ዘንድ ተወዳጅ በሆኑ ታዋቂ ተዋንያን እያሰራችሁ ቀጥላችሁ ቢሆንና እንደሌላው የሆሊውድ ፊልም ኢትዮጵያውያንም የሚያዩ የሚያነቡበት መንገድ ፈጥራችሁ ቢሆን ኖሮ ደንግጠው ባልመሳጧችሁ ነበር፡፡

ፍሥሐ ያዚ

ያንን አስለቃሽና አሳዛኝ፣ መሳጭና አይረሴ፣ የፍቅር ታሪክም ይሁን የቤተሰብ ታሪክ አድርጋችሁ ሰርታችሁ፣ ቢል ቦርድ በምትሉት የደረጃ ሰንጠረዥ አንደኛ ደረጃ ላይ አስቀምጣችሁ፣ ለዓመታት የቆየ ብትሉትና ሰፋ ያለ ፕሮፖጋንዳ ብትነዙበት፣ተዋናዮቹ በማስመሰል ሳይሆን በትክክል ተወደውና ተደንቀው፣ ፊልሙም ተወዶና ተደንቆ፣ ከፍተኛ የሆነና ማንም ያላገኘውን ገንዘብ ማግኘታቸውን ብታስራጩ፣ፊልሙ ያስገባውን ገቢም ከፍ አድርጋችሁ ይፋ ብታደርጉ፣ከተዋናዮቹ ውስጥም እዚህ ያሉ ቆንጃጅት ኢትዮጵያውያንን ብታካትቱ፣ ገቢውንም ችግር ውስጥ ላሉ ኢትዮጵያውያን ህፃናት መርጃ ብታደርጉ፣ቤተክርስቲያን ማደሻ ብላችሁ ስጦታ ብትሰጡ፣ ምን ይፈጠራል?

ይህን አይነት አንድ፣ሌላ አይነት አንድ፣እያደረጋችሁ ብታስኬዱት ኖሮ ነው መሸርሸር ትችሉ የነበረው።

አንጀሊና ጆሊና ቢዮንሴ ኢትዮጵያዊ ሴቶችን በሚማርክ አስደናቂ አለባበስ ለብሰው፣ወጣ ያለ አኳኋል ተኩለው፣ በዘናጭ የፀጉር ስታይል ደምቀው፣ ዝንጥ እምር ብለው፣በሌዝቢያንስ የፍቅር ታሪክ ዙሪያ በሚያትት ፊልም ላይ ፍፁም ፍቅረኞች ሆነው በደንብ እየተሳሳሙ ቢተውኑ ምን ይከሰታል? እምን፣ሽርሸራ ከዚህ ይጀምራል።ኢትዮጵያዊ የመሃል ከተማ ሴቶች ከሂል ጫማ ጀምሮ እስከ ሊፒስቲክ፣ እስከ አረማመድ፣ እስከ አለባበስ፣ እያዩ የሚማረኩ፣ እሱንም ለማድረግ ጉድጓድ የሚገቡ፣ እነሱን መስለው ለመታየት አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁና፣ሲኮርጁም የኖሩ ናቸው።ያንን ሲያደርጉ ከኖሩ ይህንንስ አይተው ከማድነቅና ከመከተል፣ባይከተሉ እንኳ ዘመናዊነት መሆኑን ወደ ማሰብ መምጣት የማይችሉ ይመስሏችኋል?

‹‹ብራድ ፒትና ጆይዚ በተመሳሳይ ድንቅና መሳጭ የጌይ ታሪክ በሚታተትበት ፊልም ተፋቅረው ቢላቀሱና፣በአሳዛኝና በአስቸጋሪ ሁኔታ አልፈው ሲጋቡ፣ በሰርጆሪ ሲወልዱ፣ ማሳየት ምን ችግር አለው?ተቀባይነት ያግኝም አያግኝም የልዑላችን ዓላማ ነውና መሞከር፣ ደጋግሞ መሞከር፣ ማለማመድ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያውያንን በዚህ መሰሉ መንገድ፣ ባህልና አቋማቸውን፣ልማድና ሐይማኖታዊ አመለካከታቸውን፣ኋላ ቀር አስተሳሰባቸውን፣ ካልነካካችሁባቸውና ቀደም ብላችሁ ካልሸራረፋችሁባቸው በቀር በቀላሉ ማሳመን ከበድበድ ሊላችሁ ይችላል።

‹‹በጊዜ ሂደት ቢያንስ አስደንጋጭነቱን ብቻ ከማሰብ ተላቅቀው፣ ከታዋቂ ሰዎች ተግባር ጋር ማገናኘትና መመሰጥ እንዲችሉ ማድረግ ሲቻል፣ ዘመናዊ ሰዎች ተግባር መሆኑን እንዲያስቡና ቀለል አድርገው እንዲያዩት አድርጎ ማለማመድ ሲቻል፣ የሰዶምና ገሞራን ምሳሌ ብቻ ይዘው

ማንነፀሪያ እንኳን ሳይኖራቸው ወደሚኖሩ ህዝቦች ሄዳችሁ ሞክራችሁና ፎርሻችሁ መጣችሁ!

‹‹እዚህ ያሉና እዚሁ ተወልደው ያደጉ ወጣት ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራዎቻቸውን ሆሊውድ እያስገባችሁ፣ ዝነኛ እንዲሆኑ እያደረጋችሁ፣ በደንብ መጠቀምና እንዳሻችሁ መንዳት እየቻላችሁ፤ለየአገሩ መንግስት ጉዳዩን በመተው፤እኛ በእርዳታ አስፈራርተን እንድናስፀድቅላችሁ ትፈልጋላችሁ::ያን ማድረግ እንችላለን::ግን ከዚያ ይልቅ አሁን ባልኳችሁ አይነት መንገድ ብትገቡባቸው ነው የተሻለና ውጤታማ ብሎም ቀጣይነት ያለው ሊሆን የሚችለው::አሜሪካ ከተቀበለች ወደው ሳይሆን በግድ ይቀበላሉ እያላችሁ የተዋችኋቸውን ኢትዮጵያውያንን፤ከህግ ከለላ ባለፈ፤ በተለማመደና በታመነበት መንገድ እንዲቀበሉት ማድረግ የተሻለ ነው:: በግድና በማስፈራራት ሳይሆን እንዲያምኑበት በማድረግ ማስረፅ ነው ጠቃሚ የሚሆነው::

ይህ ቀጣይ ስራችሁ ይሁን::ከዚህ ኋላ ቀር አመለካከታቸው መውጣት እስኪለባቸው ድረስ በየዘርፉ ልትዘምቱባቸው ይገባል::

‹‹ይህ ብቻ አይደለም::በየሚዲያው ከሚቀርበው የናሽናል ጂኦግራፊ ታሪክ ሳይቀር መነሳት አለባችሁ::ዛሬ አንበሳና ነብር ከታዩ፤ነገ ስለ በረዶና ስለ ውሽንፍር ሲወራ፤ ‹‹ከስድስት ሚሊዮን ዓመታት በፊት.....›› እያላችሁ በጥሩ የቪዲዮ ቅንብር እያቀረባችሁ፤‹‹ይህ ተራራ በእሳተ ገሞራ ተከፈለ፤ ከዚያ የአህጉሩ ገፅታ ተለውጦ ለሶስት ሚሊዮን ዓመታት ከቆየ በኋላ...››እያላችሁ ህዝቡን ከአዳምና ሄዋን ታሪክ ለማላቀቅ መጣር አለባችሁ::ግዝገዛ ማለት ከዚህም ይጀምራል::እንዲህ እንዲያ እየተባለ ነው በረጅም ጊዜ ጥረትና መስዋዕትነት የህዝቦችን ባህል፣ አመለካከት፣ልማድና እሳቤ እንዲሁም ሐይማኖታዊ አቋም መሸርሸር የሚቻለው::

አሁንም አስታውሱ!ይህ እራሱ እንኳ፤እንዲሁ ተዘልሎ አይገባበትም:: ለዚህም ቅድመ ስራ አለው::በሌላ በተለመደና ሌላ ዓላማ በሌለው ምርጥ ምርጥ ስራ መገናኛ ብዙሃኑን በሁሉም ዘንድ ቀድሞ ማስወደድና ማስለመድ ያስፈልጋል::መፅሐፍም ከሆነ መጀመሪያ ፀሀፊውን ማስወደድ ያስፈልጋል::ዘፋኝም ከሆነ መጀመሪያ ተወዳጅ ማድረግና ዝናውን መተንተን ማናኘት ያስፈልጋል::ሰባኪም ከሆነ መጀመሪያ በምዕመኑ ዘንድ በጥብቅ ተወዳጅ ማድረግ ስፈልጋል::ተወዳጅነትና ተቀባይነት ካገኘ በኋላ እሱን ተጠቅሞ በሱ አማካኝነት ዓላማን እያሰረፁ የሚፈለገውን ህዝብ እንደልብ መንዳት ይቻላል:: እንጂ ተዘልሎ አይገባም::በተለይ ኢትዮጵያውያን ላይ አይሆንም!

‹‹ስለዚህ እኛ የትርጉም ባለሙያዎችን በዚህ ጉባኤ ስንወቅስና እንዴት አማርኛ አቃታችሁ? ስንል፤እኛ የእነሱን ለማንበብና ስለነሱ ለማወቅ

ሳይሆን፤በኛ በኩል ምርጥ ሆኖ የሚቀርብን ስራ፤ ፊልምም ከሆነ በማየት ብቻ ከመረዳት ይልቅ፤ሙሉ ታሪኩን በሙሉ ትርጉም አቅርቦ ታሪኩን ሙሉ በሙሉ ማስረፅ ያስፈልጋል ማለታችን ነው።።
በዚህ መሰሉ ዘርፍ ስራችሁን ስትቀጥሉ፤የብሮድካስት ተደራሽነቱ ያን ያህል ቢሆንና እንደልብ ቁጥሩን ጨምሮ ማስፋፋት ባይቻል እንኳ፤ ያለውን ከመጠቀም ጎን ለጎን በመፅሐፍ መልክ የነገርኳችሁን አይነት ታሪኮች እየተፃፉ ቀርበውና በቀላሉ ተገኝተው ሙሉውን መፅሐፍ በሰጠናቸውና ወደ ፊትም በምንሰጣቸው የቴክኖለጂ ውጤቶችና መተግበሪያዎች ኮፒ ፔስት እያደረጉ ሙሉውን ታሪክ በቋንቋቸው ማንበብ እንዲኖርባቸው ጭምር ነው።።ከዚያም ያለፈ ሚና አለው።።
በዚህ ረገድ እናንተ ስራውን ስትሰሩ፤ እኛና የሃያላን አገራት መሪዎች የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ሚዲያውም፣ ኢንተርኔቱም፣ በአገሪቱ ተስፋፍቶ እንደ ልብ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት እናግዛችኋለን።።
‹‹ብተረፈ አንድ ፈረንጅ ደርሶ በአማርኛ ሊፅፍ አይችልም።።በእንግሊዝኛ ፅፎ ኢትዮጵያውያኑ እንዲደርሳቸውና ተርጉመው እንዲያነቡት አንብበው እንዲያስነብቡት ነው የምንሻው።።ይህንን ለማድረግና ሌሎች ተመሳሳይ አካሄድ ለሚሹ ነጥቦቻችን ይጠቅሙን ዘንድ ነው ገደብ አልባ የሆነና በትክክል መተርጎም የሚችል መተግበሪያ የምንለው።።እንጂ አበበ በሶ በላ የሚል ዓረፍተ ነገር መተርጎም ተቻለ አልተቻለ ለኛ ምናችን ነው?ምንም!
‹‹ባለሙያው እንዳለው ለእነሱ ትልቅ እውቀትና እድል ነው እንግሊዝኛ መቻል።።ችለው ምን ያደርጉበታል?ያገሬውን ህዝብ እንደሆነ በቋንቋው ነው የሚያገለግሉት።።መምህራኑ በእንግሊዝኛ ቢያስተምሩ፣ ተማሪው እንግሊዝኛ ቢማር፣ እንዲሁ የኛን እውቀት ለማወቅና ለማሳወቅ ብቻ ነው።።እኛን ለመምሰል ነው።።
ያወቁትም ግፋ ቢል የሆነ ነገር በእንግሊዝኛ ፅፈው በኛ አገር አሳትመው ለኛ ያስነብቡናል።።ያ ለነሱ የትልቅነት የአዋቂነት መገለጫና ማረጋገጫ ይሆናቸው ይሆናል።።ለኛ ግን ምንም ነው።።
ስለዚህ ትርጉምም ሆነ ሌላው ጥቃቅን የመሰለ ጉዳይ በእነሱ ዘንድ መገኘት መቻሉ ለኛ በእጅጉ ያስፈልገናል።።ህጎቻችንም ሆነ ዕለታዊ ዜናዎቻችንን በቀላሉ በያዙትና በሚይዙት ዘመናዊ የእጅ ስልኮቻቸው ሳይቀር እየተረጎሙ የማወቅ፣ የመረዳት፤የመለማመድ፣ መብታቸው ሊከበር ይገባል!ከኛ አኩል ለማሰብ መዘጋጀት አለባቸው።።ለማክሮ 6 ብቻ ሳይሆን፤በፊልምም፤በመፅሐፍም በሌላም መሰል መንገድ የባህል ውርርስ ለመፈፀም የግድ የትርጉም መተግበሪያው አስፈላጊ ነው።።ገባህ ላሪ?››
‹‹አዎን ንግስት ሆይ››

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

‹‹ሌሎቻችሁስ የኢትዮጵያውያን ንቃተ ህሊና እምን ድረስ እንደሆነ፣ አይነትና መገለጫው ምን እንደሚመስል፣ነገር ግን ለምንና እንዴት እንደደኸዩ፣ለምን እንደተራቡና እንደተራቆቱ ገባችሁ?››

‹‹አዎን ንግስት ሆይ››የጋራ ድምፅ፡፡

‹‹ሌሎቻችሁ የኪነ ጥበብና የሚዲያ ሰዎች፣እንዲሁም የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ ህግ አስፀዳቂዎችና ተወካዮች፣ የኢትዮጵያውያንን ባህል፣እምነት፣ ሐይማኖታዊ አመለካከትና እሳቤ፣እንዲሁም ልማድ እንዴት መሸርሸር እንዳለባችሁ፣በምን መንገድ ተጠቅማችሁ እያለማመዳችሁ የጭንቅላት አጠባ ማድረግ እንዳለባችሁ፣ያ ካልሆነ በቀር ይህን ፈታኝ ህዝብ በቀላሉ ወደ ልዑላችን ዓላማ ማምጣት እንደማትችሉ ተረዳችሁ?››

‹‹አዎን ንግስት ሆይ››አሁንም የጋራ ድምፅ፡፡

‹‹አዎን!በሁሉም ዘርፍ መዘመት አለበት!ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን!›

‹‹ክብር ለባለ ድል አብዮተኞችን!››

‹‹አሜን!››

‹‹መልካም፣በዛሬው እለት የመስዋዕት ስነ ስርዓቱን በጋራ አድርገናል፡፡በዚህ ስነ ስርዓት ላይም እናንተን ከ G 20 አገራት መሪዎች ጋር አስተዋውቀን፣ ከአንድነት ወደ ውህደት መምጣታችሁን አረጋግጠናል፡፡እኛም ዓመታዊ ቃል ኪዳናችንን በጋራ አድሰናል፡፡ይህ ተግባርም ከዚህ በኋላ በየዓመቱ በተመሳሳይ ጊዜ የሚቀጥል ነው፡፡እናም አሁን በኔ በተመራው የዝግ ጉባኤ ላይ በተነሱ ነጥቦች ዙሪያ ከመሪዎች በኩል የሚቀርቡ ጥያቄዎች ካሉ እነሱን ተቀብዬ ምላሽ ከሰጠሁ በኋላ ይሆናል ጉባኤውን የማጠናቅቀው፡፡ ስለዚህ ጥያቄያችሁን ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡ክብር ለልዑላችን!››

‹‹አሜን›› ከማለታቸው በፊት መብራት ጠፋ፡፡

****

አዲስ አበባ ግንቦት 19 2007 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ ስድስት ኪሎ አካባቢ በአሮጌ የቆርቆሮ ቁርጥራጮች በታጠረ ጊቢ ውስጥ የምትገኘው ጠባቧ የቀበሌ ቤት ይህን ሁሉ ለማመን የሚከብድ ትዕይንት እያስተናገደች ነበር።

ቤቷ ውስጥ ያሉት ፍፁም፣ዳዊት፣ ዳንኤልና ዲያቆን ይሆናል ናቸው። በጋራ ሆነው የሜልቦርኑን፣የኒዮርኩንና የቤልጀሙን ዝግ ጉባኤ እየተከታተሉ ሳለ በድንገት መብራት ሲጠፋ ሃርድ ዲስኩን ዲስክቶፕ ኮምፒዩተር ላይ ሰክተው ነበርና የሚከታተሉት ትዕይንቱን ለማቋረጥ ተገደዱ።

ይህን ቪዲዮ ወደ ኢትዮጵያ ያመጣው ዳንኤል ቶማስ በድጋሚ እያየው የነበረ ቪዲዮ ነውና የተለየ ገፅታ አይነበብበትም።ዳዊትም ደጋግሞ ሲያየው የከረመ ነውና እንዲሁ እንደማንኛውም አስፈሪ ፊልም ዘና ብሎ ነበር የሚከታተለው።ፍፁም ግን ይህን ክፍል ብቻ ከዚህ ቀደም ስላላዩው እንደተለመደው ፊቱ በእልህና በቁጣ አዘል እንባ ርሷል።ትዕይንቱ ተጀምሮ እስኪጨረስ እንባዎቹ በጉንጮቹ መፍሰሳቸውን ለአፍታ እንኳ አላቋረጡም። ፡የዲያቆን ይሆናል ሁኔታ ደግሞ እጅግ የማይታመን ነበር።

ዳንኤል ቶማስ ከትዕይንቱ መቋረጥ በኋላ፣ከፍፁም አጠገብ ነበርና የተቀመጠው ድንጉጡንና ምስኪኑን ፍፅምን በአንድ እጁ አቅፎ ጀርባውን እየደባበሰ፣በሌላ እጁ እንባዎቹን እየጠራረገለት ሊያፅናናው ሊያረጋጋው ሞከረ።

ፍዝዝ ቅዝዝ ብሎ የሚያነባው ፍፁም ግን እንዲህ በቀላሉ የሚረጋጋ አልሆነም።

ቀደም ሲል ዳንኤልና ዳዊት ብዙዎቹን የቪዲዮ ክፍሎች እየከፈቱ በሚያዩበት ጊዜ ፍፁምም አብሮ ማየት እንዳለበት ወስነዋልና እንዳይመለከት ማገድ አልቻሉም።ሆኖም እንዳይበዛበት እያሉ ቀስ እያደረጉ ነበርና የሚያሳትፉት ይህን ክፍል ዛሬ አብሯቸው እንዲመለከት አድርገዋል።ይህን ሲያደርጉም በሚያየው ነገር ተረብሾ እንደሚረብሻቸው እያወቁ ነው።ስለዚህ እንደተለመደው ከእያንዳንዱ ትዕይንት መጠናቀቅና መቋረጥ በኋላ የመጀመሪያ የጋራ ስራቸው ድንጉጡንና ሆደ ባሻውን ፍፁምን ማፅናናትና ማረጋጋት ነውና እሱን ገቡበት።

‹‹ፍፄ! ተነጋግረን ተስማምተናል አይደል?የእነዚህ ሰዎች አብደትና የልዑል ተብየው ውድቀት እስካሁን አልገባህም?እኔ የአሸናፊው የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ!ብለህ ማልቀስህን ትተህ በእነዚህ ጅልነት አልሳቅህም?ይህን በማየትህ እንዴት ይህን ሁሉ እንባ ታፈሳለህ?እንግዳውንም አትረብሸው››አለው ዳዊት።

ፍፁም ያዜ

ፍፁም አንገቱን ደፍቶ ከነበረበት ቀና በማለት የታዛዥነትና የ ልክ ነህ እሱማ ፊት እያሳየ መቅለስለስ ጀመረ::

‹‹ፍፁም!››አለው ጠንከር ብሎ::

‹‹አቤት ዴቭ…›› በማለት ተውኝ ሳልቅስበት አይነት ማጉረምረም ውስጥ ገባ::

‹‹ጥረግ እንባህን!››

‹‹እሺ››

‹‹ተነስና በሩን ከፍተህ ነፋስ ተቀበል::ከዚያ ተረጋግተህ ተቀመጥ!ቪዲዮውን መብራት ሲመጣ እንቀጥለዋለን!እንዲህ የምታለቅስ ከሆነ ግን አብረህን አታይም!››አለው::

ፍፁም ጉትት እያለ ተነስቶ የታዘዘውን ከመፈፀሙ በፊት ንግግሩን ሲቃ እያቋረጠው…..‹‹እሺ….ግን…..በቃ…..የሆነ…..ወይ ጮክ ብዬ እንዳለቅስ እንዶ ፍቀዱልኝና…..››ሲል ጀመረና፤ያበጠው ይፈንዳ በሚል እንደልማዱ፤ ‹‹እ…እ…እእእ…..››እያለ፤ሞቅ ባለ ድምፅ ለቅሶውን ለቀቀው::

ዳንኤልና ዳዊት ማፅናናታቸውን ተወት አድርገው ለውስን ደቂቃ በዝምታ ያዩት ጀመር::ፍፁም እየደጋገመ እእእእ….እያለ በጎርናና ድምፁ ካቀለጠው በኋላ፤ለቅሶውን ጋብ እያደረገ ጎን ለጎንም በለበሰው ባለኮፍያ ሹራብ እጅጌ እንባዎቹን ሲጠራርግ ቆየ::ካሁን አሁን ሙሉ ለሙሉ ለቅሶውን ያቆማል ብለው ጥቂት ጠበቁ::ፍፁም ግን እንደማቆም እያለ እንደገና ሲቀጥል፤ የለቅሶ ድምፁን ቀነስ አድርጎ እንደገና ጨመር፤ጋብ፤ለቀቅ፤እያደረገ አንዛዛው::በዚህ ጊዜ ዳንኤል ተነስቶ አቅፎ እያባበለና የዳዊትን የማረጋጊያ ቃላት እየደገመ ሳያለቅስ ቃል መግባቱን እያስታወሰ በግድና በተማፅኖ አረጋጋው::

ፍፁም ለቅሶውን እየቋጨ በነበረ ጊዜ ዳንኤል በሩን ከፈቶ አየር እንዲገባ አደረገ::ፍፁምንም ለቅሶውን ጎረቤት እንዳይሰማ አስፈራርቶ ዝም አሰኘው:: እንዳይቀጥል በመስጋትም በቀመበት አቅፎ ይዞ ፀጉሩን እያሻሸ እያባበለው ቆዩ::

ፍፁም ለቅሶውን ያቁም እንጂ ከሱ ውጪ ማንም አይለውም ተብሎ የሚታሰበውን ረጅም የግርምት ‹‹እንዶ…..››ደጋግሞ እያለ የተመለከተውን ጉድ እያሰበ መሪገሙን አላቆመም:: ‹‹እን……ዶ…..!››ይላል::እነዚህን ሶስት ሆሄያት አጣምሮ፤‹‹እንዶ›› የምትለውን ቃል ጀምሮ ለመጨረስ ፍፁም ከአምስት ሰከንድ በላይ ይወስድበታል::

ከዚህ ቀደም የእሱን እን…..ዶ ዳንኤልም ዳዊትም ልክ እንደ እሱ ሊሉት ሞክረው ከሶስት ሰከንድ በላይ መዝለቅ አልቻሉም::የፍፁምን ረጅ…..ም እን…..ዶ ማንም አይላትም::

ቀጠለ....‹‹እንዴ.......! እነዚህ እርኩሶች.....እንዴ.....ጭራሽ..! እን.....ዴ!....ኪዳነምረትን እነዚህ ሰዎች ሁሉም ቡሽቲዎች ናቸው!›› ሲል ዳዊት በሃይለ ቃል አስቆመው፡፡

‹‹ፍፁም!ይህን ቃል አትጠቀም ብዬ ስንቴ ነው የነገርኩህ?!ይህን የአስፓልት ዳር ቃል አርም!አላልኩህም?››ሲለው፤

‹‹ይቅርታ ዴቭ...ግን...እን....ዴ...››ለቅሶውን እንደገና ሊጀምር ብሎ ተወው፡፡በለቅሶው ፋንታ፤‹‹እሽ ቆይ አሁን እነዚህ ምን ሊባሉ ነው?እነዚህን ለመስደብ ቃላት መምረጥ ያስፈልጋል?እሽ አሁን እነዚህ ምንድን ናቸው?ምንድነው እየሆኑ ያሉት? ማለት...እን....ዴ!››እንደገና ጀመረና ዳንኤል ላይ ልጥፍ እንዳለ ዝግ ባለ ድምፅ፤ስቅ ስቅ ስቅ እያለ አለቀሰ፡፡

‹‹ኧረ በፈጠረህ ፍፄ!ዝም በልና ምን እየሆኑ እንዳለ እናስረዳሃለን፡፡ሁሌ እንደ አዲስ የምትሆነው ነገር አይገባኝም፡፡ባለፈው ማንነታቸውን አስረድተንህ አንተም አይታሃቸው ገብቶህ ነበር፡፡እንደገና....››

‹‹ልክ ነህ ዴቭ ገብቶኛል እኮ...ግን ባለፈው ያየነው..እሽ....እነዚህ....››

‹‹ቁጭ በል፡፡ዳኒም ተቀመጥ›› ረጅሙ ሶፋ ላይ አጠገብ ላጠገብ ተቀመጡ፡፡ ፊት ለፊታቸው ያለው ዳዊት በዚህ ትዕይንት ማናቸውም መረበሽ እንደሌለባቸውና፤ማሰብና ማተኮር ያለባቸው ይህ መረጃ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ ስለሚሆንበት መንገድ ብቻ መሆኑን ደጋግሞ ሲናገር ቆየ፡፡

‹‹ፍፁም!አስተውል፡፡አንተ ይሄን የመሰለ መረጃ እጃቸው ገብቶ እንዲያዩት ከሆኑት ውስጥ ማለትም ከእኛ አንዱ ነህ፡፡ስለዚህ ጉዳዩ ይመለከትሃል፡፡ እነዚህ ሰዎች መረጃው ከእጃቸው ወጥቶ ማፈትለኩንና በኢትዮጵያውያኑ እጅ መግባቱን ተረድተው ቢመጡና ቢይዙን እንዲህ እያለቀስክና እየተርበተበትክ እየደነገጥክ ነው የምትቋቋማቸው?እኛ ይህን መረጃ ሳናወጣው አንድ ነገር ብንሆን ሃላፊነቱ ያንተ መሆኑን አታውቅም?››

‹‹አውቃለሁ ዴቭ...››

‹‹ታዲያ በየጊዜው በምታየው ነገር እንዴት እንዲህ ትሆናለህ?››

‹‹ይቅርታ ዴቭ አይለምደኝም...ግን...በጣም...እንዴ...››እንባውን ጠራረገ፡፡

‹‹አሁንም አስተውል ፍፄ!አንተ ይሄን አይተህ መባባት የለብህም!ሃላፊነት አለብህ!እነዚህ ቡድኖች ጎላቸው ኢትዮጵያ ናት ብለህ የማስተማርና ወገንህን ቢያንስ የማንቃት ከፍተኛ ሃላፊነት አለብህ!ይህን ለማስረዳትና ወገኖችህን ለማዳን ደግሞ መጀመሪያ ጠንካራ መሆን አለብህ፡፡የተረጋጋህና ከስሜታዊነት የራቅህ መሆን አለብህ፡፡አንተ ይህን ቪዲዮ ስታይ ሃላፊነትህንም እያሰብክ እንጂ እያዘንክ እያለቀስክ መሆን የለበትም፡፡ይህን ለመጨረሻ ጊዜ እነግርሃለሁ!ተግባባን?››ፍፁም አንገቱን በሃይል እየወዘወዘ፤‹‹አዎ ገብቶኛል!››አለው ጠንክር ለማለት እየሞከረ፡፡

የሳጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ

ማንም ሰው በተለይም ኢትዮጵያዊ ይህን ተዓምረኛና አስደንጋጭ፤ ብሎም ዘግናኝ ቪዲዮ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያይ መረበሽና መደንገጡ የማይቀር ቢሆንም፤ዲያቆን ይሆናል ግን ምንም የመሰለው አይመስልም።ያለ አንዳች መገረምና መደነቅ እንዲሁ እንደተረጋጋ ነበር ሲከታተል የቆየው።
ዳዊት ፍፁምን አስጠንቅቆ ካበቃ በኋላ፤ቤቱ ውስጥ ለአፍታ ያህል ከበድ ያለ ዝምታ ሰፈነ።
በዚህ ጊዜ ዲያቆን ይሆናል እንደ ዳዊትና እንደ ዳንኤል ፍፁምን አንዳች ነገር ብሎ ማፅናናት እንደሚገባው ተረድቶ፤‹‹አይዞህ ፍፁሜ።ወንድሞችህ እንዳሉት እንዲህ መሆን የለብህም።በእርግጥ ይህ ያንተ ችግር ብቻ አይደለም።የመላው አማኝና አማኝ ነይ ባይ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ችግር ነው። ቅዱስ ቃሉን ካለማወቅ የሚመነጭ ችግር።ለማንኛውም አይዞህ።እንባህን አብስ ፍፁሜ››
‹‹እሺ››
በሰላሳዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ዲያቆን ይሆናል ይህን ተናግሮ ያንኑ የተረጋጋ ፊቱን እንደያዘ ጭራሽ ፈገግታም ጨምሮበት ዝም አለ።
ዳዊት፤ ዲያቆን ይሆናል ይህን ቪዲዮ አይቶ አንዳች የድንጋጤና የመገረም ፊት ሳያሳይ ይቀራል ብሎ አላሰበም።ይህን ጉድ አይቶ እንዲህ የተረጋጋ ሆኖ ይታያል ብሎም አልጠበቀም።እናም በጣም ገረመው።ዳንኤልም በበኩሉ ከዚህ በፊት ይህን ቪዲዮ ዳዊት አሳይቶት ይሆናል ብሎ እስከመገመት ደረሰ።
ዲያቆን ይሆናል ምንም አይነት የመገረምም ሆነ የመደንገጥ ፊት ባለማሳየቱና ይልቁንም ሲመጣ ከነበረው የበለጠ ፊቱ በፈገግታ ደምቆ ሲመለከት፤የዳንኤልንም ግምት ሲረዳ፤ዳዊት፤‹‹ምነው ምንም አልመሰለህምሳ?ቪዲዮውን ከዚህ በፊት ያየህው እኮነው የመሰልከው ሁኔ››አለው።
‹‹አሃ ወንድም ዳዊት እንደ ፍፁም እንዳለቅስ ጠብቀህ ነበር?››
‹‹እንደዚያ ማለቴ ሳይሆን...መቸም...ሁሉም ነገር የተዓፈና የምታውቀው ቢሆንም፤ትንሽ...ቢያንስ ኢትዮጵያ ጎላቸው መሆኗና....››ብሎ ሲጀምር፤
‹‹አይ ዳዊቴ...በርግጥ እሱ ነገር ገርሞኛል።ግን ጎላቸው ኢትዮጵያ ሆነች ሌላ አገር ሆነ ምን ለውጥ ያመጣ ብለህ?አጥማጁ ሳጥናኤል እስከሆነ ድረስ የሚጠመደው መላው የዓለም ህዝብ ነው››
‹‹እሱስ ልክ ነህ››
‹‹እንጂ ቪዲዮውን ከዚህ ቀደም ማን ሰጥቶኝ አዬዋለሁ ወንድም ዳዊት?በቅርቡ ተመሳሳይ የሆነ መረጃ የወጣበት መጽሐፍ አንብቤያለሁ።

ያን ስላነበብኩ ግን አይደለም ያልገረመኝ፡፡ያን ባላነብም አይገርመኝም››ሲል መለሰ፡፡

‹‹በእርግጥ ልክ ነህ፣ቢሆንም ግን….ያው… እነዚህ በሌላ ገፅታቸው የምናውቃቸው መሪዎች፣ጳጳሱ፣ንግስቲቱ፣ሳይንቲስቱ…እንዲህ ሲሆኑ ነው….. እንጂ ጉዳዩ እንዳልከው የሚያስደነግጥና የሚያስገርም ሆኖ አይደለም፡፡በተለይ ላንተ የሚጠበቅና ተራ የሆነ ድርጊት መሆኑ….››ዳዊት ሃፍረት ቢጤ ተሰማው፡፡በግድ ተገረም በግድ ደንግጥ እያለ ያለም መሰለውና በእንጥልጥል ተወው፡፡

‹‹እሱማ ልክ ነህ ዳዊቴ፣ነገር ግን ከኔ የሚጠበቀው መገረምና መደንገጥ አይደለም ብዬ ነው፡፡ እንጂ እንኳን ይሄን፣የድራማ ሴራ እየተከታተልንስ እንገረም እንደነግጥ የለም?በዚህ ጉዳይ እንዲያ መሆን ከኔ ስለማይጠበቅ ነው ቸለል ያልኩት፡፡ለዚያ ነው ያልተገረምኩ ያልደነገጥኩት፡፡በእርግጥም ይሄን አይቶ መደንገጥ እንኳን ከእኔ ከእናንተም አይጠበቅም፡፡ከማንኛውም ክርስቲያን አይጠበቅም፡፡ስለዚህ…..በኔ በኩል አስገራሚ ነውና ተገርሜያለሁ፡፡ሆኖም አላስደነገጠኝምና አልደነገጥኩም፡፡ እንግዲህ….ባለመደንገጤ ይቅርታ››አለና ደመቅ ያለ ፈገግታውን ለገሳቸው፡ ፡በዚህ ጊዜ የቤቱ ድባብ በቅፅበት ተለወጠና እርጋታ ሰፈነ፡፡ፍፁምም ፈገግ ብሎ ቀና አለ፡፡ቀና ብሎ ወደ እሱ ሲያይም፣ዲያቆን ይሆናል፣‹‹እ…ም ፍፄ እንደሱ ነው ፈገግ ማለት ያለብህ!››አለና ከፈገግታ አላልፎ ድምፅ አውጥቶ እንዲስቅ አደረገው፡፡

‹‹ወንድም ዳዊት፣እንዴት አየህው? ባየህው ነገር ላይ ተንተርሰህስ ምን ትላለህ?እስቲ የምትለውን በል ይባላል እንጂ፣ለምን አልደነገጥክም ብለህ መደንገጥ?››ብሎ መሳቅ ጀመረ፡፡

‹‹አይ፣ልክ ነህ፡፡እኔም እንዲያ በማለቴ ተጸፅቻለሁ፣አፍሬያለሁ፡፡ስለዚህ የምትለውን በል››አለው፣እየሳቀ፡፡

‹‹እኔ እንኳን ብዙም የምለው የለኝም ብለው ጀምረው ማብቂያ ወደሌለው ስፊ ሀተታ እንደሚገቡት አለልቺ ሰዎች እንዳልሆንባችሁ እንጂ፣ የምትለውን በል ባትሉኝም የምለውን ሳልል አልሄዳትም››ሲል፣ገብቶት ይሁን ሳይገባው፣ዳንኤል፣‹‹ኧረ አትሆንብንም፣ቀጥል ግዴለም››አለው፡፡ ዳንኤል ዲያቆን ይሆናልን ገና እንዳየው ነው የወደደው፡፡እርጋታውን፣ ፈገግታውን፣ትህትናውን፣ሁለ ነገሩን አይቶ ሳይጨርስ እንዲሁ ደርሶ ተቀብሎታል፡፡

‹‹ወንድሞች፣መጥፎ እድል ሆኖ አሳማ በተፈጥሮው ከሌሎች እንስሶች በተለየ ሁኔታ ወደ ሰማይ ማየት አይችልም፡፡በዓይኑ አቀማመጥ ምክንያት ወደ ላይ ማየት የማይችል እንስሳ ነው፡፡አሳማ ወደ ምድር እንጂ ወደ

ሰማይ ማየት እንደማይችለው ሁሉ፤እነዚህም ልክ እንደ አሳማ ወደ ላይ ማየት ያልታደሉ፤በሃሰትና በቅዕበታዊ እስማት እየማለሉ፤እሉንም ሌላ ወደ ምንም ሳያዩ ቀርተው በአሳዛኝ መንገድ የጠፉና የከፋው መንፈስ መጫወቻ ሆነው የቀሩ ናቸው።ስለዚህ ለእነሱ አዝነን ልናነባላቸው እንጂ ፊርተናቸውና አስደንግጠውን ልናለቅስላቸው አይገባም።

እነዚህ ሰዎችም ሆኑ ድቅሎች በሚስጥር ዘሮቻችንን እና መናፍስቱን ተገናኝተን ስለጠንን ሲሉ ሰየጠንን፤አስለጠንን ሲሉ አሰየጠንን፤ ማለታቸው ነው።ልዑላችን ድል ያደርጋል ሲሉም በመጨረሻው ጦርነት ይህን ሁሉ የፈጣሪ ፍጡር የሆነውን የምድር ሰው በሙሉ፤ አሰይጥነን በኛ ስር በማድረግ ይዘነው እንጠፋለን ማለታቸው ነው።እነዚህ ተስፋ ቢስ የሆኑ እርኩሳን መናፍስቶች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሲጠፉ፤ከጠፉን አይቀር እጥፊያችን አበሳጭተን ፍጥረቱን አሳስተን ተያይዘን እንቀልጣለን እንጂ!የሚል የአቅመቢስነትና የተስፋ ቢስ ፍጥረታት የመጨረሻ በቀልን ለማከናወን የተዘጋጁ ከንቱዎች ናቸው።እጥፍቶ ጠፊዎች።

ከፋው ዲያብሎስ እና ከመንግስተ ሰማይ የተባረሩ ጭፍሮችም ሆኑ ሁሉም ተከታዮቹ የመጨረሻ ውድቀታቸውን አሳምረው ያወቁት በመጀመሪያው የክህደታቸው ዕለት ነው።ሆኖም ሰይጣን ተስፋ የለውም፤ተስፋ ግን አይቆርጥም ተብሎለታልና በቅዱሱ ፈጣሪ ዓላማና ለእሱ ዓላማ በአምሳሉ የተፈጠሩ ሰዎችን በጥቂት ቁንፅል የሰማይ እውቀታቸው እያታለሉና እያማለሉ እነሱን ይዘው ወደ እሳት ባህር አብረው ለመጣልና ለማስጣል ቆርጠው የተነሱ ሆነዋል።እንጂ ለድል እንደማይበቁ ንግስቲቱም ሆነ ዘሮቻቸው፤እንዲሁም ዋና አለቃቸው አሳምረው ያውቁታል።ይቺን ብቻ ነው የዋሿቸው።

ንግስቲቱ ከተናገሩት ውስጥ ብዙ ምድራዊ እውነቶች አሉ።እነዚያን ተጨባጭ እውነቶች ግን የተጠቀሙባቸው የመጨረሻውን የሀሰት ወሬ ለማሳመን ይረዳቸው ዘንድ ነው።ይህን ሁሉ እውነት ሸንፈታቸውን ለመሸፈኛነት ነውና የተገለገሉበት እውነት ተናገሩ ብሎ ለማለትም አያስችልም።ዓለምን ሁሉ የሚያስቱት ግን በእነዚህ ተጨባጭ እውነቶች በማሳመን ነውና ብዙዎችን ሊያስቱ ይችላሉ።በተረፈ የተዓፈላቸውን ነው ቃል በቃል ሲተገብሩና ሲያቅዱም ያየነው።እቅዳቸውም የሀሰተኛ አለቃቸው እቅድ ነው።

የዮሐንስ ወንጌል ምዕ.8. ቁ.44 ላይ፤

‹‹እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ።እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም።ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤ ሐሰተኛ